ቅን መሪ

2ኛ ዕትም

ትእዛዙ ካሣ

ነሐሴ 2012 ዓ.ም.

© ቅን መሪ 2012 ዓ.ም.
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

ሁለተኛ ዕትም ነሐሴ 2012 ዓ.ም.
የጀመሪያ ዕትም ሰኔ 2012 ዓ.ም.

ገቢው ሙሉ በሙሉ ለበጎ አድራጎት ሥራ የሚውል

ስለ መጽሐፉ አስተያየት ካልዎ

kenmeri2018@gmail.com

—እጅግ አድርጌ አመሰግናችኋለሁ—

የረዱኝ ብዙ ናቸው:: ከፍዬ የማልጨርሰው የብዙ ሰዎች ውለታም አለብኝ:: አንዱን አንሥቼ ሌላውን መተውም የተገባ አልመሰለኝም:: በጎ ላደረጉልኝ ሁሉ በቸርነቱ መልካሙን ሁሉ እንዲያደርግላቸው እግዚአብሔርን እለምናለሁ::

ማውጫ

መቅድም..... 9

መግቢያ..... 15

ክፍል አንድ

በቅንነት ላይ የተመሠረተ የአመራር ባህል

ምዕራፍ አንድ

ቅን መሪ

1.ቅንነት ምን ማለት ነው?..... 22

1.1 ቅን መሪን ፍለጋ 22

1.2 መሪ እንዴት ቅን ሊሆን ይቻለዋል?..... 32

1.3 የዋህነት እና ቅንነት..... 36

1.3.1 የዋህነትን እንደ ደካምነት..... 38

1.3.2 የዋህ ሕዝብ..... 42

1.4 ቅንነት ከወዴት ይገኛል? 45

1.5 ቅንንት እንዴት ይገለጻል?..... 49

ምዕራፍ ሁለት

ታማኝነት

2. ታማኝነት ምንድን ነው?..... 51

2.1 መተማመን ሲጎድል..... 54

2.2 ታማኝነትን የሚያጎድሉ ምክንያቶች..... 59

2.3 ሐቀኛነት ምንድን ነው?..... 68

2.3.1 በመሪዎች ዘንድ ውሸት ልማድ ሲሆን..... 71
2.3.2 ሐቀኛነት ለምን?..... 74
2.3.3 እንዴት ሐቀኛ መሆን ይቻላል? 83

ምዕራፍ ሦስት

ፍትሐዊነት

3. ፍትሐዊነት ምን ማለት ነው?..... 86
3.1 ለፍትሕ መቆም ለምን?..... 90
3.1 ማኅበራዊ ፍትሕ..... 94
3.2 እውነተኛ ፍርድ መፍረድ..... 97
3.3 በደልን መቃወም..... 101
3.4 አድሏዊነትን ማስቀረት..... 104

ምዕራፍ አራት

ትሕትና

4 ትሕትና ምንድን ነው?..... 110
4.1 መሪነትና ትሕትና..... 116
4.2 ትሕትና ለምን? 119
4.3 ትሕትናን እንደ ደካምነት..... 135
4.4 ትሕትናና በራስ መተማመን..... 138

ምዕራፍ አምስት

ከሰው ጋር ተግባብቶ መሥራት

5 አብሮ መሥራት 141
5.1 የዐላማ አንድነት አለመኖር..... 145

5.2 ብቻን የመሮጥ ዝንባሌ..... 146
5.3 መከባበርና መቻቻል..... 149
5.4 ብልጣብልጥነት..... 151
5.5 ማጣጣል..... 152
5.6 ተግባቦት ሲጎድል..... 154
5.7 መካረር..... 155
5.8 ፍረጃ..... 157

ክፍል ሁለት

አገልጋይነት

ምዕራፍ ስድስት

አገልግሎት

6. አገልግሎት ምንድን ነው?..... 166
6.1 ጥሪ 174
6.2 መክሊት..... 177
6.3 አገልግሎት ለምን? 179
6.4 የበጎ ፈቃድ አገልግሎት..... 185

ምዕራፍ ሰባት

አገልጋይ መሪ

7. መሪነትና አገልግሎት..... 188
7.1 አገልጋይ መሪ እንዴት ይገለጻል? 193
7.1.1 ትኩረቱ ሰው የሆነ 193
7.1.2 ቅድሚያ ለሰው ሀብት..... 197

7.1.3 ለመሥዋዕትነት ቁርጠኝነቱ ያለው..... 202
7.1.4 አገር ወዳድ 204
7.1.5 መልካም እረኛ 209
7.1.6 ተግቶ የሚያተጋ..... 213
7.1.7 በዐላማው ጽኑ 220

ምዕራፍ ስምንት

ሥልጣንና አገልግሎት

8 ሥልጣን..... 230
8.1 ሥልጣን ምንድን ነው?..... 232
8.2 ሥልጣንን ማካፈል..... 237
8.3 የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የቄሳርን ለቄሳር... 244

ክፍል ሦስት

መሪነትና ሥነምግባር

ምዕራፍ ዘጠኝ

ሥነ ምግባር

9.ሥነ ምግባር ምንድን ነው?..... 256
9.1 በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሥነ ምግባር 258
9.2 የሥነ ምግባር ዐላማዎች..... 260
9.3 ትክክል የሆነው የሚለየው በምን መንገድ ነው? ... 269
9.4 ሕግና ሥነ ምግባር..... 271
9.5 የሥነ ምግባር (የሞራል) ዝቅጠት 274

9.6 ሃይማኖተኛ ሕዝብ..... 275

9.7 ሥነ ምግባርን የመገንባት ድርሻ 281

ምዕራፍ አሥር

ግብረ ገብ መሪ

10 መሪነትና ሥነ ምግባር..... 289

10.1 በምሳሌነት የሚመራ..... 293

10.2 ፈሪሃ እግዚአብሔር ከመሪዎች ሲጎድል..... 299

10.3 የመርህ ሰው 306

10.3.1 ግትርነት እና ለመርህ መቆም..... 310

10.3.2 መርህ ሲሸረሸር..... 312

ስንብት..... 316

ዋቤ መጻሕፍት..... 321

መቅድም

ኢትዮጵያ የማደግ ተስፋ ነበራት ማደግ ያልቻለችው ጥሩ መሪ በማጣቷ ነው የሚል ነገር ተደጋግሞ ይነሣል። ይህ ጉዳይ በራሱ ሰፊ ጥናት የሚጠይቅና ውይይት የሚጋብዝ ቢሆንም አንድ እውነት ግን በውስጡ ይዟል። ከሃምሳ ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ የሥልጣኔ ደረጃ የነበሩና ብዙም የተፈጥሮ ሀብት የሌላቸው አገሮች ሲያድጉ ሲመነደጉ አይተናል። ምክንያቱ ምንድነው? ሲባል ደግሞ ጥሩ መሪዎች ማግኘት መቻላቸው፣ በሰው ሀብት እድገት ላይ በመሥራታቸው፣ የሰው ሀብታቸውን በአግባቡ መጠቀም በመቻላቸው፣ እርስ በርስ ከመናቆር ተሳስበውና ተባብረው በመሥራታቸው እና በዚህም የተረጋጋ አገርን በመፍጠራቸው የሚል መልስ ነው ብዙውን ጊዜ የሚገኘው።

ኢትዮጵያ ለማደግ ተስፋ ያላት አገር ናት ቢባል እውነትነት ያለው ነው። የአየር ንብረቷ ለጥቂት አገሮች ብቻ የታደለ ጸጋ ነው። በሱናሚ፣ በቶርኔዶ፣ በሀሪኬን ወይም በመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት አገር ፈርሶ አይሠራም። በረዶ መጥረግ፣ በበረዶ ምክንያት ሥራ መዝጋት፣ የሞቀውን ለማቀዝቀዝ የቀዘቀዘውን ለማሞቅ የሚያስፈልግ ባለመሆኑ ብቻ ብዙ ገንዘብ ማዳን ይቻላል። የሙቀት የቅዝቃዜ የሚባል የልብስ ጣጣም በዚያች አገር ብዙም የለም። ፀሐይ ከሌሎች ስትደበቅ እዚህ ግን አሥራ ሦስት ወር ሙሉ ለፈለጋት ሁሉ ትገኛለች። በአግባቡ ባይያዝም መሬቱም በአንጻራዊነት ሰፊ ነው። መሬቷ ተዘርቶባት የማታበቅለው የለም። ከዚህ ሁሉ ጋር የሚያኮራ የነጻነት ታሪክ የሚፈጥረው በራስ

መተማመን እና በማንነት መኩራት፣ ከጠንካራ መንፈሳዊ እና ማኅበራዊ እሴት ጋር ሲደማመር የሚፈጥረው ሀብት ትልቅ ነው። ይህን ሁሉ ነገር በአግባቡ መጠቀም አልተቻለም እንጂ ምን ጎድሎ ሊያሰኝ ይችላል።

ይህ ሁሉ ባለበት ለምንድነው የድህነቱ መዓት ሊያባራ ያልቻለው? ለሚለው ጥያቄ ጣት ሊቀሰርበት የሚችል አንዱ ሁነኛ ምክንያት የዘመናት የአመራር ችግር እና በአግባቡ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት አለመቻሉ የሚለው መልስ ሊሆን ይችላል።

ቅንና ባለ ራእይ መሪዎችን መታደል ለአንድ አገር ትልቅ ሀብት ነው። አገር በመሪ ይነሣል፤ በመሪም ይወድቃል። በመሪ ብልጽግና ይገኛል፤ መሪ ሊያራቁትም ይችላል። በመሪ ፍትሕ ይሰፍናል በመሪ ፍትሕ ይጓደላል። በመሪ ሥነ ምግባር ይስፋፋል፤ በመሪ የሞራል ዝቅጠት ይመጣል። በመሪ እምነት ይጸናል፤ በመሪም እምነት ይጠፋል። መሪ ይከፋፍላል፣ መሪ የተበታተነውን ያሰባስባል። መሪ የግጭት ምንጭ ይሆናል፤ የጠፋ ሰላምም በመሪ ይመለሳል። በመሪ አገር ይሰፋል፤ በመሪም አገር ይጠባል። በተቋማት ደረጃም ጠንካራ መሪ ጠንካራ ተቋምን ይፈጥራል፤ ደካማ መሪ ሲተካ የተገነባውን ሊያፈርሰው ይችላል። በጥቅሉ መሪ ያነሣል፤ መሪ ይጥላል።

ክፉ መሪዎች በሚሠሩት ስሕተት በማያገባውና በማያውቀው ጦርነት ስንቱ ያልቃል፤ የሚለማ ሀብት ሳይጥፋ ስንቱ ይራባል፣ ይታረዛል፣ ንጹሕ ውኃ በማጣት ይጠማል፤ ታሞ መዳን ይሳነዋል። ክፉ መሪዎች በሚሠሩት ስሕተት በማያገባውና በማያውቀው ስንቱ ከፈጣሪ የተሰጠውን የተፈጥሮ መብት ይገደባል፤ ይታፈናል፤ በባርነት ቀንበር ይማቅቃል፤ በፍርሃት እንዲኖርም ይገደዳል፣ ያለወንጀሉም ይተሠራል፣ ይሰቃያል፣ ይገደላል። ክፉ መሪዎች በሚሠሩት ስሕተት በማያገባውና በማያውቀው ስንቱ ስደተኞችን ሊያስተናግድ የሚችል መልካም አገር እያለው ይሰደዳል፤ ይለምናል፤ በበርሀ ይበተናል፤ የውቅያኖያኖስም ሲሳይ ይሆናል፤ በሰው አገርም ይታሰራል። ክፉ መሪዎች በሚሠሩት ስሕተት ስንቱ ሠርቶ ማደግ፣ መበልጸግ ሲቻለው ሥራ በማጣት በችጋር ይሰቃያል። ይህ ሁሉ የሚሆነው ቅንና ባለራእይ መሪዎች በየዘርፉ ሲጠፉ ነው።

ለትልቅ ሕልም ዕልፍ አዕላፍትን ማሰለፍ የሚቻለው የሚታመን መሪ መሆን ሲቻል ነው:: በቅንነት የሚመራ፣ ቃሉና ተግባሩ የተስማማ መሪ ተከታይ ያገኛል:: ቅን መሪ ለጊዜው ለሚገኝ ትርፍ ማታለልን አይመርጥም:: የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም የጥል ወይም የመለያየት ዘርን አይዘራም:: እንዲህ ዐይነቱ መሪ በአንዱ ውድቀት የሌላውን ጥቅም አይሻም:: የቀደመውን ትውልድ ከአሁኑ ጋር አስታርቆ ለነገው ትውልድ የሚያኮራ ታሪክን ማስረከብ የሚቻለው በቅንነት መምራት ሲቻል ነው::

የተወሰኑ አገሮች የተረጋጋና ሰላማዊ አመራር ሲኖራቸው ሌሎቹ ደግሞ ምስቅልቅል የበዛበት፣ በግጭት የታጀበ፣ ጦርነትና ሰላም የሚፈራረቅበት የአመራር ባህል ይኖራቸዋል። ይህ ለምን ሆነ? የሚለውን ለመመለስ ሰፊ ትንተናና ዕውቀት የሚፈልግ ቢሆንም ሁለት ምክንያቶች ግን ጎልተው ስለሚታዩ መጥቀስ ይቻላል:: አንደኛው በግልጽ የሚታይ የተረጋጋ አመራር መፍጠር የቻሉት አገሮች መሪዎች ተስማምተው ችግራቸውን በሰላም እየፈቱ በጋራ ተግባብተው መሥራት መቻላቸው ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ለማድረግ የሕግ የበላይነት የማይሸረሸርበት ተቋማዊ ሥርዓትን ለማስፈን በመቻላቸው ነው ማለት ይቻላል:: በተቃራኒው ከቅንነት ይልቅ ሴራ በሚበዛበት የአመራር ባህል በመተማመን እና በመግባባት መሥራት ባለመቻሉ የማያባራ ግጭት ከመኖሩም በላይ እንዲህ ባለ አመራር ተጠያቂነትና የሕግ የበላይነት የሚያስከብር ተቋማዊ ሥርዓት መፍጠር ስለማይቻል ችግሩን የበለጠ የተወሳሰበ ያደርገዋል::

ተቋማዊ ሥርዓት፣ ተቋማዊ አሠራር በጎለበተባቸውና ተቋማዊ ዓቅም ጠንካራ በሆነባቸው አገሮች በታሪክ አጋጣሚ ክፉ መሪ ሥልጣን ላይ ቢወጣ እንኳ አገሪቱን ወደ ኋላ ይመልሳታል የሚል ስጋት አይኖርም:: ሁሉም ነገር በሥርዓት፣ በሕግ የሚወሰን ነውና:: ከሕግ ውጭ ልሥራ ቢባል ያለው እድል በጣም ጠባብ ነው:: ሁሉም ነገር በሰው ላይ ሳይሆን በተቋም ላይ የተንጠለጠለ ነው:: ሕጉን እንደፈለጉ ለማጣመም እና የግል ፍላጎታቸውን በፈቀዱት መልክ ተግባራዊ ለማድረግ ብዙም እድል የሚሰጣቸው አይደለም:: ምክንያቱም አገሩ የሕግ አገር ስለሆነ እና

መሪዎች ከሕግ በታች በመሆናቸው ነው። በዚህ ዘመን እንዲህ ባሉ አገሮች የሕግ የበላይነትና የአሳብ ልዕልና እንጂ ጉልበት ቦታ የለውም። በአብዛኛው ጉልበታቸውን የሚጠቀሙት ትክክልም ይሁን አይሁን ብሔራዊ የሚሉትን ጥቅም ለማስከበር ነው። በውስጣዊ ጉዳያቸው ግን መጫረስ፣ መተላለቅ ካቆሙ ሰነባብተዋል።

እንዲህ ባሉ የተረጋጉ አገሮች ቅን መሪን ማግኘት ጸጋ ቢሆንም ከምንም በላይ አስፈላጊ የሚሆነው ግን የተቋም ዓቅም አናሳ በሆነበትና የሕግ የበላይነት ሙሉ በሙሉ ባልተረጋገጠባቸው አገሮች ነው። ቅን መሪ ሲገኝ ወደሚፈለገው ዘላቂነት ወዳለው ተቋማዊ አሠራር መሸጋገር ይቻላልና ተቋማዊ ዓቅም ደካማ በሆነበት ሁኔታ ቅን መሪን ማግኘት መታደል ነው ማለት ይቻላል።

በተመሳሳይ እንዲህ ባሉ የተረጋጉ አገሮች ለገንዘብ ወይም ለዝና፣ ወይም ለሌላ የግል ጥቅም ሥልጣንን ከሚቆነጥጡ ይልቅ በቅንነት አገሬን ላገልግል ብለው ወደ ሥልጣን የሚመጡ ሳይበዙ አይቀርም። አገር ማገልገል አንድ ጠንካራ እሴት ነው። ከግል ጥቅም ዐላማ ማስቀደም እንደ ባህል ስላደገ፣ እርስ በርስ ከሚጠላለፈው በአንድ ዐላማ የሚሰባሰበው፣ ተግባብቶና ተረዳድቶ ለአንድ ዐላማ የሚተጋው ይበዛል። ክርክሩ የአሳብ ነው እንጂ አንዱ በሌላው ላይ ጣት መቀሰር፣ አንዱ ሌላውን ጠልፎ መጣል እንደማያዋጣ የተማሩበት ይመስላል። ከመካከል የተሻለ ሲገኝ ከሚመቀኙት ይልቅ ያንን ብልህ ሰው ለጋራ ብልጽግና መጠቀም እንደሚያዋጣ ስለገባቸው ይንከባከቡታል።

የመሪ ግብረ ገብነቱ ያለው የግል ሕይወቱም ሚዛን ውስጥ መግባቱ የሚጠበቅ ነው። የሥነ ምግባር ጉድለት ማጥቂያ መንገድ ሊሆን ስለሚችልም ተቀናቃኝን ለማሸነፍ የግልና የቤተሰብ ሕይወት ይብጠረጠራል፤ በየቦታው ያለ ጉድለት ሁሉ ይፈተሻል። መሪ በቀደመ ታሪኩ፣ በአኗኗሩ፣ በቅንነቱ፣ በግልጽነቱ፣ በታማኝነቱ፣ በሥነምግባሩ፣ ባለው ፈሪሃ እግዚአብሔር ይመዘናል።

በእኛ ዘንድ ያለው ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነው:: በየዘመኑ ቅኝ መሪዎች የመኖራቸውን ያህል የሚበዛው የአመራር ባህል ግን እርስ በርስ መተማመን የጎደለበት፣ አንዱ ሌላውን ጠልፎ የሚጥልበት፣ ሴራ የሚበዛበት፣ መደማመጥ የጠፋበት ፣ በአሳብ መሸናነፍ ሳይሆን ጉልበት ያለው የሌለውን በኃይል የሚገዛበት፣ የሚያስርበት፣ የሚገድልበት፣ በዚህም ምክንያት ብዙ ደም የፈሰሰበት ስደት የበዛበት ታሪክ ነው:: የአመራር ችግሩም በየጊዜው እየባሰ እንጂ እየተሻለ አልሄደም:: ይባስ ብሎ አለመታመን፣ ሌብነት፣ ሙሰኝነት እየተስፋፋ፣ ራስ ወዳድነት እና ዘረኝነት ሥር እየሰደደ መጣ:: ከመተባበር መለያየት በሁሉም መስክ ቡድንተኛነት እና ጠባብነት መስፋፋቱን ሲቀጥል በዚያው መጠን የመሪዎች የሞራል ዝቅጠትም እየባሰ የሄደበት ዘመን ነው ማለት ይቻላል::

የዚህ መጽሐፍ እይታ ይህ ሁሉ የሆነው የመሪዎች የዓቅም ውሱንነት ብቻ ሳይሆን የቅንነት መጥፋት፣ የፈሪሃ እግዚአብሔር አለመኖርና አገሪቱ የነበሯት በጎ እሴቶች እየተሸረሸሩ መሄድ ናቸው የሚል ነው:: መሪዎች ቅንነት ሲጎድላቸው ብልጣብልጥነት፣ ውሸት፣ ሸፍጥ፣ ተንኮል እና ሌብነት ባህል እየሆነ መጣ የሚል ዕሳቤ አለው:: በተመሳሳይም እንዲህ ዐይነቱ የሥነ ምግባር ማሽቆልቆልና የእሴት መሸርሸር በየደረጃው በትምህርት ቤት፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በማኅበራዊ ተቋማት መሪዎችም ተጽእኖ ሊያሳድር ችሏል የሚል እይታም ተካቶበታል:: ከዚህ በተጨማሪም ሥልጣንን የማገልገያ መሳሪያ መሆኑን የመረዳትና በተግባርም አገልግሎት የመስጠት ባህል ሊዳብር አልቻለም የሚለውም የመጽሐፉ አንዱ እይታ ነው::

ለአንባቢያን እንዲመች ታስቦ መጽሐፉ በሁለት ክፍል የሚቀርብ ይሆናል:: የመጀመሪያው ክፍል “ቅን መሪ” የተሰኘው ይህ መጽሐፍ ሲሆን የዚህ ተከታይ መጽሐፍ ደግሞ “ባለ ራእይ መሪ” በሚል ርእስ በጥቂት ሳምንታት የሚቀርብ ይሆናል:: የመሪ ስኬታማነት መልካም

ጠባይ ከችሎታ ጋር ሲደመር ነው (Character + Capacity= Effective Leader) **በሚለው እሳቤ "ቅን መሪ" የሚለው ስለ መሪ ጠባዕያት የሚዳስስ ሲሆን ባለ ራእይ መሪ የሚለው ደግሞ የመሪ ችሎታን የሚመለከት ይሆናል**::

መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በቅንነትና በአገልጋይነት ላይ የተመሠረተ የአመራር ባህልን በማሳደግ ከአመራር ችግር ለመውጣት በሚደረገው ጥረት አስተዋጽዖ ለማበርከት ታስቦ ነው። መሪ ማለት የሥልጣን ወንበር ላይ የተቀመጠ ሰው ማለት ብቻ አይደለም። በሥልጣን ወንበር ቢቀመጥም ባይቀመጥም ለሚያምንበት ዕላማ ተከታዮችን ማፍራት የቻለና ተከታዮቹን አስተባብሮ ዕላማውን የሚያስፈጽም ሁሉ መሪ ነው። ቤተሰብን ማስተዳደር እንኳ የመሪነት ክህሎትን ይፈልጋል። በቅንነት መምራት፣ አገልጋይነትና ግብረ ገብነት የማይነካው ዘርፍ የለም። በሁሉም ዘርፍ በሁሉም እርከን ያሉ መሪዎችን ሁሉ የሚመለከት ነው። በየዘርፉ በየደረጃው የመሪነት ሚና የሚኖረው ትውልድ ላይ ዛሬ ሥራ ቢሠራ ነገን የተሻለ ማድረግ ይቻላል ከሚል እምነት የተጻፈው ይህ መጽሐፍ ለዛሬዎቹ መሪዎች ብቻ ሳይሆን ለነገዎቹም መሪዎች ነው።

በቅንነት መምራትና አገልጋይነት በየደረጃው ያሉ የሃይማኖት መሪዎችን፣ በየደረጃው ያሉ የሲቪክ ተቋማት መሪዎችን፣ በየደረጃው ያሉ የማኅበረሰብ መሪዎችን፥ ልሂቃንን፥ በየደረጃው ያሉ የፖለቲካ መሪዎችን ይመለከታል። የንግድ ተቋማት መሪዎችንም እንዲሁ። የሥራ አመራር በመሪዎችና በተመሪዎች መከካከል ያለ ግንኙነት ከመሆኑ አንጻር ተመሪዎችም

የሚጠቀሙበት መጽሐፍ ነው:: በአጠቃላይ ቅንነት፣ አገልጋይነት፣ ግብረ ገብነት የማይነካው የማኅበረሰብ ክፍል የለም፡፡

መጽሐፉ በሦስት ክፍሎች የተከፈለ ነው:: አወቃቀሩም የመጽሐፉን ዐላማ የተከተለ ነው::

ክፍል አንድ አምስት ምዕራፎችን አካቷል:: በቅንነት ላይ የተመሠረተ የአመራር ባህል የሚል ርእስ ሲኖረው ስለ ቅንነትና ቅን መሪ በሰፊው ይተነትናል:: ክፍል አንድ ለማሳየት የሚሞክረው መልካም አመራርን ለማፍራት ቅንነት የሚኖረውን ሚና ነው:: የተሻለ አገርን መገንባትን በተመለከተ ከሚፈለገው አገራዊ ግብ ላይ ለመድረስ በቅንነት ላይ የተመሠረተ የአመራር ባህልን አስፈላጊነት ማስረዳት አንዱ የመጽሐፉ ዐላማ ነው:: መነሻውም የአመራር ስኬት ወይም ውድቀት ከቅንነት መኖር ወይም ከቅንነት መጥፋት ጋር የተቆራኘ ነው የሚል ነው:: መሪነትና ቅንነት ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ በመጀመሪያው ምዕራፍ ተካቷል:: ታማኝነት ነው አንዱ የቅንነት መገለጫ:: ቅንነት ታማኝነትና ሐቀኝነት የተያያዙ እንደመሆናቸው በምዕራፍ ሁለት ለመዳሰስ ተሞክሯል:: ይህ ክፍል ታማኝነትን እንዴት ማግኘት ይቻላል? በአስቸጋሪ ሁኔታ ሐቀኛ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው በሚል የተወሰነ አሳብን ለማካፈል የሚሞከር ነው:: ፍትሐዊነት ከታማኝነት፣ ከሐቀኝነት ጋር የሚያያዝ እንደመሆኑም ምዕራፍ ሦስት የሚመለከተው ፍትሐዊነትን ነው:: ቅንነት ከትሕትናና ከየዋህነት ጋር ያለውን ግንኙነትና ስለ ትሑት መሪ የሚዳስሰው ደግሞ ምዕራፍ አራት ነው:: በዚህ ክፍል የመጨረሻው ምዕራፍ አብሮ ስለ መሥራት የሚዳስስ ነው:: የቅንነት አንዱ ውጤት የሆነው በመግባባትና በስምምነት ለጋራ ዐላማ በጋራ መሥራት እንዴት ይቻላል የሚለውን በምዕራፍ አምስት ለማካተት ተሞክሯል::

ሁለተኛው ክፍል አገልግሎትና አገልጋይነትን የተመለከተ ነው:: በአገልግሎት ላይ የተመሠረተ የአመራር ባህል ሲያድግ የተሻለ አመራርን ለማስፈን ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል የሚለውን ለመዳሰስ የሚሞክር ነው:: ሥልጣንን ለመገልገያነት ሳይሆን ሌሎችን ለማገልገል መሳሪያነቱን አምኖ የሚቀበል አገልጋይ መሪን ማፍራት እስካልተቻለ ድረስ የተሻለ

አመራርን መፍጠር አይቻልም የሚል አቋም የተንጸባረቀበት ነው:: በዚህ ክፍል በሦስት ምዕራፎች የተያያዙና አንዱ ለሌላው መቆም የሚያስፈልጉ ሐሳቦች ተካተውበታል:: ምዕራፍ ስድስት ትኩረት የሚያደርገው የአገልግሎትን ምንነት በመዳሰስ ላይ ነው:: ምዕራፍ ሰባት አገልግሎትንና መሪነትን በተመለከተ ይተነትናል:: በዚህ ምዕራፍ ስለ አገልጋይ መሪ ምንነትና የአገልጋይ መሪ መገለጫዎችን በሰፊው ለማንሣት ተሞክሯል:: ምዕራፍ ስምንት ሥልጣንና አገልግሎት ስላላቸው ግንኙነትና በተለይም ሥልጣን የአገልግሎት መሣሪያ ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ የተወሰኑ ሐሳቦችን ይዳስሳል::

ሦስተኛው ክፍል ቅንና አገልጋይ መሪዎችን ለማፍራትና በቅንነትና አገልጋይነት ላይ የተመሠረተ የአመራር ባህልን ለማስፋፋት ሥነ ምግባር ያለውን ድርሻ አካትቷል:: ይህ ክፍል ሁለት ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን ምዕራፍ ዘጠኝ ሥነ ምግባር ምን ማለት እንደሆነና ሥነ ምግባርን የመገንባት ድርሻን አጉልቶ የሚያሳይ ነው:: ምዕራፍ አሥር የመጨረሻው ምዕራፍ ሲሆን ስለ ግብረ ገብ መሪ የሚተነትን ነው:: መሪነትና ሥነ ምግባር ስላላቸው ግንኙነትና በዚህ ረገድ ስላሉ ችግሮች በዚህ ምዕራፍ ይዳሰሳል::

የመጽሐፉ ግብ የተሻለ አመራርን መገንባት ሲሆን የተሳካለት መሪ መሆን የሚቻለው ችሎታ ከመልካም ጠባይ ጋር መያዝ ሲቻል ነው የሚለውን ትኩረት ያደርጋል:: መልካም ጠባይ ለመሪ ስኬት ያለውን አስተዋጽዖ በአሥሩ ምዕራፎች የተካተተ ሲሆን የመሪ ችሎታ ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ በቅርብ ወራት በሚታተመው "ባለ ራእይ መሪ" ተብሎ በተሰየመው መጽሐፍ የሚቀርብ ይሆናል:: ብልህነትና አስተዋይነት የመሪ ችሎታ የሚገለጽባቸው ሲሆን ተቋማዊ ዓቅምንና ተቋማዊ አሠራርን ማጎልበት፣ ባለ ራእይነት፥ ውሳኔ አሰጣጥ፥ ለውጥን መምራት፥ በጋራ ራእይና በጋራ እሴት ማስተባበርና ማስተሳሰር እንዲሁም አለመግባባትንና ግጭትን በሰላም መፍታት የመሳሰሉ አንኳር ጉዳዮች "በባለ ራእይ መሪ" መጽሐፍ የሚካተቱ ይሆናል::

የሥራ አመራር ክህሎትን ከተጨባጭ ተሞክሮዎች ጋር በማዋሐድ ስለቀረበ ብዙ ዕውቀቶችን ለመገብየት ያስችላል የሚለውም ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው:: ዋና ዋና የሚባሉ የመሪነት ክህሎቶችና ጠባዕያት በሰፊው ተካተውበታል:: ከእያንዳንዱ ምዕራፍ ምናልባትም ከአንድ በላይ መጽሐፍ ሊጻፍባቸው የሚችሉ ሰፋፊ ሐሳቦች ሊፈልቁበት ይችላል፡፡ ችግሮቹም ሰፋፊና አንዳንዱም ውስብስብ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል:: የአንድ አገርን የአመራር ባህል በጥልቀት ለመመርመር እና በመረጃ ለማስደገፍ ብዙ ዓመታትን የሚፈጁ ጥናቶች፣ ውይይቶችና የበቁ ባለሙያዎችም እንደሚፈልጉም መረዳት አይከብድም:: በመሆኑም ይህ መጽሐፍ ትኩረቱ እነዚህ ጉዳዮች የበለጠ ምርምር ጥናትና ግልጽ ውይይት እንዲደረግባቸውና ለአገር ግንባታ በጎ አስተዋጸዖ ማበረከት እንዲቻል ማመላከት ነው::

ከላይ እንደተጠቀሰው በእያንዳንዱ ጉዳይ ጥናትና ምርምር ማድረግ ከዚህ መጽሐፍ ማዕቀፍ በላይ ቢሆንም ጉዳዩቹ በተለያዩ ጊዜ በመጻሕፍት የተጻፉትን፣ በታሪክ የሚነገሩትን፣ በየቀን ውሎ የሚታዩትን፣ በየዕለቱ በሕዝብ ሚዲያ ወይም በሌላ መንገድ የሚነገሩትን፣ መሬት ላይ ያሉ ነባራዊ እውነታዎችን መሠረት ያደረጉ ሥራዎች ናቸው:: ጉዳዮቹንም ለመዳሰስ የተሞከረው በመርህ ደረጃ ያለውን መሠረት በማድረግ ነው:: በአጠቃላይ ሥራው ለሌሎች ሥራዎች መንደርደሪያ ሆኖ ሊቆጠር የሚችል ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ማጣቀሻ የተወሰደ ቢሆንም ሁሉም አንባቢ ሊጠቀምበት በሚችል መልኩ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው:: ለሚያምንም ሆነ ለማያምንም ታሪኮቹ ለመረዳት ቀላልና ብዙ ግንዛቤን እንዲሁም ዕውቀትን የሚሰጡ በመሆናቸው ማንኛውም ሰው ሊጠቀምበት ይችላል:: በመሪነት ዙሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ የተመዘገቡ ታሪኮች ዘመናት የሚሸራቸው አይደሉም:: መጽሐፍ ቅዱስ የብዙ መሪዎችን ታሪክ በውስጡ ይዟል:: የጠንካራ መሪዎችንም፣ የደካማ መሪዎችንም፣ የቅን መሪዎችንም፣ የክፉ መሪዎችንም፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበራቸው መሪዎችን የትዕቢተኛና

ዓመፅኛ መሪዎችንም:: ይህ ሁሉ የተጻፈው ለትምህርት ነው:: ከበጎው እንድንማርበት፣ ክፉውን ታሪክም ላለመድገም::

በዚህ መጽሐፍ ፈሪሃ እግዚአብሔር በሚል የተጠቀሰው የአንድን ወይም የሌላ እምነት ተከታይን ለማለት ሳይሆን በሚያምንበት እምነት ፈጣሪውን የሚፈራ ለማለት ነው:: የሰው እምነት ቢለያይም ከልዩነቱ ይልቅ አንድነቱ ይበዛል:: እምነታችን ቢለያይም ፈጣሪን በመፍራት፣ ለእውነትና ለፍትሕ በመቆም፣ በግብረ ገብነት እና በመሳሰሉ ጉዳዮች አንድነት አለን:: በእምነት ጉዳይ መለያየቱ እንዳለ ሆኖ በቅነንት፥ በአገልጋይነት፥ በግበረ ገብነት በሰላም፣ በፍቅር፣ በይቅርታ፣ በመረዳዳት፣ በመቻቻል እና በመሳሰሉ ጉዳዮች አንድነት ስላለ ከልዩነቱ አንድነቱ ይበዛል:: የተለያዩ የእምነት ተቋማት በጋራ የሚሠሩ ሥራዎችን ተባብረው ሲሠሩ ማየትም የተለመደ ነው::

በፍልስፍናው መንገድ ብዙ የተባለለት ስለሆነ በዚህ መንገድ ማየቱ ደግሞ የተለየ እይታን እንደሚፈጥር በማሰብ እንዲህ ባለ መልኩ ቀርቧል::

መልካም ንባብ!

ክፍል አንድ

በቅንነት ላይ የተመሠረተ የአመራር ባህል

ምዕራፍ አንድ

ቅን መሪ

1.ቅንነት ምን ማለት ነው?

ቅንነት በብዛት ሲነገር የሚሰማ ቢሆንም ቅን መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ ቅንነት እንዴት እንደሚገኝ ግን ሰፊ ውይይት የሚፈልግ ጥልቅ አሳብ ነው::

አማርኛ መዝገበ ቃላት[1] ቅንነት ለሚለው ቃል የሚሰጠው ትርጉም፡- በልብ ተንኮል አለመኖር፣ ገርነት፣ ቅን መኾን የሚል ነው:: የእግሊዘኛ ትርጉሙንም benevolent, sincerity, forthrightness, frankness, correctness, heartiness, positiveness በሚለው ቀርቧል:: ቅን ለሚለው የሚሰጠው ትርጉም ደግሞ በመንፈሱ ጠማምነት የሌለበት፣ መልካም አሳቢ፣ በጎ ሰው፣ በጎ ልብ፣ ልበ ገር የሚል ነው::

ቅዱስ መጽሐፍም የቅንነትን ትርጉም በሰፊው ሊያስረዳን ይችላል:: ቅንነት የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታም ይሁን በተዛማጅ

[1] https://dictionary.abyssinica.com/%E1%89%85%E1%8A%95%E1%8A%90%E1%89%B5

በብዛት የተጠቀሰ ሲሆን በቀጥታ ቃሉ ከተጠቀሰባቸው መልእክቶች የሚከተሉትን ለአብነት ያህል መመልከት ይቻላል::

“ዳዊትም አባትህ በየዋህ ልብና በቅንነት እንደ ሄደ አንተ ደግሞ በፊቴ ብትሄድ፣ ያዘዝሁህንም ሁሉ ብታደርግ፣ ሥርዓቴንም ፍርዴንም ብትጠብቅ፣ እኔ ከእሥራኤል ዙፋን ከዘርህ ሰው አታጣም ብዬ ለአባትህ ለዳዊት እንደ ተናገርሁ፣ የመንግሥትህን ዙፋን በእሥራኤል ላይ ለዘላለም አጸናለሁ።” (1ኛነገ 9፥14) የሚለው አንዱ ሲሆን ዳዊት እንዴት አድርጎ ሕዝቡን ቢመራ ነው በቅንነት መራቸው የተባለለት የሚለውን ለማወቅ የዳዊት ሕይወት ምን ይመስል እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው የተመዘገበ ነው።

“በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፣ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፣ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም” በሚለው ደግሞ ቅንነት ከፈሪሃ እግዚአብሔር፣ ከጽድቅ ወይም ከክፋት መራቅ ጋር ተያይዟል:: (ኢዮ 2፥3)

“ቅኖች ቅንነታቸው ትመራቸዋለች፣ ወስላቶችን ግን ጠማማነታቸው ታጠፋቸዋለች።” በሚለው ወስላታነት የቅንነት ተቃራኒ ሆኖ መቅረቡ ቅንነትን ለመረዳት ተጨማሪ ግንዛቤን የሚፈጥር ነው:: (ምሳ 11፥3)

“ያለ ነውር የሚሄድ ተማምኖ ይሄዳል፣ መንገዱን የሚያጣምም ግን ይታወቃል።” በሚለው ኃይለ ቃል የቅንነት ተቃራኒ ጠማማነት እንደሆነ እንረዳለን:: (ምሳ 10፥9)

“ጠላቴ እልል አይልብኝምና ስለዚህ እንደ ወደድኸኝ አወቅሁ። እኔን ግን ስለ ቅንነቴ ተቀበልኸኝ፣ በፊትህም ለዘላለም አጸናኸኝ።” የሚለው የቅንነት ዋጋ ምን ያህል የከበረ እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነው:: (መዝ 40፥11-12)

በቅንነት ላይ ለተመሠረተ አመራር የሚቀርበው የእንግሊዘኛው ትርጉም Benevolent leadership የሚለው ነው:: በቅንነት ላይ የተመሠረተ አመራር በዚህ ትርጉም መሠረትም በጎ ፍላጎት፣ መልካም ማድረግን፣

ፍትሐዊነትን፣ አገልጋይነትን የሚመለከት የአመራር ባህል ነው::[2]

እንግዲህ በዚህ መጸሐፍ ለቅንነት የተሰጠው ትርጉም እነዚህን ሁሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው:: ይህ ሰው ቅን ሰው ነው፤ ቅን አሳብ ያለው ሰው ነው፤ ቅን ልብ ያለው ሰው ነው፤ አስተሳሰቡ ቅን ነው፤ አመለካከቱ ቀና ነው፤ ነገሩን ሁሉ በቅንነት የሚያይ ሰው ነው፤ ቅን መንፈስ ያለው ሰው ነው፤ ሥራውን በቅንነት የሚሠራ ሰው ነው፤ እውነትን የሚወድ ሰው ነው፤ ፍትሕን የሚወድ ሰው ነው፤ ቀጥተኛ ሰው ነው በሚል መልኩ ቅን ሰውን የመግለጽ ልማድ አለ::

በተቃራኒው ጠማማ ነው፤ ተንኮለኛ ሰው ነው፤ ውስብስብ ሰው ነው፤ ሸፍጥና ሴራን የሚያበዛ ሰው ነው፤ ክፉ ሰው ነው፤ ብልጣብልጥና ቀጣፊ ነው፤ አጭበርባሪና ዋሾ ነው፤ ጮሌ ነው፤ አታላይ ነው፤ ሸረኛ ሰው ነው፤ አስመሳይ ሰው ነው፤ ነገረኛ ሰው ነው በሚል ደግሞ ቅንነት የጎደለውን ሰው ይገልጹታል::

“እንዲያው አልሳካለት ብሎ እንጂ ከልቡ ነው የሚሠራው” በሌላ በኩል ደግሞ “ዓቅም ነበረው ግን ምን ያደርጋል ጠማማ ነው” የሚለው ቅን መሪንና ክፉ መሪን ለመግለጽ ሲነገር የሚሰማ ነው:: ጥሩ ጭንቅላት ያለው መሪ ነበር ግን ምን ያደርጋል ተንኮለኛ ነው:: ብሩህ አእምሮ ያለው መሪ ነው ጠማማ ነው እንጂ የሚል አገላለጽም የተለመደ ነው:: ቅንነት የጎደላቸው መሪዎች ተንኮል ጠንስሰው፣ ተንኮል አቅደው ተንኮል ሲሠሩ በአንጻሩ ቅን መሪዎች ለበጎ ዐላማ በጎ ነገርን አልመው ከልባቸው የሚጥሩ ናቸው:: አንድ ሰው ልቡ የሚያስበውና የሚናገረው ለየቅል ከሆነ ይህ የተንኮለኛነት አንዱ መገለጫ ሊሆን ይችላል:: የልብ ፍላጎትንና እውነተኛ ዐላማን ደብቆ በሚያባብል እና በሚያታልል ቃል ማሳሳት እንዲህ ካሉ ሰዎች በተደጋጋሚ የሚታይ ነው::

[2] Benevolent leadership is an expression of benevolence, the will and good intentions, and the actions taken by the leader for the greater good (Ghosh, 2015). Benevolent leadership not to be served but rather how to serve, guide, and create a sense of well-being and justice (Rianse, 2012).

ተንኮል፣ ውስብስብነት፣ ሽፍጥ፣ ሴራ፣ ብልጣብልጥነት፣ ጮሌነት፣ ስግብግብነት፣ አጭበርባሪነት፣ አስመሳይነት፣ አለመታመን፣ ሐሰተኛነት፣ እብሪት፣ ጠማማነት፣ ጠባብነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከቅንነት መጉደል ጋር የሚያያዙ ናቸው:: እንዲህ ዐይነት መሪዎች ገደብ ለሌለው የሥልጣን ፍላጎታቸው ሲሉ የሚሠሩት ተንኮል ነው አሁን ላለንበት ችግር የዳረገን የሚል አሳብም በተደጋጋሚ ይነሣል:: መሪዎች የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም ሲሉ እርስ በርስ የሚያስማማ ሳይሆን የሚያለያይ ትርክትና የሴራ ፖለቲካ ነው ሀገሪቷ ወደፊት እንዳትጓዝ ያደረጋት የሚል ነገር ነው በየጊዜው የሚሰማው:: ቅንነቱ ቢኖር ኖሮ አገሪቱን የማቃናት እድል ነበራቸው የሚል ነው አሳቡ:: ቅንነት የጎደለው አመራር ነው የሚል አነጋገርም የተለመደ ነው:: ዐላማቸው ቅንነት የጎደለው ነው፤ ሲያጭበረብሩን እንጂ አጀንዳቸው ሌላ ነው፤ የተደበቀ መሠሪ ዐላማ አላቸው የሚለውም እንዲሁ:: እንዲህ ዐይነቱ አመራር ነው ሽፍጥና ተንኮል የሞላበት ቅንነት የጎደለበት አመራር የሚባለው::

ቅን ያሰበ ሁሉ ይሳካለታል ማለት ግን አይደለም:: ያ ሌላ ነገር ነው:: ዋናው በቀና መንፈስ ማሰብና ጥረት ማድረጉ ላይ ነው:: ቅን ሰው ማለት ለበጎ ዐላማ፣ ለጥሩ ውጤት በቀና ልቦና፣ ሰውን ለመጥቀም አስቦ የሚሠራ ማለት እንጂ ፍጹም፣ ጻድቅ፣ ማለት ሊሆን አይችልምና::

ቅንነት በብዙ ነገር ይገለጻል:: ቀና ልቦና፣ ቀና አስተሳሰብ እና ቀና አመለካከት መኖር አንዱ የቅንነት መገለጫ ሊሆን ይችላል:: ታማኝነት፣ ሐቀኛነት፣ ፍትሐዊነት፣አገልጋይነት ከቅንነት ጋር የሚያይዛቸው ብዙ ነገር አለ:: ቅንነት በተግባር ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰብም በስሜትም በንግግርም የሚገለጽ ነው:: ቅንነት እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር በእጅጉ እንደሚያያዝም “እርሱ ፍጹምና ቅን፣ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፣ ከክፋትም የራቀ ሰው...” ሲል እግዚአብሔር ኢዮብን የገለጸበት መንገድ ያሳየናል:: ልቡ ቅን የሆነ ስለ ሰው ክብር ያለው አስተሳሰብ ቅንነት ከጎለዳቸውና እግዚአብሔርን ከማይፈሩ ሰዎች የተለየ ነውና::

ቅንነትን እና መሪነትን በተመለከተ እነዚህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ማንሣትም ተገቢ ነው::

- ቅን መሪ ስንል ምን ማለታችን ነው?
- የአመራር ችግር ምንጩ ምን ያህል ከቅንነት መጥፋት፣ ቅን መሪዎችን ከማጣት ጋር የሚያያዝ ነው?
- መሪ ቅን መሆን ይቻለዋል ወይ? መሪ ትሑት፣ ደግ፣ ሩኅሩኅ ሊሆን እንዴት ይችላል?
- እንደ አገር በአመዛኙ የአመራር ባህሉ ቅንነት፣ ደግነት፣ ግልጽነት፣ ታማኝነት፣ መደጋገፍና አብሮ የመሥራት ነው? ወይስ የሴራ የመጠላለፍ፣ የተንኮል፣ የብልጠትና የማጭበርበር?
- ቅንነት በሌለበት ሁኔታ፣ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት በሚያደባበት፣ መከባበር ሳይሆን መናናቅ፣ መደጋገፍ ሳይሆን አንዱ ሌላውን ጠልፎ ለመጣልና ጥሎ ለማለፍ፣ ከርኅራኄ ይልቅ መጨካከን በበዛበት ሁኔታ የተሰካ አመራርን ማምጣት እንዴት ይቻላል?
- የመናቆር፣ የመጠላለፍ፣ ያለመከባበር፣ የመናናቅ፣ የመካረር፣ ከዚያም ሲያልፍ የመጠፋፋት የአመራር ባህል ምክንያቱ ምንድን ነው?
- ለቅንነት ዋጋ የሚሰጥ፣ ቅን መሪዎችን የሚናፍቅ ወይስ ጨካኝ መሪዎችን እንደ ጀግና የሚያሞግስ ከቅንነት ይልቅ ለክፋት የሚመች ባህል ነው ኅልቶ የሚታዬው ወይስ በተቃራኒው? መሪዎች ምን ያህል ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲኖራቸው የመፈለግ ባህል አለ?
- ለቅንነት ዋጋ የሚሰጥ ባህል ደካማ በሆነበት ቅን መሪ እንዴት ሊበቅል፣ እንዴትስ ሊያድግ ይችላል?
- ቅንነት በሚጎድልበት ሁኔታስ ምን ያህል ወደፊት መጓዝ ይቻላል?

እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች በቀላሉ መልስ የሚገኝላቸው አይደለም። ነገር ግን እነዚህንና የመሳሰሉትን ነጥቦች እያነሡ መወያየት ሲቻል፣ የችግሩን ምንጭ ለመለዬትና የጎደለውን በማወቅ ወደ መትሐኤ ሊያመራ ይችላል ከሚል ነው። ጥያቄዎችን በበቂ ሁኔታ ለመመለስ ሰፊ ጥናት የሚፈልግ ቢሆንም ጉዳዮችን እንደሚከተለው ዘርዘር አድርጎ ማየትም ይቻላል።

1.1 ቅን መሪን ፍለጋ

በ 1994 ዓ.ም "የምሁራን ውይይት" ላይ አንድ ምሁር ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ባቀረቡት ምክር አዘል ጥያቄ "ኪሲ በርእስዎ ቁጥጥር ስር ስላለች አሁን ምን ልናደርግ ነው የምንችለው? እኔ የምለው ቅንነት ብቻ ነው የሚያስፈልገው፣ እርስዎ ቅን እንዲሆኑ ነው የምመኘው፣ በቅንነት እንዲመሩን ብቻ ነው እኔ የምመኘው፣ የዚች አገር እድል በእርስዎ ቁጥጥር ስር ስላለ ቅንነት እንዳይለየዎ ብቻ ነው ተስፋ ለማድረግ የምችለው" [3] የሚለው ንግግር የብዙዎችን ቀልብ የሳበ ስለነበረ አሁንም ድረስ የሚያስታውሱት ይኖራሉ። ቅን መሪን መመኘትን በደንብ ሊያሳይ የሚችል አገላለጽ ነው። በእነዚህ ጊዜ እንኳን ቅንነቱ ቢኖር ስንት ነገር ማስተካከል በተቻለ ነበር

ስለ ቅን መሪ ሲነሳ በሰው ላይ የተንጠለጠለ ሳይሆን በተቋም ላይ የተደላደለ ስርዓት ነው የሚያስፈልገው የሚል ሙግት መቅረቡ የሚጠበቅ ነው። የሕግ የበላይነትና ተጠያቂነት ያለበት ጠንካራ ተቋማዊ ስርዓት መኖሩ እንጂ መሪ ቅን ሆነ አልሆነ ምንም አይፈይድም የሚል ነው አስተያዬቱ። እንዲህ ዐይነቱ አስተያዬት እውነትነት ያለው ቢሆንም ቅን መሪ አያስፈልግም የሚል መደምደሚያ ግን አያደርስም። ምክንያቱም አንደኛ ጠንካራ ተቋማዊ አሰራርና ጠንካራ ተቋማት ሊገነቡ የሚችሉት ቅን መሪዎች ባሉበት ነው። ተንኮል ባለበት አካሄድ ያሉትም ተቋማት እንዬት እንደሚዳከሙና ሁሉም ነገር በአምባገነን መሪዎች እጅ እንደሚወድቅ በተግባር የታዬ ስለሆነ። ሁለተኛው ጠንካራ ተቋማዊ ዓቅምና የሕግ የባላይነት ባለበት ሁኔታ እንኳ ጠንካራ ተቋምዊ ስርዓት

[3] https://www.youtube.com/watch?v=erFyU_2s6cc

ሊናድ እንደሚችልም በተወሰኑ አገሮች ታሪክ ለማዬት ተችሏል። በሦስተኛ ደረጃ ጠንካራ ተቋማዊ ዓቅም የሕግ የበላይነትና የተጠያቂነት ስርዓት ቢኖር እንኳ ታማኝነት በሌለበት፣ እብሪት በሚበዛበትና ግብረገብነት በጎደለበት ሁኔታ ሕግ ብቻውን ሙሉ ዓቅም ላይኖረው ይችላል የሚለውን ታሳቢ ያደረገ ነው። በመጨረሻም ቅን መሪ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል በተቋም ላይ የተመሠረተ አሰራር፣ ጠንካራ ተቋማት፣ የሕግ የባላይነትና የተጠያቂነት ስርዓት ጎን ለጎን አስፈላጊ ናቸው የሚለውን ታሳቢ የሚያደርግ ነው እሳቤው። በቅርብ የሚታተመው የዚህ መጽሐፍ ተከታይ የሆነው "ባለ ራእይ መሪ" የሚለው መጽሐፍ የሚሸፍነው ይህንን ጉዳይ ነው።

ያም ሆነ ይህ መሪ በማጣት ለብዙ ዘመናት የተጎዳ ሕዝብ አዲስ መሪን በሙሉ ልብ መቀበል ይችገራል። ብዙ ተስፋ ተጥሎባቸው ፍጻሜያቸው ግን ጥፋት የሆኑ መሪዎችን አይቷልና ብዙ ጥያቄዎችን ያወጣል ያወርዳል። ይህ መሪ የሚታመን ነው? ክልቡ ነው ወይስ እየሸነገለን ነው? ይህ ነገር ከአንገት ነው ወይስ ከአንጀት? የሚናገረውን የሚያደርገውን ወይስ መስማት የምንፈልገውን ነው? እውነተኛ ወይስ አስመሳይ ሰው ነው? እስከ መጨረሻው እንዲህ ይዘልቅ ወይስ ይቀየር ይሆን? በማለት ይጠይቃል። እነዚህ መሪዎች ሌላ የተደበቀ አጀንዳ አላቸው፤ የእነንትና ጀርባቸው ሲጠና፤ ጀርባቸው ሲፈተሽ ብዙ ጉድ አለው፤ ዐላማቸውና የሚናገሩት ለየቅል ነው፤ ሲያታልሉን ነው እንጂ መሠሪ ዐላማ ያለው አካሄድ ነው፤ የሚል ነገር መስማትም የተለመደ ሆኖአል። እንዲህ ዐይነቱ ችግር የቅንነት መጉድል ባለበት የአመራር ባህል የሚከሠት ነው። በጥቅሉ እነዚህ እና የመሳሰሉት ጥያቄዎች በአንድ ነገር ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው። ቅን መሪን ፍለጋ።

መልሱ ግን ቀላል አይደለም። "የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው፣ ማንስ ያውቀዋል?" እንደተባለ የመሪን ልብ ሊያወቅ የሚችለው ከእግዚአብሔር ሌላ ራሱ መሪው ብቻ ነው። (ኤር. 17.9) ጥፋትም ይሁን ልማት ሁሉን ሊያረጋግጥ የሚቻለው ጊዜ ብቻ ነውና። ትልቁ ቁም ነገር ቅን መሪን ማግኘቱ ላይ ነው።

ከእግዚአብሔር በታች ለበጎም ለክፉም የአገር ዕጣ ፈንታ በመሪ ይወሰናል:: መልካም መሪ አገርን ሊያቃና እንደሚችል ሁሉ በክፉ መሪ የተነሣ አገር ሊያሽቆለቁልም ይችላል:: መርከቡ በመሪው እጅ ነው:: መሪ አንዱ ሥልጣን ከያዘ የአገርን ታሪክ ሊቀይር የሚችልበት ኃይል አለው:: ጥያቄው በእጁ የገባውን ኃይል ለበጎ ወይስ ለክፉ ሊጠቀምበት ይችላል? የሚለው ነው እንጂ:: የተቋም መውደቅና መነሣትም በአብዛኛው በመሪው ዓቅም ብቻ ሳይሆን በመሪው ቅንነትም ይወሰናል:: አከራካሪ ሊሆን ቢችልም በተለይ ተቋማዊ ሥርዓትና የሕግ የበላይነት ባልጎለበት ሁኔታ አብዛኛው ነገር የሚወሰነው በመሪው ቅንነት ነው ለማለት ይቻላል::

በዓለም ታሪክ ሲወሱ የሚኖሩ፣ ለዘመናት አሻራቸውን የተዉ፣ በየትውልድ እንደ አርአያ የሚጠቀሱ መሪዎች ዋናው መገለጫቸው በቅንነት መምራታቸው፣ የተጣለባቸውን ሓላፊነት በቅንነትና በታማኝነት መወጣቸው፣ የተሰጣቸውን አደራ መጠበቃቸው፣ ሥልጣንን ለራስ ጥቅም ለራስ መበልጸጊያ ሳይሆን ሕዝባቸውን ለማገልገል ማዋላቸው፣ የሚናገሩትን ነገር በአመዛኙ በተግባር ማሳየት መቻላቸው መሆኑም የታወቀ ነው::

ቅኖች መሪዎች ማለት ፍጹማን መሪዎች ማለት ግን አይደለም:: ዘወትር ከስሕተታቸው በቅንንነት ለመማር የማይሰለቹ መሆናቸው ነው እንጂ:: ቅኖች መሪዎችን ቅኖች የሚያሰኛቸው ሰባት ጊዜ ቢወድቁ ሰባት ጊዜ የሚነሡና ከስሕተታቸው እየተማሩ ከትንናት ዛሬ የተሻሉ መሪዎች ሆነው መገኘታቸው ነው:: መሪነት ብዙ ፈታኝ ሁኔታዎች አሉበትና ሁሉም በአንጻራዊነት ነው ሊታይ የሚገባው:: ቅንነታቸው ከክፋታቸው በእጅጉ ያመዝናል ማለት እንጂ ቅኖች መሪዎችን ብዑዓን ናቸው ማለትም አይደለም:: በቅነታቸው የሚታወሱ መሪዎች ድካም ቢኖርባቸውም የሚቻላቸውን ሁሉ በቀና ልቦና ይሠሩ የነበሩ፣ የሚመሩትን አገር ወይም የተቋም ጥቅም አሳልፈው የማይሰጡ፣ ሕዝባቸውን ወይም የሚመሩትን ወገን ለግል ጥቅማቸውና ለሥልጣናቸው ሲሉ የማያጭበረብሩ፣ የማያታልሉ መሪዎች ናቸው እንጂ ብዑዓን ሊሆኑ አይችሉም::

የእኛ አገር የአመራር ችግር ዋናው ምክንያት ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ለመመለስ ብዙ ጥናቶችን እና ምርምሮችን እንደሚጠይቅ የሚጠበቅ ቢሆንም የቅንነት መጥፋት ግን ተደጋግመው ከሚነሡ ዋና ዋና ችግሮች መካከል በቀዳሚነት ተርታ የሚሰለፍ ነው:: በየዘመኑ ቅኖች መሪዎች የመኖራቸውን ያህል ከቀደምት ነገሥታት ጀምሮ አብዛኛው ታሪክ ለሥልጣን በሚደረግ ሽኩቻ አንዱ ሌላውን ጥሎ የማለፍ፣ የነገርና የሴራ፣ የሸፍጥና የመከዳዳት፣ ያለመተማመን እና የመጠራጠር ታሪክ መሆኑን ነው የተጻፉ መጻሕፍት፣ የሚነገሩት ታሪኮች የሚያስረዱት:: በዘመናችን በዐይን ያየናቸውም የሚጠቁሙን እንዲህ ዐይነቱን ችግር ነው:: ችግሩ የከረመ ቢሆንም አሁን ያለው ትውልድ ከመሪዎቹ እያየ ያደገው በቅንነት ተማምነውና ተግባብተው በአንድ ላይ ሲሠሩ ሳይሆን በጋራ እየሠሩ፣ ለአንድ ዐላማ በአንድ ድርጅት ሥር ሆነው እርስ በርስ ሲካካዱ ነው:: የአመኗቸው ሰዎች ሳይቀር ያለ ፍርድ ሲረሽኑ፣ በወጡበት ሳይመለሱ የውኃ ሽታ ሆነው እንዲቀሩ ያደረገ ታሪክ ነው ያሳለፈው አሁን ያለው ትውልድ:: በተለይ ባለፉት ሃምሳና ስድሳ ዓመታት ጧት በጓድነት ተሰልፈው በጥቂት ቀናት መካከል በጠላትነት ተፈራርጀው ቅኖች በተንኮለኞች ተበልተው በወጡበት ሲቀሩ ይህንም እንደ ጀግንነት እየተቆጠረ ይፎከርበት የነበረ ዘመን ነው ያለፈው:: መጠላለፉና ችኩቻው በፖለቲካው ዘርፍ ብቻም አይደለም በሌላውም ዘንድ የሚታይ ነው::

መጠላለፉ እየባሰ እንጂ እየተሻለም አልመጣም:: መምራት ያለሴራ የማይቻል ይመስል አንዱ ድርጅት ከሁለት እየተከፈለ፤ ጉልበተኞች ደካሞችን ወደ እስር ሲያግዟቸው፣ የጥድፊያ ሕግ ተረቅቆ በሐሰት ክስ የሐሰት ዳኛ ተሰይሞ በሐሰት ምስክር ሲፈረድባቸው ማየት እየተለመደ መጣ:: ፓርቲዎች ከሁለት ተሰነጠቁ የሚለውም የየዕለት ወሬ ነበረ:: ይህ መከፋፈል እንደ በሽታ ወደ ሌሎችም ተዛመተምና የሃይማኖት መሪዎች ተከፋፈሉ የሚለው የተለመደ ዜና ሆነ:: መሪዎች እርስ በርሳቸው ተጠላለፉ፤ እገሌ የተባለው መሪ በሙስና ስም የታሰረው በተንኮል ነው እና ሌላም ሌላም ባህል እስከመሆን ደረሰ::

እንዲህ ዐይነቱ ነው ቅንነት የጎደለበት ሴራና ሸፍጥ የሞላበት አመራር ማለት። የሚተማመን ሳይሆን ዘወትር በዐይነ ቁራኛ የሚተያይ፤ ለአንድ ዐላማ የተሰለፈ አንድ ላይ የሚሠራ በአንድ የሚውል ነገር ግን ነገ ምን ብለው ይከሱኝ፣ ምን ብለው ያስሩኝ ይሆን? እያለ በስጋት የሚኖር አመራር ሲኖር ነው ቅንነት የጎደለበት ሴራና ሸፍጥ የሞላበት አመራር ማለት። በአንድ የሚውሉ መሪዎች በጥርጥርና በጠላትነት እንዲተያዩ የሚያደርግ የአመራር ባህል ሲኖር ነው ቅንነት የሌለበት አመራር ማለት። እንዲህ ባለ ሁኔታ መተማመን የለም፤ የሚያምንም የለም፤ የሚታመንም የለም። የልብ ወዳጅ ሊሆን የሚችል ፈልጎ ማግኘት ከባድ ይሆናል። አንዱ ሌላውን ይጠረጥራል፣ አንዱ ሌላውን ጠልፎ ለመጣል ያደባል።

በየዘመኑ በቅንነት የኖሩ ቅንነትን የዘሩ ብዙ የሃይማኖት መሪዎች የመኖራቸውን ያህል በሃይማኖት ተቋማት እንኳ ቅን መሪዎችን ማግኘት ጭንቅ እየሆነ ነው። በአንዳንዶቹ ዘንድ የሚሰማውን ጉድ ለተከታተለ ያለው ክፋትና መጠላለፍ ከእምነት ሰዎች የማይጠበቅ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ፈሪሃ እግዚአብሔር የላቸውም ከሚባሉት እንኳ የሚብስ ይመስላል። በቅንነት የሚያገለግሉት እያነሱ በብላጣብልጥነት ከሃይማኖቱ ዐላማ ይልቅ ለጊዜያዊ ጥቅም የሚሯሯጡት እየበረከቱ ሲሄዱ ማየት ከተጀመረ ዓመታት ተቆጠሩ። ቅንነት ከሃይማኖት መሪዎች ሲጠፋ ግን ችግሩ የከፋ ነው። ለሌሎች መሪዎችና ለሕዝቡ ሁሉ አርአያ እንዲሆኑ የሚጠበቁ መሪዎች በተግባር ሌላ ሆነው ከተገኙ ችግሩ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ" እንደሚባለው ነው የሚሆነው። እንደ ጻፎችና ፈሪሳውያን ግብዝነት ልማድ በሚሆንበት ጊዜ ቅንነት ሞኝነት ሆኖ እስከመቆጠር ይደርሳል።

ቅንነት የጎደላቸው መሪዎች እንደ ጻፎችና ፈሪሳውያን የሚስብኩትን ሕይወት አይኖሩበትም። ጻፎችና ፈሪሳውያን ጻድቃን ሳይሆኑ ጻድቅ መስለው የሚታዩ፣ ለሰውም እንዲታዩ ሥራቸውን ሁሉ የሚያደርጉ፣ ማዕረግና ክበሬታን የሚወዱ፣ ሳያውቁ እናውቃለን የሚሉ፣ ትችት የሚያበዙ፣ ያለፈውን የሚወቅሱ ግን የሚወቀሱበትን ሥራ አብልጠው

የሚሠሩ፣ ትንንሽ ስሕተቶችን የሚያነሉ በተግባር ግን የበለጠውን ኃጢአት የሚፈጽሙ እንደነበሩ ተጽፏል:: (ማቴ. 23) ይህ ሁሉ የቅንነት መጥፋት ነው:: እንዲህ ዐይነቱ የጻፎችና ፈሪሳውያን ቅንነት የጎደለው አኗኗር በአንድም በሌላም በመሪዎች ላይ ሲገለጽ ማየት የተለመደበት ዓለም ነው:: እንዲህ ያለው የአስመሳይነት፣ የተችነት፣ የወቃሽነት፣ የአደርባይነት፣ ከምንም በላይ ደግሞ የግብዝነት በሽታ ያልነበኘው ስንት መሪ ማግኘት ይቻል ይሆን? የሚለው ሊጠየቅ ነው የችግሩን ስፋትና ጥልቀት መረዳት የሚቻለው::

1.2 መሪ እንዴት ቅን ሊሆን ይቻለዋል?

ስለ ቅን መሪ ሲነሣ እንዴት በቅንነት መምራት ይቻላል? መሪ እንዴት ቅን ሊሆን ይችላል? የሚል ጥያቄ መጠየቁ የሚጠበቅ ነው:: የመጀመሪያው ነጥብ መሪነት አስቸጋሪ ነው፤ መሪ ብዙ ፈታኝ ውሳኔዎችን መወሰን አለበት፤ የውሳኔ ምርጫዎች ከባድና ውስብስብ የሚሆኑበት ጊዜም ብዙ ነውና መሪ ቅን መሆን አይቻለውም የሚል ነው:: በተለይ የመሪነት ቦታው ከፍ ባለ ቁጥር ችግሩ የሚጨምር ነውና ቅንነትን መተግበር ከባድ ነው የሚል ነገርም መነሳቱ አይቀርም:: ተንኮልና ብልጣብልጥነት በበዛበት ዓለም ቅንነት አያስኖርም፤ ቅንነትን በተግባር መኖር ቀላል አይደለም፤ የምንኖርበት ዓለም ከቅንነት ይልቅ በአቋራጭ ሥልጣን መያዝን፣ በብልጠት በሴራና በተንኮል መግዛትን ባህል ያደረገ ነውና ቅንነት ለመሪ አይስማማም የሚል አመለካከትም በዝቶ ይሰማል:: እንዲያውም "ፖለቲከኛ ቅን መሆን አይችልም" የሚባል ነገርም አለ:: "አንተ ፖለቲከኛ አትመስልም ውሸቱን፣ ማስመሰሉንና ተንኮሉን፣ ምናምኑን አትችልበትም" የሚባል አገላለጽም ፖለቲከኛነት ያለመሠሪነትና ብልጣብልጥነት የሚቻል አይሆንም የሚለውን አሳብ የሚያንጸባርቅ ይመስላል::

በእርግጥ የቅንነት ባህል ብዙም ባልተለመደበት ሁኔታ ስለ ቅንነት መናገር የዋህነት ነው ሊያስብል ይችላል:: የሴራና የተንኮል፣ የመጠላለፍና ጥሎ የማለፍ፣ የመሠሪነትና ማስመሰል፣ የቂምና የቁርሾ ባህል በነገሠበት

ሁኔታ እጅ ለእጅ ተያይዞና ተደጋግፎ የሚሠራ አመራርን ማግኘትም ይከብዳል:: ያሳለፍነው ታሪክ ሴራ የሚበዛበት፣ ለአንድ ዐላማ የተማማሉ ሰዎች የሚካካዱበት፣ በአሳብ ስለተለያዩ ብቻ የሚጠፋፉበት፣ አንዱ ሌላውን መወጣጫ መጠቀሚያ የሚያደርግበት ባህል ይታይበት ስለነበር ስለ ቅን መሪዎች ማሰብ ባዶ ተስፋ ቢመስል የሚገርም አይሆንም:: የተለመደው ብልጣብልጥነት ከሆነ፣ የተለመደው ጥሎ ማለፍ ከሆነ፣ የተለመደው ማታለል ከሆነ ቅንነትን ማሰብ ቂልነት ሆኖ ቢቆጠር የሚደንቅ አይሆንም:: ቅንነት ባልተለመደበት ሁኔታ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሙግቶች ሁሉ እውነትነት አላቸው::

ቅን መሪ ቢገኝም ተንኮለኞችና ጠማማ መሪዎች ስለሚቀናቀኑት ሳይወድ በግድ ተንኮልን ይማራል የሚል መከራከሪያም አለ:: "ቅን አይበረክትም" የሚለው ብሂልም ያለ ምክንያት አልተነገረም:: ክፉዎች በበዙበት ቅኖች ቦታ እንደማይኖራቸው የሚያመላክት ነው:: ተንኮልና ብልጣብልጥነት በበዛበት ዓለም በቅንነት መምራት በእርግጥም ቀላል አይሆንም:: ቅን መሪ ሊበረክት የሚችለው ቅን ሰዎች በዙሪያው ሲኖሩ ነው:: ተንኮሎኞች ከፍ ከፍ ባሉበት ቅንነትን እንደ ሞኝነት፣ የዋህነትን እንደ ደካምነት የሚረዱ ሰዎች በሚበዙበት፣ ሁሉንም ነገር በጥርጣሬ የሚያዩ ተሰሚነት በሚያገኙበት፣ የሴራ ወሬ በሚያይልበት ሁኔታ ቅኖች መሪዎች ቢገኙ እንኳ ዕድሜ አይኖራቸውም የሚለው አሳብ ውድቅ ሊሆን አይችልም::

በሌላ በኩል ተንኮል በበዛበት የፖለቲካ ባህል መሪ ተቀናቃኞቹን ለመምታትና ሥልጣኑን ለማጽናትም ይሁን የሥልጣን ዘመኑን ለማዝለግ የሚጠቅመው ቅንነትን ሳይሆን መሠሪነት ነው የሚለውም እውነትነት ይኖረዋል:: ቁምነገሩ ግን ክፉ መሪ በተንኮል የሥልጣን ዕድሜውን ማራዘሙ የሚጠቅመው ለራሱ ብቻ መሆኑ ነው:: በሚመራቸው ሰዎች ላይ የሚጨምረው ቢኖር በደል ብቻ ነው የሚሆነው:: ምክንያቱም ከክፉ መሪ መልካም ነገር በዘላቂነት ማግኘት አይቻልምና::

ይህ ሁሉ ሙግት ግን መሪ ቅን መሆን አይችልም ለሚለው ማረጋጋጫ ሊሆን አይችልም:: ፈተናው እነዚህን ተግዳሮቶች አልፎ፣ ችግሮችን

አቻችሎ በቅንነት መምራት እንዴት ይቻላል? የሚለውን መመለስ መቻል ነው:: እንዲህ ተግዳሮት የበዛበት መሆኑ ነው ቅንነትን በተግባር ከባድ የሚያደርገውም:: መሪነት ማለት ለሚያምኑበት በጎ ዐላማ ተከታይን ማፍራትና ተከታይን ማሰለፍ ማለት ነው:: መሪነት ማለት ለአንድ ተልዕኮ የተለያዩ አካላትን ማስተባበርና ራእይን ማስፈጸም ማለት ነው:: ይህ ሁሉ የሚቻለው በሸፍጥ በሴራ ሳይሆን በቅንነት ነው፤ በማታለል ሳይሆን በታማኝነት ነው:: እርስ በርስ ከመጠራጠር በመተማመን፣ በተንኮል ሳይሆን በየዋህነት፣ በአድሎዊነት ሳይሆን በፍትሐዊነት፣ በሽኩቻ ሳይሆን በመደጋገፍ ተከታይን ማስተባበር፣ የተከታይን አመኔታ ማግኘትና ብዙዎቹን በሚያምኑበት ዐላማ ማሰለፍና ዘላቂ ለውጥ ማምጣት ይቻላልና:: ይህ ሁሉ ግን ያለ ቅንነት ሊሆን የሚችል አይደለም::

በተለይ መሪዎች ዐላማቸው አገልጋይነት ከሆነ በቅንነት ከመምራት ሌላ አማራጭ ሊኖራቸው አይችልም የሚለው ሚዛን ሊደፋ የሚገባው ነው:: ፖለቲከኛ መሆንም ዐላማው ሕዝብን እና አገርን ለማገልገል ከሆነም ያለ ቅንነት ሕዝብን እና አገርን ማገልገል እንዴት ይቻላል? የሚለው ነው ትልቁ ጥያቄ:: ያለ ቅንነት በጉልበት መግዛት ይቻል ይሆናል እንጂ መምራት አይቻልም የሚለው ነው ዋናው ቁምነገር:: በተንኮልና በማጭበርበር ጊዜያዊ ስኬት ይገኝ እንደሆነ እንጂ ዘላቂና ዘመን ተሻጋሪ ሥራን ሠርቶ ማለፍም አይቻልም:: ይህም በኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ታሪክ በተግባር የታየ እውነት ነው ለማለት ይችላል:: ዘላቂ ስኬት የሚገኘው ከቅንነት ነው:: የተንኮል መጨረሻውም አያምርም:: ጥፋቱ ግን ለመሪው ብቻ ሳይሆን ለሚመራው ሕዝብ ጭምር የሚተርፍ መሆኑ ነው አስከፊነቱ::

ያለ ቅንነት ተግባብቶ እና ተማምኖ በአንድ የሚሠራ ጠንካራ አመራር መፍጠር እንደማይቻል በተግባር ተደጋግሞ የታየ ነው:: ለዘመናት እያስቸገረ ያለውም ካለመተማመን የተነሣ መሪዎች አብሮ መሥራት አለመቻላቸው መሆኑም ውጤቱ ይመስከራል:: መሪዎች እርስ በርስ በሚያደርጉት ሽኩቻ በየዘመኑ ብዙ ደም ይፈሳል፤ ብዙ ሀብትም ይወድማል:: እርስ በርስ ልብ ለልብ ተግባብተው በአንድነት መሥራት

ባለመቻላቸው አንድ እርምጃ ወደፊት አንድ እርምጃ ወደኋላ እየሆነ ሁሌም ከአዙሪት መውጣትም አሰቸጋሪ ነው የሚሆነው:: ያለ ቅንነት ከስም ባለፈ አገልጋይነትን እንዴት መተግበርስ ይቻላል?

በእርግጥም ለአንድ መሪ ቅንነት ትልቅ ሀብት ነው:: መሪ ምንም ያህል ችሎታና ዓቅም ቢኖረው አካሄዱ ሁሉ ጠማማ ከሆነ፣ የሚዋሸና የሚያታልል ከሆነ፣ የሚያምነውና ሕልሙን የሚጋራው፣ የሚከተለው ሰው ማግኘት እንዴት ይቻለዋል? መሪ ምንም ያህል ችሎታና ዓቅም ቢኖረው ልቡ ቆሻሻ ከሆነ፣ አካሄዱ ሁሉ መሠሪነትና ክፋት የሞለበት ከሆነ ዘላቂነት ያለውና ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ መሥራትስ እንዴት ይቻለዋል? እንዲያውም ከችሎታ ይልቅ ለመሪ ትልቁ ገንዘብ መልካም ሰብእና፣ በጎ አስተሳሰብና ቀና ልቦና ነው ማለት ይቻላል:: በምን ሥራህ፣ በየትኛው ማንነት መታወስ ትሻለህ? ተብሎ የሚጠየቅ መሪ በተግባር ግብሩ ሌላ ቢሆንም መቼም በቅንነት፣ በታማኝነት፣ በሐቀኛነት የሚል መልስ መስጠቱ አይቀርም:: አጭበርባሪ፣ አታላይ፣ ጠማማ ተብሎ መታወስ የሚፈልግ መሪ ይኖራል ብሎ ማሰብም አይቻልምና:: ጥሎበት ካልሆነም ከመሠሪ፣ ጠማማና አስመሳይ አለቃ ጋር መሥራት የሚፈልግም አይገኝም:: ካለም ቢጤውን ፍለጋ ነው የሚሆነው::

ቅዱስ መጽሐፍ የሚያስተምረንም በየዋህነትና በቅንነት መምራት እንደሚቻል ብቻም ሳይሆን እንደሚገባም ነው:: ለዚህም ሰሎሞን በነገሠ ጊዜ "ዳዊትም አባትህ በየዋህ ልብና በቅንነት እንደ ሄደ አንተ ደግሞ በፊቴ ብትሄድ..." ሲል እግዚአብሔር ሰሎሞንን መናገሩ ቅንነት ከመሪ የሚጠበቅ ሥነ ምግባር መሆኑን ያረጋግጥልናል:: (1ነገ. 9፥4) "በቅንነት የሚሄድ ይድናል፣ በጠማምነት የሚሄድ ግን ወዲያው ይወድቃል::" ተብሎ እንደተጻፈም በብልጠት፣ በሴራ፣ በማታለል ለጊዜው መግዛት ቢቻል እንጂ በዘላቂነት መምራት አይቻልም:: (ምሳሌ 28፥18) በጽድቅ የሚሄድ፣ ቅን ነገርንም የሚናገር፣ በሽንገላ የሚገኝ ትርፍን የሚንቅ፣ መማለጃን ከመጨበጥ እጁን የሚያራግፍ፣ ደም ማፍሰስን ከመስማት ጆሮቹን የሚያደነቍር፣ ክፋትንም ከማየት ዓይኖቹን የሚጨፍን ሰው

በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ እንደሆነም በመጽሐፍ ተጽፏል:: (ኢሳ. 33፥15)

1.3 የዋህነት እና ቅንነት

“እንዲያው እኮ የዋህ ነው፥ ሕዝቡ አልገባውም መሰለኝ” የሚባል አነጋገር አለ:: “ቅንነት መቼ ያዋጣና መጨከን ነው የሚያዋጣው” የሚል ነገርም የተለመደ ነው:: እንዲህ አይነቱ አስተሳሰብ የዋህነትን እንደ ደካምነት ከማዬት የሚመጣ ሊሆን ይችላል::

የአማርኛ መዝገበ ቃላት የዋህ ለሚለው ቃል “ገር፣ ቅን፣ መሠሪነት የክፋት ብልጠት የሌለው” በሚል የሚተረጉመው ሲሆን በዚሁ መዝገበ ቃላት የእንግሊዘኛ ትርጉሙን naïve, straightforward, bland, candid, dovelike, meek, silly, unsuspecting በሚል ያስቀምጠዋል:: በዚህ ትርጉም መሠረት ቅንነትና የዋህነት የሚያያዙ ነገሮች ናቸው::

“የዋሆች ብፁዓን ናቸው” ተብሎ እንደተጻፈ የዋህነት ትልቅ ሀብት ነው:: (ማቴ 5፥5) የዋህነት ቅንነት ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ ነው:: “በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም፣ እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ” እንዲል በቅዱስ መጽሐፍ የዋህነት ከቅንነት፣ ከትዕግሥት፣ ከትሕትና ጋር በጣምራ የሚገለጽ ነው:: (ኤፌ 4፥2)

የዋህነት ደግነትን፣ ርኅራኄ፣ ራስን መሆንን፣ ሰውን ማመንን፣ ራስን አለመኮፈስን የሚያሳይ ነው:: ነገሮችን በየዋህነት ማየት ማለት ግራና ቀኝ አለማየት፣ ሁሉንም ነገር ጥቁር እና ነጭ እንደሆነ ሁሉ በሞኝነት መቀበል ወይም በቀላሉ መታለል ማለት ግን አይደለም:: ቅንነትን የዋህነትን ከደካምነት ጋር የሚያይዙት አሉና:: እንዲያውም የዋህነት ከዚህ በተቃራኒው ነው:: የዋህነት ቸኩሎ አይፈርጅምና ነገርን ከሥሩ፣ ምክንያቶችን ከየአቅጣጫው አበጥሮና ተንትኖ ለማየት እድል የሚሰጥ ነው:: ቀና አመለካከት ሲኖር አንዱን ጠላት ሌላውን ወዳጅ ፤ አንዱን አዋቂ ሌላውን መሃይም በሚል ስለማይከፋፍልም ሁሉንም በማቅረብ አንድን ጉዳይ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር ለማየትም ያስችላል::

በተመሳሳይ የዋህ ሰው ስንል አዛኝነትን፣ ይቅር ባይነትን የሚያመለክት ነው:: ርኅራኄ (compassion) በመንፈሳዊው ዓለም ብቻም ሳይሆን በሥራ አመራር ሳይንስ መሪዎች ሊኖራቸው ከሚገቡ ስብዕናዎች መካከል በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው[4]::

መሪ መሆን ኮስታራነትን እንደሚፈልግ የማሰብ ነገር ይታያል:: ትንሽም ስልጣን ሲያገዝ መኮፈስና አንዳንዴም ጨካኝ መሆን በመሪዎች የሚታይ ክስተት ነው:: አንዱ ዘመን ከሌላው ይሻል ይሆናል እንጂ የጭካኔ ባህል ማሳያ የሚሆኑ ብዙ ክሥተቶችም በየዘመኑ ነበሩ:: ጭካኔ ያቆመበት ጊዜም አልታየም:: በየዘመኑ በሚመሩት ሕዝብ ላይ ምነው እንደዚህ ጨካኝ ሆኑበት የተባሉ መሪዎችም አንድ ሁለት ብቻ አይደሉም:: ከብልሀት ይልቅ በጉልበትና ጭካኔ በተሞላበት የአመራር ዘይቤ በየዘመኑ ለገዥዎች አልተመቹም የተባሉ፣ ለሥልጣን አስገተዋል ወይም ዙፋን ለመንጠቅ ሞክረዋል የተባሉ መሪዎች በአመዛኙ በጭካኔ የተቀጡበት ታሪክ የሩቅ ብቻ ሳይሆን የቅርብም ትዝታ ነው:: ጭካኔ የተሞላበት የአመራር ዘይቤ አንዳንድ መሪዎች በአመዛኙ የሚታወቁበት ነው ማለት ይቻላል:: ይህ የጭካኔ ባህል በመሪዎች ዘንድ ቀድሞውንም ሥር የሰደደ በሽታ ቢሆንም ባለፉት ዘመናት ብሶበታል የሚያሰኙ ብዙ ክሥተቶች ማለፈቸውም የአደባባይ ምስጢር ነው::

ከ 1953 ዓ.ም. መንፈንቅለ መንግሥት መክሸፉ ጀምሮ ቢቆጠር እንኳ ስንት ምሁራን እና ጄነራሎች ናቸው በሞት የተቀጡት? በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ በአሰቃቂ እስር የተሰቃዩት? እንዳይመለሱ ሆነው ከአገር የተሰደዱት? በትዕግሥት አልባ ውሳኔ ሁሉንም ነገር በግልፈተኛነትና በጉልበት ለመቆጣጠር በሚደረግ መከራ ብዙ ደም ፈሷል::

[4] Compassion reduces fear, reflecting as it does a concern for others' well-being. This, not money and power, is what really attracts friends. When the mind is compassionate, it is calm and we're able to use our sense of reason practically, realistically, and with determination.https://hbr.org/2019/02/the-dalai-lama-on-why-leaders-should-be-mindful-selfless-and-compassionate

በተለያየ ጊዜ በጭካኔ የተገደሉና ከአገር እንዲሰደዱ የተደርጉ የአገራቱ ብርቅዬ ልጆች፤ ምነው እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ የተደከመባቸው ለአገር ውለታ የዋሉ፣ ለወደፊትም የአገር ተስፋ የሚሆኑ መሪዎችን ከመግደል ወይም ከሀገር ከማሰደድ ይልቅ ቀለል ባለ ቅጣት ማስተማርና ተመልሰው ለአገር አገልግሎት እንዲያበረክቱ ማድረግ አይቻልም ወይ? የሚለው ጥያቄ ዛሬም ድረስ በቁጭት የሚነሣ ነው:: እውነት ነው በጨካኝ መሪዎች አገር ስንት ጄነራሎችን፣ ስንት ምሁራንን፣ ስንት ጀግኖችን፣ ስንት የሃይማኖት መሪዎችን አጥታለች? አገር እነዚያን የመሳሰሉ መሪዎች በዚያ ሁኔታ ባታጣቸው ኖሮ ምን ያህል ወደፊት ባራመዱን ነበር ብሎ ማሰብ ሲቻል ነው ነገሩ የባሰ የሚያስቆጨው:: ይህ ሁሉ የሆነው ግን በመሪዎች ዘንድ የታጋሽነት፣ የርኅራኄ፣ የመሐሪነት፣ የይቅር ባይነት፣ የየዋህነት እሴት አናሳ በመሆኑ ሊሆን ይችላል:: የሥራ አመራር ከድጡ ወደማጡ የሚሸጋገረውም እንዲህ ባለው ባህል ምክንያት ነው:: ኮሽ ባለ ቁጥር ማሰር፣ በጭካኔ መቅጣት ብዙ ጊዜ ተሞክሮ የከሸፈ የሥራ አመራር ዘይቤ ነውና::

1.3.1 የዋህነትን እንደ ደካምነት

የመሪዎችን የዋህነት እንደ ደካምነት የሚቆጠርበት ጊዜም ቀላል የሚባል አይደለም:: ሰውን በግፍ የጨረሱ መሪዎች እስካሁን ድረስ እንደ ቆራጥ፣ እንደ ጀግና የሚወደሱበት ባህል አለ:: አንዳንዶችም “ይህ ሕዝብ እንዲህ ፍቅር፣ ክብር አይገባውም፤ መሪው ጨካኝ መሆን አለበት፤ ሕዝቡን የሚገዛው ጉልበት ነው” ሲሉ ይሰማሉ::

ይህ የሚሆነው ግን የዋህነት እንደተባለው ሞኝነት ወይም ደካምነት ስለሆነ ሳይሆን ከየዋህነት ይልቅ መሠሪነት በዝቶ በመገኘቱ ሊሆን ይችላል:: መተማመን በጠፋበት፣ መካካድ በሚበዛበት፣ ጭካኔ በሚያይልበት ሁኔታ የዋህነት ሞኝነት ሆኖ መቆጠሩ ግን እውነትነት ይኖረዋል:: በየዘመኑ በየዋህነት ወዳጅ ባሏቸው ሰዎች የተከዱ፣ እንኳን ለሞት ለከረረ ንግግር የሚያበቃ ምክንያት አለ ብለው ባላሰቡበት እንደ ጭቃ እሾህ ድብቅ በሆኑ ወዳጅ መሳይ ሰዎች ተገፍተው ግፍና ስቃይ

ያዩ መሪዎችን ስናስብ መሪ ደግ እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚለው ጥያቄ ቢነሣ ተገቢ ነው:: የዋህነት እንደ ሞኝነት ወይም እንደ ደካምነት የሚቆጠረው ክፋት በሚበዛበትና ክፋት እንደ በጎ በሚታይበት ሁኔታ ነው:: የዋህ መሪ እንደ ደካማ፣ ክፉ መሪን እንደ ጀግና የሚታይ ከሆነ በቅንነት መምራት ተረት ሆኖ ይቀራልም:: በጮሌነት የሚገኝ ጊዜያዊ ድል እንደ ጀግንነት በሚቆጠርበት ባህል በእርግጥም የሚያስከብረው የዋህነት ሳይሆን መሠሪነት ቢሆን የሚያስደንቅ አይሆንም:: በየዋህነትና በደካምነት መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት የሚችል ሰው ቁጥሩ አናሳ በሆነ ጊዜም ቅን መሪ ሳይሆን ጨካኝ መሪ የበለጠ ሊከበር ይችላል፡፡

የዋህ መሪ ማለት ግን ልፍስፍስ መሪ ማለት አይደለም:: የዋህ መሪ የዋህነቱ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው መሆኑ ነው:: የዋህ መሪ የዋህነቱ እውነትን መውደዱ ነው:: የዋህ መሪ የዋህነቱ የሚመራውን ሕዝብ መውደዱ ነው::

የዋህነት እንደ ደካምነት በሚቆጠርበት ሁኔታ በየዋህነት በታማኝነትና በትሕትና አገራቸውን ለማገልገል ደፋ ቀና ከሚሉት ይልቅ በተንኮልና በብልጣብልጥነት የሥልጣን ጥማታቸውን ለማርካት ላይ ታች የሚሉ መሪዎች ተከታያቸው ሊበዛም ይችላል:: በሰዎች ዘንድ የዋህ መሪን ሳይሆን ጨካኝ መሪን፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለውን ቅን መሪን ሳይሆን ተንኮለኛ መሪን የመምረጥ ዝንባሌ እንዳለ በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ታሪክ ይመሰክራል:: ሳሙኤል ከእግዚአብሔር እንደታዘዘው በሳኦል ፈንታ ከእሴይ ልጆች መካከል ቀብቶ ሊያነግሥ ወደ ቤተ ልሔም ሔደ፡፡ እሴይንም ልጆችህን አቅርብልኝ፣ ከመካከላቸው አንዱን ለንግሥና እቀባዋለሁ አለው:: እሴም ከታላቁና ከመልከ መልካሙ ከኤልያብ ጀምሮ ሰባት ልጆቹን ተራ በተራ ለሳሙኤል ቢያቀርብለትም እግዚአብሔር ሊቀበለው አልቻለም:: ያን ጊዜ እሴይ ተስፋ ቆረጠ:: እረኛው ዳዊት በእሴይ ዐይን ለንግሥና ይመጥናል ተብሎ አልታሰበምና ታናሹን ልጁን ዳዊትን ግን ዘነጋው:: ያን ጊዜ ነበር እግዚአብሔር ሳሙኤልን “ፊቱን የቁመቱንም ዘለግታ አትይ፤ ሰው እንዲያይ እግዚአብሔር አያይምና

ናቅሁት፤ ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል" ሲል የተናገረው:: (1 ሳሙ· 16፥ 1-12)

ሰው ብዙውን ጊዜ በመመሪያ በንግግሩ፣ በግርማ ሞገሱ፣ በተወዳጅነቱና በተከታዮቹ ብዛት ይሳባል:: ዛሬም ቢሆን የሰው ዝንባሌ እንዲሁ ስለሆነ ከቅን መሪ ይልቅ በውጫዊው መስፈርት እየተማረከ ክፉውን መሪ ሊመርጥ ይችላል:: ሰው የሰውን የልብ ክፋት መርምሮ ማወቅ አይቻለውምና ሊሳሳት ይችላልም:: በመናገር ችሎታቸው ሰውን የሚያማልሉ፣ ለወገን ተቆርቋሪ የሚመስሉ፣ ልባቸው ግን ምናልባትም በተንኮል የተሞላና ከራሳቸው ጥቅም ባሻገር ሌላ የረባ ዐላማ የሌላቸው ሰዎችን በስሜት መከተል በሚኖርበት ጊዜ "ፊቱን የቁመቱንም ዘለግታ አትይ፤ ... ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል" በሚለው ኃይለ ቃል ደወልነት መንቃት ስለሚገባ ነው ታሪኩ መመዝገቡ:: ማስተዋል ሲጠፋ ሁሉንም በስሜትና በሥጋዊ ዐይን ብቻ ማየትም ይለመዳል:: ክፉ መሪዎች ሥልጣን የሚቆናጠጡት እንዲህ ባለው አካሔድ ነው:: የዳዊት ምርጫ እንደሚያሳየን ግን ትልቅ ዋጋ ያለው የሰው ሰውኛው መስፈርት ሳይሆን ንጹሕ ልብ ቅን አስተሳሰብ፣ የዋህ ልብ ነው:: ንጹሕ ልብን፣ ቅንነትን፣ የዋህነትን ነው ልብን እና ኩላሊትን የሚመረምር እግዚአብሔርም የሚወደውም:: ሕዝብን ለመምራት የሚጠቅመውም እንዲህ ዐይነቱ ንጹሕ ልብን፣ ቅንነትን፣ የዋህነትን የያዘ መሪ በመሆኑ ነው ዳዊት የመመረጡ ምስጢር::

በእርግጥ መሪ ከየዋህነት ጋር ቆራጥነትና ጀግንነት ከሌለው ልፍስፍስና ደካማ አድርጎ ቢያስቆጥረው የሚጠበቅ ነው:: መሪ ደካማ ሆኖ መምራት የሚሣነው ከሆነ፣ መሪ ጠንካራ ሆኖ የሚመራቸውን በአግባቡ ካልጠበቃቸው፣ ሕልማቸው ላይ ካላደረሳቸው ቅንነቱ ብቻውን ምን ፋይዳ ይኖረዋል? ተብሎ ቢጠየቅ ተገቢ ነው:: ቅን መሪ ርግብ ብቻ አይደለም:; ርግብነቱን ያላግባብ ሊጠቀምበት ለፈለገ ሁሉ እንደ እባብ ልባምም ነው:: የዋህ መሪ በሚያስፈልግበት ጊዜ ደግ ይሆናል፤ በማያስፈልግበት ጊዜ ደግሞ ይጨክናል:: የዋህ መሪ በሚያስፈልግበት ጊዜ ይራራል እንደ አስፈላጊነቱም ይመራል:: ሁሉም ነገር መጠን አለው:: ሁሉም ነገር ልክ

አለው:: ከልኩ ሲያልፍ ውኃም አጥፊ ይሆናል:: መድኃኒትም መጠኑ ሲያልፍ ወደ መርዝነት ይቀየራል:: የሚያምረው ሁለቱም ሲጣመር፣ ሁሉም ነገር ሲመጣጠን ነው:: ትልቁ ቁም ነገር ሁሉንም እንደየሁኔታው ማመጣጠን መቻል ነው:: ሁኔታው በፈቀደ መጠን እንደ እርግብ የዋህ መሆን ቢቻልም እንደ እባብ ልባም መሆንም ሳይዘነጋ ነው:: "እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ" (ማቴ 10፥1) የሚለው መመርያ ያለ ምክንያት አልተነገረም:: በግና ተኩላ በአንድነት በሚኖሩበት ዓለም እንደ ርግብ የዋህነት አስፈላጊ ቢሆንም በጥበብ፣ በጥንቃቄ መሆን እንዳለበት የሚያስገነዝብ ኃይለ ቃል ነው::

"በልቡ ቅንነት ጠበቃቸው፣ በእጁም ብልሃት መራቸው::" (መዝ 78፥72) ተብሎ እንደተጻፈ ከቅንነት ጋር ብልህነት ለአንድ መሪ ወሳኝ ነው:: ቅን መሪ ቅንነትን ከብልህነትና ከአስተዋይነት ጋር አመጣጥኖ የያዘ፣ የሚራራውን ያህል፤ ይቅር የሚለውን ያህል፤ ለሰው የሚያዝነውን ያህል፤ ሓላፊነቱን ለመወጣት በክፉዎች ላይ የሚጨክን ነው:: ቅንነት እንደ ደካምነት የመቁጠር ዝንባሌ ባለበት ሁኔታ ሆደ ሰፊነት እንዳለ ሆኖ የሕግ የበላይነትን ማስከበር፤ የነጻነትና ደኅንነትን ድንበርን ማስመር የመሪ ድርሻ መሆኑም አጠያያቂ አይደለም:: ይህ ሀገርን ለሚመሩ መሪዎች ብቻም አይደለም፤ በሁሉም ዘርፍ በሁሉም እርከን ለሚገኙ መሪዎችም ትርጉም የሚሰጠው እንዲህ ሲሆን ነው:: በየትኛውም የሓላፊነት ወንበር ላለ ሰው ደግነትን ሓላፊነትን ከመወጣት ጋር አመጣጥኖ መያዝ በተግባር ከባድ ቢሆንም ወንበሩ ላይ አለመቀመጥ እንጂ ከተቀመጡ ቆፍጠን ማለት ግድ ነው የሚሆነው::

መሪ ስኬታማ ሊሆን የሚችለው የክፉዎችን ክፋት ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ በብላጣብልጦች የማይበለጥ በአስመሳዮች የማይታለል በሴረኞች ተጠልፎ የማይወድቅ፣ ብልህና አስተዋይ፣ ራሱን እና አካባቢውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሆኖ ሲገኝ ነው:: መሪ የሚመራቸውን ሰዎች የትዕግሥትና ፍርሃት፣ የየዋህነትና የደካምነት ልክ መገንዘብ መቻሉ ነው አካባቢውን መረዳት የቻለ መሪ የሚያሰኘው:: ልኩን የሚያውቅ፣ መብቱን ብቻ ሳይሆን ግዴታውን የሚረዳ ማኅበረሰብ ባለበት የዋህነት ፍሬ ያፈራል::

የስሜት ልህቀት (Emotional Intelligence) በመባል በሚታወቀው ሳይንስ ከአራቱ አስፈላጊ ክህሎቶች አንደኛው አካባቢን መረዳት ነው[5]:: ራስን ማወቅ፥ ራስን መግዛት እና ከሰው ሁሉ ጋር መግባባት አካባቢን ጠንቅቆ ከማወቅ ጋር ሲቀናጅ ለስኬት ይጠቅማል የሚል ነው እሳቤው:: አንድ መሪ የሚመራቸውን ሰዎች ማወቅ መቻሉ፥ ምን እንደሚወዱና ምን እንደሚጠሉ፥ እሴታቸው ምን እንደሚመስል፥ የሚኖራቸውን አመለካከት ለመረዳት መሞክሩ ለመሪው ስኬት ጠቃሚ ነው የሚል ነው ነገሩን በጥልቀት ያጠኑት ባለሙያዎች የሚናገሩት::

1.3.2 የዋህ ሕዝብ

የዋህ መሪ የዋህ ተከታይ ከሌለው ጉዞው እንዴት ሊሰምር ይችላል? የሚለው ጥያቄም ሊታለፍ የሚገባው አይደለም:: እንዲያው ይህን የዋህ ህዝብ ያሳስቱታልና የመሳሰለውን መስማት እንግዳ ነገር አይደለም:: የዋህነት በትክክለኛ ትርጉሙ የደግነት፣ የቀናነት፣ የርኅራኄና የይቅርባይነት ልብን የሚያመለክት ነው:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ደግ ሕዝብ ነው የሚያሰኘው ታሪክ ብዙ ነው:: ደግነት ነው ለዘመናት የተሰበከውም:: በየዘመኑ የተነገረው ይሄው ነው:: እውነት ነው "ይህ ሕዝብ ደግ ሕዝብ ነው" የሚያሰኘው ብዙ ታሪክ አለው:: እንግዳ ተቀባይ ደግ ሕዝብ ነው:: በድለውት መሪዎቹን ይቅር የሚል ደግ ሕዝብ ነው:: ክፉ መሪዎች ሲፈራረቁበት ታግሦ የሚያሳልፍ ደግ ሕዝብ ነው:: ቢርበው ቢጠማው ራቡን ጥሙን ታግሦ ያለችውን ተካፍሎ ችግርን፣ የመከራ ጊዜን የሚያሳልፍ ደግ ሕዝብ ነው:: መሪዎቹ ሲዋሹት፣ ሲያታልሉት፣ በስሙ ሲነግዱበት አውቆ እንዳላወቀ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ ቀን እስኪወጣ የሚያሳልፍ ደግ ሕዝብ ነው:: ክፉ መሪዎች እርስ በርሱ ሊያባሉት፣ አብሮነቱን ሊነጣጥሉት ጃስ ቢሉትም ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ አንድነቱን በፍቅር ያጸና ደግ ሕዝብ ነው:: "የእሥራኤል ልጆች ሆይ፣ እናንተ

[5] "EI," defined as comprising four domains: self-awareness, self-management, social awareness, and relationship management. https://hbr.org/2017/02/emotional-intelligence-has-12-elements-which-do-you-need-to-work-on

ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር።" ተብሎ በነቢዩ እንደተነገረ በእግዚአብሔር የተመሰከረለት ደግ ሕዝብ ነው:: (አሞጽ 9፥7)

የኢትዮጵያን ሕዝብ ደግነት ለማወቅ ሌሎች ሕዝቦች እርስ በርስ በጭካኔ የተጨራረሱበትን ታሪክ ከቅርብም ከሩቁም ማየት በቂ ማስረጃ ሊሆን ይችላል:: ዛሬ እንደሚወራው ሳይሆን በመሪዎች ተንኮልና በመሪዎች አዝማችነት ካልሆነ በቀር ሕዝብ ከሕዝብ ተጣልቶ እንዲህ ዐይነት እልቂት ደረሰ የሚባልበት ታሪክ በዚች አገር ታሪክስ መቼ ተፈጽሞ ያውቅና::

በሌላ በኩል የዋህ ሕዝብ ሁሉንም በደግነት የሚመለከት አስተዋይ ሕዝብ ማለት እንጂ ማንም የሚነዳው ሞኝ ማለት ግን አይደለም:: ክፉ መሪዎችን ከቅን መሪዎች ለይቶ ማወቅ ተስኖት ማንም በፈለገው የጥፋት መንገድ የሚነዳው ከሆነ፣ እንደሚታረድ በግ ወደ መታረጃ ሲወሰድ ዝም ብሎ መነዳት ሲኖር ሞኝነት እንጂ የዋህነት ሊባል አይችልም:: የዋህ ሕዝብ እርስ በርስ የሚተማመን እንጂ እርስ በርሱ የሚጨካከን ማለትም አይደለም:: የዋህነት ችግር የሚሆነው ሰው ከሰው ይልቅ ለማይረባ ጥቅም አብሮ የኖረ ወዳጁን በሚጠፋ ገንዘብ፣ ረብ በሌለው ጥቅም ዘላቂውን ሳይሆን ጊዜያዊውን ትርፍ ሲያሰቀድም ነው:: እንዲህ ባለ ሁኔታ የዋህነት ሊጎዳ ይችላል።

አሁን ያለውን ክፉ ነገር የሚያይ ሁሉ ምነው ያ ሁሉ ደግነት የት ጠፋ? ሲባል ምን ይደረግ ለብዙ ዓመታት ክፉ ዘር ስለተዘራ እኮ ነው የሚል ምላሽ ይሰማል:: እንዴት ሰው የመሆን ትርጉሙ የሚያመዛዝን፣ ትክክሉን ከሐሰቱ ለመለየት የሚያስችል አእምሮ ከፈጣሪ የተሰጠው ማለት አይደለም ወይ? ሮቦት ይመስል ማንም የፈለገውን የሚጭንበት ከሆነ ሰው የመሆን ትርጉሙ ምን ሊሆን ነው? ብሎ መጠየቅ ግን ያስፈልጋል:: ክፉ ነገርን ሲጭኑበት የሚጫን፣ ክፉ ነገርን የሚቀበል፣ ክፉ ነገርን ተቀብሎ የሚያሳድግ ከሆነ የዋህነት እንዴት ሊባል ይችላል? ክፉ ዘር ተዘርቶ ፍሬ ስላፈራ ነው እንዲህ የተቸገርነው ከማለት ይልቅ እንክርዳዱን ከስንዴው መለየት፣ አረሙን መንቀል እንጂ ችግሩን ብቻ

ማውራትስ ምን ይጠቅማል? የሚያስፈልገው እንክርዳዱን ከፍሬው እየለዩ ከክፉ ሀሳብ መራቅ፤ ሲቻል ደግሞ የተሳሳቱ ሰዎችን መክሮ ዘክሮ መመለስ ነው::

ለዘመናት በአብሮነት የኖረውን ጎረቤቱን ክፉ መሪዎች ተነሥተው ሊያለያዩት ሲሞክሩ እንዴት እንዲህ ይደረጋል? ብሎ መጠየቅ ካልተቻለ የዋህነት ጎጂ ነው የሚሆነው:: በሃይማኖት ስም ቤተ ክርስቲያን ወይም መስጊድ አቃጥል ሲባል የሚያቃጥል ሰውስ ምን ሊባል ነው የሚችለው? በስሙ ሊከብሩበት፣ በስሙ ሲነግዱበት ክፉ መሪዎችን ተከትሎ የክፉ አሳብ ማስፈጸሚያ መሆን ደግነት ሳይሆን ሞኝነት ነው:: በሬ ወለደ ሲባል እንዴት ሆኖ? ማለት የማይችል ከሆነ የዋህነት ሳይሆን አላዋቂነት ነው:: ከሀገር መንደርን የሚያስቀድም፣ ከእውነት ለስሜት የሚታዘዝ፣ በነዱት የሚነዳ፣ ከፈጣሪ ይልቅ ለሰው የሚያደላ፣ ለዘመናት የዘለቀውን ወዳጅነት ረስቶ በወዳጁ የሚጨክን፣ ከሰውነት ይልቅ ዘር የሚያስበልጥ ከሆነ ይህ እንዴት የደግነት መገለጫ ሊሆን ይችላልስ?

ዛሬ በሌሎች ላይ የጨከነ ልብ፣ ነገ ወደ እኔ ቢዞርስ ብሎ ማሰብም ያስፈልጋል:: ክፋት መጀመሪያው እንጂ መጨረሻው አይታወቅም ነው የሚባለው:: ወንድምህ ሲታማ ለእኔ ብለህ ስማ ነው ነገሩ:: የክፋት አመጣጡ ሁሌም እንዲሁ ነው:: ዛሬ ተባብሮ ማጥቃት እንዳለ ሁሉ ነገ እርስ በርስ መተላለቅ ሊኖር እንደሚችል ማሰብ ይገባል:: ዛሬ የእኛ ወገን የተባለው ነገ በሌላ መለኪያ የእኛ አይደለም በሚል ሊገለል እንደማይችል ዋስትና መስጠት የሚችል ማነው? የሚያዋጣው የዋህነቱ ነው:: “ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም” እንደተባለ ዘላቂው ፍቅር ብቻ ነውና:: (1ኛቆሮ. 13፥8)

በተመሳሳይ ሁሉንም ነገር በፖለቲካዊ ዐይን ማዬቱም የዋህነት ሊባል አይችልም:; ሁሉም ነገር ለምን ፖለቲካዊ ይሆናል? ሁሉም ነገር ለምን በፖሊተከኞች እጅ ይወሰናል? ብሎ መጠየቅም አስተዋይነት ነው:: ፖለቲከኞች በተቀያየሩ ቁጥር በፈለጉት ልክ የሚሰፉን፣ ሲፈልጉ በብሔረሰብ ሲፈልጉ በመደብ ሲመድቡን፣ አገር ፈርሶ ሲሠራ፣ የሕዝቡ አስተዋጽዖ የሃይማኖት መሪዎች የሀገር ሽማግሌዎች አስተዋጽዖ የት ነው

ያለው? የልሂቃን ድምፅ አይሰማም ወይ? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። ደግ ሕዝብ ሊሆን የሚገባው እንዲህ ነበረ።

በአጠቃላይ የማያመዛዝን፣ በጭፍኑ የሚደግፍ፣ በጭፍኑ የሚቃወም ሳይሆን በምክንያትነት የሚያምን፣ የማይታለል፣ ጠያቂ፣ ዘላቂውን እና የሚጠቅመውን የሚያስቀድም የዋህ ሕዝብን መታደል ትልቅ ጸጋ ነው። የነበረውስ እሴት እንዲህ አልነበረም ወይ? አሁን የት ደረሰ?

1.4 ቅንነት ከመዴት ይገኛል?

ቅኖች መሪዎችን ለማፍራት ሕዝብ ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል። ቅንነት ያለው ማኅበረሰብ ሲገኝ ቅንነትን መማር ይቻላል። ክፉ መሪዎችን የሚያወገዝ፣ ቅን መሪዎችን የሚከተልና የሚያበረታታ ማኅበረሰብ ባለበት ቅን መሪን መውለድ ቀላል ሊሆን ይችላል። መሠሪነትን የሚጠላ፣ ግልጽነትን ሐቀኛነትን ታማኝነትን የሚወድ ሕዝብ ሲገኝ ቅን መሪን ማፍራት ቀላል ይሆናል። ክፋትን የሚጸየፍ፣ በጎነትን የሚወድ ሕዝብ ባለበት ተንኮለኞች ቦታ አይኖራቸውም። ለብላጣብልጦች ቦታ የሚነፍግ፣ የዋህ መሪዎችን የሚደገፍ ማኅበረሰብ ሲገኝም ቅን መሪ ይበረክታል።

ቅንነትን በተግባር የሚያሳዩ መሪዎች በየዘርፉ ከኖሩም ሰው ከሚሰማው ብቻ ሳይሆን ከሚያየውም በጎ ነገር ለመማር የተመቸ እድል ያገኛል። ቅንነትን የሚሰብኩ፣ ቅንነትን የሚያስተምሩ ቅንነትን በሕይወት የሚኖሩ፣ ቅንነትን እንደ እሴት የሚጠብቁና የሚንከባከቡ የሃይማኖት መሪዎች፣ የማኅበረሰብ መሪዎች፣ የፖለቲካ መሪዎች፣ የሚዲያ ሰዎች፣ ልሂቃን በየትውልዱ ሲገኙ ቅንነት ሥር ይሰድዳል። በአጠቃላይ እንደሚባለውም የሰው አመለካከቱ የሚገነባው ከቤተሰብ፥ ከጓደኛ፥ ከትምህርት ቤት፥ ከጎረቤት፥ ከአካባቢ፥ ከማኅበረሰብ፥ ከሃይማኖትና ባህሉ ከሚያዩው ከሚሰማው ከሚማረው ነው። በአመዛኙ የሰው ስብዕናው በለጋነቱ የሚታነጽ ነው ባለሙያዎቹ እንደሚሉት።

በሌላ በኩል ክፉ አሳብ፣ ተንኮልና ጠማማነት፣ መጐምጀት፣ ክፋት፣ ምቀኝነት፣ ትዕቢት ሁሉ ከውስጥ ይወጣልና የቅንነት መጉደል ችግሩ

ወስጣዊ ነው ማለት ይቻላል። በተለይ ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት የሚቻለው ይህንን እውነታ ነው። "ምናምንቱ ሰው የበደለኛም ልጅ በጠማማ አፍ ይሄዳል፤ በዐይኑ ይጠቅሳል፤ በእግሩ ይናገራል፤ በጣቱ ያስተምራል፤ ጠማማነት በልቡ አለ፤ ሁልጊዜም ክፋትን ያስባል፤ ጠብንም ይዘራል።" እንዲል ጠማማነት የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት ውጤት ሊሆን ይችላል። (ምሳ 6፥12-14) በተመሳሳይ "ከልብ ክፉ አሳብ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በውሸት መመስከር፣ ስድብ ይወጣልና።" እንደተባለም ክፋት ከልብ የሚመነጭ ነው። ችግሩ በልብ መመሰሉ ከውስጥ የመነጨ መሆኑን ነው የሚያመለክተው። (ማቴ 15፥19) በመሆኑም ቅንነት ሰውን ያለ ልዩነት መውደድ፣ ይቅርባይነት፣ ታጋሽነት፣ የሌላውን ስሜት መረዳት፣ አዛኝነት ከንጹሕ ልብ ይፈልቃል፤ ከንጹሕ ልብም ይቀዳል።

የክፋት አስተሳሰብስ እንዴት ነው ሊቀዬር የሚችለው? ለሚለው ግን ሰው እንደ እየአመለካከቱና እምነቱ መልሱ ሊለያይ እንደሚችል የሚጠበቅ ነው። በፈጣሪ ለሚያምን ሰውና ለማያምን ሰው የሚኖረው አረዳድ ሊለያይ ቢችልም ክፉ ጠባይ በዕውቀት ወይም በትምህርት ብቻ ሊቀየር የሚችል አይደለም። በፈጣሪ ለሚያምን ሰው እምነቱ ቢለያይም ልብ ሲቀየር ነው ዘላቂና እውነተኛ ጠባይ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው የሚለው ሚዛን ሊደፋ ይችላል። እንደ ቅዱስ ዳዊት "አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ።" ብሎ ንጹሕ ልብ እንዲሰጠው የሚለምን መሪ ሕዝቡን በቅንነት መምራት ይቻለዋል። (መዝ. 50፥10) ንጹሕ ልብ ማለት ቀና አስተሳሰብ፣ ቀና አመለካከት ማለት ነውና። "አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ" ሲል እንደተናገረው ድንጋዩንና ደንዳናውን ልብ የሚቀይር እርሱ ፈጣሪ ብቻ ነውና ንጹሕ ልብ የሚገኘው ከላይ ነው። (ሕዝ 36፥23)

ያም ሆነ ይህ መለወጥ ይቻላል በሚለው ግን ብዙም ልዩነት ላይኖር ይችላል። "ተፈጥሮን ተመክሮ አያድነውም" የሚል ብሂል አለና "ተፈጥሮዬ ነው መቀዬር አልችልም" የሚል ሰው ቢኖር ግን የሚደንቅ አይሆንም።

ለተበደሉት የሚራራ፣ ሁሉንም በእኩልነት የሚወድ፣ በይቅርታ የሚምር ልብ የሚገኘው አሮጌው ልብ ሲታደስ ነው:: እውነት ነው ልብ ሳይታደስ ለውጥ እንዴት ሊኖር ይችላል? ልብ ካልታደሰ ለጊዜው ቅን መስሎ መታየት ቢቻልም ውሎ ሲያደር ወደ ጥንቱና እውነተኛው ማንነት መመለስ አይቀርም:: ልብ ካልታደሰ ክፉው ዓለም ከሚያስበው የተለየ ማሰብስ እንዴት ይቻላል? ዓለም ከሚሠራው ክፉ ተግባር ለመለየትም ቀላል አይሆንም:: ክፉ መሪዎች ባለፉበት ጎዳና የሠሩትን ክፉ ሥራ እና የጥፋት መንገድ መተው የሚቻለው ልብ ሲቀየር ነው የሚለው ተቀባይነት ይኖረዋል:: መጽሐፍ ቅዱስም የልብ እድሳት በማድረግ የአስተሳሰብ ወይም የአመለካከት ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል "በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ" ሲል መምከሩም ይህንን የሚያሳይ ነው:: (ሮሜ. 12፥2)

አዲስ ወይን በአሮጌ አቁማዳ አይቀመጥምና ልብ ሳይቀየር በኃይል የመመካት፣ የጥላቻና የክፋት፣ የጭካኔ፣ የቂመኛነት፣ የበቀል፣ የዘረኝነትና ማን አለብኝነት ስሜት ሳይቀየር ሥልጣን ላይ መውጣት ሲመጣ ያን ጊዜ ሥልጣን የጥፋት መሣሪያ ይሆናል። ምክንያቱም አዲስ የወይን ጠጅ በአሮጌ አቁማዳ ስለሚሆን ነው:: በአሮጌ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ ሲቀመጥ አቁማዳውን እንደሚቀደው ሁሉ፤ በዓለም ታሪክ እንደታዬው ክፉ ሰዎች ሥልጣን ላይ ሲቀመጡ ብዙ ውድመትን የሚያደርስ ጦርነትን እስከማወጅ ይደርሳሉ። አዲስ የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ መቀመጥ ሲገባው በአሮጌው ቢቀመጥ ከወይኑ ብርታት የተነሣ አቁማዳው ይቀደዳል ወይኑም ይፈሳል:: ስለሆነም ወይኑም አቁማዳውም ሁሉቱም ይበላሻሉ። በአሮጌና በክፉ አመለካከት ላይ ሥልጣን ሲጨመርበት "በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ" እንደሚባለው ሊሆን ይችላል::መጽሐፍ የሚያስተምረን፣ በገሀዱ ዓለም ያለው እውነታም ይሄው ነው:: (ማቴ 9፥14-17)

በተመሳሳይ ለሰው ያለው ፍቅር፣ ለእግዚአብሔርና ለሰው ያለው ታማኝነት፣ አገርን እና ሕዝብን የሚረዳበት አስተሳሰብ፣ ያለው አመለካከት ሳይቀየር መሪ በወረቀት ላይ ጥሩ ሕግ ቢጽፍም፣ ፍትሕን፣ ነጻነትን ለማምጣት

ቢምል ቢገዘትም ልቡ እስካልተቀየረ ድረስ እውነተኛ ለውጥ ሊያመጣ እንደማይችልም የዓለም ታሪክ ምስክር ነው:: በቅንነት የሚተረጉመውና የሚፈጽመው ካልተገኘ ጥሩ ሕግ ቢጻፍም ሕጉ የወረቀቱን ዋጋ ያህል እንኳ ሊመዝንም አይችልም::

መለወጥ ምን ያህል ቀላል ነው? የተወሰኑ መሪዎች ከታሪክ የማይማሩት፥ እድሜ ሲያስተምራቸው የማይታዩው ለምንድን ነው? የሚለው ሌላው ለመመለስ ቀላል የማይሆን ጥያቄ ነው:: ይህንን ጉዳይ በቅዱስ መጽሐፍ መነጸርነት ማዬት ግን ይቻላል:: አንደኛው ክፉ መሪ እንደ ፈርዖን እንዲህ በቀላሉ የማይለውጥ መሆኑ ነው:: ሁሉንም ነገር በጉልበት ማድረግ ይቻላል ብሎ ስለሚያምንም ጥፋት ያበዛል፤ አስተሳሰቡ ይጨልማል:: እግዚአብሔርንም አላውቅም እስከማለትም ይደርሳል:: ፈርዖን አንዱ መቅሠፍት ሲመጣ ልቡ ደንገጥ ይላል፤ ሲያልፍ ደግሞ ፈጥኖ ይረሰዋል:: ፈርዖን እጅ የሰጠው ቅጣቱ ቤቱ ሲገባ ነው:: እስከዚያ ድረስ በነበሩት ዘጠኙ ተአምራት ሕመሙ በሌሎች ላይ ስለነበረ ቁስሉ ሊሰማው አልቻለም ነበር:: የራሱን ልጅ ጨምሮ የግብፃውያንን በኵር ሁሉ የሚገድል መልአክ ሞት በተላከ ጊዜ ሕመሙ ያን ጊዜ ተሰማው:: የእግዚአብሔርንም ጽኑ እጅ ምን እንደሚመስል ለማየት ቻለ:: በዚህ ጊዜ ነበር ሕዝቡን የለቀቀው:: የሚገርመው ግን አሁንም ሕዝቡን ከለቀቀ በኋላ እንደገና መልቀቁ ቆጨውና እስከ ቀይ ባሕር ተከተላቸው::

ብዙ ጊዜ እነዚህ መሪዎች ምነው አይቀየሩም? የምንለው የመሪ ልብ ሲደነድን ይህን ያህል ስለሚሆን ሊሆን ይችላል:: “ብዙ ጊዜ ተዘልፎ አንገቱን ያደነደነ ድንገት ይሰበራል፤ ፈውስም የለውም::” እንዲል ጽዋው ሞልቶ ሲፈስ፣ ታግሦ ታግሦ የእግዚአብሔር ወይም የሕዝብ ቁጣ ሲገለጥ ማምለጥ ባይቻልም:: (ምሳ. 29፥1) ከዚህም ሌላ አብሮ አደግ ክፋት ቶሎ አይለቅም እንደተባለ አብሮ ያደገ አስተሳሰብን ወይም አመለካከትን መቀዬር ቀላል አይሆንም::

በእርግጥ ማስተዋል ላለው ጊዜ ትልቁ ትምህርት ቤት ነው:: ዕድሜም ለሰው የተሰጠ ለመማሪያ፣ ከክፉ ሥራ ተጸጽቶ ወደ መልካሙ ጎዳና ለመመለስ ነበር:: እውነታው የሚያሳየው ግን በተቃራኒው ነው:: ክፉ

መሪዎች በሥልጣን ብዙ በቆዩ ጊዜ ከክፋታቸው ተምረው ከመመለስ ይልቅ በክፋታቸው እየባሱ፣ ልባቸው እየደነደነ፣ ክፉውን ሥራ እየለመዱት፣ የባሰ አዲስ ክፋትን እየተማሩ፣ በክፋት እየባሱ ሲሄዱ ነው የሚታዩት:: እንዲያውም በሥልጣን ላይ በከራረሙ ቁጥር እንኳን ከሥልጣን የሚነሡ ሞት እንዳለባቸው የሚረሱት ይመስላል:: የተቋም ስርዓት ባልጎለበተባቸው አገሮች እንዲህ ዐይነት መሪዎች ከሃያ ከሠላሳ ዓመታት ሥልጣን በኋላ በዕድሜ ጃጅተው ተጎትተው እና ተዋርደው ከሥልጣን ሲባረሩ ማየት የትናንት ብቻ ሳይሆን የዛሬም ታሪክ ነው::

ጊዜ ካለፈ ብዙ ጥፋት ከደረሰ በኋላ ልብ መግዛት፣ ማስተዋል፣ ከዕድሜ መማር ይቻል ይሆናል:: ሁሉም የሚያምረው ግን በጊዜው ሲሆን ነው:: የብዙ ሰዎች ቤት ከፈረሰ፣ የብዙ ሰዎች ሕይወት ከጠፋ፣ ብዙ ጉዳት በአገር ላይ ከደረሰ በኋላ መጸጸት ቢኖር የማይጠቅም ጸጸት ነው የሚሆነው:: ብዙ ጥፋት ያደረሱ መሪዎች ሥልጣን ላይ እያሉ ያሻቸውን ማድረግ በሚችሉበት ጊዜ ማስተዋል በመጥፋቱ ብዙ ጥፋት ሲያደርሱ ጥፋት እንደሚሠሩ እንኳ የሚገነዘቡትም አይመስልም:: ራሳቸውን ለማዳመጥ፣ የቀደመ ሥራቸውን ለመመርመር እድል ካገኙ በሠሩት ሥራ ማዘን፣ መጸጸት የሚጀመሩት በችግር መካከል ሲወድቁ ነው:: ብዙ ዓመታትን በእስር ያሳለፉ መሪዎች ከእስር ከወጡ በኋላ ሲጸጸቱ መስማት የተለመደ ቢሆንም ነገሩ ከመሸ ስለሚሆን የእነሱን ቀሪ ዘመን ለማስተካከል ይረዳ እንደሆን እንጂ የፈሰሰውን ውኃ ግን ማፈስ አይቻልም:: ምነው እንዲህ ዐይነቱ ልብ ቀደም ብሎ ተገኝቶ በነበረ ማሰኘቱ ግን የማይቀር ነው::

1.5 ቅንነት እንዴት ይገለጻል?

በአጠቃላይ ቅንነት በየዋህነት፣ በታማኝነት፣ በሐቀኛነት፣ በትሕትና፣ በፍትሐዊነት ይገለጻል:: ቅንነት ባለበት ታማኝነትን ማትረፍ ይቻላል:: ታማኝነት በሐቀኛነት ይገኛል:: ትሕትናን፣ የዋህነትን፣ ሐቀኛነትን፣ ታማኝነትን መያዝ ስኬታማ መሪ ለመሆን፣ እውነተኛ ተከታይን ለማፍራትና ከሰዎች ጋር ተግባብቶ ለመሥራት ቁልፍ ዕሴቶች ናቸውና

ቅንነት ከሰው ጋር ተግባብቶ ለመሥራትም ያስችላል:: ፍትሕንና ለእውነትን ማድላትንም የሚያገናኛቸው ብዙ ነገር አለ:: ለፍትሕ መቆም እውነትን መያዝ፣ ለእውነት ማድላትን ይጠይቃልና:: እውነትን የሚያውቅ ለእውነት የሚያደላና ለእውነት የሚቆም መሪ በቆመለት መርህ ዋጋ ቢያስከፍለውም እንኳ ለመርህ መቆሙ የሚጠበቅ ነው:: አገልጋይነትም የቅንነት ውጤት ነው ማለት ይቻላል:: ከቅንነት ፈሪሃ እግዚአብሔር ይገኛል፤ ፈሪሃ እግዚአብሔርም ቅን ያደርጋል:: እነዚህ እሳቤዎችም የተሳሰሩ ናቸው:: በሚቀጥሉት ምዕራፎች የሚቀርቡትም እነዚህ ጉዳዮች ናቸው::

ምዕራፍ ሁለት

ታማኝነት

2. ታማኝነት ምንድን ነው?

ታማኝነት (Integrity) በሥራ አመራር ብዙ መጽሐፍት የተጻፉለት፥ በሰፊው የሚጠናና በብዙ ተቋማት ክፍል ተበጅቶለት፤ ባለሙያ ተቀጥሮለት፤ በጀት ተመድቦለት የሚሠራ ሥራ መሆኑም የሚታወቅ ነው:: አማዞን ከሰባ ሺህ መጻሕፍት በታማኝነት (Integrity) ዙሪያ እንደተጻፉ ያሳያል:: ሐቀኝነት (honesty) እንዲሁ ብዙ ተብሎለታል፥ ተጽፎለታልም[6]:: አተረጓጎሙና አተገባበሩ ሊለያይ ቢችልም ተቀባይነት ካላቸው ሞራላዊ እሴቶችም ታማኝነት በዋናነት ይገኝበታል::

የአማርኛ መዝገበ ቃላት ታማኝነት የሚለውን ቃል እርግጠኛነት፣ ሐቀኛ መኾን፣ እውነተኛነት በሚል የሚተረጉመው ሲሆን በዚሁ መዝገበ ቃላት የእንግሊዘኛ ትርጉሙን integrity, fidelity, loyalty በሚል ያስቀምጠዋል:: አማርኛው መዝገበ ቃላት ታማኝ የሚለውን ተአማኒ፣ ቅኑዕ ሲለው

[6] https://www.amazon.com/s?k=integrity&crid=248DXWNT82A2O&sprefix=inetegrity%2Caps%2C137&ref=nb_sb_ss_sc_1_10

የእንግሊዘኛ ትርጉሙን ደግሞ trustworthy, upstanding, responsible, faithful, loyal, devoted, reliable, sincere በሚል ያስቀምጠዋል::

ታማኝነት የማይዋሽ፣ የማይሰርቅ፣ የማያታልል፣ ለእውነት የሚቆም እና የመሳሰሉትን የሚመለከት በመሆኑ በጥቅሉ ከበጎ ስብእና (virtues) እንዲሁም ከሥነ ምግባር ጋር የሚያያዝ ነው:: ታማኝነት በቃል ኪዳኑ የሚጸና፣ አደራውን የሚጠብቅ፣ ባስቀመጡት ቦታ የሚገኝ፣ በቃሉ የሚገኝ፣ ቃሉና ተግባሩ የሚስማማ፣ ተስፋ የሚደረግበት የሚሉትን ሐሳቦች ሊያጠቃልልም ይችላል:: ከሀዲ፣ የእናት ጡት ነካሽ፣ ባስቀመጡት የማይገኝ፣ አደራውን የበላ፣ ሲያምኑት የማይታመን የሚሉት አሳቦች የሚያመለክቱት ደግሞ የታማኝነትን ተቃራኒ ነው::

በሥራ አመራር ታማኝነትን በቃልና በኑሮ ምሳሌ የሚሆን፣ የሚናገረውን ሆኖ የሚገኝ፣ የሚያምንበትን በተግባር መኖር የሚችል በሚል ይተረጉሙታል[7]:: ቃልና ተግባሩ የተስማማ፣ በቃሉ የሚገኝ፣ መሆን የሚፈልገውን በኑሮ የሚገልጽ እንጂ በማስመሰልና በማታለል ሁለት ዐይነት ሰብእናን ያልተላበሰ ሰውን የሚገልጽ ነው ታማኝነት:: ሁለተኛው የታማኝነት ትርጉም ሙሉ ሰው መሆን (Integral or wholeness) ማለት ነው:: ሌብነትን እጸየፋለው የሚል መሪ ደጋግሞ የሚዋሽ ከሆነ ታማኝነት አለው ለማለት አያስችልምና::

መሪነት ከምንም በላይ በመተማመን ላይ የተመሠረተ ነው:: ታማኝነት በሌለበት ምን ነገር ማከናወን ይቻላልስ? መሪ ተከታይ ያስፈልገዋል:: ሰዎች ደግሞ አንድን መሪ ለመከተል ሊያምኑት ይገባል:: ተከታይ መሪውን ለመከተል ፈቃደኛ ሳይሆን የመሪውን ራእይ ለመከተል አይፈቅድም:: መሪውን ለመከተል ደግሞ መሪውን በአግባቡ ማወቅ ይፈልጋል:: መሪው ምን አሳብ አለው? ከማለቱ በፊት በአብዛኛው መሪው ማን ነው? ምን

[7] Steven M. R. Covey describes “While integrity means honesty, it’s much more. It’s integratedness. It’s walking your talk. It’s being congruent, inside and out. It’s having the courage to act in accordance with your values and beliefs.” Second, integrity is also described as wholeness::

ዐይነት ሰው ነው? የሚታመን መሪ ነው ወይስ አስመሳይና ጮሌ ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ማሰቀደሙ አይቀርም::

ታማኝነት ለመሪዎች ስኬት ትልቁን ዋጋ የሚይዝም ነው:: ለምሳሌ በሀርቫርድ ቢዝነስ ሪቪው(Harvard Business Review) እንደቀረበው በአሜሪካ አገር በተመረጡ መሪዎች በተደረገ ጥናት መሪዎቹ ለስኬታማነታቸው ከጠቀማቸው ነገር ዋነኛው ምንድን ነው? በሚል ለተካሄደው ጥናት የስኬታማነት መመዘኛ ሆነው የቀረቡ አራት ነጥቦች ነበሩ:: እነሱም 1) ውሳኔ አሰጣጥ (deciding with speed and conviction) 2) ውጤታማነት (Engaging for impact) 3) የለውጥ መሪ (Adapting proactively) 4) ታማኝነት ወይም ቃልና ተግባሩ የተስማማ (delivering reliabliy) ናቸው:: ዘጠና አራት በመቶው (94%) ታማኝነት ወይም ቃል የገባውን የመፈጸም ብቃት መኖር ለመሪዎቹ የስኬት ምንጭ መሆኑም የተደረሰበት ድምዳሜ ነው[8]::

ታማኝነት ለመሪነት ቁልፍ ነው:: አንድ መሪ በጥርጣሬ የሚታይ ከሆነ፣ የሚያስበውና የሚናገረው ለየቅል ተደርጎ ከተወሰደ፣ የሚገባው ቃል ከቃል የማያልፍ በተግባር ጠብ የማይል እንደሆነ ከተቆጠረ፣ በመሪውና በተመሪው መካከል ሊያገናኝ የማይችል ከባድ ገደል አለ ማለት ይቻላል:: መሪ "አይ እርሱ ቃል ይገባል እንጂ ቃሉን አይፈጽምም" ከተባለ ትልቅ ችግር ነው:: "ወሬ ብቻ ነው በተግባር ጠብ የሚል ነገር የለውም" ከተባለ መሪን ሊያስንቀው ይችላል:: ታማኝ መሪ ከቃል ይልቅ ተግባሩ ይቀድማል:: መሪ ብዙ የሚከውን፣ መጥኖ ቃል የሚገባ ሲሆን ታማኝነትን ያተርፋል:: ተከታዮቹም የሚከተሉት ከቃሉ ይልቅ ተግባሩን አይተው ይሆናል::

በኢትዮጵያ ያለው አንዱ መሠረታዊ የአመራር ችግር የታማኝነት እጦት እንደሆነ በተደጋጋሚ ይነሣል:: እርስ በርስ አለመተማመን ብቻ ሳይሆን በመሪና በተመሪ መካከልም ጥርጣሬ የሚነግሥበት ጊዜ ብዙ ነው::

[8] A stunning 94% of the strong CEO candidates we analyzed scored high on consistently following through on their commitments. https://hbr.org/2017/05/what-sets-successful-ceos-apart

በመሪና በተመሪ መካከል መተማመን በሚጠፋበት ጊዜ መጠራጠር፣ ግምት፣ መላምት፣ ሐሜት፣ በሬ ወለደ ወሬ ይበዛል:: " ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው" እንደሚባለው በክፉ ወሬ አገር ይታወካል፤ አገር ይታመሳል::

2.1 መተማመን ሲጎድል

የመሪዎች አንዱ የመታመን መገለጫም መሐላ ለፈጸሙበት፣ ቃል ለገቡት በአደራ የተቀበሉትን ሓላፊነት መወጣት መቻል ነው:: "በቅንነት፣ በታማኝነትና በቁርጠኝነት ለማገልገልና የተጣለብኝን ሓላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ቃል እገባለሁ" የሚለው ቃል ኪዳን ከቃል ባለፈ ለስንቶቹ መሪዎች ትርጉም ይሰጣቸዋል? ለቃል ኪዳኑ የሚታመን ስንት መሪ ማግኘት ይቻል ይሆን? ቃሉን ከመናገር ባለፈ የቃሉን ትርጉም፣ የቃል ኪዳንን ታላቅነት ምን ያህሉ መሪዎች ያስተውሉታልስ? ወይስ ሹመትን በቃል ኪዳን ማጽናት እንዲያው ልማድና ሥርዓት ሆኖ እንጂ ትርጉም አለው ብሎ ከልቡ የሚወስደው መሪ እምብዛም ነው?

በእርግጥም ቃሉን ፈጥኖ እየረሳው እንጂ ቃል ያልገባ ማን አለ፥ ሀሺሙም ቃል ገብቷል፥ ዳኛውም ቃለ መሃላውን ደጋግሞታል፥ ሌላውም በየዘርፉ እንዲሁ:: ቃል መግባቱ ከልብ ከሆነ ቅንነቱ በተግባር የት አለ? ታማኝነቱስ የት ነው ተግባራዊ ሲሆን የሚታዬው? አገልጋይነቱስ እንዴት ነው እየተገለጸ ያለው? በአጠቃላይ ቃል ምን ያህል ዋጋ ይሰጠዋል? በቃሉ የሚታመንስ ስንት ሰው ይገኛል? የሚለው ነው ውይይት የሚሻው ጉዳይ:: ቃል ኪዳን ትልቅ እዳ ነው ለሚያስተውል ሰው:: "የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ" የሚል ብሂል በሰዎች መካከል መተማመን፣ አደራ መጠበቅ፣ ቃል ከገቡ መፈጸም ምን ያህል ጥብቅ መሆኑንም የሚያሳይ ነው::

ቃል የገቡበት ሹመትም (Oath of office) ትልቅ አደራ ነው:: የሕግ የበላይነት በጎለበተባቸው አገሮች የአገር መሪዎች በሥልጣናቸው ባልገዋል ተብሎ ሲታሰብ በሕግ አውጭዎች ተደጋግሞ የሚነገረው "ለሓላፊነት ቃል ኪዳን የገባነው (Oath of Office) ባለሥልጣናት ሥልጣናቸውን ያላግባብ

እንዳይጠቀሙ መከላከልን ይጭመራል እና አስቸጋሪ ቢሆንም ምርመራ ማድረግና መሪዎችን ተጠያቂ እንዲሆኑ ማስቻል ግዴታችን ነው የሚል ነው:: ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ2019 በአሜሪካ ፕሬዚደንቱ ሥልጣናቸውን ያላግባብ ተጠቅመዋል በሚል በሕግ አውጭው የተደረገው ምርመራ ይህንን ያሳያል:: የቃል ኪዳንን ታላቅነት ለሚረዳ እንዲሁ ነው::

ለቃል ኪዳን መታመን ማለት ለተወሰኑ አለቆች መታመን ማለት ብቻም አይደለም:: ቃል ኪዳኑ የተገባው አገርን ለማገልገል መሆኑ ቀርቶ መሪዎችን ለማገልገል እንደሆነ የሚቆጠርበት ጊዜ አለ:: የሀገር ጥቅም አደጋ ላይ እየወደቀ ተባባሪ መሆን ወይም አላዬሁም አልሰማሁም ማለት የሚመጣው እንዲህ ካለው የተሳሳተ አረዳድ ይሆናል:: በእርግጥ ጥቅሜ እስካልተነካ ድረስ አገር ተጎዳ አልተጎዳ እኔ ምን ቸገረኝ የሚሉ ሰዎች በየዘመኑ አይጠፉም:: "የእርሳቸው ቃል ኪዳን አለብኝ፥ ላልከዳቸው ቃሌን ሰጥቻቸዋለሁ" በሚል ሀገርን የሚጎዱ ክስተቶች ስንት ጊዜ ይፈጸማሉ! በተለይ ቡድንተኝነት ስር በሰደደበት ሁኔታ በሀገር ስም፥ በሕዝብ ስም የተቀበሉትን አደራ ይረሳና፥ ታማኝነቱ ለጠባቡ ዐላማ፥ ለጠባቡ ቡድን እየሆነ ጥፋት የሚደርስበት ጊዜ አንድና ሁለት ብቻ አይደለም:: ታሪክን የኋሊት መቃኘት ሲቻል አንዱ የሚያሳዬን እንዲህ አይነቱን ገጠመኝ ነው::

በሌላ በኩል በየዘርፉ ያሉ መሪዎች እርስ በርስ በመተማመን በጋራ መሥራት፣ ለታመኑበት ሓላፊነት ታምነው መገኘት ብቻ ሳይሆን የሚተማመን ማኅበረሰብ መፍጠርም ቀዳሚ ተግባራቸው ሊሆን ይገባል:: መተማመን አገራዊ እሴትነቱ እንዲጎለብት በትጋት መሥራት ከሚመለከታቸው መሪዎች ሁሉ የሚጠበቅ ነው::

የመተማመን እሴታችን ምን ነካው? ብዙዎች የሚጠይቁት ጥያቄ ነው:: እስኪ ዛሬ በየትኛው ዓለም ነው ቅቤ ከሙዝ፣ ሽክላ ከበርበሬ፣ ዱቄት ከጀሶ ወዘተ እየተቀላቀለ የሚሸጥበት አገር? ተከዳን የሚል ለቅሶ የሚሰማው ብዙ ቦታ ነው:: ወደ ውጭ የሚላክ ቡና ተቀሸበ፤ ጊዜው ያለፈበት ምግብ ማሸጊያው ተቀይሮ ተሸጠ፤ ስንዴ ላይ ጠጠር ተቀላቅሎ ከውጭ ገባ፤ ሐኪሞች ገቢ ለማግኘት እያወቁ የማያስፈልግ

ምርመራ አዘዙልን፤ ውኃ በሐሰት ታሽጎ ተሸጠ፤ ቤት እንሠራለን ብለው ገንዘባችንን ዘረፉን፤ ሥራ እንቀጥራልን ብለው አጭበረበሩን ... ምን የማይሠራ ነገር አለ? ያድናል ተብሎ በገንዘብ የተገዛ መድኃኒት ሳይቀር የማዳን ጊዜው አልፎበት ስንት ሰው ታመመ? ስንቱስ ሞተ? በተበላሸ ዘይት፣ በተበላሸ ምግብ፣ ስንት ሰው ታመመ? ስንት ሰው ሞተ? የስንቱስ ቤት ፈረሰ? በአለፉት ዓመታት በአንድ ወይም በሌላ ክህደት ያልደረሰበት ስንት ሰው ይገኝ ይሆንስ? ይህ ሁሉ ሲደማመር ነው እንደ ማኅበረሰብ ወዴት እየሄድን ነው? የሚያሰኘው::

በሚዛን ማጭበርበሩም ብዙዎች የሚያለቅሱበት እንደሆነ ነው የሚነገረው:: ይኸስም ይብዛም ማጭበርበር የሌለበት ንግድ ዛሬ የት ይገኝ ይሆን? ሚዛን የማያጎድል፣ በዋጋ የማያጭበረብር፣ በተመሳሳይ እቃ ሸማቹን የማያታልል ስንት ነጋዴ ማግኘት ይቻል ይሆን? "በፍርድ፣ በመለካትም፣ በመመዘንም፣ በመስፈርም ዓመፃ አታድርጉ፤ የእውነትም ሚዛን፣ የእውነትም መመዘኛ፣ የእውነትም መስፈሪያ፣ ይሁንላችሁ" ተብሎ እንደተጻፈ በሚዛን ማጭበርበር በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው:: (ዘሌ 19፥35-36) በኢትዮጵያዊያን ባሕልም በሚዛን ማጭበርበር በአብዛኛው ነውር የነበረበት ዘመን ሩቅ አልነበረም::

በኢትዮጵያ እንዳሁኑ ሳይሆን ለረጅም ዘመናት ጎልቶ ይታይ የነበረው አንዱ እሴትም መተማመን ነው:: አደራ ከሰማይ ከብዶ ይታይ የነበረበት አገር እንደነበር ነጋሪ አይሻም:: "አደራ ጥብቅ፤ ሰማይ ሩቅ" የሚል ብሂልም ያለ ምክንያት አልተነገረም:: እስከ ቅርብ ድረስ ነጋዴ ሸጠህ ላክልኝ ብሎ ጥሪቱን በንግድ ሥራ በሩቅ ለሚያውቀው ነጋዴ በእምነት ሲያስረክብ ደረሰኝ ወይም መተማመኛ ውል አልነበረም:: መተማመን በመኖሩም አስፈላጊም አልነበረም:: የቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት መስሊም ወዳጆች ቤት በአደራ የሚቀመጥበት ዘመንም ሩቅ አልነበረም::

"ሰርቄ እበላለሁ እንጂ አደራዬንስ አልበላም" የሚል አንድ ታሪክ አለ:: ነገሩ የአደራን ታላቅነት ለማሳየት የተነገረ ነው:: አደራን መብላት ከሌብነት የከፋ ነው የሚል ነው የዚያኑ ጊዜ እምነት:: ትክክል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ክርክር ሌላ ጉዳይ ነው:: አሁን አደራ ምንድን

ነው? ቃል ኪዳን ሲረክስ፣ አደራ ዋጋ ሲያጣ ነው የመተማመን እሴት ተሸረሸረ ሊባል የሚችለው::

አሁን ሊጠየቅ የሚገባው እንዴት መተማመን መገለጫው በነበረ ሕዝብ መተማመን ጠፍቶ ጉድ ሊያሰኝ ቻለ? መተማመን ጠንካራ እሴት በነበረበት አገር ምን ተፈጥሮ ነው እንጀራ ላይ ጀሶ፣ በርበሬ ላይ ሸክላ፣ ቅቤ ላይ ሙዝ፣ ዱቄት ላይ ጀሶ በመጨመር ለማይረባ ጊዜያዊ ትርፍ የሰውን ሕይወትን አደጋ ላይ ለመለጣል የጨከነ ልብ ሊፈጠር የቻለው? ምን ዐይነት ስግብግብነት ቢሰፍን ነው ወንድምና እኅት፣ ልጅና እናት እንዲህ በገንዘብ ምክንያት የሚጨካከኑበት ዘመን ላይ የተደረሰው? ትልቁ ጥያቄ መሆን ያለበት ይሄ ነው:: ነገሩ ሰፊ ጥናትና ምርምር የሚፈልግ ቢሆንም አለመተማመን ከመሪዎች ጋር የሚያያዝ እንደሚሆን ግን መገንዘብ ይቻላል::

የሚታመኑ መሪዎች በሚጠፉበት፣ የጥላቻ ታሪክ እየተነገረ አንዱ ማኅበረሰብ ለሌላው ታሪካዊ ጠላት ለሌላው ስጋት አድርጎ በሚነገርበት የፖለቲካ ባህል፣ የመገናኛ ብዙኃን በሚዋሹበት፣ የአገር ሽማግሌ ወገንተኛ በሚሆንበት፣ የሃይማኖት መሪዎች ከፈጣሪ ይልቅ ለሰው በሚያደሉበት፣ ታላቅን ማክበር እየጠፋ እኛ ብቻ እናውቃለን በሚባልበት ሁኔታ አለመተማመን ቢሰፍን ምን የሚደንቅ ነገር አለው? በሐቅ መኖር እንደ ቂልነት ሲቆጠር፣ "የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ" የሚል ብሂል ነውር መሆኑ ቀርቶ እንደ ጀግንነት ሲነገር፣ ከሰው ልጆች መተማመን ቢጎድል የሚደንቅ ነገር አይሆንም:: በሐሰት ትርክት ቂምና ቁርሾ ሲዘራ፣ እንደ ይሁዳ ወዳጅ ወዳጁን ሲከዳ፣ ወንድም ወንድሙን በገንዘብ ሲሸጥ የሚፈጠረው ማኅበረሰብ እርስ በርሱ የማይተማመን፣ በጥላቻ እና በበቀል ስሜት የሚፈላለግ ሊሆን ይችላል::

ቅዱስ ዳዊት "አቤቱ አድነኝ፣ ደግ ሰው አልቋልና ከሰው ልጆችም መተማመን ጎድሏልና::" እንዳለ የመተማመን መጉደል የደግ ሰው መጥፋት፣ የፈሪሃ እግዚአብሔር መቀጨጭ ውጤት እንደሚሆንም መረዳት አይከብድም:: (መዝ. 11፥1-8) አንዱ የእምነት መገለጫ መተማመን ነው:: ሰው

ሰውን ባያፍር፣ ሰው እግዚአብሔርን ቢፈራ ደንገጥ ማለት ይኖር ነበር:: ሃይማኖተኛ በሆነ ሕዝብ መካከል አመኔታ ከጠፋ፣ መከዳዳት ባህል ከሆነ፣ ሰው በቃሉ ካልተገኘ የሃይማኖት ትርጉም ጥያቄ ውስጥ መግባቱ ግን አይቀርም:: በስም ብቻ እንጂ በተግባር የሃይማኖት ሰዎች አይደሉም ሊያሰኝ ይችላልና:: በእርግጥም "ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን፤ እውነትንም አናደርግም፤" ተብሎ እንደተጻፈ እግዚአብሔርን እናውቃለን እያሉ በጨለማ መመላለስ ሐሰተኛ ያደርጋል:: (1ኛ ዮሐ. 1፥6) የሚወራውን፣ የሚታሰበውን ያህል በዚች አገር ፈሪሃ እግዚአብሔር ቢኖር ኖሮ እንዲህ ጎረቤት ከጎረቤት የሚጨካከንበት ሁኔታ ባልተከሠተ ነበር:: የሚወራውን፣ የሚታሰበውን ያህል ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለበት አገር ቢሆን በቤተ እምነቶች ሳይቀር መካካድ እንዲህ ተስፋፋቶ ባልታየም ነበር:: የሚወራውን፣ የሚታሰበውን ያህል ፈሪሃ እግዚአብሔር ቢኖር ኖሮ በየጊዜው እርስ በርሱ የማይተማመን አመራርን ማፍራት ባልተቻለም ነበር::

መተማመን የአንድ አገር ትልቅ ሀብት ነው:: *መተማመን* ባለበት መግባባት አለ:: *መተማመን* ባለበት መረዳዳት አለ:: *መተማመን* ባለበት መቻቻል አለ:: *መተማመን* ባለበት ፍቅር አለ:: በአንጻሩም *መተማመን* በሌለበት አብሮ መኖር እንዴት ይቻላል? ማኅበራዊ መስተጋብር፣ መገበያየትም አደጋ ይገጥመዋል:: *መተማመን* በሌለበት ሰላምስ እንዴት ሊኖር ይችላል? *መተማመን* ሲጎድል ፍቅር ይቀዘቅዛል፤ ጥላቻ ይጎለብታል:: *መተማመን* ሲጎድል እውነትና ሐሰቱ እየተደበላለቀ ግራ መጋባት ይበዛል:: በአጠቃላይ ማኅበረሰብ በ*መተማመን* ላይ የተመሰረተ ነው:: አብሮ ለመኖርም ትልቁ ቁልፍ ጉዳይ *መተማመን* ነው ማለት ይቻላል::

በአጠቃላይ ያለመተማመን የሰው ሕይወት ምን ትርጉም ይኖረዋል? መተማመን በሌለበት የሰው ልጅ በአንድ ላይ አብሮ እንዴት ሊኖርስ ይቻለዋል? በመተማመን ሊገበያይ ካልቻለ፣ በመተማመን ሊጋባ ካልቻለ፣ በመተማመን ሊታከም ካልቻለ፣ በመተማመን በጎዘንም በደስታም ችግርንም ይሁን ደስታን በጋራ ማሳለፍ ካልቻለ፣ በመተማመን ሰላሙን

በጋራ ማስጠበቅ ካልቻለ ማኅበራዊ መስተጋበር እንዴት ሊቀጥል ይችላል? እርቅ፣ ሽምግልና፣ መደማመጥ፣ መተባበር፣ አብሮ መበልጸግ ይህ ሁሉ ያለመተማመን ከንቱ ድካም ነው የሚሆነው::

በጋራ መበልጸግ ብቻ ሳይሆን በጋራ መኖር የሚቻለውም መተማመን ሲኖር ነው:: ጎረቤት ጎረቤቱን የሚያምን ሲሆን፣ ቤተሰብ ከቤተሰብ ጋር መተማመን ሲኖረው፣ ነጋዴ ከነጋዴ ጋር መተማመን ሲኖረው፣ በመሪዎች መካከል መተማመን ሲኖር፣ ጠንካራ ማኅበረሰብን መፍጠር ይቻላል:: መተማመን ሲጎድል መካሰስ ይበዛል፤ ጥርጣሬ ይበዛል፤ መካካድ ይነግሣል፤ ሴራና መጠፋፋት ባህል ይሆናል::

አንድ አገር በታማኝነት፣ በበጎ ስም ሲጠራ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው የታወቀ ነው:: የሚታመኑ ሰዎች አይደሉም ተብሎ በክፉ መጠራትም ብዙ ነገር ያሳጣል:: "ከመልካም ሽቶ መልካም ስም" እንደሚባለው ታማኝ ሕዝብ አይደሉም የሚል ስም አንዴ ከወጣም የትም አገር ቢሄዱ ያ ስም መከተሉም አይቀርም:: ከኢትዮጵያውያን ጋር ንግድ አትነግዱ ቡና አጉድለው ነው የሚልኩት፤ እምነትን ያጎድላሉ ከተባለ የሚጎዳው አገርን ነው፤ የሚጎዳው ድሀ ገበሬን ጭምር ነው:: ከዚህ አካባቢ ቂቤ አትግዙ፤ ቂቤው ጥሩ ቢሆንም ሰዎቹ የሚታመኑ አይደሉም ከተባለ በማጭበርበር ከሚገኘው ጊዜያዊ ትርፍ ይልቅ የረጅም ጊዜ ኪሳራው እንደሚበልጥ ነጋሪ አያስፈልገውም:: እንዲህ ያለው አካባቢ ለቱሪስት ጉብኝት የሚመች ነበር የአካባቢው ሕዝብ ግን ታማኝ አይደለም፤ ማጭበርበር ይበዛበታል ከተባለም የጎብኚውን ቁጥር ይቀንሰዋል::

2.2 ታማኝነትን የሚያጎድሉ ምክንያቶች

1ኛ. አንደኛው ችግር ጉድለት አለብኝ ከማለት ይልቅ ራስን ነጻ ለማድረግ አሳማኝ የሚባል ምክንያት የማቅረብ ዝንባሌ መኖሩ ነው:: መቼም መዋሸት ጥሩ ተግባር ነው የሚል አይገኝም:: መስረቅም እንዲሁ:: እጁ በአንድ ወይም በሌላ በትንሹም ቢሆን በትልቁ ያልተነካካ፣ እጁ በሙስና ያልቆሸሸ ስንት ሰው ማግኘት ይቻል ይሆን? የሚለው ጥያቄ ሲጠየቅ

ነው ቃልና ተግባር ለየቅል መሆናቸው የሚታወቀው:: ታማኝነትን በሕይወት መኖር መቻል ላይ ነው ቁም ነገሩ:: ታማኝነት ግን በተግባር ቀላል አይደለም:: ችግር አለብኝ፣ ታማኝነት ይጎድለኛል ብሎ ከሚያስበው ይልቅ እኔን የመሰለ ታማኝ ሰው የት ይገኝና የሚለው ልቆ የሚታይበት ጊዜ ይኖራል:: ምንም ማድረግ አልችልም ከመዋሸት ወይም ከመስረቅ በስተቀር ሌላ አማራጭ የለኝም ማለትም እንግዳ ነገር አይደለም:: ምን ችግር አለው እኔ ብቻ አይደለሁም ብዙ ሰው ይዋሻል ብዙ ሰው ይሰርቃል የሚለው አባባልም የተለመደ ሆኗል:: ችግር የሚሆነው ምን አለበት የሚል ምክንያት በማቅረብ ነጻ ለመሆን ሲሞክር ነው::

2ኛ.ሁለተኛው ችግር አተረጓጎሙ ላይ ነው:: ለምሳሌ ፖለቲከኛ ውሸትና ማጭበርበር የተፈቀደለት ይመስል መሪ ሲዋሽ ውሸት ተደርጎ አለመቆጠሩ ነው ችግር የሚሆነው:: ምን ይደረግ የሥራው ጠባይ ነው የሚባልበት ጊዜም ብዙ ነው:: ምን ይደረግ መዋሸት ግድ ነው የሚል ምክንያት ይቀርብለታል:: በቅርብ አንድ ጋዜጠኛ ዶክትሩን "ለምን ፖለቲከኛ አልሆኑም? ስትል ጠየቀቻቸው:: የሰጡት መልስ አጭርና ግልጽ ነበር:: "እንዲህ ባለ አገር እንደ እኔ ቀጥተኛና እውነተኛ ነገር የሚናገር ሰው ፖለቲከኛ መሆን አይችልም" የሚል ነበር ምላሻቸው:: ሙግት የሚፈልገው አሳብ እንዲህ ዐይነቱ ነው:: ፖለቲከኛ እውነትን ከመናገር ቀጥተኛና ግልጽ ሰው ከመሆን የሚያግደው ምክንያት ምን አለ? የሚለው::

አሁን አሁን እንዲያውም ታማኝ መሆን ፈዛዛ ወይም ነገር የማይገባው ኋላ ቀር የሚያሰኝ ሆኗአል:: ምን ይደረግ ሰርቆ ኑሮን ካልደጎሙት ኑሮ ከባድ ነው የሚለውም እንደማጽናኛ የሚቀርብ ምክንያት ነው:: ሌሎቹ በሚሊዮን እየሰረቁ የእኔ ትንሽ ገንዘብ መስረቅ ምን አላት ለማለትም የሚከጅላቸውም አይጠፉም:: አለቃዬ ጉቦ ከተቀበለ እኔ ከሰው መለየት እንዴት እችላለሁ? የሚሉም ቁጥራቸው ቀላል አይሆንም:: አንዳንዱም ሌብነት፣ ጉቦ መቀበል እንደ ቢዝነስ የሚቆጠርበት ጊዜም አለ:: ባለፉት ዓመታት በተለይ በንግድ የተሰማሩ ሰዎች ንግድ ውስጥ ለመቆየት

ጉቦ መስጠት፣ ከሌቦች ጋር መተባበር ካልተቻለ ከንግድ ውጭ መሆን ነው፤ ሌላ አማራጭ አልነበረም የሚባልበት ዘመን እንደነበረ የአደባባይ ምስጢር ነው::

ታማኝነትን በተግባር መኖር ከባድ የሚያደርገውም እንዲህ አይነቱ ፈተና የበዛበት መሆኑ ነው:: ታማኝነት በቃል የሚነገረውን ያህል ቀላል አይሆንም:: መስቀለኛው መንገድ ይበዛበታል:: የሚቻለውን ሁሉ ጥረት ማድረጉ ላይ ነው ቁም ነገሩ:: አሳማኝ ምክንያት ማቅረቡ ነጻ አያደርግምና:: "ከሁሉ በሚያንስ የታመነ በብዙ ደግሞ የታመነ ነው፣ ከሁሉ በሚያንስም የሚያምፅ በብዙ ደግሞ ዓመፀኛ ነው።" በትንሹ አለመታመን በብዙም ላለመታመንም ማረጋጋጫ ነው:: (ሉቃ. 16፥10) በትንሹ ያልታመነ እድል ሲገኝ በትልቁ የባሰ እንደሚሆን የሚጠበቅ ነውና::

3ኛ. ሌላው ተግዳሮት አርአያ የሚሆን መሪ መጥፋቱ ነው:: ሰው ከጆሮው ይልቅ አይኑን የበለጠ ያምናል ይባላል:: የሰውን ፊት አይቶ የማያዳላ ሁሉንም በሕጉና በሥርዓቱ ያለ አድልዎ የሚመራ ከሆነ፣ የሚናገረውን በቃል ብቻ የሚቀር ሳይሆን በሕይወትም የሚኖረው ከሆነ፣ መሪ እምነት ይጣልበታል:: የፖለቲካ መሪዎች እርስ በርስ መግባባት፣ ልዩነታቸውን በንግግር ማቻቻል አቅቷቸው በአደባባይ ሲዘላለፉ፣ አንዱ ሌላውን ሲከስ፣ በጠብ ሲፈላለጉ፣ እርስ በርስ እስከ መገዳደል ሲደርሱ ያያቸው እነዚህ መሪዎች መቶ ሚሊዮን ሕዝብን አስተባብረው፣ አስማምተውና አቀናጅተው ሊመሩን አይችሉም ብሎ ቢጠረጥር ምን ይደንቃል? የሃይማኖት አባቶች እርስ በርሳቸው ተለያይተው አንዱ ሌላውን እያወገዘ ባለበት ሁኔታ ስለ ፍቅር ቢሰብኩ፣ ስለ እርቅ ቢያስተምሩ ሰሚ የት ይገኛል? ከማን ያየነውን ያሰኛልና:: ሚዲያን የሚመሩ ሰዎች አንድ የሚዲያ ተቋምን ተስማምተው መምራት ሳይችሉ አገር በአደባባይ እያያቸው እነዚሁ ሰዎች ስለ አንድነት፣ ስለ አገር መረጋጋት፣ ስለ ሰላምና እርቅ ቢሰብኩ ማን ሊያምን ይችላል? መጀመሪያ እናንተ አንድ ሁኑና ተስማምታችሁ ሥሩ ያሰኛልና:: ከላይ ያለው ሹም እየሰረቀ

የበታቾቹን አትስረቁ ቢል፣ ከላይ ያለው መሪ ዘረኛ ሆኖ ዘረኝነትን እንዋጋ ቢል ሰሚ ከወዴት የገኛል?

4ኛ. የማይፈጸም ነገር ቃል መግባት ሌላው የችግሩ መገለጫ ነው:: ቃል መግባት ቀላል ነው:: ቃል መግባት ዋጋ አይከፈልበትም:: ከባዱ ቃልን ወደ ተግባር መለወጡ ላይ ነው:: ከእንግዲህ ዐይነቱ ጠባይ ነው አንዱ ያለ መታመን ጣጣ የሚመጣው:: መሪ የሚታመነው ከቃሉ በላይ በተግባሩ መሆኑ የሚረሳበት ጊዜ ያለ ይመስላል:: ሰው የሚለካው በተናገረው ልክ ሳይሆን በሚፈጽመው ልክ ነው:: ቃል ገብቶ ካለመፈጸም በትንሹ ቃል ገብቶ ከተቻለ ቃል ከገቡት በላይ መፈጸም እወነተኛ ተከታይን ለማፍራት ያስችላልና:: ያለዚያ "እርሱን ያመነ እና ጉም የዘገነ" በሚል መሪውን ፍጹም ታአማኒነትን ሊያሳጣው ይችላል::

የሚናገረውን የሚከውን፣ ቃሉና ተግባሩ የተስማሙ፣ በቃል ኪዳኑ የሚገኝ፣ የገባውን ቃል የሚፈጽም ሲሆን መሪ ታማኝነትን ያገኛል:: ቃልና ተግባሩ የማይገናኙ ሲሆን፣ ቃል ኪዳን ሲረክስና ከቃል የማያልፍ ሆኖ ሲገኝ መሪ ተፈትኖ ሊወድቅ ይችላል:: ቃልና ተግባሩ የተስማሙለት፣ የተፈተነና ትናንትም ዛሬም የማይለውጥ መሪ ሲገኝ እገሌ የሚባል መሪ ታማኝ ነው፤ በቃሉ የሚገኝ ነው፤ በተግባር የተፈተነ ነው፤ በማይሠራው ቃል አይገባም፣ ቃል የገባውን ሳይፈጽም እረፍት የለውም የሚል ስም ይወጣለታል::

መጽሐፍ "ከንፈሩን የሚገታ አስተዋይ ነው::" እንዲል መሪ ምኞቱን ሁሉ ቃል ከመግባት የሚችለውን ብቻ ተስፋ ቢሰጥ የተሻለ ነው:: (ምሳ. 10፥19) በኋላ ሳይፈጸም ሲቀር ይህን ያህል ቃል ገብቶ፣ የማይጨበጥ ተስፋ ሰጥቶን፣ በተግባር ግን የውኃ ሽታ ሆኖ ቀረ ከመባል ሊሳካ የሚችለውን መጥኖ ተስፋ መስጠት ለሁሉም የሚበጅ ነው:: ብዙውን ጊዜ መሪዎች ቃል የሚገቡትን ያህል በተግባር ሆነው አይገኙምና ከጅምሩ ብዙም ቢናገሩ ሕዝብ ግን ተስፋ የሚያደርገው በከፊል ልብ ነው:: በተለይ አንዳንድ መሪዎች ሲናገሩ የተስፋ ዳቦ የሚያስገምጡ ቢሆንም በተግባር ግን ብዙም ጠብ ሊላቸው የሚችሉ አይደሉም:: ውጤታማ መሪ

“አፉ ቂቤ “ የሚባል ዐይነት ሳይሆን ብዙ የሚከውን ጥቂት የሚናገር ነው:: ንግግር ሲበዛ መሳትም ይመጣል:: ለመሪ አጨብጫቢው ብዙ ነውና “ሲስቁበት የተሳቀለት ይመስለዋል” እንደሚባለው፣ ባጨበጨቡ ቁጠር ያጨበጨቡለት እየመሰለው ያለውን ሁሉ ቢዘረግፉትም ንግግር ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል:: አስተዋይ መሪ ነገሩ የተመጠነ ነው:: ቁም ነገር የሚገኘው በቃል ብዛት ሳይሆን በፍሬ ነገሩ መሆኑን ይረዳልና::

5ኛ. መተማመን የሚቻለው ግልጽነት ሲኖር ነው:: ለጊዜው ቢደብቁት ጊዜው ሲደርስ ችግሩ መታውቁም አይቀርምና:: ግልጽነት ሲኖር በግልጽ የተሠራው ይሄ ነው፤ ስላልተሠራው ያልተሠራበት ምክንያት ይሄ ነው፤ ከዚህ ቀጥሎ የምንሄደው እንዲህ ባለ መንገድ ነው ማለት ይቻላል:: እንዲህ ሲሆን በግምትና በይሆናል ከሚፈጠር ግራ መጋባት ያድናል:: ችግር ቢገጥም እንኳ መሪ ብቻውን ችግሩን ከማፈን በግልጽነት ማካፈልና ከሚመራቸው ሰዎች ጋር መወያየት አንድም መፍትሔ ሊገኝለት ይችላል ካልሆነም ችግሩን አብሮ ለመጋፈጥ እድል ይሰጠዋል:: መቼም ሁሉም ነገር በይፋ እንደማይነገር የሚታወቅ ቢሆንም ሁሉም ነገር ምስጢራዊ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ያልተሠራው ተሠራ ያልተደረገው ተደረገ፣ የሚል ወሬ እንዲበራከትና ውሸት ሥራቸው ለሆኑ ሰዎች ነጩን ጥቁር አድርጎ ለማቅረብ የተመቸ ነው የሚሆነው:: መረጃ በበዛበት የሚዲያ ዘመን ክፉ ወሬ አገር ሊያጠፋ ይችላልም:: በተመሳሳይ ከተለያየ አቅጣጫ እርስ በርሱ የሚጣረስ መረጃ የሚቀርብበት ጊዜ ሲከሠት፣ አንዱ መሪ የተናገረውን ሌላው ሲያጣጥለው፣ አንዱ መሪ ዛሬ የተናገረውን ነገ ደግሞ ተቃርኖ ያለው ሌላ ንግግር በሚቀርብበት ጊዜ ግራ መጋባት ብቻ ሳይሆን መተማመንን በእጅጉ ይፈትነዋል::

በተለይ አዲስ ለውጥ ሲመጣ፣ ለውጥን ከሚያደናቅፉ ምክንያቶች መካከል ለውጡ ምን ይዞብን ይመጣ ይሆን? የሚል ፍርሃትና ጥርጣሬ አንዱና ዋናው ምክንያት ነው:: በተቋም ደረጃም ይሁን በአገር ደረጃ ወይም በማኅበረሰብ ደረጃ ለውጡ የሚነካቸው ሁሉ ስለ ነገ መጪነቃቸው አይቀርም:: በተለይ መዳረሻው ግልጽ ሆኖ የማይታይ ወይም የማይታወቅ

ከሆነ፣ በዚያም ላይ መሪው ከሥር ከሥሩ በአንድነት ስለሚሄዱበት መንገድም ስለ ሚደርሱበት ፍጻሜም ለተከታዮቹ ካልተናገረ ግራ መጋባት ይመጣል:: ለውጥ የተሻለ ሳይሆን የባሰ ነገር ይዞበት እየመጣ መከራ መቀበል በለመደ ማኅበረሰብ መካከል ለውጥን መተግበር የባሰ አስቸጋሪ የሚያደረገው አንዱ ምክንያትም ይሄው ነው::

በሌላ በኩል እውነተኛ መሪዎች ሲበረክቱ እውነተኛ ማኅበረሰብን ለመፍጠር እንደሚያግዝ ሁሉ፣ ግልጽነት በመሪዎች ሲዘወተር ግልጽነት በማኅበረሰቡ እንዲለመድ የራሱ አስተዋጽዖ እንደሚኖረውም የሚታመን ነው:: ግልጽ የሆነ ማኅበረሰብን ለመገንባት መሪዎች አብነት ሆነው ከማሳየት ባሻገር ግልጽነት የሚያድግበትን ሥራ መሥራትና ለዚህም የሚመች ከፍርሃት ነጻ የሆነ ከባቢን በመፍጠር መሪዎች ትልቅ አስተዋጾ ይኖራቸዋል:: ዘመኑም ግልጽነትን ግድ የሚል ነው ማለት ይቻላል:: በዚህ የሚዲያ ዘመን በቅኔና በአሽሙር፣ በሐሜትና ሹክሹክታ የሚነገርበት ባህል እየቀነሰ በግልጽነት የሚነገርበትን ባህል ማዳበር ተገቢ ነው:: ግልጽነት በሌለበት መሪዎች ለሚያወጡት ፖሊሲ በቂ ግብአት እና የሕዝብ አስተያየት ለማግኘት ከባድ ይሆናል:: መቼም በዚህ የመረጃ ዘመን እንደ ጥንቱ "እረኛ ምን ይላል? " እያሉ መረጃን ማግኘት የሚቻልበት ዘመን አይደለምም::

6ኛ. መተማመን የጋራ ነው:: የሚታመን መሪ እንደሚያስፈልግ ሁሉ የሚያምን ተከታይም ሊኖር ይገባል:: መሪዎችን ማመን የሚጎድለው ከመሪዎች አለመታመን ብቻ ሳይሆን ተመሪውም ተጠራጣሪና የማያምን በሚሆንበት ጊዜም ሊፈጠር እንደሚችልም የሚዘነጋ አይደለም:: በተለይ መረጃ ሲጠፋ አሉባልታ መረጃ ይሆናልና ግምት እንደ እውነት ይቆጠራል:: የሚሆነውን ለሚያስተውል ሴራ የሚባለው ነገር ምናልባት እንደዚህ ዘመን በዚህ አገር ነበር? ወይስ አዲስ ባህል ሆኖ እየመጣ ነው? ያሰኛል:: አንድ ክሥተት ሲከሠት ከክሥተቱ በላይ ሐሜቱ ይበረክታል፤ ሁሉም የየራሱን መላምት እንደ መረጃ ያሠራጫል:: እነ እገሌን አትመኗቸው ሲል እውነት ከእርሱ ጋር ብቻ እንዳለ ሆኖ ትንተና

የሚያቀርብ ይበዛል:: መሪዎቹን በሚጠራጠር ማኅበረሰብ ደግሞ እንዲህ ዐይነት የሴራ ወሬ ተከታይ አያጣም::

ጥርጣሬ ሲበዛ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍ በሽታ ይሆናል፡፡ ሌሎችን የማያምን ብቻ ሳይሆን እርስ በርሱ የማይተማመን ሁሉንም ነገር በጥርጣሬ የሚታየበት ባህል ሊፈጥር ሲችል አደገኛነቱን ማሰብም አያዳግትም:: በዚህ ሁሉ የሚደርሰውን ውድመት ማስተዋል የሚቻለው ግን እንዲህ ዐይነቱ የሴራ፣ የሐሜት፣ የፈጠራ ወሬዎች ፍሬ አፍርተው ግጭት ሲያስከትሉና መተላለቅን ሲያመጡ፣ ብዙ እልቂትና ውደመት ከደረሰ በኋላ ነው:: ነጋዴዎቹ የፈጠራ ወሬያቸውን ይዘራሉ እንጂ የመከራው ተካፍይ እንደማይሆኑም ያውቁታል:: የመከራው እሳት የሚያቃጥለው ከምኑም የሌለበት ንጹሓኑን ነው::

እንዲህ ዐይነቱ ክፍተት የሚፈጠረው፣ በአንድ በኩል የመረጃ እጥረት በመኖሩ ሊሆን ይችላል:: መረጃን መደበቅ ለጊዜው የሚያዋጣ መንገድ አድርጎ የማየት ዝንባሌ ባለበት፤ በተለይ መረጃን የመጠዬቅ ባህል በሌለበት ቢጠይቅም ሰሚ በማይገኝበት ሁኔታ፣ ክፉ ወሬ ቦታ ያገኛል:: መረጃ ሲጠፋ ያልተደረገውን ተደረገ፤ ያልሆነውን ሆነ ያልታሰበውን ተፈጸመ ብለው ለሚያወሩ ሰዎች የተመቸ ነው የሚሆነው:: የመረጃ እጥረት ባለበት ሁኔታ እና አሉባልታንና እውነታን በአግባቡ ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል የሥልጣኔ ደረጃ በሌለበት፣ እንዲሁም ሰውን በጭፍን ከመደገፍ ወይም ከመጥላት ይልቅ እውነታውን ማስቀደም እና ከእውነት ጋር የመሰለፍ ልማድ አናሳ በሆነበት ሁኔታ አለማመን፣ መጠራጠር፣ መወናበድ እና ግራ መጋባት ሊያመዝን ይችላል::

በአንጻሩም በሬ ወለደ ሲባል እንዴት ሆኖ? ማለት የሚችል ጠያቂ ማኅበረሰብ ከሌለ አሉባልታ አገር ለማጥፋት ጊዜው የተመቻቸ ነው:: አሉባልታ ሐሜት ሆኖ የሚቀርበት፣ ወሬ ከመንደር የማያልፍበት ዘመን አሁን የለም:: ዘመኑ አሉባልታ እንኳን በቀላሉ ሊታለሉ የሚችሉትን፤ አዋቂዎች የተባሉትን ሳይቀር ሊያሳስት በሚችል መልኩ ዜና መስሎ፣ ተከሽኖ ጥቂት እውነት በሐሰት ተሸፍኖ በደቂቃዎች ዓለምን ማዳረስ የሚችልበት ዘመን ነው:: እንዲህ ባለ የሐሰት ወሬ በሚበዛት ዘመን

መድኃኒቱ እውነቱን ከሐሰት ለመለየት ጥረት የሚያደርግ፣ ሚርቱን ሚርት ነው የሚል ጠያቂ ማኅበረሰብ መፍጠር ነው:: “ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን ” ነው የቅዱስ መጽሐፍም ቃል::

7ኛ. ታማኝነት ለመጎልበትም ሆነ ለማሻቀልቀሉ የማኅበረሰቡ እሴትም ትልቅ አስተዋጽዖ አለው:: ማኅበረሰቡ ሌብነት ምን ያህል ነው የሚጸየፈው? ሰርቆ መክበር አሁን እንዴት ነው በማኅብረሰቡ ዘንድ የሚታየው? በሐሰት መናገር፣ በሐሰት መመስከር፣ አደርባይነት የመሳሰሉ ነገሮች በማኅበረሰቡ ዘንድ ያላቸው እይታ ምን ይመስላል? ቀደም ሲል የነበረው እሴትስ ምን ይመስል ነበረ? የሚሉትን ስንመረምር ነው አስተዋጽዖውን መረዳት የሚቻለው:: መረጃን ባግባቡ የሚቀበል፣ ከአሉባልታ ይልቅ እውነቱን ለማወቅ የሚተጋና መረጃን ለማመሳከር ዓቅም ያለውና መረጃንም ከተለያዩ ምንጮች ለማግኘት የሚችል ትውልድ ከተፈጠረ አሉባልታን መቀነስ ይቻል ይሆናል:: መረጃን በመሰለኝና በደሳለኝ ለመተንተን ከመሞከር እውነቱን ለማጣራት ከየአቅጣጫው ነገሮችን ይፈትሻልና:: ዘወትር በጥርጣሬ ከማየት በሓላፊነት ስሜት የተነገረ ነው ብሎ የመሪዎችን ድምፅ የሚሰማ፣ ከሚወደው ወገን ጥፋት ሲፈጠር ይህማ አይሆንም የክፉ መሪዎች ደባ ነው ከማለት ይልቅ እውነትን ከሐሰቱ መርምሮ የሚለይም ይሆናል:: በገለልተኝነት ከወገንተኛነት ነጻ ሆኖ ነገሮችን ማየት የሚችል፣ ለመረጃ ቅርብ የሆነ ማኅበረሰብ ባለበት ሁኔታ በሬ ወለደ ዐይነት አሉባልታና ወሬ፣ ሽፍጥና ሴራ ብዙም ቦታ ሊያገኙ አይችሉም:: የሐሰት መስካሪ በግላጭ በአደባባይ በገንዘብ የሚገዛበት ደረጃ መደረሱ ለበጎ እሴት መሸርሸር ማሳያ ሊሆን ይችላል::

ጠንካራ ማኅበራዊ እሴትና ፈሪሃ እግዚአብሔር በነበረበት ዘመን ሰርቆ ፎቅ መሥራት ከጎረቤት ክብርን ሳይሆን ሀሜትና መገለልን ሊያስከትል ይችል ነበረ:: ከጎረቤት የተደበቀ ነገር ምን አለ? ከሕዝብ ዐይንና ጆሮ የተደበቀ ምን ነገር አለ? እንዲህ ዐይነት ሌብነት ጸያፍ ተደርጎ በሚታይበት ማኅበረሰብ ታማኝነት ይጎለብታል:: መዋሸት ኃጢአት ብቻ ሳይሆን በማኅበረሰቡም ነውር ተደርጎ በሚቆጠርበት ጊዜ ሐሰተኛ አይበረክትም:: ቃልን ማፍረስ፣ መካካድ በማኅበረሰብ የተጠላ ነገር ሲሆን መተማመን ይጎለብታል:: በአንጻሩ ማጭበርበር፣ ማታለል፣ ሌብነቱ እንደ ሥልጣኔ፣

እንደ መሰልጠን ተደርጎ ሲወሰድ ብዙ ክሥረት የሚደርሰው ያን ጊዜ ነው::

8ኛ. ተቋማዊ ሥርዓት ደካማ መሆን ታማኝነትን እንዲሸረሸር ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንደኛው ነው:: በተቋም ደረጃ ታማኝነትን ለማጎልበት አራት ነገሮች አስፈላጊ እንደሆኑ ይጠቀሳል:: እነርሱም 1) ሥነ ምግባርን ማጎልበት 2) የቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር 3) የተጠያቂነት ሥርዓትን ማጠናከር እና 4) ተቋማዊ ዓቅምን መገንባት ናቸው:: ታማኝነትን ለመገንባት የጠባይ ለውጥ ለማምጣት ከሚደረገው ሥራ በተጨማሪ ተቋማዊ ሥርዓትን፣ ተጠያቂነትን እና ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓትን መገንባት አስፈላጊ ነው:: እነዚህ አራት ነገሮች ሌብነትን፣ አጭበርባሪነትን፣ ሐሰተኛነትን ለመከላከል የማይተካ ሚና አላቸውና::

ብዙ ተቋማትም ታማኝነትን እንደ ዋነኛ እሴት ማካተታቸው የተለመደ ነው:: ታማኝነት መለያችን ነው፣ ለታማኝነት የቆምን ነን፣ በታማኝነት እናገለግላለን በሚሉ አገላለጽ ታማኝነትን እንደ እሴት የሚያስቀድሙ ተቋማት ቁጥራቸው ቀላል አይሆንም:: ትልቁ ጥያቄ ግን ከወረቀት ባለፈ ታማኝነትን በተግባር ለመተርጎምና የታማኝነት እሴትን ለማስፋፋት ተቋሙና የተቋሙ መሪዎች ምን ያህል ቁርጠኝነት አላቸው? የሚል ነው:: ግብሩ በወረቀት ላይ እሴት ተብሎ ከሰፈረው በተቃራኒው ሆኖ የሚገኝበት ጊዜ ቀላል አይደለምና:: ምክንያቱ ምንድን ነው? ቢባል እሴት ሕይወት የሚኖረው ከቃል ባለፈ በተግባር የሚተገብሩት በመሆኑ ነው:: በተቋም ደረጃ እንዲህ ዐይነቱን እሴት በሕይወት ለመኖር ከቁርጠኝነት በተጨማሪ በቂ የሰው ኃይልና ገንዘብ ተመድቦለት አሠራርና ሕግ ተበጅቶለት በየጊዜው እየተፈተሸ በየጊዜው እዲሻሻልና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ ይፈልጋል:: መሪዎች ታማኝነትን፥ ሐቀኝነትን በሚመሩት ተቋም እንዲጎለብት ማድረግ የሚችሉት የሚሰብኩትን በሕይወት እየኖሩ ምሳሌ መሆን ሲችሉ ነው የሚለውም በሰፊው የተጻፈበት ነው[9]:: ዛሬ በየተቋማቱ

[9] The consistent living out of values is the way leaders demonstrate their honesty and trustworthiness. The Leadership Challenge, James Kouses, Page 40, file:///C:/Users/wb242998/OneDrive%20-%20WBG/References/LEADERSHIP%20CHALLENGE.pdf

የሚዘረፈው ገንዘብ ግምት ውስጥ ከገባ ታማኝነትን ለማጎልበት አስፈላጊ ወጭ ማድረግ አዋጭ መሆኑን መገንዘብም አያዳግትም::

9ኛ. ታማኝነትን ከሚሸረሽሩ ነገሮች በቀዳሚነት የሚነሣው የመዋሸት ባህል ነው:: ይህ ጉዳይ ሐቀኝነት በሚለው ርእስ ሥር በሰፊው የሚዳሰስ ይሆናል::

በአጠቃላይ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ተመሪ አንድ ጊዜ በመሪዎቹ ላይ አመኔታ ካጣ ያኔ ነው ብዙ ነገር መበላሸት የሚጀምረው:: በሀገር ደረጃም ይሁን በተቋም ደረጃ ተመሳሳይ ነው:: ታማኝነት እንዳይሸረሸር መጠበቅ ነው እንጂ አንዴ ከተሸረሸረ መልሶ መገንባት የዳገት ጉዞ ነው የሚሆነው:: መድኃኒቱ ታማኝነት እንዳይሸረሸር መጠበቅ ነው:: በሌላ በኩል በመሪነት ሕይወት ታማኝነትን ከማግኘት የሚበልጥ ስኬት የለም:: ታማኝነትን ማትረፍ ሲቻል ተከታይ መሪውን ይሰማል፤ ለመሪው ይታዘዛል፤ ለመሪው ሕይውቱን አሰልፎ እስከ መስጠትም ይደርሳል:: መሪው የማይታመን ከሆነ፣ መሪ በጥራጣሬ የሚታይ ከሆነስ ራእይውን ማን ይጋራዋል? ሕልሙን ማን ይካፈለዋል? ንግግሩንስ ማን ከቁብ ይቆጥረዋል?

2.3 ሐቀኝነት ምንድን ነው?

የአማርኛ መዝገበ ቃላት ሐቀኝነት የሚለውን ቃል ሐቀኛ መኾን፣ እውነተኛነት በሚል የሚተረጉመው ሲሆን በዚሁ መዝገበ ቃላት የእንግሊዘኛ ትርጉሙን honesty, integrity, probity በሚል ያስቀምጠዋል::

ሐቀኛ ሰው ማለት እውነትን የሚናገር፣ እውነት የሚሠራ፣ እውነትን የሚመስክር ማለት ነው:: ለጊዜያዊ ጥቅም መዋሸት፣ በንጹሕ ሰው ላይ በሐሰት መመስከር፣ ማታለል፣ ሽንገላ እኒህ ሁሉ የእውነት ተቃራኒዎች ናቸው:: አንዱ የታማኝነት መገለጫም ሐቀኝነት ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውሸተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ አሰጸያፊ እንደሆነ ሁሉ፣ እውነትን የሚያደርጉ ግን በእርሱ ዘንድ የተወደዱ

መሆኑን “ሐሰተኛ ምላስን እግዚአብሔር ይጠላል፤ የሸንገላ ከንፈርንም ያጠፋቸዋል” ተብሎ ተጽፏል:: (ምሳ 17፥4) ሐሰተኛነት፣ ሐሰት መናገር፣ በሐሰት መመስከር፣ ማታለል፣ መሸንገል እና አስመሳይነት ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስጠይቅ ነው::

በሐሰት መመስከር ከአሥርቱ ትእዛዛት መካከል አንዱን መጣስ እንደሆነም የታወቀ ነው:: እንዲያውም እግዚአብሔር የሚጠላቸው ተብለው ከተዘረዘሩት መካከል ሐሰተኛ ምላስ፣ ሐሰተኛ ምስክር እና ጠብን የሚዘራ የሚሉት ሦስቱ ሐሰትን የተመለከቱ ናቸው፡፡ “እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች ናቸው፣ ሰባትንም ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፈዋለች፡፡ ትዕቢተኛ ዐይን፣ ሐሰተኛ ምላስ፣ ንጹሕን ደም የምታፈስስ እጅ፣ ክፉ አሳብን የሚያበቅል ልብ፣ ወደ ክፉ የምትሮጥ እግር፣ በሐሰት የሚናገር ሐሰተኛ ምስክር፣ በወንድማማች መካከልም ጠብን የሚዘራ፡፡” ተብሎ እንደተጻፈ:: (ምሳ 6፥16-19) መዋሸት፣ በሐሰት መመስከር፣ ጠብን መዝራት ከቶ በየትኛው ሃይማኖት ወይም የማኅበረሰብ እሴት ተቀባይነት ሊኖረው ይችላልስ?

“አቤቱ፣ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል? በቅንነት የሚሄድ፣ ጽድቅንም የሚያደርግ፣ በልቡም እውነትን የሚናገር በአንደበቱ የማይሸነግል፣ በባልንጀራው ላይ ክፋትን የማያደርግ“ ሲልም ለዘላለማዊ ሕይወት ሰው ከሚመዘንባቸው መለኪያዎች መካከልም እውነተኛነት አንዱ እንደሆነም ቅዱስ ዳዊት ይናገራል:: (መዝ 14፥1-2)

እንዲሁም እውነት የሚያምረው ከፍቅር ጋር እንደሆነም፣ “ነገር ግን እውነትን በፍቅር እንያዝ” ሲል ይመክራል:: (ኤፌ 4፥15) እውነትን በፍቅር መያዝ ማለት ምስጢር ያለው ነው:: ምርጫው መስቀለኛ የሚሆንበት ጊዜ ብዙ ነውና:: ለእውነት ማድላት ሲኖር ፍቅር ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ ለፍቅር ማድላት ሲኖር እውነት ሊጎዳ ይችላል:: ሁሉንም ማቻቻል፣ ሁሉንም አመጣጥኖ መሄድ መስቀለኛ መንገድ ያለበት ፈተና በመሆኑ ነው እውነትን ከፍቅር ጋር እንያዝ መባሉ::

መሪነት የሚፈልገው አንዱ ጥበብ ይሄ ነው፥ የእውነትንም የፍቅርንም ሚዛን አለመሳት::

ሐቀኛነት አለመሳሳት ማለት አይደለም:: ሰው ሆኖ አለመሳሳት አይቻልምና:: ሐቀኛነት ግን ስሕተት ሲፈጽም ተሳስቻለሁ ብሎ በጎደለው ነገር መጸጸትና ይቅርታ መጠየቅ፣ ወደፊትም ተመሳሳይ ስሕተት እንዳይፈጽም ጥንቃቄ ማድረግ መቻል ነው:: ሐቀኛነት በንጹሕ ልብ፣ በቀና መንፈስ እውነትን ለመናገር፣ እውነትን ለመሥራት፣ ከእውነት ጋር ለመቆም ጥረት ማድረግ ነው:: ከዓቅም በላይ በማወቅም ባለማወቅም ስሕተት ቢፈጠር ያ የእርሱ ድርሻ አይደለም:: በውሱን ዓቅም መካከል የሚቻለውን ሁሉ በቅንነት እየሠሩ መሳሳት ሰው የመሆን አንዱ መገለጫ ነውና:: "ፍጥረታችንን እርሱ ያውቃልና፣ አቤቱ፣ እኛ አፈር እንደ ሆንን አስብ::" ተብሎ መጻፉም ይህንን ያሳያል:: (መዝ. 101፥14)

በአንጻሩም ቅንነት በሚጎድልበት ክፋት በሚያይልበት ሁኔታ በተግባር የሚበዛው ሐሰተኛ እንደሆነ እና እውነተኛ ሰው ማግኘት ጭንቅ እንደሆነም "እኔም ከድንጋጤዬ የተነሣ ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው አልሁ" የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን:: (መዝ. 116፥11) ወደ ውሸት ማዘንበል የክፋት ውጤት መሆኑንም "ክፉ ሰው የበደለኛን ከንፈር ይሰማል፣ ሐሰተኛም ወደ ተንኰለኛ ምላስ ያደምጣል::" የሚለው ያሳየናል:: (ምሳ. 17፥4)

በአጠቃላይ በተግባር ብዙ ጉልደት ቢታይበትም ሐቀኝነት በየተቋማቱም ይሰበካል፥ ብዙ መጽሐፍትም ተጽፏለታል:: በሥራ አመራር ሳይንስም በሌሎችም ባለሙያዎች ብዙ ጥናት ያደርጉበታልም:: ተቋማት በእሴቶቻቸው አካተውታል:: በትምህርት ቤት በቤተሰብ ልጆች እውነተኛነትን እንዲለማመዱትም ብርቱ ጥረት ይደረግበታል:: ተጠያቂነት ባለበት አገር መዋሸት ብዙ ዋጋን ሲያስከፍል ነው የሚታዬውም:: መዋሸት፥ ማታለል፥ መሸንገል፥ ማሳሳት፥ በሐሰት መመስከር በሕግ የማያስጠይቅበት አገርስ ወዴት ይገኛል?

በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሐቀኛነት በጥቅሉ በምን መልኩ ሊገለጽ ይችላል? በፖለቲካው ዓለም፣ በመንፈሳዊው ዓለም፣ በንግዱና በአጠቃላይ በሌላው ማኅበረሰብ የየቀን ውሎ ሐቀኛነት እንደ እሴት እያደገ ነው የሄደው ወይስ እያሽቆለቆለ? ውሸት ባህል የሚሆነው ምን ሲሆን ነው? ውሸት ባህል ሲሆንስ የሚያመጣው አደጋ ምን ያህል ነው? ለእውነት የሚያደሉ፣ ለእውነት የሚቆሙ መሪዎችን ማፍራት የሚቻለው በምን ሁኔታስ ነው? የሚሉት ጉዳዮች ብዙ ውይይቶችን ሊጋብዙ እንደሚችሉ የሚጠበቅ ነው:: በአብዛኛው ዓለም ልንገለጽበት የምንችለው ኢትዮጵያውያን ታማኞች ናቸው፤ እውነተኞች ናቸው፤ የተጣለባቸውን አደራ አክባሪ፣ የተናገሩን የሚፈጽሙ፣ በቃላቸው የሚገኙ፣ ከውሸት ይልቅ ለእውነት የሚያደሉ በሚል ነው? ወይስ በተቃራኒው? የሚለውም በግልጽ ውይይት ቢደረግበት ጉድለቱን ለማወቅና ጉድለቱን ለማስተካከል ብዙ ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል::

መቼም ውሸትን እንደ በጎ ነገር የሚቀበል፣ ውሸትን የሚያበረታታ ማኅበረሰብ እና ባህል ይኖራል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም:: በተግባር ያለው እውነታ ሌላ የሚሆንበት ጊዜ ቢኖርም:: በየትኛውም ሃይማኖት ውሸት፣ በሐሰት መመስከር፣ ሽንገላ፣ አታላይነት ይህ ሁሉ የተጠላ ተግባር ነው:: በተግባር ያለው እውነታ ሌላ የሚሆንበት ጊዜ ቢኖርም::

2.3.1 በመሪዎች ዘንድ ውሸት ልማድ ሲሆን

መሪ ሲናገር አድማጭ ብዙውን ጊዜ መጀመሪያ የሚጠይቀው ይሄ ሰው የሚናገረው ከአንገት ነው ከአንጀት? የሚል ነው:: ከአንጀት ነው ብሎ ሲያስብ አድማጭም ከልቡ ያዳምጠዋል:: ከአንገት ነው ብሎ ሲያስብ ደግሞ ይሰመዋል እንጂ ሊያዳምጠው አይችልም፤ በቀኝ ጆሮ የገባውን ከልብ ሳይደርስ በግራ ጆሮ ይፈሳል:: የመሪውን ማንነት ከማንም በላይ የሚያውቀው ተመሪው ነውና:: ታማኝ መሪ ሲናገር ተከታዮቹ ድምፁን ይሰሙታል:: የሚናገረውን ነገርም በማስመስል ሳይሆን በእውነት እና በግልጽነት እንደሚናገር ስለሚታመን የሚሰማው ሁሉ በአንድ ጆሮ ሰምቶ በሌላው ከማፍሰስ ይልቅ ልብን ከፍቶ ያዳምጠዋል:: ልባቸውን

ለተከታዮቻቸው የሚሰጡ መሪዎች ተከታዮቻቸውም የሚያዳምጧቸው በጆሮ ብቻ ሳይሆን በልብም ጭምር ይሆናል:: "መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉምም፤ ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱምም"ተብሎ እንደተጻፈ መስማት ሁሉ ማዳመጥ ሊሆን አይችልምና:: (ኢሳ. 6፥9)

ውሸት ሲደጋገም ሕዝቡ ተስፋ ቆርጦ ቴሌቭዝን ማዳመጥ እስከማቆም ደርሶ ነበር በሚባልበት ጊዜ ጋዜጠኛው "እንደምን አመሻችሁ አታምኑኝም እንጂ ሰዓቱ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆኗል" አለ ተብሎ ይቀለድ ነበር:: ሕዝብ በመሪዎቹ ላይ እምነት ሲያጣ እውነት ቢነገር እንኳ ሰሚ ጆሮ ሊጠፋ እንደሚችል የሚያሳይ ነው:: ሐሰት ባህል በሆነበት፣ መዋሸት እንደ ጥበብ በሚቆጠርበት ሁኔታ መሪዎችን ማመን ከባድ ቢሆን የሚደንቅ አይደለም::

መሪዎችን መጠራጠርና አለማመን ያለ ምክንያት አይመጣምም:: ሐሰት በመሪዎች ሲነገር መስማት እንግዳ ነገር አይደለም:: ሸንገላ፣ ማታለል፣ መዋሸት እንደ ጥበብ፣ እውነትን መደበቅ እንደ ጀግንነት በሚቆጠርበት ዓለም ሕዝብ መሪዎችን ለማመን ቢቸገር የሚገርም አይደለም:: መሪዎች ሲዋሹ ታማኝነት ይሸረሸራል:: የማታለያና የሸንገላ ቃል በሚበዛበት ሁኔታ አመኔታ እንዴት ሊኖር ይችላል?

ውሸትን ልማድ ያደረጉ መሪዎች የሚናገሩት የሚያምኑበትን ሳይሆን ሕዝብ ሊሰማ ይገበዋል ተብሎ የሚታመንበትን፣ እውነቱን ሳይሆን እውነት እንዲመስል የተዘጋጀ ጉዳይ ነው። "ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል" እንደተባለ ውሸትን ስለደጋገሙት እውነት የሆነ ይመስላቸዋል እንጂ ውሸት እየተናገሩ እንደሆነ እንኳ ይረሳልም:: "ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል" የሚለውን ፍልስፍናም ብዙ መሪዎች አሁንም ሲከተሉት ይታያል:: ውሸት ሲደጋገም ጊዜው እስኪደርስ እና እውነቱ እስኪገለጥ እውነትም ይመስል ይሆናል:: ውሸት ምንም ያህል ጊዜ ቢደጋገም፣ በምንም ዐይነት ጥበብ ቢነገር እውነት ግን ሊሆን አይችልም:: በድምፅ ብልጫም ውሸት እውነት አይሆንም:: እውነት ሚሊዮኖች

ስላመጹበትም፣ እውትነቱን አይለቅም:: ሚሊዮኖች ተሰባስበው ሐሰትን እውነት ነው ብለው ስለተስማሙም ሐሰት እውነት ሊሆንም አይችልም::

የሚከፋው ግን ውሸት በተደጋገመ ቁጥር እውነት ቢነገር እንኳ ያው የተለመደው ውሸት ነው ተብሎ ይወሰድና እውነትም የማይታመንበት ጊዜ ሲደርስ ነው:: አንድ የሚነገር ታሪክ አለ:: ቀበሮ መጣ እያለ በተደጋጋሚ የሰፈሩን ሰዎች ሲያታልል ቆይቶ አንድ ቀን እውነተኛው ቀበሮ መጣበትና ኡኡታውን ቢያሰማ ሰፈርተኛው ተሰላችቶ ስለነበር ያው ልማደኛ ዋሾ ነው ብለው ሳይደርሱለት በቀበሮ እንደተበላው እረኛ ታሪክ ነው የሚሆነው:: በየትኛውም ደረጃ ያለ መሪ ደጋግሞ ከዋሸ እውነት ቢናገርም እንኳ የሚያምነው ሊጠፋ ይችላል:: አንዴ ውሸታም ነው የሚል ስም ከወጣ ያን ስም ማስቀየር ከባድ ነው የሚሆነው::

በተመሳሳይ ውሸትን ልማድ ያደረጉ መሪዎች ብዙውን ጊዜ የሚጨነቁት ስለ ማሳመን እንጂ ስለ እውነት አይደለም ይባላልም:: ዋናው ቁምነገር ውሸት ተናግሮም ቢሆን ማሳመን ነው የሚል ነው ፍልስፍናው:: ብልጣብልጥነትን የሚያበዙ መሪዎች እውነት ተናግሮ ከማሳመን ይልቅ የሚጠቀሙትም ማታላልን ነው:: በእርግጥ ለጊዜው ማታለል ወይም መሸንገል ይቻል ይሆናል:: "ያለ ነውር የሚሄድ ተማምኖ ይሄዳል፣ መንገዱን የሚያጣምም ግን ይታወቃል::" እንደተባለ ይዘገይ ይሆናል እንጂ ሁሉም በጊዜው መገለጡ፣ እውነተኛ ማንነት መታወቁም ግን አይቀርም:: (ምሳ. 10፥9) ማስመሰል መመሳሰል የሚቻለው ለጊዜው ነው:: ወርቅ ቅብ ሲከራርም መገርጣቱ አይቀርም:: የሚዘልቀው ወርቅ ቅብ ሳይሆን እውነተኛ ወርቅ የሆነ እንደሆነ ነው:: ጊዜ የማይገልጠው ነገርስ ምን ይኖራል? ሁሉም የጊዜ ጉዳይ ነው:: ሰው መታለሉን ባወቀ ጊዜ ግን መታለልን የሚወድ የለምና፣ ቢንቁኝ ነው ስለሚያሰኝ የባሰ ቁጣን ይቀሰቅሳል::

"እውነት ትመነምናለች እንጂ አትበጠሰም" እንደሚባለው አነጋገርም እውነትን በሐሰት ማዳፈን፣ ሐሰቱን እውነት ማስመሰል ይቻል ይሆናል እንጂ እውነትን ማጥፋት፣ እውነትን መደምሰስ እንደማይቻል ግን የታወቀ ነው:: "ኢኮኖሚ አሥር በመቶ አደገ ተባለ እኮ" ቢሉት አንዱ የኔ

ቢጤ ድሀ “የእኔ ኑሮ በአሥር በመቶ ሲቀንስ እንጂ ሲያድግ አላየሁም” አለ ይባላል፡፡ ሕዝብ ጉልበት አጥቶ፣ አንደበቱ ታፍኖ መናገር ባይችል እንጂ ከሚነገረው ቁጥር እና ትርክት በላይ በየዕለቱ የሚኖረውን ኑሮ ከማንም በላይ ራሱ ያውቀዋል:: በየሰፈሩ በየጎጡ የሚሠራው ሥራ ሁሉ የተሰወረ ቢመስልም ከሕዝቡ ዐይን እና ጆሮ የራቀ ባለመሆኑ ሕዝቡ ውሸት ሲነገር ውሸት መሆኑን አይስተውም::

2.3.2 ሐቀኛነት ከምን?

ሐቀኝነት በተግባር ከባድ ቢሆንም ተመራጭ የሚያደርጉት ምክንያቶች ግን ብዙ ናቸው::

1ኛ. ጤናማ ማኅበረሰብን ለመገንባትም ይሁን ጤናማ ተቋምን ለመምራት ሐቀኝነት እንደ እሴት አስፈላጊ ነው:: ሐቀኝነት የማኅበረሰብ እሴት ለማድረግ አርያ የሚሆኑ መሪዎች ማስፈለጋቸው ግድ ነው:: አንድ መሪ ተከታዮቹ ራእዩን እንዲጋሩት፥ ከጎኑ እንዲቆሙና እንዲከተሉት ለማድረግም ሐቀኝነት የማይተካ ሚና እንዳለው ነው የሥራ አመራር ጠበብትም የሚናገሩት[10]:: ሐቀኞች ሰዎች ሊበዙ የሚችሉት አርአያ የሚሆኑ መሪዎች ሲገኙ ነው[11]:: ሐሰተኞች ሲበዙም የሚነግስው ሐሰተኛነት ነው:: ሐቀኝነት በቤተሰብ በጎረቤት በትምህርት ቤት ሲሰበክም ሐቀኛ ልጆችን ማፍራት ይቻላል:: መሪዎች ከእውነት ይልቅ ሐሰተኝነትን ሲያስፋፉ ጤናማ ማኅበረሰብን ለመፍጠርም አስቸጋሪ ይሆናል:: ለምሳሌ በሐሰት መመስከር በተግባር ብዙ ችግር ከሚስተዋልባቸው በተለይ ባለፉት ዓመታት ብዙ ሮሮ ይሰማባቸው ከነበሩና እንደ ማኅበረሰብ ወዴት እየሄድን ነው? ካስባሉ ጉዳዮች መካከል ዋነኛ ሆኖ የሚጠቀስ ነው:: የሐሰት ምስክር በደላላ ሁሉ እየተፈለገ የሚገኝበት ዘመን ላይ ተደርሷል

[10] Trustworthiness, often a synonym for honesty, plays a major role in how leaders Enable Others to Act, as does the leader’s own competency. file:///C:/Users/wb242998/OneDrive%20%20WBG/References/LEADERSHIP%20CHALLENGE.pdf The Leadership Challenge, Page 36

[11] Great Leaders Use Honesty to Help Their Successors, https://hbr.org/2013/03/great-leaders-help-their-succe

የሚባል ነገር አለ:: እንዴት እዚህ ተደረሰ? ለሚለው መልሱ ቀላል ባይሆንም በመሪዎች ደረጃ ለፖለቲካ ፍጆታ የሐሰት ክስ ተዘጋጅቶ፣ የሐሰት ምስክር ተገዝቶ የሐሰት ፍርድ ከተደረገ የሐሰት መስካሪ ቢበዛ ምን ይደንቃል? መሪዎች እውነትን ለማስፋፋት አርአያ መሆን ሲገባቸው በአደባባይ በሐሰት ክስ የሐሰት ምስክርን አቁመው ተቀናቃኞቻቸውን ለመምታት የሚያደርጉት ሥራ ማኅበረሰቡ ስለ ሐቀኝነት ያለውን በጎ እሴት ቢጎዳው የሚጠበቅ ነው::

የሐሰት ምስክርነት ማለት ፍርድ ቤት ቀርቦ ባላዩት፣ ባልሰሙት፣ በማያውቁት ነገር በሐሰት መመስከር ብቻ ማለት አይደለም:: በሚዲያ መዋሸትስ ምን ሊባል ነው? እውነቱን እያወቁ አንዱን ወገን ደግፎ ሌላውን ለማጥቃት በሐሰት መናገርስ ምን ሊባል ነው? የንጹሓንን ስም በሐሰት ማጥፋት፣ ጥላሸት መቀባትስ? በማያውቁት ነገር እውነቱን እንደሚያውቁ አድርጎ ወሬ ማባዛት፣ በሐሰት ትርክት ጠብን መዝራት ይህ ሁሉ በሐሰት መመስከር ካልተባለ ምን ሊባል ይችላል? ሌላው ቢቀር በባልና ሚስት፣ በልጅ እና አባት፣ በወንድምና እኅት፣ ቤተሰብ ከቤተሰብ፣ ጎረቤት ከጎረቤት የማይወሻሽ አንዱ በሌላው በሐሰት የማይናገር በሐሰት የማይመስክር ስንት ሰው ማግኘት ይቻል ይሆን? እንዲህ ባለው ሁኔታስ የሚተማመን ማኅበረሰብን መገንባት እንዴት ይቻላል? ማኅበረሰቡስ እርስ በርሱ መተማመን ካልቻለ ጤናማ ማኅበረሰብን እንዴት መምራት ይቻላል? የሚለው ነው ሐቀኝነትን ተፈላጊ የሚያደርገው አንዱ ምክንያት::

2ኛ. ሐቀኝነት በመተማመን አብሮ ለመሥራት ይጠቅማል፤ የቡድን ሥራን ያሳለጠታል:: ሽንገላና ሸፍጥ በሚበዛበት ወዳጅ ወዳጁን አያምንም:: ከፊት ለፊት እየሳቀ ከጀርባ የሚወጋ ሁለት ዐይነት ሰብዕና ያለው ሰው የሚፈጠረው እንዲህ መተማመን በሌለበት፣ ሐሰት ባህል በሚሆንበት ሁኔታ ነው:: አብሮ እየበላ አብሮ እየዋለ ወንድም ወንድሙን የሚገድል፣ ሲያምኑት የሚከዳ፣ እንደ ጭቃ እሾህ እየሳቀ የሚወጋ፣ የሚታመን ወዳጅ መስሎ ከጀርባ የሚያርድ ሰው ይበዛል:: እንዲህ ሲሆንም ስሕተትን በሌላ ስሕተት፣ ውሸትን በሌላ የረቀቀ ውሸት መደበቅ ይበረክታል:: እንዲህ ባለ ጊዜ መተማመንም ይመነምናል:: መተማመን በሌለበትስ እንዴት

ልብ ለልብ ተግባብቶ፣ በአንድ አሳብ ተስማምቶና ተደማምጦ ለጋራ ዐላማ አብሮ መሥራት ይቻላል? ሐቀኝነትን ተመራጭ የሚያደርገው ሁለተኛው ምክንያት ይሄ ነው::

3ኛ. እውነትን ተመራጭ የሚያደርገው በዘላቂነት የሚያዋጣው ከሐሰት ይልቅ ሐቀኝነት በመሆኑም ነው:: ውሸት የሚበረክተው ለጊዜው የሚያዋጣ መስሎ ስለሚታይ ሊሆን ይችላል:: አንድ ሰው ሲዋሽ ውሸት ያዋጣኛል፤ እውነት ዋጋ ያስከፍለኛል ሲል ነው:: መዋሸት በዘላቂነት ያዋጣል ወይ? የሚለውን ግን መመርመር ያስፈልጋል:: ቢያንስ ዋሽቶ ጥሩ እንቅልፍ መተኛት አይቻልም:: አንድ ቀን እውነቱ ቢታወቅ በሚል በስጋት መኖርን ያመጣልና:: ሕሊና ይወቅሳል፣ ሕሊና ከእንቅልፍ ይቀሰቅሳል:: ኮሽ ባለ ቁጥር መደንገጥን ያስከትላል:: እንዲህ ዐይነቱ ነገር በተግባርም የሚታይ ነው:: በእርግጥም ወንጀሉ ከተደበቀ ከስንት ዓመታት በኋላ ተቆፍሮ እየወጣ በደለኞች ሲያዙና ሲቀጡ የዓለም ታሪክ በየዘመኑ ያስተምረናል:: በአንጻሩም ተሳስቻለሁና ይቅርታ አድርጉልኝ ማለት የሕሊና እረፍትን ይሰጣል፤ ቀጣዩን ጉዞም ያስተካክላል::

በተለይ ከውሸት ጋር እውነትን ደብለቅ አደርጎና ውሸቱን እውነት አስመስሎ እንዲሁም በሙያ ታግዞ ለጊዜው ማታለል ይቻል ይሆናል:: አሁን አሁን እየተለመደ የመጣውም እንዲህ ዐይነቱ ነገር ነው:: ግማሽ ውሸትን በግማሽ እውነት ጠቅልሎ እውነት አስመስሎ ማቅረብ ተደጋግሞ ከብዙ መሪዎች የሚታይ ክሥተት ነው:: እውነት ያለበት ውሸት እውነት መሆን ባይችልም ለማሳሳት ግን የተመቸ ሊሆን ይችላል:: ውሸት ጊዜያዊ ድል ቢያስገኝም ውሎ ሲያድር ግን እውነት ማሸነፉ አይቀርም:: የኋላ ኋላ እውነት ሲገለጽ የባስ ዋጋ ማስከፈሉ አይቀርምና ለጊዜው ህመም ቢኖረውም ለእውነት መቆም አዋጭ ነው የሚባለውም ይህንን በማሰብም ነው::

በእርግጥ ውሸት ልማድ ሲሆን ሰው ከዕድሜው እንኳ መማር ይሳነዋል:: እንደ ዋሸ መቃብር ይወርዳል:: በእኛ ዘመን እንኳ እንዲህ ዐይነት ስንት ሰዎችን እያየን ነው? ምነው በዚህ ዕድሜያቸው፣ አሁን እንኳ አይማሩም እንዴ? መዋሸቱ አይበቃቸው? ምነው የንስሓ ጊዜ ቢኖራቸው የሚባሉ ሰዎች ስንት ናቸው?

4ኛ. ጮሌነት አይዘልቅም:: የቀጠፉበት ምላስ ተሳስሮ ለባለተራ መዘባበቻ መሆንን ይመጣልም:: "ብልጥ ያለ አንድ ጊዜ አይበልጥ" እንዲሉ ማታለል ቢቻል ለጊዜው ነው እንጂ ዘወትር ሲያታልሉ መኖር እንደማይቻልም የሚታይ እውነት ነው:: ለጊዜው በማታለል የተሳካላቸው ሰዎች ጊዜው ሲደርስ፣ በደላቸው ሲገለጽና እውነቱ ሲታወቅ ለካ እነዚህ ሰዎች እንዲህ ነበሩ እንዴ እያሰኘ እንዴት እንደሚሸማቀቁና ማቅ እንደሚለብሱ ማዬትም እንግዳ ነገር አይደለም:: ለትንሽ ትርፍ መዋሸትን የመረጡ ሁሉ ጊዜው ሲደርስ እጅግ ብዙ ዋጋን ሲከፍሉበት ማዬት የተለመደ ነው:: እንዲህ ዐይነቱ ክስተት ከውሸታቸው ብዛት ከእንግዲህ እንዲህ ዐይነት መሪዎችን ማን ያምናል? ወደፊትም ይቀየራሉ ብለንም አናምንም በሚል በማጭበርበር ሲደግፍ የነበረ ደጋፊን ዐይንህ ለአፈር ሊያሰኝም ይችላል:: ቢዘገይም የውሸት ውጤቱ ይህን የመሰለ ነው::

"ቅኖች ቅንነታቸው ትመራቸዋለች፤ ወስላቶችን ግን ጠማማነታቸው ታጠፋቸዋለች::" ተብሎ እንደተጻፈ በሰፈሩት ቁና መሰፈርም አይቀርም:: (ምሳ 11፥3) አሁን ብናታልል ጊዜው ሲደርስ እኛን የሚያታልል ሰው ይነሣል:: እንዲህ ዐይነት ስንት ገጠመኞችን ማዬት ችለናል? በመጽሐፍ ቅዱስም በዔሳውና ያዕቆብ መካከል የተፈጠረ ታሪክ የሚያረጋግጥልን ይህን እውነት ነው::

ያዕቆብ የብኩርናውን በረከት ከወንድሙ ከዔሳው ለመውሰድ አባቱ ይስሐቅን ማታለልን መረጠ:: አታሎም ለጊዜው ተሳክቶለት በረከቱን ተቀበለ:: ቀጣዩ የያዕቆብ ሕይወት ግን በማንኪያ የወሰደውን በጭልፋ ሲከፍል ነው የሚያሳየን:: አጎቱ ላባ ያዕቆብን አታለለውና ያዕቆብ ለላባ በከንቱ ሰባት ዓመት ተገዛ:: በዚህም አላበቃም፣ ቆየና ደግሞ ያዕቆብ በገዛ ልጆቹ እንደገና ተታለለ:: ልጆቹ የሚወደውን ልጁን ዮሴፍን ወደ ግብፅ አገር በግፍ ሸጠውት ሳለ ቀበሮ በላው ብለው ያዕቆብን አታለሉት:: (ዘፍ 29፥31) ማታለል እንዲህ የባሰ መታለልን ሊያስከትል ይችላል:: ትናንት ሲዋሹ የነበሩ ሰዎች፣ ትናንት ሲያታልሉ የነበሩ ሰዎች ዛሬ የት ነው ያሉት? ሁሉም የጊዜ ጉዳይ ነው::

5ኛ. ውሸትን እስከወዲያኛው መቅበር አለመቻሉም ነው ሐሰተኝነትን አዋጭ የማያደርገው ሌላው ምክንያት:: እውነት አያረጅም፤ ጊዜ ይወስድ ይሆናል እንጂ እውነት ተቀብሮም አይቀርም የሚለው ብዙውን ጊዜ የሚረሳ ይመስላል:: ለዘመናት የተደበቁ ወንጀሎች ጊዜው ሲደርስ መውጣታቸው የተለመደ ጉዳይ ነው:: የማይታወቅ የተከደነ የማይገለጥ የተሰወረ ነገር ያለ ቢመስልም ጊዜው ሲደርስ ታፍኖ የቆየው ሲገለጥ ሽታው ይብስ ይሆናል እንጂ ለዘላለሙ ተከድኖ የሚቀር ነገር አይደለም:: "እንግዲህ አትፍሩአቸው፤ የማይገለጥ የተከደነ፣ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለምና።" መባሉም ለዚህ ነው:: (ማቴ. 10፥26) ሌላው ቢቀር ዘመኑም ለመዋሸት የተመቸ የመሆኑን ያህል ውሸትን ለመደበቅ ግን እንደ ቀደመው ዘመን የሚያስችል አይደለም:: አሁን ጊዜው የቴክኖሎጂ ነው:: በዚህ በዲጂታል ዘመን በድብቅ የተሠራው ሥራ ከየትኛውም አቅጣጫ ፎቶ እንደሚነሳ፤ የተደመበቀ ምስጢር እንዴት ተቆፍሮ እንደሚወጣ ሲታሰብ ውሸት ከትርፉ ኪሳራው የበዛበት ዘመን ነው ያሰኛል::

ውሸትን በሌላ ውሸት መሸፈንም የሐሰተኝነት አስከፊ ገጽታ ነው:: ንጉሥ ዳዊት ለዚህ ጥሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል:: የጦር መኰንኑን የኦርዮን ሚስት ቤርሳቤህን በግፍ ቀምቶ፤ ይህን በደሉን ለመሸፈን ኦርዮን በጦር ግንባር አስገድሎ፤ በደም የጨቀየ እጁን ታጥቦ አገር አማን ብሎ ለመኖር ያደረገው ጥረት በጊዜው መክሸፉ እውነቱም መውጣቱ አልቀረም:: ዳዊትን በመሰለ ንጉሥ ዘንድ እንኳ ውሸትን መቅበር አልተቻለም:: መታሰብ ያለበት እውነቱ ሲገለጥ ምን ያህል ዋጋን ያስከፍላል? የሚለው ነው እንጂ ቢዘገይም እውነት ተቀብሮ እንደማይቀር ይህ የዳዊት ታሪክ ማሳያ ነው:: ስሕተትን አምኖ ይቅርታ ከመጠየቅና ንስሓ ከመግባት ይልቅ ውሸትን በሌላ ውሸት ለመደበቅ መሞከር የሚያስከፍለው ዋጋ የከፋ ሊሆን ይችላል:: ዳዊት ምን ያህል ጊዜ ነው ያዘነው? ምን ያህል ጊዜ ነው ማቅ የለበሰው? የሚወደውን ልጁን በሞት እስኪያጣ ድረስ ቅጣቱ ከባድ ነበርና:: ይህን ሊያስተምረን ነው ታሪኩም መመዝገቡ:: (2ኛ ሳሙ. 11)

6ኛ.አደርባይነት ሲበዛም የሚያስከትለው ጣጣ ዘርፈ ብዙ መሆኑም ነው ሐቀኝነትን ማስፋፋት ተመራጭ የሚያደርገው ጉልበቱ ያለው፣ ገንዘቡ ያለው፣ ሥልጣኑ ያለው ከሐሰተኞች ዘንድ ከሆነ እንግዲህ ምን ማድረግ ይቻላል? ለመኖር ሲባል አብሮ መዋሸት፣ አብሮ ማስመሰል እና መመሳሰል ግድ ነው የሚል ነገር የተለመደ ሆኗል:: በእርግጥም እንዲህ ዐይነቱ ነገር ቀላል መልስ የሚገኝለት አይደለም:: ዓለምን አስቸጋሪ ከሚያደርጋት አንዱ ምክንያት ይሄው ነው:: ክፉ ሲሠራ እያዩ፣ በደል እያዩና እየሰሙ ስለ እውነት መናገር፣ ስለ እውነት መመስከር፣ ስለ እውነት መቆም የሚያስፈራበት ጊዜ ብዙ ሊሆን ይችላል:: ለጥቅም ሲባል ራስን መሸጥ ግን ሌላ ነገር ነው::

አደርባይነትም ባህል የሚሆነው እንዲህ ባለው ሁኔታ ነው:: አደርባይነት ሲበዛ ሳይጠሩ አቤት ሳይላኩ ወዴት የሚሉ ሰዎች በሚበዙበት ጊዜ ሐሰተኛ በዝቶ እውነት ሊቀበር ይደርሳል:: አደርባይነት ሲበዛ ከፍርሃት የተነሣ መሪዎችን የሚገስጽ የእውነት ሰው ይጠፋል:: እውነት መናገር አስፈሪ በሚሆንበት ሁኔታ አስመስሎ መኖር፣ ተመሳስሎ መኖር ነው የሚበዛው:: መሪዎችም በዙሪያቸው የሚሰበስቡት ስሕተታቸውን የሚነግራቸውን ሳይሆን መስማት የሚፈልጉትን የሚያስተጋባላቸውን ይሆናል:: መሪ ሲሳሳት ተሳሳትህ ከማለት ይልቅ መሪ ገደል እስከሚገባ "ሕዝቡ እኮ በጣም ይወድሀል ሺህ ዓመት ንገሥልን እያሉ ይጸልዩልሀል" የሚለው በዙሪያው ሲበዛ መሪ አወዳደቁ የከፋም ይሆናል::

አደርባይነትን የሚያሳይ አንድ የቆዬ ታሪክ አለ[12]:: በቀደመ ዘመን የተነገረ ነው:: ነገሩ እንዲህ ነው:: "በዚያ ዘመን ልብስን አጥብቆ የሚወድ አንድ ንጉሥ ነበረ:: ልብስን ከመጠን በላይ ከመውደዱ የተነሣ በየሰዓቱ ልብስ ይቀያይር ነበር:: ንጉሡ ሥራው ሁሉ መሸቀርቀር ነው:: ለተቀረው ንጉሣዊ ሥራ እምብዛም የሚጨነቅ አልነበረም:: ንጉሡ በሚኖርባት ከተማ ከተለያየ አገር በከተማዋ ለመኖር የሚጎርፉ ብዙ እንግዶች ነበሩ:: በዚያን ጊዜ ሁለት ልብስ ሰፊዎች ወደ ከተማዋ መጥተው ይኖሩ ነበር::

[12] The Emperor's New Clothes, Denmark
https://www.pitt.edu/~dash/type1620.html#andersen

ሲኖሩም ይህን የንጉሡን ቅጥ ያጣ የልብስ ፍቅር ይሰማሉ::

በዚህም አንድ ዘዴን ዘየዱ:: ለንጉሡ የሚቀርቡ ሰዎችን ፈልገው ልዩ የልብስ መስፋት ችሎታ እንዳላቸውና እነርሱ የሚሰፉት ልብስም በመልኩም ሆነ በአሰፋፉ የተለየ ጥበብ የሚታይበት፣ ልብሱንም ለማየት ብቃት እንደሚጠይቅ ይናገራሉ:: ይህንን አዲሱን ልብስ ማየት የሚችል ማንኛውም ሰው ሁለት ነገሮችን ማሟላት ይጠበቅበታል አሉ:: አንደኛው በሥልጣን ላይ ያለ ሰው ከሆነ ለያዘው ሓላፊነት ብቁ የሆነ እንደሆነ ሲሆን ሌላው ደግሞ ኃጢአት የሌለበት ሲሆን ይገባዋል አሉ:: ንጉሡም ይህን ሲሰማ እጅግ ተደሰተ:: በመንግሥቱ ለሓላፊነት የማይበቃውን ባለሥልጣን ሁሉ ለማየት ጓጓ:: ሕዝቡም እንዲሁ ከጎረቤቱ ኃጢአት የበዛበትን ሰው ለማየት:: ንጉሡም ለልብስ ሰፊዎቹ የሚያስፈልጋቸውን ሰጠና ሥራው እንዲፋጠን አዘዘ:: ሰፊዎቹም ገንዘብና ቁሳቁስን ተቀብለው ወደ መሥሪያ ቦታቸው በቶሎ ሄዱና ሥራቸውን እንደጀመሩ ያስመስሉ ጀመር:: በየቀኑ ይቀዳሉ፤ ይሰፋሉ፤ ስለ ዲዛይኑ ይከራከራሉ:: ይህንም ሁሉ ጎረቤት ይሰማል:: ንጉሡም ከመጓጓት የተነሣ የልብሱን ሁኔታና የደረሱበትን ያይ ዘንድ ከባለሟሎቹ አንዱን መላክ አሰበና ማንን እንደሚልክ ተጨነቀ:: ከመካከላቸውም በችሎታው የላቀውንና ታማኝ የሚባለውን ባለሟል መርጦ ላከው::

ባለሟሉም እንደደረሰ ያጋጠመው ያልጠበቀው ነገር ነበር:: ዐይኑን ማመን አቃተው:: ምንም የሚታይ የለም:: ሰፊዎቹ ግን ያጣድፉት ጀመር:: እንዴት ነው ዲዛይኑ? እንዴት ነው ቀለሙ? ወደዱት ወይ? እያሉ ባለሟሉን ይጠይቃሉ:: ባለሟሉ የሚመልሰውን አጣ:: የሚታይ የለም እንዳይል የተከበረ ባለሟል ነው:: እንዴት ለሓላፊነት የማይመጥን ይሰኝ:: አየሁ እንዳይል የሚታይ ምንም ነገር የለ:: ከትንሽ ቆይታ በኋላ ትንሽ አሰብ አደረገና አድናቆቱን መግለጽ ጀመረ:: ግሩም ዲዛይን፤ ግሩም ቀለም፤ ግሩም አሠራር እጹብ ድንቅ ልብስ ነው አለ! ለንጉሡም ይህንኑ ምስክርነት ሰጠ:: የንጉሡም ጉጉት ጨመረ:: ሌላ ባለሟልም ተልኮ እንዲሁ አድናቆቱን መሰከረ:: እንዲህ እያለ ለንጉሥ ልብሱን የሚያስረክቡበት ቀን ደረሰ::

ንጉሡ ግን ለማመን የማይቻል ዱብ እዳ ሆነበት:: በድንጋጤ ተዋጠ:: ዐይኔ ነው? አለ:: እኔም ለንጉሥነት የማልመጥን ነኝ? ሲል እራሱን ጠየቀ:: እንደገና ለራሱ መልስ ሰጠ:: አይሆንም ይህ ሊሆን አይችልም ሲል ለባለሟሎቹ የታየ ልብስ እንዴት ለሱ ሊታይ እንዳልቻለ ግራ ተጋባ:: ምንም ቢሆን ግን እጅ መስጠት አይገባም ብሎ አሰበና እርሱም ልብሱን ማድነቅ ጀመረ:: ያጀቡት ባለሟሎች ሁሉ አድናቆታቸውን ገለጹ:: "ንጉሥ ሺህ ዓመት ይንገሥ" አሉ:: ባለሟሎችም ሕዝብ ይጠራና ንጉሡ ለሕዝብ በአደባባይ ይህን ድንቅ ልብስ ያሳይ አሉ:: ንጉሡም ባይጥመውም ተስማማ:: አልባሾቹም ኩቱን አምጣ፣ አሁን ደግሞ ሱሪውን፣ አሁን ካፖርቱን ደርብ እያሉ የሚለበስ ባይኖርም ንጉሥን አለበሱትና አደባባይ ወጡ:: ለተሰበሰበው ሕዝብ ንጉሡ ልብሱን ለማሳየት ይንጎራደድ ነበር:: ተሰብሳቢውም ልብሱን አያደነቀ ደስታውን እና እልልታውን ያቀልጠው ጀመር:: የሚታይ ግን ምንም ነገር የለም:: ከሕዝቡ መካከል ግን ይህን በድፈረት ማን ይናገር? ኃጢአተኛ ተብሎ መወገዝን ስለሚያመጣ አደጋ አለው:: በዚህ መካከል አንድ ልጃገረድ አባቷን ተከትላ አደባባይ ሄዳ ነበርና "ግን እኮ ምንም የሚታይ ልብስ የለም፤ ንጉሡ ራቁታቸውን ናቸው" አለች:: አባት እያወቀም ቢሆን ልጁን ሊገስጻት ሞከረ:: ልጃገረዲቱ ግን አብዝታ ጮኸች:: ከጎን ያሉ ሰዎችም ሰሙ:: አንዱ ለሌላው "ልጅቷ ያለችው ልክ ነው" እያለ ሲያንሾካሹክ ሁሉም ጋር እንደተዳረሰ ሁሉም በአንድነት ጮሁና "ንጉሡ እርቃናቸውን ናቸው" አሉ:: ንጉሡም ያን ጊዜ በብርድ ይንቀጠቀጥ ጀመር:: "እውነት ነው" አለ፣ ከዚህ መካከል አንድ ሰው ብቻ እውነት የሚናገር በመገኘቱ እየተደነቀ! አደርባይነት ሲባዛ እንዲሁ ይሆናል::

በአጠቃላይ የእውነት መንገድ ጠባብ ቢሆንም መንገዱን ለማስፋትና የሚሄዱበትንም ሰዎች ለማብዛት ዘርፈ ብዙ ሥራ ጠያቂ ነው:: የጠባይ እና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት በሃይማኖት ተቋማት፣ በሲቪክ ተቋማት፣ በትምህርት ቤቶችና በቤተሰብ ገና ከለጋነት ዕድሜ ጀምሮ ሥራ ቢጀመር ልጆች ሲያድጉ ፍሬውም የሚያምር ይሆናል:: በየተቋማቱ

ሐቀኝነትን የሚያበረታታ ወይስ መዋሸትን እና ማስመሰልን የሚያበረታታ ሁኔታ ነው የሚበዛው? የሚለውን መፈተሽ እስካልተቻለም ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ከባድ ነው የሚሆነው:: የሐቀኝነት እሴትን በየተቋማቱ ትኩረት ሰጥቶ ማጎልበትና የጎድለውን ማሟላትም መፍትሔ ሊሆን ይችላል::

በተመሳሳይ የሚተማመንና የተረጋጋ ማኅበረሰብን መገንባት የሚቻለው በየዘርፉ ያሉ መሪዎች ሁሉም የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ማድረግ ሲችሉ ነው:: ማኅበረሰቡ ባለው ማኅበራዊ መስተጋብር የሐሰት መስካሪዎችን ሲገስጽ፣ የሃይማኖት ተቋማት እንዲህ ባሉ ችግሮች ዙሪያ ዘለቄታ ባለው መልክ ለመቀየር ጥረት ሲያደርጉ ለውጥ ሊመጣ ይችላል:: ሐቀኝነት ሥር እንዲሰድ ሐሰተኝነትን የማያበረታታ፣ መዋሸትንና የሐሰት ምስክርን የሚጸየፍ ማኅበረሰብን መገንባት ያስፈልጋል::

መሪዎች ሐቀኞች ሲሆኑም ከታች ያለው ሹምም እነሱን ይከተላል:: መሪዎች ሐቀኞች ሲሆኑ ሕዝብም እነርሱን አርአያ ያደርጋል:: ከዚህ ሁሉ ጋር ግን ሐቀኝነትን እና ታማኝነትን የሚያጎለበት ተቋማዊ አሠራር መተኪያ የሌለው ነው:: ለምሳሌ ከሥነ ምግባር ደንብ የተላለፉ ሰዎችን ከሚከታተሉና ከሚጠይቁ ተቋማት በተጨማሪ ሐሰት የሚጋለጥበት፣ ያላግባብ ሥልጣንን መጠቀም በሚታይበት ጊዜ እንዲህ ዐይነቱን ሥራ ሹክ የሚባልበት ተቋምና ሥርዓት ቢኖር ውጤታማ መሆን ይችላል:: ተቋማዊ ሥርዓት በጎለበተባቸው አገሮች ጡርንባ ነፊዎች (whistle Blowers) የሚባል አለ:: አገራዊ ጥቅም አደጋ ወድቋል፣ የአገር ጸጥታን ሊጎዳ ይችላል ወይም ባለሥልጣን ለግል ጥቅሙ ያላግባብ ሥልጣኑን ተጠቅሟል ሲባል እንዲህ ዐይነት ሰዎች ነገሩን ለገለልተኛ ተቋማት ሹክ ስለሚሉ እንዲህ ባለው አሠራር ሐቀኝነት ይስፋፋል::

2.3.3 እንዴት ሐቀኛ መሆን ይቻላል?

ምርጫዎች በአብዛኛው በመስቀለኛ መንገድ የተሞሉና ፈታኝ በሆነበት ሁኔታ መሪ ምን ያህል ሐቀኛ ሊሆን ይችላል? የሚለው በተደጋጋሚ የሚነሣ ጥያቄ ነው:: በእርግጥ እውነትን መከተል በተግባር ቀላል የማይሆንባቸው ምክንያቶች አሉ:: የእውነት መንገድ ጠባብ የሚጓዙባትም ሰዎች ጥቂቶች ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱስም የየእለት ኑራችን የሚያስተምረን ይህንን ነው:: በሰፊው ጎዳና ሳይሆን በጠባቡ መንገድ መጓዝ፣ ከሰፊው ጠባቡን መምረጥ መቻል ነው ፈተናው::

በሚመች ጊዜ አለመዋሸት ቀላል ነው:: እውነትን መናገር በማይቻልበት ሁኔታ እውነትን መመስከር መቻል ነው ትልቁ ቁም ነገር:: ሲመች የእውነት ሰው ሳይመች ከውሸት ጋር መሰለፍ እንዲህ ዐይነቱ ነገር የሚከብድ አይደለም:: ፈተና የሚመጣው እውነትና ሐሰት ምርጫ ሆነው በሚቀርቡበት ሰዓት ነው:: "የቀረው ይቅር እንጂ አልዋሸም፤ እውነት ተናግሬ የሚመጣውን እቀበላለሁ" ማለት በእውነት ጸንተው ለሚቆሙ ሰዎች ብቻ የሚቻል ነው::

ሐሰተኛ በበዛበት እውነትን መያዝ ዋጋ ማስከፈሉ ስለማይቀር ነው እውነትን መያዝ ከባድ የሚያደርገው:: እውነት መናገር፣ ለእውነት መኖር እንደ እኛ ባለ አገር ብዙ ዋጋ ያስከፍላልም:: ከሥራ መባረርን ያመጣል፤ ያሳሥራል፤ ያስገድላል፤ ልጆች ይራባሉ፤ ቤተሰብ ይበተናል፤ ሰዎች በፍርሃት ይርቃሉ፤ ብቸኛ ሊያደርግ ይችላል፤ ያሰድዳል፤ በፍርሃት ተሸማቆ መኖርም ግድ ሊሆን ይችላል:: ሐሰተኛ በበዛበት ሁኔታ እውነት የያዘ ሰው እንደ ሞኝ፣ እንዳላዋቂ አንዳንዱም እንደ ወፈፌ የሚቆጠርበት ጊዜም ይኖራል::

ትንሾች ስለ እውነት ቢጮሁ የሚበልጠው ሐሰተኛ ከሆነ ሰሚስ ከወዴት ይገኛል? የሚሰማው የበለጠ የሚጮኸው ድምፅ ነውና:: እውነት ሳይሆን ጉልበት አሸናፊ በሚሆንበት፣ የደቦ ፍርድ በሚያይልበት ሁኔታ እውነት የያዙ ሰዎች ስለ እውነት እንናገር ቢሉስ ማን ያናግራቸዋል? ስለ እውነት እንመስክር ቢባል ማን ይፈቅዳል? "እውነትን ተናግሮ ከመሸበት

ማደር" እንደሚባለው የሚመጣውን ሁሉ በጸጋ ለመቀበል ካልተዘጋጁ በቀር ሐሰተኛ በሚበዛበት፣ ብዙ ሰው ከሐሰት ጋር በሚሰለፍበት ዓለም ከእውነት ጋር መሰለፍ ብዙ መሥዋዕትነትን መጠየቁ አይቀሬ ነው።

ለጥቅም ብዬ ራሴን አልሸጥም፤ ለሐሰተኞች አልሰግድም፤ ለሌቦች አላጎበድድም፤ በሌብነት ከተዘረፈ ገንዘብ አልካፈልም፤ በሐሰት ከሚገኝ ጊዜያዊ ጥቅም እውነትን አስቀድማለሁ የሚል ሰው ቁጥሩ አናሳ የሚሆነውም ከዚህ የተነሣ ሊሆን ይችላል። በእርግጥ ቁጥራቸው ምናልባት ጥቂት ሊሆን ይችላል እንጂ ለእውነት ብዙ ዋጋ የከፈሉ፣ ለእውነት የሞቱ፣ ለእውነት የተሰደዱ፣ ለእውነት ከሥራቸው የተባረሩ፣ ለእውነት ቤተሰባቸው የተበተነባቸው፣ ለእውነት በእስር የማቀቁ፣ ለእውነት አካላቸው የጎደሉ ጀግኖች ዛሬም ቢሆን አይጠፉም።

በአጠቃላይ ለእውነት መቆም ዋጋን ማስከፈሉ ብዙም የሚያከራክር ላይሆን ይችላል። ለጊዜው ዋጋ ቢያስከፍልም የማታ የማታ እውነት ማሸነፏ ግን አይቀሬ ነው። እውነት የኋላ ኋላ ማሸነፏ አይቀርምና ለእውነት መቆም ለጊዜው ዋጋ ቢያስከፍልም በፍጻሜው ያለ ፍሬ አይቀርም። ቢዘገይም የማይረሳና የማይጠፋ ክብርን ማጎናጸፉም ከታሪክ መማር ይቻላል። ሐቀኝነትን ተመራጭ የሚያደርገው ይህንን እያሰቡም ነው። በቅዱስ መጽሐፍ የነቢዩ ዳንኤል ታሪክ ይህን እውነት ነው የሚያሳዬው። በትንቢተ ዳንኤል እንደተመዘገበው ዳንኤል ለእውነት በመቆሙ፣ በሚያምንበትም በመጽናቱ፣ በታታሪነቱና በስኬቱ በዙሪያው ያሉ ሰዎች ቅንዓት ተነሣሥተው በሐሰት ከሰሱት። የተራቡ አንበሶች ወዳሉበት ጉድጓድም በግፍ እንዲጣል አደረጉት። ዳንኤል ግን መከራውን ተሳቆ እውነትን አልካደም። ቢዘገይም በጽናቱም ማሸነፉም የግድ ሆነ። የእውነት አምላክ እግዚአብሔርም ከተራቡ አንበሶች አፍ አዳነው፤ ከመከራም ሰወረው።

ለእውነት መቆም ምን ማለት መሆኑን አጉልቶ የሚያሳይ ሌላም ታሪክ አለ። በመጽሐፈ አስቴር እንደተመዘገበው አስቴር ወገኖቿ በባርነት በስደት ባሉበት አገር ንግሥትነትን የታደለች ሴት ነበረች። ሀማ በተባለ ክፉ ሰው ከሳሽነት በሐሰት ክስ እልቂት በአይሁድ ላይ በታወጀ ጊዜ

ንግሥት እንደመሆኗ ወደ ንጉሡ ለመግባትና እውነቱን ለማስረዳት የሚቻላት ወገኖቿንም ከእልቂት ለማዳን እድል የነበራት አንድ ሰው አስቴር ብቻ ነበረች:: ይህን ማድረግ ግን ለአስቴር ዋጋን ሊያስከፍል ይችላል:: ያለፈቃድ በንጉሡ ፊት መቆምና ስለ እውነት መናገር እጅግ ከባድ ነበርና::

አስቴር ግን ከራሷ ወገኖቿን የምታስቀድም፣ ስለ ብዙዎች ደኅንነት መሥዋዕትነትን ለመቀበል እንኳ የቆረጠች ጀግና ሴት ነበረች:: "አንተ ደግሞ እርሱን እንዳትመስል ለሰነፍ እንደ ስንፍናው አትመልስለት:: ለራሱ ጠቢብ የሆነ እንዳይመስለው ለሰነፍ እንደ ስንፍናው መልስለት::" እንዲል ክፉ ሰው ክፋቱ ካልታወቀበት ክፋት ያበዛልና በሐማ ላይ እውነትን መመስከር እንደሚገባት አመነች:: (ምሳ. 26፥45) አላየሁም አልሰማሁም አይመለከተኝም ማለት ሲቻላት፣ ኑሮዬ ይበልጥብኛል ማለት ሲቻላት "ብጠፋም ልጥፋ" በማለት ለወገኖቿ ክብሯን በውርደት ሕይወቷን በሞት ለወጠች:: (መጽ.አስ. 4፥16) ፍትሕን የሚወድ ሰው ካልሆነ በቀር እውነቱ ወጥቶ የወገኖቹን ነፍስ መታደግ ከቻልኩ ብጠፋም ልጥፋ ብሎ መወሰን በዚያ ሁኔታ እጅግ ከባድ ነው:: አስቴር ግን አደረገችው:: በአንድ ሰው ድፍረትም እውነት ታወቀ ሴራ አድራጊውም ንጹሑም ተለየ:: በአንድ ሰው ድፍረት ሴራ አድራጊዎች በቆፈረሩት ጉድጓድ ሊገቡ ቻሉ:: "ጉድጓድ ስትቆፍር አታርቀው ማን እንደሚገባበት አይታወቅምና " የተባለው በሐማ ደርሶ ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው ገመድ እርሱ እንዲሰቀልበት ሆነ:: "ሰው ማለት ሰው የጠፋ ዕለት ሰው ሆኖ የተገኘ ነው" የሚባለው በተግባር የታዬበትም ነው ይህ የንግሥቲቷ የአስቴር ታሪክ::

ምዕራፍ ሦስት

ፍትሐዊነት

3. ፍትሐዊነት ምን ማለት ነው?

ፍትሕ የሚለው እሳቤ በፍልስፍናውም በፖለቲካው በሌላውም ዘርፍ ብዙ የተባለለት፥ ብዙ የተጻፈበት መሆኑ የታወቀ ነው:: ፍትሕ ከቅንነት ጋር የሚያያዝ እንደመሆኑ አሳቡን ከቅንነት አንጻር በቅዱስ መጽሐፍ መነጸርነት ማዬቱም ጠቃሚ ይሆናል::

የአማርኛ መዝገበ ቃላት ፍትሕ የሚለውን ቃል ፍርድ፣ የሚገባ ነገር፣ በጠበኛና በጠበኛ መሐል ነገር መርምሮ በአጥፊው ላይ ፍርድ ብይን ፈርዶ ጥፋቱን ማስታወቅና መቅጣት ማሠር በሚል የሚተረጉመው ሲሆን በዚሁ መዝገበ ቃላት የእንግሊዘኛ ትርጉሙን impartiality, fairness, reasonableness በማለት ያስቀምጠዋል:: የእንግሊዘኛው መዝገበ ቃላት ለፍትህ የሚሰጠው ትርጉም ግን ከዚህም ሰፋ ያለ ነው[13]:: ፍትሐዊነትን እና ቅንነትን የሚያገኛቸው ብዙ ነገር አለ:: ለቅንነት በዚሁ መዝገበ

[13]Justice is the quality of being just; righteousness, equitableness, or moral rightness: to uphold the justice of a cause. Dictionary.com. Justice is the principle or ideal of just dealing or right action, conformity to truth, fact, or reason, the quality of conforming to law https://www.merriam-webster.com/dictionary/justice

ቃላት የተሰጠው አንዱ ትርጉም ፍትሐዊነት የሚል ነውና:: ቅንነት ሲጎድል አድሏዊነት የሚጠበቅ ነው:: ቅንነት በሌለበት ፍትሕን መጠበቅ ከባድ እንደሚሆንም ብዙም የሚያከራክር አይደለም::

ፍትሕ በቃል የሚነገረውን ያህል፣ የሚወራለትን ያህል በተግባር የማይሟላ ጉዳይ ነው:: በዚህ ዓለም ከሚጓደሉ ነገሮች አንዱ ፍትሕ እንደሆነም የሚያከራክር አይደለም:: አድሏዊነትን ባየን ቁጥር "ምን ይደረግ ዓለም ፍትሐዊ አይለችም" የሚል ነገር መናገር የተመለደውም ከዚህ የተነሣ ይሆናል:: መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረንም በስንዴና በእንክርዳድ ወይም በበግና በፍየል የተመሰሉ ደግና ክፉ ሰዎች በአንድነት በሚኖሩበት ዓለም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ፍትሕ በዚህ ዓለም የማይሟላ እንደሆነ ነው:: (ማቴ 13፥29-30) በጎችና ተኩላዎች፣ ስንዴውና እንክርዳዱ ተቀላቅሎ በሚኖርበት ዓለም ከሰው ልጅ ክፋት የተነሣ መጠኑ ያንስ ወይም ይበዛ ይሆናል እንጂ በደል ያልተፈጸመበት ዘመን፣ ኢፍትሐዊነት የሌለበት አገርስ የት ይገኛል?

ፍትሕ በቃል የሚነገርለትን ያህል በተግባር ቀላል አይደለም:: የሕግ የበላይነት ተረጋግጦባቸዋል በሚባሉ አገሮች እንኳ ፍትሕ ተጓደለ በሚል በየጊዜው የሚጮሁት ብዙዎች ናቸው:: ቢሆንም የሕግ የበላይነት ያለባቸው አገሮች ቢያንስ በሕግ የተቀመጠውን የሰው መብት ለሁሉም ለሚሟላት የሚያስችል አሠራር እና በደል ቢኖር እንኳ አቤት የሚባልበት አጥፊውም የሥራውን ዋጋ የሚያገኝበት የተጠያቂነት ሥርዓት ስላለ በእጅጉ የተሻሉ ናቸው ያሰኛል::

የፍትሕ መዛባት በዚች ዓለም የተለመደ ነው:: ድሀና ሀብታም፣ ወፍራም ወገን ያለውና የሌለው፣ በአንድም በሌላም መንገድ ከባለጉልበታሞች ጋር ትስስር ያለውና የሌለው መቼ ነው እኩል እድል አግኝተው፣ እኩል ተዳኝተው የሚያውቁት? በባንክ ብድሩ ወይስ በፍርድ ቤቱ ወይስ በሥራ ቅጥሩ ወይስ በንግዱ? ሥልጣን ያለውና ሥልጣን የሌለው ሰው እኩል የሚዳኝበት እድልም ጠባብ ነው:: የሥልጣን ክፍፍሉ፣ የሀብት ክፍፍሉ፣

ነጻነቱ፣ ዳኝነቱ እና የመሳሰለው ሁሉ እድል ለተጣመመችባቸውና እድል ለሰጠቻቸው ሰዎች በእኩልነት እንደማይገኝም የታወቀ ነው::

ፍትሕ ከሚዛባበት ምክንያት አንዱ ሁሉም ፍትሐዊነት ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን እንደሚመቸው ስለሚተረጉመው ሊሆን ይችላል:: የማደርገው ነገር ትክክል አይደለም፣ የምሠራው ሥራ ኢፍትሐዊ ነው የሚል ሰው እምብዛም አይገኝም:: ፍትሕን የሚረዳበት መንገድ መለያየቱ እንጂ:: ለአንዱ ኢፍትሐዊ የሆነ አሠራር ለሌላው ፍትሐዊ እንደሆነ የሚቆጠርበት ጊዜ ብዙ ነው:: ነገሩን ከራስ ጠባብ ፍላጎት አንጻር ማየት በተንሰራፋበት ባህል፣ የተለመደው ዜሮ ድምር የሚባለው ዐይነት ነው:: አንዱ ሲያገኝ ሌላው የሚያጣበት አሠራር:: ስግብግብነት በሰፈነበት ሁኔታ፣ ዋናው እኔ መጠቀሜ እንጂ ሌላው መጎዳቱ ብዙም የሚያሳስበኝ ጉዳይ አይደለም የሚሉ በበዙበት ስለ ፍትሕ ማሰብ ከባድ ይሆናል:: በዚያ ላይ የሰው አመለካከቱ ዓለምን የሚያይበት መነጸሩ እንደ መልካችን፣ እንደየባህላችን፣ እንደየእምነታቸን የመለያየቱን ያህል ለአንዱ ኢፍትሐዊ የሆነ ነገር ለሌላው ፍትሐዊ ተደርጎ ሊወሰድም ይችላል::

መከፋፈልና ጠባብነት በነገሠበት ሁኔታ አንዱን ወገን በሌላው ላይ አነሣሥቶ ሰውን እያስፈጀ ራሱን ፍትሐዊ እንደሆነ የማሰብ ነገር የሚመጣውም ከዚህ የተነሣ ሊሆን ይችላል:: እንዲህ ላለው ሰው እርሱ ወገኔ ለሚለው ወገን የሚፈለገውን ዐላማ እስካሳካለት ድረስ በሌላው ላይ የሚደርሰው ጉዳት አያሳስበውም:: እንዲህ ላለው ሰው ፍትሕን እያደረገ እንደሆነ ሲሰማው የሚታይበት ጊዜ ብዙ ነው:: ስግብግበንትና ራስ ወዳድነት በሚበዛበት ዓለም ድሀውን እየበዘበዙ በድሀው ጉልበት ሀብት እያከማቹ በድካማቸው ብቻ እንዳገኙት የሚያስቡ ባለጠጎችም በዓለም ላይ ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም:: ባለቸው እድልና ገንዘብ ተጠቅመው በኢፍትሐዊ መንገድ የባንክ ብድር እንደሚያገኙ፣ በኢፍትሐዊ መንገድ የድሀውን ጉልበት እንደሚበዘብዙ፣ በኢፍትሐዊ መንገድ ከሹመኞች ጋር ባላቸው ቀረቤታ ያለው ሁሉ እድል ያላግባብ እንደሚጠቀሙበት ይዘነጉታል::

ቅንነትና ፍትሕ በሌለበት ሁኔታ የትኛው ያዋጣኛል፣ የትኛው ይጠቅመኛል፣ የትኛው አደጋ ያመጣብኛል የሚል ጨዋታ እንጂ እውነቱ የቱ ነው? ትክክለኛው ፍርድ የትኛው ነው? ፍትሐዊው ነገር የትኛው ነው? ብሎ ስለ እውነተኛ ፍርድ ማሰብም ብዙም የተለመደ አይደለም:: ባለሥልጣን ወንጀል ሠርቶ ተጠያቂ ሳይሆን ማየትም እንግዳ ነገር አይደለም:: እነ እገሌ ለፍርድ አይቀርቡም እንዴ? እነ እገሌ በሠሩት በደል ተጠያቂዎች አይሆኑም እንዴ? መቼ ነው ሰው የሠራውን የእጁን ሥራ ተመጣጣኝ ቅጣት ማግኘት የሚችለው? የሚል ጩኸት ብዙውን ጊዜ መልስ የማያገኘው ከዚህ የተነሣ ሊሆን ይችላል:: እኩል የሰረቁ ሰዎች፣ እኩል የበደሉ ሰዎች፣ እኩል ተጠያቂ ሲሆኑ ያየንበት ጊዜ መቼ ነው? የፍትሕ መንጋደድ የተለመደ ሆኗል:: በየዘመኑ ብዙ በደል ይፈጸማል፤ ኃይል የሌላቸው ሰዎች በጉልበተኞች ግፍ ይቀበላሉ:: ሁለተኛው ፍትሕ የሚዛባበት ምክንያት እንዲህ አይነቱ ነገር ሊሆን ይችላል::

ከላይ እንደተጠቀሰው ለአንዱ ኢፍትሐዊ የሆነው ለሌላው ፍትሐዊ እየሆነ፣ አንዱ በጠባቡ የሚያስበው በሰፊው መታሰብ የሚገባው እየሆነ እንጂ ፍትሐዊነትን የማይሰብክ ሃይማኖትስ ከወዴት ይገኛል? ኢፍትሐዊነትን የሚያስተምር የእምነት ተቋምም በዓለም ላይ እስካሁን አልተሰማም:: ለሰብአዊ መብት ቆመናል የሚሉ የዓለም ወገኖችና ተቋማት ሁሉ የሚያስተጋቡት ተመሳሳይ ነው፤ ፍትሐዊነት እንዲኖር:: ይህ ሁሉ ጥረት እየተደረገ በተግባር ያለው ለምን ከዚህ በተቃራኒው ሆነ? ለሚለው ጥያቄ ቀላል መልስ ለማግኘት የሚያስቸገር ነው የሚሆነው::

ለፍትሕ መሟገት ማለት ተቆርቋሪ ለሌላቸው መቆርቆር፣ አፍ ለሌላቸው ሰዎች አፍ መሆን፣ ለተጠቁት መቆም፣ ለተበደሉ ሰዎች ጠበቃ መሆን፣ ግፍና በደልን መቃወም ማለት ነው:: ሰው በቋንቋው፣ በዘሩ፣ በሃይማኖቱ፣ በጾታው በድህነቱ፣ በአካል ጉዳት እና በሌላም ምክንያት አድሎዎና መገፋት እንዳይደርስበት ለመከላከል የሚቻለውን ሁሉ አስተዋጽዖ ማድረግ ማለት ነው ለፍትሕ መቆርቆር ማለት:: ፍትሐዊነት ማለት የእኔ ወገን የእነሱ ወገን ሳይሉ ማንም ይሁን ማንም ያላግባብ በደል ሲደርስ ለተበደለ ወገን ያለ ልዩነት መቆም መቻል ነው::

ፍትሐዊነት ማለት ወገኔ የሚሉትን ተጠቃሚ ለማድረግ ሌላውን ወገኔ አይደለም የሚሉትን መበደል ማለትም አይደለም:: ይህማ ኢፍትሐዊነት ነው:: ለፍትሕ መቆም ማለት የእኔ ወገን የሚሉት ሌሎችን ሲበድል፣ ሌሎችን ሲያሰድድ፣ በሌሎች ላይ በደል ሲያደርግ አላየሁም አልሰማሁም ማለትም አይደለም:: በደል ያደረሱት ወገን ስለሆኑ በደልነቱን የሚያስቀረው የለምና:: ማንም ይሥራው ማንም ኢፍትሐዊ አሠራር ሆነ አካሔድ ኢፍትሐዊነት ነው:: የደረሰው በደል በማንም ይሁን በማን በደል ከበደልነቱ አያልፍም::

3.1 ለፍትሕ መቆም ለምን?

ለፍትሕ መቆርቆርን ምክንያታዊ የሚያደርጉት ነገሮች ብዙ ናቸው:: ድሆች ምድሪቱ ያፈራቸውን ሀብት በእኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ተገድበዋል የሚለው የሚያከራክር አይደለም:: ድሆች እንደ ባለጠጎች እድል ቢኖራቸው አምራች ዜጋና ባለ ጠጋ መሆን ይችሉ ነበር የሚል መከራከሪያ ቢነሣም እውነትነት ይኖረዋል:: የመማር እድል ያላገኙ የድሀ ልጆች እድሉን ቢያገኙ ከመካከላቸው ብዙ ሳይንቲስቶችን ማግኘት ይቻል ነበር ቢባልም እውነትነት አለው:: ይህ ሁሉ ግን ፍትሐዊነት በሚኖርበት ጊዜ ለማየት የሚቻል ነው::

መጽሐፍ ቅዱስም ለፍትሕ ስለ መቆም በሰፊው ይናገራል:: ከምንም አስቀድሞ ከእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ ፍትሐዊነት እንደሆነ የታወቀና በመጽሐፍ ቅዱስም በሰፊው የተነገረ ነው:: "እርሱ አምላክ ነው፤ ሥራውም ፍጹም ነው፤ መንገዱም ሁሉ የቀና ነው፤ የታመነ አምላክ፣ ክፋትም የሌለበት፣ እርሱ እውነተኛና ቅን ነው::" የሚለው ይህን ሐቅ በደንብ ሊያሳይ ይችላል:: (ዘዳ 32፥4፣) እግዚአብሔር ፍትሕ የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ የፍትሕ አምላክ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፍትሕን እንደሚወድም "እኔ እግዚአብሔር ፍርድን የምወድድ ስርቆትንና በደልን የምጠላ ነኝ" ተብሎ ተጽፏል:: (ኢሳ 61፥9)

ይህም በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም የሚታይ ነው። ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ከተናቀ የዓሳ ማጥመድ ሥራ ከመጥራት ጀምሮ፤ ፈሪሳውያን ከኃጢአተኞችና ቀራጮች ጋር ይበላል በሚል እስኪከሱት ድረስ ሴቶችን፣ ድሆችን የተገፉ ወገኖችን በማቅረብ በተግባር አሳይቶናል።

"እስከ መቼ ሐሰትን ትፈርዳላችሁ? እስከ መቼ ለኃጢአተኞች ፊት ታደላላችሁ? ለድሆችና ለድሀ አደጎች ፍረዱ፤ ለችግረኛውና ለምስኪኑ ጽድቅን አድርጉ፤ ብቸኛውንና ችግረኛውን አድኑ፤ ከኃጢአተኞችም እጅ አስጥሉአቸው።" እንደተባለ ሰው የመሆን አንዱ ዐላማም ፍትሕን ማድረግ ነው። (መዝ 81፥2-4) በሌላም ቦታ "መልካም መሥራትን ተማሩ፤ ፍርድን ፈልጉ፤ የተገፋውን አድኑ፤ ለድሀ አደጉ ፍረዱለት ስለ መበለቲቱም ተሟገቱ።" መባሉ ለፍትሕ መቆም ሰው የመሆን አንዱ ዐላማ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። (ኢሳ 1፥17) እግዚአብሔር ከሰው የሚፈልገው ምን እንደሆነ ሲያሳስብም "ሰው ሆይ መልካሙን ነግሮሃል፤ እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን? ተብሎም ተጽፏል። (ሚክ 6፥8)

"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ተናግሮአል። እውነተኛውን ፍርድ ፍረዱ፣ ቸርነትንና ምሕረትን ሁላችሁ ለወንድሞቻችሁ አድርጉ፣ መበለቲቱንና ድሀ አደጉን፣ መጻተኛውንና ችግረኛውን አትበድሉ፣ ከእናንተም ማንም በወንድሙ ላይ ክፉውን ነገር በልቡ አያስብ።" ተብሎ እንደተጻፈም ለፍትሕ መቆም ማለት የተገፋውን ማዳን ለድሀ አደጉ መፍረድ፣ ስለ መበለቲቱም መሟገት፣ ለምስኪኑ ጽድቅ፣ ቅሬታ ቢኖር እንኳ ቸርነትንና ምሕረትን ማድረግ፣ መጤ ተብሎ ቢታሰብ እንኳ መጻተኛውንና ችግረኛውን አለመበደል ማለት ነው። ስለሆነም ለባለ ጉልበታሞች ሳይሆን ዓቅም ለሌላቸው መቆም፣ እውነተኛ ፍርድ መፍረድ፣ ስደተኞችን እና ችገረኞችን መርዳት ከሰው የሚጠበቅ መሆኑን እንገነዘባለን። (ኢሳ 11፥7፣ ዘካ 7፥9፣ መዝ 82፥3) ፍትሕ ማድረግ ለፍትሕ

መቆም ሰው የመሆን አንዱ ዓላማ ነው የሚባለውም ይህንን ሁሉ በማሰብ ነው::

ለፍትሕ መቆም ማለት በቀኝ እጅ ራስን እያጎረሱ የተረፈውን በግራ እጅ ለሌላው ማጉረስ ማለት ግን አይደለም:: በፍትሕ ስም የድሆችን ሀብት ለራስ እያግበሰበሱ ወይም በፍትሕ ስም የራስን የሥልጣን ፍላጎት ለማርካት ራስን ወኪል በማድረግ የሥልጣን መወጣጫ መንገድ መፈለግ፣ ለራስ ማዕረግና ሥልጣን በሞቀ ቤት ሆኖ በፍትሕ ስም የድሀ ልጆችን እሳት መማገድ፣ በፍትሕ ስም ማጭበርበር እንጂ ለፍትሕ መቆም ሊባል የሚችል አይደለም:: ታግለንልሀል ያሉትን ወገናቸውን ሲዘርፉት፣ የበለጠ ሲያሰቃዩት የታዩ መሪዎች ቁጥራቸው ስንት ነው? የሞተው የድሀ ልጅ፣ መሥዋዕት የተቀበለው የድሀ ልጅ፣ ሥልጣኑና ቅንጦቱ ግን የሚደርሳቸው በፍትሕ ስም የሚነግዱት ነጋዴዎችና ከእነርሱ ጋር ተባባሪ የሆነ አሽቃባጮች ናቸው::

ለራስ ጥቅም የሌላውን ቁስል ነካክቶ ሕዝብን ማነሣሣት የሚከብድ አይደለም:: የአዞ ዕንባን እያነቡ ሆድ የባሰውን ማስለቀስም ይቻል ይሆናል:: ያጣኻውን ላስመልስልህ ነው የምደክመው ብሎ ማታለልም የተለመደ ተግባር ነው:: የዋሁን ሕዝብ መጠቀሚያ ማድረግ ግን እንዲያውም የባሰ ኢፍትሐዊነት እንጂ ለእውነት መቆም ሊባል የሚችልበት ምክንያት አይኖረውም::

ለፍትሕ የሚቆረቆሩ ሰዎች ግን እንደሚጠበቀው ቁጥራቸው አናሳ ሊሆን ይችላል:: የሚበዛው እኔን ከደላኝ ምንተዳዬ የሚለው ነውና:: የሚበዛው እኔ ካልተነካሁ ምን አገባኝ የሚለው ነውና:: ይህ ባይሆን እንኳ የሚበዛው ጎመን በጤና የሚለው ሊሆን ይችላል:: ለዚህ አንዱ ምክንያት የሌሎች በደል፣ የሌሎች ልቅሶ፣ የሌሎች ስደት፣ መፈናቀል ችግሩ የሚሰማው የራስን ቤት ሲያንኳኳ በመሆኑ ነው:: እስከዚያ ከማዶ የተነሣው እሳት እዚህኛውም ቤት የሚደርስ መስሎ አይታይም፣ ያልተጠበቀ ነፋስ እስኪያመጣው ድረስ:: አንድ ተረት ማንሣት እዚህ ላይ ተገቢ ይሆናል:: “ሁለት ጓደኛሞች በእግር መንገድ ሲጓዙ መሸባቸውና ዛፍ ተጠግተው እንዳሸለቡ ጅብ መጣባቸው ይባላል:: ጅቡም ከሁለቱ የአንዳኛውን እግር

መዳበስ እንደጀመረ ሰውዬው አውቋል:: ቀስ ብሎ ከታች ወደላይ እግሩን ይበላው ጀመር:: በዚህ ጊዜ ሁለተኛው ሰው ድምፅ ይሰማና ምንድን ነው ነገሩ? ብሎ ባልንጀራውን ቢጠይቀው "አይ ድምፅህን አጥፋ አንድ እግሬን ነው" አለው ይባላል:: በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ ችግሩ የእያንዳንዱን ቤት ካላንኳኳ እኔ ምን ችገረኝ ወይም ጎመን በጤና ማለት ባህል ይሆናል::

በተመሳሳይ በደል በዛብን፣ ነጻነት እንፈልጋለን በማለት ብዙ መሥዋዕትነትን የተቀበሉ ሰዎች ቦታውን ሲይዙት ያን ሁሉ ጩኸት ረስተው እንዴት በዳይ ሊሆኑ ቻሉ? የሚለው ተደጋግሞ የሚነሣ ጥያቄ ነው:: ብዙ ነው እንዲህ ዐይነት ነገር የሚያጋጥምበት ጊዜ:: በመጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ዐይነቱ ታሪክ ታይቷል:: "አሁንም እነሆ የእሥራኤል ልጆች ጩኸት ወደ እኔ ወጣ፤ ግብፃውያንም የሚያደርጉባቸውን ግፍ ደግሞ አየሁ::" በማለት እግዚአብሔር ነጻ ያወጣቸው ሰዎች በተራቸው ሌሎችን ሲበድሉ እንደነበርና በዚህም እግዚአብሔር እንዳዘነባቸው ተጽፏል:: "መበለቶችም ቅሚያቸው እንዲሆኑ፣ ድሀ አደጎችንም ብዝበዛቸው እንዲያደርጉ፣ የድሀውን ፍርድ ያጣምሙ ዘንድ፣ የችግረኛውንም ሕዝቤን ፍርድ ያጐድሉ ዘንድ የግፍን ትእዛዛት ለሚያዝዙ፣ ክፉንም ጽሕፈት ለሚጽፉ ወዮላቸው!" የሚል ማስጠንቀቂያ ተጽፎ ይገኛል:: (ኢሳ 10፥1-3) በአንድ ወቅት ስድተኛ የነበሩ አሁን ደግሞ ባላገር የሆኑ ሰዎች ባለርስት ሲሆኑ የቀደመውን ስደተኛነታቸውን ረስተው ሌሎችን በአግባቡ መያዝ ስላልቻሉ የተጻፈ መሆኑን የምንረዳበት ትእዛዝና ማስጠንቀቂያ ነው::

ሌላው ቢቀር ፍትሕና እውነት በሚጠብቅባቸው አንዳንድ የሃይማኖት ተቋማት እንኳ የሚሰማው መማረርና ልቅሶም ከሌሎቹ ተቋማት ቢከፋ እንጂ የተሻለ እንዳልሆነ ነው የሚታየው:: ለምን? ቢባል በዋናነት ማማኘት የሚቻለው መልስ በስም እንጂ በተግባር ለእውነት የቆመ የእውነት ሰው ቁጥሩ አናሳ በመሆኑ ነው የሚል ይሆናል:: አብዛኛው ሕዝብ ሃይማኖተኛ በሚባልበት አገር ምን ቢሆን ነው እንዲህ ለፍትሕ የሚቆም፣ ለፍትሕ የሚያደላ ቁጥሩ አናሳ የሚሆነው? ይህን ያህል የፍትሕ እጦት የሚታየው? የሚለውም በተመሳሳይ ለፍትሕ የሚቆሙ

ከጊዜያዊ ጥቅም ይልቅ እውነትን የሚያስቀድሙ እውነተኛ የእምነት ሰዎች ቁጥር አናሳ በመሆናቸው እንደሆነ መገመት ይቻላል::

በጥቅሉ ፍትሐዊነትን ማኅበራዊ ፍትሕ፣ እውነተኛ ፍርድ መፍረድ፣ በደልን መቃወም እና አድሏዊነትን ማስቀረት በሚሉ በአራት ጉዳዮች ከፍሎ ማየት ይቻላል::

3.1 ማኅበራዊ ፍትሕ

ምን ያህል በተግባር ተፈጻሚ ይሆናል? የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ የፖለቲካ መሪዎች በተለይ ባለፈው ግማሽ ክፍለ ዘመን ማኅበራዊ ፍትሕን ለማምጣት ትኩረት አድርገው እንደሚታገሉና ዋና ዐላማቸውም ለሁሉም የምትመችና ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩል የሚስተናገድባት ኢትዮጵያን መገንባት መሆኑን ከመናገር አይቦዝኑም:: መሪዎቹ ከሚናገሩት አንጻር ለማኅበራዊ ፍትሕ ምን ያህል የቆሙ ናቸው? ቆምንልህ ለሚሉለት ወገን እንኳ ምን ያህል ፍትሕ ማምጣት ችለዋል? ችግሩንስ በአግባቡ መረዳት ችለዋል ወይ? የሚሉት ግን ብዙ ሊያወያዩ የሚችሉ ነጥቦች ናቸው:: በግለሰብም ይሁን በማኅበር አድሏዊ የሀብት ክፍፍል፣ አድሏዊ የሥልጣን ክፍፍል፣ የተዛባ የማኅበርዊ ግንኙነት፣ ጭቆናና የመሳሰሉ ችግሮች መፍታት በእርግጥም ዘላቂ ሰላምን ለማምጣትና በመተሳሰብና በመፈቃቀር በጋራ አገርን ለማልማት ያለው ጠቀሜታ የሚያከራክር ባለመሆኑ በጉዳዩ አስፈላጊነት የማይስማማ ብዙም አይኖርም:: ትልቁ ልዩነት ይህ የተባለው ፍትሕ በምን መንገድ ነው የሚመጣው? ለእያንዳንዱ ወገን ፍትሕ ማለት ምን ማለት ነው? በሚለው ላይ ነው:: ምናልባትም እንዲህ ባሉ ጉዳዮች መስማማት ባለመቻላቸውና ችግሩን በአግባቡ ተረድተው በመግባባት ሁነኛ መላ ለማምጣት ቅንንቱ ስለሚጎድል እንደሚታየው ችግሩ እየባሰ እንጂ እየተሻለ የሚሄድ አልሆነም::

ማኅበራዊ ፍትሕን ለማምጣት የሚደረገው ጥረት ፍሬ ማፍራት ለምን ተሳነው? የሚለውን በቅን ልቦና መመርመር ቢቻል ወደፊት መሻሻል ሊኖር ይችላል:: መከፋፈል እና ጥላቻ እየተሰበከ ማኅበራዊ ፍትሕን እውን

ማድረግ እንዴት ይቻላል? የሚለውን ደጋግሞ መጠየቅ የሚያስፈልግበት ሰዓት ነው:: ወደፊት ከማየት ይልቅ የበዳይና የተበዳይ ትርክትን እና ያለፈ ቁርሾን እያቀነቀኑ ለውጥ እንዴት ሊመጣ ይችላል? የሚለውንም እንዲሁ:: አንዱ ማኅበረሰብ ከሌላው የሚተሳሰርበትንና አንዱ ማኅበረሰብ ከሌላው ጋር የሚተባበርበትን ሳይሆን እኛ እና እናንተ የሚል መራራቅን የሚያመጣ ሥራ ጎልቶ በሚታይበት ሁኔታ ማኅበራዊ ፍትሕን እንዴት ማስፈን ይቻላል? የነበረውን ችግር መፍታት ቀርቶ ችግሩን የበለጠ እየተባባሰስ አይደለም ወይ? የሚለው ነው አጽንኦት የሚያስፈልገው ጉዳይ:: ይህን ሁሉ በገለልተኛነት ለመመርመር ግን ከሁሉም መሪዎች ቀናነትና አስተዋይነትን ይጠይቃል::

አሁን ዲሞክራሲ አለ በሚባልባቸው አገሮች በየዘመኑ የነበረውን የፍትሕ መዛባት በማስተካከል ለውጥ እንዳመጡ በውጤቱ ማየት ይቻላል:: እንደ አሜሪካ ያሉ አገሮች ዛሬና ከዛሬ ሃምሳ፣ ሰባ ወይም መቶ ዓመት በፊት በማኅበራዊ ፍትሕ ረገድ ያለው ልዩነት የሰማይና የምድር ያህል ርቀት የሚታይበት ነው:: በአውሮጳም ያለው ተመሳሳይ ነው:: በብዙ አገራት ሰፊ የፍትሕ መሻሻል በየጊዜው የታየበት ክፍለ ዘመን መሆኑንም መካድ አይቻልም:: በብዙ አገሮች የማኅበራዊ ዋስትና ማረጋገጥ ተችሏል:: በእነዚህ አገራት አረጋውያን ጧሪ ቀባሪ አያጡም:: መንግሥቶቻቸው ሙሉ ሓላፊነት በመውሰድ ይንከባከቧቸዋል:: ለአካል ጉዳተኞች የሚደረገው እንክብካቤም የሚደንቅ ነው:: ድሆች ይደጎማሉ:: እኩል እድል ያላገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች የተሻለ የትምህርት እድል ይሰጣቸዋል:: ለስደተኞች ሳይቀር የሚቻለውን ሁሉ ድጋፍ ማድረግም በብዙ አገሮች የሚታይ ተግባር ነው:: ይህ ሁሉ ካለፈው ስሕተታቸው መማር በመቻላቸውና እንደ እኛ ወደ ኋላ ሳይሆን ወደፊት በማየታቸው የመጣ ነው ማለት ይቻላል:: የማኅበራዊ አድሎውና ግፉ ከልክ ያለፈ የነበረበት ዘመን ሩቅ አይደለም:: መቶ ዓመት ባልሞላ ጊዜ እንዲህ መለወጥ ከተቻለ እንዲህ ካሉ አገሮች ትምህርት ቀስሞ ወደፊት መገስገስ በተቻለም ነበር::

ለማኅበራዊ ፍትሕ መሟገት በሁሉም ዓለም የተለመደ ነው። ዐላማቸው ለማኅበረሰብ ፍትሕ መመንት የሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎች በየሀገሩ አሉ፤ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ብዙ ናቸው፤ የሃይማኖት ተቋማትም በአብዛኛው ለማኅበረሰብ ፍትሕ ይጮኻሉ። አክቲቪስቶችና ሌሎችም ተግባራቸው የሚያተኩረው እንዲህ ባለው የግለሰብም ይሁን የማኅበረሰብ ፍትሕ ነው።

እንዲያውም በአደጉ አገሮች ማኅበራዊ ፍትሕ ከዚያም ያልፋል። ሸማቹን ማኅበረሰብ ያላግባብ እንዳይበዘበዙት ከመከላከል ጀምሮ ባለጠጎች ትርፋቸውን የሚያገኙት ከማኅበረሰቡ በሚገኝ ሀብት ነውና ከትርፋቸው በከፊል ለማኅበረሰብ ልማት እንዲያውሉ (corporate social responsibility[14]) ግፊት ማድረግ በአደገው ዓለም የተለመደ ነው። ኮርፖሬሽኖችም በፈቃዳቸው የሥራቸው አካል አድርገው ለማኅበረሰብ ዘላቂ ልማትን እንደሚሠሩም የታወቀ ነው። እንዲህ ዐይነት ተግባር በኢትዮጵያ ብዙም ያልተለመደ ቢሆንም ቢሠራበት ግን ለባለ ጠጎችም ለድሆችም ብዙ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ማሰብ ይቻላል።

ኢፍትሐዊነት የሚመጣው ራስ ወዳድ ሰዎች በሚበዙበት ጊዜ ነው። ስግብግብነት በሚበዛበት ጊዜ ባለጠጎች ያለውን ሁሉ እየጠቀለሉት ድሆች የበለጠ እየደኸዩ ሀብት በጥቂቶች እጅ መከማቸቱ የማይቀር ይሆናል። ለእኔ ብቻ የሚለው አስተሳሰብ በሚበዛበት ጊዜ ፍትሕ በገንዘብ እና በሥልጣን ኃይል ከድሆች ይነጠቃል። የድሆቹ ንብረት ያለበቂ ካሳ እየተነጠቀ ለባለ ጊዜ ይሰጣል። በመሆኑም ባለ ሀብቶች ድሀውን እንዳይበድሉ ብቻ ሳይሆን ድሀውን የትርፋቸው ተጋሪ እንዲሆን ማስቻል ዘላቂ ሰላምንና የጋራ ብልጽግናን የሚያመጣ ተግባር ነው በሚል የሚሠራ ነው ሌላኛው የማኅበራዊ ፍትሕ ገጽታ።

[14] Corporate social responsibility (CSR) is a self-regulating business model that helps a company be socially accountable. To engage in CSR means that, in the ordinary course of business, a company is operating in ways that enhance society and the environment, instead of contributing negatively to them. https://www.investopedia.com/terms/c/corp-social-responsibility.asp

በእኛ ዘንድ ከፋም ለማም በአብዛኛው ለማኅበራዊ ፍትሕ ሲንቀሳቀሱ የሚስተዋሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው። ሌላው ቢቀር የሃይማኖት ተቋማት ማኅበራዊ ፍትሕን ለማስፋፋት መንፈሳዊ ግዴታ እንዳለባቸው ምን ያህል ተረድተውታል? የሚለው ነጥብ ጥያቄ የሚያስነሣ ነው። የሃይማኖት ተቋማት ምን ያህል ነው ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉት? ምን ያህል ትኩረት ይሰጡታል? የሚሉ አሳቦች ሲነሡ ነው እየተሠራ ያለውን ሥራ ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባው።

በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ሰው መብቱ ሊረገጥ፣ ሊገፋ፣ ሊገለል፣ ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅምና እድል ጊዜ በሰጣቸው ጉልበተኞች ሊያጣ፣ ሊከለከል ይችላል። "አፍህን ስለ ዲዳው ክፈት፤ ተስፋ ስለሌላቸውም ሁሉ ተፋረድ። አፍህን ክፈት በእውነትም ፍረድ፤ ለድሀና ለምስኪን ፍረድ።" ተብሎ እንደተጻፈ ድምፅ ለሌላቸው ድምፅ፣ ዓቅም ለሌላቸው ዓቅም በመሆን ስለ ፍትሕ መሟገት ተገቢ ነው። (ምሳ. 31፥8-9)

በእርግጥ ለተጠቃው ሳይሆን በአሸናፊው ወገን መሰለፍ፣ ከምስኪኑ ጋር ሳይሆን ከጎይለኛው ጋር መወገን ነው የተለመደው። ነገር ግን ለተገፉት መቆም፣ በደካማው ወገን መሰለፍ ነው ከባዱ። ዲዳ ለሆኑ አፍ መሆን ማለት በደላቸውን ወጥተው መናገር ለማይችሉት፣ በምንም ዐይነት ሚዲያን የማግኘት ዕድል ለተነፈጋቸው፣ ድምጻቸው የሚሰማበትን ዕድል መፍጠር ማለት ነው። በደላቸው ብዙ ሆኖ ሳለ በድህነታቸው ምክንያት ጉዳያቸውን ከምንም የሚቆጥረው በሌለበት ሁኔታ የሌሎች ሰዎች ቁስል ቁስላችን፣ ዕንባቸው ዕንባችን፣ በደላቸው በደላችን በማለት እንዲህ ስላሉ ደካማ ሰዎች መሟገት፣ ድምፅን ማሰማት፣ ጥብቅና መቆም ነው ዲዳ ለሆኑ አፍ መሆን ማለት።

3.2 እውነተኛ ፍርድ መፍረድ

በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ እንዲህ ልቅሶ በበረከተበት ወቅት ምን ያህል ለሙያው የታመነ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው እንዲያም ባይሆን እንኳ ለገዛ ሕሊናው የታመነ ዳኛ ማግኘት ይቻል ይሆን? ስንት ከሙስና

የጸዱ፣ የባለሥልጣናትን ቁጣ ሳይፈሩ ሕግን የሚያስቀድሙና በሕግ ብቻ የሚሠሩ ዳኞችንና ጠበቆችን ማግኘት ተችሏል? ለሚለው ጥያቄ የቁጥሩን ልክ ማግኘት የሚከብድ ቢሆንም በአንድ ወቅት እንዲህ ዐይነት ሰዎችን ማግኘት መርፌን በባትሪ የመፈለግ ያህል ከባድ እንደነበረ ነው የሚነገረው:: ለምን እንዲህ ሆነ? ቢባል ደግሞ ከባለሥልጣን ይልቅ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ከሰው ይልቅ ለሕግ የሚገዛ፣ ተጠያቂነት ባይኖር እንኳ ለሕሊናው የሚታመን፣ ለዘር ለጎሳ ለወዳጅ ዘመድ የማያደላ፣ በገንዘብ እና በሌላ ጥቅም ፍርድን የማያጣምም፣ ፍትሕን በጥቅም የማይለወጥ ሰው ቁጥሩ አናሳ በመሆኑ ነው የሚል መልስ የሚጠበቅ ይሆናል::

ፍርድን ማጣመም፣ አድልዎ ማድረግ ቀላል ሊሆን ይችላል:: እውነተኛ ፍርድን ለመፍረድ ግን ነጻ ሕሊና ያስፈልጋል:: መሪ በተሰጠው ሥልጣን ሀብታምና ድሀን ሳይለይ፣ ባለሥልጣን እና ተርታ ሰው ሳይል፣ ወገኔ እና ጠላቴ ብሎ ሳይከፋፍል፣ ለሰው ፊት ሳያዳላ እውነተኛ ፍርድን ለመፍረድ ቅንነትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ሊኖር ይገባል::

ቅን ዳኛ ከጠፋ ሕግ አላግባብ ጥቅም ላይ የመዋል እድሉም ከፍ ያለ ነው:: ፍትሕ ከሌለ በፍርድ ስም ጉልበተኛ ይፈረድለታል፤ በደካማም ይፈረድበታል:: ፍትሕ በሌለበት ገንዘብ ፍርድን የማጣመም አቅሙ ከፍ ያለ እንደሆነም የታወቀ ነው:: ደግ ዳኛ ከሌለ ድሀን ማን ይሰመዋል? እውነተኛ ዳኛ ከሌለ ሕግ ሳይሆን ገንዘብ ይፈርዳል፤ ሕግ ሳይሆን ሥልጣን ይፈርዳል:: በዚህ ጊዜ አቅመ ደካማ ይበደላል፤ ፍርድ በጉቦና በዝምድና ይሆናል፤ ሀብት በጥቂት ሰዎች እጅ ይከማቻል፤ ድሀ ይጮኻል ያለቅሳልም ግን ሰሚ አያገኝም::

ይህ ሁሉ በደል በፍትሕ ስም ሲፈጸም፣ በሐሰት ምስክር ስንት ንጹሐን ሲፈረድባቸው፣ በመልካም አስተዳደር እጦት ብዙ ሰው ሲያለቅስ ሕግ ስለሌለ ሳይሆን ቅን መሪዎች በመጥፋታቸው እንዲሁም ያለውን ሕግ እንኳ በአግባቡ መተርጎምና ማስፈጸም ባለመቻሉ ለመሆኑ ከውጤቱ መገመት ይቻላል:: የዳኝነት ወንበር ላይ የተቀመጠ ሰው በቅን አስተሳሰብ በበጎ ሕሊና እውነትን የሚያስቀድም፣ ለእውነት የሚያደላ፣ በጥቅም

የማይደለል፣ ሙያውን የሚያከበር ካልሆነ ምንም ያህል የተዋጣለት ሕግ ቢኖርም ፍትሐዊ ሥርዓትን ለማስፈን እንዴት ይቻላል? ፍትሕ በወረቀት የሰፈረ ሕግን ብቻ ሳይሆን ፈሪሃ እግዚአብሔርና ንጹሕ ሕሊና ያለው ዳኛንም ይፈልጋልና:: ሕግ ተርጓሚው ዳኛ ነውና ሕግን ሊያጣምም ሕግን ሊያቃናም ይቻለዋል::

በመጽሐፍ ቅዱስ በሐሰት ክስ፣ በሐሰት ዳኛ፣ በሐሰት ምስክር በፍትሕ ስም የሐሰት ፍርድ መፍረድን የሚያሳዩ ብዙ ታሪኮች አሉ:: በሰውስ ላይ ይሁን አምላክንስ በፍርድ አደባባይ እንዲህ ባለው በሐሰተኛ ክስና በሐሰተኛ ምስክር ሐሰተኛ ፍርድ እንደተፈረደበት ማን ይስተዋል?

ንጹሕ ሕሊና የሌለው ዳኛ በበዛበት አገር፣ ሕግ ብቻውን ብዙም ዋጋ እንደሌለው የታየ እውነት ነው:: ሕጉ ከወረቀት ሊያልፍ አይችልምና:: እንዲያውም በሐሰት ማስረጃ፣ በሐሰት ምስክር፣ በሐሰት ዳኝነት በፍትሕ ስም ፍርድ ሲበደል ማየት የሚያሳዝን ቢሆንም በሕግ ሽፋን የበለጠ ግፍ ሊሠራ ይችላል:: ብዙ ንጹሐን የዕድሜ ልክ እሥራት ሲፈረድባቸው፣ ብዙዎች እስከወዲያኛው ሲሸኙ፣ ብዙዎች ሀብታቸውን በግፍ ሲነጠቁ ይህ ሁሉ የሆነው በፍትሕ ስም ዳኛ ተሰይሞ፣ የፍርድ አንቀጽ ተጠቅሶ ነው:: ይህ ሁሉ የሚሆነው ኢፍትሐዊነት በሚበዛበት ሁኔታ ነው:: በዘመናችን እንኳ እንዲህ ዐይነቱን ነገር ስንቱን አይተናል? "በፍርድ ዓመፃ አታድርጉ፤ ለድሀ አታድላ፤ ባለ ጠጋውንም አታክብር፤ ነገር ግን ለባልንጀራህ በእውነት ፍረድ::" እንደተባለ በፍትሕ ስም ዓመፃ ማድረግ ግን የከፋ በደል ነው:: (ዘሌ. 19፥15)

አስመሳይነትና አጭበርባሪነት በሞላበት የፖለቲካ ባህል አብዛኛው ግፍ አብዛኛው በደል የሚፈጸመው በፍትሕ ስም መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው:: በሐሰት ዳኛ፣ በሐሰት ክስ፣ በሐሰት ሕግ የተፈረደባቸው ሰዎችንም ወኅኒ ቤት ይቁጠራቸው:: "አእምሮ የጐደለው መኰንን ትልቅ ግፈኛ ነው፤ ግፍን የሚጠላ ግን ብዙ ዘመን ይኖራል::" እንዲል ይህ ሁሉ የሚሆነው አእምሮ ሲጎድል ሊሆንም ይችላል:: (ምሳ 28፥5)

በአንጻሩ ማስተዋልና ጥበብ ካልተሰጠ በቀር ፍርድ አስቸጋሪ ነው። ማስተዋልና ጥበብ ካልተሰጠ ሐሰተኛውን እውነተኛ፣ እውነተኛውን ሐሰተኛ ማድረግ ይመጣል። ጥበብና ማስተዋል ካልተሰጠ ሌባውን ንጹሕ፣ ንጹሑን ሌባ ሊባል ይችላል። ጥበብና ማስተዋል ካልተሰጠ ወንጀለኛውን ጻድቅ ጻድቁን ወንጀለኛ ለማለት ቀላል ይሆናል። እንዲህ ዐይነት ፍርድ በየጊዜው ማጋጠሙ የተለመደ ነው። ባልሠሩት ባልፈጸሙት ወንጀል ለእስር የሚዳረጉ፣ በሞት የተቀጡ፣ ከብዙ ዓመታት እስር በኋላ ነጻ ተብለው የሚለቀቁ ዕውቀትና ሥልጣኔ አለበት በሚባልባቸው አገሮች ሳይቀር የትየለሌ ናቸው። በዚህ የሰው ተንኮል በረቀቀበት ውስብስብ ዓለም እውነቱን ከሐሰት፣ የሚጠቅመውን ከማይጠቅመው ለይቶ ለመወሰን የማስተዋልና የመመርመር ጥበብ ከላይ ካልተሰጠ በሥጋዊ ጥበብ ብቻ የሚቻል አይደለም። ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸው መሪዎች ታሪክ የሚያስተምረን ይህንን ነው።

ጥበብ የተሰጠው ንጉሥ ሰሎሞን አስቸጋሪ ፍርድን በጥበብ እንዴት እንደፈታ የሚያሳይ ታሪክ እንዲህ ይላል። "በአንድ ቤት የሚኖሩ ሁለት ሴቶች በሦስት ቀን ልዩነት ልጆች ወለዱና የአንደኛዋ በድንገት ሲሞትባት የሌላዋን ልጅ የእኔ ነው በማለቷ ይህን አስቸጋሪ ፍርድ ይዘው ንጉሥ ሰሎሞን ዘንድ ቀረቡ። እንዲህ ዐይነት ፍርድ አስቸጋሪ ነው። ንጉሡ ሰሎሞንም ሰይፍ አምጡልኝ አለ። ሰይፍም ይዘው ወደ ንጉሡ ፊት መጡ። ንጉሡም ደኅነኛውን ሕፃን ለሁለት ከፍላችሁ ለአንዲቱ አንዱን ክፍል ለሁለተኛይቱም ሁለተኛውን ክፍል ስጡ አለ። የደኅነኛውም ሕፃን እናት አንጀትዋ ስለ ልጅዋ ናፍቆአልና ጌታዬ ሆይ ደኅነኛውን ለእርስዋ ስጣት እንጂ አትግደል ብላ ለንጉሡ ተናገረች። ያችኛይቱ ግን ይከፈል እንጂ ለእኔም ለአንቺም አይሁን አለች። ንጉሡም መልሶ ይህችኛይቱ እናቱ ናትና ደኅነኛውን ሕፃን ለእርስዋ ስጡአት እንጂ አትግደሉት አለ። ንጉሡም የፈረደውን ፍርድ እሥራኤል ሁሉ ሰሙ፤ ፍርድን ለማድረግ የእግዚአብሔር ጥበብ እንደ ነበረበት አይተዋልና ንጉሡን ፈሩ።" የሚል ታሪክ ተመዝግቦ እናገኛለን። (1ኛነገ. 3፥16-28) ጥበብ ሲገኝ እንዲህ ማስተዋል ይገኛል። ጥበብ ከላይ ከተገኘም ለፍርድ መጠንቀቅ፣ የተሰውረውን ረቂቁንና አስቸጋሪውን ፍርድ መመርመር ይቻላል።

እግዚአብሔርን በመፍራት የሚገኝ ጥበብ ትክክሉን ከሐሰቱ ለመለየት ያስችላል:: ጥበብ ከእግዚአብሔር ሲሰጥ መፈራትና ሞገስንም ያስገኛል::

እንዲህ ዐይነቱን ጥበብ ንጉሥ ሰሎሞን እንዴት እንዳገኘው የሚያሳይ ታሪክም ይህንን የሚያሳይ ነው፡፡ ሰሎሞን በነገሠ ጊዜ እግዚአብሔር ምን እንድሰጥህ ለምን ሲለው "በሕዝብህ ላይ መፍረድ ይችል ዘንድ፣ መልካሙንና ክፉውንም ይለይ ዘንድ ለባሪያህ አስተዋይ ልቦና ስጠው፤ አለዚያማ በዚህ በታላቅ ሕዝብህ ላይ ይፈርድ ዘንድ ማን ይችላል" ሲል ከልመናው ሁሉ የመምራትን ጥበብ ማስቀደሙን ይናገራል:: ሰሎሞን ባለጠግነትንና ክብርን ዕድሜ ወይም ዝናን ከመጠየቅ ይልቅ የመሪነትን አስቸጋሪነት ተረድቶ ሕዝቡን የሚመራበትን ጥበብና ማስተዋልን አስቀደመ፡፡ በፈሪሃ እግዚአብሔር በሚገኝ ጥበብ መምራት፣ የማይረሳ ታሪክን ሠርቶ ለማለፍ ያስችላል የሚባለውም እንዲህ ዐይነቱን ታሪክ እያሰቡ ነው::

በሕዝብ ላይ መፍረድና ሕዝብን ማስተዳደር እንደ ቀላል ነገር ሲቆጠር ነው ነገር መበላሸት የሚጀምረው:: በኃይል ሥልጣን ላይ መውጣት ስለተቻለ ብቻ ሕዝብን ማስተዳደር፣ በዚህ ታላቅ ሕዝብ ለመፍረድ የሚያስችል ብቃት አለ ማለት አይደለምና::

3.3 በደልን መቃወም

ፍትሐዊ መሆን ከምንም በላይ አስቸጋሪ የሚሆነው ሥልጣን ላይ ሲወጡ ነው ይባላል:: ሥልጣን ሲኖር፣ በሥልጣን ሁሉንም ማድረግ በሚቻልበት ጊዜ፣ አንዱን መሾም ሌላውን መሻር የሚቻልበት እድል በእጅ ሲገባ የሰው ማንነቱ ያን ጊዜ ነው የሚፈተነው:: "ንጉሥ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ" እንደሚባለው ሥልጣን ሲይዙ ያሻን ማድረግ፣ የአይኑ ቀለም ዐላማረኝም ብሎ የፈለጉትን ማሰር፣ የፈለጉትን መግደል በሚቻልበት ሁኔታ ለእውነት መቆምና ሥልጣንን ማክበር ሲቻል ነው የእውነት ሰው መሆኑን የሚያስመሰክረው::

በየዘመኑ በሥልጣን በሰከሩ ሰዎች ብዙ በደል ይፈጸማል። በተለይም ኃይል የሌላቸው ሰዎች በጉልበተኞች ግፍ ይቀበላሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ የተመዘገበ አንድ ታሪክ ይህን የሚያሳይ ነው። በነቢዩ በኤልያስ ዘመን አክዓብ የሚባል ክፉ መሪ ነገሠ። ሚስቱም ኤልዛቤል ከእርሱ የከፋች ነበረች። በዚያ ዘመን ናቡቴ የሚባል ሰው ነበረ። ለናቡቴ በሰማርያ ንጉሥ በአክዓብ ቤት አጠገብ የወይን ቦታ ነበረው። አክዓብም ናቡቴን በቤቱ አቅራቢያ ነውና የአትክልት ቦታ አደርገው ዘንድ የወይን ቦታህን ስጠኝ፣ ስለ እርሱም ከእርሱ የተሻለ የወይን ቦታ እሰጥሃለሁ፣ ወይም ብትወድድ ግምቱን ገንዘብ እሰጥሃለሁ ብሎ ተናገረው። ናቡቴም አክዓብን የአባቶቼን ርስት እሰጥህ ዘንድ እግዚአብሔር ያርቅልኝ አለው።

ናቡቴ የአባቶቼን ርስት አልሰጥህም ብሎ ስለ ተናገረው አክዓብ ተቈጥቶና ተናድዶ ወደ ቤቱ ገባ። በአልጋውም ላይ ተጋድሞ ፊቱን ተሸፋፈነ፤ እንጀራም አልበላም። ሚስቱም ኤልዛቤል ወደ እርሱ መጥታ ልብህ የሚያዝን እንጀራስ የማትበላ ስለምንድር ነው? አለችው። እርሱም ናቡቴን የወይንህን ቦታ በገንዘብ ስጠኝ፣ ወይም ብትወድድ በፋንታው ሌላ የወይን ቦታ እሰጥሃለሁ ብዬ ተናገርሁት፤ እርሱ ግን የወይን ቦታዬን አልሰጥህም ብሎ ስለ መለሰልኝ ነው አላት። ሚስቱም ኤልዛቤል አንተ አሁን የእሥራኤልን መንግሥት ትገዛለህን? ተነሣ እንጀራም ብላ ልብህም ደስ ይበላት፤ የናቡቴን የወይን ቦታ እሰጥሃለሁ አለችው። በአክዓብም ስም ደብዳቤ ጻፈች፤ በማኅተሙም አተመችው። በከተማው ወደ ነበሩትና ከናቡቴም ጋር ወደ ተቀመጡት ሽማግሌዎችና ከበርቴዎች ደብዳቤውን ላከች። በደብዳቤውም ስለ ጾም አዋጅ ንገሩ ናቡቴንም በሕዝቡ ፊት አስቀምጡት፤ ሁለትም ምናምንቴ ሰዎች በፊቱ አስቀምጡና እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሰድቦአል ብለው ይመስክሩበት፤ አውጥታችሁም እስኪሞት ድረስ ውገሩት ብላ ጻፈች። በከተማውም የተቀመጡት የከተማው ሰዎችና ሽማግሌዎች ከበርቴዎችም ኤልዛቤል እንዳዘዘቻቸውና ወደ እነርሱ በተላከው ደብዳቤ እንደ ተጻፈ እንዲሁ አደረጉ። የጾም አዋጅ ነገሩ ናቡቴንም በሕዝቡ ፊት አስቀመጡት። ሁለቱም ምናምንቴ ሰዎች ገብተው በፊቱ ተቀመጡ፤ ምናምንቴዎቹ ሰዎችም በሕዝቡ ፊት ናቡቴ እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሰድቦአል ብለው

በናቡቴ ላይ መሰከሩ። የዚያን ጊዜም ከከተማ አውጥተው እስኪሞት ድረስ ወገሩት። ወደ ኤልዛቤልም ናቡቴ ተወግሮ ሞተ ብለው ላኩ። ኤልዛቤልም ናቡቴ ተወግሮ እንደ ሞተ በሰማች ጊዜ አክዓብን ናቡቴ ሞቶአል እንጂ በሕይወት አይደለምና በገንዘብ ይሰጥህ ዘንድ እንቢ ያለውን የናቡቴን የወይን ቦታ ተነሥተህ ውረስ" አለችው ይላል ታሪኩ። (1ኛነገ. 20)

ክፉ ሰዎች ክፉ ሰውን የበለጠ ክፉ ያደርጉታል ይባላል። እንደ ኤልዛቤል ክፉ መካሪና በሐሰት መስካሪ የሆኑ ምናምንቴ ሰዎች በሚበዙበት የሐሰት ፍርድ ይበረክታል። ናቡቴ የተገደለው በፍርድ ስም ዳኛ ተሰይሞ ነው። በዚያን ጊዜ ከእግዚአብሔር ሰው ከኤልያስ በቀር ለናቡቴ የሚቆምና የሚከራከር ባለመገኘቱም በሐሰት ዳኛ፣ በሐሰት ምስክሮች፣ በሐሰት ፍርድ ናቡቴ ሞት ተፈረደበት። እንዴት እንዲህ ዐይነት ግፍ ይደረጋል ብለው መቃወም የሚገባቸው ሰዎች ሁሉም በሐሰት ሥራ ተባባሪ ነው የሆኑት። በቀል የእኔ ነው ያለ እውነተኛ አምላክ እስኪፈርድ ድረስ ሐሰትም ነገሠ።

እውነተኛ ፍርድ ግን ይዘገይ ይሆናል እንጂ ፈጽሞ አይቀርም። ፍትሕ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነውና። በፈታሒነቱም "እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደ ሆነ በእውነት አስተዋልሁ" ተብሎ እንደተጻፈ ሁሉም ሰው በእርሱ ፊት እኩል ነው። (የሐዋ.ሥ 10፥34) እግዚአብሔር ባለ ጠጋን ስለ ባለ ጠግነቱ አያፍረውም። ኃያልም በእርሱ ዘንድ ከንቱ ነው። የሰውን ፊትን አይቶም አያዳላም። የእግዚአብሔር ፍርድ አድሎዎ የለበትም። ኤልያስም አክዓብን "ናቡቴን ገድለህ ወረስኸውን? በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ለማድረግ ራስህን ሸጠሃልና እነሆ፣ ክፉ ነገር አመጣብሃለሁ። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ስፍራ የአንተን ደም ደግሞ ውሾች ይልሱታል፣ ፈጽሞም እጠርግሃለሁ። ከአክዓብም ወገን በከተማይቱ ውስጥ የሞተውን ውሾች ይበሉታል። በሜዳውም የሞተውን የሰማይ ወፎች ይበሉታል። ኤልዛቤልንም የናቡቴ ቅጥር አጠገብ ውሾች ይበሉአታል" ብሎ ተናገረ።

እግዚአብሔር የተናገረው የግድ ይፈጸማልና እንደተነገረም የሁለቱም አሟሟታቸው የከፋ ሆነ:: በግፍ የቀሙትን መሬት እንኳ ሊጠቀሙበት አልቻሉም:: የሰው ልጅ ለመማር ዳተኛ ሆኖ ስሕተት መድገም ስለሚያበዛ ነው እንጂ ጥጋበኛን ለጊዜው ጥጋብ ዐይኑን ቢያሳውረውም ፍጻሜው እንደ አክዓብና ኤልዛቤል የከፋ መሆኑ አይቀሬ ነው::

በየዘመኑ እንዲህ ዐይነት ታሪክ በሰፊው ተሰምቷል:: ሰዎች በግፍ ንብረታቸውን ሲነጠቁ አልሰጥም በማለታቸው ደግሞ በሐሰት ምስክርና ዳኛ ወህኒ ይወርዱና ይማቅቁ፣ ንግዳቸውንና የንግድ አሳባቸውንም በባለ ጊዜ ይነጠቁ እንደነበር አሁን የአደባባይ ምስጢር ሆኗል:: የፍቅር እስከ መቃብሩ ገጸ ባሕርይ በዛብህ “ዳኛ የለም እንጂ ዳኛማ ቢኖር ዳሩ ዳኛ የለም ልተወው ግዴለም“ እንዳለው ተበድለው ሰሚ አናገኝምና ብንተወው ይሻላል ብለው አልቅሰው የቀረቱንም ቤት ይቁጠራቸው:: እንደ ናቡቴ የአባቶቹን ርስት በገንዘብ አልለውጥም ያሉ የንጉሥን ትእዘዝ እንኳ ሳይፈሩ ከገንዘብ ርስትን ያስቀደሙ፣ እንደ ናቡቴ የሕይወት ዋጋ መክፈላቸው ግን አይቀርም::

እውነትን ለሚያውቅ ሰው ርስት በሆድ አይለወጥም:: የአባቶቹን ርስት ማለት መሬቱን ብቻ ማለት አይደለም:: ትርጉሙ ከዚያ በላይ ነው:: እንደ ናቡቴ ለገባው ሰው ርስት በፍርሃት አይሸጥም:: በርስት ሁሉም ይገኛልና ርስት ከገንዘብ በላይ ትርጉም ያለው ነው::

3.4 እድኪዊነትን ማስቀረት

ፍትሐዊነት ማለት አድኅዊነትን ማስወገድ (fairness, impartial treatment, lack of favoritism toward one side or another) መቻል ማለትም ነው:: አድኅዊነት የሚባለው ሰውን በቋንቋው፣ በዘሩ፣ በሃይማኖቱ፣ በድህነቱ፣ በአስተሳሰቡ፣ በጾታው ወይም በሌላ ምክንያት አንዱን ከሌላው ማስበለጥ፣ እኩል እድል ያላቸውን ሰዎች አንዱን አስበልጦ ሌላውን መግፋት ሲኖር ነው:: ለፍትሕ የሚቆም ሰው ዘር አይመርጥም፤ ጾታ አይመርጥም፤ ቀለም አይመርጥም፤ ቋንቋ አይመርጥም:: ብቻ ለተጠቃው ወገን ይቆማል::

ለእውነት መቆም ማለት እንዲህ ሲሆን ነው:: ጥያቄው ሰውን ሁሉ በእኩልነት አያለሁ ብሎ ከልቡ የሚያምን ስንት ሰው ማግኘት ይቻላል? የሚለው ነው እንጂ ለተበደሉ ሰዎች ለመቆም ሰውን በሰውነቱ መቀበል፤ ሰው የፈጣሪ የእጁ ሥራ ነው፤ ሰው ሁሉ እኩል ነው ብሎ ከልብ ማመን ይበቃል:: የሰውን ፊት አይቶ የማያዳላ፣ ወገኔ ቤተሰቤ ወዳጄ የሚለውን የማያስቀድም፣ ሁሉንም በእኩል የሚያስተናግድ፣ ሌላው ቢቀር ሰውን አለባበሱን አይቶ አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ የማያደርግ ስንት ሰው ይገኝ ይሆን? የሚለው ሲጠየቅ ነው አድሏዊነት ምን ያህል የተንሰራፋ እንደሆነ የሚታወቀው::

ሰው በፖለቲካ ታማኝነቱ ወይም ለገዥዎች በማጎብደዱ ሳይሆን በዜግነት መብቱ በችሎታው ብቻ ተመዝኖ እኩል እድል ማግኘት ሲችል ነው ፍትሕ አለ የሚባለው:: ሰው በቋንቋው፣ በሃይማኖቱ፣ በዘሩ ሳይሆን በሥራ ልምዱና በትምህርት ደረጃው፣ በእውቀቱና በክህሎቱ፣ በአጠቃላይ ብቃቱ ተመዝኖ የሚገባውን ሲያገኝ ፍትሕ አለ ያሰኛል:: ማንን ታውቃለህ ሳይሆን ምን ታውቃለህ የሚባልበት አሠራር ተግባራዊ ሲሆን አድሏዊነት ቦታ አይኖረውም:: በተግባር ያለው ግን ከዚህ የራቀ ነው:: የዚህ ዓለም ነገር ጠባዩ ልዩ ነው:: ምን ታውቃለህ ሳይሆን ማንን ታውቃለህ የሚለው ሥር የሰደደ ባህል ሆኗል:: እከክልኝ ልከክልህ በሚበዛበት ዓለም ከችሎታና ብቃት ታማኝነት ቀዳሚ ሥፋራ ይሰጠዋል:: ሰው በአስተሳሰቡ፣ በሥነ ምግባሩ ሳይሆን በሀብቱ፣ በሥልጣኑና በልብሱ ጥራት የሚከበርበት ዓለም ነው::

ከአድሏዊነት የጸዱ መሆን በተግባር ከባድ ነው:: ምናልባት አንዱ ዘመን ከሌላው ይሻል ይሆናል ወይም አንዱ ከሌላው ይከፋ ይሆናል እንጂ በኢትዮጵያ አድሏዊነት አልታየም የሚባልበት ዘመን በታሪክ እምብዛም ማግኘት አይቻልም:: ይህን ለማየት ግን አድሎ ባደረገው ወገን ሳይሆን አድልዎ በተደረገበት ወገን ሆኖ ማየት ያስፈልጋል:: በደልን የሚያውቀው የደረሰበት እንጂ በደል አድራሹ አይደለም:: በዳይ ነበርሁ ብሎ ማሰብ የሚጠበቅ አይደለም:: አንድን ሕመም በደንብ የሚያውቀው ታማሚው ብቻ ነው::

አድሏዊነት ደምቆ የሚታየው በእኛ ላይ ሲፈጽሙብን እንጂ በሌሎች ሲፈጸም ይደበዝዝና ብዙም አይታይም ይባላልም:: ይህን ለመረዳት ብዙም ርቅት ሄደን ማስረጃ ለማግኘት መድከም አያስፈልገንም:: የእኛኑ ታሪክ ማየት በቂ ነው:: የሥርዓት ለውጥ በአመዛኙ የሚመጣው አድሏዊነት በዛ፤ ፍትሐዊነት ጎደለ፤ የተወሰኑ ወገኖች ተጠቀሙ፤ እኛ ተገልለናል ተገፍተናል፤ አሠራሩ አድሏዊነት አለበት በሚል እንቅስቃሴ ነው:: ጥያቄው እንዲህ በማለት አድሏዊነትን ለማስቀረት ታገልን ያሉ ሰዎች ሥልጣኑን ሲይዙት ምን ሆኑ? የሚለው ነው እንጂ::

አድሏዊነት የማይደረግበት ምን ነገር ነበር? ጨረታ ወይስ የባንክ ብድር? የሥራ እድገት ወይስ የትምህርት እድል? የውጭ ምንዛሬ ወይስ የሥራ እድል? እድገት ወይስ ሹመት? ከዚህ የጸዱ ስንት መሪዎችን፣ ስንት ተቋማትን ማግኘት ይቻል ይሆንስ? ሌላው ቢቀር ፈሪሃ እግዚአብሔር መሠረታቸው ነው የሚባሉ የእምነት ተቋማት ከእንዲህ ዐይነት አድሏዊነት ምን ያህል የጸዱ ናቸው? ዋናው ጥያቄ ግን ችግሩ እየተሻለ ነው ወይስ እየባሰ ሄደ? ካለፈው ስሕተት መማር ተችሏል ወይስ አንድ ዐይነት ስሕተት እየተደጋገመ ነው? የሚለው ነው:: ያም ሆነ ይህ ትልቁ ሊያሳስብ የሚገባው ጉዳይ እንዲህ ካለው ባህል እንዴት መውጣት ይቻላል? የሚለው ነው:: ቢያንስ እንኳ በዚህ በሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ብዙ አገሮች መሻሻል ባሳዩበት የእኛ የቁልቁለት ጉዞ መሆን አልነበረበትም የሚለው ነጥብም የሚያስማማ ነው የሚሆነው::

አድሏዊነትን ለማስቀረት አድሏዊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተስተካከለ አረዳድ መኖሩ አስፈላጊ ነው:: አሁን እያስቸገረ ያለው የእኛ ወገን የእነርሱ ወገን በሚል የዘረኝነት አሳብ እየተስፋፋ ባለበት ሁኔታ የእኛ ወገን የሚለውን እስከጠቀመ ድረስ ሌላው እየተጎዳም ቢሆን እንዲህ ላለው ሰው እየተሠራ ያለው ነገር አድሏዊነት ሆኖ አለመቆጠሩ ነው:: ከዚህ በፊት ተበድለናል እና አሁን የበለጠ መጠቀም አለብን ማለት እንዴት ፍትሐዊ ሊሆን ይችላል? ፍትሐዊ የሚሆነው እኩል ተጠቃሚ እንሁን የሚለው ነውና:: ያለፈውን ለማካካስ ሲሞክር ግን ኢፍትሐዊ መሆኑ አይቀርም::

የችግሩ ምንጭ ፍትሐዊነትን እየተማርንበት የምናድግበት መንገድ ሊሆን ይችላል:: አንድ ሰው ለራሱ ሃይማኖት ተከታዮች አድሎ ካደረገ አድሏዊ ተደርጎ የማያይበት ሁኔታ ሰፊ ነው:: ለቤተሰቡ፣ ለጎሳው ሲያደላ ነውር ሳይሆን ምስጋና የሚያተርፍበት ባሕልም እንዲሁ:: ሰው በተሰጠው ሥልጣንና የሥራ ሓላፊነት ወገንተኛ እንዳይሆን፣ በሕጉና በሕጉ ብቻ መሥራት ሞራላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ግዴታ መሆኑን ከልጅነት ጀምሮ በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት ምን ያህል ነው የሚማረው? ምን ያህል እንዲህ ዐይነት ሥራ በዘላቂነት የሚሠራበት አሠራር ተዘርግቷልስ? የሚሉትን መፈተሽ ያስፈልጋል::

አድኪዊነትን ማስቀረት ብዙ ጠቀሜታ አለው::

1ኛ. መሪ ለተከታዮቹ ፍትሐዊ ከሆነ ተከታዮቹ በበጎ እንዲያዩትና የሥራ ተነሽነታቸውን ከፍ የማድረግ እድል አለው የሚለው አንዱ ነው:: ብዙ መሪዎች በተለያየ ምክንያት ከአድሏዊ አሠራር የጸዱ አይደሉም ማለት ይቻላል:: መልካም የሠራ የሚጎዳበት፣ ክፉ የሠራ የሚሸለምበት ጊዜ ብዙ ነውና:: አንዱ በሠራው ሌላው የሚመሰገንበትና እድገትና ሽልማት የሚያገኝበት ጊዜም እንዲሁ:: መሪ አድሏዊ ከሆነ ግን ፍትሐዊና ሚዛናዊ አሠራር ሊኖር አይችልም:: ችግሩ ከላይ ባሉ መሪዎች ሲሆን ደግሞ ለመፍታትም አስቸጋሪ ይሆናል:: ሰው የሥራውን ዋጋ ሳያገኝ ከቀረ፣ ትጉህ ሠራተኛ ምስጋናም እውቅናም ከሌለው፤ የደከመ ሳይሆን ያሾፈ የሚሸለም የሚሾም ከሆነ "ምን አደከመኝ" ይላል:: የሥራ ተነሳሺነት በዚህ ሁኔታ ይደክማል:: በቀላሉ እንደ ተላላፊ በሽታ ለሁሉም የመዳረስ እድል ስላለውም ተቋሙን ክፉኛ ሊጎዳ ይችላል::

2ኛ. ከአዲላዊነት የጸዳ አሠራር ሲኖር የሕግ የበላይነትን ለማስፈንና ተአማኒነትን ለማትርፍ ይረዳል:: ፍትሕ ማለት ሁሉንም በተሰጠው ሓላፊነት ልክ ተጠያቂ ማድረግ ማለት ነው:: እኩል የሰረቁ ሰዎች አንዱ ተጠይቆ ሌላው ሲታለፍ ፍትሕ ስለሚዛባ የበለጠ ቅሬታን ያስነሣል:: ሕዝቡን በእኩል የበደሉ ሰዎች አንዱ ታስሮ ሌላው ሲሾም ምነው ይህማ ከመጀመሪያው ግፍ የባሰ አይሆንም እንዴ ያሰኛልና:: ተባብረው ያጠፉ

ሰዎች ከላይ ያዘዘው ቀርቶ ታችኛውን ተጠያቂ ሁን ሲባል ፍትሕ ገደል ይገባል:: ሕግ ለሁሉም በእኩል ተፈጻሚ ሲሆን የሚያጉረመርሙትን ሰዎች የማዘጋት ዐቅምም ይኖረዋል:: ሁሉም ባጠፋው ጥፋት ልክ እኩል ተጠያቂ ሲሆን ቅጣቱ ተፈጻሚ በሆነባቸው ሰዎች ሳይቀር ብዙም ተቃውሞ አያስከትልም:: ቅጣት ቢሆን እንኳ ቅጣቱ የበለጠ የሚያመው ፍትሐዊነት ሲጓደል ነው:: እንዴት እኔ ብቻ? የሚለው ነገር ትልቅ ሕመምን ማስከተሉ የሚጠበቅ ነውና::

3ኛ. አድሏዊነትን በተመለከተ በየጊዜው የተለያዩ ምርምሮች ያደረጉ ሰዎች የጥናታቸውን ውጤት ሲያጠቃልሉ በሥራ ቦታ እንኳ የሥራ እድገት ወይም የደሞዝ ጭማሪ ሲደረግ ሠራተኞች በቅድሚያ የሚጠይቁት የተደረገው ሥራ ግልጽነት አለው ወይ? ፍትሐዊ ነው ወይ? አድሏዊነት የለበትም ወይ? የሚለውን ነው በማለት ይናገራሉ[15]:: ክፉም ይሁን መልካም ነገር ሲደረግ ብዙ ጊዜ የሚቀድመው ጥያቄ ለምን በእኔ ላይ ብቻ ይህ ተደረገ? ለምን በሌሎች ላይ አልተደረገም? ወይም ለምን ለእነርሱ ተደረገ? ለምን ለእኔ አልተደረገም? የሚል ነው:: "በፍትሕ ከተወሰደብኝ በቅሎዬ ያለ ፍትሕ የተነጠኳት ዶሮዬ የበለጠ ይቆጨኛል" የሚባል አነጋገር እንዲህ ላለው አሠራር የተነገረ ነው:: አንድ ሰው በሠራው ሥራ የሚሾም የሚሸለም ሲሆን ሥራው ፍትሐዊ ከሆነ ቀሪዎችን ያበረታታል እንጂ ቅሬታን አያስነሣም:: ለመሪውም ታማኝነትን እና ተቀባይነትን ያተርፍለታል:: ሌላው ቢቀር የሠራተኛ ቅነሳ በሚደረግበት ጊዜ ቅነሳው ግልጽነት ያለውና በቂ መረጃ ለሠራተኞች የሚሰጥ ከሆነ፣ ከአድሏዊነት የጸዳ ከሆነ፣ ቅሬታንና መካሰስን ይቀንሳል ወይም ያስቀራል የሚል ነው ከላይ የተጠቀሰው የጥናት ውጤት ግኝት:: ከአድሏዊነት የጸዳ አሠራርን በየተቋማቱ መዘርጋት ከተቻለ ወደ ፍርድ ቤት የሚሄዱትን የሰራተኛ

[15] A study of nearly 1,000 people in the mid-1990s, led by Duke's Allan Lind and Ohio State's Jerald Greenberg, found that a major determinant of whether employees sue for wrongful termination is their perception of how fairly the termination process was carried out. https://hbr.org/2006/03/why-its-so-hard-to-be-fair

ክሶች፣ ቅሬታዎችና የተቋሙን ስም ማጉደፍን እነዚህ ሁሉ ስለሚቀንስ ከኪሳራው ትርፉ ላቅ ይላል የሚል ነው የጥናቶች ወጤት የሚያሳየው። እንዲህ ዐይነቱን ነገር በተግባርም ማዬት ይቻላል።

በአጠቃላይ ፍትሐዊነት በቃል የሚነገረውን ያህል በተግባር ቀላል አይደለም። ስለሆነም የጠባይና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ከሚሰራው ሥራ በተጨማሪ ጠንካራ ተቋማዊ አሠራርን፣ የሕግ የበላይነትን እንዲሁም ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓትን በየተቋማቱ መገንባት አስፈላጊ ነው። የጠባይ ለውጥ ለማምጣት ዘላቂ በሆነ መልኩ ከሕጻንነት ጀምሮ ሥራ ቢሠራ ብዙ መሻሻል ሊገኝበትም ይችላል። ከምንም በላይ በሁሉም ዘርፍ ያሉ መሪዎች አርአያነታቸው ከፍ ያለ ነው። በተለይም የሃይማኖት መሪዎችና የማኅበረሰብ መሪዎች ትውልድን በመቅረጽና ፍትሐዊነትን ጨምሮ ሌሎች ሞራላዊ እሴቶች ሥር እንዲሰዱ ለማስቻል ጉልህ ሚና እንደሚኖራቸው ይጠበቃል።

ምዕራፍ አራት

ትሕትና

4 ትሕትና ምንድን ነው?

ትሕትና ከቅንነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው:: ያለ ትሕና ቅንነት እንዴት ይቻላልስ? በሥራ አመራርም የመሪዎችን ስብዕና በተመለከተ ከሚነሱ አንኳር ጉዳዮች ትሕትና ሰፊ ቦታ አለው:: በግለሰብ፤ በትዳር ሕይወት፤ እንዲሁም በቤተሰብ፥ በማኅበራዊ ግንኙነት ትሕትና ለስኬታችን ወይም ለውድቀታችን ጉልህ ስፍራ እንዳለውም የሚታመን ነው:: አንድ መሪ ከስኬታማነቱ ጀርባ በአመለካከቱም በተግባሩም ትሕትና ያለውን አስተዋጾ በሰፊው ሲነገር፤ ምሁራንም ብዙ ሲጽፉበትና ሲሞግቱበትም ይታያል:: ትሕትና በብዙ ሊቃውንት ብዙ የተነገረለት፥ በእጅጉ የተጻፈለት እንደሆነም የታወቀ ነው:: አማዞን (Amazon) እንኳ ከስምንት ሺህ መጻሕፍት በላይ በትሕትና (humility) ዙሪያ እንደተጻፉ ያሳያል[16]:: ትሑት መሪ (humble leader) እንዲሁ ብዙ ተብሎለታል፥ ተጽፎለታልም::

[16] https://www.amazon.com/s?k=humility&crid=3L7ZA7VT5O2RF&sprefix=humility%2Caps%2C143&ref=nb_sb_ss_i_4_8

የአማርኛ መዝገበ ቃላት ትሕትና ለሚለው ቃል ጠባዩን በትሕትና ማስገዛት፣ ማዋረድ፣ አለመኵራት፣ ግብረ ገብ መኾን፣ የፈቃድ ውርደት፣ ዝቅታ፣ በሚል የሚተረጉመው ሲሆን ትሑት ሰውን ደግሞ ራሱን በማዋረድ ዝቅ የሚያደርግ የሚል ትርጉም ሰጥቶታል። በዚሁ መዝገበ ቃላት የእንግሊዘኛ ትርጉሙ humility, humbleness, civility, courtesy, graciousness, cordiality, lowliness በሚል ያስቀምጠዋል::

በመጽሐፍ ቅዱስም ትሕትና ጉልህ ስፍራ ከተሰጣቸው እሴቶች አንዱ ነው:: "ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንካ አታድርጉ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር" የሚለው መልእክት ትሕትና እኔ እበልጣለሁ ከማለት ባልጀራዬ ከእኔ ይሻላል እስከማለት የሚያደርስ መሆኑን ያስተምራል። (ፊል. 2፥3-5)

ራስን ዝቅ ማድረግ፣ ታናሽ ታላቁን ማክበር በእግዚአብሔር የተወደደ እንደሆነም "እንዲሁም፣ ጕበዞች ሆይ፣ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፤ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።" የሚለው ያሳያል (1ኛጴጥ. 5፥5)

"እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፣ ምሕረትን፣ ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣ ትሕትናን፣ የዋህነትን፣ ትዕግሥትን ልበሱ።" እንደተባለ ትሕትና ከየዋህነት፣ ከምሕረት፣ ርኅራኄ፣ ቸርነት፣ ትዕግሥት ጋር የማይነጣጠል ነው:: (ቆላ 3፥12: ኤፌ. 4፥2)

ትሕትና በአሳብም፣ በስሜትም በተግባርም ነው የሚገለጸው:: ትሕትና የራስ ባልሆነና ታይቶ በሚጠፋ ነገር አለመመካት ነው:: ትሕትና ሁሉን እችላለሁ፤ ከሁሉም በላይ ነኝ፤ ከሌላው እበልጣለሁ ከሚል ቅዠት መውጣት መቻልንም ያመለክታል:: ትሕትና ራስን ከሚገባው በላይ ከፍ ከፍ አለማድረግን፤ ሰው ማክበርን ቢቻል ደግሞ ባልንጀራን ከራስ እንደሚሻል አድርጎ መቁጠርን፣ ቀደም ቀደም አለማለትን ቢቻል ደግሞ

ሌሎችን ማስቀደምን፣ የሚገባው ሆኖ አይገባኝም ብሎ ማመንን፣ ልታይ ልታይ አለማለትን፣ የዐላማውን መሳካት እንጂ ምስጋናን አለመሻትን፣ ከምንም በላይ ደግሞ ከራስ ይልቅ በእግዚአብሔር መታመንንም ይጨምራል::

የትሕትና ተቃራኒው ትዕቢት ወይም እብሪት ነው:: ትዕቢት በዚሁ መዝገበ ቃላት ትቢተኛነት፣ ኩራት፣ የልብ እድገት፣ ከፍታ ብሎ ሲተረጉመው የእንግሊዘኛ ትርጉሙን ደግሞ arrogance, vanity, smugness, conceit, snobbery, elation, haughtiness, pride በሚል ያስቀምጠዋል:: እንደሚታወቀው ትዕቢት ለሰው ልጅ ውድቀት ምክንያት ነው:: አዳምና ሔዋን በተሰጣቸው ክብርና ገዥነት ከማመስገን ይልቅ በትዕቢት ያልተሰጣቸውን አምላክነትን ሲሹ ወድቀዋልና:: ብዙውን ጊዜ ትዕቢት የሚመጣውም ለራስ ከመጠን ያለፈ ግምት በመስጠት፣ ስኬትን በማጋነን ራስን በአግባቡ ካለመረዳት ሲሆን ፈሪሃ እግዚአብሔርን አለመያዝ ደግሞ ለዚህ ምንጭ ሊሆን ይችላል:: "እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን ይጠላል፣ ትዕቢትንና እብሪትን ክፉንም መንገድ ጠማማውንም አፍ እጠላለሁ" ተብሎ እንደተጻፈ:: (ምሳ. 8፥13)

በተለይ ለመሪ ትልቁ ጥበብ የመሪነትን አሸጋሪነት ተረድቶ የዓቅም ውሱንነትን ማወቅ ነው ማለት ይቻላል:: ክፉ መሪ በጉልበቱ እጅግ ከመታመኑ የተነሣ እግዚአብሔርን ሳይቀር እስከ መዳፈር፣ በእግዚአብሔር እስከ መዘበት፣ ከእጁ የሚያድናችሁ የለም እስከ ማለት ይደርሳል:: ክፉ መሪዎች ብዙ ገድል ሠርተናል፤ ብዙ ገንዘብ አፍርተናል፤ በብዙ ሠራዊት ተከበናል ማለት ሲጀምሩ ምድርን ሁሉ የሚገዙ መስሎ እስኪሰማቸው ድረስ ልባቸው ሊታበይ ይችላልም:: በዓለም ታሪክ የብዙ አምባገነን መሪዎች ታሪክ የሚያሳየው ይህን የመሰለ እውነት ነው:: ዓለምን እንገዛለን ብለው የተነሡ መሪዎች ለቅዠታቸው ምንጩ ይሄው ያለቅጥ መታበይ እንደሆነ ነው ታሪካቸው የሚያሳዬው::

"ትዕቢትን የሚያደርግ በቤቴ መካከል አይኖርም፤ ዓመፅን የሚናገር በዓይኔ ፊት አይቀናም::" እንዲል ትዕቢት በተግባር ብቻ ሳይሆን በቃልም በአሳብም የሚገለጽ ነው:: (መዝ. 101፥7)

“እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች ናቸው፡፡ ሰባትንም ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፈዋለች ትዕቢተኛ ዐይን፣ ሐሰተኛ ምላስ፣ ንጹሕን ደም የምታፈስስ እጅ፣ ክፉ አሳብን የሚያበቅል ልብ፣ ወደ ክፉ የምትሮጥ እግር፣ በሐሰት የሚናገር ሐሰተኛ ምስክር በወንድማማች መካከልም ጠብን የሚዘራ።” ተብሎ እንደተጻፈም ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፈዋለች ተብለው ከተዘረዘሩት ሰባት ነገሮች በተራ ቁጥር አንድ የተጠቀሰው ትዕቢት ነው:: (ምሳ 6፥16-19)

ለምንድን ነው እግዚአብሔር ትዕቢትን ይጠላል ከማለት አልፎ እግዚአብሔር ትዕቢትን ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፈዋለች በሚል የተገለጸው? ብሎ መጠዬቅም ተገቢ ነው:: በሁለቱ መካከል ልዩነት አለ:: በትዕቢት ምክንያት የማይታሰብ፣ የማይሠራ ምን ክፋት አለና? ትዕቢት የክፋት ሁሉ ሥር ሊባል የሚችል ነው:: ከትዕቢት የተነሣ ሰው እኔ የተለዬሁ ነኝ፣ ከሁሉ እበልጣለሁ፣ የሚገዳደረኝ የለም የሚል ክፉ አመለካከት ሲነጸናወተው፣ እንዲህ ባለው ክፉ አመለካከት ምክንያት የማይፈጸም ምን ኃጢአት ይኖራልስ? ይህ በሃይማኖታዊ እይታ ስለታዬ ብቻም አይደለም:: ከዚያም ውጭ ባለው አስተሳሰብ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው:: በዓለም ዙሪያ በየዘመኑ የነበሩ እንዲህ ዐይነት መሪዎችን ማሰብ ይበቃል:: ሰው በኃይሉ፣ በሥልጣኑ፣ በደጋፊው ብዛት፣ በእውቀቱ፣ በወገኑ፣ በሀብቱና በመሳሰለው ታይቶ በሚጠፋ ጊዜያዊ ነገር ሲመካ ውጤቱ ምን እንደሚሆን መገመት አያስቸግርም::

በተመሳሳይ ትምክህት የትዕቢት መገለጫ ነው:: በተለያየ ስያሜ ብንጠራውም ኩራት ወይም አንዳንዴ ጉራ፣ እኔ እበልጣለሁ የሚል አመለካከት፣ በእውቀት በሥልጣን በሀብት በወገን በታሪክ የመመካት ነገርን ሁሉ የሚያመለክት ነው:: በተግባር ከዚህ የጸዳ ስንት ሰው ማግኘት ይቻል ይሆን? የሚለው እንዳለ ሆኖ ትምክህት ወይም ትምክህተኛ የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ሲነሣና አንዱ ሌላውን ሲከስበት ይደመጣል:: እኔ እበልጣለሁ የሚለው አመለካከት ሙሉ እይታን ስለሚጋርድ ሌላውን አሳንሶ ወይም እንኳ ሳ ማየትንም ያመጣል:: ፉክክር በሚበዛበት ጊዜ አንዱ ሌላውን ለመብለጥ የራሱን ከሌላው የተሻለ አስተዋጽዖ፣ የተሻለ ታሪክ፣

የተሻለ ክብር፣ የተሻለ እውቀት፣ የተሻለ ባህል፣ የተሻለ ቋንቋ፣ የተሻለ ሃይማኖት፣ የተሻለ ሀብት እንዳለው እያሰበና በዚህ እየተኩራራ ሌላውን ዝቅ አድርጎ ማዬት ይጀምራል:: ከሌላው እኩል መሆን ክብር ነው ብሎ ከማሰብ ይልቅ ከሌላው መብለጥ ነው ክብር የሚል የተዛባ አመለካከት ለዚህ ዋናው ምክንያት ሊሆን ይችላል:: ይህ ደግሞ የተለመደ በሽታ ነው::

ትምክህት መገለጫው ብዙ ነው:: ፊደል ቆጣጥሮ አንድ ወይም ሁለት ድግሪ ወይም ዶክተር ፕሮፌሰር የሚለውን ማዕረግ ሲደርብ ሰማይ የጨበጠ ያህል የሚሰማው ሰው አይጠፋም:: በትንሽ ሥልጣን የሚሰክረውም ብዙ ነው:: ሠርቶም፤ ሰርቆም ትንሽ ሀብት ሲያከማች ድህን የሚጸየፈውን ሰው ብዛት ቤት ይቁጠረው:: አጥንትና ደም የሚቆጥረውና በዚያ የሚመካውስ ቁጥሩ ስንት ይሆን? ሌላው ቀርቶ በሃይማኖቱ የሚኮራና የሌላውን የሚያናንቅ ሰው መስማት እንኳ የሚታይበት ዓለም ላይ ነው ያለነው::

ወንድሙን ገድሎ የሚፎክር፣ በትንሽ ድል የሚያቅራራ፣ አባቶቹ በሠሩት ገድል ምንም አስተዋጽዖ ባላዳረገበት የራሱ ገድል እንደሆነ ደረቱን የሚነፋውም ቁጥሩ እየበዛ ነው:: ብዙ ነው የትምክህት ዐይነቱ:: እንዲህ ባለው ድል መኩራትና ለበለጠ በጎ ሥራ መነሣሣት አይደለም የትምክህት ክፋቱ:: ችግሩ እንዲህ ባለው ድል መኩራራትና ሌላውን መናቅ፣ እንዲህ ባለው ድል መስከርና ከሰው የተለየሁ ነኝ እኔን የመሰለ ሰው የለም ማለት ሲጀመር ነው:: ትሕትናን ከባድ የሚያደርገውም ይህን ሁሉ ሲታሰብ ነው:: ይህን ሁሉ አሸንፎ ትሑት መሆን በእርግጥም ትልቁ ገድል ነው ማለት ይችላል::

“ኢትዮጵያውያን ኩሩዎች ናቸው” የሚባለው አነጋገር በራስ መተማመንን፣ በራስ ነገር መኩራትን፣ አልበገር ባይነትን እና ልበ ሙሉነትን የሚገልጽ ሲሆን የሚፈለግ ነው:: ከዚያ አልፎ ግን ትዕቢትንና ከሌላው እበልጣለሁ የሚል የትምህክት መንፈስን ሲይዝ ግብዝነት ሊሆን ይችላል:: የብዙ ሺህ ዓመታት ታሪክ ባለቤቶች ነን ማለት ያኮራል:: በየዘመኑ ለራሳቸው ትልቅ ክብርና ልብ ሙሉነት ያላቸው በፈጣሪ የሚታመኑ በደማቸውና

በአጥንታቸው የኢትዮጵያን ነጻነት ያስከበሩ የጀግኖች ልጆች ነን ማለት ያኮራል:: በቅኝ ገዢዎች ያልተከለሰ ያልተበረዘ የጥንታውያን ሃይማኖቶች አገር ሰው መሆን መታደል ስለሆነ ያኮራል:: ይህንን ኩራት ግን የተሻለ ታሪክ ለመሥራት ሲጠቀሙበት እንጂ ባለፈው ታሪክ በመኩራራት ለጉራ ካዋሉት ከሰው ከመነጠል በቀር ለምንም አይጠቅምም::

ኩራት ለትምክህት ሲውል ነው ችግሩ:: በዚህ ሁሉ እየተኩራሩ ሌሎችን መናቅ፣ ራስን መኮፈስና ባለፈ ገድል ሲፎክሩ መኖር፣ ይሄ ነው ትምክህት ማለት:: አፍሪካውያን እንዴት ነው የሚያዩን? ሌላው ዓለምስ? ለምን? የሚለውን መጠየቅም ተገቢ ነው:: ትምክህት ከሌሎች መነጠልን ያመጣል ወይም አላስፈላጊ ፍትጊያን ይጋብዛልና::

ትህምክተኛ በሚል ፖለቲከኞች አንዱ ሌላውን ሲካሰሱ ምን ማለታቸው ነው? በእውነት አተረጓጉሙና ነገሩን የሚያዩበት መነጽር ቢለያይ እንጂ ከትምህክት የጸዳ ስንት ሰው ማግኘት ይቻል ይሆንስ? የሚለውንም መጠየቁ ተገቢ ነው:: ትምክህት በዝቷል የሚባልበት ዘመን ነውና:: የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ "እኛ እንበልጣለን፤ ጊዜው የእኛ ነው፤ ይሞክሩን ያውቁናል እናሳያቸዋለን፤ ይዋጣልን እንተያያለን" የማይባልበት አካባቢ የትኛው ነው? እንዲህ ዐይነቱ ነገር ሲደጋገም ነው እብሪት በርክቷል የሚያሰኘው:: ጥያቄው እንዲህ ያለው ትምክህት መልኩን እየቀያየረ የሚመጣው ለምንድን ነው? እንዲህ ካለው ክፉ በሽታ መላቀቅና አላስፈላጊ ፍትጊያን ማስቀረት የሚቻለውስ ምን ቢሆን ነው? የሚለው ነው::

"አሁን ግን በትዕቢታችሁ ትመካላችሁ፣ እንደዚህ ያለ ትምክህት ሁሉ ክፉ ነው::" እንደተባለ ትምክህት የክፋት መገለጫ ነው:: ተቀባይ ሊሆን የሚችልበት ምክንያትም የለም:: (ያዕ. 4፥16) "ትዕቢት ጥፋትን፣ ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል::" ተብሎ እንደተጻፈም የእብሪት ፋጻሜውም ብዙ ጊዜ እንደሚታየው ውድቀት ነው የሚሆነው:: (ምሳ. 16፥18)

በሌላ በኩል ሁሉም መፍትሔ ከሰው እንደማይገኝ ማስተዋል መቻልም ነው አንዱ የትሕትና መገለጫ:: አሁን የትኛው የፖለቲካ ፓርቲ ነው፣

የትኛው መሪ ነው ለችግራችን ሁሉ መፍትሔ ማምጣት የሚቻለው? እንኳን እንዲህ ባለበት ሁኔታ በተረጋጋ ሁኔታ ቢሆን እንኳ ሁሉም ችግር በመሪዎች ዓቅም ብቻ እንዴት ሊፈታ ይችላል? "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ጠቢብ በጥበቡ አይመካ፤ ኃያልም በኃይሉ አይመካ፤ ባለ ጠጋም በብልጥግናው አይመካ፤ ነገር ግን የሚመካው ምሕረትንና ፍርድን ጽድቅንም በምድር ላይ የማደርግ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን በማወቁና በማስተዋሉ በዚህ ይመካ። ደስ የሚያሰኙኝ እነዚህ ናቸውና፣ ይላል እግዚአብሔር።" ተብሎ እንደተጻፈ ወደ እግዚአብሔር መጮህም የመፍትሔው ትልቁ አካል ነው። (ኤር 9፥23) ይህ ግን ትሕትና ይፈልጋል። በጩኸት ብቻ የሚመጣ መፍትሔም የለም። በጩኸት የፈረሰ ከተማም የለም። በጩኸት የፈረሰ ከተማ ኢያሪኮ ብቻ ነው የሚታወቀው። እርሱም በሕዝቡ ጮኸት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ኃይል ተጨምሮበት ነው። ጩኸት የበለጠ ችግርን የሚያባብስ ከሆነ ቆም ብሎ ማሰብ የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው የሚባለው ይህንን እያሰቡ ነው።

4.1 መሪነትና ትሕትና

በኢትዮጵያውያን ባህል ትሕትና ያለው ዋጋ ምን ያህል ነው? በየዘመኑ የነበሩ መሪዎች ምን ያህሉ በትሕትና የሚታወቁ ነበሩ? መሪዎች ለሚመሩት ሕዝብ ያላቸው ከበሬታ ወይም ንቀት ምን ያህል ነው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ለማጥናት ሰፊ ሥራ የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ትሕትና ለአንድ መሪ ስኬት ወይም ውድቀት ያለው ሚና ግን ጥያቄ የሚነሣበት አይደለም።

ለዘመናት ኢትዮጵያውያን ትሑታን ናቸው የሚለው ስም ነው ጎልቶ የሚነገረው። በውጭውም ዓለም ኢትዮጵያውያን ትሑታን ናቸው የሚል ስም መስማት የተለመደ ነው። በአንጻሩም የለም ትሕትና እየጠፋ፣ ከመከባበር ይልቅ መፎካከር፣ ከመመሰጋገን ይልቅ የማጣጣል፣ አንዱ ሌላውን የመንቀፍ፣ አንዱ የሌላውን ሥራ የማናናቅ ልማድ ጎልቶ በሚታይበት ሁኔታ ትሕትና አለ አያሰኝም የሚሉ ወገኖችም የዚያኑ

ያህል ናቸው:: እንዲያውም ያለመደማመጥ አንዱ ምክንያትም የትሕትና መጥፋት ነው የሚል አሳብ ይነሣል:: አውቃለሁ የሚለው የበዛበት ዘመን ነው፤ አድምጡኝ የሚለው የበዛበት ዘመን ነው፤ ማዕረግ የሚያስቀድመው፣ አክበሩኝ የሚለው ሰው የበዛበት ዘመን ነው፤ የሚል ነጥብም ይነሣል:: ገድሉን የሚያወራ፣ በትንሽ ትሩፋት የሚኩራራ፣ ያልሠራውን ሠራሁ ብሎ የሚፎክረው ይበዛል የሚባል ነገር መስማትም የተለመደ ሆኗል:: ያም ሆነ ይህ መሪዎች ትሑታን ሲሆኑ ምሳሌነታቸው ትሑታን ተከታዮችን ለማፍራት ያስችለል:: መልካም ዛፍ መልካም ፍሬን እንደሚያፈራ ሁሉ ትሑት መሪ ሊገኝ የሚችለውም ትሑት ሕዝብ ሲኖር ነው::

ትዕቢት መጀመሪያው እንጂ መጨራሻው አይታወቅም ይባላል:: እሰከ መመለክ የሚደርሱ መሪዎች በዚህ ዓለም የሚታዩት ከዚህ የተነሣ ሊሆን ይችላል:: በሕይወት እያሉ በስማቸው ሀውልት እንዲሰራላቸው ያደርጉና ምን ላድርግ ሕዝቡ ከፍቅራቸው የተነሣ ሐውልት ካላቆምንልህ ብሎ ግድ አለኝ ሲሉ በሚንቁት ሕዝብ ይዘብቱበታል:: ጥቅም ፈለጊው አፋሽ አጎንባሽ ብዙ ነውና እንዲህ ዐይነት መሪ ሲገኝ ጥቅማቸው አይቋረጥ እንጂ መሪው ሰው ሳይሆን ከአማልክት መካከል አንዱ እንደሆነ አድርገው ይሰብኩለታል:: በምድር መመላለሱ ነው እንጂ ቅዱስ ነው ብለው ያውጁለታል:: እንዲህ ዐይነቱን ነገር የሚቃወም ሰው ከተነሳም እጣ ፈንታው ሞት ወይም እስራት ሊሆን ይችላል::

በጥቅሉ በመሪዎች ዘንድ የትሕትና መጥፋት ብዙ መገለጫዎች ይኖሩታል::

- ሁሉን እችላለሁ፣ ሁሉን እናውቃለን የማለት ዝንባሌ፣ ሳያውቁ አዋቂ መስሎ መታየት፣
- በጉልበት መመካት፣ ሁሉን በኃይል ማሰብ፣ ዓለምን የጨበጡ መምሰል፣

- ከሌላው እበልጣለሁ የሚል ከንቱ ትምክህት፣ የተለዩ እንደሆኑ እስከማመን መድረስ፣
- መኮፈስ፣ መጀነን፣ ጉራ፣ በትንሽ ገድል መኩራራት፣
- አለመከባበር፣ ንቀት፣ ኩራት፣ በእብሪት መፎከር፣ የሚመሩትን ሕዝብ አሳንሶ ማየትና እንዳላዋቂ መቁጠር፣
- የሰው አሳብ የሰው አስተያየት አለመቀበል፣ ከእነርሱ ካልመጣ ሁሉንም አሳብ የማጣጣል ዝንባሌ፣
- ግትርነት፣ ካልሞትኩ ሐሳቤ አይቀየርም ማለት፣
- አለመደማመጥ፣ ሊሰሙ የሚፍልጉትን ብቻ መርጦ ማዳመጥ ለአስተያየት ጆሮን መድፈን፣
- ዕውቀትንና አዋቂዎችን ማጣጣል፣ አዋቂዎችን መናቅ፣
- የቀደመውን በዜሮ ማጣፋትና ከዜሮ መጀመር፣ የቀደመውን ሁሉ መክሰስ፣ መውቀስ፣ እኛ እንበልጣል ፣ እኛ ብቻ አዋቂ የማለት ዝንባሌ፣
- ከሕግ በላይ መሆን፣ ያውጡትን ሕግ አለማክበር፣ ሁሉ በእጁ ነው በሚል በማናለብኝነት ስሜት ከሕግ ውጭ የጥድፊያ ውሳኔ መወሰን፣
- የፈጣሪን ሕልውና እስከመካድ መድረስ ወዘተ. ይገኙበታል።

4.2 ትሕትና ከምን?

ትሑት መሆን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ያለው የሥራ አመራር አስተሳሰብ ትሕትና ስኬታማ መሪ ለመሆን ወሳኝ ጠባይ ነው የሚል ነው:: ለምሳሌ አንድ የሀርቨርድ ሪቪው መጽሔት ላይ የወጣ ጥናት[17] ስኬታማ መሪዎች የሚባሉ ትሑታን መሪዎች ናቸው በሚል ያስቀምጠዋል:: ሌሎች ተመሳሳይ ጥናቶችም ይህንኑ ያሳያሉ:: በአሁኑ ጊዜም ቢሆን መሪዎችን ለመቅጠር ከሚቀርቡ መስፈርቶች አንዱ ትሕትና ሆኖ ማየትም ተለምዷል:: በእርግጥ ስኬታማነትን ሰዎች የሚያዩበት መንገድ የተለያዩ ሊሆን እንደመቻሉ እንዲህ ዐይነቱ እሳቤ ክርክር ሊነሳበት እንደሚችልም መረዳት ይቻላል:: በዘመናት ስኬታማ መሪዎች ከሚባሉት የሚልቁት ትሑታን ናቸው የሚባለውን ያህል ሌሎች ደግሞ ስኬታማነትን እንደሚያዩበት መነጽር ከዚህ በተቃራኒው ሐሳባቸው ሲያቀርቡም ይታያሉ[18]::

በጥቅሉ መሪነትን በተመለከተ ከትሕትና የሚገኙ ስምንት (8) ጠቀሜታዎችን ዘርዘር አድርጎ ማየት መልካም ነው::

❁ ሰዎችን ከማቅረብ

ትሕትና ሰዎችን ለማቅረብና አስተባብሮ ለማሠራት ልዩ ኃይል አለው:: መሪነት በየትኛውም ደረጃ ይሁን በየትኛውም ዘርፍ የቡድን ሥራ ነውና:: የመሪ ዋናው ተግባሩ ደግሞ በየሙያው፣ በየዘርፉ ሥራን በብቃት ሊመሩ ወይም ሊሠሩ ለሚችሉ ሰዎች ማከፋፈልና ማስተባበር ነው:: መሪ የሚገጥሙት ችግሮች እየተወሳሰቡና እየጨመሩ ባለበት ዓለም ከቀኝም ከግራም በዙሪያው ጠንካራ ሰዎች ያስፈልጉታልም:: ድክመቱን ሳይፈሩ የሚነግሩትን፣ በነገር ሁሉ ቀርበው የሚያግዙትን ሰዎች ማግኘት የሚችለው ደግሞ መሪ ትሑት የሆነ እንደሆነ ነው::

---

[17] The best Leaders are humble leaders. https://hbr.org/2014/05/the-best-leaders-are-humble-leaders

[18] Humility in Leadership, http://essay.utwente.nl/64933/1/Stru%CC%88fing_MA_Management%20and%20Governance.pdf

ሌላውን የሚያዋርድ ራሱን የሚያከብር፣ ሌላውን የሚያጣጥል ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ፣ ራሱን ልዩ ፍጡር እንደሆነ ለማሳመን የሚጥር ሌላውን የሚያንኳስስ፣ ራሱን ንጹሕ ሌላውን ቆሻሻ ለማድረግ የሚጣጣር መሪ ጋር ግዴታ ካልሆነበት በቀር ደስ ብሎት መሥራት የሚፈለግ እንዴት ይኖራል? እንዲህ ዐይነቱ ሰው አምባገነን የመሆን እድሉ ከፍ እንደሚልም የሚያጠያይቅ አይደለም:: አምባገነን መሪዎች ደግሞ እንዴት ባሉ ሰዎች እንደሚከበቡ በየዘመኑ የታየ ነው:: ሳይጠሯቸው አቤት፣ ሳይልኳቸው ወደየት የሚሉ ሰዎች በመብራት ተፈልገው ሥልጣን ይሰጣቸዋል እንጂ ይገዳደረኛል፣ እርሱ ሲልቅ እኔን ያሳንሰኛል፣ ለምን? እንዴት? የሚል ጥያቄ ያቀርባል የሚባል ሰው እንዲህ ባሉ መሪዎች ዘንድ አይወደድም:: የሚያቀርበውም አይገኝም::

ትሑት መሪ ራሱን የተሻለ ሰው አድርጎ ለማሳየት የሚጥር ሳይሆን በዙሪያው ያሉትን ተከታዮች የተሻለ ዓቅም እንዲያገኙ፣ የተሻሉ ሰዎች እንዲሆኑ የሚያበረታታ፣ እድል የሚፈጥር፣ "እኔ ላንስ እርሱ ከፍ ከፍ ሊል" ይገባል ብሎ የሚያምን ነው:: አንጉል ሙገሳንና አሽቃባጭነትንም ሆን ብሎ ይርቃቸዋል:: ሌሎችን ማመስገንን እንጂ አመስግኑኝ ማለትን የሚወድ አይደለም:: "ሌላ ያመስግንህ እንጂ አፍህ አይደለም፤ ባዕድ ሰው እንጂ ከንፈርህ አይደለም::" የሚለውን ምክር በሕይወቱ የሚተገብር መሪ እንዲህ ዐይነቱ ነው:: (ምሳ. 27፥2)

ትሕትና በሌለበት ከሰው ጋር ተግባብቶ ለመሥራት ያስቸግራል:: ከእርሱ ጋር መሥራት አልፈልግም፤ እንዲህ ካለ ሰው ጋር መሥራት አልችልም፤ ለሌላ ሰው እድል አይሰጥም፤ ሌላ አሳብ ለመስማት ትዕግሥት የለውም፤ ሁሉን አውቃለሁ ባይ ጉረኛ ነው፣ ምንም ሳያውቅ አውቃለሁ ባይ አለማወቁን የማያውቅ ግብዝ ነው፤ የሚባል መሪ በየቦታው ያጋጥማል:: የትዕቢት ውጤቱ ይህንን የመሰለ ነው::

አመለካከት ከትሕትና ጋርም በእጅጉ ይያያዛል[19]:: ዘረኝነት፣ ከፋፋይነት፣ አምባገነንነት እነዚህን የመሰሉ አስተሳሰቦች ምንጫቸው ከአመለካከት ጋር የሚያይዛቸው ነገር አለ:: ሰዎችን አሳንሶ ማዬት፥ ለራስ የተጋነነ ዋጋን መስጠት፥ ሁሉን አውቃለሁ ባይነት፣ ሰዎችን መፈረጅ፣ ሰዎችን መከፋፈል የሚመጣው ዕብሪት ባለበት ሁኔታ ነው:: የእኔ ዘር ይብልጣል የሚል ትምክህተኛነት፣ በጉልበት መመካትና መኩራራት ይህ ሁሉ ከአመለካከት ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል:: ታዲያ ትሕትና ነው መድኃኒቱ::

መሪ በትሕትና እና በቀና ልቦና ማዳመጥ ሲችል ነው በአንድ ችግር በጋራ ውይይት ለውጥ ማምጣት የሚቻለውም:: ትሑት መሪ አቃፊ ነው:: የሚያገል ሳይሆን የሚያቀርብ ነው:: በጥርጣሬ ከማየት ቀና ልቦናን ያስቀድማል:: ትሑት መሪ አመለካከቱ፣ ለሰው ያለው ቅን አሳብና፣ ለሰው ያለው ቀና ልቦና ሰውን ያቀርባል:: መሪ ከተኮፈሰ፣ መሪ በትዕቢት ራሱን ከሌላው ካራቀ፣ መሪ ፍሩኝ እጅግ አክበሩኝ የተለየሁ ነኝ የሚል ከሆነ፣ መሪ እኔ ብቻ ያልኩትን ስሙ እኔ ብቻ ያልኩትን አድርጉ ካለ፣ ሁሉን አዋቂ ነኝ ሁሉን መወሰን አለብኝ ካለ፣ በፍቅርና በመተሳሰብ ለአንድ ዐላማ መሰለፍና ተቀራርቦ ለመሥራት እንዴት ይቻላል?

☸ ኬኮችን ከማትጋት

ለመሪ ስኬታማነት ተግቶ የማትጋት አቅሙ ጉልህ ስፍራ አለው:: ትሕትና ሌሎችን ለማትጋት ዓቅም ይሰጣል:: ትዕቢት ሲጸናወት ሁሉን እኔ ሠራሁት፤ ለሁሉም ነገር ምስጋናውን የምወስደው እኔ ነኝ፤ የእኔ አሳብ ነው፤ የእኔ የጭንቅላት ውጤት ነው፤ የእኔ የድካም ውጤት ነው ማለት ይበዛል:: ትዕቢት ሲበዛ ለሁሉም ነገር ዋጋ ስጡኝ ማለት ይጨምራል፡፡ የሌሎችን ዋጋ ከንቱ ማድረግም አንዱ መገለጫው ነው:: ጥሩ ሲሠራ ለሁሉም ነገር ምስጋናውን ጠቅልሎ መውሰድ፤ ክፉ ሲሠራ

[19] Open-mindedness raises similar issues to modesty and humility in that it involves taking a special attitude to oneself. https://plato.stanford.edu/entries/modesty-humility/#OpenMind

ደግሞ በሌላው ላይ ጣት መቀሰር ነው አንዱ የትዕቢተኛ ልማድ። በየጊዜው እንዲህ ዐይነት መሪ ስንት ያጋጥማል?

እንመካከር ከማለት ይልቅ ሁሉም ነገር በቀጭን ትእዛዝ በሚወርድበት ጊዜ እኔ ምን ችገረኝ ሥራ የተባልኩትን እሠራለሁ ይሆናል ነገሩ ሁሉ። በግዴለሽነት በመሠራቱም ሥራው የተበላሸ ቢሆን እንኳ "እኔ የሠራሁት የታዘዝኩትን ነው" የሚል መልስ የሚጠበቅ ነው። በዚህም ለጥራት የሚጨነቅ ሰው ስለሚጠፋ ጥራት ገደል ይገባል። እኛ ብቻ አዋቂ ነን፣ የምንላችሁን ብቻ አድርጉ የሚሉ አለቆች በሚበዙት የሥራ ተነሣሽነት፣ የሥራ ትጋት፣ የሥራ ፈጠራ ሊዳከም ይችላል። በተመሳሳይ እብሪት በበዛበት አሳብ ባቀርብ ማን ሰሚ ይኖራል በሚል ስጋት አሳብ አፍላቂነትም አይኖርም።

እንዲህ ዐይነት መሪዎች በሚበዙት ሁኔታ የሥራ ተነሣሽነት ምን ያህል እንደሚጎዳ ማሰብ ይቻላል። ሰው የበኩልን አስተዋጽዖ ለማድረግ ልቡ የሚነሣሣው ሁሉን አውቃለሁ የማይል፣ ለሰው አሳብ ዋጋ የሚሰጥ፣ በአሳብ የሚያምን ትሑት መሪ በሚኖርበት ጊዜ ነው። እኔን አመስግኑኝ ከማለት ይልቅ ለሌሎች ምስጋና መስጠትን የሚያበዛ፣ ጥፋትን ቢሠራ እንኳ በሌሎች ከማሳበብ ይልቅ ሓላፊነቱን ቀድሞ የሚወስድ፣ የበታቾቹን ከመውቀስ ይልቅ ጥፋቱን የሚጋራና የበታቾቹን ከተጠያቂነት የሚያድን፣ እንዲሁም ሰው ለሠራው ሥራ ተገቢውን ዋጋ የሚሰጥ መሪ ተከታዮቹን ለማትጋት ልዩ ኃይል ይኖረዋል። ተግቶ ማትጋት ግን ሰፋ ጉዳይ ነውና አግባብ በሆነው ቦታ በሰፊው የሚዳሰስ ይሆናል።

❁ ጥራ አድማጭ ለመሆን

የማዳመጥ ችሎታ በመሪዎች ዘንድ እጅግ ተፈላጊ ክህሎት እየሆነ መጥቷል። ለመሪ ከባዱም ከመናገር ይልቅ ማዳመጥ መቻል ነው ማለት ይቻላል። በዝቶ የሚታዬው እስኪ ላዳምጥ፣ እስኪ ልማር፣ እስኪ ችግሩን በደንብ ከተረዱት በችግሩ ውስጥ ካለፉት ልምዱና እውቀቱ ካላቸው ሰዎች ልረዳ የሚለው ወይስ ራሱን እንዳዋቂ የሚቆጥረውና ያለውን ለመወርወር የሚቻኮለው? የሚለውን በመጠዬቅ የችግሩን ልክ ለመረዳት

ይቻላል:: መሪዎች የሌላውን ወገን አሳብ እና እይታ ለማዳመጥ ሳይሆን የራሳቸውን ለመጫንና ለማሳመን ጥረት ሲያደርጉ ማዬት እንግዳ ነገር አይደለም:: የራስን ሕይወት መመርመርና ያለንን ዝንባሌ ምን እንደሆነ ለማወቅም ከባድ አይሆንም፤ ፈታኝ የሚሆንብን መናገሩ ወይስ በጥሞና ማዳመጥ መቻል?

ትሕትና በሌለብት ሰው ለመናገር የፈጠነ ለማዳመጥ የዘገየ መሆኑም የሚጠበቅ ነው:: ሁሉን አዋቂ ነኝ ከእኔ የተሻለ አዋቂ የለም ብሎ ለሚያስብ፣ የራሱ ብቻ ካልሆነ የሌላውን አሳብ ሁሉ ብላሽ አድርጎ የሚመለከት ሰው፣ ለማዳመጥ የሚያስችል ልብ ከውዴት ያገኛልስ? "የሰነፍ መንገድ በዐይኑ የቀናች ናት፤ ጠቢብ ግን ምክርን ይሰማል።" የሚለው የጠቢቡ ቃልም ይህን የሚያሳይ ነው:: (ምሳ. 12፥15)

በጥቅሉ የመሪ ስኬት ለማዳመጥ፣ ለመማር፣ በሌላው ወገን ሆኖ የሌሎችን ችግር ለመረዳት፣ አንድን ነገር በትዕግሥት ከሁሉም አቅጣጫ ለማዬት መቻሉ ጋር የተቆራኘ ነው የሚለው በሰፊው የተጻፈበትና በብዙ መሪዎች የሚነገር ነው::

መሪ የተነገረውን ብቻ ሳይሆን ያልተነገረውን ማዳመጥ የሚችል መሆን አለበት፡፡ በተለይም ወደላይ በወጣ ቁጥር ለመሪ ክፉው ወሬ እየተጣራ ደግ ደጉ ብቻ ስለሚነገረው መሪ ድክመቱንና ያለውን ችግር የመስማት እድሉ ጠባብ ይሆናል:: የተነገረውን ብቻ ማዳመጥ ሙሉ እውቀትን አይሰጥምም:: ያልተነገረውን ነገር ማዳመጥ ግን ችሎታ የሚፈልግ ነው:: ከሚነገረው ባሻገር የተናጋሪውን ስሜት መረዳት የማዳመጥ ችሎታን ይጠይቃል:: ሰው ሲናገር ከቃሉ ጀርባ ስሜት አለው:: የመልእክቱ ምንነት ሰማንያ አምስት በመቶው (85%) እንዲህ ባለው በስሜት ወይም በምልክት የሚነገረው ነው ይባላል:: ፈረንጆቹ body language[20] የሚሉት ማለት ነው:: የሚነገረው ብቻ ሳይሆን የሚነገርበትን መንገድ ማስተዋል መቻል ወሳኝ ነው:: አፍ አንድ ነገር እያወራ ልብ የሚያስበው ሌላ

[20] Body language is nonverbal communication that involves body movement. "Gesturing" can also be termed as body language. 51 Body Language Gestures, and What They Signal, https://lacinai.se/wp-content/uploads/2015/10/51-Body-Language-Gestures-and-What-They-Signal-.pdf

የሚሆንበት ጊዜ ብዙ ነውና:: እውነተኛው መልእክት በስሜት ይገለጻል፣ ይህ ደግሞ በአነጋገሩና በምናሳዬው የሰውነት እንቅስቃሴ ይታወቃል::

የማዳመጥ ችሎታ ማለት ሰው ሲናገር ጸጥ ብሎ ማስጭረስ፣ ራስን እየወዘወዙ ተናጋሪን ማበረታታት ወይም ተናጋሪን አለማቋረጥ ማለት ብቻም አይደለም:: እነዚህ ነገሮች አስፈላጊ ቢሆኑም የማዳመጥ ችሎታ ግን ከዚህም የሚልቅ ነው:: በሀርቫርድ ሪቪው መጽሔት የቀረበ አንድ ጥናት እንደሚያሳዬው ጥሩ አድማጭ ናቸው በሚል የሚመደቡ ሰዎች ጥያቄን በመጠዬቅ የበለጠ ነገሩን ለመረዳት ጥረት የሚያደርጉ፥ ለተናጋሪው አክብሮትና ዋጋን በመስጠት የሚያበረታቱ፤ በንግግሩ ሁሉ በንቃት የሚሳተፉ እና በመጨረሻም አስተያዬታቸውን በአክብሮት የመግለጽ ችሎታ ያላቸው ናቸው[21]:: ከምንም በላይ አስቀድሞ የመፈረጅ ዝንባሌን መቆጣጠር እና የሚያሳክክና የማይመች ቢሆን እንኳ በትዕግሥት አዳምጦ የመበየን ችሎታ ነው የማዳመጥ ክህሎት የሚባለው:: የመፈረጅ ስሜትን ገታ አድርጎ በክፍት አእምሮ ነገርን እሰከ ፍጻሜው ማዳመጥ መቻል መታደል ነው ማለት ይቻላል:: ብዙ ተግዳሮት ያለበት ነውና:: ከአንድ ወገን ብቻ ስምቶ መፍረድም ከባድ አይሆንም:: ችሎታ የሚፈልገው ሁሉንም ወገን አዳምጦ ያለ አድልዎ በገለልተኝነት መወሰን መቻል ነው::

ትሕትና ሲኖር ሰውን ማድመጥ፣ ለሌሎች ሰዎች አስተያየትና ለባለሙያ ምክር ጆሮን መስጠትም ይቻላል:: ማዳመጥን የታደለ መሪ ጆሮዎችን ለሁሉም ሰው እና ለሁሉም አስተያየት ክፍት ማድርግ የቻለ መሪ ማለት ነው:: ለምስጋና ብቻ ሳይሆን ለነቀፋም፣ ከሚደግፉት ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከሚቃወሙትም፣ መስማት የሚፈልገውን ብቻ ሳይሆን ለመስማት ጆሮውን የሚያሳክከውንም ለመስማት የተዘጋጀ መሪ "ጠቢብ እነዚህን ከመስማት ጥበብን ይጨምራል አስተዋይም መልካም ምክርን

[21] What Great Listeners Actually Do? people perceive the best listeners to be those who periodically ask questions that promote discovery and insight. The best listeners made the conversation a positive experience for the other party, Good listening was seen as a cooperative conversation, Good listeners tended to make suggestions, https://hbr.org/2016/07/what-great-listeners-actually-do

ገንዘቡ ያደርጋል።" እንደተባለ ችግርን በጊዜው ለመቅረፍ፣ የተሠወረውን ለማየት፣ ያላወቀውን ለማወቅና ለመማር እድል ያገኛል:: (ምሳ. 1-5) ትዕቢት ሲበዛ ውዳሴ ከንቱን እንጂ ነቀፌታን፣ ወቀሳንና ቅሬታን ለማዳመጥ የሚችል ጆሮና ልብ ማግኘት ከባድ ይሆናል::

በተመሳሳይ ምስጋናን መስማት ቀላል ነው:: ከሚፈልጉት ወገን የሚፈልጉትን አሳብ መርጦ መስማት ችሎታ አይፈልግም:: ተቀናቃኝ ከሚሉት ወይም ከሚጠሉት ሰው የማይመችን ወይም የሚጠሉትን አሳብ ማዳመጥ ግን ትዕግሥትን ይፈልጋል:: ወቀሳን ወይም ነቀፌታን ማዳመጥ ትሑት ልብና ትዕግሥት ላላቸው ሰዎች ብቻ የሚቻል ነው::

ትሕትና በሌለበት እንዴት መደማመጥስ ይቻላል? መደማመጥ ግን የጋራ ነው:: ዛሬ አብዛኛው ይናገራል እንጂ አዳማጭ ማግኘት ቀላል አይደለም:: ትሕትና የሌለብት ድፍረት ይበዛል:: ዕውቀት ቢኖርም ባይኖርም፣ መረጃ ቢኖርም በግምት ቢሆንም፣ በመሰለኝ በደሳለኝ የሚነገረው ብዙ ነው:: በጉልበት የሚመካው በበዛበት፣ በየአቅጣጫው እንተያይ፣ እንፈታተሽ፣ ይዋጣልን፣ አሳይሀለሁ ወዘተ. የሚል ፉከራ በርክቶ በሚሰማት ሁኔታ ችግራችን የተጠራቀመ እንደመሆኑም እንኳን እንዲህ ባለ ሁኔታ ሰከን ብሎና ተደማምጦም መፍትሔ ማምጣት ቅርብና ቀላል ላይሆን ይችላል:: ጉልበት መፍትሔ እንደማያመጣም ብዙ ዘመን ተሞክሮ ታይቷል:: መፍትሔ የሚመጣው ያበጠው ልብ ተንፈስ ብሎ፣ የሚፈላው ሰከን ብሎ፣ ሁሉም ወደ ልቡ ተመልሶ በጉልበት ከመመካት ፍቅርና እና መተሳሰብን ሲያስቀድም እንደሚሆንም ለማንም የተሰወረ ሊሆን አይችልም። ይህ ሁሉ የሚቻለውም ግን ትሕትና ሲኖር ነው:: ሸለቆው ሁሉ ከፍ ሊል፣ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ሊል፣ ጠማማውም ሊቃና፣ ስርንጒጡም ሜዳ ሊሆን ካልቻለ ችግሩ ቢባባስ እንጂ እንዲህ ባለ ሁኔታ መፍትሔ እንደማይመጣ ነው ቅዱስ መጽሐፍም የሚያስተምረን:: (ኢሳ. 40፥4)

ችግሮቻችን ለመፍታት የማይቻሉ፣ ውስብስብና ከዓለም የተለዩ ሆነ ነው ወይስ በትሕትና መደማመጥ ስላቃተን? የሚል ጥያቄ ማንሣት የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው:: በዕብሪት ነገሩን ሁሉ ከማካረር ለጋራ መፍትሔና ለጋራ ጥቅም በማስተዋል የሚሠሩ መሪዎችን በብዛት ማግኘት የሚቻለው አንዱ የሌላውን ነገር በትሕትና በጥሞና ነገሬ ብሎ ማዳመጥ ሲችል ነው:: ትዕቢት ሲበዛ መጫጫህና ፉከራ ብቻ እንጂ ችግሩን ለይቶ መፍትሔ ለማምጣት አይቻልም:: ችግሩ ምንድነው? ምን መፍትሔ ይኖረዋል? መፍትሔው የሚመጣው በምን መንገድ ነው? መፍትሔው ስንት ጊዜ ይወስዳል? ለመፍትሔው ከእያንዳንዱ ወገን የሚጠበቀው ምንድን ነው? የሚለውን በመደማመጥ ለይቶ ለማውጣት ትሕትና ጉልህ ሚና ይኖረዋል:: ይህ ደግሞ መሰልጠንም አስተዋይነትም ነው::

❁ ተደማጭነትን ከማግኘት

የመናገር ችሎታ ተግባቦት የሚገለጽበት ሌላው መንገድ ነው:: የመናገር ችሎታ የሚለካው ደግሞ መደመጥ በመቻል ነው:: መናገር መቻል ብቻም አይደለም ቁም ነገሩ:: መልዕክቱ በተነገረበት ልክ አድማጭ ምን ያህል ገብቶታል? የሚለው ነው ውጤታማ ንግግር የሚያሰኘው:: አንድን ንግግር አድማጭ በተነገረበት መንፈስ፣ በተነገረበት አውድና በተነገረበት መጠን መልዕክቱ ሳይዛባ በተነገረው ልክ ምን ያህል ተረድቶታል? የሚለው ነው ጥሩ ተናጋሪ ነው የሚያስብለው:: አድማጩና ተናጋሪው ምን ያህል ተናበዋል? ተናጋሪው አድማጮቹን ምን ያህል ያውቃቸዋል? ተናጋሪው ለአድማጩ በሚመጥንና በሚገባ መልኩ ንግግሩን ምን ያህል ማቅረብ ችሏል? የሚለውም ለስኬታማ ንግግር አስፈላጊ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ መሪ አነጋገሩ በትሕትና ሲሞላ አድማጭ ያገኛል:: ንግግር ለአድማጭ የሚገባውን አክብሮት በመስጠት በትሕትና የተሞላ ሲሆን የሰውን ቀልብ መያዝ እንደሚቻል በተግባርም የሚታይ ነው:: ሰው አክብሮት ሲሰጡት ጆሮውንም ይሰጣል፥ ልቡንም ሊከፍት ይችላል::

ነገሩን ያጠኑት ተመራማሪዎችም ይሄንን ነው የሚሉት:: አለመታመንና ጥርጣሬ በበዛበት ወቅት በማስመሰል ሳይሆን በእውነት፥ በእብሪት ሳይሆን በትሕትና መናገር ሲቻል የተናገሩት አየር ላይ አይቀርም የሚል ነው አስተያዬቱ[22]::

ሰውን ያበሻቅጣል፤ ሰውን ያንቋሸሻል፤ በማን አለብኝነት የሚናገረውን አያውቅም፤ የመጣለትን ሁሉ ያለገደብ ይናገራል የሚባልን መሪን "በሰው ፊት ቀልቤን ገፎ ቢያዋርደኝስ" በሚል ስጋት መቅረብ ያስፈራል:: አንዱን ዝቅ ሌላውን ከፍ ማድረግ የሚመጣው ዕብሪት ባለበት ሁኔታ ነውና:: ሥልጣን አለኝ ጠያቂ የለብኝም ብሎ የሚያስብ አምባገነን መሪ ለአፉ ጠባቂ አይኖረውም:: አውቆም ሳያውቅም እንደመጣለት ይናገራል፡፡ የሚያስለቅስ ቢሆንም መሪ ነውና ይሳቅለታል:: እንዲህ ባለው ያልተገራ ንግግር በየዘመኑ ብዙ ነገር ፈርሷል፣ ብዙ ሰውም ተጎድቷል::

መቼም አፍን በሰለጠኑ ወታደሮች ማስጠበቅ እንደማይቻል የታወቀ ነው:: አስተዋይነት ነው የሚያስፈልገው:: ከመናገር በፊት ጠያቂ ባይኖር እንኳ ደጋግሞ ማሰብ ነው የሚያስፈልገው:: ከሰው ዓቅም በላይ የሆነው ነገር በበዛበት ዓለም "አቤቱ፣ ለአፌ ጠባቂ አኑር፣ የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ፡፡" በማለትም የፈጣሪን ርዳታ መለመንም ይጠቅማል:: (መዝ 141፥3) ይህ ሁሉ የሚቻለው ደግሞ የትሕትና ልብ ሲኖር ነው::

ቃል ያንጻል ቃል ይሰብራል:: እንዳጠቃቀሙ ነው:: በንግግር ማፈረስም መገንባትም ይቻላልና የመሪ ቃል የሚያሳዝን ሳይሆን የሚያንጽ ሊሆን ይገባል:: "ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ፣ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ፡፡" እንደተባለ (ኤፌ. 4፥23) መሪ በሚናገረው ቃል ብዙ ሰዎችን ሊያቆስል ይችላል፡፡ ያውም እስከወዲያኛው ሊጠገን የማይችል ቁስል:: መሪ በእብሪት ሲሞላ ንግግሩ አፍራሽ ይሆናል::

መሪ ንግግሩ በጥንቃቄ የተሞላ የተመጠነ ምን እንደሚናገር ብቻ ሳይሆን የሚናገረውን ነገር በምን ዐይነት ሁኔታ እንደሚናገረው እጅግ ጥንቃቄ የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው:: በተለይ በዚህ ሐሰቱን እውነት አስመስሎ

ማውራት በሚቻልበት፤ መረጃ ከዓለም ጫፍ ወደ ሌላኛው ጫፍ በፍጥነት በሚዳረስበት፣ ሁሉም የሚዲያ ባለቤት በሆነበት ዘመን የምላስ ወለምታ ትልልቅ ህልሞችን የማኮላሸት ዓቅም እንዳለው ለማንም ግልጽ ነው:: ለንግግር አስቀድሞ መጠንቀቅ እንጂ ከአፍ ካመለጠ የፈሰሰ ውኃን ለማፈስ እንደመሞከር ነው የሚሆነው:: የመሪ ቃል ጭራን የመሰንጠቅ ያህል በየአቅጣጫው መብጠልጥሉ የሚጠበቅ ነውና፡፡ እንደ መሪነቱ ደረጃ የመሪ ቃል ፈር ከሳተ የሚያደርሰውም ጉዳት ዘርፈ ብዙና ከባድ ሊሆን ይችላል:: ያልተመጠነ ንግግር ዋጋ ማስከፈሉም አይቀርም:: “ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ ከቃልህ የተነሣ ትኰነናለህ” የሚለው ቃልም የሚያስገነዝበን ይህን ነው:: (ማቴ. 12፥37)

በአጠቃላይ የመናገር ችሎታ እጅግ ሰፊና ብዙ የሚነገርለት የተጻፈበትም መሆኑ የታወቀ ቢሆንም እዚህ ለማንሳት የተፈለገው ከትሕትና ጋር በተያያዘ ያለውን ነው:: ጉዳዩን ግን በሌላ ቦታም እንደ አግባብነቱ ለማንሳት ይሞክራል::

❁ ራስን ከማወቅ

ትሕትና ራስን ለማወቅ፣ ራስን ከሚገባው በላይ አግዝፎ ላለማየት ይጠቅማል:: ራስን ማወቅ (self awareness) በሳይንሱም ቢሆን ትልቅ ጥበብ ነው:: የስሜት ልህቀት (Emotional Intelligince) የሚባለው አራት ክፍሎች አሉት፡፡ እነሱም ራስን ማወቅ (self-awareness)፣ ራስን መግዛት (self-management)፣ አካባቢን መረዳትና (social awareness) የተሳካ ግንኙነት (relationship management) ናቸው[23]:: ስለራሳችን ያለን ግምት የተስተካከለ መሆኑም ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው፤ የምንሠራው ሁሉ ከዚህ ይመነጫልና::

[23] Emotional Intllegence. https://hbr.org/2017/02/emotional-intelligence-has-12-elements-which-do-you-need-to-work-on

ለራሳችን ያለን ግምት እና ሌሎች ሰዎች እኛን የሚገልጹበት መንገድ ምን ያህል የተቀራረበ ነው? ደካማ ጎናችንን ምን ያህል እናውቀዋለን? የሚለውን ስንጠይቅ ነው ለራሳችን ያለን ግምት ምን ያህል የተጋነነ መሆኑን ማስተዋል የሚቻለው:: ሰው በአብዛኛው ስለ ራሱ ያለው ግምት የተሳሳተ ነው ይባላል:: "ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ" እንደሚባለው አነጋገር ሰው ራሱን መካብ ይወዳል:: ድክመትን ለይቶ ማወቅ፣ ይህ ነገር ይጎድለኛል፤ እንዲህ ዐይነቱን ነገር ከእኔ ይልቅ የተሻለ ዕውቀት ያላቸው ሰዎችን ብጠይቅ ይሻላል እንዲህ ባለው ጉዳይ የተሻለ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች አስተያየት ቢሰጡበት ይሻላል ማለት የሚቻለው ራስን በአግባቡ ማወቅ ሲቻል ነው:: እውነታው ግን ከዚህ በተቃራኒው ሊሆን ይችላል:: ብዙውን ጊዜ ከምናውቀው በላይ ያወቅን መምሰል፣ ካለን መልካም ማንነት በላይ ገዝፎ መታየት ነው የሰው ዝንባሌ::

ራስን በየቀኑ በመስታወት የመመልከት ልማድ የመኖሩን ያህል ራስን መመርመር፣ ጠንካራ ጎንና ደካማ ጎንን መመዘን፣ የየቀኑን ውሎ ስኬትና ጥፋት ማንሰላሰል ብዙም የተለመደ አይደለም:: በዚያ ላይ አስተያዬት ለመቀበልና ራስን ለማሻሻል ያለን ዝግጁነት ምን ያህል ነው? የሚለውም ይወስነዋል:: ሌላው ቀርቶ ግልጽነት በሚጎድልበት ሁኔታ ድክመታችንን የሚነግረን ሰው አናሳ ነው የሚሆነው:: ተንኮልና መጠላለፍ በበዛበት የአመራር ባህል ደግሞ በቀናነት የመገማገምና ወደፊት ሊያሳድገን የሚችል አስተያዬት ከሥራ ቦታ የማግኘት እድሉም አናሳ ሊሆን ይችላል:: በተለይ እንደ እኛ ባለ አገር መሪዎችን በድፍረት ድክመታቸውን እንዲያስተካክሉ አስተያዬት መስጠት ብዙ ዋጋ ስለሚያስከፍል ብዙም የተለመደ አይደለም:: ዘመናዊ በሚባሉ ተቋማት ሦስት መቶ ስልሳ ድግሪ (360 Degree) የሚባል የመሪዎችን የሥራ አፈጻጸም የሚገመገሙበት ሥርዓት አለ[24]:: መሪዎች ከበታች ሠራተኛ፣ እንዲሁም ከሌሎች ከሥራ ከሚገናኛቸው አካላት ሁሉ ግምግማና አስተያየት የሚሰጥበት ሥርዓት ነው:: አስተያየት ሰጪው ማንነቱን ስለማይገልጥ በነጻነት ከሁሉም

[24] Benefits of 360 Degree Feedback, Increases self-awareness, Clarifies behaviors, Measures "how" things get done as opposed to "what" get's done, Promotes dialogue, Improves working relationships, Encourages personal development…..https://decision-wise.com/benefits-of-360-degree-feedback/

አቅጣጫ የሚሰበስበው አስተያየት በሥራ አፈጻጸምም ይሁን በጠባይ የመሪውን ማንነት ለመገምገም ይረዳል። ጥሩ መረጃ ለማግኘትና መሪን በቀጣይ እንዲስተካከልና በተሰጠው አስተያዬት እየተመራ እንዲያድግ ስለሚያስችል ውጤታማ አሠራር ነው ይባልለታል።

በእርግጥ ራስን ማወቅ የዕድሜ ልክ ሥራ ነው። ዕድሜ ልክ ከምናውቀው የማናውቀው እንደሚበዛ፣ ከመልካም ሥራችን ያጠፋነው ስሕተታችን እንደሚበረክት ካስተዋልን፣ ለራስ ያለን የተጋነነ ግምት እየተስተካከለ የበለጠ ራሳችንን እያወቅን እንሄዳለን። በቅዱስ መጽሐፍም ራስን ማወቅ የማያቋርጥ የሕይወት ጉዞ መሆኑን "ወንድሞች ሆይ፣ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቁጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፣" ሲል ቅዱስ ጳውሎስ መናገሩም ለዚህ ነው።(ፍሊ. 3፥13) በግርድፍ ትርጉሙ "ብዙ መማር በቻልኩ ቁጥር ምን ያህል እንደሚቀረኝ መገንዘብ ችያለሁ" የሚል የአልበርት አንስታይን አባባልም ከዚህ ጋር የሚስማማ ይሆናል። [25]

በሌላ በኩል ራስን በአግባቡ ለማየት የገዛ ዐይንን ማጥራት ይፈልጋል። "አንተ ግብዝ፣ አስቀድመህ ከዐይንህ ምሰሶውን አውጣ፣ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዐይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።" እንዲል ሙሉ እይታን የሚጋርድ ጉድፍ ወይም ምሰሶ ካለ ጉድፉ ሳይጠራ ወይም ምሰሶው ሳይወጣ አጥርቶ ማየት አይቻልምና። (ማቴ 7፥5) ትልቁ መሰሶ ግብዝነት፣ ሌላውን አሳንሶ ማየት፣ ራስን ከመጠን በላይ አጋኖ ማየት፣ ለራስ የተጋነነ ዋጋ መስጠት ሊሆን ይችላል።

ራስን ማወቅ አንዱ ሊገለጽበት የሚችለው የመጡበትን አለመርሳት መቻልም ነው። ስንቶቹ መሪዎች ይሆኑ ራሳቸውን በአግባቡ ማወቅ የሚችሉት? ስንቶችስ የመጡበትን ያስታውሱት ይሆን? ስንት ብቃት የነበራቸው፣ ለሕዝብ የሚቆረቆሩና በቅንነት የሚያገለግሉ ሰዎች ባሉበት አገር በለስ ቢቀናኝ ነው እንጂ በየትኛው የትምህርት ዝግጅት፣ በየትኛው የሥራ ልምድ ወይስ በየትኛው ብቃት ነው ወንበሩ ላይ የተቀመጥኩት?

[25]"The more I learn, the more I realize how much I don't know." Albert Einstein

ማለት መቻል ነው ራስን ማወቅ ማለት:: ስንቶቹ መሪዎች ነበሩ ለያዙት ቦታ በቂ የትምህርት ዝግጅት ወይም ልምድና አቅሙ የነበራቸው? እንዲህ ካሉ መሪዎች በዝቶ የሚታየው የትሕትና ሕይወት ነው ወይስ በተቃራኒው? ትሕትና ሲጠፋ የመጡበትን መርሳት ይኖራል:: በኃይል መመካት ይመጣል::

ራሱን የሚያውቅ ሰው እንደ ቅዱስ ዳዊት "አቤቱ አምላክ ሆይ እስከዚህ ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ ምንድር ነው?" ማለትን አይረሳም:: (1ኛዜና መዋዕል 17፥16) ዳዊት ገናና ንጉሥ ሆኖ ሳለ የመጣበትን፣ የነበረበትን እያሰበ እዚህ ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ? የአባቴስ ቤት ምንድን ነው? ለመሪነት ብታበቃኝም " እኔ ግን ትል ነኝ ሰውም አይደለሁም" ሲል መናገሩ የትሕትና ልብ ስላለው ነው:: (መዝ 21፥ 6)

ለትዕቢተኛ መሪዎች እንዲህ ዐይንቱ ነገር ሞኝነት ሊሆን ይችላል:: ሁሉንም በጉልበታቸው ሁሉንም በዕውቀታቸው ወይም በብልጠታቸው እንዲያም ሲል በሠራዊታቸው ኃይል እንዳገኙት ማሰባቸው አይቀርምና:: ኃይል ቢኖርም፣ ሥልጣን ቢኖርም፣ ሁሉን ማድረግ የሚቻል ቢሆን እንኳ እኔ ማነኝ? የሚለውን ማሰብ የሚጠቅመው ራሱ መሪውን ነው:: እድሉን ስላገኘሁ ነው እንጂ ሌሎችም እንደ እኔ እድሉን ቢያገኙ ከእኔ የተሻሉ ሰዎች አሉ የሚል መሪ ሲገኝ ብዙዎቹ ሊከተሉት ይፍልጋሉ:: ይህ ግን፣ የጠመንጃ ኃይል ሲኖር፣ በሥልጣን ፈረስ ላይ ሲወጡ ቀላል አይሆንም::

❁ ተገልጋይን ከማስደሰት

ሰው ጉዳዩ መፈጸሙን ብቻ ሳይሆን በክብር መስተናገድን ይፈልጋል:: ድሀም ይሁን ሀብታም፣ ባለሥልጣን ይሁን ተርታ ሰው መከበርን የማይፈልግ የለም:: ይህ ሰው የመሆን አንዱ መገለጫ ነው ማለት ይቻላል:: ባለጉዳይን በትሕትና ቢቻል በፈገግታም ጭምር ማስተናገድ ቢኖር ለተገልጋዩ የሚጨምረው እርካታ ከጉዳዩ መሳካት የማይተናነስ ሊሆን ይችላል::

ከሃይማኖት ተቋማት ጀምሮ በየዘርፉ ያሉ መሪዎች ሕይወት ምን ያህል ትሕትና ይታይበታል? የሚለውን መጠየቅ ያስፈልጋል:: ባለ ጉዳይን ማጉላላት፣ ማመናጨቅን ጨምሮ፣ የሚገባውን ክብር አለመስጠት ከብዙ መሪዎች የሚጎድል ነው:: ጎልቶ የሚታዬው አክብሩኝ እንዲያም ሲል ስገዱልኝ እንጂ ዝቅ ብሎ ማገልገል ብዙም አልተለመደም:: ይህ ከምን የተነሣ ነው? ለሚለው መልስ ለማግኘት ቀላል ባይሆንም መሪ ሆኖ በትሕትና ዝቅ ብሎ ማገልገል ነውር ነው የሚመስለው:: ነገሩ እየባሰበት ነው ወይም መሻሻል አሳይቷል? የሚለውም ተገልጋዩ የሚፈርደው ነው::

“ከፍትፍቱ ፊቱ” የሚለው ብሂል እንደሚያሳዬው ፈገግታ ለሁሉም ሰው ደስታን እንደሚሰጥ የተረጋገጠ ነው:: አንድ ሰው አገልግሎቱን ማግኘቱን ብቻ ሳይሆን አገልግሎት ያገኘበት መንገድ፣ የአስተናጋጁ ትሕትና ለተገልጋዩ ብዙ ትርጉምን ይሰጣል:: ብዙ ተቋማትም የደንበኞች አገልግሎት በሚል ብዙ ወጭ አውጥተው ስልጠናዎችን መስጠታቸውና የአገልግሎቱን ጥራት በየጊዜው መለካታቸውም እንዲህ ካለው ምክንያት የተነሣ ነው:: ቱሪስት ሲመጣም አንዱ ምቾቱን የሚለካበት መንገድም የአገልግሎት አሰጣጡ ነው:: በየተቋማቱ እንዲህ ዐይነቱ የትሕትና ባህልና አመለካከት ሲስፋፋ መልካም አስተዳደርን ለማምጣት ብቻ ሳይሆን ለአገር ገጽታም የሚኖረው አስተዋጽዖ ቀላል አይሆንም:: ትሑታን ሕዝቦች ናቸው የሚል ስም ትልቅ ሀብት ነው:: “ከመልካም ሽቶ መልካም ስም” እንዲሉ::

ሌላው ቢቀር በአገልግሎት ተቋማት እንኳ ደንበኞችን በፈገግታና በትሕትና ማስተናገድ እንደ አገር ብዙ የምንታማበት ነው:: በተለይ የውጭው ዓለም ልምድ ለሌለው ሰው የችግሩ መጠን ብዙም ላይታይ ይችል ይሆናል እንጂ ከውጭው ዓለም ጋር ቢወዳደር ደንበኞችን በትሕትና የማስተናገድ ባህላችን መሻሻል የሚገባው እንደሆነ የሚያጠያይቅ አይደለም::

❁ ከስሕተት ለመማር

ኩራት ባለበት ስሕተትን ማመን፣ ተሳስቻለሁ ማለት ጭንቅ ነው። ተሳስቻለሁ ማለት ራስን እንደማዋረድ፤ እንደመሸነፍ ሊታይ ይችላል። ትሑት መሪ ትችትም ይሁን ነቀፌታን የማዳመጥ ዓቅም ስላለው ከስሕተቱ ለመማርና የተሻለ ሰው እንዲሆን ትሕትናው ያግዘዋል።

አንድን መሪ ከሌላው የሚለውየውና ዘመን ተሻጋሪ አሻራን ትቶ ለማለፍ የሚያስችለውን ጥበብ የሚያገኘው የተለየ አስተሳሰብ ወይም የተለየ ብሩህ አእምሮ ስላለው ብቻ አይደለም። አስተዋይ መሪ ዕድሜ ልኩን ተማሪ ነው። አስተዋይ መሪ ከትልቁም ከትንሹም ለመማር የሚፈቅድ ነው። በትናንት ስሕተቱ የሚያፍርና ስሕተቱን የሚደብቅ ሳይሆን ከስሕተቱ ተምሮ ስሕተቱን ለላመድገም እና ነገ የተሻለ መሪ ለመሆን ራሱን ያዘጋጃል። ለአንድ መሪ ከስሕተቱ ለመማር ያለው ፈቃደኝነት ያለማቋረጥ እንዲያድግ ያግዘዋል። ከስሕተቱ የሚማር መሪ በየጊዜው ያድጋል፤ ይለወጣልም።

አንድ ታሪክ እዚህ ላይ ማንሣት ጠቃሚ ይሆናል። አንድ ወጣት በአንድ ግዙፍ ተቋም በመካከለኛ የመሪነት ደረጃ እንደተሾመ ሓላፊነቱ ያስጨንቀዋል። በዚህ ጊዜ ወደ ተቋሙ ሓላፊ ይሄድና "ይህን ግዙፍ ድርጅት ለመምራት የሚያስችልህን ጥበብ እንዴት ልታገኝ ቻልህ?" ይለዋል። የድርጅቱ ሓላፊም ትንሽ አሰብ ያደርግና "ያስተማረኝ ዕድሜ ነው" ብሎ ይመልስለታል። ወጣቱ መሪ አሁንም እንዴት? ይለዋል። መሪውም የወጣቱን ጀርባ መታ መታ እያደረገ እዚህ ለመድረስ ብዙ ማበላሸት ነበረብኝ፤ ትልቁን ጥበብ ያገኘሁት ከእያንዳንዱ ስሕተቴ ከእያንዳንዱ ደካማ ውሳኔዬ መማር በመቻሌ ነው ሲል መለሰለት ይባላል። የሚልቀው ጥበብ የሚገኘው ከቃል ትምህርት ይልቅ በሕይወት ተሞክሮ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው።

ስሕተትን ከመካድና ከመደበቅ ይልቅ ስሕተትን ማመን፣ ስሕተት እንዳይደገም ማድረግ መቻል ለማደግ፥ የተሻለ ሰው ለመሆን ይጠቅማል። ስሕተት እንዳይደገም ስሕተትን የመካድና የመደበቅ አመለካከትን

አስወግዶ ስሕተትን የማመን እና ይቅርታን የመጠየቅ ባህል ማዳበር ጠቃሚ ነው:: የበለጸጉና የተረጋጉ በሚባሉ አገሮች ችግር ሲከሠት የበለጠ ጠንክሮ መውጣት፣ ከአንድ ችግር ማግስት ከስሕተታቸው ተምረው ዳግም እንዳይከሠት ማድረግ የተለመደ ነው:: ተመሳሳይ ስሕተት እንዲደጋገም ብዙም እድል አይሰጡትም:: ከትናንት ዛሬ የተሻሉ የሆኑት በዚሁ መንገድ ነው ማለት ይቻላል:: አንድ ችግር ከተፈጠረ በኋላ ችግሩ ዳግም እንዳይፈጠር ችግሩ የተከሠተበትን ምክንያት፣ የችግሩን ምንጭ፣ የነበሩ ክፍተቶች ሁሉ ይጠናሉ:: ቀዳዳው ተለቃቅሞ ይደፈናል:: ተቋም ይቋቋማል:: የነበረውም ተቋም ከችግሩ በኋላ የበለጠ ጠንክሮ ይወጣል:: እንዲህ ሲሆን ችግር ዳግም የመከሠት እድሉ ጠባብ ይሆናል::

ማስተዋል ሲጠፋ ስሕተት ተደጋግሞ ሊሠራ ይቻላል:: ጥበብ ሲጎድል አንዱ የሚከሠተው ችግር ይሄው ነው:: ክፉን ታሪክ ላለመድገም ትምህርት እንዲሆን ነው ታሪክ የሚጻፈውም:: ቅዱስ መጽሐፍም የተጻፈበት አንዱ ምክንያት ከቀደመው ታሪክ ከጥሩውም፣ ከመጥፎውም ተምረን ክፉውን መንገድ ለመተውና ቀናውን መንገድ ለመምረጥ እንዲያስችለን ነው:: ከዚህ ቀደም ያልተፈጸመ ያልተሠራ አዲስ ነገር ኖሮ አይደለም:: የታጠበ እርያ ወደ ጭቃ እንደሚመለስ የሰው ልጅም ከስሕተት ለመማር ዳተኛ ስለሆነ ያለፈውን ታሪክ ደግሞ ላለመሥራት ያለፈውን ስለማይመረምር ነው እንጂ:: የዛሬ ክፉ መሪዎች ትናንትም ነበሩ:: እንደ ናቡከደነፆር፣ እንደ ፈርዖን ያሉ ክፉ መሪዎች በመጽሐፍ ታሪካቸው ተመዝግቧል:: ማስተዋል ስለሚጠፋ ግን እነሱኑ የመሰሉ መሪዎችን ዓለም ማስትናገዷን አላቆመችም:: ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለውን መመለስ ቀላል ባይሆንም ከታሪክም ከስሕተትም ለመማር የሚያስችል የትሕትና ልብ አናሳ መሆኑንና ለመማር ያለውን ዳተኝነት ግን ሊያመልክት ይችላል:: ከስሕተት መማር መቻል ትልቅ ጥበብ ነው::

ካለፈው ስሕተታችን መማር የምንችለው መቼ ነው? የሚለው ካልሆነ በቀር ሁሉም መልኩን እየቀያየረ ይመጣል እንጂ ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር የለም:: ያልወጣንበት ዳገት፣ ያልወረድንበት ቁልቁለት፣ ያላለፍንበት መንገድ፣ ያልታየ ችግር፣ ያልተሞከረ የፖለቲካ አስተሳሰብ በዚች አገር ምን አለ? ኮምኒስትነት ተሞክሯል። እምነት አልባነት ተሞክሯል።

ዘውዳዊነት ተሞክሯል። ዘረኝነት ተሞክሯል። መከፋፈል ተሞክሯል። የሃይማኖት ጦርነት ተሞክሯል። የሴራ ፖለቲካውን ኖረንበታል። የወንድማማቾች ጦርነትንም አይተነዋል። አብዮት፣ ባላባትነት፣ ገባርነት፣ በዘመነ መሳፍንት በትናንሽ መንግሥታት መተዳደርም ተሞክሯል። ነጻ አውጭነት ተሞክሯል፣ ሁሉም ተሞክሯል። መድኃኒት ግን እስካሁን አልተገኘም። ለምን? ቢባል ካለፈው መማር አለመቻላችን ነው። ለዚህ ደግሞ የትሕትና መጥፋት ትልቁን ቦታ መያዙ አይቀርም።

4.3 ትሕትናን እንደ ደካምነት

መሪ ትሑት ከሆነ መናቅን፣ መቃለልን ሊያስከትልበት ስለሚችል ቆፍጣናነት፣ ኮስታራነት ነው የሚያዋጣው የሚል አመለካከት የሚታይበት ጊዜ አለ። መሪን የሚያስከብረው ትሕትና ሳይሆን ተፈሪነት ነው የሚል አመለካከትም ይንጸባረቃል። ትሑት መሪን ደካማ አድርጎ የማየት ዝንባሌም ያለ ይመስላል።

እንዲህ ዐይነት አመለካከትም ያለ ምክንያት አይመጣም። ለዘመናት በዘለቀው የጌታና የሎሌ ሥርዓት መሪዎች ከፈጣሪ የተመረጡ፣ ከሕዝብ የተለዩና በተፈጥሮ ተለይተው የከበሩ ተደርጎ በሚሰበክበት፣ በሚታሰብበትና በተኖረበት ዘመን መሪዎች በአመዛኙ የሚታውቁት በመኮፈስና በኩራት በእብሪትና አንዱ ከሌላው እኔ እበልጣለሁ ወይም መብለጥ አለብኝ በሚል እሽቅድድም ነው። ትሕትና በዚያ ዘመን ትርጉም ይሰጠል ከተባለ ከመካከል ለዚህ የታደሉ መሪዎች ሲገኙ ብቻ ነው የሚሆነው። ከዚያም ወዲህ በፖለቲካው ዓለም ብቻ ሳይሆን የሃይማኖት ተቋማትን ጨምሮ በሌሎች ዘርፎችም የሥልጣኑ ኮርቻ ላይ በወጡና ከፍ ከፍ ባሉ ቁጥር መኮሳተርና መታበይ የተለመደ ነው።

እንዲያውም ቀደም ሲል የትሕትና ሕይወት የነበረው ሰው ሥልጣን ላይ ሲወጣ እንዲያው የሚኮፈስ፣ ማዕረግን እና ከበሬታን ብቻ የሚወድ፣ ፍሩኝ፣ አክብሩኝ የሚልና ጭራሹንም ከሚመስለው ብቻ እንጂ ከአብዛኛው ድሀ የሚርቅ እስከ መሆን ይደርሳል። አንድ ሰው

ሥልጣን ሲይዝ ኩራትና መኮፈስ ከሚመራቸው ሰዎች እየራቀ መሄድ፣ የሚበዛው እንዲህ ዐይነቱ አመለካከት በመኖሩ ሊሆን ይችላል:: እንዲህ ባለ አምባገነናዊ ባህል ትሑት መሪ እንደ ልፍስፍስ መሪ የመታየቱ ጉዳይ የሚደንቅ አይሆንም::

ላወቀበት ግን ትሕትና ያስከብራል እንጂ ንቀትን አያመጣም:: መኮፈስና መኮሳተር ተፈሪ ሊያደርግ ይችላል እንጂ አያስከብርም:: ፍሩኝ አክብሩኝ የማለት፤ የመኮፈስና የመጀነን ባህል ሰው በፍርሃት እንዲታዘዝ ያደርግ እንደሆን እንጂ ታማኝ አገልጋይን፤ እውነተኛ ተከታይን ለማፍራትም አያስችልም:: በተለይ አምባገነናዊ አገዛዝ በዘመናዊ አስተዳደር እየተተካ፤ መሪ ገዥ መሆኑ ቀርቶ የሕዝብ አገልጋይነቱ እየታመነበት እና እየተሠራበት ባለው በአሁኑ ዘመን ዝቅ ብሎ ማገልገል፣ በትሕትና ሕዝብን ማክበር፣ በትሕትና ሕዝብን ማዳመጥ፣ በትሕትና ከሕዝብ ጋር መዋል፣ በሕዝብ መካከል እየተገኙ የሕዝቡን እውነተኛ ችግር ማዳመጥ አማራጭ የሌለው የአመራር ስልት ነው:: በተቋም ደረጃም ቢሆን ተመሳሳይ ነው:: መሪ አገልጋይ ነኝ የሚል ከሆነ የሚመራቸውን ሰዎች በትሕትና ዝቅ ብሎ ማገልገል ይጠበቅበታልና::

ሠለጠነ በሚባለው ዓለም በአመዛኙ በየዘርፉ ያሉ መሪዎች ሥልጣን ስላላቸው ብቻ ከሌሎች ሰዎች የተለዩ እንደሆኑ የማመን ነገር ብዙም አይስተዋልም:: በተለይ በአንዳንድ አገሮች እንደ ተርታው ሕዝብ በሕዝብ መጓጓዣ ተጉዘው ሥራ ይገባሉ፤ እንደ ማንኛውም ሠራተኛ ይስተናገዳሉ፤ በአንድ ይመገባሉ:: በአመዛኙ ሕዝብን ዝቅ ብሎ ማገልገል፣ ሕዝብን ማዳመጥ፣ ዝቅ ብሎ ከሕዝብ ጋር መዋል የተለመደ ነው:: መሪዎች የሕዝቡን ቃል ያከብራሉ፤ ሕዝብን ያዳምጣሉ:: ለአለቃ ማጎብደድ፣ ጎንበስ ቀና ማለት፣ መሽቆጥቆጥ በአብዛኛው እየተረሳም ይመስላል:: ዲሞክራሲ አለበት በሚባለው ዓለም ቢያስን ዳግም ለመመረጥ ሕዝብን በትሕትና ዝቅ ብሎ ማገልገል ግዴታቸው መሆኑንም ያውቃሉ:: እውነትም መሪ ገዥ ሳይሆን የሕዝብ አገልጋይ ከሆነ የሚያገለግለውን ሕዝብ የሚያከብር እንጂ የሚንቅ ሊሆን አይገባውም:: እውነተኛ የሕዝብ አገልጋይ መሪ ባለበት ሁኔታ መሪ ለሕዝብ የሚያጎበድድ እንጂ ሕዝብ

ለመሪ ሊያጎበድድ አይችልም ምክንያቱም ሥልጣን የተገኘው ከሕዝብ ስለሆነ የመሪዎች አለቃ ሕዝብ እንጂ መሪ የሕዝብ አለቃ አይደለምና::

በእርግጥ መሪ በሁሉም ነገር "መሪ" መምሰል አለበት:: "መሪ አይመስልም" የሚባል አነጋገር አለ:: መሪ ለያዘው ቦታ የሚያስፈልገውን ክብር፣ የሚያስፈልገውን ፕሮቶኮል፣ የሚያስፈልገውን አቀራረብ ለሚመራቸው ሰዎች በሚመጥን ደረጃ ከትሕና ጋር መያዝ እንዳለበት ይታመናል:: መሪ በሚያደርገው ንግግር መሪነቱን የሚያረጋግጥ ፈርጠም ያለና በአግባቡ መምራት እንደሚችል የሚያመለክት መሆንም ይጠበቅበታል:: ትሕትና "መሪ መምሰልን" አይከለክልም:: መሪ ትሕትናው ከሚመራቸው ሰዎች አመለካከት፣ ባህል፣ አረዳድ አንጻር የተመጣጠነ ሲሆን "መሪ አይመስልም" የሚባለውን አስተያየት ማስቀረት ይቻላል:: በሌላ በኩል ተመሪው ትሕትናን ከደካምነት ለይቶ ማወቅ የሚሳነው ከሆነ፣ ትሕትናን መረዳት ካልቻለ የአመራር ዘይቤው ይህን የተመሪውን ባህልና ሥነ ልቦና የሚመጥን መሆን አለበት:: መሪ ትሕትናን የደካምነቱ መደበቂያ ካደረገው ግን ሌላ ችግር ነው::

ሁሉም ነገር የሚያምረው ሲመጣጠን ነው:: ትሕትና ውጤታማ እንዲሆን አጠቃቀሙ ምን መሆን አለበት? ልኩ ምን መሆን አለበት? መቼ ነው የሚሠራው? መቼ ነው የማይሠራው? የሚለውን መገንዘብ መቻል ነው ቁም ነገሩ:: ለምሳሌ በሀርቫርድ ቢዝነስ ሪቪው የቀረበ ጥናት[26] የሚያሳየውም ይህንን የመሰለ አሳብ ነው:: ትሕትናን ከቁርጠኛነት ጋር አጣጥሞ መምራት ከተቻለ ትሕትና ከበሬታን እንጂ መናቅን ሊያስከትል የሚችልበት ምክንያት እንዴት ሊኖር ይችላልስ?

ትሕትናን ከቁርጠኛነት ጋር አጣጥሞ መምራት የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል:: ለዚህ ደግሞ አብነት የሚሆነን በመጽሐፍ ቅዱስ የሙሴ ታሪክ ነው:: "በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ" የተባለለት ሙሴ ሁሉንም ያመጣጠነ መሪ ነበር:: (ዘኁ. 12፥3) እሥራኤልን ከአስጨናቂው ከፈርዖን እጅ እንዲያወጣ የተላከ ደፋር

[26] Humility and servant leadership do not imply that leaders have low self-esteem, or take on an attitude of servility.https://hbr.org/2018/04/how-humble-leadership-really-works

መሪ፣ ሕዝቡን በእግዚአብሔር ተአምር ቀይ ባሕርን ከፍሎ ያሻገረ፣ አስቸጋሪ ሕዝብን አርባ ዓመት በበርሀ የመራ፣ ጠላቶቻቸውን ተዋግቶ ያሸነፈ፣ በሕዝቡ ዓመፅ ከዐላማው ያልተሸነፈ መሪ ነበር እንጂ ትሑቱ ሙሴ ልፍስፍስ መሪ አልነበረም::

ሌላም ምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቧል፡፡ የዳዊት ታሪክ በትሕትና መምራት እንደሚቻል የሚያሳይ ነው:: "በልቡ ቅንነት ጠበቃቸው፣ በእጁም ብልሃት መራቸው" የተባለለት ዳዊት ሕዝቡን የመራቸው በኃይል፣ በተንኮል ሳይሆን በልቡ ቅንነት በመሆኑ የንግሥና ዘመኑ የሰላም ዘመን ነበረ:: እግዚአብሔር እንደ ልቤ ብሎ የጠራው በእግዚአብሔር ልብ የተመሰለ ትሑቱ ሰው ዳዊት፣ ቅንነትን ከብልሀት ጋር አጣምሮ የያዘ የተለያየውን ሕዝብ አንድ አድርጎ የመራ ጠላቶቻቸውን አሸነፎ አገሪቱን ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ የሰላም እና የመረጋጋት አገር ያደረገ መሪ እንጂ ደካማ መሪ አልነበረም፡፡ (1ኛሳሙ 13፥14) ከዚህ በተጨማሪ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ "እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና" ሲል መናገሩ ትሕትናና የዋህነት ያለውን ዋጋ የሚያሳይ ከመሆኑም ባሻገር ትሕትና የጥንካሬ እንጂ የደካምነት መገለጫ አለመሆኑን ያስረዳል:: (ማቴ 11፥29)

በአጠቃላይ ትሕትና ለመሪዎች ያስፈልጋል ወይም አያስፈልግም? የሚል አይደለም ጥያቄው:: እብሪተኛ፣ ትምክህተኛ ነህ መባልን የሚፈልግ ወይም ራሱን በዚህ መንገድ መግለጽ የሚፈልግ መሪ አይታይም:: ችግሩ ያለው በተግባር ትሑት መሆን እንዴት ይቻላል? የሚለው ነው እንጂ::

4.4 ትሕትናና በራስ መተማመን

በትሕትናና (Humility) በራስ መተማመን (Self Confidence) መካከል ያለውን ሚዛን መጠበቅ ከሚስተዋሉ ችግሮች መካከል በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚገባው ነው:: ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ የሚበረታታበት፣ ራስን ካልሸጡ፤ ከፍ ከፍ ካላደርጉ ስኬታማ መሆን አይቻልም ተብሎ የሚሰበክበት፣ ስልጠና የሚሰጥበት ዓለም እንደመሆኑም ትሕትና እንደ

ደካምነት፤ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግን በራስ እንደመተማመን ሊታይ ይችላል:: በአንድም በሌላም የሚሰበከው ራስን ከፍ ከፍ አድርጎ ማሳየት፣ ራስን መሸጥ፣ ራስን መካብ፣ መኩራራት ስኬታማ ለመሆን መሰላል ነው የሚለው አስተሳሰብ ነው[27]:: ራስን ዝቅ ዝቅ ማድረግ፣ ራስን አለመኮፈስ በራስ መተማመን እንደጎደለው እንደ ደካማ ሆኖ የሚነገርበት ጊዜ ቀላል የሚባል አይደለም::

ትሕትና ማለት ራስን መጣል ማለት ግን አይደለም:: በፈቃድ ራስን ዝቅ ማድረግና ራስን መጣል ልዩነት አላቸው:: ትሕትናና በራስ አለመተማመንም እንዲሁ የተለያዩ ናቸው::

ትሕትና በራስ መተማመንን አይከለክልምም:: ራስን ማወቅና በራስን መተማመን አስፈላጊ ነው:: ትሕትና ራስን ዋጋ ማሳጣት፣ ለራስ የሚገባውን ክብር አለመስጠት ለመርህ አለመቆም፣ መሥራት የሚገባውን አለመሥራት፣ መናገር በሚገባ ጊዜ አለመናገር ማለትም አይደለም:: ትሑት መሪ ትሕትናውን በራስ መተማመን እንደጎደለው ሰው፣ ትሕትናውን ለራሱ ያነሰ ዋጋ እንደሚሰጥ ሰው የሚወስዱ ስለሚኖሩ ይህን ጠንቅቆ የሚረዳና ነውና እንዲህ ላሉ ሰዎች በሚገባቸው ቋንቋ ማስረዳት የሚያስችል ዓቅም ያለው ማለት ነው:: እንዲያውም ቅዱስ መጽሐፍ የሚያስተምረው "ኃይልን በሚሰጠኝ በፈጣሪ ሁሉን እችላለሁ" ማለትን ነው:: "ማንም ታናሽነትህን አይናቀው" ነው የተባለውም:: (1ኛ ጢሞ 4፥12) "አትፍራ" የሚል ቃል የተነገረውም ብዙ ቦታ ነው:: ትልቁ ምስጢር ትሕትናን በራስ ከመተማመን ጋር አመጣጥኖ መያዝ ነው:: ትልቁ ጥበብ ትሕትናን ከቆራጥነት ጋር አመጣጥኖ መያዝ ነው::

እብሪት የሚመጣው በራስ መተማመን ከመጠኑ ሲያልፍ ነው:: በራስ መተማመን መጠኑን ሲያልፍ ድፍረት ይሰፍናል:: ቅዱስ ዳዊት "የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ" እንዳለ በራስ መተማመን መሬት ከለቀቀ የድፍረት ኃጢአት ሊያስከትል ይችላል:: (መዝ 19፥3) የድፍረት

[27] In most societies, self—confidence is widely regarded as a valuable individual asset, https://www.princeton.edu/~rbenabou/papers/papers/CONFQJE2.pdf

ኃጢአት ማለት በትሕትና መጥፋት ምክንያት የሚነገር፣ የሚሠራ ክፉ ድርጊት ማለት ነው:: አሁን ድፍረት በስፋት የሚታይበት ዘመን ላይ ስላለን ነገሩን ለመረዳት አይቸግርም:: የሚታየው ጭካኔ ሁሉ የድፍረት መገለጫ ነው:: ይሉኝታ፣ ላለማሳዘን መጠንቀቅ፣ ለሌላው ሞራል ማሰብ፣ በሌላው ጫማ ሆኖ ማሰብስ ምን ያህል የወረደበት ዘመን ነው? ታላቅን ማክበር አሁን ምን ያህል ዋጋ ይሰጠዋል? ሽማግሌን ለማዳመጥ ትዕግሥት ያለው ሰውስ ስንት ይገኛል? ይህ ሁሉ ሲደማመር ነው የድፍረት ኃጢአት ምን ያህል የበረከተበት ዘመን ነው የሚያሰኘው::

ምዕራፍ አምስት

ከሰው ጋር ተግባብቶ መሥራት

5 አብሮ መሥራት

ቅንነት ከሰው ሁሉ ጋር ተግባብቶ ለመሥራት ዓቅም ይሰጣል:: ቀና ልቦና፥ ቀና አስተሳሰብ፥ የዋህነት፥ ታማኝነት፥ ትሕትና፥ ፍትሐዊነት እና የመሳሰለው መልካም ስብዕና ከሰው ሁሉ ጋር ተግባብቶ ለመሥራት ያለውን ጠቀሜታ ምን ያህል እንደሚሆን ማሰብ አይከብድም::

ከሰው ሁሉ ጋር ተግባብቶ መሥራት በብዙ ተቋማት ወሳኝ ከሚባሉ እሴቶች መካከል የሚጠቀስ ነው:: ለጋራ ዐላማ በጋራ መሥራት መቻል በእርግጥም መተኪያ የሌለው ቁልፍ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል:: ለአንድ መሪ ለስኬታማነቱ ቀዳሚው ነገር ጠንካራ ሰዎችን በዙሪያው ማሰባሰብ መቻሉና፣ የሚመራቸውን ሰዎች በመግባባትና በመተባበር የጋራ ዐላማቸውን በጋራ እንዲያሳኩ ማስቻል ነውና::

“ኢትዮጵያውያን አብረው መብላት እንጂ አብረው መሥራት አይችሉም” የሚለው ምን ያህል ይገልጸናል? የሚለው ሊያከራክር የሚገባው ቢሆንም የሥራ አመራርን በተመለከተ በጥቅሉ አብሮ የመሥራት እሴታችን ደካማ እንደሆነ የሚገልጹ ብዙ ምልክቶች መኖራቸው ግን የሚካድ

አይደለም:: እንደሚባለው የሥራ አመራርን አብሮ የመሥራት እሴታችን ለምን ደካማ ሊሆን እንደቻለ፣ የድክመቶቹን ዐይነትና በዘመናት መካከል ያለውን እድገት ወይም ማሽቆልቆል መመርመር ሲቻል መፍትሔ ማምጣት ይቻላል:: በመሪዎች ዘንድ አብሮ የመሥራት ባህል ችግር የሆነው ለምንድን ነው? ለዘመናት በአንድ ዐላማ የተሰለፉ መሪዎች የሚካካዱት፣ በአንድ ጀምረው የማይዘልቁት ከምን የተነሣ ነው? በብዙ አገሮች አብሮ የመሥራት እሴት ጠንካራ ሲሆን በእኛ ዘንድ እንዲህ ከባድ የሆነበት ምክንያት ከምን የተነሣ ነው? የሚሉ እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ሰፊ ጥናት እና ውይይት የሚጋብዙ ቢሆኑም አብሮ መሥራት ያለመቻል ባህል በሰፊው የሚታይ ችግር ነው:: ችግሩን ከቅንነት መጉደል ጋር የሚያያዘውም ብዙ ነገር አለ:: በቡድን መሥራትና በቡድን መጠላለፍም ልዩነት አለው:: ለክፉ ሥራም መቧደን ይቻላል:: ለጥፋትም መተባበር ይቻላልና:: መሻኮቱም፥ መጠላለፉም በአመዛኙ በቡድን ነው የሚደረገው:: እንዲያውም በዝቶ የሚታየው እንዲህ ዐይነቱ መቧደን ነው ማለት ይቻላል::

አብሮ የመሥራት (Team Work) ተግዳሮት ከተቋማት ዐቅምና አሰራር ጋር የሚያያዝ ቢሆንም ምንጩ የጠባይ ችግር ነው ማለት ይቻላል:: ትዕቢት፣ ክርክር፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት በሚበዛበት አብሮ መሥራት ቀላል አይሆንም:: ተግባብቶና ተረዳድቶ በአንድነት መሥራት የሚቻለው ፍቅር፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት ሲኖር ነው:: ከሰው ጋር ተግባብቶ የመሥራት ክህሎት ቅንነትን፣ ሌላው ከእኔ ይሻላል የሚል የትሕትና አመለካከትን፣ ከራስ ክብርና ከግለሰብ ስኬት የሚበልጠውን ትልቁን ዐላማና የቡድን ስኬት ማስቀደምን፣ ጥቃቅን ልዩነትን ስለሚበልጠው ዐላማ ንቆ ወይም ታግሦ ማሳለፍን፣ የአሳብ ልዩነት ቢኖር እንኳ መቻቻልና ለልዩነት ቦታ መስጠትን ይፈልጋልም:: በእርግጥ ጠንካራ የቡድን አሠራር ጠንካራ ተቋምና ተቋማዊ አሠራር ከመኖርና ካለመኖር ጋር የሚያያዝ እንደሆነም የሚዘነጋ አይደለም::

የተሻለ አገርን ለመገንባት ዐላማ ያደረጉ ሁሉ አብረው መሥራት ቢችሉ የተሻለ መሆኑ ምንም ጥያቄ አያሻውም:: አብሮ መሥራት ካልተቻለ ግን

በረባ ባረባው መለያየት እየበዛ ውጤታማ ሥራ ሳይሠራ ይቀራል:: ይህ በሁሉም ዘርፍ፤ በሁሉም የመሪነት እርከን ያሉ መሪዎችን የሚመለከት ነው::

አንድን ተቋም ጠንካራ አብሮ የመሥራት እሴት መኖሩን ወይም አለመኖሩን እንዲሁም አንድን ቡድን ጠንካራ ወይም ደካማ ነው ለማለት ወይም ያለበትን ደረጃ ለመገምገም ከብዙ አቅጣጫ ማየትና፣ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ጠለቅ ያለ ምርመራ ማድረግ ተገቢ ነው:: የችግሩ ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም የችግሩ ዐይነት ከተቋም ተቋም ሊለያይ እንደሚችልም የሚጠበቅ ነው::

- የጋራ ግብ ኖሮት የጋራ ግብን ለማሳካት በአንድ አቅጣጫ የሚጓዝ ወይስ የጋራ ግብ የሌለው ለጊዜያዊ ጥቅም የተሰባሰበና በተለያየ አቅጣጫ የሚጓዘው፣ የግቡ መሳካት የሚያስጨንቀው ወይስ የራሱን ጥቅም የሚያሳድደው ይበዛበታል?

- ሽኩቻ ወይስ መተጋገዝ፣ መጠላለፍ ወይስ መደጋገፍ የትኛው ይበረታል? ምስጋናውን፣ መገሳውን ለእኔ ብቻ የሚለው ወይስ ድሉም ውድቀቱም የጋራ ነው የሚለው የትኛው ይበዛል?

- ምን ያህል መግባባት አለ? ባለመግባባት ጊዜ ይባክናል ወይስ መናበብ አለ? ከመጓተት የተነሣ ሥራ ይበደላል ወይስ ውጤታማ ለመሆን የሚያስችል ሁኔታ ነው ያለው? ምን ያህል ልብ ለልብ መግባባት፣ ምን ያህል መተማመን አለ? ተግባብቶና ተደማምጦ መሥራት የሚያስችል ሁኔታ ነው ያለው ወይስ አንዱ ሌላውን የሚሰልልበት? አንዱ ከሌላው እንዳይተማመን የተደገረበት የመጠራጠርና ያለመተማመን ሁኔታ ይበዛል?

- ምን ያህል መከባበር አለ? መመሰጋገን ወይስ ማጥላላትና መነቃቀፍ የትኛው ነው ሥር የሰደደው?

- ልዩነት ሲፈጠር ምን ያህል በመደማመጥ፣ አሳብ በማቅረብ አሳብን በአሳብ የማሸነፍና ልዩነትን ወይም አለመግባባትን በሰላም የመፍታት ዓቅም ወይም ልማድ አለ?

- አድሏዊነት፣ አግላይነት እንዳይኖር የሚያስችል አሠራርና የተቋም ባህል ምን ያህል ሥራ ላይ ውሏል? አንዱ በሠራው ሌላው የሚሸለምበት አድሏዊ አሠራር ወይስ ፍትሐዊነት የሰፈነበት ሁኔታ በዝቶ የሚታየው ምንድን ነው?

- ለመተባበር የሚያስችል አሠራር፣ አደረጃጀት፣ የመረጃ ፍሰት ነው ያለው ወይስ በተቃራኒው? ለመማር፣ ዕውቀትን ለማሸጋገር የሚያስችል አሠራርና ባህል አለ ወይስ ሁሉም በሩን ዘግቶ የሚሠራበት ሁኔታ ነው ያለው? የቡድኑ አባላት ከሥራው ጋር ምን ያህል የተመጣጠኑ ናቸው?

- ለሥራው ስኬት የሚያስፈልጉ ከተለያየ ሙያና አስተሳሰብ የተውጣጡ ሰዎች ተወክለውበታል ወይስ አንድ ዐይነት ሰዎች? አሳብን በነጻነት ለመግለጽ የሚያስችል፣ የተለየና አዲስ አሳብን የሚያብረታታ ወይስ ሁሉንም ነገር ከላይ ባሉ ሰዎች የተነገረውን ብቻ የሚፈጸምበት፣ አቤት ወዴት የሚሉ ሰዎች ብቻ የሚፈለጉበት፣ ማጨብጨብ ብቻ የበዛበት የትኛው ባህል ነው በዝቶ የሚታየው?

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮችን በየተቋሙ፣ በየሥራ ክፍሉ፣ በየቡድኑ መፈተሸና ችግሮችን በቅንነት እየነቀሱ ማውጣት ሲቻል ወደፊት አብሮ በመሥራት ረገድ መሻሻል ይኖራል::

በጥቅሉ በመግባባት፣ በመደጋገፍና በመረዳዳት አብሮ መሥራት ችግር የሚሆንባቸው ምክንያቶች ብዙ ናቸው:: እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ዘጠኝ ጉዳዮችን ዘርዘር አድርጎ መመልከት ይጠቅማል::

5.1 የዐላማ አንድነት አለመኖር

አብሮ የመሥራት ችግር መገለጫ ከሆኑ ነገሮች አንዱ የጋራ ዐላማ በሌለበት መሰባሰብ ሲኖር ነው:: የጋራ ዐላማ በሌለበት ለጊዜያዊ ጥቅም ሲባል አብሮ መሰለፍ በመሪዎች ተደጋግሞ ይታያልም:: ተባብረን የጋራ ጠላታችንን እንጣል የሚለው አንዱ የዚህ መገለጫ ሊሆን ይችላል:: ከዚያስ? የሚለውን የሚመልስ ዘላቂ ግብ ግን ላይኖር ይችላል:: ግቡ ጊዜያው ነው:: የየግል ዐላማችንን ለማሳካት የተለያየ ዐላማ ቢኖረንም ለመተጋገዝ ሲባል ብቻ አብረን እንሥራ በሚባልበት ጊዜ "ሌባ የሚጣላው ሲሰርቅ ሳይሆን ሲካፈል ነው" እንደሚባለው ጠቡ የሚጀምረው በለስ የቀና ዕለት ይሆናል:: ያን ጊዜ መለያየት ይመጣል:: በእርግጥም የዐላማ አንድነት በሌለበት እንዴት የአሳብ አንድነት ሊኖር ይችላል? የዐላማ አንድነት በሌለበትስ እንዴት አንድ ልብ መሆን ይቻላል? ብሎ መጠየቅም ተገቢ ነው:: የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ በመጨ የተያያዘ ነገር መላቀቁም አይቀርም:: የተቃረነ ዐላማ ይዞ ለአንድ ተልእኮ መሰለፍም አይቻልም:: የጋራ ተልእኮ ሳይኖር በአንድ ላይ ለመሥራት ሲሞከር በተቃራኒው ቡድን ላይ ከሚያቆጥረው ይልቅ በራሱ ቡድን ላይ ጎል የሚያስቆጥረው ሊበዛም ይችላል::

በጋራ ዐላማ መሰባሰብ በሌለበት እኛ እና እነርሱ በሚል መፋተግ ሊበዛ ይችላል:: ተደጋግሞ የሚታየውም እንዲህ ዐይነቱ ችግር ነው:: እኛ እና እነሱ የሚል ክፍፍል በሚበዛበት ሁኔታ መፍትሔው ላይ ይቅርና ችግሩ ላይ መስማማት እንኳ ከባድ ሊሆን ይችላል:: አንድን ችግር ሁሉም የሚያየው በጋራ ሳይሆን ከራሱ አንጻር ይሆንና አንድ ችግር የተለያየ ትርጓሜ ሊሰጠው ይችላል:: ችግሩን የጋራ አድርጎ የጋራ ግንዛቤና አረዳድ መፍጠር ባልተቻለበት ሁኔታ በመፍትሔው ላይም እንዲሁ መለያየት የሚጠበቅ ነው::[28]

[28] Members need to know, and agree on, what they're supposed to be doing together. Unless a leader articulates a clear direction, there is a real risk that different members will pursue different agendas. https://static1.squarespace.com/static/5ae63ba18f51303ed37a87a7/t/5c3759ac8a922d778016da1c/1547131312970/Teams.pdf

በአንድ ልብ መግባባት በሌለበት ሁኔታ በአንድ ላይ ለአንድ ዐላማ ተሰልፍን በሚሉ መሪዎች መካከል መከፋፈሉ ሰፍቶ "እኔ የእገሌ ነኝ" ፤ "እኔ የእገሌ ነኝ" የሚሉ ብዙ ቡድኖች ይፈጠሩና ፉክክሩ ይጠነክራል:: ጥናቶች የሚያሳዩትም ይህን የመሰለ ነገር ነው[29]:: ስኬታማ የቡድን ሥራ እንዲኖር በአንድ አሳብና በአንድ ልብ መግባባት ወሳኝ ነው የሚል ነው:: ሁሉም ትኩረቱን የዐላማው መሳካት ላይ ማድረግ የሚቻለው በጋራ ዐላማ መሰባሰብ ሲቻል ነው::

ለሁሉም የሚበጅ ዘላቂ ለውጥ ማምጣት የሚቻለው በሰለጠነው ዓለም በብዛት እንደሚታየው መቧደን በደምና በሥጋ በሰፈር ልጅነትና በቋንቋ መሆኑ ቀርቶ ሥራውን ማዕከል ያደረገ፣ በአሳብና በጋራ ዐላማ ላይ የተመሠረ አሰላለፍ ሲይዝ ነው የሚለው ነገር ሚዛን የሚዳፋው ከዚህ የተነሣ ነው:: በእርግጥ በዐላማ ለመሰባሰብ የሚታመንበትና ትርጉም ያለው ዐላማ ያስፈልጋል:: በአሳብ ዙሪያ ለመሰባሰብም አሳብ ያስፈልጋል:: ከጉልበት ይልቅ በአሳብ ልዕልና ማመንንም ይጠይቃል::

5.2 ብቻን የመሮጥ ዝንባሌ

ሰብሰብ ብሎ ከመሥራት ይልቅ ብቻን የመሮጥ ዝንባሌ ሌላው የችግሩ መገለጫ ነው:: አንድ ድርጅት የተመሠረተበት ዐላማ ከሌላው ድርጅት ዐላማ ጋር ተመሳሳይነት ካለውና ሁለቱ ድርጅቶች ቢጣመሩ ዐላማውን በተሻለ ፍጥነት ለማሳካት የሚያስችላቸው ከሆነ መጣመራቸው አዋጭ ይሆናል:: በብዙ ዓለማት የሚታየውም ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታን የሚያመጣ ነገር በተገኘበት ሁሉ መሰባሰብ ነው:: በፖለቲካው ዓለም፣ በንግዱ ዓለም፣ በሲቪክ ተቋማት፣ በሠራተኛ ማኅበራት እና በሌላውም እንዲህ ዐይነቱ ነገር ነው የሚታየው:: መሰባሰባችን የተሻለ ያደርገናል የሚል እምነት በብዛት የሚታይ ነው::

[29] Distance and diversity, as well as digital communication and changing membership, make them especially prone to the problems of "us versus them" thinking and incomplete information. The solution to both is developing a shared mindset among team members. https://hbr.org/2016/06/the-secrets-of-great-teamwork

“ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” የሚለው ብሂል ከቃል ባለፈ በተግባር በዝቶ የሚታየው እንዲህ ባሉ አገሮች ነው ማለት ይቻላል:: ቅዱስ መጽሐፍም የሚያስተምረን ይህንን ነው:: “ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል። ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና፣ አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሣው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት። ... በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም።” እንዲል:: (መክ 4፥9-12) የዚህ ቃል መልእክቱ ሁለት ነው። መቀናጀት ችግርን ለመቋቋምና ችግርን ለመሻገር ያስችላል የሚለው አንዱ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አንድነት ታላቅ ያደርጋል የሚለው ነው::

ለምሳሌ በየክልሉ ለአንድ ክልል ሕዝብ ቆመናል የሚሉ የፖለቲካ ድርጀቶች ዐላማችን የሚሉት የክልሉን ሕዝብ ኑሮ ማሻሻል፣ መልካም አስተዳደር ማምጣት፣ ማኅበራዊ እድገትን ማስፋፋት፣ ሰላምን ማረጋገጥ ከሆነ አንድ ዐላማ ያላቸው ሰዎች በአንድ ዐላማ መሰባሰብ ለምን ተቸገሩ? የሚለው ጥያቄ አብሮ የመሥራት ችግር መኖሩን ጠቋሚ ሊሆን ይችላል:: እርስ በርስ መሻኮታቸው እነሱንም እንመረዋለን የሚሉትን ሕዝብም እንደሚጎዳ በአንጻሩ ደግሞ መተባበራቸው የተሻለ ዓቅምን ሊፈጥርላቸው እንደሚችል ለማንም ግልጽ ነው:: ችግሩ ታዲያ ምንድነው? ከተባለ አብሮ የመሥራት፣ በአሳብ የመነጋገርና፣ በአሳብ ዙሪያ የመሰባሰብ፣ ከመሻኮት ይልቅ መተባበር እንደ ትልቅ ችግር ሆኖ መቀጠሉ ሊሆን ይችላል:: ችግሩን በመረዳት፣ በመተንተን እና አማራጭ መፍትሔዎች ላይ ልዩነት ስላለ ነው የሚባል ከሆነም እንዲህ ዐይነቱ ነገር የሚጠበቅ ነው:: ጥያቄ የሚሆነው እንዲህ ዐይነት ልዩነቶችን ቁጭ ብሎ መነጋገር፣ መደማመጥና በሚያግባቡ ጉዳዮች ላይ የጋራ ስምምነት ማድረግና በጋራ መሥራት ለምን አልተቻለም? የሚለው ነው እንጂ:: መሪዎች አንድ ሳይሆኑንስ የሚመሩትን ሕዝብ አንድ ማድረግ እንዴት ይችላሉ? መሪዎች ከጊዜያዊ የሥልጣን ጥም ባለፈ የረባ ዐላማ ባይኖራቸውና እንመረዋለን ለሚሉት ሕዝብ ባይገዳቸው ነው እንጂ ሊያሰኝ ይችላልም::

በተመሳሳይ ሁለት ተቋማት መናበብ ሲያቅታቸው አንዱ የሠራውን ሌላው ሲያፈርስ የሚታይበት ጊዜ ብዙ ነው:: በቅንጅት መሥራት ችግር የሚሆነው ለምንድን ነው? አንዱ ድርጅት ሲገነባ ሌላው ያንኑ ያፈርሰዋል፣ አንዱ ሲቆፍር ሌላው ይደፍናል:: አንድ ዐይነት ሥራ በተለያዩ ተቋማት ሲሠራ ማየትም እንግዳ ነገር አይደለም:: ለምን መናበብ አልተቻለም? ለምን አንድ ላይ ቁጭ ብሎ ማቀድ አልተቻለም? መቀናጀት የተሻለ ውጤት ለማምጣት እንዲሁም ወጭን እና ጊዜን እንደሚቀንስ የሚታወቅ ቢሆንም ይህ አለመሆኑ አብሮ የመሥራት ባህል ደካማ የመሆኑ አንዱ መገለጫ ሊሆን ይችላል:: ተቋማዊ አሠራርን ማጎልበት ዘላቂ መፍትሔው ቢሆንም አብሮ የመሥራት ባህሉ እስኪጎለብት ግን ለውጥ ማየትን አዳጋች ያደርገዋል::

በተመሳሳይ መሰባሰብና መጀመር ቢቻል እንኳ አብሮ መዝለቅ የሚችለው ከስንት አንድ ነው:: መሥራቹ ሊቀመንበር ሆኖ ካልቀጠለ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ ይበጠበጣል:: አሁን ደግሞ በቃህ ምክትል ወይም ተራ አባል ሁን ከተባለ ምክንያት ተፈልጎ ተቋሙን ማፍረስ የማይቀር ይሆናል:: አንድ የነበረው ተቋም ከሁለት ወይም ከሦስት ሲከፋፈል ማዬትም እንግዳ ነገር አይደለም:: ለአንድ ዐላማ ተሰልፈው ተማምለው የነበሩ ወዳጆች በዚህ ምክንያት መካሰስ ይጀምራሉ፤ መወነጃጀልም ይመጣል፤ በባላንጣነትም ይሰለፋሉ:: እንዲህ ዐይነቶች የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የንግድ ድርጅቶች፣ ማኅበራት ስንት አይተናል? ያልተከፋፈለ ስንት የፖለቲካ ፓርቲ ማግኘት ይቻላልስ?

የአሳብ ልዩነት ከተነሣም ተመሳሳይ ነው:: አሳባችንን እናቻችለው የሚል ብዙም አልተለመደም:: የአሳብ ልዩነቱ እስከ መገዳደል ያደርሳል:: እንዲህ ባለው ችግር ምክንያትስ ስንት ደም ፈሷል? ስንቱስ ተሰዷል?

5.3 መከባበርና መቻቻል

አብሮ መሥራት መከባበርንም ይፈልጋል:: አንዱ የሌላውን አሳብ ማክበር፣ በአሳብ አለመስማማት ሲኖር ደግሞ በሠለጠነ መንገድ መፍታት፣ አሳብን ባለማንቋሸሽ በአክብሮት መግለጽ መቻል፣ ይህ ሁሉ የሚቻለው መከባበር ሲኖር ነው:: "እንዲህ ባለ ምክንያት በዚህ አሳብ አልስማም" ማለት ሲቻል "ይህ ቆሻሻ አሳብ ነው፣ እንዴት እንዲህ ዐይነት አሳብ ይቀርባል፣ ይህ ካንተ የማይጠበቅ ነው" የሚል ማሸማቀቂያ በተለመደበት ሁኔታ አብሮ የመሥራት ባህል ችግር ቢገጥመው ለምን ይደንቃል!

እኔ ብቻ አውቃለሁ እኔን ብቻ ስሙኝ የሚለው፣ የእኔ አሳብ ካላሸነፈ የሚለው ሰው በሚበዛት ሁኔታም የቡድን ሥራ ደካማ ቢሆን የሚገርም አይሆንም:: የቡድን ሥራ እውን የሚሆነው መጠላለፍ ቀርቶ መደጋገፍ፣ መካሰስ ቀርቶ መመሰጋገን፣ የእኔ ብቻ የሥራ ውጤት ማለት ቀርቶ የእኛ የሥራ ውጤት፣ እኔ ብቻ አውቃለሁ ቀርቶ የሁሉም አሳብ፣ እኔ ያልኩት መፈጸም አለበት ማለት ቀርቶ ሌላው ከእኔ ይሻላል የሚል አመለካከት መሬት ሲረግጥ ነው:: እንዲሁም ጠንካራ የቡድን ሥራ ሁሉን አውቃለሁ ቀርቶ ሁሉም በየሙያው በየልምዱ የላቀ ዕውቀት አለው፣ የእኔ ስኬት ከማለት የእኛ ስኬት፣ እኔ ብቻ ያገባኛል ከማለት ሁሉም ያስፈልጋል ማለት ሲቻል ነው የሚመጣው:: እኔ አውቃለሁን ትቶ በሰከነ አእምሮ አንዱ ከሌላው ለመማር ልቡን ሲያዘጋጅ አብሮ የመሥራት ባህል ይጎለብታል::

አብሮ መሥራት መቻቻልንም ይፈልጋል:: መቻቻል የሚያስፈልገው ልዩነት ስላለ ነው:: ለአንዱ ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው በሌላው ዘንድ ትርጉም አልባ ሊሆን ይችላል፤ አንዱ የሚወደውን ሌላው ሊጠላው ይችላል፤ በአንዱ ዘንድ የሚከበረው በሌላው ዘንድ ብዙም ክብር ላይኖረውም ይችላል:: ይህ ሁሉ ልዩነት በሃይማኖት፣ በባህል፣ በአኗኗር፣ በቋንቋ ወይም በሌላ መንገድ ቢንጸባረቅ ከልዩነት የተነሣ የሚመጣ ነውና የሚደንቅ አይደለም:: ቁምነገሩ በመቻቻል በሰላም ከሁሉም ጋር አብሮ መሥራት መቻል አማራጭ የሌለው መሆኑን መገንዘቡ ላይ ነው::

ዘመኑ የብዝኃነት ዘመን መሆኑም የሚዘነጋ አይደለም:: በዚህ ዓለም ይበልጥ እየተሳሰረ ባለበት ሉላዊነት ዘመን ከአንድ አገር ሰዎች ጋር ብቻ ሳይሆን በእምነት፣ በቋንቋ፣ በባህል ጭራሹንም ከማይተዋወቁት ሰው ጋር አብሮ መሥራት በብዛት እየተለመደ ባለበት ብዝኃነትን ተረድቶ፣ ተቻችሎና ሁሉንም አክብሮ መሥራት መቻል ነው የስኬት አንዱ አስፈላጊ መስፈርት:: መቻቻል የሚመጣውም የአንዱ ነገር ሌላው ባይጥመው እንኳ ስለ ፍቅር ሲባል የሌላውን አክብሮ፣ የሚያስፈልገውን ተገቢ ዋጋ መስጠት ሲቻል ነው::

ብዝኃንት ማለት ግን ከዚህም ሰፋ ይላል:: ተቃራኒ አሳብ ካላቸው ሰዎች ጋር ተስማምቶ ለመሥራት እንዲሁም ልዩነትን በሰላም ለመፍታትም ይሁን አንድ በሚያደርግ ጉዳይ ለጋራ ዐላማ በጋራ ለመተባበር ትዕግሥትና ጥበብ የሚያስፈልግበት ዘመን ነው:: ተቃራኒ አሳብ በሚፈራበት ባህል፣ ልዩነትን አቻችሎ አሳብ እናጋጭና ጥሩ ነገር እንሥራ ማለት ብዙም አልተለመደም:: ከትንሹ ተቋም እስከ ትልቁ ድረስ የአሳብ ልዩነትን አቻችሎ የጋራ በሆነና በሚያግባባ ጉዳይ በጋራ የመሥራት ልምድ ምን ያህል ነው? የሚለውን መጠዬቅ ተገቢ ነው:: የተለየ አሳብ ያለው ሰው በጥርጣሬ የሚታየበትና እንዲህ የተለየ አቋም አለው፣ የተለየ አሳብ አለው የሚባል ሰው የሚገፋበት ክሥተት ማየት እንግዳ ነገር አይደለም:: ጠላት ወይም ተፎካካሪ የሚባለው ወገን ያለው አሳብና የእኛ አሳብ ያለው ልዩነት ምንድን ነው? እንዴት ተቀራርቦ መፍትሔ ማምጣት ይችላል? የሚለው መጎልበት ቢችል የት በተደረሰ የሚለው ቁጭት የሚሰማው ይህንን ሁሉ በማሰብ ሊሆን ይችላል::

ተቃራኒ አሳብ በሚፈራበት ባህል ለሁሉም ነገር የሚያጨበጭብ እንጂ እንዴት እንዲህ ይሆናል? የሚል ሰው ብዙም አይወደድም:: እንደ ገደል ማሚቶ አንድ ዐይነት ድምጽ የሚያስተጋባ እንጂ የተለየ አቅጣጫን፣ የተለየ እይታን ሊያሳይ ይችላል የሚባል ሰው ቦታ የለውም:: ጠንካራ መሪዎች ግን በራሳቸው የሚተማመኑ ናቸውና እሽ በጀ የሚሉትን ብቻ ሳይሆን ተቃራኒ አሳብ ያላቸውን ጠንካራ ሰዎችን በዙሪያቸው ማሰባሰብን አይፈሩም:: እንዲህ ዐይነቱ ነገር በሰለጠነው ዓለም የተለመደ ነው:: ማን

የተሻለ አሳብ ሊያመጣ ይችላል? ማን የተሻለ ዓቅም አለው? ማን ከዚህ ችግር ሊያወጣን ይችላል? የሚለው ነው እንጂ ፖለቲካው አስተሳሰቡ ወይም ሌላው መስፈርት ብዙም ሲያስጨንቃቸው አይታይም:: አንዳንዴም ተቀናቃኞቻቸውን እንኳ ለከፍተኛ ሓላፊነት ሲሾሙ ይታያል::[30]

በቡድን ሥራ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ሁሉም አሳቡን በነጻነት ያለፍርሃት እንዲሰጥ የሚያበረታታ ባህል በሚኖርበት ሁኔታ ይህን ብናገር ምን ይደርስብኝ? በሚል በፍርሃት መሸማቀቅ ስለማይኖር አሳብን በነጻነት የማከፈል እና አዳዲስ ሐሳቦችን ማፍለቅም ይቻላል::

5.4 ብልጣብልጥነት

ብልጣብልጥነት በበዛት ሁኔታ ጥሎ ማለፍ ባህል ይሆናል:: በዚህ ጊዜ አስመሳይነት፣ አሽቃባጭነት ይገናል:: ምን ያህል ጊዜ ነው ሌሎች በደከመበት ከምኑም ያልነበሩበት ጮሌዎች ምስጋናውንም፣ ሽልማቱንም፣ እድገቱንም እንደ ጭልፊት ጥርግርግ የሚያደርጉት? እንዲህ ባለ ሁኔታ የቡድን ሥራ ዐላማው በመተጋገዝ ሥራው እንዲሳካ ጥረት ማድረግ መሆኑ ይቀርና አንዱ ከሌላው በልጦ ለመታየት ያልተገባ ፉክክር ማድረግ ይመጣል::

ለጋራ ችግር የጋራ መፍትሔን በጋራ ሠርቶ ለማምጣት ተነሣሽነትና ትጋት የሚኖረው ፍትሐዊነት ሲኖር ነው:: አንዱ በደከመበት ያልደከመው የሚሸለምበት አድሏዊነት የሰፈነበት አሠራር እስካለ ድረስ ልብ ለልብ ተገናኝቶ በፍቅርና በመተማመን የሚሠራ ሰው ማግኘት ከንቱ ድካም ነው የሚሆነው:: ሌላውን መወጣጫ አድርጎ እንደ ሸንኮራ አገዳ መጦ መጣል ሲቀርና ስኬታችን የጋራ ነው፤ ውድቀታችንም የጋራ ነው የሚለው ሲበዛ አብሮ የመሥራት ባህል ይዳብራል::

[30] The reappointment of Bush's defense secretary, Robert Gates, reveals Obama's self-confidence. Appointing people like Clinton also shows his eagerness to harness the talent of his former opponents…. This suggests that president's own ability to absorb differing opinions. Off and Running: Barack Obama Jump-Starts His Team-https://static1.squarespace.com/static/5ae63ba18f51303ed37a87a7/t/5c3759ac8a922d778016da1c/1547131312970/Teams.pdf

በተመሳሳይ የቡድን ሥራ ሊጎለብት የሚችለው መተማመንም ሲኖር ነው። ብልጣብልጥነት ሳይሆን ፍትሐዊነት በሚኖርበት መተማመን ይጎለብታል። አንዱ ለሌላው ውድቀት ሳይሆን ለሌላው ማደግ እንደሚሠራ ሲታመን መተማመን አይጎድልም። ስሕተት ቢኖር እንኳ አለቃ ሠራተኛውን አሳልፎ የማይሰጥ፤ ሠራተኛውን የሚከላከለለት ሲሆን አሳልፎ አይሰጠኝም የሚል እምነት ይገነባል። አንዱ ለሌላው ችግር ሲደርስለት፣ ከግል ስኬት ይልቅ የቡድኑን ስኬት ሲያስቀድም፣ አብሮ የመሥራት ባህል ይገነባል። መተማመን ባለበት ላመኑበት ዐላማ በጋራ መሥራት ብቻ ሳይሆን በጋራ ለመሞትም መቁረጥ ይመጣል።

በአንጻሩ አንዱ ሌላውን በሚሰልልበት፣ አንዱ ሌላውን መውደቂያ ጉድጓዴን የሚቆፍርልኝ ነው ብሎ በሚጠራጠርበት ሁኔታ የጋራ ዐላማ ቢኖርም የልብ አንድነት፣ የአሳብ አንድነት ስለማይኖር ውጤታማ የቡድን ሥራ ማምጣት ከባድ ነው የሚሆነው። በመጠራጠር አንዱ ሌላውን ይሰልለኛል በሚል የፍርሃት ቆፈን ከተያዘ ከመግባባት ይልቅ መፈራራት ነው የሚነግሠው።

5.5 ማጣጣል

መመሰጋገን ያን ያህል አለመደብንም ይባላል። አንዱ የሠራውን ሌላው የማድነቅ ሳይሆን የማንቋሸሽ፣ የማናናቅ ልማድ ከበዛም የቡድን ሥራ ደካማ ሊሆን ይችላል። በአደገው ዓለም ከሚወደዱ ነገሮች በቀዳሚነት ሊነሣ የሚገባው የመመሰጋገን ባህሉ ነው። ልጆች አፋቸውን የሚፈቱት አመሰግናለሁ በሚለው ቃል ነው የሚመስለው። በጎ ነገር በታየበት ሁሉ “አመሰግናለሁ” ፣ ስሕተት ነው ተብሎ ሲታሰብ ደግሞ “ይቅርታ” ማለት ከመለመዱ የተነሣ የሁሉም የጋራ ቋንቋ ሆኗል ያሰኛል።

በሥራ ዓለምም በጋራ የሚሠራው ሥራ እየበዛ በመጣበት ሁኔታ አንድ ሰው አስተያዬት ወይም ግብረ መልስ ሲያቀርብ ከአሉታዊው ሳይሆን ከምስጋና ነው የሚጀምረው። ጠንካራውን ሥራ በማድነቅ፣ በማመስገን መጀመር የተለመደ ነው። በቡድን ሥራ መመሰጋገን፣ አንዱ ሌላውን

ማበረታታትም እንዲሁ ጠንካራ ባህላቸው ነው:: ምንም ይሁን፣ ማንም ይሥራው ጥሩ ሥራ ከታዬ የሚያበረታታተው ሰው ከእየአቅጣጫው ነው የሚጎርፈው:: ሞራልና ድጋፍ የሚሰጥና፣ የሚያበረታታ በበዛበት ሁኔታ ነው ዓለምን የሚቀይሩ ብዙ አዋቂዎችንና ብዙ ኮከብ ሰዎችን ማግኘት የቻሉትም:: እንዴት ጠልፈን እንጣለው የሚል ባህል ሳይሆን በዝቶ የሚታየው በዚህ በጎ ሥራ ማጎበረሰቡ የሚጠቀም ከሆነ፣ አገራቱ የምትጠቀም ከሆነ እንዴት እናግዘው የሚል ነው የሚመስለው:: እንዲህ ባሉ አገሮች ችግሩ አይኖርም ማለት ሳይሆን ሁሉም ነገር በአንጻራዊነት ከታዬ ለማለት ያህል ብቻ ነው::

በእኛ ዘንድ ልቆ የሚታየው የትኛው ነው? አስተያየት ሲሰጥ ከምስጋና ወይስ ከማጥላላት ነው የሚጀምረው? የተሻለ ሰው ሲገኝ ጠልፎ መጣል ወይስ ማበረታት ነው የሚቀድመው? ልዩነት ሲኖር ክብር ባለው መንገድ አሳቡን ከሰው በመለየት ወይስ አሳብንና ሰውን በመጨፍለቅ ነው አስተያየቱ የሚሰጠው? በቡድን ሥራ ከታችኛው አካል እስከ ላይኛው፣ ከትልቁ እስከ ትንሹ ያለውን አስተዋጽዖ የመገንዘብና የማመስገን ወይስ ሁሉም ሥራ የጥቂት ሰዎች አስተዋጽዖ የማስመሰል? ይህ ሁሉ ጠለቅ ያለ ዳሰሳ የሚፈልግ ነው::

ጥሩ ለሠራ ምስጋና ሲኖር ለበለጠ ሥራ ጉልበት ይሰጣል:: የተሻለ ሥራ ሲሠራ፣ ሥራው በጅምር እንዳይቀር ከሚያደርጉት ነገሮች ትልቁን ቦታ የሚይዘው ሞራል ነው ማለት ይችላል:: ምስጋና የሰው አእምሮን ያነቃቃል፤ ደስታንም ጉልበትም ይሰጣልና:: የተሻለ መሥራት ዋጋ እንዳለው ሲያስቡ የበለጠ እንዲተጉ ስለሚያደርግ ምስጋና ለማትጋት ያለው ሚና ወሳኝ ነው::

የመመሰጋገን ሳይሆን የመነቃቀፍ ባህል ባለበት፣ መልካም ሥራ ተሠርቶ የሚያጣጥለው ሰው በሚበዛበት ሁኔታ ለበለጠ ሥራ መነሣሣት እንዴት ሊኖር ይችላል? ከሚያበረታታው ይልቅ አቃቂር የሚያወጣው ሰው በሚበዛበት ሁኔታ የተሻለ ለመሥራት የሚፍጨረጨረው ሰው ተስፋ መቁረጡ፣ ምስጋና ለሌለው ነገር ምን አደከመኝ ማለቱ የሚጠበቅ ነው::

የማጣጣል ባህል የሚጎዳውም ለበጎ ሥራ የሚተጉትን ብቻ ሳይሆን አገርንም ጭምር ሊሆን ይችላል። ከመመሰጋገን ይልቅ ማጣጣል፣ ከመሞጋገስ ይልቅ መነቃቀፍ፣ ከማበረታታት ይልቅ ጎትቶ መጣል በሚበዛበት ሁኔታ ተስፋ የሚቆርጠው ስለሚበዛ፣ ሞራሉ የደቀቀ እርስ በርሱ የማይተማመን የቡድን ሥራ ደካማ የሆነበትን ከባቢ ሊፈጥር እንደሚችል የእኛው ታሪክ በቂ ማሳያ ሊሆን ይችላል።

5.6 ተግባቦት ሲጎድል

ተግባቦት (Communications) የሚፈለግበት ቦታ ብዙ ቢሆንም አብሮ ለመሥራት ግን ቁልፍ ክህሎት ነው። ተግባቦት ሲጎድልም ጉዳቱ የዚያኑ ያህል ይሆናል። በቡድን ሥራ ውስጥ መግባባት ሲጠፋ የማያግባባ ብዙ ጉዳይ አለ ማለት ላይሆን ይችላል። ከችግሩ በላይ የሚፈጠረው ብሽቦታ ላለመግባባቱ ዋናው ምክንያት ነው የሚሆነው። "እንዲህ ዐይነት አስተያየት የሰጠው እኔን ለመንካት ነው፤ የእኔን አሳብ ውድቅ ያደረገብኝ እኔን ለመበቀል ነው" የሚል ነገር የተለመደ ነው። እንዲህ ዐይነቱ ነገር ሁሉም በየፊናው በሚያስብበት፣ በግልጽ መነጋገር ባህል ባልሆነበት ሁኔታ የሚፈጠር ችግር ሊሆን ይችላል። በሌላ ጊዜም አስተያዬት የሚሰጥ ሰው ተናጋሪው የተናገረውን ሳይሆን ራሱ ለመናገር የፈለገውን በመሰለውና በፈለገው መንገድ ሲናገር በተናገሪው ላይ የሚፈጥረው ቅሬታና ግርታ ተደጋግሞ የሚታይ ክሥተት ነው።

ጥሩ አሳብ በአነጋገር መወላገድ ምክንያት ነገር ሲያፈርስ ማየትም የተለመደ ነው። "እንዲያው እኮ ልቡ የዋህ ነው፣ አፉ ነው እንጂ ጉድ የሚሠራው" የሚባል አነጋገርም ተናጋሪው ተግባቦት ያንስዋል ማለትን ያመለክታል። እንዲያው "የምናገረው ሁሉ በመጥፎ እየተተረጎመ ከሰው ጋር ያጣላኛል" የሚባል ነገር መስማትም እንግዳ ነገር አይደለም። ችግሩ ከአተረጓጎሙ ብቻ ላይሆን ይችላል። ንግግሩ ሲወላገድ የተጣመመ ትርጉም ማስከተሉ የሚጠበቅ ነውና። ለምሳሌ ለስለስ ብሎ ቢቀርብ ቀልብ የሚገዛ አሳብ በቁጣ ከቀረበ ሰው ሊያስቀይም ይችላል።

ተግባቦት ብዙ ነገርን የሚያካትት ነው:: በቂ መረጃ አይሰጠንም፤ መረጃ በወቅቱ አይሰጠንም፤ አሠራሩ ግልጽ አይደለም፤ በመሪዎች ዘንድ ግልጽነት አይታይም፤ የሚሰጠው መረጃ ሐሰተኛ ነው የሚለው ሁሉ የተግባቦትን ችግር ነው የሚያመለክተው:: መነጋገር ሲገባ ሐሜትና አሉባልታው አሉህ አሉሽ ሲበዛም ትንሹ ነገር እያገዘፈ ለጥል ለጦርነት ምክንያት ይሆናል:: ግልጽነት ባህል ባልሆነበት ሁኔታ የሚደበቀው መረጃ በሚበዛበት፣ ያልተደረገው ተደረገ ያልተሠራው ተሠራ ስለሚያሰኝም ብዙ መራራቅን፣ የልብ መሸፈትን ያስከትላል:: መልካሙን ነገር አጣሞ የሚናገር ወይም መልካሙን ከመናገር ጠማማውን የሚያስቀድም፣ የተነገረውን ገልብጦ የሚሰማ ሲበዛም የሚያጣላ ነገር ሳይኖር ጠብ ሊበረታም ይችላል:: ይህ ሁሉ ሲደማመር ነው እንግዲህ የተግባቦት እጦት አብሮ ለመሥራት እንቅፋት የሚሆነው::

5.7 መካረር

የመካረር ልማድ መኖሩን የሚያሳዩ መገለጫዎችም አሉ:: ሰከን ብሎ ከመነጋገር ይልቅ ዱላ ቀረሽ ንግግር በሚቀድምበት ጊዜ መካረር ይኖራል:: በቀረበ ጉዳይ ላይ ከመነጋገር ይልቅ፣ ክርክሩ ከጉዳዩ አቅራቢ ወይም ከአሳቡ ባለቤት ጋር በሚሆንበት ጊዜም መካረር ይመጣል:: ጉዳዩ ይረሳና በግለሰቦች መካከል ክፉ ቃል መወራወር፣ መወነጃጀል፣ መካሰስና ጣት መቀሳሰር የዚህ ውጤት ሊሆን ይችላል:: ቀልድ እምብዛም በማይታይበት፣ ሁሉም ነገር ድርቅ ያለ ንግግር በሚሆንበት ሁኔታ ውጥረት ይበዛል::

ምን ያህል ስብሰባዎች ናቸው በውጥረት የሚሞሉት? ከመካረሩ የተነሣ አንዳንዱም ቡጢ ይታይበታል:: ሌላው ቢቀር በሚዲያ እንኳ ከሚታዩ ውይይቶች ምን ያህሉ ናቸው በቁጣና በመጯጯህ የሚሞሉት? መካረሩ ከምን የተነሣ ነው? ከመካረርና ከመጯጯህ ይልቅ መደማመጥ የማይቻለው ለምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ ጠለቅ ያለ ምርመራ የሚያስፈልገው ቢሆንም ሰውንና አሳብን ለይቶ ማየት ካለመቻል ሊመጣ ይችላል:: አሳብ ሳይኖርና በአሳብ ማሸነፍ ሲሳን በመጮህ፣ አሳብ ያለውን

ሰው በመዝለፍና በማስፈራራት ማሸነፍ ይቻላል በሚል እምነት መካረር ሊከሰት ይችላልም:: የተደበቀ ቂምና ጥላቻን ይዞ ወደ ውይይት ሲገባ፣ ቁጣ ከፍ ሲል፣ ንዴት ሲያይል ቀላል የሆነው ጉዳይ ከቁጥጥር ውጭ የመሆን እድሉም ከፍ ያለ ይሆናል::

ቁጣ፣ ንዴት በሳይንሱም በመጽሐፍ ቅዱስም ብዙ የተባለለት ነው:: ራስን መግዛት አለመቻልም እንዲሁ:: በጥላቻ መካከል፣ ቁጣ የሚጠበቅ ነው:: ቁጣ ደግሞ ትዕግሥት አያውቅም:: ማመዛዘን የሚቻለው የሰከነ፣ የተረጋጋ፣ ከቂም በቀል፣ ከጥላቻ የራቀ ስሜት ሲኖር ነው:: ንዴት ባለበት ማስተዋል ይጠፋል:: ለመደማመጥ፣ አንዱ የሌላውን ብሶት ለመስማት የፈጠነ ለቁጣ የዘገየ ሊሆን ይገባል:: በጋለ ስሜት፣ በቁጣ ላይ ሆኖ አለመግባባትን ለመፍታት መሞከር በእሳት ላይ ጋዝ እንደ ማርከፍከፍ የሚሆንበት ጊዜም ቀላል አይደለም::

“ሰነፍ ሰው ቊጣውን ሁሉ ያወጣል፣ ጠቢብ ግን በውስጡ ያስቀረዋል” እንዲልም ቁጣን መቆጣጠር አለመቻል ደካምነት ነው:: (ምሳ 19፥11) ቁጣን መቆጣጠር፣ ራስን መግዛት፣ ቅሬታን በቁጣ ከመግለጽ ይልቅ በሰላማዊ መንገድ መግለጽ ነው አስተዋይነት:: ቅሬታን በቁጣ ከመግለጽ ይልቅ በሰላማዊ መንገድ መግለጽ መሰልጠንም ነው:: ቁጣ ክፉ በሽታ ነው የሚባለውም ያለ ምክንያት አይደለም:: “ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቊጣም የዘገየ ይሁን” እንዲል መድኃኒቱ ደግሞ መታገስ መቻል ነው:: (ያዕ 1፥19) ስሜትን ገዝቶ ቁጣን ማስታገስ ካልተቻለ ልጓም የሌለው በቅሎ፤ ፍሬን የበጠሰ መኪና እንደማለት ነው::

“መራርነትና ንዴት፣ ቁጣም፣ ጩኸትም፣ መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ” እንደተባለ ለመደማመጥና በጋራ ሠርቶ የጋራ መፍትሔን ለማምጣት መራርነትን ማስወገድም ጠቀሜታ አለው:: (ኤፌ 4፥31-32)

በአጠቃላይ ከመካረር ይልቅ ለዛ ያለው ውይይት፣ በንግግር መሐል ቀልድ ጣል ማድረግ ነገርን የማለዘብ ዓቅም አለው:: መሪዎች ብዙ ጊዜ ስኬታማ ለመሆን ከሚያግዛቸው ነገሮች አንዱ እንዲህ ዐይነት ችሎታ

ያላቸው መሆኑ ነው:: በፈረንጆቹ ለዛ ያለው ንግግር ወይም ቀልድ ጣል ማድረግ (Sense of Humor) በሚል የሚጠሩት ማለት ነው:: ለዛ ባለው ንግግር ዘና የሚያደርግ ከባቢን ከመፍጠር በተጨማሪ የሥራ ቅልጥፍናን እና መቀራረብን እንደሚጨምር ነው ጥናቶች የሚያሳዩት[31]::

5.8 ፍረጃ

እገሌ ከተናገረ ከአፉ መልካም ነገር አይወጣም፤ የእነ እገሌ አቋም የታወቀ ነው፤ የተናገረው ነገር እንዲህ ቢሆንም ለማለት የፈለገው ግን እንዲህ ነው፤ የእርሱ አሳብ ሁሌም የታወቀ ነው እና የመሳሰሉት አስተያየቶች ናቸው ፍረጃ የሚባሉት:: እገሌ የዚህ ብሔር አባል ነው ስለዚህ የሚናገረው እንዲህ ቢሆንም አሳቡ ግን የብሔሩን አቋም የሚያንጸባርቅ ነው፤ እገሌ የዚህ የፖለቲካ ፓርቲ አባል ወይም ደጋፊ መሆኑን አትርሱ የሚያስተላልፈው በተዘዋዋሪ ቢሆንም የፓርቲውን አሳብ ነው፤ እገሌ ደግሞ የዚህኛው እምነት ተከታይ ስለሆነ ሌላ ምን ሊናገር ይችላል የሚል ፍረጃም የተለመደ ሆኗል::

እንዲህ ዐይነት አመለካከት ሲኖር ነው ሰውን በግለሰብነቱ ከመለካት ይልቅ በጎሳው፣ በፖለቲካ አመለካከቱ፣ በሃይማኖቱ፣ በጸታው፣ በሙያውና ይህንን በመሰለው መስፈርት በጥቅሉ የመፈረጅ ዝንባሌ የሚመጣው:: ያለንበት ዘመን እንዲህ ዐይነቱ ነገር በዝቶ የሚታይበት ስለሆነ ችግሩን ለመረዳት አይከብድም:: አንድ ሰው ከቤተሰቦቹ የተለየ አስተሳሰብና አመለካከት ቢኖረው ለምን ይደንቃል? እንኳን አይደለም ከጎሳው ከቡድኑም የተለየ ቢሆን:: ሰው መቼም ሮቦት አይደለም:: እያንዳንዱ ሰው ልዩ ሆኖ ተፈጥሯልና እንደ ግለሰብነቱ የራሱ እምነት፣ የራሱ አመለካከት፣ የራሱ አስተሳሰብ ቢኖረው እንዴት እንግዳ ነገር ሊሆን ይችላል? መፈራረጅ በሚበዛበት በአሳብ እየተሸናነፉ አብሮ መሥራትስ እንዴት ይቻላል? የሚሉትን መጠየቅ ያስፈልጋል::

[31] Leading with Humor, https://hbr.org/2014/05/leading-with-humor

የመፈረጅ ዝንባሌ በሚያይልበት ሁኔታ መግባት አዳጋች ይሆናል:: “እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፣ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፣ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል:: በወንድምህም ዐይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፣ በዐይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም? ወይም ወንድምህን ከዐይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም፣ በዐይንህ ምሰሶ አለ። አንተ ግብዝ አስቀድመህ ከዐይንህ ምሰሶውን አውጣ፣ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዐይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።” የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መፈረጅ የሚያስከትለውን ጉዳት የሚያመላክት ነው:: (ማቴ. 7፥1-5) ፍረጃ ነው አንዱ የግብዝነት መገለጫም:: ፍረጃ ሙሉ እይታን ይጋርዳል:: አንድ አሳብ በጎ አሳብ መሆኑ ወይም አለመሆኑ ሳይመረመር ገና በሩቁ መፈረጅ የሚከሰተው አጥርቶ ማየት ስለማይቻል ነው “አስቀድመህ ከዐይንህ ምሰሶውን አውጣ” የተባለው::

አብሮ የመሥራት ባህል ጠንካራ በሆነባቸው አገሮችና ተቋማት ሰውን የመፈረጅ ዝንባሌ አነስተኛ ነው ማለት ይቻላል:: ጠንካራ የቡድን ሥራ ባህል በሆነባቸው አገሮች “ምን ለማለት እንደፈለግህ እባክህ አብራራልን” ይባላል እንጂ፣ “ለመናገር የፈለከውን አውቂያለሁ” የሚል ጥንቆላ የሚመስል አስተያየት መስጠት ነውር ነው:: ለመረዳት መሞከር፣ በቂ ማብራሪያ ለማግኘት መጠየቅ ሲገባ አስቀድሞ እንዲህ ማለት ፈልጎ ነው፣ የእርሱ አቋም የታወቀ ነው፣ ይህ ሰው ጠላታችን ነው፣ እንዲህ ዐይነት ሰው ያስጠላኛል፣ ለማዳመጥ ትዕግሥት የለኝም የሚል አሳብን ማስቀደም አንዱ የፍረጃ መገለጫ ነው። እንዲህ ዐይነቱ ልማድ በነገሠበት ሁኔታ መግባባት አስቸጋሪ ነው የሚሆነውም::

በሌላ በኩል ሰውን በሀብት፣ በቋንቋ፣ በብሔር፣ በአለባበስ፣ በደጋፊ ብዛት በማዕረግ የመለካት ዝንባሌ የተለመደ ነው:: “እስኪ እናዳምጠው ታዋቂ ሰው ነው” የሚባለውን ያህል “ይሄ ደግሞ ማን ነው? ብዙም አይታወቅም እንዴት ሊሆን ይችላል?” የሚል ፍረጃ እንግዳ ነገር አይደለም:: “ከናዝሬት መልካም ነገር እንዴት ሊወጣ ይችላል?” እንደተባለው ዐይነት ሁሉንም ነገር በሩቅ የመፈረጅ አባዜ ሲጸናወት የሚመጣ ነው:: የማጣጣል ችግር አንዱም ከዚህ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል:: ሥራውን ሳያዩ በሩቅ

የማመስገን፣ ሥራውን ሳያዩ በሩቁ የማጣጣል፣ በስሚ ስሚ የመጥላትና የመውደድ፣ አንዱን የማሳነስ ሌላውን የማግዘፍ፣ አንዱን የመንቀፍ ሌላውን የማጀገን ልማድ ምን ያህል ነው? እንዴትስ ከእንዲህ ዐይነቱ ችግር መውጣት ይቻላል? የሚለው ግን ሰፊ ውይይትን የሚፈልግ ሊሆን ይችላል:: በአለባበሱ፣ በአነጋገሩ፣ በደጋፊው ብዛት፣ በሀብቱ፣ በአድናቂ ብዛት ሰውን የመስቀል፣ ሰውን የማውረድ ታሪክ እንግዳ ነገር አይደለም:: በአሁኑ ጊዜ በሥራ አመራር ድንቁርና (Unconscious bias) በመባል ምርምር የሚደረግበትና ስልጠና የሚሰጥበት ነው:: እንዲህ ዐይነቱ ነገር በሥራም በሕይወትም በሰፊው የሚያጋጥም ሲሆን ብዙ ተጽእኖም የሚያስከትል ሊሆን ይችላል[32]:: አደገ በሚባለው ዓለም ጭምር መሻሻል ቢታይበትም አሁን ድረስ በጾታ፣ በቀለም፣ በቋንቋ፣ በዘር አድሏዊነት የሚታየው እንዲህ ባለው ምክንያት ጭምር ነው::

5.9 አሳብን ከሰው ለይቶ ማየት

አሳብን በአሳብ ከማሸንፍ ይልቅ በአሳብ መሸነፍ እንደመረታት፣ እንደ ግለሰብ ሽንፈት፣ አንዳንዱም እንደ ውርደት የሚቆጠርበት ጊዜ አለ:: አሳብን መንቀፍ ሰውን ከማዋረድ ጋር ተቀላቅሎ በሚታይበት ሁኔታ አለመግባባት የመፈጠር እድሉ ከፍተኛ ነው የሚሆነውም:: "አሳቤን ተቃወመኝ፤ አሳቤን ውድቅ አደረገብኝ" ከማለት ይልቅ "ጉድ ሠራኝ፤ ሆን ብሎ እኔን ለማጥቃት የሰነዘረው አሳብ ነው" የማለት ዝንባሌ ሲያመዝን አሳቡ የተሸነፈበት ሰው ወደ ቂምና ጥላቻ ከፍ ሲልም ወደ በቀልና የኃይል ርምጃ በመሻገር መካረሩ በርትቶ እስከ መገዳደል ሲያደርስ የሚታየው እንዲህ ባለው ሁኔታ ሊሆን ይችላል::

[32] Our Baises affect our lives and work, http://documents.manchester.ac.uk/display.aspx?DocID=26064

ሰለጠኑ በሚባሉ አገሮች ምንም ያህል ሲጫጫኹ ቢውሉ፣ ምንም ያህል መዘላለፍ ቢኖር እንኳ አሳቡ ውድቅ እንዳይደረግ የተሻለ አሳብን ማምጣት እና በአሳብ መርታት መሞከር እንጂ ግለሰባዊ አድርጎ የመውሰድ፣ እንዲህ ባለው የጠነከረ ንግግር የመቀየም ልማድ እምብዛም አይታይም:: ከዱላ ቀረሽ ክርክር በኋላ በጓደኝነት መሳሳቅ፣ በጓደኝነት መብላት መጠጣትም የተለመደ ነው::

አሳብን መደገፍ ወይም መቃወም የአሳቡን ባለቤት ከመደገፍ ወይም ከመቃወም ጋር መያያዝ የለበትም የሚለውን ከመረዳት የመጣ ሊሆን ይችላል:: የምደግፈው ሰው አሳቡ የተሳሳተ ከሆነ አሳቡን መንቀፍ ሰውዬውን እንደመጥላት ተደርጎ ከተወሰደ ችግር የሚሆነው ያን ጊዜ ነው:: ጠላት የሚሆነው ሰውዬው የያዘው አሳብ እንጂ ሰውዬው ሊሆን አይችልም:: አሳብን በአሳብ ማሸነፍ፣ በአንድ ሰው አሳብ አለመስማማት ሲፈጠር እንደ ሰለጠኑ ሰዎች "በአሳቡ አልስማም ነገር ግን ከአክብሮት ጋር ነው" ብሎ መግለጽ ሲቻል የአሳብ ልዩነት የሰዎች ተቃርኖ መሆኑ ይቀራል:: ችግር የሚሆነው በአሳቤ ያልተስማማ ወይም አሳቤን የተቃወመ ሁሉ እንደ ጠላት የማዬው ከሆነ ነው:: በአሳብና በአሳቡ ባለቤት መካከል ያለውን ልዩነት በአግባቡ ማየት ካለመቻል የተነሣ አሳብን በጉልበት ለማፈን መሞከር ይጀመራል:: መሪዎችም በአሳብ ዙሪያ ከመወያየት ይልቅ የተለየ አሳብ ያለውን ሰው እንዴት እንደሚያጠፉ የሚመክሩ ከሆነ ነው ችግር የሚሆነው::

አሳብን በአሳብ ማሸንፍ የማይችሉ ሰዎች "የፈሪ ዱላ" እንደሚባለው የሚቀድማቸው ሰውን ጥላሸት መቀባት ነው:: አሳቡን በአሳብ መርታት ሲሳናቸው የስድብ መዓት ያወርዱበታል፣ የአሉባልታና የፈጠራ ወሬ ከየቦታው ተለቃቅሞ እንዳይነሣ ሆኖ ይከመርበታል:: ተሳዳቢዎችን የተሻሉ ሰዎች ባያደርጋቸውም ይህ የክፉዎች አሳብ፣ የደካሞች ስልት ጥላሸት በሚቀባው ሰው ላይ ግን ብዙ ጉዳት ማድረሱ አይቀርም:: ጥላሸት በመቀባትና የሰውን ስም በማጥፋት ላይ የተመሠረተ ልማድ ሲኖር ትኩረት የሚደረገው የተሻለ አሳብን በማመንጨት ሳይሆን ሰውን

ጠልፎ ለመጣል በሚሠራ የክፋት ወሬ ላይ ይሆናል:: በእርግጥ በአሳብ ማሸነፍ የሚቻለው አሳብ ሲኖር ነው::

በአሳብ ልዕልና የማመን ባህል ደካማ የሆነው ለምንድን ነው? የሚለውን በጥሞና መመርመር ካልተቻለ ወደፊትም መሻሻል ላይኖር ይችላል::

አሳብን በአሳብ የመርታት፣ በአሳብ ዙሪያ በግልጽነት የመወያየት፣ በአሳብ ልዩነት ምክንያት ወደ ግጭት አለማምራት የሚቻለው ምን ቢደረግ ነው? የሚለው ላይ ትኩረት ቢደረግና ተጨባጭ ሥራ መሥራት ቢቻል ለውጥ ሊመጣ ይችላል:: አስተዳደጋችን በአሳብ ዙሪያ በነጻነት ላለመነጋገር ምን ያህል ነው ተጽእኖ ያደረገው? የትምህርት አቀራረቡና በተማሪና በአስተማሪ መካከል ያለው ግንኙነትስ? በሃይማኖት ተቋማት መሪዎችና በተከታዮቻቸው መካከል በአሳብ ዙሪያ ለመወያየት ያለው ነጻነትስ ምን ይመስላል? እነዚህ ሁሉ ጠለቅ ያለ ዳሰሳና ግልጽ ውይይትን የሚፈልጉ ጉዳዮች ናቸው:: በአሳብ ነጻነትና በግልጽነት ከሚታወቁ አገሮችም በጎ ተሞክሮን በመወሰድ ጭምር በጉዳዮቹ ላይ ተቋማዊና ዘላቂ ሥራዎች በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብ፣ በእምነት ተቋማት፣ በትምህርት ቤት፣ በፖለቲካውና በሌሎች መሪዎች ጠንካራ ሥራ መሥራት ካልተቻለስ ለውጥ እንዴት ሊመጣ ይችላል? ትልቅ ጥያቄ መሆን ያለበት ይህ ነው::

በአጠቃላይ ችግሮች የበለጠ እየተወሳሰቡ፣ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በግል ከመሮጥ ይልቅ በቡድን የመሥራት ባህል እያደገ ባለበትና የቴክኖሎጂ እድገቱም ለዚህ እየተመቸ በመጣበት በአሁኑ ጊዜ ብቻን የሚሮጥበት ዘመን አይደለም:: ለእያንዳንዱ ሥራ የተሻለ ዕውቀት፣ ልምድና ክህሎት ያለው የሠለጠነ ባለሙያ በሚፈለግበት ዘመን አንድ ወይም ሁለት ሰው ከሚሠራው ሥራ በቡድን የሚሠራው ሥራ እንደሚበዛም የሚታወቅ ነው:: በአሁኑ ጊዜ ከግል ችሎታ ይልቅ ከሰው ጋር ተግባብቶና ተረዳድቶ በፍቅር የሚሠራ ባለሙያ ተመራጭ ሆኗል:: ጊዜው አሁን የቡድን ሥራን የሚሻ ነው:: ጠንካራ ቡድን አስፈሪ የሆኑ የግልሰቦችን ስብስብ ማሸነፍ እንኳ ይቻለዋል::

በተናጥል ሥራ ብዙ እርቀት መሄድ እንደማይቻል፣ መተባበር የተሻለ ስኬታማ እንደሚያደርግ ያለው ግንዛቤ ሲያድግም አብሮ የመሥራት ባህል ሊጎለብት ይችላል:: በተናጠል የማይችለውን ትልልቅ ሥራ አብሮ በመሥራት ትልልቅ ሕልምን ማሳካት ይቻላል የሚል እምነት እስኪጎለበት ግን ተያይዞ ከማደግ ይልቅ ተያይዞ መፋተግ መቀጠሉ አይቀርም::

የግል ስኬት ብቻውን እንደማያዋጣ የተገነዘቡ አገሮች ትኩረታቸውን ሁሉ ወደ አንድ አቅጣጫ በማድረግ የቡድን ሥራን መግባባትንና መረዳዳትን ለማጎልበት ብዙ ገንዘብ ወጭ ያደርጋሉ:: በዚህም የላቁ አገሮች ስኬታማ ሆነው በየጊዜው በእደገት ላይ እድገት ሲያስመዘግቡ እናያለን:: በተለይ በዚህ ሉላዊነት (globalaization) ዘመን ዓለም በሁሉም ነገር እየተሳሰረ ባለበት ጊዜ አብሮ መሥራት ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነው:: ተባብሮ መሥራት ካልተቻለ ከውድድር ውጭ መሆን ይመጣል:: አብሮ የመሥራት ባህልን ያዳበሩ ተወዳዳሪ አገሮች ያሸንፋሉ፣ አብሮ መሥራት አቅቶናል አልቻልንም የሚሉት ደግሞ ይሸነፋሉ:: አብሮ መሥራት አለመቻል ደካምነትም ነው:: አብሮ መሥራት አለመቻል ውጤታማ ሥራን የሚያስቀር ብቻ ሳይሆን አብሮ ለመሥራት ባለመቻል በሚፈጠር አለመግባባት ግጭቶችን የሚወልድ እንደሚሆንም ከታሪክ መማር ይቻላል::

ይህን የመሰለ የችግር ቋጠሮ ለመፍታት ብዙ ማሰብ፣ ብዙ ማጥናት፣ ብዙ መወያየት ማስፈለጉ የማይቀር ቢሆንም አብሮ መሥራት ያለመቻልን፣ የችግሩን ምንጭ መረዳትና ምንጩን ለማከም መሞከር ግን ጊዜ የሚሰጥ ጉዳይ አይደለም:: መሪዎች አብረው ለመሥራት የመቸገራቸው ምክንያት ምንጩ ምንድነው? ሁሉም ሥልጣን ወዳድ መሆኑ? ሁሉም አለቅነት መውደዱ? አንደኛ ሰው እንጂ ሁለተኛ ሦስተኛ ሰው መሆን አለመፈለግ? መምራት እንጂ መመራት አለመፈለግ? ወይስ ሰፊ እይታ አለመኖር? ወይስ ከአስተዳደግ ወይም ከትምህርት አሰጣጡ ጋር ተያይዞ

በብቸኝነት የመሮጥ እንጂ ከሰው ጋር ለጋራ ዐላማ በጋራ የመሥራት ልማድ አናሳ መሆን? ወይስ አለመተማመን ቅናትና ምቀኝነት ስለሚበዛ? ይህ ሁሉ ውይይትን ፈላጊ ነው::

ክፍል ሁለት

አገልጋይነት

ምዕራፍ ስድስት

አገልግሎት

6. አገልግሎት ምንድን ነው?

ስለ አገልጋይ መሪ ከመዳሰስ በፊት ስለ አገልግሎት ምንነት ሰፋ አድርጎ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል:: የአግልግሎትን ምንነት በደንብ መረዳት ሲቻል አገልጋይ መሪ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት ይቀላል በሚል ሙሉ ምዕራፉ አገልግሎትን የሚዳስስ ሲሆን አገልጋይ መሪ ደግሞ በሚቀጥለው ምዕራፍ ይሸፈናል::

አገልግሎት ቅንነት ከሚገለጽባቸው መንግዶች ዋነኛው ነው ማለት ይቻላል:: ለወገን እና አገር መቆርቆር የሚቻለው፤ ከግል ጥቅም ይልቅ ለብዙሆች ጥቅም ማሰብ የሚቻለው፤ ራስን ጎድቶ ሌሎችን የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው ለማድረግ መትጋት የሚቻለው፤ ቅን ልቦና ቅን አስተሳሰብ ሲኖር ነው:: አገልግሎት ለሌላው ማስብን፣ ለሌላው መቆርቆር የሚያስችል የአዛኝነትና የፍቅር ልብን ይፈልጋልና:: አገልግሎት ሌሎችን ከፍ ከፍ ለማድረግ ራስን ዝቅ ማድረግን ይጠይቃልም:: ከራስ

ቤት አልፎ ለጎረቤት ማሰብ የሚቻለውም የአገልጋይነት ልብ ሲኖር ነው። ምክንያቱም አገልግሎት ሲቻል ከራስ ይልቅ ሌሎችን ማስቀደምን ሳይቻል ደግሞ ለራስም እየኖሩ ለሌላው ማሰብን ግድ ይላልና። ይህ ሁሉ ያለ ቅንነት የሚሆን አይደለም።

በአገልግሎት ስም ሥልጣን ላይ ወጥቶ ሥልጣንን ለራስ መጠቀሚያ፣ ለራስ ፍላጎት ማርኪያ፣ የግል ጥቅምን ለማሳደጃ ማዋል የሚመጣው ቅንነት ሲጎድል ለመሆኑም ውጤቱ ራሱ ምስክር ነው። በተለይ ጠንካራ ተቋማዊ ስርዓት፣ የሕግ የበላይነትና ተጠያቂነት በሌለበት ሁኔታ ሥልጣንን ለግል ጥቅም እንዳይውል የሚገድበው የመሪዎቹ ቅንነት ነው ማለት ይቻላል።

መቼም በጎ ሕሊና ያለው ሰው ሁሉ በሕይወት ዘመኑ ምን ሠራሁ? ምን ማድረግ አለብኝ? ብሎ መጠይቁ የሚጠበቅ ነው። በጎ ሕሊና ካለ የእኔ አስተዋጽዖ፣ ሰው የመሆኔ ትርጉም ምንድን ነው? በምን እታወሳለሁ? ምን ታሪክ ሠርቼ ማለፍ አለብኝ? ያለኝን የተሰጠኝን ለወገኔ እንዴት ላከፍል? እና የመሳሰሉትን መጠየቅ አይቀርም። የአገልግሎት አጀማመር እንዲህ ካለው አስተሳሰብ ነው።

በአገልግሎት ቅንነት በተግባር ይገለጽበታል። መልካም ምኞት፣ በጎ ፍላጎት፣ ቀና አስተሳሰብና ስለ በጎ ሥራ የሚኖር ቀናዒነት በተግባር የሚገለጸው በአገልግሎት ነውና። መቼም መልካም ምኞት ብቻውን ለውጥ ሊያመጣ እንደማይችል የታወቀ ነው።

የአገልግሎት ምንጩ እግዚአብሔር ቢሆንም ተግባሩ ግን በእምነት ተቋማት ብቻ የተወሰነ አይደለም። የእግዚአብሔር ሥራ በአምልኮ ቦታ ወይም በእምነት ዙሪያ ብቻ ነው የሚሠራው ማለትም ትክክል አይሆንም። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሁሉም አምላክ ነውና በሁሉም ቦታ በፈቀደው ሰው፣ በፈቀደው ጊዜ፣ የፈቀደውን ሥራ ይሠራልና። “እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን” እንደተባለ አገልግሎት ዘርፈ ብዙ ነው። (ሮሜ 12፥6) ሰው ሁሉ በተሰማራበት መስክ ጥሪውንና ጸጋውን አውቆ ለሰው የሚጠቅመው ምንድን ነው? በማለት እግዚአብሔርን

በማመን በበጎ ሥራ ሁሉ ማገልገል ይቻላል:: ሰው ሁሉ በተሰማራበት መስክ እግዚአብሔርን በመፍራት ለሌሎች የሚያደርገው በጎ ተግባር ሁሉ አገልግሎት ነው:: መጠኑና ዐይነቱ ቢለያይም አገልግሎት ዘርፈ ብዙና ሰፊ ነውና::

በቃልም በሕይወትም በዕውቀታቸው ለዓለም ያበሩ፣ እንደ ሻማ እየቀለጡ የብዙዎችን ጨለማ የገፈፉ፣ በበጎ ሥራ የብዙዎችን ሕይወት የቀየሩ፣ መልካሙን መንገድ ለሰው ያሳዩ፣ እንደ ከዋክብት ያበሩ ብዙ አገልጋዮችን ዓለም አይታለች:: እንዲህ ዐይነት በጎ ሥራ ደግሞ በሃይማኖት ተቋማት ብቻ የሚወሰን አይደለም:: ሰው ሁሉ በተሠማራበት መስክ ቤተሰብን ከመንከባከብ ጀምሮ ሊሠሩት የሚገባ ተግባር ነው እንጂ:: ብርሃን መሆን ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተሰጠም አይደለም:: በፈሪሃ እግዚአብሔር የሚኖሩ ሁሉ እንደተሰጣቸው ጸጋ መጠን የበኩላቸውን ማድረግ የሚጠበቅ ነውና::

በገሀዱ ዓለምም አገልግሎት የሚባለው ነገር በብዙ ወገኖች ነው የሚነገረው:: የፖለቲካ መሪዎች ራሳቸውን የሚያዩት በአገልጋይነት ነው:: የሕዝብ አገልጋዮች ነን በሚል ነው በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚሠሩ ሰዎችም ራሳቸውን የሚገልጹት:: የአገርን ዳር ድንበር፣ የሕዝብን ሰላም የሚያስጠበቁ የጸጥታ ኃይሎች በተመሳሳይ የሕዝብና የአገር አገልጋዮች በመባል ነው የሚጠሩት:: ለሕዝብ ነጻነት ታገልን የሚሉ ሁሉ ራሳቸውን የሚገልጹት አገልጋይ በሚል ሲሆን ያለፉትን ጓዶቻቸውንም ሰማዕታት በሚል እንደሚጠሩም የታወቀ ነው:: በግብረ ሠናይ ሥራ የተሰማሩ ሰዎችም ሥራቸው አገልግሎትን የሚመለከት ነው:: ቤተሰብን መርዳት፣ ጧሪ ቀባሪ የሌላቸውን ወገኖች መደገፍ፣ በሚቻለው ሁሉ ለሰው በጎ ማድረግ፤ ይህ ሁሉ አገልግሎትን ይመለከታል:: አገልግሎት “ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏት” እንደተባለ ልጆችን ወልዶ በአግባቡ አሳድጎ ተረካቢ ትውልድን ማፍራት የሚለውን ሁሉ ሊያቅፍ ይችላል:: ይህ ሁሉ ከራስ አልፎ ለሌላው ጥቅም የሚደረግ በጎ ሥራ ነውና::

በእርግጥ እግዚአብሔርን በማመን የሚደረግ አገልግሎትና ከዚያ ውጭ የሚደረግ አገልግሎት ልዩነት አለው:: ምክንያቱም "ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፣ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋል።" ተብሎ እንደተጻፈ በጎ ሥራ በእምነት ሲሆን ነው ትርጉም የሚኖረው:: (ዕብ. 11፥6) በተመሳሳይ መንፈሳዊ አገልግሎትና ሌላው አገልግሎት ዐላማውም ሆኖ ዐይነቱ የተለየ እንደሆነ የታወቀ ነው:: በመንፈሳዊ አገልግሎት እግዚአብሔርንም ሰውንም ማገልገል እንደሚቻል ሁሉ በሌላውም በጎ አገልግሎት እግዚአብሔርንም ሰውንም ማገልገል ይቻላል የሚለው ነው ዋናው ቁምነገሩ::

አገልግሎት በጥቅሉ በአንድም በሌላም ድጋፍ ለሚፈልጉ ሰዎች የሚቻለውን ሁሉ በጎ ማድረግ መቻል ነው:: በፍርድ ቀን ክርስቶስ አድርጋችሁልኛል ብሎ በቀኙ የቆሙትን አመስግኖ ወደ ዘላለም መንግሥት ግቡ ሲል፣ እንዲሁም አላደረጋችሁልኝምና ከእኔ ራቁ ሲል፣ በቀኝም በግራም የቆሙት አንድ ዐይነት ጥያቄ ይጠይቃሉ:: "መቼ አደረግንልህ? ወይም መቼ መጥተህ ሳናደርግልህ ቀረን?" የሚል ጥያቄ:: መልሱም የአገልግሎትን ምንነት የሚያስገነዝብ ነው:: "ንጉሡም መልሶ እውነት እላችኋለሁ፣ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል":: ያላደረጉትንም "ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል" የሚል ነው:: (ማቴ. 25፥34-45) ከዚህ የተነሣ ነው ሰውን ማገልገል፣ ለሰው በጎ ማድረግ፣ እግዚአብሔርን እንደ ማገልገል ሆኖ መቆጠሩ:: ከሁሉ ለሚያንሱ ማለትም አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሁሉ ማለት ነው::

ስለ አገልግሎት ምንነት በቅዱስ መጽሐፍ መነጸርነት በስፋት ለመረዳት ይቻላል:: አገልግሎት ምንድን ነው? ለሚለውም የሚከተሉትን ዘርዘር አድርጎ ማዬት ይጠቅማል::

❁ ብርሃን መሆን

የአገልግሎት አንዱ እሳቤ “እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ..ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ” ተብሎ እንደተጻፈ ብርሃን መሆን ነው::(ማቴ. 5፥14-16) የሰው ሕይወት በጨለማ የሚመሰልበት ጊዜ አለ፤ በብርሃን የሚመሰልበት ጊዜም አለ:: የጨለማ ዘመን ነበር የሚል አነጋገርም የተለመደ ነው:: የሰው ሥራ ነው በጨለማ ወይም በብርሃን የሚመሰለው፡፡ ክፉ ሥራ በጨለማ ሲመሰል መልካም ሥራ ደግሞ በብርሃን ተመስሏል:: (ሉቃ. 1፥79፣ ዮሐ. 12፥46: ኢሳ 9፥2)

አገልግሎት ቀን ለጨለመባቸው መንገድ ለጠፋባቸው የሚያበሩበት ብርሃን ነው:: “በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙንም የሚጠላ እስከ አሁን በጨለማ አለ፡፡” እንዲል በጥላቻ የሚኖር ሰው በጨለማ ይኖራልና እንዲህ ዐይነቱን ሰው ከጥላቻ ስሜት እንዲወጣ ማድረግ ነው ብርሃንነት:: (1ኛዮሐ. 2፥9) ሰው ከክፉ አስተሳሰብ ተላቆ ቀናውንና በጎውን መንገድ እንዲይዝ ማድረግም ብርሃንነት ነው:: ብርሃንነት ሰውን ክክፉ ሥራ ወደ በጎ ሥራ እንዲመለስ በማድረግም ሊገለጽ ይችላል:: ሰውን እግዚአብሔርን ከሚያሳዝን፣ ከማይጠቅምና ራስን አገርን ከሚጎዳ ተግባር ከምቀኝነት፣ ከገዳይነት፣ ከመራርነት፣ ከቂመኛነት፣ ከዘረኝነት፣ አድመኝነት፣ ከዝሙትና ሱስ ተላቆ መልካም ዜጋ እንዲሆን ማስቻልም ብርሃንነት ነው::

ዕውቀት ባልተስፋፋበት አገር ዕውቀትን በማካፈል፣ ያልተማረው ፊደል ያልቆጣጠረው በሚበዛበት ሕዝብን በማስተማር፣ በዕውቀት በሙያ በማገልገልም ብርሃን መሆን ይቻላል:: የዕውቀት ማነስ ባለበት አገር የተረጋጋ፣ ሰላማዊ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው፣ እርስ በርሱ የሚፋቀር እና የሚከባበር ማኅበረሰብን መገንባት አስቸጋሪ እንደሚሆን የቅርቡ ታሪክ እንኳ ማስረጃ እየሆነን ነው:: የነቃ፣ ያወቀ ማኅበረሰብ ቁጥር በሚያስንበት ነው ቁጥራቸው ትንሽ በሆኑ ክፉ መሪዎች ለክፉ ዐላማ፣ ለግጭት፣ ለብጥብጥ መነዳት የሚመጣውም፡፡ ለምን? ብሎ መጠየቅ የማይችለው፣ እምነቱን ጠንቅቆ ያልተረዳው በሚበዛበት ሰዎችን ለጥልና ለግጭት ለማነሳሳት ከባድ ላይሆን ይችላል::

የሰዎችን ሕይወት ማብራትም ይቻላል:: የሰዎችን ሕይወት ማጨለምም ይቻላል:: የምርጫ ጉዳይ ነው:: በጎውን ጎዳና በእምነት ለመረጡ እንደ ብዙዎቹ ብርሃን መሆን ይቻላል:: በዓመፅና በትዕቢት ክፉውን ጎዳና ለመረጡ ደግሞ የሰዎችን ሕይወት የሚያበራ ሳይሆን የሚያጨልም፣ የሰዎችን ኑሮ የሚያሻሽል ሳይሆን የሚያጎስቁል፣ የሰዎችን አስተሳሰብ የሚያሰፋ ሳይሆን የሚያጠብ፣ ሰዎችን በፍቅር የሚያስተሳስር ሳይሆን መለያየትን የሚያመጣ መሆንም ይቻላል::

"የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ፣ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፤ ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፤ ይልቁን ግለጡት እንጂ" የሚለው ቃል የሚያስገነዝበንም ብርሃን መሆን እንሚቻልም እንደሚገባም ነው:: (ኤፌ. 5፥9-11)

❁ ለበረከት መሆን

ሁለተኛው የአገልግሎት ትርጉም የብዙዎች አባት አብርሃም "ለበረከት ሁን" እንደተባለ አገልግሎት ለሌላው በረከት መሆንም ነው:: (ዘፍ 12፥2) ክፋት ሲበዛ ለመርገም ምክንያት እንደሚሆን ሁሉ በጎ ሥራ ለብዙዎች በረከትን ያስገኛልና:: በአገልግሎት የሰዎችን ሕይወት ማሻሻል ሲቻል ነው በረከት ሊባል የሚችለው:: ሕዝብን ከተመጽዋችነት አውጥቶ ከራብ የሚታደግ ሰው መሆን ማለት ነው ለበረከት ሁን ማለት:: በልዩ ልዩ ምክንያት የተለያየውን ሕዝብ በፍቅርና በሰላም ተሳስሮ እንዲኖር የሚያስችል መሪ ሲገኝ ነው በረከት ተገኘ የሚባለው:: አገር ከማፍረስ አገርን የሚያንጽ መሪ ሲገኝ ነው የበረከት መሪ የሚያሰኘው:: ትልልቅ ሕልሞችን አልሞ ዘመንን ማሸገር ሲቻል ነው በረከት መሆን የሚባለው:: ከባርነት ነጻ የሚያወጣ ማለት ነው ለበረከት ሁን ማለት:: በጸሎቱ የሚባረክ የተጣላውን የሚያስታርቅ የተበተነውን የሚሰበስብ፣ ከመንገድ የራቀውን የሚመልስ መሪ ሲገኝ ነው ለበረከት የሚሆን መሪ ተገኘ የሚባለው::

አንድ ሰው አገልግያለሁ ብሎ ሲያስብ በአገልግሎቱ ምን በረከትን አስገኘሁ? ወይስ አገልግሎቴ መርገምን ነው ያመጣው? ብሎ መጠየቅ የሚገባውም ከዚህ የተነሣ ነው::

❁ ጨው መሆን

ሦስተኛው የአገልግሎት ትርጉም "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ" እንዲል ጨው መሆን መቻል ነው:: (ማቴ. 5፥13) ለማጣፈጥ ነው ጨው የሚፈለገው:: ብዙ መጣፈጥ የሚያስፈልገው ነገር ስላለ ነው አገልግሎት በጨው የመመሰሉ ምስጢርም:: ጨው መርዛማ ነገርን እንደሚፈወስ የሚያሳይ ታሪክም በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ተጽፏል:: "የከተማይቱም ሰዎች ኤልሳዕን እነሆ፣ ጌታችን እንደምታይ የዚች ከተማ ኑሮ መልካም ነው፤ ውኃው ግን ክፉ ነው፣ ምድሪቱም ፍሬዋን ትጨነግፋለች አሉት:: እርሱም አዲስ ማሰሮ አምጡልኝ፤ ጨውም ጨምሩበት አለ፤ ያንም አመጡለት:: ውኃው ወዳለበቱም ምንጭ ወጥቶ ጨው ጣለበትና እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ይህን ውኃ ፈውሼዋለሁ፤ ከዚህም በኋላ ሞትና ጭንገፋ አይሆንበትም አለ:: ኤልሳዕም እንደ ተናገረው ነገር ውኃው እስከ ዛሬ ድረስ ተፈውሶአል::" የሚል ነው ታሪኩ:: (2ኛነገ. 2፥19-22)

በዚሁ መንገድ በአገልግሎቴ የስንቱን መራራ ሕይወት አጣፈጥሁ? የስንቱን መርዛማ ሕይወት እንዲፈውስ አደርግሁ? ብሎ መጠየቅ ይገባል:: አልጫነት በዝቶ የሚጣፍጥ ነገር በሚጠፋበት፤ ቀቢጸ ተስፋና ፍርሃት በሚከሠትበት ጊዜ ተስፋ ሰጭ ሆኖ መገኘት ማለት ነው ጨው መሆን ማለት:: ክፉ አሳብን የሚያመክንና በጎውን የሚዘራ ሆኖ መገኘት ነው ጨው መሆን ማለት:: የሚያጣላ ሳይሆን የሚያስታርቅ፣ የሚለያይ ሳይሆን አንድ የሚያደርግ በሚበዛበት ጊዜ አልጫው ዓለም ይጣፍጣልና:: ክፉዎችን የሚመክር እና የሚያስተካክል፣ ልጆችን በመልካም ሥነ ምግባር ኮትኩቶ የሚያሳድገው ሲበዛ አልጫውን ዓለም የሚያጣፍጥ ትውልድን ማግኘት ይቻላል:: እድል ያጡ ሰዎችን እድል እንዲያገኙና ሕልማቸውን እንዲያሳኩ ማድረግም ነው ጨው መሆን ማለት:: ተምረው

የብዙዎችን ሕይወት ሊቀይሩ የሚችሉ አዳጊዎችን እንዲማሩና፣ ሙሉ አቅማቸውንና እድላቸውን እንዲጠቀሙበት የሚያስችል አገልግሎትም በጨው ሊመሰል ይችላል። ከፈጣሪ የተሰጣቸውን ዓቅም ተጠቅመው አምራች መሆን የሚችሉ ዜጎች ሙሉ አቅማቸውን እንዲጠቀሙ ማገዝ ሲቻል ነው ጨው መሆን ማለት።

ጨው መሆን ትልቅ እድል ነው። ግን ለተጠቀመበት ነው። ጥሪውን ለሚያቃልለው "ጨው ለራስህ ብለህ ጣፍጥ ያለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሀል" እንደተባለው ነው የሚሆነው። የወንጌሉም ቃል ይህን የመሰለ ነው። "ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም" እንዲል። (ማቴ 5፥17) ከዚህ የተነሣም ነው ከመገልገል ይልቅ ማገልገል መቻል እድል ነው የሚባለውም።

❁ መሠዋዕትነት

በአራተኛ ትርጉሙ አገልግሎት መሥዋዕትነት ነው። አገልግሎት ለእኔ ብቻ ከማለት ለሌሎች በማሰብ ጊዜን፣ ዕውቀትን፣ ገንዘብን መሥዋዕት ማድረግን ይጠይቃልና። ለብዙዎች ኑሮ መሻሻል፣ ለብዙዎች ነጻነት፣ ለፍትሕና እኩልነት የራስን ኑሮ እየጎዱም ቢሆን ለሌሎች መኖር መሥዋዕትነት ነው። የተሻለ ኑሮን መኖር እየቻሉ እንዲህ ላለ ዐላማ የተሻለ ኑሮ ይቅርብኝ ለሌሎች እሠራለሁ ማለት ሲቻል ነው መሥዋዕትነት ማለት። ለሌላቸው ማካፈል፣ ራስን ጎድቶም ቢሆን ዓቅም የፈቀደውን ሁሉ ለሌሎች ማድረግ መቻል ነው መሥዋዕትነት። ከዚያም ሲያልፍ የሕይወት መሥዋዕትነትን እስከመክፈልም ሊደርስ ይችላል።

"እንግዲህ፣ ወንድሞች ሆይ፣ ስውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፣ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።" የሚለው ቃልም የሚያሳዬው አገልግሎት መስዋዕትነት ነው የሚለውን ነው። (ሮሜ. 12፥1-2)

ሌሎችን ለራስ መጠቀሚያ ማድረግ አገልግሎት ሊሆን አይችልም:: በአገልግሎት ስም የራስን ኑሮ፣ የራስን ዝና፣ የራስን ሕይወት መገንባት ማገልገል ሳይሆን በሌሎች መገልገል ነው መባል የሚገባው:: ስንት ድሆች በሚያለቅሱበት አገር የራስን ኪስ ለማድለብ በድሆች ስም እየነገዱ አገልግሎት ላይ ነኝ ማለት በአገልግሎት ማላገጥ ነው የሚሆነው::

6.1 ጥሪ

ብዙውን ጊዜ መልሱ ቀላል ባይሆንም የሕይወቱ ጥሪ (calling[33]) ምንድን ነው? የተሰጠኝ መክሊት ምንድን ነው? እና የመሳሰለውን ጥያቄ መጠየቅ የተለመደ ነው:: የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት የሚደረግ ጥረት ነው የሕይወት ትርጉም (Purpose of life) የሚባለውም::

መልሱ ሊለያይ ይቻላል እንጂ እንዲህ ዐይነቱን ጥያቄ በፈጣሪ የሚያምንም ሆነ የማያምን ሰው ሁሉ መጠየቁ አይቀርም:: ሰው ሁሉ እንደ እየእምነቱ ወይም እንደ አረዳዱ እንዲህ ላሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት መሞከርም የሕይወት አካል ነው:: አተረጓጎሙ ይለያይ እንጂ የሰው ሕይወት ዐላማ የለሽ ነው የሚል ሰውም እምብዛም አይሰማም:: እምነት አልባ ነን የሚሉ ሰዎች እንኳ ትርጉሙ ቢለያይም መልካም ማድረግ፣ አገርንና ሕዝብን ማገልገልን ሰው የመሆን ግዴታ እንደሆነ በአንድም በሌላም ሲገልጹት፣ በተግባርም ይህንኑ ሲፈጽሙት ማየት የተለመደ ነው:: ጠቢቡ ሰሎሞንም "ሰባኪው ከንቱ፣ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው ይላል። ከፀሐይ በታች በሚደክምበት ድካም ሁሉ የሰው ትርፉ ምንድር ነው?::" ሲል ትልቁን የሕይወት ጥያቄ ይጠይቃል:: (መክ. 1፥2-3) ሕይወት ዐላማ የለሽ ከሆነ ሕይወት ትርጉም አልባ መሆኑ አይቀሬ ነውና:: ሕይወት ትርጉም አልባ ከሆነስ ሰው የመኖር ተስፋው ምን ሊሆን ይችላል?

[33] Calling means a strong inner impulse toward a particular course of action especially when accompanied by conviction of divine influence, the vocation or profession in which one customarily engages, https://www.merriam-webster.com/dictionary/calling

የሰው ሕይወት ትርጉም አለው:: ያለ ዐላማ የተፈጠረ ሰውም የለም:: በተሰጠው ዘመን በጎ ተግባርን ሠርቶ ማለፍም ሰው የመሆን አንዱ ዐላማ ነው:: ሰው የተፈጠረበት ዐላማ ምንድን ነው? ለሚለው መጽሐፍ ቅዱስ አንዱ የሚሰጠው ቀጥተኛ መልስ "እኛ ፍጥረቱ ነንና፣ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ" የሚል ነው:: (ኤፌ. 2፥10) ሰው የተፈጠረበት አንዱ ዐላማ መልካም ለማድረግ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት ትርጉም ምንድን ነው? ለሚለውም ጥያቄ መልስ ሆኖ የቀረበው አንዱ አገልግሎት ነው:: ከላይ እንደተገለጸው የዓለም ብርሃን ሁኑ ሲባል፣ የዓለም ጨው ሁኑ ሲባል፣ ለበረከት ሁኑ ሲባል፣ መሥዋዕት ሁኑ ሲባል የሰው ሕይወት ዐላማው በተሰጠው መክሊት ልክ አገልግሎትን ማበርከት ለመሆኑ ማስረጃ ሊሆን ይችላል:: ከዚህ በተጨማሪም የሰው ልጅ ዐላማ በፈሪሃ እግዚአብሔር ለፍትሕ መቆም፣ ምሕረትን ማድረግ እንደሆነም "ሰው ሆይ፣ መልካሙን ነግሮሃል፣ እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?" የሚል ተጽፏል:: (ሚክ. 6፥9)

"የተጠሩ ብዙዎች፣ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና" ተብሎ እንደተጻፈ የአገልግሎት ጥሪ ለሁሉም ነው:: (ማቴ 22፥4) ያልተጠራም የለም:: ማንም ሰው የሕይወት ጥሪ አለው:: ፈልጎ የማግኘትና ያለማግኘት፣ መጠቀምና አለመጠቀም ግን የሰው ድርሻ ነው:: ታላላቅ ሥራን ሠርተው ለማለፍ የቻሉ ሰዎች አንዱ ምስጢርም ጥሪያቸውን አውቀው፣ ለጥሪው ምላሽ መስጠት መቻላቸው፣ መክሊታቸውን አውቀው በመክሊታቸው መሰማራታቸው ሊሆን ይችላል::

ለበጎ ዐላማ ለመጠራት የልብ መሻት ያስፈልጋል:: "የልብ መዘጋጀት ከሰው ነው፣ የምላስ መልስ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው" እንደተባለ በጎ ምኞትን፣ የልብ መሻትን እግዚአብሔር ያያል:: (ምሳ. 16-1) እንደ ሙሴ "የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ አሁንም እነሆ ሕዝቤን ታወጣ ዘንድ እልክሃለሁ" ለመባል ከራስ ይልቅ ወገንን የሚያስቀድም ልብ ሊኖር ያስፈልጋል:: (ዘጸ. 3፥7) እንዲህ ዐይነት ልብ ሲያገኝ ከሁሉ ለሚበልጥ በጎ

ተልእኮ እግዚአብሔር ይጠራል:: አገልጋይ መሪም ጥሪውን ያውቃል:: ይህ በሃይማኖት ዐይን ሲታይ ብቻም አይደለም:: ሰው ከልብ የሚወደውን የልብ ፍላጎቱን (passion)፥ የልብ መሻቱን ወይም ጥሪውን ሲከተል ስኬታማነት ይኖራል፥ በሚወዱት ነገር መድከም ወይም መስልቸት የለምና:: እንጀራ ፍለጋ ከሚሮጠው ሩጫ ባሻገር ይህንን የልብ ፍላጎት መሻትና መከተል እርካታን ይሰጣል የሚል እምነት ነው ያለው[34]::

"መከሩ ብዙ ሠራተኞቹ ጥቂት ናቸው" የሚል ቃልም በመጽሐፍ ተጽፎ እናገኛለን:: (ሉቃ. 10፥2) እውነተኛ አገልጋዮች ጥቂት መሆናቸውን የሚያሳይ ነው:: የሚበዛው ለራሱ ብቻ የሚኖረው ነውና:: እንዲያውም እግዚአብሔር "ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል?" እያለ መጠየቁም የእውነተኞች አገልጋዮች መታጣትን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል:: (ኢሳ 6፥8) እውነተኛ አገልጋይ ማግኘት ቀላል አይደለም:: ለምን ቢባል ለራሱ የሚያደላው፣ ራሱን የሚያስቀድመው፣ እኔን ከደላኝ ምን ችገረኝ የሚለው ስለሚበዛ ይሆናል:: እንደተጻፈ ሰው ለአግልግሎት ሲጠራ በምክንያት ማፈግፈግም የተለመደ ነው:: በወንጌልም የተጠሩ ሰዎችን እምቢተኝነት እንዲህ ሲል ተመዝግቧል:: "ሁላቸውም በአንድነት ያመካኙ ጀመር:: የፊተኛው መሬት ገዝቼአለሁ ወጥቼም ላየው ግድ ያስፈልገኛል ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለው:: ሌላውም አምስት ጥምድ በሬዎች ገዝቼአለሁ ልፈትናቸውም እሄዳለሁ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለው:: ሌላውም ሚስት አግብቼአለሁ ስለዚህም ልመጣ አልችልም አለው::" የሚለው ምሳሌ እንደሚያሳየን ጥሪውን ከሚቀበለው ይልቅ፣ ለእኔ ብቻ የሚለው ይበዛል:: (ሉቃ. 12፥18) ይህ በሃይማኖታዊ መነጽርነት ስለሚታይ ብቻም አይደለም፥ በሌላውም እንዲሁ ነው የሚሆነው:: ምን ያህል ጊዜ ነው ከራስ ጥቅም የወገንን ጥቅም ማስቀደም የሚቻለው?

[34] We are often told to pursue work we're passionate about, but for many people, this simply isn't feasible. Luckily, research shows that doing something you care about outside of work can benefit both your personal life and your career. https://hbr.org/tip/2019/12/pursue-a-passion-outside-of-work

6.2 መክሊት

የተሰጠኝ መክሊት ምንድን ነው? በተሰጠኝ መክሊት ምን ያህል አተርፍኩበት? ወይስ መክሊቴን በፍርሃት ቀብሬው እኖራለሁ? የሚለውን መጠየቅም ከሰው የሚጠበቅ ነው:: የአገልግሎትን ዐይነትና መጠን የሚያመለክት ነው መክሊት በመባል በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው:: "እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን" እንዲልም መክሊት ጸጋ በመባልም ይጠራል:: (ሮሜ. 12፥6) ብዙ ጊዜ ጸጋዬ ምንድን ነው? በሚል መጠየቅም የተለመደ ነው:: ችሎታ (talent) በሚል የሚጠራበት ጊዜም አለ::

የሰው መክሊቱ የተለያየ ነው:: መክሊት ያልተሰጠውም የለም:: አንድ ወይም ሁለት መክሊት መሆኑም አይደለም ቁምነገሩ:: "ለእያንዳንዱ እንደ ዓቅሙ፣ ለአንዱ አምስት መክሊት ለአንዱ ሁለት ለአንዱም አንድ ሰጠ" እንዲል መክሊቱ አንድ ወይም ሁለት ወይም አምስት መሆኑ የፈጣሪ ፈቃድ ነው የሚሆነው:: (ማቴ. 25፥15-26) እንዲያውም መክሊቱን የሚቀብረው ሁለት ወይም አምስት መክሊት ከተሰጣቸው ይልቅ አንድ መክሊት ብቻ የተሰጠው ሰው እንደሆነ ነው መጽሐፍ የሚናገረው:: ሁለት ወይም አምስት መክሊት የተሰጣቸው ሰዎች በተሰጣቸው መክሊት ወጥተው ወርደው ትርፍ ሲያተርፉበት አንድ የተሰጠው ግን ሲቀብረው ነው የሚያሳየው የመጽሐፍ ቅዱሱ ታሪክ:: "ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል።" የሚል ቃልም ይገኛል:: (ማቴ. 25፥29) ላለው ሁሉ ይሰጠዋል ምክንያቱም በተሰጠው መክሊት ብዙዎችን በማገልገል ያተርፍበታልና:: ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል ምክንያቱም ስለማይሠራበት፣ መክሊቱን ስለሚቀብረው አያስፈልገውምና ከእንዲህ ዐይነቱ ሰው ተነጥቆ ሠርቶ ለሚያተርፍበት ሰው ይሰጣል:: በገሀዱ ዓለም የሚበዛውም እንዲህ ዐይነቱ ታሪክ ነው:: ብዙ የተሰጣቸው ብዙ ሲያተርፉ፤ አንድ የተሰጣቸው ንፉግ ወይም ፈሪ ሲሆኑና ያችውንም አንዲን ሳይጠቀሙባት፤ ለወገናቸው አንድ ቁም ነገር ሳይሠሩ፤ ለራሳቸውም ሳይሆኑ እንደመጡ ወደ ነበሩበት ሲመለሱ ነው የሚታየው:: "በዚህ ቀን ተወለደ፣ ለራሱ ብቻ ኖረ፣ በዚህ

ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ" የሚል የሕይወት ታሪክ የሚፈልግ ሰው ባይኖርም አንዷን መክሊት እንደቀበረው ሰው፤ ይህን የሚመስል ታሪክ ያላቸው ሰዎች ቁጥራቸው ቀላል አይሆንም:: ዋናው ነገር መክሊትን ሳይጠቀሙበት እንዳያልፍ ሁሌም እየተመኙ ምንም ሳያከናውኑ በምኞት እየኖሩ መጠራት እንዳይኖር ነገ ሳይሉ ዛሬ ወደ ሥራ መግባት መቻል ነው::

መክሊትን ማወቅ ማለት ምን ብሠራ የተሻለ ውጤታማ እሆናለሁ? ጸጋዬ ምንድን ነው? ምን የተሻለ ክህሎት አለኝ? ብሎ በመጠየቅ የራስን ጠንካራ ጎንና ደካማ ጎን በመፈተሽ ደካማውን እያሻሻሉ ጠንካራው ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት መቻል ማለትም ነው:: ሰው በተሰጠው ጸጋ ትኩረት አድርጎ ሊሠራበት ይገባል ነው የሚባለው:: ጸጋን ፈልጎ ማግኘትና በተሰጠን መክሊት መሠማራት መቻል ስኬታማ ሥራን ለመሥራት ያስችላል የሚለው ነገር በአንድም በሌላም የሚነገር ነው:: በሥራ አመራር ሳይንስም አንድ ሰው ስኬታማ የሚሆነው ጠንካራ ጎኑን ለይቶ ሲያውቅና በጠንካራ ጎኑ ሲጠቀምበት ነው[35]:: እንዲያውም ደካማ ጎንን ለማስተካከል ከሚደረገው ጥረት ይልቅ ባለ ጠንካራ ጎን መጠቀም ሲቻል ስኬታማ ያደርጋል የሚል አስተሳሰብ ነው ጎልቶ የሚታዬው::

በተመሳሳይ መክሊት የሚያስተምረን አንድ ሰው ሁሉንም መሆን አይችልም የሚለውንም ነው:: "እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር::" እንዲል:: (ሮሜ. 12፥6-8) እግዚአብሔር ስጦታውን ሁሉ እንደወደደ ለሰው ሁሉ አካፍሎታል እንጂ ሁሉንም መክሊት ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ አልሰጠምና:: ሁሉን መሆንም አይቻልም:: ሁሉን ለመሆን

[35] Build Strengths That Complement Your Weaknesses, https://hbr.org/tip/2018/12/build-strengths-that-complement-your-weaknesses

መመኮር ከሁሉም አንድ ያጣ መሆንን ሊያስከትልም ይችላል:: ጸጋን ፈልጎ ማግኘትና በተሰጠን ጸጋ መሥራት ነው ስኬታማ የሚያደርገው::

6.3 አገልግሎት ለምን?

አገልግሎትን ከሰው ሕይወት ጋር የሚያቆራኙት ብዙ ምክንያቶች አሉ::

1ኛ. አገልግሎትን ግድ ከሚሉ ምክንያቶች የመጀመሪያው " ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው" ተብሎ እንደተጻፈ የተቀበሉትን መስጠት ስለሚገባ ነው:: (የሐዋ.ሥ 20፥35) ለመስጠት ዓቅም ያስፈልጋልና ዓቅም አግኝቶ መስጠት መቻል መታደል ነው:: ምጽዋትን ከመቀበል መመጽወት መቻል ጸጋ ነው የሚለውም ትርጉም ይሰጣል:: ተረጅ ከመሆን ሌሎችን መርዳት መቻልም እንዲሁ:: በተለያየ ምክንያት እድል ያላገኙ፣ ሠርተው ራሳቸውን መደገፍ ያልቻሉ ሰዎችም የሚመኙት ከመቀበል መስጠት የሚችሉበትን ዓቅም ማግኘት ነው የሚሆነው:: እድል ተጣማባቸው፣ ዓቅም አጥሯቸው፣ ወይም ያላግባብ ተገፍተው ራሳቸውን መደገፍ የማይችሉ ሰዎች ተመጽዋች መሆናቸው ደስታን እንደማይሰጣቸው መገመት አያስቸግርም:: የሰውን እጅ ማየት፣ በሌሎች እየተረዱ መኖር ደስታን የሚሰጠው ካለ ሰነፍ ብቻ ነው የሚሆነው:: "ምነው ከምንረዳ አቅሙን አግኝተን መርዳት በቻልን ነበር" ማለት ከሰው ሁሉ የሚጠበቅ ነው::

ዕውቀት አግኝቶ በዕውቀት ማገልገል ደስታው ለሰጭውም ነው:: ገንዘብ አግኝቶ ገንዘብ መለገስ መቻልም ከተቀባዩ በላይ ሰጪውን ነው የሚያስደስተው:: የመምራት ዓቅም አግኝቶ በተለያየ የአመራር ደረጃ ሕዝብን ማገልገል መቻልም ላስተዋለው መታደል ነው:: በሌላውም መስክ ሁሉ ማገልገል መቻል ከተገልጋዩ ይልቅ አገልግሎቱን ለሚያበረክተው ሰው ደስታው እንደሚበዛለት ነው በተግባር የሚታዬውም:: እኛችንን በዘረጋን ጊዜ ሁሉ ምን ያህል ደስታና የውስጥ እርካታ ነው የሚሰማንስ?

2ኛ. እድለኛነትን ማሰብ መቻል ነው በጎ ማድረግን ከሚያስገድዱ ነገሮች አንዱ:: በጎ ማድረግ የቻልኩት እድለኛ ስለሆንኩ ነው ብሎ ለሚያስብ አገልግሎት መስጠት መቻልን ጸጋ አድርጎ ያየዋል:: በዚህ ዓለም ስኬታማ የሚባሉ ሰዎች እንደእየእምነታቸው አቀራረባቸው ቢለያይም የጋራ የሆነ አገላለጽ ግን አላቸው:: ስኬታማነታቸውን ሲገልጹ ከሌላው የተሻለ ስለሠራሁ፣ ከሌላው የተለየ ብልህ ስለሆንሁ፣ ወይም ከሌላው የተለየ ስለሮጥሁ ነው የሚል ነገር ሲናገሩ ብዙም አይሰማም:: ይልቁንም "ለስኬታችን ምክንያቱ በትክክለኛው አገርና፣ በትክክለኛው ጊዜ ስለተወለድን እና እድለኛ ስለሆንን ነው" የሚል አገላለጽ አላቸው:: ጊዜና እድል ሲገጣጠም ስኬት እንደሚኖር ሳይታለም የተፈታ ነው:: ይህን የሚያሳይ ነው በመጽሐፍ የተጻፈውም:: "እኔም ተመለስሁ፣ ከፀሐይ በታችም ሩጫ ለፈጣኖች፣ ሰልፍም ለኃያላን፣ እንጀራም ለጠቢባን፣ ባለጠግነትም ለአስተዋዮች፣ ሞገስም ለአዋቂዎች እንዳልሆነ አየሁ:: ጊዜና እድል ግን ሁሉን ያገናኛቸዋል::" እንዲል:: (መክ 9፥11) እድለኛነትን ማስታወስ ሲቻል ነው አገልግሎትን ማበርከት የሚቻለው የሚባለውም ከዚህ የተነሣ ነው::

እኔ እድለኛ ስለሆንሁ እድል ለተጣመመባቸው ሰዎች በጎ ማድረግ አለብኝ ማለት በጎ ሕሊና ካለው ሁሉ የሚጠበቅ ነው:: እድለኛ ሆኜ የትምህርት እድል በማግኘቴና በመማሬ "ያልተማረ" ወገኔን ማገልገል ይገባኛል ማለት በጎ ሕሊና ካለው ሁሉ ይጠበቃልም:: እድለኛ ሆኜ ባለሃብት በመሆኔ የድሀ ልጆችን እንዲማሩ፣ የተራቡት የዕለት ምግብ እንዲያገኙ የበኩሌን ማድረግ አለብኝ ማለት ለተሰጠን ነገር የምናመሰግንበት ሌላው መንገድ ነው::

3ኛ. በተመሳሳይ "የተቀበልኩትን ነው የምሰጠው" የሚል እሳቤ በጎ የማድረግ አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል:: አገልግሎት እንደተቀበልን የመስጠት ግዴታ አለብን ብሎ ማሰብ መቻልም ነው:: (2ኛ ቆሮ 9፥7) ጥሬ ግሬ ነው ሀብታም የሆንኩት ከሚል ከንቱ መታበይ ይልቅ ሀብት ያፈራሁባትን አገሬን፣ ሀብት ያስገኘኝን ድሀው ወገኔን ማለት ሲቻል አገልግሎትን መዘንጋት አይኖርም:: አካል የጎደለባቸውን ልንረዳ ብንችል

ሙሉ ጤንነትን ስለተቀበልን ነው። አቅመ ደካሞችን በእውቀታችን በሀብታችን ብናገለግልም እኛ አስቀድሞ ስለተሰጠን ነው። ለማገልገል የሚያበቃ ዓቅምን ለማግኘት እድሉ ስለተገኘ ነው በመሪነት ወይም በሌላ ተግባር ሕዝብን ማገልገል የሚቻለውም። የሌለው ሊሰጥ አይችልምና። ከሌለ መስጠት አይቻልምና። እግዚአብሔር ስለ ሰጠኝ ያለኝን ማከፋል ይገባኛል ማለት ነው አገልግሎት ማለት የሚባለውም ለዚህ ነው።

ሳይደላው እንዲደላን ያስቻለን፤ "ሳይማር ያስተማረን" ማኅበረሰብ ስላለ ነው የደረስንበት ደረጃ መድረስ የቻልነው የሚለውን ለማይዘነጋ ሰው አገልግሎትን የሕይወቱ አካል ማድረጉ የሚጠበቅ ነው። "ሳይማር ያስተማረንን" በዕውቀት በሙያ ማገልገል አለብን ማለት መቻል ነው የተቀበልነውን ነው የምንሰጠው ማለት። የተቀበልነውን ነው የምንሰጠው ማለት ሀብት እንድናገኝ ያስቻለንን ማኅበረሰብ ከአገኘነው ሀብት ድርሻ የማግኘት መብት አለው ማለትም ሊሆን ይችላል። ሀብት ላገኘንበት ማኅበረሰብ መልሰን እንሰጣለን የሚል ንግግር በለጋስነት ከታወቁ ሰዎች መስማትም የተለመደ ነው። የንግድ ተቋማትም ከሚያገኙት ትርፍ በዓመት የተወሰነውን ለሚገኙበት ማኅበረሰብ ወይም ከዚያም ባለፈ ለበጎ አድራጎት ሥራ የሚያውሉ ሰዎችን በብዛት ማዬት የሚቻለው በዚሁ መርህ መሠረት አገልግሎትን እንደ ግዴታቸው ስለሚቆጥሩት ይሆናል።

በአምስቱ መክሊት አምስት ማትረፍ እንደቻለው አገልጋይ፤ ላለው ይጨመርለታል ነውና የተቀበሉትን መስጠት ሲቻል የበለጠ ማግኘትም ይቻላል። ለመስጠትም ብዙም ትርፍ ነገር የግድ ሊኖር አይገባም። መስጠት የሚቻለው ካለው ላይ ቀንሶ ነው። "እንዲያው ሀብታም ብሆን ኖሮ ስንት ድሀ መርዳት እችል ነበር" የሚል ምኞት መስማት የተለመደ ነው። ካለው ከትንሹ መስጠት ከልተለመደ አይሞላም እንጂ ሞላልን በምንል ጊዜም እዳይጎድልብን የበለጠ ላለመሰሰታችን ምን ዋስትና ይኖረናል? የሚለውን ማሰብ ተገቢ ነው። እንዲህ ዐይነቱ ስስት ነው በገሀዱ ዓለም በዝቶ የሚታየውም። እንንዲያውም ከሀብታም ይልቅ ድሀ ለጋስ ነው ይባላል። ለእኔ ብቻ ከማለት ለሌላውም ማሰብ ሲቻል፣

ካለው ከውሱኑ ጊዜ፣ ካለው ከውሱኑ ዕውቀት፣ ካለው ከውሱኑ ሀብት፣ ቀንሶ ማካፈል ይቻላል:: በወንጌል እንደተጻፈ "አንዲትም ድሀ መበለት መጥታ አንድ ሳንቲም የሚያህሉ ሁለት ናስ ጣለች። ጌታም ይህን አይቶ ለደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ከትርፋቸው ጥለዋልና፣ ይህች ግን ከጕድለትዋ የነበራትን ሁሉ ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አላቸው":: (ማር 12፥44) ይህ ነው በጥቂቱ መታመን ማለት:: በጥቂቱ መታመን ሲቻልም ነው በብዙ መሾም የሚቻለው:: ባለው በጥቂቱ መታመን ማለት ትርፍ ነገር እስኪገኝ ሳይጠብቁ ባለው ነገር ሁሉ የሚቻለውን ለማገልገል ሲሞክር ነው:: ያን ጊዜ በብዙ መታመን ደግሞ ይቻላል:: በትንሽ ነገር ተጀምሮ ዛሬ ትልልቅ ሥራዎች እየሠሩ ያሉ ተቋማት እንዲሁ በጥቂቱ ስለታመኑ፣ በነበረው ውሱን ጥሪት በጎ ዐላማን ስላስቀደሙ፣ ብዙ ቢሰጣቸው የበለጠ መሥራት እንደሚችሉ ተፈትነዋልና የሚሠሩት ሥራ ሲባረክላቸው፣ ባላቸው ላይ ሲጨምርላቸው ማየት የተለመደ ነው::

4ኛ. በሌላ በኩል ለራስ ብቻ በመኖር እርካታ አይገኝምና ማገልገል ደስታን፣ እውነተኛ እርካታን፣ ውስጣዊ ሰላምን ያስገኛል የሚል ነው ሌላው የአገልግሎት መነሻ:: "ሰው ደስ ከሚለውና በሕይወቱ ሳለ መልካምን ነገር ከሚያደርግ በቀር መልካም ነገር እንደሌለ አወቅሁ።" ሲል ጠቢቡ ሰሎሞን የጻፈው ቃል ትልቅ ምስጢርን ይነገረናል:: (መክ. 3፥1-18) ለሰው ውስጣዊ እርካታ፣ እውነተኛ ሰላም እና ፍጹም ደስታን የሚያስገኝለት መልካም ማድረግ ነው:: ዘመናቸውን ሙሉ ለሰዎች መልካም በማድረግ ያሳለፉ ሰዎች ታሪክም ይሄንን ሐቅ ነው የሚያሳየው:: በለጋስነታቸው የታወቁ ሰዎች እንዲህ በሰፊ እጅ መለገስ የፈለጉት ከምን የተነሣ ነው? ለሚለው ጥያቄ ምልሻቸው አጭር ነው:: "እርካታንና ውስጣዊ ደስታን ስለሚፈጥርልኝ" የሚለው ነው ከሚበዙቱ የሚሰማው:: ከራሳቸው ይልቅ ለሰው የሚኖሩ ሰዎች የሚናገሩትም በገንዘብ ወይም በሌላ ቁስ ከሚገኝ እርካታ የበለጠ ደስታን በአገልግሎታቸው እንደሚያገኙ ነው::

ራስን መውደድና ራስን ብቻ መውደድ ልዩነት አለው:: ሰው ራሱን ሊጠላ አይችልምና:: መልካም አይደለም የሚባለው ራስን ብቻ መውደድ ነው:: የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆነው ክቡር የሰው ልጅ በየጎዳናው ወድቆ፣ በራብ እና በበሽታ በሚሰቃይበት ዓለም ራስን ማዕከል አድርጎ ለራስ ብቻ መኖር እርካታን አይሰጥም የሚለው ነው ቁምነገሩ::

የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ብዙ ገንዘብ ስላለ ብዙ ደስታን ማግኘት እንደማይቻል ማንም ሊመስክር የሚችለው በመጽሐፍም የተጻፈ እውነታ ነው (ሉቃ 12፥15):: ብዙ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ብዙ መዝናናት፣ የተመኙትን ሁሉ ማድረግ እንደሚችሉ ቢታወቅም እውነተኛ ሰላምን እና ደስታን ግን በገንዘብ መግዛት እንደማይቻል የብዙ ባለ ጠጎች ታሪክ ራሱ ማሳያ ሊሆን ይችላል:: ብዙ ምቾት በእጃቸው የሆነ ሰዎች ውስጣዊ ደስታና ሰላም ሲርቃቸው፣ በአደንዛዥ እፅ ተደግፈው ኑሮ ሲገፉ ወይም ራሳቸውን ሲያጠፉ የሚታይበት አጋጣሚ በተለይ በአደገው ዓለም ቀላል የሚባል አይደለም:: ራስ ወዳድ ብቻ በመሆን፣ ለራስ ብቻ በመኖር መቼም ውስጣዊ ሰላም፣ እርካታና ደስታ እንደማይገኝ ማሳያ ሊሆን ይችላል::

መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረንም ይህን እውነታ ነው:: "ብዙ ዘራችሁ፣ ጥቂትም አገባችሁ:: በላችሁ፣ ነገር ግን አልጠገባችሁም:: ጠጣችሁ ነገር ግን አልረካችሁም:: ለበሳችሁ ነገር ግን አልሞቃችሁም ደመወዙን የተቀበለ ሰው በቀዳዳ ከረጢት ያደርገው ዘንድ ደመወዙን ተቀበለ:: .... ይህ ስለ ምንድር ነው? ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር:: እናንተ ሁሉ ወደ እየቤታችሁ እየሮጣችሁ የእኔ ቤት ፈርሶ ስለ ተቀመጠ ነው::" የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ቤት የተባለ ክቡር የሰው ልጅ እየተጎሳቆለ ባለበት ዓለም "እኔን ከደላኝ ምን ቸገረኝ" ቢሉት እርካታም፣ ውስጣዊ ደስታም፣ በረከትም እንደማይገኝ የሚያሳስብ ነው:: (ሐጌ. 1፥7-9) ይህን ደግሞ ሁሉም በቀላሉ ሊረዳው የሚችል ነው፤ በሕይወት የሚታይ ስለሆነ::

5ኛ. ከዚህ በተጨማሪም በጎ ሥራን መሥራት ሲቻል ነው እንጂ መታወስ የሚቻለው ብዙ በመሰብሰብና በማከማቸት በበጎ መታወስ አይቻልም:: በዘመናችን ከምናውቃቸው ባለጠጎች መካከል ብዙ አከማችተው በጎ ተግባር ሳይከውኑበት ያለፉ ሰዎችን የሚያስታውሳቸው ሰው እምብዛም ነው የሚሆነው:: ሕዝብ የማይረሳው በጎ የዋለለትን ነው:: ሕዝብ የማይረሳው ተርቦ ያጎረሰውን፣ ታሞ ያሳከመውን፣ ልጆቹን ያስተማረለትን፣ ልማት የሠራለትን ነው:: በመንፈሳዊ ሕይወት ኮትኩቶ ያሳደገውን፣ ከክፉ ምግባር በምክሩ የመለሰውን ነው ሕዝብ የሚያስታወሰው:: እንዲህ ዐይነት በጎ ሥራ ለልጅ ብቻ አይደለም ከዚያም ባለፈ ለልጅ ልጅ ሊተላለፍም ይችላል:: መልካም ስምን ለልጅ እንደማውረስ ያለስ ምን የተሻለ እድል ይኖራል? አሻራ (legacy) የምንለውም እንዲህ ዐይነቱን ውርስ ነው::

6ኛ. በመጨረሻም አገልግሎት የነጻ ቢባል እንኳ ገንዘብ ወይም ሌላ ቁሳዊ ጥቅም አናገኝበትም ለማለት ነው እንጂ ሰማያዊ ዋጋ ግን አለው:: ወጥተው ወርደው ብዙ ያተረፉ፣ የአገርን ነጻነት ጠብቀው ለትውልድ ያስተላለፉ፣ ጥሪትን እንጂ እዳን ለትውልድ ያላወረሱ፣ "ሳይማሩ ያስተማሩ"፣ አገርን የሰበሰቡ፣ ትውልድን በእምነትና በበጎ ምግባር ያነጹ፣ መንጋውን እንደሚገባ የጠበቁ፣ የዓለምን አልጫነት ያጣፈጡ አገልጋዮች በየዘመኑ ይኖራሉ:: እነዚህ በጎ ሰዎች "አንተ በጎ ታማኝም አገልጋይ፣ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ፣ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ" እንደሚባሉም ለሚያምን ሁሉ የተሰጠ ተስፋ፣ ከአገልግሎት የሚገኝ ትልቁ ትርፍ ነው ማለት ይቻላል:: (ማቴ. 25፥14-25) "እግዚአብሔር፣ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፣ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና":: ተብሎ መጻፉም ለዚህ ተስፋ ማረጋገጫ ነው:: (ዕብ 6፥10) እኔ ምን አገባኝ ብለው ለራሳቸው ብቻ የኖሩ መሥዋዕትነትን ፈርተው ከእውቀታቸውና ከገንዘባቸው ጋር የተቀበሩ ሰዎችስ ትርፋቸው ምንድን ነው?

6.4 የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

አገልግሎት የሚገለጽበት አንዱ መንገድ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በሚባለው ነው:: የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በአንዳንድ አገሮች ትልቅ ድርሻ ያለው ነው:: በኢትዮጵያ ያን ያህል ያደገ አይደለም እንጂ:: ለምሳሌ ናሽናል ሰርቪስ በሚባል ድርጅት የወጣው መረጃ[36] እንደሚያሳየው በአሜሪካ በ2018 ብቻ አንድ መቶ ስድሳ ሰባት ቢሊዮን ዶላር ($167 ቢሊዮን) የሚገመት አገልግሎት በበጎ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን፣ በዚህም ሰባ ሰባት ሚሊዮን (77 ሚሊዮን) የሚጠጉ ሰዎች ተሳትፈውበታል:: ጊዜ እጅግ ውድ በሆነበት አገር ይህን ያህል ሕዝብ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲሳተፉ ማየት አገሪቱ ምን ያህል እድለኛ ናት፣ ይህንን ዐይነት ባህልስ የተከሉ ሰዎች ምን ያህል አስተዋዮች ናቸው ያሰኛል:: በእርግጥ እንዲህ ዐይነቱ በጎ ተግባር ገና ከልጅነት ዕድሜ ጀምሮ ታስቦበት እንደሚሠራ ነው ለማየት የሚቻለው:: ልጆች ከአሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በትምህርት ቤትና በሌሎች ተቋማት እንዲለማመዱ ይደረጋል:: በሥራ ቦታም ብዙ ተቋማት ሠራተኞቻቸውን በሥራ ሰዓታቸው የበጎ አገልግሎትን እንዲያበረክቱ ያደርጋሉ::

በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ብቻ አይደለም አገሪቱን የታደለች ናት የሚያሰኛት:: ሌላም ተመሳሳይ በጎ ባህል አላቸው:: አንድ ሰው ሲያልፍ ያለውን ሀብት እንደኛ ለቤተሰብ ብቻ ማውረስ አይደለም የተለመደው:: ለዩንቨርስቲዎችና ለምርምር ተቋማት፣ ለቤተ መጻሕፍት፣ ለሆስፒታሎች፣ ለእምነት ተቋማትና ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችም ማውረስ እንዲሁ የተለመደ ነው:: ባለጠጎችም በተመሳሳይ ገንዘባቸውን ለእነዚህ ዐይነት ተቋማት በየጊዜው በገፍ ነው የሚለግሱት:: ባለ ጠጎች ብቻም አይደሉ ለጋሾቹ:: እንዲያው መለገስ ባህላቸው ሆኗል ያሰኛል እንጂ:: ትልቁም ትንሹም ያቅሙን ያህል ይወረውራል:: የሚለመደው ደግሞ ከልጅነት ነው:: እንዲህ ባለ መዋጮ የሚሠራው ሥራ ስፍር ቁጥር የለውም::

[36] In 2018 , 77.4 Million Americans volutered, 6.9 billion hours served, $167 Billion dollars economic value, https://www.nationalservice.gov/serve/via

በዚህም ምክንያት የትምህርት ተቋማቶቻቸውን፣ ሆስፒታሎቻቸውን፣ ቤተ መጻሕፍቶቻቸውን፣ ሙዚየሞቻቸውን፣ የምርምር ተቋሞቻቸውን በዓለም ላይ ስመ ጥር ሆነው እንዲቀጥሉ አስችሏቸዋል::

አገልግሎት የሚፈጸመውም በዕውቀትና በሙያ ብቻ አይደለም፡፡ ካወቁበት ገንዘብም ትልቅ ማገልገያ መሳሪያ ነው:: በሚጠፋና በሚያልፍ ገንዘብ የማይጠፋና ዘላለማዊ ሥራን ሠርቶ ማለፍ ይቻላል:: ገንዘብንም ሲሠሩበት እንጂ ትርጉም ያለው ቢያከማቹት ዋጋ ቢስ ነው የሚሆነው:: ገንዘብ ትርጉም የሚሰጠው ሲያከማቹት ሳይሆን ሲሠሩበት መሆኑን የተረዱ በዓለም ላይ አሉ የተባሉ ብዙ ባለጠጎች አብዛኛውን ሀብታቸውን ለበጎ አድራጎት ሥራ ሲለግሱና ቀሪ ዘመናቸውንም ለበጎ አድራጎት ሥራ ሲያውሉም እያየን ነው[37]:: ይህ ነው አንዱ የአገልግሎት መገለጫ::

“በልባቸውም ቤታቸው ለዘላለም የሚኖር፣ ማደሪያቸውም ለልጆች ልጅ የሚሆን ይመስላቸዋል፣ ... ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም፣ እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ፡፡” እንደተባለ በገንዘባቸው በጎ ተግባርን የሚፈጽሙበት እንዳሉ ሁሉ ከሚጠቀሙበት ይልቅ አከማችተውት የሚያልፉትም የዚያኑ ያህል ይሆናሉ፡፡(መዝ. 49፥12) ለማን እንደሚሰስቡለት ባያውቅም የበለጠ ለማከማቸትና የበለጠ ለመሰብሰብ ደፋ ቀና ሲል የሚያልፈውም ቁጥሩ ቀላል አይደለም:: ያለ አገልግሎት ለራስ ብቻ በመኖር ሀብት መሰብሰብና ማከማቸት ቢቻልም አሻራን መተው ይቅርና ካለፉ በኋላ ገንዘባቸውን ማን እንደሚወርሰውና የወረሱ ሰዎች በገንዘቡ መልካም ወይም ክፉ እንደሚሠሩበት የማወቅና የማዘዝ ሥልጣን እንኳ አይኖራቸውምም::

የእኛን ሁኔታ ስንመለከት እንደሚታወቀው የቤተሰብ መረዳዳቱ ጠንካራ እሴት ቢሆንም በተለይ በዕውቀትና በገንዘብ ያለ ክፍያ በማገልገል ረገድ ውጤታማነቱ አርኪ አይደለም:: ቁጥራቸው ውሱን ቢሆንም የሰው ኃይል አስተባብረው በአስቸጋሪ ሁኔታ የሚችሉትን አስተዋጽዖ ያደረጉ

[37] America’s most generous billionaires gave half as much to charity in 2018 as in the previous year, https://www.vox.com/2019/2/12/18222403/tech-philanthropy-rankings-bezos-gates-zuckerberg

ተቋማት ግን ምሳሌነታቸው አልተነገርም እንጂ እድሉን አግኝተው በአገር ደረጃ እንዲነገር ቢደረግ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ለማስለመድ ትልቅ ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል::

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በኢትዮጵያ እስካሁን ያላደገበት ምክንያት ምንድን ነው? ወደፊትስ በምን መልኩ ማሳደግ ይቻላል? የሚለው ጥያቄ ሰፊ ጥናትና ውይይትን የሚጠይቅ ሆኖ በሁሉም ዘርፍ ያሉ መሪዎች አገልግሎትን ለማስፋፋት ቀዳሚ ድርሻ እንዳላቸው ግን አጠያያቂ አይሆንም:: ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሚታየው መነሣሣትና በጎ ጅምር የዚህ ማሳያ ሊሆን ይችላል:: በሌሎች አገሮች እንደሚታዬው በትምህርት ቤት፣ በመንግሥትና ንግድ ተቋማት፣ በሙያ ማኅበራት ወዘተ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሊያድግ የሚችልበትን ፖለሲ ከማዘጋጀት ጀምሮ ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ቢቻልና ያለመታከት የቅስቀሳና የማበረታታት ሥራ ቢሠራ ውጤት ሊገኝበት ይችላል::

አገልግሎት በግብታዊነት ከሚደረግ በእቅድና በጥናት ላይ የተመሠረተ ቢሆን የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚችልም የሚያጠያይቅ አይሆንም:: በተናጥል ለጊዜያዊ እርዳታ ከመረባረብ ሁሉም ባለደርሻ አካላትን በማስተባበር ተቀናጅቶ መሥራት ቢቻል የበለጠ ውጤታማ መሆን ይቻላል:: ከምንም በላይ ግን "ዓሣን አትስጠው ይልቁንም ዓሣ ማጥመድን አስተምረው[38]" እንደተባለው የሰዎችን ችግር ከመፍታት ሰዎች ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ማስቻል ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ወሳኝ ነው::

[38] 'Give a man a fish and he will eat for a day. Teach a man how to fish and you feed him for a lifetime.'

ምዕራፍ ሰባት

አገልጋይ መሪ

7. መሪነትና አገልግሎት

“መሪ አገልጋይ ነው” (Seravant Leader) የሚለው እሳቤ ሁለት ዋና ዋና ቁምነገሮችን የያዘ ነው:: አንደኛው የሥልጣን ዐላማ ሀብት ማጋበሻ፣ ስምና ዝና ማትረፊያ፣ ዘመድ አዝማድ መጥቀሚያ፣ የሥልጣን ጥምን ማርኪያ ሳይሆን ሥልጣን የማገልገያ መሳሪያ ነው የሚለው ነው:: “መሪ አገልጋይ ነው” በሚለው እሳቤ መሠረት ሥልጣን የሚያገለግላቸውን ስዎች ኑሮ ለመቀየር፣ የተሻለ ነገን እንዲያዩ ለማድረግ እንጂ ለራስ መገልገያ መሆን የለበትም የሚለው ነው ሥልጣን የማገልገያ መሳሪያ ነው ማለት:: በእርግጥ ስልጣንን ሌሎችን ለማገልገል ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻለው አገልግሎትን መረዳት ሲቻል ነው:: ብዙ መሪዎች “አገልጋይ ነን “ የማለታቸውን ያህል አገልግሎትን መረዳት የሚቻላቸው ጥቂት ናቸው ማለት ይቻላል:: አገልግሎትን የተረዱ መሪዎች ቢበዙ ኖሮ ለራሳቸው ብቻ የሚኖሩ ራስ ወዳድ የሆኑ፤ በአገልግሎት ስም ሕዝብን የሚዘርፉ፣ በብዙዎች ሞት የእነርሱን ነጻነት የሚያውጁ መሪዎችን ማየት ባልተቻለም ነበርና:: ለሰው የሚኖሩ ብቻ ሳይሆን፣ ለሰው ሕይወታቸውን

አሳልፈው የሚሰጡ፣ ለሀገራቸው የተሰው፣ እየተቸገሩ ሕዝባቸውን ያበለጸጉ፣ ለብዙዎች ነጻነት ዕድሜ ልክ የታሠሩ፣ የተሰጣቸውን የሰጡ በመክሊታቸው ያተረፉ እንዳሉም ሁሉ በአገልግሎት ስም ሥልጣንን ለግል ጥቅም ብቻ የሚያውሉም ብዙዎች ናቸውና::

ይህ አሁን በዘመናዊ ሥራ አመራር በአዲስ መልክ እየተስፋፋ ያለው "መሪ አገልጋይ ነው" የሚለው እሳቤ ራሱ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ለአገልግሎት ከማሰማራቱ አስቀድሞ የተናገረው መመሪያ መሆኑንም ማዬት ይቻላል:: "የአሕዛብ አለቆች እንዲገዙአቸው ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ:: በእናንተስ እንዲህ አይደለም፣ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን" እንዳላቸው:: (ማቴ. 20፥20-28) ለምንድን ነው ጌታ እንዲህ ዐይነቱን መመሪያ ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸው? ምክንያቱም በጊዜው የነበረው ልማድ ሥልጣን ከያዙ በሥልጣን መገልገል እንጂ ማገልገል የሚባል ነገር ስላልነበረ ሥልጣን ማገልገያ እንጂ መገልገያ መሆን አይገባውም ሲላቸው ነው::

ሁለተኛው "መሪ አገልጋይ ነው" የሚለው እሳቤ የሚያመለክተው በውድ እንጂ በግድ መምራት አይቻልም የሚለውን ነው:: ተከታይ ያለው ማለት ነው መሪ ማለት:: ተከታይ ሳይኖር መሪ መሆን አይቻልምና:: እውነተኛ ተከታይን ለማፍራት ደግሞ እውነተኛ አገልጋይ መሆንን ይጠይቃል:: ተከታይን ለማፍራት የሚያስፈልገው መፈራት ሳይሆን መታመን ነው:: ተከታይን ለማፍራት የሚያስፈልገው መፈራት ሳይሆን መከበር ነው:: ለመታመን ለመከበር ደግሞ ብልጣብልጥነት ሳይሆን ቅን መሆን፣ ሥልጣንን ለራስ መገልገያ ማዋል ሳይሆን ሌሎችን ለማገልገያነት መጠቀም ዘላቂና ዘመን ተሻጋሪ ሥራን ትቶ ለማለፍ እንደሚያስችል ነው በዓለም ታሪክ የሚታዬው እውነት:: "ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ" እንዲል ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘው ምክርም ተመሳሳይ ነው:: (1ኛጴጥ. 5፥3)

መምራትና መንዳት ልዩነት አለው:: እረኛና ምንደኛም የተለያዩ ናቸው:: እረኛ ነው ወይስ ምንደኛ? የሚለውን ለመለዬት ከፊታቸው ይሄዳል ወይስ በጎቹን ከኋላ ያሳድዳቸዋል? በጎቹ እረኛውን ይከተሉታል ወይስ እረኛው ይነዳቸዋል? ድምጹን ሰምተው እረኛቸው መሆኑን አውቀው ይከተሉታል ወይስ ድምጹን ሰምተው ምንደኛ መሆኑን ተረድተው ከእርሱ ይሸሻሉ? በጎቹን ይበትናቸዋል ወይስ አንድ መንጋ ያደርጋቸዋል? እረኛው ስለ በጎቹ ነፍሱን ይሰጣል ወይስ በጎቹን አውሬ እያስበላ ራሱን ያድናል? ለምለም መስክ ፈልጎ አሰማራቸው ወይስ በስንፍና አሥራባቸው? የሚለውን መጠዬቅ ተገቢ ነው:: አገልጋይ መሪ በመልካም እረኛ የሚመሰል ነውና::

በጎይል ሳይሆን ተመሪ መሪውን ያለ ግዳጅ ወዶ ፈቅዶ ሲከተል ስኬት ይኖራል:: ከመፈራታቸው ብዛት ሰው የሚንቀጠቀጥላቸው መሪዎች ፍጻሜያቸው ምን እንደሆነ በተለያየ ዘመን የታየ ነው:: በሌላ በኩል አሁን ባለው የሥራ አመራር ጥበብ የጌታና የሎሌ ሥርዓት ጊዜ አልፎበታል ማለት ይቻላል:: እንደ ፍቅር እስከ መቃብሩ ገጸ ባህሪ ፊታውራሪ አሰጌ "ባላገር ምን ያውቃል ያዘዙትን ከመፈጸም በቀር" ቢሉት በዚህ ዘመን አላዋቂነት ነው የሚሆነው:: እኔ አውቅልሀለሁ ሳይሆን እንመካከር ማለት ተሳትፎን ያሳድጋል:: ጊዜው ዝቅ ብሎ በትሕትና ማገልገል ሲቻል ብቻ ስኬታማ መሆን የሚቻልበት ነው:: ጊዜው በጎይል የሚገዙበት ሳይሆን በትሕትና ዝቅ ብሎ የሚያገለግሉበትም ነው::

አገልጋይ መሪ አለቅነትንና አገልጋይነትን በአንድነት ማጣመርን የሚጠይቅ ነው:: ለዘመናት አለቃ መሆን ጌታ እንደመሆን እንጂ አገልጋይ እንደመሆን አይቆጠርም፣ እንዲህም ታስቦ አያውቅም:: ዛሬ ዛሬ ግን መሪዎች የሚመሯቸውን ሰዎች "የእናንተ አገልጋይ ነን" የሚል ንግግር ሲናገሩ መስማት የተለመደ ነው:: አለቅነትን ከአገልጋይነት አጣምሮ ከያዘ ጌታም አገልጋይም (I am your Boss and I am Your Servant) መሆን ይችላል። አገልጋይ መሪ የሚለውን ከባድ የሚያደርገውም አለቃ ሆኖ አገልጋይነትን ማጣመር በማስፈለጉ ነው:: ከአለቅነት ጋር የሚሄደው ጌታ መሆን በአገልጋዮች መገልገልን ነውና:: ጌታ ሆኖ ሳለ ራሱን እንደ አገልጋይ ዝቅ ማድረግ በተግባር ቀላልም አይደለም:: እንዲህ ዐይነቱ

አመራር ነው በአገልግሎት እሳቤ ላይ የተመሠረተ አመራር (Servant Leadership) በመባል የሚጠራው::

በመጽሐፍ ቅዱስም ክርስቶስ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪና ጌታ ሆኖ ሳለ የደቀመዛሙርቱን እግር ማጠቡ የሚያሳየው ምሳሌነትም ጌታ ሆኖ አገልጋይ መሆን እንደሚቻል ነው:: "እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፣ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ:: እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል::" የሚለው መልእክቱ ጌታ ሆኖ ሳለ አገልጋይ መሆን ይቻላል የሚለውን በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ያረጋገጠ ነው:: (ዮሐ. 13፥13-14)

ይህ ዐይነት በአገልግሎት እሳቤ ላይ የተመሠረተ አመራር በሃይማኖት ተቋማት ወይም በጎ አድራጎት ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን በንግድ ተቋማትና በመንግሥት ተቋማትም በሥራ ላይ የዋለ እና እየተስፋፋ ያለ የሥራ አመራር አስተሳሰብ ነው:: በዚህ ዘርፍ ፈር ቀዳጅ እንደሆነ ከሚነገርለት ግሪንሊፍ ከተባለ የኮርፖሬሽን መሪ ከጻፈው መጽሐፍ[39] ጨምሮ ሌሎች ብዙ መጻሕፍትም ተጽፈውለታል::

በኢትዮጵያ በመሪዎች ዘንድ ይህ የአገልጋይነት እሴት ምን ይመስላል? ያሉት ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች? አገልጋይነትን ለማስፋፋት ያለው እድልና ተግዳሮት እንዲሁም የችግሮቹ መንስኤዎች? በዘመናት መካከል ያለው እድገት ወይም ማሽቆልቆል ምን ይመስላል? የሚለውን በሰፊው ማጥናትና እንዲህ ላሉ ጥያቄዎች በቂ መልስ ማግኘት ቢቻል የሥራ አመራር ችግሮቻችንን ለመፍታት የራሱ በጎ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው ማሰብ ይቻላል:: የገዥነት እንጂ የአገልጋይነት ባህል

[39] In his 1977 Book, Greenleaf argues that the essence of leadership is service, and that the leader should practice service to those he leads. The servant leader takes care to make certain that other people's highest priority needs are being served. He writes, "The best test, and difficult to administer, is this: Do those served grow as persons? Do they, while being served, become healthier, wiser, freer, more autonomous, more likely themselves to become servants.

እንግዳ በሆነበት አገር ዝቅ ማለት፣ መታዘዝ፣ ተጠያቂነት፣ ከራስ ይልቅ ሕዝብን ማስቀደም የሚለውን ለመተግበር የሰማይ ያህል ሩቅ ሆኖ ሊታይ ይችላል:: "ከእንጨት መርጦ ለታቦት ከሰው መርጦ ለሹመት" እንደሚባለው መሪነት ማለት ለገዥነት መመረጥ ተደርጎ ስንት ዘመን ሲተረክ ኖሮ ይህንን አመለካከት መቀየር ወይም መንቀል እንዴትስ ቀላል ይሆናል? የገዥነት አስተሳሰብን እንጠላለን፣ የሕዝብ አገልጋይ ነን የሚሉ መሪዎች እንኳ ሥልጣኑን ሲይዙት፣ ሥልጣን በእጃቸው ሲገባ ወዲያው እንደ ቀደሙት ገዥ ብቻ ሳይሆን አምባገነን ሆነው በታዩበት አገር የአገልጋይነትን ባህል ለመትከል ምን ያህል ብዙ ሥራ የሚፈልግ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው::

አገልጋይነት እሴታቸው የሆኑ መሪዎችን መፍጠር የሚቻለው፣ አገልጋይነት እንደ ባህል ሊያድግ የሚችለው በምን መንገድ ነው? የሚለው ጉዳይ ብዙ ምርምርን የሚፈልግ ቢሆንም የተወሰኑ ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎችንም ማንሣትና መወያዬት ጠቃሚ ይሆናል::

- ከግል ጥቅም፣ ዝና እና ክብር ይልቅ ሥልጣንን ለሕዝብ አገልግሎት የመጠቀም ባህል በኢትዮጵያ ምን ይመስላል?

- ሌሎችን ለማገልገል መጎዳት፣ ሌሎችን ለማክበር ራስን ዝቅ በማድረግ፣ መሥዋዕትነትን በመቀበል ዐላማቸውን አገልግሎትን የሚያደረጉ፣ በዐላማቸውም የሚጸኑ አገልጋዮችን ማፍራት የሚቻለውስ እንዴት ነው?

- እኔን ሰምታችሁ የምላችሁን አድርጉ ሳይሆን እኔን አይታችሁ እንደ እኔ ሁኑ የሚሉ፣ ቃላቸውና ግብራቸው የተስማማ፣ የሚሰብኩትን በሕይወት የሚኖሩ መሪዎችን ማፍራት የሚቻለው በምን መንገድ ነው?

- ሥልጣን የሕዝብ ማገልገያ ሆኖ ከተቆጠረ ከሥልጣን መልቀቅ የሚያስፈራው ለምንድን ነው? ለሕዝብ ታገልን የሚሉ፣ ሕይወታቸውን ለመገበር የቆረጡ፣ ጓደኞቻቸውን የቀበሩ፣ ብዙ

መከራን ያሳለፉ ሰዎች ሥልጣን ላይ ሲወጡ ምን ነክቷቸው ነው ሥልጣንን ለመክበሪያ፣ ለመከበሪያ፣ ለዘመድ አዝማድ መጥቀሚያ የሚያውሉት? ቃል ኪዳናቸውን እንዴት ሊረሱት ቻሉ? ወይስ ቀድሞውኑም ቢሆን ዐላማቸው ሥልጣንን ለመያዝና የራሳቸው ጥቅም ለማሳደድ ነበር?

- ሥልጣን ማገልገያ መሆኑን የተረዳ፣ በሥልጣን የማይባልግ፣ ሥልጣንን ለተረኛ አገልጋይ በፈቃዱ የሚለቅ አገልጋይ መሪ እንዴት ነው የሚገኘው?

እነዚህና የመሳሰሉ ነጥቦች በዚህና በሚቀጥለው ምዕራፍ በስፊው ይዳሰሳሉ::

7.1 አገልጋይ መሪ እንዴት ይገለጻል?

አገልጋይ መሪን ከሚገልጹት መካከል የሚከተሉት ሰባት (7) ጠባዕያት በዐብይትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ::

7.1.1 ትኩረቱ ሰው የሆነ

አገልጋይ መሪ ትኩረቱ ሰው ነው:: ከምንም ሰው ይቀድማል:: ከምንም ሰው ይከብራል:: ለዚህ ደግሞ የሰውን ክቡርነት የተረዳ ነው::

ሰው ምንድን ነው? ለፖለቲከኞች ሰው ምንድን ነው? ፈሪሃ እግዚአብሔር ላላቸው ሰዎችና ፈሪሃ እግዚአብሔር ለሌላቸው፣ በፈጣሪ ለሚያምኑና የፈጣሪን ሕልውና ለሚክዱ ሰዎች ሰው ምንድን ነው? የሚያምኑና የማያምኑ ሰዎች ዓለምን የሚያዩበት መነጽር፣ ዓለምን የሚረዱበት አመለካከት የተለያየ ሊሆን እንደመቻሉ የሰውን ክቡርነት በመረዳት ረገድም በሚያምንና በማያምን ሰው መካከል ልዩነት እንደሚኖር ይጠበቃል:: መሪ ዓለምን የሚያይበት መነጽር፣ ስለ ዓለም ያለው አረዳድና አመለካከት፣ እምነቱ ሁሉ በመሪነት ፍልስፍናው ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድርበትም የታወቀ ነው::

ሰውን ያለ ልዩነት ለማገልገል ከሁሉም አስቀድሞ ሰው በፈጣሪው ዘንድ ያለውን ክብር ማወቅ ያስፈልጋል:: የሰውን ክቡርነት ማወቅ ሲቻል ነው የሰው ሕይወት የከበረ መነሻ ያለው፣ ዐላማ ያለው፣ ትርጉም ያለው፣ የዘላለም ሕይወት ተስፋ ያለው መሆኑን መረዳት የሚቻለው:: የፈጣሪውን መልክና ምሳሌ የያዘ ለክብር በፈጣሪው አምሳል የተፈጠረ ክቡር ፍጥረት መሆኑን መረዳት ሲቻልም ነው ሰውን ከእንስሳት ለይቶ ማየት የሚቻለውም:: ድሀም ቢሆን ባለ ጠጋ፣ የተራቀቀ የተመራመረ ቢሆን መሃይም፣ ሴት ቢሆን ወንድ፣ ጥቁር ቢሆን ነጭ፣ ያንዱ ጎሳ ቢሆን የሌላው ጎሳ፣ ሁሉም ሰው በፈጣሪ መልክና ምሳሌ ለክብር ተፈጥሯልና በፈጣሪው ፊት እኩል ነው:: ለክብር የተፈጠረ ክቡር ፍጥረት ሰው፣ ድሀም ይሁን ሀብታም መከበርንም ይሻል::

አገልጋይ መሪም ይህን የተረዳ ነው:: የሰውን ክብር ካለመረዳት ሰውን እንደ እንስሳ ለሆዱ ብቻ የሚኖር፣ ሕሊና ቢስ፣ እምነት አልባ፣ አደርባይ አድርጎ ብቻ መመልከት ይመጣልና:: የሰውን ክብር ካለመረዳት ሰውን እንደ እንስሳ ተስፋ ቢስ፣ ዋጋ ቢስ አድርጎ ማዬትም ይኖራል:: የክፉ መሪዎች ችግርም ይሄው ነው:: ሰውን ለሆዱ ብቻ የሚኖር አድርጎ የመመልከት ችግር አለ:: ከሆድ ባሻገር ሰው እምነት ያለው፣ ሕሊና ያለው፣ ከሆድ ባሻገር ለእምነቱና ለሕሊናውም የሚኖር፣ የዘላለም ሕይወት ተስፋ ያለው፣ ፍቅርን የሚራብና ለፍቅር የሚኖር ሕያው ፍጥረት መሆኑን የሚዘነጉበት ጊዜ ብዙ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ክቡርነት በአግባቡ ለመረዳት ያስችላል:: በእርግጥ "ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጐበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው? ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው፤ በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው:: በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው፣ ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት:: በጎችንም፣ ላሞችንም ሁሉ ደግሞም የምድረ በዳውን እንስሶች፣ የሰማይንም ወፎች፣ የባሕርንም ዓሦች፣ በባሕር መንገድ የሚሄደውንም ሁሉ::" ተብሎ እንደተጻፈ ሰው ከሰማይ በታች ገዥነት ከፈጣሪ የተሰጠው ጸጋ ነው:: (መዝ. 8፥4-8) ከፍጥረታት

እንደ ሰው የከበረም ማንም የለም:: ቁሳዊውም ዓለም ለሰው ተፈጥሯል እንጂ ሰው ለቁስ አልተፈጠረም::

በእርግጥ "ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም፤ እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ" እንደተባለ ሰብዓዊ ክብሩን ለሆዱ ሲያስገዛ፣ ሕሊናውን ለጥቅም ሲሸጥ፣ ሰው ክብሩ እንደ እንደሚጠፉ እንስሶች ይሆናል:: (መዝ. 49፥12) እኔን ከደላኝ ምንተዳዬ በሚል ወገንን እና አገርን የሚጎዳ፣ ፈጣሪንም የሚያሳዝን ነገር ሲፈጽሙ ከምንም የማይቆጥሩት "ሰው እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ" እንደተባለው ሲሆን ነው:: ክፉውን ከደግ ለይቶ ለማወቅ ሕሊና የተሰጠው ሰው ማመዛዘን እንደማይችሉ እንደ እንስሳት ሲሆን ነው "ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም፣ እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ" የሚባለው:: ለእውነት የሚቆም ሰው በእነሱ ዘንድ እንደ ሞኝ እንደ አላዋቂ የሚቆጥሩ ሰዎች በየትኛውም ዘመን አይጠፉም:: ለክፉ መሪዎች መጠቀሚያ የሚሆኑትም እንዲህ ዐይነት አእምሮ የጎደላቸው ሰዎች ናቸው:: ለሆዳቸው ተገዝተው ክፋትን ሲፈጽሙ የሚኖሩ፣ ለሆዳቸው ሲሉ ግደሉ ሲባሉ የሚገድሉ፣ አሰቃዩ ሲባሉ የሚያሰቃዩ፣ ከሕዝባቸው ይልቅ የጥቂት አለቆቻቸውን ክብርና ጥቅም የሚያስቀድሙ በሚኖሩ ጊዜ፣ "ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም፣ እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ" የሚለው ነገር ይፈጸማል::

ከምንም በላይ ሰውን ማስቀድም የሚቻለው የሰውን ዋጋ፣ የሰውን ክቡርነት በአግባቡ መረዳት ሲቻል ነው:: የሰውን ክቡርነት መረዳት ሲቻል የሰው ሕይወት ያላግባብ እንዳይጠፋ መጠንቀቅም ግድ ይላል:: የሰውን ክቡርነት መረዳት ሲቻል ከጦርነት ይልቅ ችግርን በሰላም ለመፍታት ቅድሚያ መስጠት ይኖራል:: በእልህና ጀብደኝነት እርስ በርስ በተደረገ ፍትጊያና አለመግባባት ምክንያት በየዘመኑ ያለቀው የሰው ሕይወት ዋጋው ምን ያህል ነው? በድንበር ምክንያት በወንድማማቾች መካከል በተደረገ ጦርነት በየዘመኑ ያለቀው የሰው ሕይወት ዋጋው ምን ያህል ነው? ያን እንደዋዛ በየትውልዱ የረገፈ አገር ሊመራ የሚችል የተማረው የሰው ኃይል ምን መተኪያ አለው? በየዘመኑ እርስ በርስ በተደረገ ጦርነትና ግጭት ምክንያት የተፈጠረውን የትውልድ ክፍተትና የተማረ

የሰው ሀብት በምን መመላት ይቻላልስ? ምን መተኪያስ ይኖረዋል? የሚሉትን ጥያቄዎች ስንጠይቅ በየዘመኑ በነበሩ መሪዎች ዘንድ ለሰው ያላቸውን ዋጋ አመላካች ሊሆን ይችላል:: ትልቁ ጥያቄ ግን ወደፊትስ ተመሳሳይ ታሪክ እንዳይደገም የሰውን ክቡርነትና የሰውን ዋጋ መረዳት፤ ማጤን የሚቻለው እንዴት ነው? የሚለው ነው::

እንጆራ ፍለጋ ተሰደው በየበርሀው የባዘኑ፣ በባዕድ አገር በእየእሥር ቤቱ የሚሰቃዩ፣ በየውቅያኖሱ የሚሰጥሙ የዜጎች ክብር፣ የዜጎች ዋጋስ ምን ያህል ነው? "ከገንዘባችሁ በፊት ሰዎቼን ፍቱልኝ" ማለት የሚቻለውም ይህን ከመረዳት ነው:: አገልጋይ መሪ ይህን የተረዳ ነው:: በስደት በየበርሀው የባዘነ ወገንን ፈልጎ ለሀገሩ እንዲበቃ ከማድረግ የበለጠስ ምን ደስታ ይኖራል? ለገባው ከዶላር ሰው እጅግ ውድ ነው:: የዜጋ ክብር የአገር ክብር ነውና:: ሰዎቿን የማታከብር አገርስ ማን ሊያከብራት ይችላል? ለዜጋ ዋጋ በሚሰጡ በአደጉ አገሮች ለአንድ ዜጋ ክብር ብዙ መሥዋዕትነት ሲከፈል ማዬትም የተለመደ ነው:: አንድን ዜጋ ከችግር ለማዳን የሚከፈለው መሥዋዕትነት ሁሉ ይከፈላል::

በወንጌልም ይህንን የመሰለ ምሳሌ አለ:: መቶ በጎች ያሉት ሰው ከመቶው አንዷ ብትጠፋበት ዘጠና ዘጠኙ ካሉልኝ ምንም ችግር የለውም ሳይል ዘጠና ዘጠኙን ትቶ የጠፋውን በግ ሊፈልግ እንደሚሄድ፣ ባገኘውም ጊዜ ከደስታ ብዛት ተሸክሞት እንደሚመለስ ተጽፏል:: (ሉቃ. 15፥4-9) ሃይማኖታዊ ምስጢሩ ጥልቅ ቢሆንም ምሳሌውን እንዳለ ለሚያይ፣ የሰው ክብር ማለት የቁጥሩ ብዛት፣ የተማሩ ወይም ያልተማሩ፣ ሥልጣን ላይ ያሉ ወይም ተርታ ሰው የመሆኑ ጉዳይ እንዳልሆነ፤ ሰው ዋጋው ከምንም በላይ መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: ይህንን በማሰብ ነው ስማቸው የታወቀ ቢሆንም ስማቸው ያልታወቀ ቢሆንም አገርንና ወገንን በዓቅማቸው ያገለገሉ፤ ለአገር ሲሉ መሥዋዕትነትን የሚቀበሉ ሰዎች የሚገባቸውን ክብር ሊነገፈጋቸው አይገባም የሚባለውም::

የሰው ክብር ላልገባቸው መሪዎች ነገሩ እንዲህ አይደለም:: ሰው ለእነርሱ የሚለካው በሀብቱ ነው፤ የሚለካው በእውቀቱ ነው፤ ሰው ለእነርሱ የሚለካው በሥልጣኑ ነው:: የሰው ክብር ላልገባቸው መሪዎች የሰው

ክብር እነርሱን ሲሆን ወይም እነርሱን ሲመስል ነው:: እሽ በጂ ብሎ ሲታዘዝ ለሕሊናው ሳይሆን ለአለቆቹ ትእዛዝ የሚገዛ ሰው እርሱ ነው በእነርሱ ዘንድ የሚከብረው:: እነርሱን የማይመስል፣ እነርሱን የሚቃወም ሰው ከክብሩ ተዋርዶ እንዲሰቃይ ማድረግ ሰው በፈጣሪው ዘንድ ያለውን ክብር ከለመረዳት የሚመጣ ነው ለማለትም ይቻላል::

7.1.2 ቅድሚያ ለሰው ሀብት

አገልጋይ መሪ ለአንድ አገር ትልቁ ሀብት ሰው መሆኑን የተረዳ ነው:: ያለ ሰው አገር ባዶ ነው:: ሁሉም በሰው ይገኛል፤ ሁሉም በሰው ይሆናል:: ሰው ከሌለ የተፈጥሮ ሀብትም በረከት መሆኑ ቀርቶ መርገም የሚሆንበት ጊዜ ብዙ ነው:: ይሄው ነው ብዙም የተፈጥሮ ሀብት የሌላቸው ግን በሰው የከበሩ ባለ ጠጋ አገሮች የመኖራቸውም ምስጢር:: እኔ ብቻ ልብላ፣ እኔ ብቻ ልበልጽግ በሚል፣ ከሰው ይልቅ ሀብት ለሚያማልለው ሕዝብ የተፈጥሮ ሀብት ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊበዛ ይችላል:: ከምንጨራረስ ሀብቱ ባልተገኘና በፍቅር በሰላም ከነድህነታችን በኖርን የሚያሰኝበት ገጠመኝ ብዙ ነው:: የተፈጥሮ ሀብት መርገም የሆነባቸው አገሮች በአፍሪካ ብቻ ስንት ናቸው? እንዲህ ባሉ አገሮች ጥናቶች የሚያሳዩት በተገኘው የተፈጥሮ ሀብት ጥቂቶቹ ሲከበሩ የሚበዙቱ ግን እያደር ሲቆረቁዙ ነው:: [40] ሰው ሲጠፋ ምርጫው ተባብሮ ከማልማት ይልቅ ተቧድኖ መጠፋፋት ነው የሚሆነው:: ሰው በከበረባቸው አገሮች የተፈጥሮ ሀብት ለትውልድ ይተርፋል:: የሚደማመጥ፣ የሚከባበር፣ የሚተሳሰብ ሰው ባለባቸው አገሮች የተፈጥሮ ሀብት በረከት ነው::

[40] "Overall, the decline in poverty rates in resource-rich countries has generally lagged that of the region's non-resource rich countries," Income distribution remains highly unequal in most countries in the region … To a large extent, the benefits of growth have not reached the poorest segments of society.", https://www.theguardian.com/global-development/2012/oct/25/natural-resources-blessing-curse-developing-countries

በሌላ በኩል ይህን የሰው ሀብት ጥቅም የተረዳ መሪ ከምንም በላይ ትኩረቱ ሰው ነው:: የተሻለ ዜጋን ለመፍጠር ከሁሉም ቅድሚያ ሰጥቶ ይሠራል:: ድልድይ ወይም መንገድ ከመሥራት አስቀድሞ ድልድይ ወይም መንገድ ሊሠራ የሚችል የሰው ኃይልን ይገነባል:: ሰው ላይ ሀብቱን ያፈሳል:: የነገውን ሰው ለማፍራት በተቻለው መጠን ሁሉ ይደክማል:: ሕንጻ ከማበራከት በሰላም በፍቅርና በመተሳሰብ መኖርን የሚያስቀድመውን የሰው አእምሮን ቅድሚያ ሰጥቶ ያንጻል:: በሥነ ምግባር የታነጸ፣ ሰውን በሰውነቱ የሚያከብር ዜጋን ማፍራት ካልተቻለ የተገነባው ሁሉ በቀላሉ ሊፈርስ እንደሚችል ይረዳልና::

የዘመኑ ውድድር ከምንም በላይ በሰው ኃይል መሆኑን የተረዱ አገሮች ዛሬ ከሁሉ አስቀድሞ የሰው ሀብታቸውን በዕውቀት ብቻ ሳይሆን በሥነ ምግባር የታነጸ እንዲሆን ለማስቻል እየተረባረቡ የሚገኝበት ጊዜ ነው:: የሰው ሀብት ቁልፍ ጉዳይ ነው፤ በተለይ በዚህ የዕውቀት ዘመን:: የቀደመ ይመራል ከኋላ የቀረ ደግሞ ይከተላል:: የዓለም ሥርዓት እንዲህ ነው:: በዕውቀት ነው መወዳደር የሚቻለው:: የትምህርት ጥራት ከመቼውም ጊዜ በላይ ሊሻሻል ሲገባው ማሽቆልቆሉ ከቀጠለ ከመንደር ባለፈ ማሰብ የሚችል ትውልድን ማፍራት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል የሚባለውም ይህንን በማሰብ ነው:: እንደ አገር አሁን የደረስንበት ሁኔታ በትምህርት፣ በአስተሳሰብ፣ በአመለካከት፣ በሥነ ምግባር እና በመሳሰሉ ዘርፎች በሰው ላይ የተሠራው ሥራ አናሳ ከመሆን ጋር የሚያያዝ ለመሆኑ ከውጤቱ መረዳት ይቻላል::

ቅንነት በጎደለበት የፖለቲካ ባህል ምክንያት፣ እንደ አገር ከታጣው ሁሉ በየዘመኑ የተሰደደው የተማረ የሰው ኃይል በምንም ሂሳብ ሊተመን የሚችል አይደለም:: እውነትም በየዘመኑ የተገደሉት፣ በየአገሩ የተሰደዱት ኢትዮጵያንውያ ዋጋ በምን ሊተመን ይችላል? አገር እንደዚያ የተደከመባቸውን ብርቅዬ ልጆቿን በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል የቅንነት ባህል ቢኖራት ዛሬ የት መድረስ በተቻለ ነበር? ያሰኛል:: ይህ ሁሉ ግን በቅንነት ለሚያየው ነው:: ተንኮል በበዛበት የፖለቲካ ባህል አገሪቱ ምን ያህል ሰው ታጣለች ሳይሆን ዋናው ጉዳይ ስጋት ናቸው

የሚባሉ ሰዎች በአንድም በሌላም መንገድ መወገዳቸው ነው የሚሆነው:: ዋናው ጉዳይ ሥልጣኑን መያዝ እንጂ የተማሩ ሰዎች ኖሩ አልኖሩ ብዙ ቁምነገር የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑ ከቀረ ሰነባበተ::

ይባስ ብሎ ያለውንም የሰው ሀብት በአግባቡ መያዝ ከልተቻለ፣ ከዕውቀትና ችሎታ ይልቅ የፖለቲካ ታማኝነትና ወገናዊ የሆነ አድሏዊ አሠራር የሚኖር ከሆነ፣ በዕውቀታቸው ብቻ ሠርተው ሀገራቸውን እያገለገሉ ለመኖር የሚፈልጉ ባለሙያዎች እንዲሰደዱ መንገድ ይከፍታል:: የተማረው የሰው ኃይል ወደ ውጭ የሚጎርፍ ከሆነም የተሻለ ልምድ እና ዕውቀት ያላቸው ሰዎችን ስለሚያሳጣ ተተኪ መሪዎችን የማፍራቱን ሂደትንም ዳገት ያደርገዋል::

አንድ ሰው እንዳሉት በእርግጥ የኢትዮጵያ የሰው ሀብት የአባይ ወንዝን ይመስላል:: ምንጩ ነው እንጂ ኢትዮጵያ ማልማት የሚጀምረው የሚመች ቦታ ሲያገኝ ነው:: የሚመቸው እስኪያገኝ የያዘውን ይዞ ይጓዛል፣ የሚጠቀምበት ሲያገኝ ያጠራቀመውን ይሰጣል:: ለመስጠትም አይሰስትም:: ሀገሩ ግን ብዙም አትፈልገውም:: የትም ተሰዶ ያጠራቀመውን ዕውቀት ግን ምንም ያልደከመበት ሀገራት እንደ አባይ በነጻ ሀገራቸውን ያለመበታል::

ዛሬ ኢትዮጵያውያንን በዓለም ላይ ቀዳሚ በሚባሉ ተቋማት በብዙ ቁጥር ከፍተኛ ቦታ ይዘው ሲሠሩ፣ በሓላፊነት ሲመሩ ማየት የተለመደ ነው:: ዛሬ እንደ አሜሪካ ባሉ አገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዶክተሮች፣ የኮምፒውተር ባለሙያዎች ማሀንዲሶችና ሌሎችም ባለሙያዎች አገር ውስጥ ካለው ቁጥሩ የሚተካከል ነው ይባላል:: ይህ ምን ያህል ክስረት እንደሆነ ሒሳቡ ቀላል ነው:: በየምክንያቱ የተሰደዱ ምሁራን በበለጸጉ አገሮች ተአምር ሲሠሩ ለሚያይ መቼ ይሆን ኢትዮጵያ ለውጭ ሲሳይ የሆኑ ተአምር ሰሪ ልጆቿን አሰባስባ የበረከቱ ተካፋይ መሆን የምትችለው? እያለ መመኘቱም የሚጠበቅ ነው:: እንዲህ ዐይነቱ ምኞት መልስ ሊያገኝ የሚችለው ከሁሉም በላይ ከራሳቸው ሥልጣን በላይ የአገርን ጥቅም የሚያስቀድሙ አገልጋይ መሪዎች ሲገኙ ነው እንጂ::

በእርግጥ ምሁራንን ቀድሞውኑ እንዳይሰደዱ ማድረግ እንጂ ከተሰደዱ በኋላ ለመመለስ ቀላል አይሆንም:: ከብዙ ድካም በኋላ በውጭ ኑሮ የመሠረተን ሰው ወደ ሀገሩ ተመልሶ ለማገልገል ብዙ ውጣ ውረድ አለው:: በዚያውም ላይ አገር የማገልገል ባህል በደንብ የዳበረ ባልሆነበት ሁኔታ ነገሩን የባሰ አስቸጋሪ ያደርገዋል:: መመለስ ባይቻል እንኳ በብዙ አገሮች እንደሚደረገው ሚያተኞች በየሙያቸው ባሉበት ሆነው የሚያገለግሉበትን እድል መፍጠር ግን ይቻላል:: ይህም ከሁሉም ወገን ቅንነትን ይፈልጋል እንጂ::

ለሰው ትኩረት መስጠትን በተመለከተ በሃይማኖት ተቋማትም ችግሩ የሚታይ ነው:: ሃይማኖት ትኩረቱ ሰው ሆኖ ሳለ በሃይማኖት ተቋማት በዝቶ የሚስተዋለው ግን ሰውን ከማነጽ ይልቅ ሕንጻን መገንባት ሆኗል:: በአንዳንዶች ዘንድ የመሪዎች ውጤት የሚለካው በሚያስገነቡት ግንብ ወይም በሚያስገኙት የገንዘብ መጠን እስኪመስል ድረስ በዝቶ የሚነገረው እንዲህ ዐይነቱ የሥራ አፈጻጸም ነው:: ምን ያህል ሰው ከሱስ ተላቆ ጤነኛ እና አምራች ዜጋ መሆን ቻለ? ምን ያህል ሰውን ከጎዳና ወይም ከዝሙት ተዳዳሪነት ሕይወት ማላቀቅ ተቻለ? ምን ያህል ስደተኞችን ማቋቋም ተቻለ? ምን ያህል የተሰበረ ቤተሰብ ሊጠገን ቻለ? ምን ያህሉ ግጭት በሰላም ተፈታ? ፍቅርና አንድነቱ ምን ያህል ጎለበተ? የእምነቱ ተከታዮችስ በበጎ አስተሳሰብና በሥነ ምግባር እያደጉ ነው? የሚለውና የመሳሰለው ሥራ ብዙም ሚዛን የሚደፋ አይመስልም:: የተቸገረን ሰው ለመርዳት ገንዘብ አዋጡ ከሚባል ይልቅ የፈረሰ ቤተ እምነትን ለማነጽ አዋጡ ቢባል የበለጠ ገንዘብ የሚያዋጣው ይበዛል የሚባለውም ለዚህ ማሳያ ሊሆን ይችላል::

ለመሆኑ ስንት ሰዎች ናቸው ሊለምኑ አፍረው በራብ የሚሰቃዩት? ስንቶቹ ናቸው ጠያቂ አጥተው በሕመም ብቻቸውን የሚሰቃዩት? ስንቶቹ ናቸው ጠያቂ ሳይኖራቸው በእሥራት ላይ ብቸኛነት ሲያሰቃያቸው ጊዜያቸውን በባዶነት የሚገፉት? በለጋ ዕድሜያቸው ባለመታነጻቸው ሲያድጉ አምራች ዜጋ ከመሆን ይልቅ አፍራሽ ዜጋ የሚሆኑትስ ስንት ናቸው? የሚሉትን መመርመር ሲቻል በእየእምነታቸው የሃይማኖት ተቋማትም ይሁኑ

የዕምነቱ ሰዎች እንዲህ ላለው ነገር የሚሰጡት ትኩረትና የሚኖራቸውን ሱታፌ ምን እንደሚመስል መገመት አያስቸግርም:: እንዲህ ዐይነቱን ጥያቄ መጠየቅ ቢኖር ቤተ እምነቶችን በከበሩ ድንጋዮች ከማንቆጥቆጥና በየሃምሳ ሜትሩ ርቀት አዳዲስ ቤተ እምነቶችን ለማነጽ ከመትጋት ይልቅ የሰዎችን ሕይወት ማነጽን ማስቀደም በተቻለም ነበር::

ጥያቄው ለምን እንዲህ ሆነ? የሚል ከሆነ ለሰው ያለው ዋጋ አናሳ ከመሆኑ ጋር ሊያያዝ የሚችል እንደሚሆን መገመት ይቻላል:: አሁን በእያንዳንዱ የሃይማኖት ተቋማት ሰው ላይ የሚሠራው ምን ያህል ነው? የተሠራው ሥራስ ምን ያህል ፍሬ አፍርቷል? ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ አስደንጋጭ እንደሚሆን የሚጠበቅ ነው:: ሃይማኖት ሰውን የሚያከብር እግዚአብሔርን የሚፈራ ትውልድን ማፍራት ካላስቻለ፣ ሃይማኖት በፍቅር የሚተሳሰብና የሚረዳዳ፣ ዘረኝነትን የሚጸየፍ፣ እውነትን የሚያውቅ፣ ለእውነት የሚያደላ፣ የአገልግሎትን በቁዔት የተረዳ፣ ለተበደሉት ፍትሕን የሚያስገኝ ትውልድን መፍጠር ካላስቻለ ፋይዳው ምን ላይ ነው? ይህም በሰው ላይ የተሠራው ሥራ ምን ያህል ደካማ መሆኑን ማሳያ ሊሆን ይችላል:: ዛሬ በአውሮጳና አሜሪካ የሚያማምሩ አብያተ ክርስቲያናት ያለ ሰው ወና ሆነው ወደ ሙዚየምነት፣ ወደ ሲኒማ ቤትነት፣ ወደ ንግድ ቤትነት እየተቀየሩ ያሉት በሰው ላይ አስቀድሞ በቂ ሥራ ባለመሠራቱና ተተኪ ትውልድ በመጥፋቱ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከእነርሱ መማር አለመቻላችንም ችግሩ የእኛን ቤት እስኪያንኳኳ የመጠበቅ ልማድ ያመጣው ነው ከማለት ሌላ ምን ሊባል ይችላልስ?

ይህ ሁሉ የአስተሳሰብ ለውጥ የሚፈልግ ጉዳይ ነው:: ሰውን ማስቀደም ሲለመድ ከዕውቀት ማነስ የተነሣ በሱስ የሚባዝነውን ትውልድ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይኖራል:: ሰውን ማእከል ማድረግ ሲቻል ትልልቅ ሕንጻዎችን ከመገንባት ይልቅ አቅመ ደካሞችን ማገዝና ራስን ማስቻል ቅድሚያ ይሰጠዋል:: ሰውን ትኩረት ማድረግ ሲቻል በችግር ምክንያት ለሴተኛ አዳሪነት የተዳረጉትን፣ በሱስ የተጠመዱትን፣ በለጋነታቸው ጥላቻን የተማሩትን፣ ከሥራ ይልቅ ለጥፋት የተሰማሩትን፣ መለያየት የሚሰብኩትን መመለስና ማቋቋም ቀዳሚው ተግባር ይሆናል::

በእርግጥም የሰውን ክቡርነት መረዳት ሲቻልና ሁሉም በሰው ይገኛል የሚል አስተሳሰብ ሲኖር ከምንም ሰው ይቀድማል የሚለው አመለካከት ገሸር ይሆናል::

ነገሩ ሃይማኖታዊ ምስጢር ቢኖረውም በመጽሐፍ ቅዱስ ይህን የሚያሳይ አንድ ታሪክ አለ:: ደቀመዛሙርቱ በሌላው ዘንድ እንደተለመደው በጊዜው የነበረውን እጹብ ድንቅ ቤተመቅደስ አድንቀው ለጌታ ያሳዩታል፡፡ ክርስቶስ ትኩረቱ ሰው እንጂ ታይቶ የሚጠፋው ቁሳዊው ነገር አይደለምና "ይህን አታድንቁ፤ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ አይቀርም" በማለት ነበር መልስ የመለሰላቸው:: (ማቴ 24፥1-2) አሁንም ግን ድንጋይ በድንጋይ ላይ የመገንባት እንጂ ዘለዓለማዊ ሕይወትና ክብር ያለውን የሰውን ልጅ የማነጽ ተግባር እምብዛም ነው:: ቁሳዊ ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ ልማድ በሆነበት ዓለም ድንጋይ በድንጋይ ላይ መፍረሱ እንደማይቀር፣ ቁሳዊው ነገር ሁሌም ጊዜያዊና ፈራሽ መሆኑ ብዙውን ጊዜ ይዘነጋል:: የሰው ሕይወት ከፈረሰ መልሶ መገንባት እጅግ አድካሚ ነው:: ሰው ላይ መሥራት ካልተቻለ የተገነባውን ለማፍረስም ቀላል እንደሚሆንም ብዙም ማሰብ አይፈልግም:: በቅርብ ሲሆን የነበረውን ማሰቡ ይበቃል:: የሚያፈርስ ሳይሆን የሚገነባ የሰው ሀብት ማፍራት ከተቻለም የፈረሰ ከተማን መልሶ መገንባት ከባድ አይሆንም::

7.1.3 ከመሥዋዕትነት ቁርጠኝነቱ ያለው

አገልጋይ መሪ ለዐላማ እንጂ ለሆዱ ያደረ አይደለም:: ከወገኖቹ ጋር መከራን ይቀበላል እንጂ በሥልጣን ተታሎ ወገኖቹን አሳልፎ አይሰጥም:: በኃጢአት ከሚገኝ ሀብት ይልቅ ማጣትን ይመርጣል:: ለተበደሉ ይቆማል እንጂ ከበዳዮች ጋር አብሮ ዓቅም የሌላቸውን አይበድልም:: አገልጋይ መሪ እኔን ከደላኝ ምን ቸገረኝ አይልምም:: ሌላውን ለማዳን ሲል እርሱ ይሰደዳል፣ ለሌላው ነጻነትም የራሱን ነጻነት እስከማጣት ይደርሳል እንጂ:: የሌሎች ሰዎችን ችግር ለመፍታት የምኞት ኑሯቸውን በፈቃዳቸው ትተው መከራ የተቀበሉ ብዙ መሪዎች በታሪክ የመመዝገባቸው

ምስጢርም ይሄው ነው:: የብዙ አገልጋይ መሪዎች አፈጣጠርም ምክንያቱ የወገኖቻቸው ስቃይ ነው::

ይህንን የሚያሳይ ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስ ይጠቅማል:: በመጽሐፈ ነህምያ እንደተጻፈው፣ ነህምያ ከራሱ ይልቅ ወገኑንና አገሩን የሚያስቀድም፣ ስለ ሀገሩና ወገኑ መሥዋዕትነትን ለመቀበል የተዘጋጀ አገልጋይ መሪ ነበረ:: ነህምያ ስደተኛ ነው:: ወደው ሳይሆን ተገደው ከተሰደዱ ስደተኛ ቤተሰቦቹ በስደት አገር በባቢሎን የተወለደ:: ክክርስቶስ ልደት በፊት በ 586 ዓመተ ዓለም ገደማ ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን አፍርሰው ወገኖቹን ለባርነት አጋዟቸው:: ነገር ግን ነህምያን እግዚአብሔር በስደት አገርም ቢሆን አልተለየውም:: በ444 ዓመተ ዓለም ገደማ የፋርስ ሰዎች ባቢሎንን በቅኝ ግዛት ሲይዙ ነህምያ በፋርስ ቤተመንግሥት እድል አገኘ:: ያውም የንጉሡ አርጤክስስ መጠጥ አቅራቢ በመሆን:: ነህምያ በስደትም ቢሆን እንዲህ ባለ ታላቅ ማዕረግ በንጉሡ ታማኝነትን ያገኘ የተሳካለት የሚባል ዐይነት ሰው ነበር:: ነገር ግን ከራሱ ምቾት ይልቅ በወገኖቹ መከራ በሀገሩ መፍረስ የሚያዝን ነውና ጉዳዩ እረፍት ነሣው::

በስደት አገር እንዲህ እንደ ዛሬው ዜና ለማግኘት ቀላል አልነበረም:: ዜና በሚዲያ አይገኝምና ሰው መጠበቅ ነበረበት:: ከኢየሩሳሌም የተመለሱ ሰዎችን ባገኘ ጊዜ በምርኮ ስለ ፈረሰችው ከተማና ስለ ወገኖቹ ጠየቀ:: ያገኘውም መልስ የሚያሳዝን ነበር:: የኢየሩሳሌም ቅጥር ፈርሶአል፤ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋል፤ ከምርኮ የተረፉት ወገኖቹም በታላቅ መከራና ስድብ ይኖራሉ:: በዚህም ነህምያ ተቀምጦ አለቀሰ:: ከጾምና ከጸሎት ጋር ብዙ ቀንም አዘነ:: ለሚያየው ሁሉ እስከሚያስታውቅ ድረስ ልቡ በኀዘን ተሰበረ:: ነህምያ ልቡ በኀዘን እንደነበረ ንጉሡ ያወቀው ፊቱን በማየት ብቻ ነበረ:: ነህምያ በኀዘን ብዛት እንደታመመ ሰው መሰለም:: ኀዘኑ ጥልቅ ነበርና:: ነህምያ ያዘነውም ጥቅሙ ተነክቶበት ወይም አንዳች ነገር ጎድሎት ሳይሆን ሀገሩ ስለፈረሰች፣ ወገኖቹ ስለተረገጡ ነበረ::

እንዲህ ባለ ጊዜ ነው የሕይወት ምርጫ ከባድ የሚሆነው:: እንደ ነህምያ መምረጥ ግን የግድ ነው:: የተጎሳቆለ ወገኑንና አገሩን ወይስ የተደላደለ ኑሮውን? ነህምያ አገሩን እና ሕዝቡን አስቀደመ:: አገልጋይ

መሪ አገልግሎትን የሚገባበት ተገዶ ሳይሆን በምርጫ ነውና:: እንዲህ ዐይነት አገልጋይ መሪዎች በታሪክም ብዙ ታይተዋል:: እግዚአብሔር "አገርን ያለሰው አያስቀርም" እንደሚባለው ሰው በጠፋ ጊዜ እንደ ነህምያ የፈረሰውን የሚሠራ የወደቀውን የሚያነሣ መሪን ያዘጋጃል::

አገልግሎት መሥዋዕትነት ነው:: ለአገር ለወገን ተጎዳሁ ዋጋ ከፈልኩ ማለት አንድ ነገር ነው:: ጥያቄው መሥዋዕትነት በምን ይገለጻል? ሚዛኑ ምንድን ነው? የሚለው ነው እንጂ:: የተከፈለው ዋጋ ምንድን ነው? ዋጋ የተከፈለው ለማን ነው? የተከፈለው ዋጋ ትርፍ አመጣ ወይስ ኪሳራ? የሚለውንም መጠየቅ ተገቢ ነው:: በአገልግሎት የጠቀምኩት እኔን ነው ወይስ ሌሎችን? ለአገር ለወገን ምን አጣሁ? የሚለውም እንዲሁ::

እንደ ነህምያ ለወገኔ፣ ለሕዝቤ፣ ለአገሬ ስል የተሻለ አማራጭ እያለኝ ይቅርብኝ አልኩ፤ በውጭ አገር የተደላደለ ኑሮ መኖር እየቻልኩ አገሬን ለማገልገል ወደ አገሬ ተመለስኩ፤ የተሻለ ደመወዝ የሚከፈለኝ ሌላ እድል እያለ በአነሰ ደመወዝ አገልግሎትን መረጥኩ፤ ለሕዝቤ ለወገኔ ስል እንቅልፍ አጣሁ፤ በትጋት ሠራሁ፤ ከፍ ሲል ደግሞ ለሕዝቤ ለወገኔ ስል ታሰርሁ፤ ተሰደድሁ የሚል እውነተኛ አገልጋይ ስንት ሰው ማግኘት ይቻል ይሆን? የሚለው ሲጠየቅ ነው መሥዋዕተነትን የከፈለው ሰው የሚባለውን ያህል ሆኖ የማይገኘው::

7.1.4 አገር ወዳድ

አገር ወዳድነት አገልግሎት ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ ነው:: እንደ ኢትዮጵያውያን አገር ወዳድ የለም፤ በሄዱበት ሁሉ አካላቸው እንጂ ልባቸው ከአገሩ አይኮበልልም ይባላል:: ይህን አሳብ በዚህ መልኩ የማይቀበሉትም የዚያኑ ያህል ናቸው:: መቆርቆራችን ከንፈር ከመምጠጥ ወይም ከወሬ የዘለለ አይደለም፤ በቁርጥ ቀን የቁርጥ ቀን ሰው ሆኖ የሚገኘው እምብዛም ነው የሚለው አሳብ ኢትዮጵያውያን የሚባለውን ያህል አገር ወዳድ አይደሉም የሚሉት ወገኖች መከራከሪያቸው ነው::

በእርግጥ በዝቶ የሚታየው መሪዎችን መውቀስ እንጂ ሁሉም በሚችለው የበኩሉን ድርሻ የመወጣቱ ነገር፣ ለጊዜያዊ ችግር መፍትሔ ለመስጠት ከሚደረግ ሩጫ ባለፈ ዘላቂነትና ወጥነት የለውም የሚለውን መካድ አይቻልም:: እንደሚባለውም የኢትዮጵያውያንን ያህል በተሰባሰቡበት ሁሉ ስለ አገራቸው የሚወያዩ፣ በአገራቸው ጉዳይ የሚጨነቁ ያለ አይመስልም:: በውጭ አገር በዝቶ የሚታየውም እንዲህ ዐይነቱ ነገር ነው:: የተግባር ሰው መሆንና መቆጨት ለየቅል መሆናቸው ነው እንጂ::

በእርግጥ አገር ወዳድነት የሚባለውን ያህል ጠንካራ ነው ወይ? ለመሪዎች አገር ወዳድነት ማለት ምን ማለት ነው? ውይይት የሚፈልገው ጉዳይ እንዲህ ዐይነቱ ነገር ነው:: በትንሹም በትልቁም፣ በሚረባውም በማይረባውም የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነትን በሰላም ማስተናገድ ባለመቻል ስንት ጥፋት እየደረሰ አገር ወዳድ ነን ማለት ምን ያህል ትርጉም ሊሰጥ ይችላል? የማስብልሽ እኔ ነኝ ሌላው ልጅሽ ሊያጠፋሽ ነው፤ የምሞትልሽ እኔ ነኝ ሌላው ገዳይሽ ነው የሚለው ፍትጊያ በሚበዛበት አገር ወዳድ መሆን እንዴት ይቻላል? ልጆቿ እርስ በርስ ሲገዳደሉባት፣ እርስ በርሳቸው ሲቦጫጨቁባት፣ አንዱ ሌላውን ሲያሳድድባት ደስ የሚላት እናትስ እንዴት ትኖራለች? ልጆቿን እየገደሉ እወድሻልሁ ማለትስ ምን ላይ ነው ትርጉም የሚሰጠው? ለእናት ሁሉም ልጆቿ ናቸውና::

አገር ወዳድነት በተግባር የሚፈተንበት አንዱ ክሥተት ምርጫው በሥልጣንና አገር በማዳን መካከል በሚሆንበት ጊዜ ነው:: አገርን ለማዳን ሥልጣንን መልቀቅ አማራጭ ሆኖ በቀረበበት ጊዜ ሁሉ አገሬ ከምትጎዳ ሥልጣን ምናባቱ ብሎ በፈቃዱ ሥልጣን የለቀቀ መሪ ማንን እናውቃለን? አገር ከምትጎዳ ልዩነታችንን እናቻችለው፥ ለሀገር ጥቅም ሲባል የእኛ የሥልጣን ጥያቄ ይቅርብን ያሉ መሪዎስ መቼ ነው የታዩት? በአመዛኙ ሲያቅት ይቀራል እንጂ አገር ጠፋች አልጠፋች ግድ የማይሰጣቸው መሪዎችን ነው ስናይ የኖርነው:: ከሥልጣናቸው አገርን የሚያስቀድሙ መሪዎች ቢኖሩን ኖሮ የአሁኒቷ ኢትዮጵያ ምን መልክ

ይኖራት ነበር? ደረጃዋስ ከየትኞቹ አገሮች ተሰላፊ ያደርጋት ነበር? ብሎ ማሰብም ይቻላል::

አንድ ዐይነት ሰዎች በመሪነት ለረጅም ዘመን ሲመሩ ማየትም የተለመደ ነው:: ለምን? ሲባል፣ ሰው ጠፋ የሚል ነው የሚሰማው:: ለምን ሰው ጠፋ? ሲባል ፖለቲካና ኮረንቲን በሩቁ የሚለው ስለሚበዛ የሚል ነው አንዱ ምክንያት:: በእርግጥ መጠላለፍ በሚበዛበት፣ ፖለቲካ ከጠመንጃ ባልተላቀቀበት ሁኔታ በፖለቲካ መሳተፍ እንደሚባለውም ሕይወትን አስይዞ ነው:: ከመሞት መሰንበት ይሻላል፤ ልጆቼን ላሳድግበት፤ ጎመን በጤና የሚለው ሚዛን ይደፋል:: ሴራና መጠላለፍ በበዛበት ሁኔታ ማገልገል ቢፈለገስ ማን የሚያሠራ ይገኝና? የሚያፈናፍን የለም፣ ሁሉም ነገር ዝግ ነው የሚል ቅሬታም የእንዲህ ዐይነቱ ስጋት መገለጫ ነው::

ይህ ግን ችግሩን ያባብሰዋል እንጂ መፍትሔ አያመጣም:: ክፋት የሚበዛው ክፉ ሰዎች ስለሚበዙ ሳይሆን የሚበዙት መልካም ሰዎች ዝምታቸው ስለሚበዛ ነው እንደሚባለው አገር ወደፊት ለማስቀጠልም ይሁን የተሻለ ነገን ለማየት ማለቃቀስ ብቻውን የሚፈይደው ነገር አለመኖሩ የሚያከራክር አይደለም::

መሥዋዕትነትን ለመቀበል የተዘጋጀ፣ ከሚያወራው የሚሠራው እስኪበዛም ለውጥ አይመጣም:: መቼም በአመዛኙ ታሪክ በሰፊው ሕዝብ አይሠራም:: ታሪክን የሚሠሩት ጥቂቶች ናቸው፡፡ ተስፋ የማይቆርጡ፣ እኔ ሞቼ የአገሬ ክብር ይመለስ በሚሉ ሰዎች:: እንደ ነህምያ ያሉ አገልጋይ መሪዎች ካልበዙ የፈረሰ አገር አይገነባም:: የፈረሰ መገንባት ብዙ ድካም ብዙ ውጣ ውረድ አለውና:: ሥራ ሲሠራ መሰደብ አለ፤ ነቃፊው ይበዛል:: ያለ መሥዋዕትነት ግን የተዋረደ ሕዝብ አይከበርም:: በባርነት ያለ ሕዝብም ነጻ አይወጣም:: እንደ ነህምያ ራሱን የሰጠ ከእኔ በፊት ወገኔና ከእኔ ክብርና ዝና የአገሬ ክብር የሚል መሪ ሲገኝ ሁሉም ይሳካል:: የማይቻል የሚመስለው ሁሉ ይከናወናል::

በተደላደለ ኑሮ ሆኖ ምንም ጠብ የሚል አስተዋጽዖ ሳያበረክት በአፍ ብቻ አገር እወዳለሁ ስለተባለ አገር ወዳድ መሆንም አይቻልም:: አገሬን እወዳለሁ የሚለው ሰው ብዙ ነው:: በየሚዲያው "አገሬን በጣም ነው የምወደው" የሚሉ ሰዎችን ማየት ባህል ወደ መሆን እየመጣ ይመስላል:: እንዲህ ዐይነት ነገር በሌሎች ባህል ብዙም አይታይም:: "ሙያ በልብ ነው" የሚሉት ዐይነት አገርን መውደድ ከአፍ ይልቅ በተግባር መግለጹን የሚወዱ ይመስላሉ:: በእርግጥም እንዲህ ዐይነቱ የአገር ፍቅር በተግባር ሲገለጽ በዐይን መታየቱ የማይቀር በመሆኑ ወሬ ብዙም የሚፈልግ ጉዳይ አይደለም::

ሹመት ሲያገዝ ከግልና ከቤተሰብ ጥቅም በላይ ማሰብ፣ የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም ብዙም ባልተለመደበት ሁኔታ አገር ወዳድነት እንዲህ ጎልቶ የሚወራውስ ምን ቢሆን ነው? የሚሉትን እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እያነሡ መነጋገርም ተገቢ ነው:: አገር መውደድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በተግባር እየኖሩት ካሉ ሀገሮች ተሞክሮ መውሰድም የመፍትሔው አንድ እርምጃ ሊሆን ይችላል:: በድህነት ተርታ ከነበሩ ዛሬ ግን በዓለም ላይ ገናና ከሆኑ፣ ከመለያየት ይልቅ ጎብረት ፈጥረው ብዙዎችን ወደ ሥልጣኔ ያደረሱ፣ ለሚበልጠው አገራዊ ዐላማ ልዩነታቸውን አቻችለው በጋራ ተግባብተውና ተቻችለው በመሥራት አገራቸውን ያዘመኑ ሰዎችን ልምድ በመቅሰም አገር ወዳድነትን ማዳበር ይቻል ይሆናል::

ያም ሆነ ይህ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ይወዳሉ የሚለው በተደጋጋሚ የሚሰማው ምን ስለሆነ ነው? የሚለውን መጠየቅ ተገቢ ነው:: አገር መውደድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ውይይት የሚፈልግ፣ በእርግጥም የምንለውን ያህል አገር ወዳድ መሆናችንን ከሌሎች ሕዝቦች አንጻር መፈተሽ የሚገባው አሳብ ነው:: የአገልግሎት ባህል ደካማ በሆነበት ሁኔታ የአገር ፍቅር ምን ያህል ሚዛን ይደፋል? ምን ያህል ሰው ነው ለአገሬ ለወገኔ ይህን መሥዋዕትነት ከፈልኩ ማለት የሚችለው? ምን ያህል ሰው ነው ለአገሬ ስል ተጎዳሁ ሊል የሚችል? የሚለው ሲጠየቅ የሚገኘው መልስ ነው የአገር ፍቅር ምን ማለት እንደሆነ የሚወስነው::

አንድ ችግር በተፈጠረ ጊዜ ማልቀስና ማዘን አገርን ወደ ፊት አያራምድም። ፈርሰው የተሠሩ ወይም ከድህነት አረንቋ ወጥተው በዓለም ቀዳሚ የሆኑ አገሮች አብዛኛው ታሪካቸው ሕዝባቸው የተግባር ሰው መሆኑን የሚያሳይ ነው። መሪዎቹም፥ ሕዝቡም የሚያስፈልገውን መሥዋዕትነት ለመክፈል ፈቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው ለውጥ እንዳመጣ አጠያያቂ አይሆንም። አገር ግንባታና ፖለቲካ የሚያያዛቸው ነገር ቢኖርም አቻጋሪ በሆነበት ሁኔታ እንኳ በመንግሥት ላይ አመኔታ ባይኖራቸውም ወይም ፖሊሲውን ባይደግፉትም የአገር ግንባታ ጉዳይ እንዲህ ላሉ ሰዎች ጥያቄ ውስጥ አይገባም። ፖለቲካው ባይጥማቸውም ለአገር ግንባታ የሚከፈለው ዋጋ ሁሉ ይከፈላል።

የነህምያ ታሪክም የሚያሳዬንም እንዲህ ዐይነቱን ነገር ነው። የነህምያም ታሪክ የሚነግረን አገር ወዳድነት ማለት በተግባር ምን እንደሆነ ነው። ቀደም ሲል የተጠቀሰው የነህምያ ኀዘንና ቁጭት ዛሬ በብዙዎቻችን እንደሚታየው የአፍ ብቻ አልነበረም። ነህምያ የአፍ ሳይሆን የተግባር ሰው ነውና። ነህምያ ለወገኖቹና ለሀገሩ ሲል ንጉሡን ሳይፈራው "ደስ ቢያሰኝህ ባሪያህም በፊትህ ሞገስ ቢያገኝ እሠራው ዘንድ ወደ አባቶቹ መቃብር ከተማ ስደደኝ" አለው። የቤተ መንግሥትን ኑሮ በስደት አገር ጥሎ ወደ ፈረሰ ከተማ ወደ ተጎሳቆለ ወገን መሄድ ግን አገልጋይ መሆንን ይጠይቃል። ከራስ ይልቅ ለብዙዎች ቅድሚያ የሚስጥ ልብ ከሌለ እንዲህ ዐይነት ውሳኔ ቀላል አልነበረም። የአባቶቹ ከተማ እስኪደርስ እንኳ ስለሚበልጠው ዐላማ ታገሠው እንጂ ብዙ ውጣ ውረድ ነበረው። ነህምያ ግን የድሎት ኑሮውን ትቶ ምንም ወደሌለበት ወደ ፈረሰ ከተማ በቁርጠኝነት ተጓዘ። የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች መልሶ መገንባት ብዙ መሰናክል፣ ብዙ ጠላት ቢኖረውም በትዕግሥት ሕዝቡን አሰተባብሮ ሠርቶ ጨረሰ። የአገር መውደድ ስሜት፣ በቃልና በተግባር ሲስማማ እንዲህ ነው።

ፕሬዚደንት ኬኔዲ አንዱ ከሚታወሱበት ንግግር “አገሬ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን አገሬን ምን አደረኩላት ብለን ልንጠይቅ ይገባል”[41] ያሉት ታላቅ አባባል ነው:: ለአገሬ ምን ማድረግ እችላለሁ? ማለት የሚቻለው በአገልግሎት መንፈስ ነው:: የአገልጋይነት ልብ ሲኖር ከእኔ ይልቅ ለሕዝቤ የሚጠቅመውን ላስቀድም ማለት ይቻላል:: አገልግሎት ምን ተደረገልኝ ወይም ይደረግልኝ ሳይሆን ምን ማድረግ አለብኝ የሚለውን ነው የሚያስቀድመው:: መሬት ካልተዘራባት ልታበቅል ወይም ፍሬ ልታፈራ እንደማትችለው ሁሉ አገር ልትሰጥ የምትችለውም ያላትን ያፈራችውን ነውና:: ከሌላት ልትሰጥ አትችልም:: አገሬ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን ለአገሬ ምን ላድርግላት ማለት መቅደም የሚገባውም ለዚህ ነው:: ሁሉም የበኩልን ሲዘራ የሚታጨድ ይኖራልና::

ያም ሆኖ ባለው ውሱን ዓቅም የተደረገውም አያንስም:: ወጣ ሲሉ ነው የሚታወቀው:: አሜሪካን በመሰለ አገር እንኳ ድግሪ በነጻ የሚያስተምር የለም:: አፈር ልሶ ነው ድግሪን ወይም ሁለተኛ ድግሪን ማግኘት የሚቻለው:: ዕድሜ ልክ የሚዘልቅ እዳ ውስጥ መዘፈቅ ግድ ይላል:: አረረም መረረም ባለው ውሱን ዓቅም እንዴት በነጻ እንደተማርን ሲታሰብ ነው ይህም አለ ለካ የሚያሰኘው:: በስደት ኑሮ እንኳ የውጭ አገር ኑሮው ምን ያህል ነው ከዚያች አገር በሚመጣው ምግብ ላይ ጥገኛ የሆነውስ? የአገር ውለታ ምን ስፍር አለው? በዚያም ላይ እናት ሳትሰስት ያቅሟን ማድረጓ ነው ቁምነገሩ:: የቀረበው ቆሎም ይሁን ጮማ፣ እናት ያላትን ሳትሰስት ካቀረበች በቂ ነው::

7.1.5 መልካም እረኛ

በመጽሐፍ ቅዱስ መሪነት በእረኛነት የተመሰለ ሲሆን ሙሴና ዳዊትን የመሰሉ ታላላቅ መሪዎችም ለመሪነት ከመመረጣቸው አስቀድሞ በእረኝነት ሙያ የነበሩ ናቸው:: የእረኝነት ግብር በሰው ዘንድ ዝቅ ተደርጎ የሚታይ ቢሆንም ሙያው በውስጡ ብዙ ምስጢርን በመያዙ ነው መሪነት በእረኝነት የመመሰሉ ምክንያት:: የመጽሐፍ ቅዱሱ እረኛ

[41] “Ask not what your country can do for you – ask what you can do for your country”

በጎቹን ከፊት የሚመራ እንጂ እንደኛ ባህል ከኋላ የሚነዳ አይደለም። በእርግጥም አገልጋይ መሪ እንዲህ ነው፤ በጎቹ የሚመሩት ሳይሆን እርሱ የሚመራቸው፣ በግድ የሚነዳቸው ሳይሆን በፈቃድ የሚከተሉት፣ በጎቹ መንገድ ሲስቱ የሚከተላቸው ሳይሆን መንገድ መርጦ የሚያሳያቸው ነው። እንዲህ የሚያደርግ ነው መልካም እረኛ ወይም አገልጋይ መሪ ማለት።

መልካም እረኛ በጎቹን ያውቃል፤ እነርሱም ያውቁታል። "መልካም እረኛ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፤ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል። የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፤ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፤ ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና።" ተበሎ እንደተጻፈ። (ዮሐ 10፥3-5) እውነተኛ እረኛ ሲገኝ በጎቹን መንዳት አያስፈልግም፤ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል። በጎቹ ከእረኛው የሚሸሹት፣ የማያውቁትና እውነተኛው እረኛ ሳይሆን ተመሳስሎ የመጣ ተኩላ ወይም ምንደኛ የሆነ እንደሆነ ነው። በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት በጎቹ ጠንቅቀው ያውቃሉና ምንደኛውን ሊከተሉት አይፈልጉም። ምናልባት ባይሆን በግድ ሊነዳቸው ይችል ይሆናል እንጂ።

መሪና ተመሪ መግባባት ከቻሉም ትልቁ ድል እርሱ ነው። መሪው ሕዝቡን፤ ሕዝቡ ደግሞ መሪውን ማመን ከቻለ በጋራ ብዙውን ችግር መፍታት ይቻላል። የመሪዎቹ ቋንቋ ሸፍጥ የበዛበት ከሆነ ግን ሕዝቡ እንዴት ሊገባው ይችላል? ቋንቋው እንግዳ ይሆንበታል እንጂ። ጥርጣሬ ከበዛስ መደማመጥ እንዴት ሊኖር ይችላል? ያለመደማመጥስ መግባባት ከወዴት ይገኛል? መልካም እረኛ በእውነት ይናገራል፤ በጎቹም በቅንንተና በእውነት ይሰሙታል። ለብልጣብልጥ መሪ ተመሪ ልቡን አይከፍትም። ያዳምጠኛል ብሎ ካላሰበ ምን አደከመኝ ጉንጭ ማልፋት ነው ይላል እንጂ። የሚያዳምጠኝ መሪ አገኘሁ ብሎ ሲያስብ ግን አፉን አይደለም ልቡንም ይከፍትለታል።

መልካም እረኛ የተነገረውን ሳይሆን ያልተነገረውንም የማዳመጥ ችሎታም አለው:: በጎቹ አልጮሁም ማለት አልራባቸውም፣ አልጠማቸውም ማለት አይደለምና:: መጮኽ አቅቷውም ሊሆን ይችላል:: መልካም እረኛ ድምፅ አልባ የሆነ የበጎችን ጩኸት አስቀድሞ የማዳመጥ ችሎታ አለው:: መልካም እረኛ ምስጋናን ብቻ ሳይሆን ነቀፌታንም ወቀሳንም ለመስማትም ጆሮዎቹ ክፍት ናቸው:: ማዳመጥ ማለት የሚፈልጉትን ብቻ መስማት ማለት አይደለምና:: ማዳመጥ ከዚያ በላይ ነው:: አዳማጭ ለመረዳት እንጂ ለማስረዳት አይፈጥንም:: አዳማጭ አይፈርጅምም:: ይሄ ሰው የማይናገረው ምን ቢሆን ነው ጸጽታም ያስፈራል የሚባልበት ጊዜ አለ:: አልጮሁም ማለት ተመችቷቸዋል ማለት ላይሆን ይችላል እንዲያውም መፍራት ያኔ ነው፥ ጸጽታው ሲበዛ::

መልካም እረኛ የበጎቹን ፍላጎት ያውቃል:: መልካም እረኛ የሚያራቁት ሳይሆን የሚያበለጽግ የሚያስርብ ሳይሆን የሚያጠግብም ነው:: ለዚህ ደግሞ ያለ እንቅልፍ ይሠራል:: ለዚህ ደግሞ ለምለም ሣር እና ውኃ እስኪገኝ፤ ድካም፣ የፀሐይ ሐሩር ቢኖር እንኳ በጎቹን ለማጥገብ፣ በጎቹን ለማርካት ሲል እርሱን እየራበው እርሱን እየጠማውም ቢሆን ሁሉን ይታገሣል:: እግዚአብሔር መሪነትን በእረኝነት የመሰለበት አንዱ ምክንያትም ለዚህ ነው:: ዳዊት "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፣ የሚያሳጣኝም የለም:: በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል::" ሲል መናገሩም ይህንን ያሳያል:: (መዝ 23፣ 1-4)

ምንደኞች ግን ከበጎቹ የሚገኘውን ጥቅም እንጂ በጎቹን አይፈልጉም:: ምንደኞች ራሳቸውን እንጂ በጎቹን አያስማሩም:: ምንደኞች የራሳቸው ምኞት እንጂ በጎቹ ተቸገሩ አልተቸገሩ፣ ተሰደዱ አልተሰደዱ፣ ውቅያኖስ ገቡ አልገቡ፣ አውሬ በላቸው በሰላም ገቡ ለእነሱ ጭንቀታቸው አይደለም:: "እረኞች በጎችን ያስማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? ጮማውን ትበላላችሁ፤ ጠጕሩንም ትለብሳላችሁ፤ የወፈሩትን ታርዳላችሁ፤ በጎቹን ግን አታስማሩም፤ የደከመውን አላጸናችሁትም፤ የታመመውንም አላከማችሁትም፤ የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም፤ የባዘነውንም አልመለሳችሁትም፤ የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም፤ በኃይልና በጭቈናም

ገዛችኋቸው። እረኛንም በማጣት ተበተኑ፤ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፤ ተበተኑም። በጎቼ በተራሮች ሁሉና በረዘሙ ኮረብቶች ሁሉ ላይ ተቅበዝብዘዋል፤ በጎቼም በምድር ፊት ሁሉ ላይ ተበትነዋል፤ የሚሻም የሚፈልግም አልነበረም።" የሚለው ቃል የሚያመልክተውም እንደነዚህ ዐይነት ምንደኛ መሪዎችን ነው። (ሕዝ 34፥3-6) እንዲህ ባለ ጊዜ በጎቹ እየከሱ እረኞቹ ይፋፋሉ፤ በጎቹ እየተራቆቱ እረኞች ያጌጣሉ።

መልካም እረኛ ግን ለሁሉም እኩል ነው። መልካም እረኛ አንዱን ከሌላው አያበላልጥም። እንዲያውም ከኃይለኛው ይልቅ ለደካማው ያደላል። ከመንጋው መካከል የተሰበረ ወይም በሌላ ምክንያት የደከመ ቢኖር በደረቱ ያቅፈዋል እንጂ ደከመ ብሎ ለአውሬ አሳልፎ አይሰጠውም። ውኃ ተጋፍቶ መጠጣት ባይችል ውኃ ቀድቶ ያጠጠዋል፤ ቢሰበር እንዲጠገን ያክመዋል፤ የተሰበረ አካሉን ያስርለታል። አገልጋይ መሪም እንዲሁ ጉልበት የሌለው በባለ ጉልበታሙ እንዳይገፋ፣ ጉልበት ያለው ሁሉን በጉልበቱ ጠቅልሎ ጉልበት የሌለው ባዶ እንዳይቀር የሚከላከልለት ነው። መሪ ማስፈልጉስ ለዚህ አይደለም ወይ?

መልካም እረኛ ስለ በጎቹ እንደ ዳዊት ከሚመጣ ጠላት ሁሉ ጋር ይዋጋልም። ለነፍሱ ሳይሳሳ በቆራጥነትና በጀግንነት ታግሎም ያሸንፋል። "እኔ ባሪያህ የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር፡፡ ከመንጋውም ጠቦት ይወስድ ነበር፤ በኋላውም እከተለውና እመታው ነበር፤ ከአፉም አስጥለው ነበር፤ በተነሣብኝም ጊዜ ጕሮሮውን ይዤ እመታውና እገድለው ነበር።" የሚል ታሪክ በቅዱስ መጽሐፍ ተመዝግቧል። (1ኛሳሙ. 17፥34-35) ይህ ታሪክ ጎልያድን የሚያሸንፍ ጠፍቶ፣ ሕዝቡ በፍርሃት በተዋጠ ጊዜ በእረኝነት ሙያው በጎቹን ከአውሬ በመታደግ ልምድ ያካበተው ዳዊት ጎልድያድን እገጥመዋለሁ፣ አሸንፈውማለሁ ቢል የሚያምነው ስላጣ የተናገረው ቃል ነው። እረኛው ዳዊት እንዲሁ ለበጎቹ ሲል መሥዋዕት እስከ መሆን የሚደርስ እረኛ ነበረ። ዳዊት መሪ እንዲሆን ያስቻለው፣ ለመረመረጥ ያበቃው አንዱ ምክንያት ልበ ሙሉና ደፋር መሆኑ ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ ታሪክ ነው።

ፈሪ መሪ መሆን አይችልም:: መሪነት እንደ ዳዊት ደፋር እረኛ መሆንን ይጠይቃል:: ድፍረትን የሚጠይቀው ውሳኔ ብዙ ነው:: "እነ እገሌ ይቀየማሉ፤ የእነ እገሌ ጥቅም ይነካል፤ ባይሳካልኝ አደጋ አለው፤ ቢቀርብኝ ባልነካካው ይሻላል" አለማለት የሚቻለው ላመኑበት ነገር ቁርጠኝነትና ድፍረት ሲኖር ነው:: ያለዚያ ሙስናን መዋጋት ፈልጌ ነበር ግን ምን ላድርግ ከአንበሳ አፍ ሥጋ እንደመንጠቅ ሆነብኝ ማለት ይመጣል:: ያለዚያ ስለፈራሁ ሳላምንበት የአገር ጥቅም አሳልፌ ሰጠሁ፤ የተሰጠኝን ሓላፊነት መወጣት እንዳልችል አስፈራሩኝ፤ ለቤተሰቤ ደህንነት ስል በሐሰት መሰከርሁ፤ ያላደረኩትን አደርኩ አልሁ" ማለትን ያመጣል:: መሪነት የሚጠይቀውን ጀግንነት ከሌለ የመሪነት ቦታ አለመያዝ የተሻለ ያዋጣል የሚባለውም ለዚህ ነው::

7.1.6 ተግቶ የሚያተጋ

መሪ ራሱ ተግቶ ተከታዮቹን ማትጋት መቻሉ መተኪያ የሌለው ክህሎት ነው:: አገልጋይ መሪ ደግሞ እንዲህ ዐይነቱ ክህሎት ከማንም በላይ ያስፈልገዋል::

ሰውን የሚያተጉት ምክንያቶች ውጫዊና ውስጣዊ (externic and intersic motivation[42]) በሚል በሁለት ይከፈላሉ:: በገንዘብ፣ በሹመት፣ በሥራ እድገት እና በመሳሰሉ ውጫዊ በሚባሉት ማባባያዎች ተከታይን ማትጋት አቅሙ እስካለ ድረስ ብዙም ጥበብን የሚጠይቅ አይደለም:: ለአገልግሎት ሰውን ማትጋት ግን ከዚህ በላይ ነው:: ለአገልግሎት ሰውን ማሰለፍ የሚቻለው ከእንዲህ ዐይነት ማባበያዎች ይልቅ ሁሉም የሚያምንበት የጋራ ዐላማን ማሳየትንና ሕልምን ማጋራትን የሚጠይቅ ነውና::

[42] Intrinsic motivation involves doing something because it's personally rewarding to you. Extrinsic motivation involves doing something because you want to earn a reward or avoid punishment, EDITED BY Carol Sansone Department of Psychology University of Utah file:///C:/Users/wb242998/OneDrive%20-%20WBG/References/intrinsic-and-extrinsic-motivation.pdf

አገልጋይ መሪ ራሱን በራሱ ያተጋል፣ ራሱ ሳይተጋ ሌሎችን ማትጋት አይቻለውምና:: አገልጋይ መሪ ከምስጋና በላይ የሚያተጋውም የቆመለት የተቀደሰ ዐላማ ነው:: አገልጋይ መሪ ሰው አየ አላዬ፣ ጭብጨባ ኖረ አልኖረ ብዙም ግድ አይሰጠውም:: እረፍት የሚነሣው፣ ከእንቅልፍ የሚቀሰቅሰው፣ የሚያስጨንቀው የዐላማው መሳካት ብቻ ነው እንጂ::[43] ምስጋና ቢኖርም፣ ባይኖርም፣ ነቀፌታ ቢበዛ፣ ተቃውሞ ቢያይልም ከዐላማው ላይ ዐይኑን አያነሣም::

የመሪ ትልቁ የስኬታማነቱ ምስጢር ግን ተግቶ ሌሎችንም ማትጋት መቻሉ ነው:: ማትጋት መቻል ነው ትልቁ ጥበብ:: መሪ ሕልሙን የሚካፈሉት፣ ዐላማውን ዐላማቸው የሚያደርጉለትን ሚሊዮኖችን ማሰለፍ መቻል የስኬቱ መጀመሪያ ነው:: መሪ ተከታዮቹን ምን እንደሚያተጋቸው ማወቅ መቻሉም ለማትጋት ትልቅ ዋጋ አለው:: የሚከተሉትንም በዋናነት ማንሣት ይቻላል::

1ኛ. ብዙዎችን ማሰለፍ የሚቻለውም በጎ ዐላማ ሲኖር ነው:: ሰውን ከሚወደውና ከሚያምንበት ውስጣዊ ምክንያት የበለጠ በዘላቂነት ሊያተጋው የሚችል ነገር ሊኖር አይችልም:: ሰዎች ከገንዘብ ከዝና ከሥልጣንና ሌላ ጊዜያዊ ጥቅም ይልቅ የሚያምኑበት የተቀደሰ ዐላማ ሲኖር ሕይወታቸውን እንኳ እስከ መስጠት እንደሚደርሱ በየታሪክ አጋጣሚው የሚታይ ነው:: ለመሞት የሚያበቃ ምክንያት አለ ተብሎ ሲታመንም ነው ለመሞት እንኳ የቆረጡ ብዙዎችን ማሰለፍ የሚቻለውም:: ሌላው ሁሉ መጠን አለው ወይም ጊዜያዊ ነው:: ገንዘብ፣ ዝና፣ ሥልጣን ለጊዜው ሊያተጋ ቢችልም ሌላ ጥቅም ሲገኝ ወይም ሲደረስበት ተራ ነገር ይሆናል:: [44]

[43] Servant-leader is motivated by contributing to a collective result or vision rather than by personal recognition, power, or material gain. The Essentials of Servant Leadership, Ann McGee-Cooper, Ed.D

[44] External motivation is more likely to create conditions of compliance or defiance; self-motivation produces far superior results. People who are self-motivated will keep working toward a result even if there's no reward, but people who are externally controlled are likely to stop trying once the rewards or punishments are removed. James M. Kouzes and Barry Z. Posner, The Leadership Challenge

ገንዘብ ትልቅ ኃይል እንዳለው የታወቀ በመጽሐፍም “ለሁለት ጌቶች መገዛት አትችሉም “ ተብሎ የተነገረለት ቢሆንም ሰው ሁሉ ለገንዘብ ብቻ ይኖራል፤ በገንዘብ ብቻ ይታለላል፤ ገንዘብን ብቻ ፈልጎ ይተጋል የሚል አስተሳሰብ ግን ትክክል አይሆንም:: ሰው ለሆዱ ብቻ አይኖርም:: ሰውን የሚያምንበትን ዐላማ በማስረዳት ለዐላማው እንዲተጋ ከማድረግ የተሻለ የማትጊያ መንገድ የለም:: ዐላማህ ዐላማዬ ነው ሲል ሰው ራሱን ይሰጣልና:: ሰው ለሚያምንበት ዐላማ እየሠራሁ ነው ብሎ ሲያስብ ድካም የሚባል ነገር አይሰማውም:: ዐላማ ጊዜያዊ ሳይሆን ሩቅ ጉዞን ለመጓዝ የሚያስችል ስንቅ ነውና:: በጎ ዐላማ ውጫዊ ሳይሆን ውስጥዊ ጥንካሬንም ይሰጣል:: የጋራ ዐላማን በቅንነት ማሳየት ሲቻል ብዙዎቹን ማሰለፍ፣ ብዙዎችን ለበጎ ዐላማ ማትጋት እንደሚቻልም በብዙ ስኬታማ መሪዎች ታሪክ የሚታይ ነው::

2ኛ. መሪ ህልሙን ማጋራት ካልቻለ ህልሙን እውን ሊያደርጉ የሚችሉ ሰዎችን ማሰለፍ አይችልም:: እንደሚቀጣጠል እሳት በተዋረድ ባሉ መሪዎች ከዚያም በሕዝቡ የሚቀጣጠል ተነሣሽነትን ለመፍጠር ትልቁ ቁልፍ ሕልምን በማጋራት ለማትጋት መቻል ነው:: መሪነት ማለት የአመኑበትን ዐላማ የብዙዎች የጋራ ዐላማ፣ ሕልሙንም የብዙዎች የጋራ ሕልም እንዲሆን ማድረግ ነው:: ራእይ እውን የሚሆነው ከመሪው ወጥቶ ሁሉም ሲጋራው ነውና:: የመሪውን ራእይ እስከ ታችኛው መዋቅር ያሉ አመራሮች ሲቀበሉትና የእነርሱም ሕልም እንዲሆን ሲፈቅዱ፣ የመሪውን ሕልም ተከታይ ገብቶት ከመሪው ጋር አብሮ ለመጓዝ ሲፈቅድ ራእይ የመሳካት እድሉ ከፍተኛ ይሆናል:: መሪ ራእዩን ማስፈጸም የሚችለው ብዙዎቹን ከጎኑም ከኋላውም በማሰለፍ ችሎታው እንደሆነም የተረዳ ነው:: ምንም ያህል በጎ ሕልም ቢኖር ያለሰው የሚፈጸም ነገር አይኖርምና:: በተወሰኑ መሪዎች በጎ ፈቃድ ብቻ ትልቅ ሕልም ግብ አይመታም:: ለዚህ ደግሞ ወሳኙ የመሪ የማሳመን ዓቅም ነው::

ማሳመን (persuation) ግን በኃይል እንደማስገደድ ቀላል አይደለም:: ማሳመን ጥበብን እና ትዕግሥትን፣ በአሳብ ልዕልና ማመንን፣ የሰዎችን ነጻነትን ማክብርን ይጠይቃልና:: አሳብን ለሌሎች ለመሸጥ የሌሎችን አሳብ አስቀድሞ መግዛትን ይጠይቃልም:: ተናግሮ ለማሳመን ልብን ከፍቶ ማዳመጥን ይሻል:: ተከታይን ለማቅረብም መጀመሪያ ወደ ተከታይ መቅረብን ይጠይቃል:: ለማሳመን ሰዎች የሚያምኑትን ነገር ብቻ ሳይሆን ለምን እንደዚያ ሊያምኑ እንደቻሉ መረዳት አስፈላጊ ነው:: ለማሳመን በሚያምንበት አሳብ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ባያምንበት እንኳ እኔ አውቅልሀለው በሚል ሳይሆን በትሑት ልብ በመወያየት የጋራ ግንዛቤን መፍጠርም ግድ ይላል:: በተለይ ለአገልግሎት ሰዎችን ለማሰለፍና ለማትጋት የተቆመለትን በጎ ዐላማ ማሳየት መቻል መተኪያ የለውም:: ብዙ ሺዎችን አሰልፈው ለውጥ ያመጡ አገር በቀል የአገልግሎት ድርጅቶች የስኬታቸው ሚስጥር "ኑ አብረን እንሥራ ለውጥም እናመጣለን" የሚለውን ደወል ዘወትር በመደወል፣ ማሳመንና ተግቶ ማትጋት መቻላቸው ነው:: ሰው በሚያደርገው አስተዋጽዖ ለውጥ ይመጣል ብሎ ካመነ፣ ሰው በሥራው አዎንታዊ አስተዋጽዖ እያደረግሁ ነው ብሎ ካመነ የሚያተጋ ሳይኖር ሊተጋ ይችላል::

3ኛ. ሰው ማኅበራዊ ፍጡር እንደመሆኑ ፍቅርም ይፈልጋል፤ ፍቅር ያበረታዋል፤ ፍቅር ኃይል ይሰጠዋል:: ፍቅር የደከመውን ያበረታል፤ ያዘነውንም ያጽናናል:: ገንዘብና ማዕረግ ወይም የሥራ እድገት ብቻ ሳይሆን ለብዙ ሰዎች ከዚያም በላይ መተሳሰብና መረዳዳት ያለበትን የሥራ ቦታ ተመራጭ ያደርጋሉ:: መተሳሰብና መረዳዳት ያለበት፣ ጥርጣሬና ትችት ያልበዛበት፣ አንዱ አንዱን የማይሰልልበት፣ ጤናማ ፉክክር እንጂ ምቀኝነት ያልበዛበት፣ ሰዎች በእኩልነት የሚከበሩበት፣ የሥራ ከባቢ ትጉህ ሠራተኞችን ለማፍራት ያስችላል::

ከግለሰብ አስተዋጽዖ ይልቅ በቡድን ሥራ ተግባብቶ መሥራት ትልቅ ቦታ የያዘበት ዘመን እንደመሆኑም ዛሬ ታላላቅ የሚባሉ ተቋማትና ኮርፖሬሽኖች ጭምር ሠራተኞቻቸው እንዲቀራረቡ በሰላም ተግባብተው እንዲሠሩ ብዙ ጥረትን ያደርጋሉ፤ ብዙ ወጭም ያወጣሉ::

ለምሳሌ አሊባባ የተባለ ግዙፍ ድርጅት መሥራች በ2018 በአንድ ንግግራቸው[45] "መሪ ስኬታማ ለመሆን ብልህነት (IQ-intelligence Quotient) ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልገው የስሜት ልህቀትና (EQ-Emotional intelligence) ተወዳጅነት (LQ-Love Quotient) ነው::" ሲሉ ነበር የተናገሩት:: በሦስተኛ ደረጃ ስለ ፍቅር የተጠቀሰው በዚህ መልኩ አዲስ ቢሆንም ፍቅር ሰዎችን ለማትጋት ያለውን ዓቅም መሪዎች እየተረዱት ለመምጣቱ ግን አመላካች ሊሆን ይችላል:: ተወዳጅነት በንግድ ተቋማት እንኳ መሪዎችን ለመምረጥ ሥራ ላይ እየዋለ ነው::

ሰው የመሳብ ችሎታ ካለህ ብልህ የሆኑ ሰዎች ካንተ ጋር ለመሥራት ይመጣሉ የሚል ነው እሳቤው:: ስለዚህ ሰውን ለማትጋት ሰውን የማቅረብ ብቻ ሳይሆን ሰውን የመያዝ ችሎታ ያስፈልጋል:: ዘወትር ስለ ሥራ ከሚያስብ መሪ ይልቅ ከሥራም ባሻገር ለሠራተኞቹ የግልና የቤተሰብ ሕይወት ቅድሚያ የሚሰጥ መሪ በሠራተኞቹ ይበልጥ ይከበራል:: ውጤታማም ይሆናል:: አገልጋይ መሪዎችም ይህን ጥበብ ያውቁበታል:: በሰዎች ጫማ ሆኖ የሰዎችን ችግር የመረዳት የሚናገሩትን ብቻ ሳይሆን ስሜታቸውንም የማዳመጥ፣ ሕልማቸውንም እንዲያሳኩ የማድረግ ጥበብ አላቸውና::

4ኛ. ሰውን የማደግ ተስፋ ያተገዋል:: የመማርና የመለወጥ እድልን የሚፈጥር፣ አዳዲስ ዕውቀት የሚገኝበት ሥራ ተመራጭ ነው:: የማደግና የመለወጥ ፍላጎት ላለው ሰው ተመራጭ የሚያደርገው እንዲህ ዐይነቱ እድል የሚገኝበትን ቦታ ነው:: አንድ ሰው የትኛው ያዋጣኛል?

[45] Love is Important In Business, Jack Ma
https://www.youtube.com/results?search_query=jak+ma+word+economic+forum+about+love

የሚለውን ሲመዝን ለጊዜው የተሻለ ደመወዝ ቢገኝበትም ነገ የተሻለ ዕውቀትን ከዚያም የተሻለ እድገትን ሊያስገኝ የሚችል ሥራ ተመራጭ ሊሆን ይችላል:: ለጊዜው ከሚገኝ ጥቅም ይልቅ በዕውቀት ማደግ፣ የተሻለ የሥራ ልምድ ማግኘት፣ የማደግ ተስፋ ሰውን የበለጠ የማትጋት ዓቅም አለው የሚባለው ከዚህ የተነሣ ነው:: የተሻለ ሰው ለመሆንና ሙሉ ዓቅምን ለመጠቀም የሚያስችል የተሻለ ሓላፊነትን የሚያስገኝ እድል ሰውን የበለጠ የመሳብ ዓቅም እንደሚኖረው በተግባርም የሚታይ በጥናቶችም የተረጋገጠ ነው::[46]

በተመሳሳይ ሰው ለሚሠራው ሥራ ነጻነትንም ይፈልጋል፡፡ ሁሉንም ነገር ይህን አድርግ፤ ይህን አታድርግ፤ ለምን እንዲህ ሆነ፤ ለምን እንዲህ አልሆነም የሚል አለቃንና እንዲህ ዐይነት የአመራር ባህል ያለበት ተቋምን ብዙውን ጊዜ ተመራጭ አይሆንም:: እንዲህ ዐይነቱ ነገር የሰው ነጻነትን ብቻ ሳይሆን የፈጠራ አቅሙንም የሚያዳክም ነው:: ሰው አቅሙን ለመጠቀም፣ አዳዲስ ነገሮችን፣ የተሻሉ አማራጮችን፣ መሻሻልን ለማምጣት ነጻነቱ ያተገዋል::

5ኛ. ሰውን ለማትጋት የሰውን መንፈሳዊ እይታ ከግንዛቤ ማስገባትም ጠቀሜታ አለው:: “ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም” እንደተባለ ሰው እንደ እንስሳ ለሆዱ ብቻ የሚኖር ፍጡር አይደም :: (ማቴ 4፥6) ሰው እንደየእምነቱ በቁሳዊ ነገር ብቻ ሊረካ የሚችል ሳይሆን እርካታ የሚገኘው ለሰዎች በጎ በማድረግም መሆኑን፣ ሰው በእምነት ሲኖር ብዙም ቁስ ሳይኖረው ያለኝ ይበቃኛል ማለት የሚቻለው ፍጡር መሆኑንም በማሰብ ሰውን በዚህ መልኩ በመረዳት ለማትጋት ይቻላል::

[46] “Motivation is based on growth needs. It is an internal engine, and its benefits show up over a long period of time.” Herzberg
Helping people grow is a key concept in servant leadership. In his classic essay, The Servant as Leader, Greenleaf urged servantleaders to focus on growth. His test for the effective servant-leader was: “Do those served grow as persons?”

ሰው እምነት አለው፥ እሴት አለው፤ በራስ መተማመንም አለው፥ የማንነት ክብርና ኩራትም አለው:: ውድ ቅርሶቻችን እኛ ዘመን ያደረሳቸው ማን ነው? እየተራቡ ፥ እየተራቆቱ፥ እየተሰደዱ በብዙ ድካምና መከራ ቅርሶቻችንን ለእኛ ያስተላለፉልን ቀደምቶቻችንን ምንስ አተጋቸው? እሴታቸው እምነታቸው አይደለምን? በነጻነት ትግል ከባንዳነት ከሚገኝ ሹመትና ሽልማት ይልቅ ነጻነት ይበልጥብኛል ብሎ በዱር በገደል መንከራተት እንዲሁም የሕይወት ዋጋ መክፈልስ ከምን የተነሳ ነው? "ኩራት እራት ነው" የሚለው ብሂልም ሰው ለሆዱ ብቻ አያድርም የሚለውን የሚያሳይ ነው:: የሰው ፍላጎት በየደረጃው አንዱ ሲሟላ ሌላውን የሚሻ ነው ከሚለው የሊቃውንቱ ፍልስፍና[47] በተቃራኒው ሊሆን የሚችለውም እንዲህ ባለው ሁኔታ ነው::

በአጠቃላይ አገልጋይ መሪዎች ተከታዮቻቸውን እንዴት ማትጋት እንደሚገባቸውም የተረዱ ናቸው:: አገልጋይ መሪ ሰውን ከምንም በላይ የሚያተጋው የሚያምንበት ዐላማ ሲኖረውና ዐላማውን ጠንቅቆ ሲረዳ መሆኑንም ጥንቅቆ የሚያውቅ ነው፡፡ ሰው ፍቅርና መተሳሰብ ያለበት ከባቢም ከገነዘበና ሌላ ውጫው ነገር የበለጠ ሊያተጋው እንደሚችልም የተረዳ ነው:: አገልጋይ መሪ እያንዳንዱን ሰው እንዴት ማትጋት እንደሚቻልም ያውቅበታል:: ለሁሉም ሰው አንድ መንገድ ሊሠራ አይችልም:: ከተግሣጽ ይልቅ ለምስጋና ትልቅ ዋጋ የሚሰጠውን በምስጋና እንደየ ጠባዩ ማትጋት ይገባል:: ለማትጋት ካሮትም የሚሠራበት ጊዜና ቦታ አለ፤ አለንጋም የሚሠራበት ጊዜና ቦታ አለ:: ምስጢሩ ጊዜውንና ቦታውን ለይቶና አውቆ መጠቀሙ ላይ ነው::

[47] Maslow's hierarchy of needs is a motivational theory in psychology comprising a five-tier model of human needs, often depicted as hierarchical levels within a pyramid. ... From the bottom of the hierarchy upwards, the needs are: physiological, safety, love and belonging, esteem, and self-actualization, https://digitalcommons.lsu.edu/cgi/viewcontent.cgi?article=4373&context=gradschool_disstheses

7.1.7 በዐላማው ጽኑ

አገልጋይ መሪ አገልግሎትን የሕይወቱ መርህ የሚያደርገው አገልግሎትን ስለሚያምንበትና ከምንም በላይ ውስጡን የሚስደስተው የልብ ማሻቱ ስለሆነ እንጂ ለሰው ለታይታ ወይም ለሌላ ጥቅም አይደለም:: ሰዎችን መርዳት ነፍሱ የሚያረካት ስለሆነ፣ ለተገፉ ሲቆምም ከውስጡ በበቀለና ባደገ ፍጹም እምነት ነው:: አገልጋይ መሪ የሚከተለው የልብ ፍላጎቱን እንጂ ጊዜያዊ ጥቅምን አይደለም:: ቀዳሚ ፍላጎቱ ማገልገል ነውና::

ስኬት የሚኖረው በስሜት ወይም ለጊዜያዊ ጥቅም ሲገባበት ሳይሆን እንዲህ ልባችን የሚደሰትበት፣ የምንመኘውና የምንፈልገውን ሥራ መሥራት ሲቻል ነው:: በሳይንሱ (Passion) ብለው [48] የሚጠሩት ለስኬት ወሳኝ እንደሆነ ነው የሚነገረው:: ከልብ የሚመኙትና የሚወዱትን ነገር መከተልና መሥራት በየትኛው ዘርፍ ለስኬታማነት ከሚጠቀሱ ነገሮች አንዱ ነው:: ይህ ለእንጀራ ብቻ ወይም በስሜት ወይም በብሶት ወይም ለጊዜያዊ ጥቅም ከሚደረግ ምርጫ የተለዬ ነው:: ለምሳሌ ሙሴ ወደ አገልግሎት የገባበት መንገድ የሚያሳዬንም ከልብ መሻትና የውስጥ ፍላጎት ምን ማለት እንደሆነ ነው:: ሙሴን የሚያስድስተው ለተገፉ መቆም ነበርና የነጻነት መሪ ሲሆን የተስፋይቱን ምድር ማውረስ የቻለ የተሳካለት መሪ ሊሆን ቻለ:: ሙሴ የፈርዖን የልጅ ልጅ ተብሎ በፈርዖን ቤት ያደገ በመሆኑ ኑሮው ሁሉ የድሎት ነበር:: ድሎቱ ግን ጊዜያዊ መሆኑን ልቡ ይነግረው ነበር:: የፈርዖን መንግሥት ጨቋኝ ፍትሕ እና ርኅራኄ የጎደለው ሲሆን ተበዳዮቹ ደግሞ ወገኖቹ እንደሆኑ ሙሴ ያውቅ ስለነበር ውስጡ እንዲህ ዐይነቱን ኑሮ ሊቀበለው አልቻለም:: "ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ፤ ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኵር ብሎ ተመልክቶአልና::" እንዲል የፈርዖን የልጅ ልጅ ተብሎ በቤተ

[48] *"It begins with the natural feeling that one wants to serve, to serve first". The Servant as a Leader by Robert K. Greenleaf,* https://www.greenleaf.org/what-is-servant-leadership/

መንግሥት ከመኖር ከወገኖቹ ጋር በሲና ምድረ በዳ፣ በቃዴስ በርሀ መከራ መቀበልን መረጠ:: (ዕብ. 11፥24-26) አገልጋይ መሪ ምርጫው እንዲህ ነው:: ከራስ ድሎት ይልቅ ለሚበልጥ ዐላማ ለተገፉ መቆምን ይመርጣል:: የሚገባበትም በስሜት ወይም ተገዶ ሳይሆን በምርጫ ነው::

መሪነት በስሜት ሊጀመር ይችላል፣ ወይም ብዙውን ጊዜ እንደሚታየው ለጥቅም ሲባል ሊገባበት ይችላል:: መሪነት በታሪክ አጋጣሚም ሊገኝም ይችላል:: አንዱ መሪዎች የሚፈተኑበት ነገር ይህ ነው:: ዐላማ ሲኖር ብቻ ነው አገልግሎት ዘላቂነት እና ስኬት ሊኖረው የሚችለው:: "ዝናብም ወረደ፤ ጎርፍም መጣ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንም ቤት ገፋው በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም።" (ማቴ 7፥25) እንደተባለ ዐላማ ያለውና ተልዕኮንውን የተረዳ መሪ በዓለት ላይ እንደተሠራ ቤት ጽኑ ነው የሚሆነው::

ዐላማን ማወቅ አንድ ነገር ነው:: በዐላማ መጽናት ነው ከባዱ ነገር:: የመሠረት ድንጋይ ማስቀመጥ አይከብድም፤ ቁም ነገሩ ሥራውን ጀምሮ ማጠናቀቁ ላይ ነው:: ጥሩ ዐላማን ጀምሮ መፈጸም ካልተቻለ ልጅ ወልዶ እንደመጣል ይሆናልና:: የቆሙለትን ዐላማ ያሰቡትን ግብ ማሳካት፣ የጀመሩትን መፈጸም ትጋትና ጽናት ይጠይቃል:: ሩጫ የጀመረ ሁሉ በሰዓቱ መጨረስ የሚችል አይደለምም::

በተለይ የመሪነት ጉዞ ውጣ ውረድ የበዛበት ነው:: አገልግሎት ሽክሙ ቀላል አይደለም:: መከራው ብዙ ነው:: አገልግሎት የብዙ ሰው ሸክምን የመሸከም ያህል ነውና:: እንደ ሻማ ሳይቀልጡ ማብራት አይቻልም:: ለማብራት መቅለጥ የግድ ነው:: አገልጋይ መሪን የሚገጥመው ውጣ ውረድ እጅግ ብዙ ነው:: በየምዕራፉ ብዙ ፈተና ያጋጥማል:: ጠላት ከውስጥም ከውጭም ይመጣል:: ተኩላ በበጎች መካከል ተኩላነቱን ገልጾ ሳይሆን የበግ ለምድ ለብሶ ነው የሚመጣው:: ይህን ሁሉ ለመቋቋም ብርታት ብቻ ሳይሆን ቁርጠኝነት ያስፈልጋል::

በመንፈስ ጀምረው በሥጋ የፈጸሙ፣ ለፍሬ ሳይደርሱ በአበባ የቀሩ፣ የገቡትን ቃል ፈጥነው የረሱ፣ አደራቸውን የበሉ ብዙ መሪዎች የመኖራቸውን ያህል ለዐላማቸው የቆሙ፣ ለቃላቸው የታመኑ ጽኑዓን መሪዎችም አሉ። አገልጋይ መሪ ጽኑ ነው። አገልጋይ መሪ በመከራ መካከል ተስፋ አይቆርጥም፣ በምኞት ተጠልፎ ከዐላማው ሳይደርስ አይሰናከልምም። መጽሐፍ "መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፣ ሩጫውን ጨርሼአለሁ" እንዲል እውነተኛ አገልጋዮች የጀመሩትን ሩጫ ሳይጨርሱ የድሉን አክሊል ሳይቀዳጁ ማቋረጥ የለም። የድል አክሊልን ለመቀዳጀት ግን መሮጥ ብቻ ሳይሆን ሮጦ ማጠናቀቅንና መቅደምን ይጠይቃል። ሩጫውን የሚጀምሩት ብዙ ቢሆኑም የድል አክሊሉን አያሰቡ ድካሙን በመታገሥ የመጨረሻው መስመር በሰዓቱ መድረስ የሚችሉ ጥቂቶች ብቻ ናቸውና።

አገልግሎት ብዙ መሰናክል አለበት። ዐላማን የሚያስቱ እንቅፋቶችም በዛ ያሉ ናቸው።

1ኛ. በዐላማ መጽናት የሚቻለው ዐላማን በትክክል መረዳት ሲቻል ነው። ዐላማን በውል ሳይረዱ በስሜት ወደ አገልግሎት ቢገቡበት ስሜቱ ሲበርድ መቀዝቀዝ ይመጣል። በመንጋ የሚጀመር ሥራም መንጋው ሲበተን አብሮ መበተኑ የማይቀር ነው። ዐላማን ሳይሆን ሰውን ቢከተሉ ሰው ተሰባሪ ነውና የተከተሉት ሰው ቢሰበር አብሮ መሰበር አይቀርም። በዐላማ መጽናት የሚቻለው ትርፍና ኪሳራውን አስልቶ ሲገባበት ነው። አውቀውት የገቡበት ጉዞ ፈተና ሲገጥም ለካ እንዲህ ነበር ብሎ ከመደንገጥም ያድናል።

ያለ ተልዕኮ መልካም ፍሬን ያፈራ መሪንም ብዙም መጥቀስ አይቻልም። የሰው ልጅ ለሚሠራው ሁሉ አስቀድሞ የሚጠይቀው ጥያቄ ለምን? የሚል ነው። ይህን ሥራ ለምንድን ነው የምሠራው? በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ የፈለግሁት ለምንድን ነው? የሃይማኖት መሪ የሆንሁት ለምንድን ነው? የሕዝብ አገልጋይ መሆን የፈለግሁት ለምንድን ነው? መታገልና መሥዋዕት መክፈል ያስፈለገኝ ለምንድን ነው? ይህ ሁሉ ድካም ምን ለማግኘት ነው? እያለ ይጠይቃል። እነዚህንና የመሳሰሉት

ጥያቄዎች መመለስ የሚቻለውም ከልብ የሚታመንበት የጠራ ዐላማ ሲኖር ነው::

“የሚሞትለት ዐላማ የሌለው ሰው ለመኖር ብቁ አይደለም” የሚለው ትልቅ አባባል ነው[49]:: ባለ ተልዕኮ መሪ የሚኖርለት ዐላማ ብቻ ሳይሆን ሊሞትለት የሚችል ዐላማም ሊኖረው ይገባል:: በሥልጣን ከሚገኘው ጊዜያዊ ጥቅም ባለፈ ግልጽ ዐላማ እና የቆመለትን ተልዕኮ በአግባቡ የተረዳ መሪ ማግኘት የሚቻለው ምን ያህል ነው? የሚለው ነው እንጂ ትልቁ ጥያቄ::

ዐላማ ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ በተግባር ለዐላማቸው ብዙ መሥዋዕትን የከፈሉ በብዙ የተፈተኑ መሪዎች የመኖራቸውን ያህል መሪነትን ለግል ጥቅም ፍጆታ ከማዋል ያለፈ ሀገር ወገን የሚጠቅም ዓላም የሌላቸው መሪዎችም ብዙዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ከራስ ጥቅም ያለፈ ዐላማ የሌላቸው በእያንዳንዱ ሹመት ምን እጠቀምበታለሁ እንጂ ምን አገለግልበታለሁ የሚለውን የማያስቡ መሪዎች ቁጥራቸው ቀላል አይሆንም:: ከግል ጥቅም የብዙኃኑን ጥቅም ለማስቀደም፣ ምን አገኝበታለሁ ከማለት ለብዙዎች ምን አስገኝበታለሁ ማለትን ይጠይቃልና:: ከገንዘብና ከተዋቂነት፣ ከጊዜያዊ መገሳና አጃቢ ማፍራት ባለፈ ዘላቂ ለውጥን ለማምጣት፣ የተጎሳቆለውን ኑሮ ለማቃናት፣ የጨለመበትን ትውልድ ከሞራል ዝቅጠት ለማውጣት የአገልግሎትን ምንነት መረዳትም ያስፈልጋል:: ዐላማም ሊኖር ይገባል::

በሃይማኖት ተቋማት እንኳ ዐላማው ገብቷቸው ወደ አገልግሎቱ የመጡ ምን ያህሉ ናቸው? ምን ያህሉ ናቸው ተልዕኳቸውንም በአግባቡ የተረዱት? ምን ያህሉስ አገልግሎቱ የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ናቸው? የሚለው ጥያቄ ቢጠይቅ ምን ያህል እውነተኛ አገልጋዮችን ማግኘት ይቻል ይሆን? ዐላማው ገብቷቸው የሚያገለግሉ ብቻ ሳይሆኑ ለዐላማቸው ለመሞት የተዘጋጁ ባለ ተልዕኮ መሪዎች የመኖራቸው ያህል ከመተዳደሪያነት ባለፈ የረባ ዐላማ የሌላቸውም የዚያኑ ያህል እንደሆኑ

[49] “**A man who does not have** something for which **he** is willing to die is **not** fit to live.” **— Martin Luther** King Jr.

ግን በየጊዜው የሚታይ እውነት ነው:: የሚያምንበት ዐላማ የሌለው መሪ ለጊዜው ነው እንጂ ፈተና ሲገጥም ማፈግፈጉ አይቀርም:: በስሜት የገቡበትን አገልግሎት በሰበብ አስባቡ ማቋረጥም የተለመደ ነው::

2ኛ. *መታገሥ* በሌለበት ዐላማን ማሳካትም ቀላል አይሆንም:: ትልቅ ዐላማ እንዲህ በዋዛ ሊሳካ አይችልምና:: ስኬት እንዲህ በቀልድ አይገኝም:: እንቅልፍ ማጣት አለ፤ የሚገጥመው እንቅፋት፣ እሾሁና አሜካላው ቀላል አይደለም:: የሚያጋጥመው በያይነቱ ነው:: ማዕበል ይመጣል ማዕበል ይሄዳል፤ ቋሚ የሚባል ማዕበል አይኖርም:: ማዕበል ያልፋል፤ እስኪያልፍ ግን ያለፋል:: መሻገሪያ መርከቡም መጨከን ብቻ ነው:: መጨከን ያስፈልጋል:: መታገሥ ግድ ይላል:: ወድቆ መነሣትን፣ ጨለማን መሻገር እንደሚቻል ማመን ከሌለ ወደ ስኬት መድረስም ይከብዳል::

አገልጋይ መሪ መከራን የሚታገሠው ከሚደርስበት ፈተና ይልቅ የተሸከመው መልካም ዐላማ ስለሚበልጥበት ነው:: በዐላማ ለመጽናት የዐላማው ትልቅነት ወሳኝነት አለው:: ዐላማ ያለው መሪ ከሚደርስበት መከራ ይልቅ የሚያሳካው ውጤት ያሳስበዋል:: ከሚደርስበት ጭንቀት ይልቅ የዐላማው መሳካት ያስጨንቀዋል:: የዐላማው ትልቅነት የሚደርስበትን እንግልት ያስረሳዋልና:: የእውነተኛ አገልጋዮች ታሪክም ይህን የመሰለ ነው::

“ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፣ በወንበዴዎች ፍርሃት፣ በወገኔ በኩል ፍርሃት፣ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፣ በከተማ ፍርሃት፣ በምድረ በዳ ፍርሃት፣ በባሕር ፍርሃት፣ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ:: በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፣ በራብና በጥም፣ ብዙ ጊዜም በመጦም፣ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ:: የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፣ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው::” የሚለው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት የሚያመለክተውም ከፈተናው ብዛትና ብርታት ይልቅ የዐላማው ትልቅነት በፈተና መጽናት የሚያስችል መሆኑን ነው:: (2ኛቆሮ. 11፥28)

ይህ ሃይማኖታዊ ስለሆነ ብቻም አይደለም፤ ሌላውም ዐላማ ተመሳሳይ ነው:: ዐላማው ትልቅ ከሆነ ትልቁ ችግር ከዐላማው አንጻር ሲመዘን ቀሎ ይገኛል:: ዐላማው ጊዜያዊ ጥቅም ማግኘት ከሆነ ግን ኮሽ ባለ ቁጥር መደንገጥ፣ ምክንያት በተገኘ ጊዜ ሁሉ ማቋረጥ ይመጣል::

3ኛ. በመከራ ከዐላማ የመደናቀፍን ያህል ድሎትም ጠልፎ ሊጥል ይችላል:: የሚልቀው ፈተና የሚከሠተው ድሎትና ምቾት ሲበዛ ነው:: በአስቸጋሪ ሁኔታ ሁሉም ድሀ ነውና ሁሉም እኩል ነው:: ሁሉም ይተሳሰባል፣ መካካድ ብዙም ላይሆን ይችላል:: መፈተን የሚመጣው ድሎት ሲጀመር ነው::

ለነጻነት እንታገላለን የሚሉ ሰዎች የራሳቸውን ኑሮ ለማስተካከል ብቻ ማሰብ ሲጀመሩ፣ ለሕዝብ ጥቅም እንታገላለን የሚሉ ሰዎች የራሳቸውን ጥቅም ሲያስቀድሙ የገቡት ቃል ኪዳን የቆሙለት ዐላማ ይረሳቸዋል:: ለምሳሌ ለሕዝብ ነጻነት ራሳችንን መሥዋዕት እስከ ማድረግ እናገለግላለን ብለው ከወጡ መሪዎች መካከል አብዛኞቹ ሲፈተኑ የሚታዩት በችግር ጊዜ ሳይሆን በድሎት ነው:: ድሎት ሲጀመር የበለጠ ሀብትን ማጋበስ ያምራቸዋል:: ዐላማ የሚባለው ነገር ተረሥቶ ዐላማው ሀብትን ማጠራቀም፣ በወገን ሀብት ራስን ማዝናናትና መቀማጠል ብቻ ይሆናል:: ለዐላማቸው የተሰዉ ሰዎችን ይረሷቸዋል፤ የገቡትን ቃል ኪዳን ፈጽሞ አያስታውሱትም:: በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ አንዱ እየተቸገረ አንዱ ሲደላው ነው፣ እርስ በእርስ መፈረካከስ፣ መለያየት የሚመጣው::

በእምነቱም ቢሆን ተመሳሳይ ነው:: ፈጣሪያቸውን ለማገልገል የቆረጡ፣ መሐላቸውን የሰጡ፣ የእምነት ሰዎች እንኳ ሥልጣን ሲመጣ ያን ጊዜ ነው የሚፈተኑት:: አገልግሎት ይረሳና ምነው እንዲህ የነበረ ሰው ምን ነካው? እስኪባል ድረስ የአስተዳደር በደልን የሚያደርሱ ለራሳቸውም ለሌላውም የማይጠቅሙ የሚሆኑ የሃይማኖት መሪዎች የመኖራቸው አንዱ ምስጢርም ይሄው ነው:: ብዙ ጊዜ የአመራር ክስረት የሚያጋጥመውም እንደ ዴማስ በጎውን ዐላማ በሆዳቸው የሚቀይሩ ሆድ አምላኩ የሆኑ ሰዎች ሲበዙ ሊሆን ይችላል:: ዐላማ ቢስ የሆነ ሰው

እንደ ዴማስ ትልቁን ራእይ በሆዱ ለውጦ በብልጭልጭ ዓለም ተታሎ የደመቀ ከተማ ሲደርስ እኔን ከተመቸኝ ምንተዳዬ ማለቱና አገልግሎትን መሰናበቱ የሚጠበቅ ነው::

“ሁለትን ነገር ከአንተ እሻለሁ፤ ሳልሞትም አትከልክለኝ ከንቱነትንና ሐሰተኛነትን ከእኔ አርቃቸው:: ድህነትንና ባለጠግነትን አትስጠኝ፣ ነገር ግን የሚያስፈልገኝን እንጀራ ስጠኝ፣ እንዳልጠግብ እንዳልክድህም:: እግዚአብሔርስ ማን ነው? እንዳልል ድሀም እንዳልሆን እንዳልሰርቅም፣ በአምላኬም ስም በሐሰት እንዳልምል::” የሚለው የጠቢቡ ሰሎሞን ልመናም የሚያመለክተው ከማጣት ባልተናነሰ ማግኘት፣ ድሎት ወይም ጥጋብ እንኳን ዐላማን ፈጣሪን የማስረሳት፣ ቃል ኪዳንን የማስካድ ዓቅም እንዳለው ነው:: (ምሳ. 30፥7-9)

አገልግሎትን የተረዳ መሪ ትናንትም ዛሬም ነገም ያው አገልጋይ መሪ ነው:: ሥልጣን ሲገኝም፣ ሀብት ሲገኝም፣ ክብርና እውቅና ቢገኝም ጉዳዩ አይደለም:: ዐላማው አገልግሎት ነው:: የቆመለትን ዐላማ እስኪፈጸም ድረስ፣ አገልጋይ መሪ ዐላማው ላይ ብቻ ነው ትኩረቱ:: ሌላው ነገር ትርፍ ነገር ነው:: በተቻለው መጠን ከንቱ ውዳሴ፣ የበዛ ዝናን እና ከበሬታንም ሆን ብሎ ሲርቃቸው ይኖራል እንጂ አይከተላቸውም::

4ኛ. በችግር ጊዜ ነው ጽናት የሚፈተነውም:: የመሪ ስኬቱ ችግርን ተቋቁሞ ከማሸነፍ ወይም በችግር ከመረታት ብቃቱ ጋር የሚያያዝም ነው:: በመሪነት ጉዞ የሚጠበቀው ብቻ ሳይሆን የማይጠበቀው የሚሆንበት ጊዜ ጥቂት አይሆንም:: በየጊዜው እንግዳ ነገር ሊከሠት ይችላል:: ያን ማዕበል ተሻገርን ሲባል ሌላ ማዕበል፣ ሰላም ሆነ ሲባል ግጭት፣ ግጭቱን ለመፍታት ሲሞከር ሌላ ያልታሰበ ምስቅልቅል፣ ግጭቱ ደግሞ ጋብ ሲል ራብ፣ ተረጋጋ ሲባል ሁከት የሚያጋጥመው አደጋ በያይነቱ ነው:: አንዱን ችግር ለመፍታት ሲሞከር ያልታሰበ ሌላ ውስብስብ ችግር ሊፈጠር ይችላልም::

የሰዎች ማንነት የተለያየ እንደመሆኑ ኮሽ ባለ ቁጥር የሚደነግጥ አለ:: በአስፈሪ ቀውስና ምስቅልቅል ምንም እንዳልተፈጠረ ተረጋግቶ የሚያረጋጋ፣ በአደጋ ውስጥም ተስፋን የሚይይ ብቻ ሳይሆን ለጨለመባቸው ተስፋን የሚሰጥ ሰውም አለ:: መሪ እንዲህ ወፍራም ቆዳ ያለው የሚባል ዐይነት ሰው ካልሆነ ብዙም ርቀት ሊጓዝ የሚችል አይደለም::

የመሪ አንዱ ትልቁ መለኪያ ቀውስ ሲያጋጥም ተረጋግቶ የመምራትና ቀውስን የማሻገር አቅሙ ነው:: ይህ ደግሞ ራስ መግዛትን፣ አካባቢን መረዳትን፣ ፈጥኖ መልስ መስጠትንና የመሳሰሉትን ችሎታዎች ይጠይቃል:: በተለይ ራስን መግዛትና በርትቶ ማበርታትን በችግር ውስጥ ሆኖ ምንም እንዳልተፈጠረ ተረጋግቶ ማረጋጋትን ተከታይ ከመሪው የሚጠብቀው ትልቅ ችሎታ ነው:: ቀውስን ለመሻገር ሕዝብን አረጋግተው ተስፋ ሰንቀው ተስፋ የሚሰጡ የፊራውን ሕዝብ የሚያበረቱ ባዩት የማይሸበሩ መሪዎች ያስፈልጋሉ:: መሪው በእነርሱ እጅ ነው:: ተሳፋሪው የተሳፈረው እነርሱን አምኖ ነው:: አብራሪው መንጫገጭ ቢኖርም አይሟችሁ እናልፈዋለን የሚል ካልሆነ፣ እርሱም ፈርቶ የሚያስፈራ ከሆነ የሚተርፍ ሰው አይኖርም::

“በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና” እንዲል በፍርሃት የሚሸበር ሳይዋጋ የተሸነፈ ነው:: “ ይቻላል” የሚል እምነት ሲኖርና “አይቻልም ከባድ ነው” የሚል እምነት ሲኖር ልዩነት አለው:: ማሸነፍ ወይም መሸነፍ ከልብ እምነት ይጀምራልና:: አሸናፊ ልብ (winning attitude) ያለው “ለሚያምን ሁሉ ይቻላል” እንደተባለ አይሆንም፣ አይቻልም የተባለው ይሳካለታል:: “ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም” እንደሚባለው ነው:: አሸናፊ ልብ ያለው መሪ እንደ ኢያሱና ካሌብ ዮርዳኖስን ያሻግራል፤ ኢያሪኮን ያፈርሳል፤ የተስፋይቱ ምድርን ያወርሳል:: እምነት ካለ፣ የልብ ውሳኔ ካለ ቀጭን ገመድ ሆኖ ያስችግር ይሆናል እንጂ መሻገር ግን ይቻላል:: የቀደሙት መሪዎቻችን ታሪክም የልበ ሙሉነትን ምንነት የሚያሳይ ነው:: በቅኝ ግዛት በወደቁና በቅኝ ግዛት አልያዝም ብላ ባመጸችው ኢትዮጵያ መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት አንገዛም የሚል የሚሸፍት

ልብ የመኖርና ያለመኖር ነው ማለት ይቻላል:: ተሞክሮ መሸነፍ ሌላ ጉዳይ ነው:: በቀደሙ አባቶቻችን ልበ ቆራጥነት፣ በአልበገር ባይ ልባቸው እና ጠንካራ እምነታቸው ነው አውሮጳውያንን መቋቋም ይቻላል ተብሎ በማይታመንበት ዘመን እውነት ሆኖ ለማሸነፍ የተቻለው::

አገልጋይ መሪ በፈተና አይበገርም:: ብዙውን ጊዜ በችግር ተወልዶ፣ በችግር አልፎ ከችግር የሚያወጣ መሪ የሚወለደው በመከራ መካከል ነውና:: አሁንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌ ማንሳቱ ነገሩን ለማጉላት ሊጠቅም ይችላል::

በዚያ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ቅዱስ ጳውሎስ እስረኛ ሆኖ በመርከብ ከሌሎች ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሰዎች ጋር ወደ ሮም ሲጓዙ ብዙ ችግር ገጠማቸው:: በመርከብ እያሉ ማዕበል ተነሣ:: አንዱን ማዕበል ሲያልፉ ሌላው ይተካል:: በመርከቡ ያሉት ሁሉ በማዕበሉ ተሸበሩ:: ተስፋ ቆረጡ:: ተስፋ ከመቁረጣቸው የተነሣም ለአሥራ አራት ቀናት ምግብ አልበሉም:: በሰው ዓቅም የሚሆነውንም ሁሉ አደረጉ:: የመርከቧን ጭነት ወደ ውኃ በመጣል ሸክሙን አቃለሉ:: ከብዙ ቀናት የስቃይ ጉዞ በኋላም የባሰ ነገር ተፈጠረ:: መርከባቸው መሰባበር ጀመረ:: ወታደሮቹም ተስፋ ቆርጠው ነበርና ከእስረኞች አንድ ስንኳ ዋኝቶ እንዳያመልጥ ይገድሉአቸው ዘንድ ተማከሩም:: በዚህ መርከብ ተረጋግቶ የሚያረጋጋ፣ ተጽናንቶ የሚያጽናና ሰው ባይኖር ኖሮ የብዙ ሰው ሕይወት ያላግባብ ባለፈም ነበር:: ቅዱስ ጳውሎስ ግን አትደንግጡ በደህና እንደርሳለን የሚጠፋ ነፍስም የለም ብሎ ምግብ እንዲበሉ አረጋጋቸው:: ይህ ነው በትንሽ ነገር መሸበር ወይም ተረጋግቶ ማረጋጋት መቻል ማለት:: በቀውስ ጊዜ የሚያስፈልገው እንደ ቅዱስ ጳውሎስ አስቀድሞ ችግር የሚተነብይ፣ ችግር ከደረሰ ደግሞ በጥበብ የሚያሻግር መሪ ነው:: (የሐዋ.ሥ 27) በዓለም ላይ በስኬታማነታቸው የሚመሰክርላቸው ብዙዎቹ መሪዎችም ለድል የበቁት ለተሰለፉበት ዕላማ እንዲህ ባለው ውጣ ውረድ በጽናት ማሸነፍ መቻላቸው እንደሆነ ነው በየታሪኩ የተጻፈው::

በሌላ በኩል አንድ ቦክሰኛ “ሊጥልህ የሚችለው ጠንካራ ቡጢ መሆኑ ሳይሆን ሳትጠብቀው በድንገት የተሰነዘረብህ ቡጢ ነው” እንዳለው ከሚታይ ትልቅ አደጋ ይልቅ ያልታሰበ ችግር ትንሽም ቢሆን ለመቆጣጠር የባሰ አስቸጋሪ ይሆናል። የጭቃ እሾህ አደገኛነቱ በጭቃ ውስጥ የተቀበረ መሆኑ ነው። መሪም እሳት ሲከሠት እየተከተሉ ማጥፋት ብቻ ሳይሆን፣ አደጋን ከመከሠቱ በፊት ይተነብያል። አደጋ ቢከሠት ፈጥኖ ለመቆጣጠር በቂ ዝግጅት ያደርጋል። ብልህ መሪ አደጋ ከደረሰ በኋላ አደጋ የሚከላከል ሳይሆን አደጋ እንዳይደርስ በመከላከል ሥራ ላይ የሚያተኩር፣ እሳት በተነሣ ጊዜ እየተከተለ የሚያጠፋ ብቻ ሳይሆን አስቀድሞ ችግር የሚከሠትበትን ቀዳዳ ሁሉ እያሸተተ የሚደፍን ነው። እሳት በተነሣ ቁጥር እየተከተሉ ለማጥፋት መሞከር ብዙ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላልና። አደጋ የትና መቼ እንዴት ሊከሠት ይችላል? ብሎ መተንበይ የአደጋውን መጠን፣ መምጫ መንገዱን፣ ዐይነቱንና መውጫ መንገዱን አውቆ ለመከላከል ይጠቅማል። እንዲህ ከሆነ እንደ ጫካ እሳት ከአንዱ ወደ ሌላ እየዘለለ ውድመት ሳይበዛ አደጋ ሊከሠት በፍጥነት ደርሶ መቆጣጠር ይቻላል።

ምዕራፍ ስምንት

ሥልጣንና አገልግሎት

8 ሥልጣን

ለአገልጋይ መሪ ሥልጣን የማገልገያ መሳሪያ ነው:: አግልግሎትን ላልተረዱ መሪዎች በተቃራኒው ሥልጣን ሓላፊነት ሳይሆን ሹመት ነው "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል" እንዲሉ:: አገልግሎትን ላልተረዱ መሪዎች ሥልጣን ለመጠቀሚያ፣ ለመበልጸጊያ፣ ከራስ አልፎ ዘመድ አዝማድን ለመጥቀሚያ፣ ለማዕረግ፣ ለገና ወይም እውቅና፣ ለመከበሪያነት፣ ለመፈራት ወይም ለመገረፊያነት ነው የሚፈለገው:: አንድ ሰው ሓላፊነት ሲሰጠው የተለመደውም እግዚአብሔር ያስችልህ፣ የተሳካ አገልግሎት እንድትፈጽምበት እግዚአብሔር ይርዳህ ሳይሆን "ሹመት ያዳብር" ነው ምርቃቱ:: በሹመት ላይ ሌላ ሹመት ደግሞ ሌላ ሹመት እየጨመርክ በሥልጣን እንድትከራርም ያድርግህ የሚል ነው ምኞቱ:: ይህም ምኞት ከድሀው ሕዝብ እየነጠቅህ ራስህን እና ዘመድ አዝማድን ሀብት በሀብት የምታንበሸብሽ ሁን፣ ተቋሙንም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በቤተ ዘመድ አጥለቅልቀው የሚል ዐይነት ነው:: የተለመደው ይህን ይመስላል:: ይህ ነገር አሁን አሁን በቤተ እምነቱም ተመሳሳይ ሆኗል::

ሥልጣንን ከራስ ጥቅም ይልቅ ለአገልግሎት ለማዋል አስቀድሞ የሥልጣን ባለቤት እግዚአብሔር ከዚያ ደግሞ ሕዝብ መሆኑን ከልብ ማመንን ይጠይቃል:: ሥልጣን የማገልገያ መሳሪያ ነው የሚለውን ተግባራዊ ለማድረግ፣ ታዛዥ ነኝ፣ አገልጋይ ነኝ ለማለት በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ ተጠያቂነት አለብኝ ብሎ ማመንንም ይፈልጋል:: ሥልጣን የማገልገያ መሳሪያ ነው የሚለውን ተግባራዊ ለማድረግም የምሠራው በደል በሕግም በእግዚአብሔርም ሊያስጠይቀኝ ይችላል፤ እንዲሁም የገባሁትን ቃል በተግባር መፈጸም ባልችል ሥልጣኔን የሰጠኝ ሕዝብ ይወስድብኛል የሚለው ከወሬ ባለፈ ወደ ልብ ሊሰርጽ ይገባል:: ሥልጣን በጉልበት የተገኘ ከሆነ ግን የሥልጣኑ ባለቤት ጉልበት ነው:: ጉልበት እስካለም ጠያቂ የለበትም:: እንዲህ ባለ ሁኔታ ማገልገል፣ ዝቅ ማለት፣ ተጠያቂነት ተረት ብቻ ነው የሚሆነው::

ሥልጣን በአግባቡ ከተጠቀሙበት እግዚአብሔርን፣ አገርንና ሕዝብን የሚያገለግሉበት መሳሪያ ነው:: የተጠቁትን ነጻ ለማውጣት፣ ለአቅመ ደካሞች ጥበቃን፣ ለታሠሩትም መፈታትን፣ ቀን ለጨለመባቸው ማየትን፣ ፍትሕ ላጡ ፍትሕን ለማስፈን የሚሠሩበት መሳሪያ ነው ሥልጣን:: አገልጋይ መሪ ሥልጣንን የሚፈልገው ራሱን ለመጥቀም ሳይሆን የብዙዎችን ሕይወት በበጎ ለመለወጥ ሥልጣን ዓቅም ስለሚፈጥርለት ነው:: አገሬን እና ሕዝቤን እንዴት ላገልግል ተብሎ ሲታሰብ አንዱ መንገድ ለመሪነት የሚያበቃ ሥልጣንን በመያዝ ነው:: ቢያንስ ራሱን ለሌሎች መሥዋዕት ለማድረግ በተግባር ሩቅ ቢሆንም ራሱንም ጠቅሞ ሕዝቡንም ለመጥቀም ሥልጣን ኃይልን ይፈጥራልና::

ፕሬዘዳንት ጆርጅ ቡሽ በ1989 እ.ኤ.አ የበዓለ ሲመታቸው ጊዜ "ሹመት የተሰጠን የራስን ዐላማ ለማራመድ ለግል ጥቅም ሀብትን ለማፍራት ወይም ለዝና ለመከበሪያ ወይም ለማዕረግ ሳይሆን ሹመት የተሰጠን ለአንድ ዐላማ ብቻ ነው:: እርሱም ሕዝብን ለማገልገል ነው"[50] እንዳሉት

[50] Use power to help people. For we are given power not to advance our own purposes nor to make a great show in the world, nor a name. There is but one just use of power and it is to serve people"- https://avalon.law.yale.edu/20th_century/bush.asp

በሰለጠኑ አገሮች ለሥልጣን ያላቸው እይታ የተሻለ ነው የሚያስብሉ መገለጫዎች ይታያሉ:: ሥልጣን የማገልገያ መሳሪያ ነው ወደሚለው የቀረበ ይመስላል:: ከልባቸው ሕዝባቸውን ለማገልገል ባላቸው ፍላጎት የተነሣ የፖለቲካ ሥልጣንን ይሁን በበጎ አድራጎት ወይም በእምነት ተቋማት የመሪነትን እድል ለማግኘት የሚሠሩ ሰዎችን ማየት የተለመደ ነው:: የሥልጣን ዘመናቸው ሲያልቅም አንዱን ምዕራፍ ዘግተው በሌላ የሕይወት ምዕራፍ ወይም በሌላ የአገልግሎት ዘርፍ ይሰማራሉ እንጂ የያዙትን ሥልጣን መጭ አድርገው ላለመያዛቸው አንዱ ምስጢርም ሥልጣንን የማገልገያ መሳሪያነቱን ከልባቸው አምነው ስለሚቀበሉት ሊሆን ይችላል:: ሥልጣን የማገልገያ መሳሪያ ነው ብሎ ከልቡ የሚያምን መሪ ለሥልጣን ሲል ተቀናቃኞቹን የሚያስገድል ወይንም እኔ ካልመራሁ አገር ይፈረሳል የሚያሰኘው ምን ነገር ይኖራል? ሥልጣኑ የተፈለገው ለአገልግሎት ከሆነ በስልጣን ለረዥም ጊዜ የቆዩ መሪዎች የተሻለ ዓቅም ያላቸውንና ዘመኑን የሚመጥኑ ተተኪ መሪዎችን ወደፊት ማምጣት ሲገባቸው እስከሞት ድረስ ሥልጣንን መጭ አድርጎ መንገታገትንስ ምን ይሉታል?

የሥልጣንን ምንነት ባልተረዱ መሪዎች ያለው እሳቤ እንዲህ አይደለም:: በሥልጣን መሰላልነት የሚፈልጉትን ለማድረግ ልባቸው እያወቀ፣ ሕዝብን ለማገልገል ፍላጎትና ቁርጠኝነት እንዳላቸው ሆኖ መታየት የተለመደ ሆኗል። ሥልጣን በእነርሱ ዘንድ ሹመትን፣ ሀብትን፣ ስምንና ዝናን እንዲሁም ከበሬታን ማግኛ መሰላል ነው:: ለነገሩ በተግባር ይገለጣል እንጂ ሥልጣንን የፈለኩት የራስን ዐላማና ጥቅም ለማራመድ ነው የሚል ይገኛል ተብሎ መቼም አይጠበቅም::

8.1 ሥልጣን ምንድን ነው?

ይህን ጥያቄ ለመመለስ ብዙ ፍልስፍና እና ፖለቲካዊ ትንታኔ በዓለም ላይ እንዳለ የሚታወቅ ቢሆንም ከፍልስፍናው ወጣ ብሎ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል መነጽርነት ጉዳዩን መመልከቱም ጠቃሚ ይሆናል::

መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣንን በተመለከተ ብዙ ቁም ነገሮችን ያስተምረናል። ከእነዚህ መካከል የሚከተሉቱን እንመለከታለን፡-

1ኛ. ከሁሉም አስቀድሞ እግዚአብሔር የሥልጣን ሁሉ ባለቤት ነው የሚለው ነው። እግዚአብሔር የነገሥታት ንጉሥ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው። "አቤቱ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና ታላቅነትና ኃይል ክብርም ድልና ግርማ ለአንተ ነው፣ አቤቱ መንግሥት የአንተ ነው አንተም በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያልህ ራስ ነህ። ባለጠግነትና ክብር ከአንተ ዘንድ ነው አንተም ሁሉን ትገዛለህ፤ ኃይልና ብርታት በእጅህ ነው፣ ታላቅ ለማድረግ ለሁሉም ኃይልን ለመስጠት በእጅህ ነው።" የሚለው ቃልም ይሄንኑ ነው የሚያሳዬው። (1ኛዜና 29፥11-12) አረዳዱና አገላለጹ ሊለያይ ቢችልም በአንድ ፈጣሪ የሚያምኑ ሁሉ ፈጣሪ የሥልጣን ሁሉ ባለቤት ነው፤ ለክፉም ይሁን ለደግ ሥራ በፈጣሪ ዘንድ ተጠያቂነት ይኖራል ብለው እንደሚያምኑ ነው የሚነገረውም። ሥልጣን በየትኛውም መንገድ ተገኘ ተብሎ ቢታሰብ እንኳ የሥልጣን ባለቤቱ የነገሥታት ንጉሥ የተባለ እግዚአብሔር ነው። ምክንያቱም ምድሪቱ የእርሱ ናት፤ በምድሪቱ ያሉ ፍጥረታት ገንዘቡ ናቸውና። እግዚአብሔርም የፈጠረውን ፍጥረት በመግቦቱና በጠብቆቱ የማይለይ አምላክ እንደመሆኑም ለፍጥረቱ ያስባል። በጎቹ የእርሱ ናቸው፣ ጠቦቶቹም የእርሱ ናቸው፣ ግልገሎቹም የእርሱ ናቸው። በጎቼን፣ ጠቦቶቼን፣ ግልገሎቼን በአግባቡ አሰማሩ፣ ጠብቋቸው ይላል። በጎቼን በአግባቡ አላሰማራችሁም ብሎም መሪዎችን ይጠይቃል። (ሕዝ 34፥ 1-23)

2ኛ. የሰው ልጅ ምድርን የሚገዛበትን ሥልጣን ያገኘውም ከፈጣሪው ነው። "እግዚአብሔርም ባረካቸው፣ እንዲህም አላቸው። ብዙ፣ ተባዙ፣ ምድርንም ሙሉአት፣ ግዙአትም፣ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም" ተብሎ እንደተጻፈ። (ዘፍ 1፥28) ይህ ነው የሰው ሥልጣንን የውክልና ሥልጣን የሚያሰኘው። ውክልና እስካለ ድረስ ደግሞ ባለቤቱ አደራ በሰጠው ነገር አደራ ተቀባዮችን አደራቸውን በአግባቡ መወጣት መቻላቻውን ወይም አደራ ማጉደላቸውን

የሚጠይቅበት ሰዓት እንደሚኖር ማመን የሚያስፈልገውም ከዚህ የተነሣ ነው:: “ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል” ተብሎ እንደተጻፈ ይዘገይ ይሆናል እንጂ ሰው የዘራውን ማጨዱ እንደማይቀርም በብዙዎች እምነቶች የሚታምንበት ነው:: (ገላ 6፥7) መክሊት የሰጠ ጌታ መክሊቱን ከትርፉ ጋራ የሚጠይቅበት ሰዓት ይመጣል:: ሰው ለሠራው ሥራ ሁሉ የሚጠየቅበት ጊዜ ይመጣል የሚለው ደግሞ አንድ መሪ ተጠያቂነት ያለበት በምድራዊው ሕግ ብቻ ሳይሆን በሰማያዊው ሕግም ጭምር መሆኑን ያመለክታል::

በአጠቃላይ ለአንድ መሪ እግዚአብሔር የሥልጣን ሁሉ ባለቤት ነው፤ የነገሥታት ንጉሥ ነው ብሎ ማመን እና አለማመን ትልቅ ልዩነት አለው:: የሥልጣን ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ነው፤ የሰው መሪነት የተገኘው ከእግዚአብሔር ነው፤ የምናስተዳድረው ሕዝብ የእግዚአብሔር ነው ብሎ ማመን እና ይህን አለማመንም ሰፊ ልዩነት አለው:: ሰው ለሚሠራው በጎም ይሁን ክፉ ሥራ በእግዚአብሔር መጠየቅ አይቀርም፤ በጎ ሥራ ዋጋ እንደሚያሰጥ ሁሉ ክፉ ሥራም ዋጋ ማስከፈሉ አይቀርም ብሎ ማመን እና አለማመን በመሪ የመሪነት ፍልስፍና ላይ መሠረታዊ ልዩነት ማምጣቱም የሚጠበቅ ነው::

3ኛ. የሰው ልጅ ሥልጣንን አጥብቆ ይፈልጋታል:: የመጀመሪያው የሰው ልጅ ውድቀት ምክንያቱ የተሰጠውን ሳይሆን ያልተሰጠውን ሥልጣን መሻቱ እንደሆነም የታወቀ ነው:: ከዚህ ወዲህ ይሁን ከዚያም በፊት የሥልጣን ፍቅር ስንት ደም ሲያፈስ እንደኖረ ለማንም የተሰወረ አይደለም:: ምድርንና ከሰማይ በታች ያሉ ፍጥረታትን ግዛ ቢባል እግዚብሔርን መሆንን ተመኝቷልና::

ሥልጣን ለብዙዎች ከተሰቀሉባት በቀላሉ የማይወርዱባት ናት:: በዓለም ላይ አንዱ ከተሰቀሉባት በፈቃድ የማይወርዱባት እንደ ሥልጣን አስቸጋሪ ምን ነገር ይኖራልስ?

ለጊዜው ላረጋጋ ነው እንጂ ሥልጣን የመያዝ ዐላማ የለኝም ተብሎ የተጀመረ ሥልጣን እንዴት ባለ ሁኔታ እንደተናቀቀ የሚታወቅ ነው:: አገር አረጋግታችኋል ወደ ወታደርነት ሙያችሁ ተመለሱ፤ ወደ

ካንፓችሁ ተከተቱ የሚል ሁሉ በሞት የተፈጀው የሥልጣን ፍቅር አደገኛ ስለሆነ ነው::

4ኛ. ሥልጣን እንደ ወራጅ ወንዝ ነው፡፡ በልኩ ሲፈስ እንደሚያምር ሁሉ ሞልቶ ሲፈስ ደግሞ ያገኘውን ሁሉ ይጠራርጋል:: የሥልጣን ፍቅር ሲጠናወት ለልጅ፣ ለወንድም፣ ለእኅት፣ ለእናትም ይሁን ለአባት የሚራራ ልብ እንኳ ይጠፋል:: በዓለም ታሪክ በሥልጣን ፍቅር የተነሣ በየዘመኑ እንዲህ ዐይነት መጠፋፋት ምን ያህል ተክስቷል? በእኛ አገርም በቅርብ ቤተሰብ ሳይቀር ለስልጣን ሲባል አንዱ ሌላውን ሲያሳድድ የሚታይባቸው ታሪኮች በዛ ያሉ ናቸው::

ለክፉ መሪዎች ደግሞ የሥልጣን ፍቅር እንደ ሄሮድስ ሕፃናትን እንኳ በግፍ ያስፈጃል:: ሄሮድስ ክርስቶስ መወለዱን በሰማ ጊዜ በሥጋዊ መንገድ ስላሰበው ክርስቶስ አድጎ ሥልጣኔን ይነጥቀኛል ከሚል እጅግ ደነገጠ:: በእርሱ መደንገጥ ምክንያትም መላዋ ኢየሩሳሌም ታወከች:: በኋላም ክርስቶስን ሊገድለው ፈልጎ እንዳልሆነለት ባወቀ ጊዜ በቤተ ልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን፣ ሁለት ዓመት የሆናቸውንና ከዚያም የሚያንሱትን ሕፃናት ሁሉ እንዳስፈጃቸው በወንጌል ተመዝግቧል:: የሥልጣን ፍቅር እስከዚህ ያደርሳል የሚለውን ሊያሳየንም ነው በቅዱስ መጽሐፍ መመዝገቡ:: (ማቴ. 2፥16)

5ኛ. ሥልጣን እያደር ይጥማል:: ክፉ መሪዎች ሥልጣናቸውን ለማራዘም ምንም ከማደረግ ወደ ኋላ እንደማይሉም በዓለም ታሪክ ተደጋግሞ የታየ እውነት ነው:: በሥልጣን ፍቅር የታወረ ክፉ መሪ ከሞት አፋፍ እንኳ ሆኖ መሸነፉን አያውቅም:: ብዙውን ጊዜ ተገፍተውና ተዋርደው ከሥልጣን የሚወርዱ መሪዎች ምነው በክብርና በሥርዓት በፈቃዳቸው ሥልጣን ለቀው ፍጻሜያቸውን ማሳመር ሲችሉ መዋረድን መረጡ? የሚለው ሲጠየቅ፤ ክፉ መሪ እየወደቀ አወዳደቁን እንኳ መረዳት እስኪሳነው ሥልጣንን ለማቆየት ምን ያህል ልቡ እንደሚደነድን የሚያሳይ ነው::

የሥልጣን ፍቅር ዕድሜም አይግደበውም:: በአፍሪካም በሌላውም ዓለምሥልጣን እስከ መቃብር የሆነባቸውን መሪዎች ባለንበት ዘመን እንኳ ስንቱን እያየን ነው:: በሥልጣን ለመቆየት የማይፈነቀል ድንጋይ የማይወጣ ተራራ የማይፈጠር ሰበብ አይኖርም:: የጀመርኩት ሰፊ እቅድ አለኝ የምጨርስበት ጊዜ ሊሰጠኝ ይገባል፡፡ ፓርቲዬ አትውረድብን እንዳንተ ያለ ሰው ማግኘት አንችልም ስለተባልኩ እንጂ መልቀቅ ፈልጌ ነበር:: ሌላ ጊዜም አንተ ከሌለህ አገር ይፈርሳል፤ ያላንተ እንጫረሳለን ስለተባልኩ እንጂ መልቀቅ ፈልጌ ነበር የሚል ሰበብ ይደረደራል:: መጠኑ ይለያይ ይሆናል እንጂ ችግሩ ሁሉም ጋር ነው:: በእድርም ይሁን በእምነት ተቋማት፣ በበጎ አድራጎት ድርጀት ወይም በንግዱም ዓለም፣ ሥልጣን ከወጡ መውረድ ከባድ ነገር ነው::

ቅዱስ መጽሐፍ የሚያስተምረን ግን ሌላ ነው:: ነቢዩ ሙሴን ያህል ሰው እንኳ የጀመረውን አልጨረሰም:: የተስፋይቱ ምድርን በሩቅ አያት እንጂ አልገባባትም:: የናቡ ተራራን ሞአብን መሻገር አልቻለም:: እግዚአብሔር የሰው ድሀ አይደለምና ሁሉም ሥራ በአንድ ሰው አይወሰንም:: ዮርዳኖስን ማሻገር ኢያሪኮን ማፍረስ፣ የተስፋይቱን ምድር ማውረስ ተራው የኢያሱ ነበርና:: (ዘዳ 34) የዚህም ዓለም ጉዞ የቅብብሎሽ ሩጫ ነው:: አንዱ ይጀምረዋል ሌላው ይቀበልና የራሱን ድርሻ ሠርቶ ለቀጣዩ ያስተላልፋል፤ ሌላው ይጨርሰዋል::

6ኛ. *ሥልጣን ያባልጋል:: ያልተገደበ ሥልጣን በሥልጣን መባለግንም* ያመጣል:: በተለይ የተጠያቂነት ሥርዓትና ባህል ባልዳበረበት ሁኔታ የሠሩትን ሠርቶ ማምለጥ እንደሚቻል ስለሚታሰብ ሥልጣን ያባልጋል:: በሥልጣን መከራረም ሲመጣ በሥልጣን የመባለግ እድልም መጨመሩ የሚጠበቅ ነው:: አብርሃም ሊንከን “አንድን ሰው ትክክለኛ ማንነቱን ልትፈትነው ከፈለግህ ሥልጣን ስጠው”[51] እንዳሉት የሰው ትክክለኛ ማንነቱም ሥልጣን ሲይዝ ይለያል:: ትሑት የሚመስለው ሰው ሥልጣን ላይ ሲወጣ መታበይ ይጀምራል:: ያዳምጥ የነበረ ጆሮውን ይደፍናል::፡

[51] Nearly all men can stand adversity, but if you want to test a man’s character, give him power.” Abrham Lincolin

ለድሀ ያዝን የነበረ ድሀ ማየትን ይጠላል። ለፍትሕ ሚች ነኝ ሲል የነበረው ለገንዘብ ሚች ሆኖ ያርፈዋል። መሪው እውነተኛ ማንነቱ ቀደሞውንም ቢሆን እንዲህ ነበረ ወይስ በሥልጣን በመታለሉ ነው ጠባዩ የተቀየረ? የሚለው ቢጠየቀም መልሱ አንዱ ወይም ሌላው ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ ግን ሥልጣን የሰውን እውነተኛ ማንነት የመግለጥ ኃይል አለው።

በሥልጣን መባለግን ሊያሳይ የሚችል አንድ ታሪክ ከቅዱስ መጽሐፍ ማንሳትም ጠቃሚ ይሆናል። ዳዊት በንግሥናው ጊዜ "ሰማይ አይታረስ ንጉሥ አይከሰስ" እንደሚባለው ከሳሽ አልነበረውምና ከጦር ጀኔራሉ ከኦርዮ ሚስት ከቤርሳቤህ ጋር ተኛ። ብዙውን ጊዜ አንድን ክፉ ሥራ በሌላ ክፉ ሥራ መሸፈን የተለመደ ነውና ይህን በደል ለመሸፈንም ሥልጣኑን በመጠቀም ኦርዮን በጦር ሜዳ በአሻጥር አስገደሎ ሚስቱ ቤርሳቤህን አገባት። የታማኝ ጀኔራሉን አንድ ሚስት በግፍ መንጠቅ ሳይበቃው ኦርዮን በግፍና በአሻጥር ለማስገደል የሠራው ሴራና በጦርነት እንደሞተ አስመስሎ ያሰነገረው የሐሰት ወሬ ዳዊትን ከመሰለ የእግዚአብሔር ሰው የሚጠበቅ ባይሆንም ሥልጣን ግን ወደዚህ ዐይነት ክፉ ድርጊት የማድረስ ዓቅም አለው። ዛሬ ብዙ መሪዎች ሥልጣናቸውን ያላግባብ በመጠቀም እንዲህ ዐይነት ተግባር መፈጸም በዓለም ዙሪያ የየዕለት ዜና ሆኗል። ዳዊት በሥልጣኑ ጠያቂ ባይኖረውም ለድሆች የሚፈርድ እግዚአብሔር ግን ዝም አላለም። ዳዊትን እጅግ በሚያሳዝን በልጁ ሞት ቀጣው እንጂ። ብልህ መሪ በማን አለብኝነት ሥልጣንን መጠቀም ቢችል እንኳ ሊዘገይ ይችላል እንጂ ዋጋ ማስከፍሉ እንደመይቀር ግን የዳዊት ሕይወት አስተማሪ ነው። (2ኛሳሙ. 11)

8.2 ሥልጣንን ማካፈል

ለዘመናት ሊፈቱ ካልቻሉ ቋጠሮዎች መካከል የሥልጣን በተወሰኑ ሰዎች መከማቸት በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። ብዙ ሰበብ ቢቀርብለትም የብዙዎቹ ግጭቶች ምክንያት የሥልጣንና የሃብት ክፍፍል መሆኑም ብዙም የሚያከራክር አይደለም። ኢፍትሐዊ የሥልጣን ክፍፍል፣

ከኢፍትሐዊ የሃብት ክፍፍል ጋር ሲያያዝ ላለመግባባቶችና እርስ በርስ ለሚፈጠሩ ግጭቶች እንደ ዋና ምክንያት የሚጠቀስ ነው:: የሕግ የበላይነት ባልሰፈነባቸው አገሮች መሪዎች ቢቀያየሩም፣ ሥርዓት ቢለዋወጥም፣ ዘመን ከዘመን ቢሸጋገርም ሥልጣን በተወሰኑ ሰዎች ዙሪያ የመከማቸት ባህል ግን መልኩን ይቀያይር እንጂ አልተቀየረም:: የችግሩ ምንጭም ከስግብግበትና ራስ ወዳድነት በተጨማሪ ለሥልጣን ያለ አመለካከት ሊቀየር አለመቻሉ ሊሆን ይችላል::

ይህንን ጉዳይ የሚያሳይ በመጽሐፍ ቅዱስ የተመዘገበ ታሪክ ማንሳቱ ነገሩን በጥልቀት ለማዬት ይጠቅማል:: ዮቶር በሲና በርሀ ሕዝቡን እንዴት ሊመራ እንደሚገባው ለሙሴ የነገረው ምክር ሥልጣን ማካፈልን በተመለከተ ብዙ ቁም ነገሮችን ያስተምረናል::

1ኛ. በተዋረድ ሥልጣንን ከማካፈል ይልቅ ሁሉን "እሳቸው ካላወቁት" የሚባሉ መሪዎችን ማየት እንግዳ ነገር አይደለም:: ይህ ችግር በየደረጃው ሊያጋጥም ይችላል:: ምክትል ለይስሙላ የሚሆንበት፣ ሁሉም ነገር በአንድ ሰው መዳፍ የሚወድቅበት፣ ሙሉ ተቋም የአንድ ሰው የሚመስልበት ጊዜም ብዙ ነው:: ችግሩ ተቋማዊ አሠራር ባልዳበረበት ሁኔታ አብዝቶ የሚከሠት ሲሆን ከመሪዎች ቅንነት ጋር የተቆራኘ ሊሆንም ይችላል::

በጊዜው ዮቶርን የገጠመው የሙሴ ታሪክ ተመሳሳይ ነው:: ምክንያቱ የተለየ ቢሆንም ሥልጣንን ካለማካፈል ወይም ሥራን ወደታች ማውረድ ካለመቻል የተነሣ ሥራ ሲበደል አስተዋለ:: "እንዲህም ሆነ፣ በነጋው ሙሴ በሕዝቡ ሊፈርድ ተቀመጠ፡፡ ሕዝቡም በሙሴ ፊት ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ ቆመው ነበር፡፡ የሙሴም አማት በሕዝቡ ያደረገውን ሁሉ ባየ ጊዜ፣ ይህ በሕዝቡ የምታደርገው ምንድር ነው? ሕዝቡ ሁሉ ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ በዙሪያህ ቆመው ሳሉ አንተ ብቻህን ስለ ምን ተቀምጠሃል? ... አንተ የምታደርገው ይህ ነገር መልካም አይደለም:: ይህ ነገር ይከብድብሃልና አንተ ከአንተም ጋር ያለው ሕዝብ ትደክማላችሁ፣ አንተ ብቻህን ልታደርገው አትችልም፡፡" ሲል ዮቶር ሙሴን እንደጠየቀውና ይህንን ችግር የሚቃለልበትን ምክር እንደመከረው ተመዝግቧል:: (ዘጸ. 18፥13-26) ታላቁ መሪ ሙሴም ትሑት ልብ አለውና

እኔን የመሰለ ሰው ማን ሊመክረኝ ይችላል ብሎ ሳይታበይ ምክሩን በደስታ ተቀበለው:: ቅንነት ሲኖር እንዲህ ነው:: ለዘመናዊው የሥራ አመራር መሠረቱ ይህ እንደሆነም ይታመናል::

ወዶ ፈቅዶ ሥልጣንን ማካፈል፣ ወዶ ፈቅዶ ሥራ ማጋራት (delegation) ምን ማለት እንደሆነ የሚያሳይ ታሪክ ነው:: ሥልጣንን ወዶ ፈቅዶ ማጋራት፣ ሥራን በየደረጃው ማከፋፈልና መሪዎች በየደረጃው የሚገባቸውን ሥራ ብቻ እንዲሠሩ ማድረግ ቀላል ቢመስልም በተግባር ግን ብዙዎቹ የሚፈተኑበት ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል:: የሥልጣን ፍቅሩ የሚያይልበት ሰው ሥልጣንን ላለማካፈል የሚያቀርበው ምክንያት ብዙ ነው:: ብቁ ሰው የለም ከሚለው ጀምሮ፣ የሥራው ጥራት ይጓደላል፣ ከታች ያሉ ሰዎች በቂ ችሎታ የላቸውም፣ ወይም ሙሉ ሓላፊነትን ለመውሰድ የሚችሉ ሰዎች አይደሉም የሚለው ሁሉ ይቀርባል:: መሪዎችን ብቁ ማድረግ ከላይ ያሉ መሪዎች ሓላፊነት መሆኑን የሚዘነጉት ይመስላል:: እኔው ራሴ ብሠራው ይቀለኛል ማለትን የሚያበዛ ሰውም አለ:: ከራሱ በቀር የሌላው ሰው ሥራ የማይጥመውም አለ:: ሥልጣን ማካፈል፥ ሥራን ለበታቾቹ ማውረድ ከሥራዬ ቢያፈናቅለኝስ በሚል እንደ ትልቅ ሥጋት አርጎ የሚያዬው ቁጥሩ ቀላል ላይሆን ይችላል:: ሥራውን ሌላ ሰው ሲይዘው የተደበቀ ስንፍና ይጋለጥብኛል፥ ትጉህ ሰው ካለ የእኔን ድክመት ያሳጣል የሚል ስጋትም የተለመደ ነው:: ሥራ በማካፈል የበለጠ ውጤታማም፥ የበለጠ ስኬታማም መሆን እንደሚቻል ያለው ግንዛቤ አናሳ ከመሆኑ የተነሳ የሚመጣ ችግርም ነው:: የትኛውን ሥራ መሥራት የትኛውን ደግሞ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ እንደሚገባ በአግባቡ ማወቅም እንዲሁ ቀላል አይደለም::

ዮቶር ለሙሴ እንዳለው ሥራን በየደረጃው ለሌሎች ማውረድ ሸክምን ማቃለል ነው:: የትኛውም መሪ ከዓቅም በላይ ሊሸከም ቢፈልግ እንኳ ሸክሙ ከበዛ መሪው ከተሸከመው ሓላፊነት ጋር መውደቁና ጉዳቱ የባሰ ሊሆን እንደሚችል በብዙ መሪዎች ሕይወት ያታዬ እውነት ነው:: አንድ ሰው ሁሉንም ሊሆን አይችልምና:: ሙሴ ብቻውን ሊሠራው የሚችልና የሚገባ ለሌላ የማይሰጥ ሓላፊነት እንደነበረ ሁሉ ማንኛውም መሪ እንደ

ደረጃው ለሌላ ማስተላለፍ የማይቻል ሓላፊነት ይኖራል:: ከዚያ በተረፈ ግን ሥራን ለሠሪው ማሸከም ካልተቻለ ሥራውም ይበደላል፣ መሪውም ያለጊዜው ከጥቅም ውጭ ይሆናል:: ጊዜያቸውን በአግባቡ በመጠቀም የሚታወቁና ስኬታማ የሚባሉ መሪዎችም አንዱ ትልቁ ችሎታቸው ሓላፊነትን ለበታቾቻቸው በአግባቡ ማውረድ መቻላቸው ነው::[52] እንዲህ ሲያደርጉ ተተኪ መሪዎችን በብቃት ማፍራትም ያስችላቸዋል:: ሥራን ወደ ታች በማውረድ ረገድ ምን ዐይነት መሪ ነኝ? የሚለውን ለመፈተሽ አንድ ጥያቄን ራስን መጠዬቅ ይበቃል:: እኔ በሥራ ገበታ ባልገኝ ምን ያህል ክፍተት ሊፈጠር ይችላል? እንዲሁም ሓላፊነቱን የተረከቡት ሰዎች ሥራውን ያለምንም ክፍተት ሊሰሩት ይቻላሉ ወይ? ለሚለው ጥያቄ የሚገኘው መልስ ያለውን ክፍተት ሊያሳየን ይችላል::

2ኛ. ሰው የሚሾመው በምን መስፈርት ነው? ጥሩ መስፈርትስ የሚባለው የቱ ነው? ለሚለው ጥያቄም የዮቶር ምክር በዚህ ችግር ለሚታመስ ሁሉ ትልቅ ትምህርትን ይሰጣል:: በዚሁ ምዕራፍ እንደተመዘገበው "አንተም ከሕዝቡ ሁሉ አዋቂዎችን እግዚአብሔርን የሚፈሩትን የታመኑ የግፍንም ረብ የሚጠሉትን ሰዎች ምረጥ" ሲል ሙሴን መከረው:: ለሰዎች ሹመት የዮቶር መስፈርት ጎሳ ወይም ታማኝነት አልነበረም:: የነገድ ውክልናም አላስፈለገም:: በዚያን ወቅት በነበረው የነገድ አደረጃጀት ለሥልጣን ክፍፍል ነገድ መስፈርት ሆኖ አለመቅረቡና ይልቁንም ችሎታን እና ግብረ ገብነትን ማዕከል ያደረገ መሆኑ የሚደንቅ ነገር ነው:: የቀረቡት ዛሬም ድረስ ተፈላጊ የሆኑ አራት መስፈርቶች ናቸው:: ከበጎ ምግባር ቅንነትና እግዚአብሔርን መፍራት ጋር የዮቶር መስፈርት ብቃት ብቻ ነበረ::

ሰው የሚሾመው በምን መስፈርት ነው? ጥሩውስ መስፈርት ምንድን ነው? የሚለው አሁን እንደምናየው ከሥልጣን ክፍፍል ጋር በተያያዘ የቆዬና አሁንም የእኛን አገር ጨምሮ በተወሰኑ አገሮች ዋነኛ ችግርና

[52] "If you want to do a few small things right, do them yourself. If you want to do great things and make a big impact, learn to delegate." John C. Maxwell, author of *Developing the Leaders Around You*.

የግጭት ምንጭ ሆኖ የቀጠለ ነው:: ከችሎታ ይልቅ ታማኝነት የፖለቲካ አመለካከትና ጎሳ ወይም ዘር ቅድሚያ ይሰጠዋል:: ሥልጣን በቤተሰብ ይያዛል:: ከዚህ የሚከፋው ደግሞ ሥልጣን በጎሳ ወይም ዘር ሲሆን ነው:: ሹመት ከችሎታ ይልቅ በጎሳ ሲሆን በተራ ቢሆንም እንኳ የእኛ ወገን ሳይሾምልን ተበድለናል አድሎዎ ተደርጎብናል የሚለው ልቅሶ መቼም ሊቆም አይችልም:: ዘሩና ሃይማኖቱ ምንም ይሁን ምን ብቃት ያለው ሰው ይሾምልን ማለት ሲቻል ውጤታማ ሥራን መሥራት ይቻላል:: ተያይዞ ማደግ ይቻላል:: ከእኔ ወገን ሲባል ግን ባለፉት ዓመታት እንደታየው እንኳን ለአገር የእኔ ላለው ወገን እንኳ ሊጠቅም አይችልም:: ቢጠቅም እንኳ በዙሪያው ካለው ከጥቂቶቹ የማያልፍ ይሆናል:: ቀድሞውኑ ብቃት የለውምና ከሚያለማው ጥፋቱ ሊብስ ይችላልም:: ወገኔ በሚለው ሕዝብ ሽፋን ተደብቆ የሚዘርፍና የሚበድል እንደሚሆንም በተደጋጋሚ የታዬ ስለሆነ የሚያከራክር አይሆንም:: ሥልጣን በኮታ ሲሆን ሥራ እንዴት እንደሚበደል አሁን ምን ተጨማሪ ማስረጃ ያስፈልጋልስ?

ሥልጣን በችሎታ ከሚሰጠው ይልቅ በፖለቲካ ወገንተኝነት ወይም ለተወሰኑ መሪዎች ባለው ታማኝነት የሚሰጠው የሚበዛው በዚሁ የቅንነት መጉደል ምክንያት ነው:: በሥልጣን አካባቢ "ሳይጠሯቸው አቤት ሳይልኳቸው ወዴት" የሚሉ ሰዎችን ካልሆነ ይገዳደረኛል ተብሎ የሚታሰብ፣ ለእውነት የሚያደላ ሐቀኛ የሚባል ሰውን ማቅረብ ላለመለዱም የዚሁ ልማድ ውጤት ሊሆን ይችላል::

በአሁኑ ጊዜ እንዲህ ዐይነቱ አሳብ ለምን ያህል ሰው ይዋጥለታል? ነው እንጂ፤ ማን ነው የተሻለ ዓቅም ያለው? ማንም ይሁን ማን ኢትዮጵያዊ እስከሆነ ለአገር የሚጠቅመውን ሥራ በተሻለ ብቃት ሊሠራልን ማን ይችላል? (merit system[53]) ወደሚለው አስተሳሰብ መምጣት እስኪቻል የተሻሉ ተቋማትን የተሻለ አገርን እንዴት ማየት ይቻላል? ሹመቱን የእነ እገሌ ወገን በብዛት ያዘው እኛ ተጎድተናል የሚል የኮታ ልማድ

[53] Merit system -a system by which appointments and promotions in the civil service are based on competence rather than political favoritism, https://www.merriam-webster.com/dictionary/merit%20system

ብዙም እርቀት እንደማይወስደን ያለፉት ዓመታት ምስክሮች ናቸው::

አንድ ሰው ለሓላፊነት ሲታጭ በብዙ አገሮች የሚደረገው ይህ ሰው ለሥራው ብቁ ነው ወይ? ለሥራው ይመጥናል ወይ? የሚለው በምንም ድርድር ውስጥ አይገባም:: ለሓላፊነት ቦታው ብቁ ያልሆነ ሰው በታማኝነቱ ወይም በታዛዥነቱ ብቻ የመሾም ሙከራ ቢደረግ እንኳ አውጭው አካል፣ ሚዲያዎች ይጮኻሉ ማስረጃ ያቀርባሉ:: ሕግ አውጭውም ውድቅ ያደርገዋል:: የፖለቲካ ታማኝነት እንደ ዋና መለኪያ ቢወሰድ እንኳ ለሥራው ብቁ ካልሆኑ ለሹመት መቅረብ አይታሰብም:: በሁሉም መለኪያ አሉ ከሚባሉ ሰዎች የተሻለ ነው የሚባለውን ሰው ማስቀደም ድርድር የሚገባ አይደለም:: በአደጉ አገሮች ከፓርቲ ወገንተኝነት ይልቅ ችሎታ ቅድሚያ ሲሰጠው ይታያል:: መሪዎች ችሎታ እስካላቸው ድረስ ተፎካካሪያቸውን እንኳ ትልቅ ሹመትን ሲሾሙ ማየትም እንግዳ ነገር አይደለም:: እስከታዘዘ፣ ፖለቲካውን እስካስፈጸመ ድረስ ማንም ይሁን ማን የሚል ባህል አገር ያጠፋል የሚለውን ተረድተውታል:: በእኛ ዘንድ ሥራውና መሪው የማይተዋወቁበት ስንት ሹመቶችን ስናይ ኖረናል? ያለፈው አልፏል በጎ ተሞክሮ ካላቸው አገሮች መማር የምንችለውስ መቼ ይሆን? የሚለው ነው አሁንም ሊያሳስብ የሚገባው:: በመንግሥት ተቋማት ብቻ የሚታይ ችግር አለመሆኑ ይልቁንም ከእምነት ተቋማት ጀምሮ ከትንሽ እስከ ትልቅ ተቋም ችግሩ መኖሩም እንዲህ ካለው አዙሪት እንዴት ይሆን መውጣት የሚቻለው? የሚለውን የበለጠ አሳሳቢ ማድረጉም አይቀርም::

3ኛ. ሌላው ጉዳይ የሥልጣን ተዋረድና አደረጃጀት ምን መምሰል እንደሚገባውም ዛሬም በሰፊው የሚሠራበት የዮቶር አሳብ እንደሆነም በሚከተለው መረዳት ይቻላል:: “አንተ በእግዚአብሔር ፊት ለሕዝቡ ሁን:: ነገራቸውንም ወደ እግዚአብሔር አድርስ፤ ሥርዓቱንም ሕጉንም አስተምራቸው:: የሚሄዱበትን መንገድ የሚያደርጉትንም ሥራ ሁሉ አሳያቸው:: የሺህ አለቆችን የመቶ አለቆችን የሃምሳ አለቆችን የአሥርም አለቆችን ሹምላቸው:: በሕዝቡ ላይ ሁልጊዜ ይፍረዱ፣ አውራውን ነገር ሁሉ ወደ አንተ ያምጡት ታናሹንም ነገር ሁሉ እነርሱ ይፍረዱ” ሲል

ዮቶር ሥልጣንን እና ሓላፊነትን ወደታች ማውረድ እንዴት እንደሚገባም ነበር ሙሴን የመከረው:: (ዘጸ. 18፥19-22)

ምን ዐይነት ሥራ ማውረድ ይቻላል? ምን ዐይነት ሥራ በየትኛው የሥራ ሓላፊ መያዝ አለበት? የሥልጣን እዝ ሰንሰለትስ ምን መሆን አለበት? የሚለው ችግር የሚሆነው የአሥር አለቃው የሺህ አለቃውን ሥራ ሲሠራ፣ መሪ የሚገባውን ሥራ ትቶ በሁሉም ነገር ያገባኛል ሲል፣ መሪ ሥራ መምረጥ ሲገባው ትንሹን ትልቁንም ጉዳይ እኔ ከሌለሁበት፣ እኔ ካላወቁሁት ሲል ነው::

እንዲህ ዐይነቱ ችግርም በሰፊው የሚታይ ነው:: ማንን ነው የምናናግረው? ወሳኙ አካል ማን ነው? የሚባልበት ጊዜ ብዙ ነውና:: ይህ ነው የሚባል መደበኛ ሥልጣን ሳይኖራቸው ሁሉንም ሠሪ አድራጊ የነበሩ ሰዎች ይታዩ የነበሩበት ዘመንም ሩቅ አይደለም:: ሥልጣን ቢከፋፈል እንኳ ለማስመስል ያህል ለይስሙላ ነው እንጂ ነገሩ ሁሉ ቅን መንፈስና ቅን ልቦና የጎደለው የማታለል ሥራ ነው የሚያሰኙ ብዙ ምልክቶችን ማየት የተለመደ ነው:: ለዚህም ወንበሩ ላይ ተቀመጡ እንጂ ሥልጣኑ ያለው በተወሰኑ ሰዎች እጅ ነው፤ እነርሱ ሳያውቁ እንኳን ትልልቅ ጉዳይ ትናንሽ የሚባሉ ጉዳዮችን ለመወሰን መሞከር ከንቱ ድካም ነው የሚባልበት ጊዜም አለ፡፡ የቀበሌ ጉዳይ ቢሆን እንኳ ከላይ ከአናቱ ያሉት መሪዎች ሳያውቁት ምንም ነገር ማድረግ የማይታሰብበት ጊዜም እንደነበረ ነው የሚነገረው:: ይህ ነገር እንደተባለው ከአንዱ ዘመን ሌላው ቢሻልም የከራረመ ችግር ነው::

በተመሳሳይ በየደረጃው ያሉ መሪዎች ሥልጣንና ሓላፊነት በቅጡ የማይታወቅ ከሆነ ወንበሩ ላይ የተቀመጠው ባለሥልጣን ወንበሩን የያዘው ለይስሙላና ወንበር ለማሞቅ እንጂ ሥልጣኑ ያለው ወንበሩ ላይ ባልተቀመጠና ከመዋቅር ውጭ በሆነ ስውር እጅ ሲሆን ሥራ ይበላሻል:: ሓላፊነቱ የተሰጠው ሹም የተሰጠውን ሓላፊነት በአግባቡ ሊጠቀምበት የማይችል ደካማ መሪ ሆኖ ሥልጣኑ በስውር እጅ ያለ ከሆነም የአመራር ምስቅልቅል መፈጠሩ የሚጠበቅ ነው:: አሥር አለቃው የሺህ አለቃውን

ሥራ ልሥራ የሚል ከሆነም የእዝ ሰንሰለቱ ይበጠሳል። ሰንሰለት ከተበጠሰ ደግሞ ምንም ዓቅም ሊኖረው አይችልም። ደካማ የተቋም አደረጃጀት በሚኖር ጊዜ ከሚከሠተው ችግር አንዱም ይህ ዐይነቱ ነው።

8.3 የእግዚአብሔርን ከእግዚአብሔር የቄሳርን ከቄሳር

አገልጋይ መሪ የእግዚአብሔርን ከቄሳር ለይቶ የሚያውቅ ነው። ከሥልጣን ጋር ተያይዞ በተደጋጋሚ ከሚከሠቱ ችግሮች መካከል የፖለቲካ በሃይማኖት ጣልቃ ገብነት፣ የሃይማኖት በፖለቲካ ጣልቃ ገብነት እንዲሁም የሃይማኖትና የፖለቲካ መደበላለቅ ቀላል የማይባል አስተዋጽዖ ያደርጋሉና። በአንድም በሌላም ለፖለቲካ ዐላማ መጠቀሚያ የሃይማኖት ተቋማትንና መሪዎቹን መቆጣጠር በብዙ ዐላማት እስካሁን ድረስ የሚታይ የተለመደ ችግር ነው። በኢትዮጵያም ለረጅም ዘመናት ከሚስተዋሉ ችግሮች የመንግሥት በሃይማኖት ተቋማት ጣልቃ ገብነት፤ የሃይማኖት በፖለቲካ ጣልቃ ገብነት በዐብይነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። በመንግሥትና በሃይማኖት መካከል ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ በነበረው ግንኙነት የታየውን አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ አስተዋጽዖ በገለልተኛነት የሚያጠናው ቢገኝ ለመጭው ትውልድ ለመማሪያነት የሚያገለግል ራሱን የቻለ መጽሐፍ ሊወጣው እንደሚችል ማሰብም ይቻላል።

አደጉ በሚባሉ አገሮች ችግሩ አሁን አሁን እምብዛም የማይታይ ቢሆንም በእኛ ዘንድ ችግሩ እንደቀጠለ ቆይቷል። ቀደም ሲል የነበረው የመንግሥትና የሃይማኖት ግንኙነት መልኩን በተወሰነ ሁኔታ ቢቀያየርም መንግሥታት በሃይማኖት ተቋማት የነበራቸው እጅ ረጅም ሆኖ እንደ ቀጠለ የሚታወቅ ነው። እንዲህ ዐይነት ችግር የሚፈጠረው ሥልጣንን ጠቅልሎ ለመያዝ ከሚደረግ ጥረት ሲሆን ይህን ደግሞ አገልግሎትን በመረዳት ረገድ ያለው ክፍተት የሚያመጣው ነው ለማለት ይቻላል።

ችግሩ ከሁለቱም ወገን የሚመጣ ነው:: የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማራመድ ሃይማኖትን እንደሸፋን መጠቀም የሚሞክሩ የሃይማኖት መሪዎችም በየዘመኑ አልጠፉም:: እውነተኛ የሃይማኖቱ መሪዎች ሳይሆኑ በስም ብቻ እየተመላለሱ ሀብትን ለማጋበስ የሚጠቀሙበት ሰዎችን ማየትም አዲስ ክሥተት አይደለም:: እንዲህ ዐይነት ሰዎች ሁለት ዐይነት ማንነት ተላብሰው የሚኖሩ ናቸው:: ሲያሻቸው ሃይማኖተኛ ይመስላሉ ሲፈልጉት ደግሞ ፖለቲከኛ ይሆናሉ:: ለእነዚህ ሰዎች ሃይማኖት መንግሥተ ሰማያትን መውረሻ ሳይሆን ለምድራዊ ሥልጣን እና ሀብት እንደ መሸጋገሪያ ወይም መሰላልነት ነው የሚያገለግለው:: ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ ተስፋፍቶ የሚገኘው ችግር እንዲህ ዐይነቱ ነው:: በተለይ በአንዳዶቹ ዘንድ ችግሩ በስፋት አደባባይ አልወጣም እንጂ ያለው ሌብነት፣ ዝርፊያ፣ ሙስናው፣ ሥልጣንን በዘመድ አዝማድ መያዝን ጨምሮ የመልካም አስተዳደር እጦቱ ሥር የሰደደ እንደሆነ ነው የሚነገረው:: አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለው ደግሞ እንዲህ ዐይነት የሃይማኖት መሪዎች መኖራቸው ነው::

የሃይማኖት መሪዎችም ሓላፊነቱን ያገኙት ለቦታው ብቁ ሆነው ሳይሆን በፖለቲካ ታማኝነታቸው ተለክቶ ከሆነ ሓላፊነታቸውን በአግባቡ ለመምራት ይቸገራሉ:: እንዲህ ባለ ሁኔታ ያለ ነቀፋ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የሚያገለግሉ ከመሆን ይልቅ አደርባይነት ሊያጠቃቸው ይችላል:: በዚህ ጊዜ የእምነቱ ተከታዮች በሃይማኖት መሪዎቻቸው ላይ አመኔታ ያጣሉ:: በእምነታቸው ይዳከማሉ:: በሥነ ምግባር የታነጸ ዜጋን ለማፍራትም ከባድ ይሆናል:: የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የሃይማኖት መሪዎችን ብቻ ሳይሆን የአንድ እምነት ተከታዮችን ሊከፋፍልም ይችላል:: በዚህም የአገር አንድነት ይዳከማል:: በዚህ ዘመን እንዲህ ባለው የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት በሃይማኖት መሪዎች መካከል ይታይ የነበረው መከፋፈል፣ እንዲሁም በእምነቱ ተከታዮችም ዘንድ የነበረው መለያየት ምን ያህል አሳሳቢ እንደነበረ የሚያውቁት ሁሉ ያውቁታል::

የሃይማኖት መሪዎችስ ለምን እንዲህ ሆኑ? ቢባል መልሱ አሁንም አገልግሎትን በአግባቡ መረዳት አለመቻላቸው በዋና ምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችል ነው:: በተለይ እንዲህ ዐይነቱ ችግር በእምነት ሰዎች ሲከሠት በአገሪቱ አንድነትና በሰዎች መቀራረብ ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ ሰፊ ጥናትን የሚፈልግ በታሪክም ትልቅ ምዕራፍን ሊይዝ የሚችል ሊሆን ይችላል::

እንዲህ ዐይነት ችግሮችን ለመቅረፍ ብዙ አገሮች መንግሥት በፖለቲካ እንዲሁም ፖለቲካ በመንግሥት ጣልቃ እንዳይገባ በሕገ መንግሥታቸው ሳይቀር ደንግገው በተግባርም ሥራ ላይ አውለውታል:: ለምሳሌ በአሜሪካ ሕገ መንግሥት ሃይማኖትና መንግሥት የተለያዩ ናቸው[54]:: ሕግ አውጭው አካል ሃይማኖትን በተመለከተም ሕግ አያወጣም:: ሰዎች ለሹመት ሲታጩም ሃይማኖታቸው መስፈርት ውስጥ እንዳይገባም ይከለክላል:: በተመሳሳይ በኢትዮጵያም በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ሃይማኖትና መንግሥት የተለያዩ መሆናቸውን መንግሥት በሃይማኖት ሃይማኖትም በመንግሥት ጣልቃ እንዳይገባ እንዲሁም የመንግሥት ሃይማኖት እንደማይኖር መደንገጉ የሚታወቅ ነው[55]:: በተግባር በሥራ ላይ ምን ያህል ውሏል የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ ማለት ነው::

በመንግሥትና በሃይማኖት ያለውን ድንበር በአግባቡ ማስመር፣ ክፍተት ያላባቸውን ሕጎች አጥንቶና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ መልክ ማስያዝ ያለፈውን ችግር እንዳይደገም ሊያግዝ እንደሚችልም ማንም የሚስተው ባይሆንም ትኩረት ሲሰጠው ግን አይታይም:: ነገሩ እንዲህ በቀላሉ በተወሰኑ ዓረፍተ ነገሮች ሊቋጭ የሚችል ጉዳይ አይደለምና:: ዝርዝር መመሪያና አሠራር ሊበጅለት የሚያስፈልገው ሰፊ

[54] The first part of the First Amendment to the **Constitution** states: “Congress shall make no law respecting an establishment of religion, or prohibiting the free exercise thereof.”, https://constitutioncenter.org/media/files/constitution.pdf

[55] Article 11 Separation of State and Religion 1. State and religion are separate. 2. There shall be no state religion. 3. The state shall not interfere in religious matters and religion shall not interfere in state affairs. https://www.wipo.int/edocs/lexdocs/laws/en/et/et007en.pdf

ጉዳይ ሊሆን ይችላል። በየዘመኑ የታዩ ችግሮችን፣ የችግሮችን ምንጭ፣ ያደረሱትን ኪሳራ በዝርዝር የሚፈተሽበት እድል ቢኖር የችግሩን ምንጭ ለማከምና ስሕተቱ እንዳይደጋገም ሊያግዝም ይችላል።

"የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር" እንደተባለ መንግሥትም የመንግሥትነት ድርሻውን ሃይማኖትም የሃይማኖት ተልእኳቸውን ሲሠሩ መደበላለቅ አይኖርም። ሁሉም የድርሻውን መስመሩን ጠብቆ ሓላፊነቱን ሲወጣም ፈሪሃ እግዚአብሔር ይሰፍናል፤ አገር ይበለጽጋል፤ አንድነትነት ይጎለብታል፤ ሰላም ይሰፍናል፤ በረከት ይበዛል። አገልግሎትን የተረዱና "የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የቄሳርን ለቄሳር" የሚሉ መሪዎች ሲገኙ የሃይማኖት ተቋማት የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው እንዲወስኑም እድል ይሰጣል። (ማር. 12፥17) ሁሉም የራሱን ቤት ማጽዳት ስለሚያስችል ሓላፊነትንም መወጣት፤ ተጠያቂነትን ማስፈንም ያስችላል። የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት በሌለበት በሃይማኖት ሽፋን ራሳቸውን የደበቁ ሰዎችም መደበቂያ ጫካቸው ስለሚመነጠር ዕድሜያቸው አጭር ይሆናል።

የመንግሥትን ሥልጣን ለሃይማኖት ዐላማ ለማዋል በሚድረግ ጥረት አንዱ ባለሥልጣን ከተማውን መስጊድ በመስጊድ ሲያደርግ ሌላው ተረኛ ቤተክርስቲያንን ሲያስፋፋ ይታያል። መቼም ለሃይማኖት ተግባር ቢውልም እንዲህ ዐይነቱ ተግባር የተወሰኑ ሰዎችን ደስ ሊያሰኝ ይችል ይሆናል እንጂ በኢፍትሐዊ መንገድ ሥልጣንን ያላግባብ በመጠቀም ሃይማኖት ተቋማትን ተጠቃሚ ለማድረግ መሞከር ከሃይማኖት መርህ የሚጣረስ ተግባር ነው። በእንዲህ ዐይነት አድሏዊ ተግባር ፈጣሪን ማስደት ይቻላል ብሎ ማሰብ እንዴት ትርጉም ሊሰጥ ይችላልስ? ሥልጣንን ያላግባብ በመጠቀም የአንዱን እምነት ተከታዮች ለመጥቀም ሌሎችን ለማዳከም መሞከር ድርጊቱ በራሱ ኢፍትሐዊ በመሆኑ እንኳን ፍትሐዊ በሆነው አምላክ ይቅርና በሰው ፊትም ነውር ነው። የሕግ የበላይነት ባለበት ሁኔታ ደግሞ ሕግ ሊታገሳቸው ከማይገቡ ነገሮች መካከል እንዲህ ዐይነቱ ድርጊት አንዱ ነው።

ሃይማኖትን ለፖለቲካ ዐላማ ማስፈጸሚያ ማድረግ የሃይማኖት መርህን መጣሱ ብቻ አይደለም ጉዳቱ። እንዲህ ዐይነት ነገር ብዝኃነት ባለበት ዓለም ለፖለቲከኞችም አይጠቅማቸውም የሚለው ነው አሁን አሁን የሚነሣው። ጸያፍ መሆኑ ብቻም ሳይሆን ሃይማኖትን ለፖለቲካ ዐላማ ማስፈጸሚያ ተጠቅሞ አንዱን በሌላው ላይ ማስነሣት እሳቱ በቀላሉ ስለማይጠፋ በሁሉም ወገን የሚያስከትለው ጉዳት ከምንም የከፋ ነው። ይህ ዐይነቱ ደባ በብዙ የዓለም ታሪክ የታየ ቢሆንም ከዚህ ያልተማሩ ሰዎች እንዲህ ዐይነቱን ክፋት ሲጠቀሙበት አሁንም ይታያል። የፖለቲካ አጀንዳ ካለ በግልጽ በፖለቲካነቱ የሚያስፈልገውን አሳብ አፍልቆ ተከታይን ማፍራትና የሚያምኑበትን ዐላማ ማራማመድ ብቻ ነው የሚያዋጣው። "የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር" ማለት የሚያስፈልገው እንዲህ ላለው ተግባርም ነው።

በአንጻሩም መንግሥትና ሃይማኖት በመካከላቸው ግድግዳ መኖሩ አስፈላጊ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ የሚለያዩ ተቋማት ሊሆኑ እንደማይችሉ ግን የታወቀ ነው። ሃይማኖት ለመንግሥት መንግሥትም ለሃይማኖት አንዱ ለሌላው ያስፈልገዋል። የሃይማኖት ተቋማት የምድሪቱ ሕግ ይመለከታቸዋል። ሕግን ለማስፈጸም ጸጥታን ለማስፈን የመንግሥትን እርዳታም መሻታቸው አይቀርም። በውጭ ጉዳይና በመሳሰለው ግንኙነት የመንግሥትን ድጋፍ ይፈልጋሉ። መንግሥት በሚያወጣቸው ሕጎችና ፖሊሲዎችም የእምነት ተቋማት ባለድርሻ አካል የሚሆኑበት ጊዜም ቀላል የሚባል አይደለም። ነጻነት ባለባቸው አገሮች እንደሚታየው የእምነት ተቋማት የተለያዩ ሕጎች እንዲወጡ ወይም እንዳይወጡ የራሳቸውን አቋም የመግለጽ፣ የመደገፍና የመቃወም ከዚያም አልፎ የሚቻላቸውን ሁሉ ጫና የማድረግ ጉዳይም የተለመደ ነው። ለምሳሌ ስለ ቤተሰብ ሕግ፣ ስለ ሱስና የመሳሰሉ ጉዳዮች የእምነት ተቋማት ትልቅ ድርሻ አላቸውና ዝም ሊሰኙ አይገባም። የእምነት ተቋማት ሥነ ምግባርን ለማስተማር ቀዳሚ ናቸው። ከፖለቲካ ወገንተኝነት ገለልተኛ በመሆን ለሁሉም የአገር መሪዎች ሥራቸው የተሳካ እንዲሆንና ለሀገር ሰላምና ብልጽግና እንዲያመጡ ስለ ዝናቡ ስለ ነፋሱ ስለ ምድሩ ስለ አየሩም ደህንነት እንዲሁ በየእምነታቸው ይጸልያሉ። የኢትዮጵያ ነገር ሲነሣ

ደግሞ የሌሎችም የየራሳቸው አስተዋጽዖ እንዳለ ሆኖ፣ የቤተ ክርስቲያን አበርክቶ ግንባር ቀደም ነው። ፊደልን ቀርጻ ያስተማረች፣ መሪዎችን አስተምራ አሠልጥና ያበረከተች፣ የሕዝብ አስተዳደርን የመሠረተች፣ በጎ እሴቶችን ያፈራች፣ ዓለም እጹብ ድንቅ የሚላቸውን ሥነ ሕንጻ ሥነ ሥዕልና ሥነ ጽሑፍንና የመሳሰለውን የሥልጣኔ አሻራን ለአገርና ለሕዝብ ያስረከበች ቤተክርስቲያን ባለችበት አገር የሃይማኖት ተቋማት አስተዋጽዖ ከሌሎች ዓለማት በተለየ ሁኔታ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ የሚካድ አይደለም።

የሃይማኖት ተቋማት በሌሎች አገሮች እንደሚታየው ከዚህም ባለፈ አገርን ሊያለሙና መንግሥትን ሊያግዙ እንደሚገባም የሚጠበቅ ነው። የእምነት ተቋማት ፍትሕን፣ ቅንነትን፣ ታማኝነትን ጉቦ መጸየፍን፣ መቻቻልን፣ እርቅን፣ ጥላቻና በቀልን ማስወገድን ለማስተማር ቀዳሚ ተቋማት ሊሆኑ በተገባ ነበር። ድህነት ትልቅ ችግር በሆነበት አገር የእምነት ተቋማት ብዙ ልማትንም ሊሠሩ የሚችሉበትም ሰፊ እድል ይኖራቸዋል። የአደጉ አገሮችን ጨምሮ በብዙ አገሮች ትምህርት ቤቶች የሚያስፋፉት፤ የጤና፣ የምክር አገልግሎት፣ የበጎ አድራጎት ሥራዎች በሰፊው የሚሠሩት በእምነት ተቋማት ነው። የእምነቱን ተከታዮች በማስተባበር፣ሃብታቸውን በማቀናጀት፣ ከለጋሾች እርዳታንም በማሰባሰብ ጭምር፤ ትውልድን በመቅረጽ፣ ጠያቂ የሌላቸውን ድሆችንና ሕመምተኞችን በመደገፍ እና ጠንካራ ማኅበራዊ መስተጋብርን በመገንባት የእምነት ተቋማት ቢጠቀሙበት ከፍ ያለ ዓቅምም ይኖራቸዋል።

በሌላ በኩል በሃይማኖት መሪዎችና በፖለቲካ መሪዎች የሚኖር ግንኙነት መቼም ቢሆን ቀላልና ቀጥተኛ ሊሆን የሚችል አይደለም። ድንበሩም ሁልጊዜ በቀላሉ የሚሰመር በቀላሉ የሚታይ አይደለምና። የሃይማኖት መሪዎች ስለ ሰው ልጆች ከፈጣሪ ስለተሰጠ ነጻነት መጠበቅ ከተናገሩ፤ ፍትሕ ሲረገጥ፣ ሰዎች ሲገደሉ፣ ድሆች ሲበደሉ የሚጮሁ ከሆነ የፖለቲካ መሪዎችን ሊያስቆጣ ይችላል። ይህንን የመሰለ ታሪክም በቅዱስ መጽሐፍ መመዝገቡም የታወቀ ነው። ለምሳሌ መጥምቁ ዮሐንስ ሄሮድስን ባልተገባ ሥራው ቢገስጸው ሄሮድስ በክፉ ሥራው ተጸጽቶ

ንስሓ ከመግባትና ከክፉ ሥራው መመለስ ሲገባው ክፋቱን የተናገረበትን ሰው ማስወገድን እንደ መፍትሔ ወሰደ:: ዮሐንስን የጠበቀው እሥራት በኋላም ሞት ነበር:: (ማቴ. 14፥1-11) ነቢያትን ነገሥታትን ሲገስጿቸው ያሳድጿቸው እንደነበርም በቅዱስ መጽሐፍ በሰፊው የተመዘገበ ነው:: በተመሳሳይ ክፉ መሪዎች በበዙበት እውነት የሚናገር ስለ እውነት የሚቆም ሰው ብዙም አይወደድም:: እጣ ፈንታው እሥራት፣ እንግልት ወይም ሞት የሚሆንበትም ጊዜ ይበዛል::

በተለይ ክፉ መሪዎች ዘወትር ከስጋት ስለማይወጡ ገለልተኛ ተቋማትን አያምኑም:: በቻሉት መጠን ሁሉም ተቋማት በቁጥጥራቸው ሥር መሆኑን ሳያረጋግጡ እንቅልፍ አይተኙም:: ፖለቲከኞች አገር ለእነርሱ ብቻ በርስትነት የተሰጠ ይመስል ሌላውን ለማራቅና በብቸኛነት ሁሉንም ጠቅልሎ ለመቆጣጠር ከሚጠቀሙበት ዘዴ አንዱ ሃይማኖት እዚህ ምን አገባው? ይህ የፖለቲካ ጉዳይ ነው የሚል የማደናገሪያ አነጋገር ነው:: ይህ ነገሩን በደንብ ካለመረዳት ወይም "ሆድ ሲያውቅ" እንደሚባለው እያወቁ ለማታለል ከሚደረግ ጥረት የሚመጣ ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ እንኳ ለሚያስተውል ነቢያት ነገሥታትን ሲገጹ የኖሩት ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ከመመለስ በተጨማሪ ክፉ መሪዎች ሕዝቡን እንዳይበድሉ፣ ፍርድ እንዳያጓድሉ፣ ግፍ እንዳይበዛ፣ ድሀ እንዳይበደል እያሉ ጭምር ነው::

የሃይማኖት መሪዎች መንገዳቸው ብዙውን ጊዜ መስቀለኛ ሊሆን ይችላል:: ምርጫው የሞትና የሕይወት እስከመሆን የሚደርስበት ጊዜ ይኖራል:: የእግዚአብሔር አገልጋዮች ፈታኝ ምርጫ ሲገጥማቸውና ምርጫው በሰውና በእግዚአብሔር በሚሆንበት ጊዜ እንደ ቅዱሳን ሐዋርያት "ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባናል" በማለት መከራ ቢመጣ እንኳ በጸጋ ይቀበላሉ:: (የሐዋ. ሥ 5፥29) በእርግጥ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባናል የሚለው መርህ ለሃይማኖት መሪዎች ብቻ ሳይሆን ፈሪሃ እግዚአብሔር ላላቸው በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ መሪዎች ሁሉ የሚያገለግል ትልቅ መርህ ነው:: እውነትን ከመናገር ዝም በሉ ሲባል ዝም አንልም ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር፣ ከሐሰት ይልቅ ለእውነት

ልንታዘዝ ይገባናል ማለት ሲቻል ነውና እውነት ቦታ የሚኖረው። ግፍን እያዩ ዝም ማለት የሕሊና ወቀሳን ማስከተሉም አይቀርም። ሕሊና ላለው ሰው አላዬሁም አልሰማሁም ማለት ቢፈለግ እንኳ በቀላሉ የሚቻል አይደለም። ንጹሕ ሕሊና ላለው የሰውን ክቡሩነት ለሚገነዘብ፣ የሰው ልጅ ነጻነት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሀብት እንጂ በመሪዎች በጎ ፈቃድ የሚቸር አለመሆኑን ለሚረዳ ፈሪሃ እግዚአብሔር ላለው ሁሉ ግፍ ሲበዛ፣ በደል ሲበዛ፣ በሚቻለው ሁሉ መጮኹ የሚጠበቅ ነው።

አንዳንዱም የሃይማኖት ሰው መሆን ፖለቲከኛ ከመሆን ጋር የሚቃረን እንጂ አብሮ የሚሄድ አይደለም የሚል አስተያየትም ይሰማል። ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሰው የፖለቲካ ሰው ሲሆን ኃጢአት ሆኖ የሚታይበት አመለካካትም በአንዳንዶች ዘንድ የሚታይ ነው። እንዲህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ምንን መሠረት ያደረገ ነው? የሚለው መጠየቅ የሚገባው ነው። እንዲያውም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች ዓቅም ካላቸው በየደረጃው በመሪነት ቢሳተፉ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፤ ሌብነትን ለማጥፋት፤ ፍትሐዊነትን እውነትን ሥነ ምግባርን ለማስፋፋት፤ ሥልጣንን ለአገልግሎት ለመጠቀም ያስችላቸዋል። ፈሪሃ እግዚአብሔር ላለው ሰው እንዲህ ዐይነት በጎ እሴቶችን ለማስፋፋትና አርአያ ሆኖ ለመምራት ያስችለዋል እንጂ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው መሆኑ እንዴት እንቅፋት ሊሆንበት ይችላል? የሚለውን መጠየቅ ያስፈልጋል። እንዲህ ዐይነት ግብረ ገብ ሰዎች እየራቁ ቦታውን ሌሎች ከያዙት የባሰ ኪሳራ መሆኑስ እንዴት ይቀራል? እንዲያውም መታሰብ ያለበት በተቃራኒው ነው። ሃይማኖትንና ሌላውን አገልግሎት ሳይቀላቅሉ፣ ሥልጣንን ለሃይማኖት ተግባር ከማዋል ተቆጥበው ከሠሩበት ሥልጣን የማገልገያ መሳሪያ ነው።

ክፉ መሪዎች በሚበዙበት ጊዜ ራስን ደብቆ ቦታውን ሙሉ በሙሉ የፈለጉትን ያድርጉት ብሎ መተው ተባባሪ አለመሆን ማለት አይደለም። ለማስተካከል የሚቻለውን አስተዋጽዖ ማድረግ ፈሪሃ እግዚአብሔር ካለው ከማንም ሰው የሚጠበቅ ነውና። ለዚህ በቅዱስ መጽሐፍ በትንቢተ ዳንኤል ታሪክ በስፋት እንደሚያሳየው የነቢዩ ዳንኤል ሕይወት ጥሩ ምሳሌ ሊሆን

ይችላል:: ዳንኤል በባቢሎን ምርኮ ከተጋዙ ሰዎች አንዱ ነው:: ምርኮኛ ቢሆንም እግዚአብሔር ግን በተሰደደበት አገርም ከፍ ከፍ አደረገው:: ጥበብንና ሞገስን የተሰጠው ዳንኤል በናቡከደነፆር ቤተ መንግሥት ትልቅ ስፍራ ያለው ሆነ:: ናቡከደነፆር ዳንኤልን በባቢሎን አውራጃ ሁሉ ላይ ሾመው:: በባቢሎንም ጠቢባን ሁሉ ላይ ዋነኛ አለቃ አደረገው:: ክፉ ሰዎች በበዙበት፣ በተበላሸ ሥርዓት ብዙ ክፉ ሰዎች በሰለጠኑበት ቤተመንግሥት መሥራት ለዳንኤል ግን ቀላል አልነበረም:: ምርጫውም እግርን እና እጅን አጣጥፎ አላየሁም አልሰማሁም "ላመን በጤና" ብሎ መቀመጥ ወይስ በእግዚአብሔር እርዳታ የበኩሉን አስተዋጽዖ በማድረግ በእግዚአብሔር ኃይል ይህን ጨካኝ ሥርዓት እንዲስተካከል ማድረግ ነበረ:: ዳንኤል የመረጠው ሁለተኛውን ምርጫ ነበር:: በዚህም ለጊዜው ፈተና ቢበዛም የኋላ ኋላ ለውጥ ማምጣት አስችሎታል:: ዳንኤል ዓመፀኛ መሪዎችን ፈርቶም ከእምነቱ ፈቀቅ አላለም:: ይልቁንም በእምነቱ ጸንቶ የእምነቱን ታላቅነት፣ የእግዚአብሔርንም ኃያልነት በማይምኑ ገዥዎች መካከል ማስመስከር የቻለ መርህ ያለው፣ እምነቱን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ በሥራውም የሚልቅ፣ እጅግ ጥበበኛና አስተዋይ መሪ ነበረ እንጂ::

የፖለቲካ መሪዎችን መተቸት የፖለቲካ ሰው፣ ወይም የአንድ ፖለቲካ አስተሳሰብ ደጋፊ፣ የሌላው ነቃፊ ተደርጎ መታየትም የለበትም:: ፖለቲካን የሚነካ ነገር ሁሉ ፖለቲካዊ አድርጎ መውሰድም የሚያስኬድ አይደለም:: ስለ ሀገሩ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ጨምሮ በማንኛውም ጉዳይ በገለልተኝነት አስተያየት የሚያቀርብ፣ ስለ ፍትሕ የሚሟገትን ሰው ፖለቲከኛ አድርጎ መውሰድ የሚስተው ነገር ይኖራል:: ስለ ሀገር የሚያስቡት ፖለቲከኞች ብቻ ይመስል ሌላ ሰው ስለ ሀገሩ በመቆርቆር እግዚአብሔር በፈቀደለት አቅሙ የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግም የግድ ፖለቲካዊ አጀንዳ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚከራከር ቢኖር አሁንም የሚስተው ነገር ይኖራል:: ስለ ሀገር መቆርቆር የሃይማኖት ሰዎችንም ይጨምራልና::

የሃይማኖት መሪዎችን መንገድ መስቀለኛ የሚያደርገው ይህ ብቻ አይደለም:: የሃይማኖት መሪዎች ለፖለቲካ ሥልጣን ባይሠሩም የግል የፖለቲካ አመለካከት ግን ይኖራቸዋል፤ የአገራቸው ጉዳይ ያገባቸዋል፤

የተሻለች አገር ለማየት እነሱም ይሻሉ:: በዚህ ጊዜ ውጥረት ሊከሠት ይችላል:: የሃይማኖት መሪን እንደ ፖለቲከኛ የመፈረጅ ሁኔታም ይፈጠራል::

በእርግጥ አንዳንዱ በእነዚህ ውጥረቶች መካከል ሚዛን መሳት ይፈጠራል:: መደበላለቅ የሚታይበት ጊዜም አለ:: በሃይማኖት ሽፋን የፖለቲካ አጀንዳ የማራመድ ዝንባሌም የሚኖራቸው መሪዎችም አይጠፉም:: ለዚህም መድኃኒቱ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የቄሳርን ለቄሳር ማለት መቻል ነው::

የሃይማኖትና መንግሥት መለያየት አንዳንዶች እንደተረዱት ፖለቲከኛ መሆን ጸረ ሃይማኖት ወይም ሃይማኖት የለሽ መሆን ማለትም አይደለም:: ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበራቸው ታላቅ ሥራን የሠሩ ብዙ ስኬታማ መሪዎች በዓለም መድረክም በኢትዮጵያም ታሪክ ነበሩ:: አሁንም አሉ፤ ነገም ይኖራሉ:: የእምነት ሰው መሆናቸው በየትኛውም መልኩ የተሻሉ መሪ እንዲሆኑ ያግዛቸዋል እንጂ ሃይማኖት ለመሪነት እንቅፋት ሊሆን አይችልም:: ፖለቲካን ከሃይማኖት ሳያቀላቅሉ የሃይማኖትና የፖለቲካን ድንበር ጠንቅቀው ላሰመሩና ለሚጠብቁ መሪዎች አገር የጋራ እምነት የግላቸው መሪነት ደግሞ ሓላፊነታቸው መሆኑን ያውቃሉ::

በአጠቃላይ ሥልጣን የማገልገያ መሳሪያነቱን መረዳት መቻል በቃል የሚነገረውን ያህል በተግባር ቀላል አይሆንም:: በእርግጥ በጎ ሥራ መሥራት እንጂ የሥልጣን እድሜውም አይደለም በታሪክ እንዲታወሱ የሚያደርገው:: በዓለም ላይ ስማቸው ገኖ የሚወሱ መሪዎች በወንበሩ ላይ የቆዩት ጥቂት ዘመን ነው:: ሥራቸው እንደኮከብ ስለሚያበራ ነው ታሪካቸው የሚወሳው:: ግመል በመርፌ ቀዳዳ የመሹለክ ያህል እየሆነ እንጂ ሥልጣንን እንደ እነ ማንዴላ፥ እንደ እነ ጋንዲ የሚንቁና ትልቁን አገራዊ ራእይ የሚያስቀድሙ መሪዎች ከተገኙ ከወንበር ቢወርዱም በሰው ሕሊና ለረዥም ጊዜ ዙፋናቸው አይነቀለም:: ይህ በፖለቲካው መስክ ብቻም አይደለም:: በሃይማኖቱም በሌላውም ዘርፍ ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም:: በማስመሰል የተሰበከው ሳይሆን ከእውነተኛ ተግባር

የሚገኘው እውነተኛ ታሪክ ነው ዘመን ተሻሪ ሊሆን የሚችለው:: የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ከሥልጣን ተገፍቶ መወረድም የማይቀር መሆኑ የሚያከራክር አይደለም:: ክፉ ስም ከመቃበር በላይ ሲሆን ግን ለቀሪም አንገት ነው የሚያስደፋው:: የሥልጣንን ምንነት የተረዱ መሪዎች ስም ከመቃበር በላይ መዋል የሚችለው በጎ መሥራት ሲቻል ብቻ መሆኑን አሁን ማን ይስተዋል? ታዲያ ምን ነው በተግባር እንዲህ ዐይነት መሪዎችን ማግኘት ጭንቅ ሊሆን ቻለ? የሚለው ነው እንጂ እንቆቅልሹ::

ክፍል ሦስት

መሪነትና ሥነምግባር

ምዕራፍ ዘጠኝ

ሥነ ምግባር

9.ሥነ ምግባር ምንድን ነው?

ስለ ግብረ ገብ መሪ ከማየታችን በፊት ስለ ሥነ ምግባር ዘርዘር አድርጎ ማየት ጠቃሚ ነው:: በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ ስለ ሥነ ምግባር የሚዳሰስ ሲሆን ስለ ግብረ ገብ መሪ የሚሸፍነው ደግሞ የመጨረሻው ምዕራፍ ይሆናል::

ሥነ ምግባር (Ethics-the discipline dealing with what is good and bad and with moral duty and obligation) **ወይም ግብረ ገብነት** (moral-conforming to a standard of right behavior [56]) **በመባል የሚጠራው እሳቤ በፍልስፍናውም በሌላውም ብዙ የተባለለት፥ በሰፊው የተጻፈለትና እጅግ ሰፊ ጉዳይ መሆኑ የሚታወቅ ነው:: ሥነ ምግባር በትምህርት ቤቶችም በስፋት መሰጠት ከጀመረም ሰነባብቷል:: ለምሳሌ በአሜሪካ ከአምስት መቶ በላይ ሥነ ምግባርን የተመለከቱ የትምህርት አይነቶች እንደሚሰጡና**

[56] conforming to a standard of right behavior, capable of right and wrong action, expressing or teaching a conception of right behavior https://www.merriam-webster.com/dictionary/moral

ከሀያ አምስት በላይ የማስተማሪያ መጽሐፍት እንደተጋጁለት አንድ ዳሰሳ ያለመለክታል[57]:: የዚህ መጽሐፍ ትኩረትም እሳቤውን በመጽሐፍ ቅዱስ መነጽርነት ማዬትና የተወሰኑ ሐሳቦችን ማካፈል ብቻ ነው የሚሆነው::

የሰው ልጅ በመተሳሰብ፣ በመፈቃቀር፣ በመረዳዳት ተግባብቶ በሰላም መኖር የሚችለው ሥነ ምግባር ስላለ ነው ማለት ይቻላል:: ይህ ነገር ጥሩ ነው፣ ይህ ነገር ጥሩ አይደለም፤ ይህ ነገር በጎ ነው፣ ይህ ነውር ነው፤ እንዲህ ማድረግ ትክክል ነው ወይም ትክክል አይደለም የሚሉትን የሚመልስ ነው ሥነ ምግባር ወይም ሞራል የሚባለው[58]::

ሥነ ምግባር ምንጩ ከሃይማኖት ይሁን ከፍልስፍና ከማኅበረሰብ እሴት ወይም ባህል ወይም መንግሥት ወይም ከግለሰብ አስተሳሰብ ሁሉም በአጠቃላይ መልካም መሥራትን የሚደግፉ፣ ክፉ መሥራትን የሚያውግዙ ናቸው:: እንደየእምነቱ ግቡም ይሁን ይዘቱ ቢለያይም፤ የሥነ ምግባር መርሆ ምንጩ የትም ይሁን የት ትክክሉ የቱ ነው? ትክክል ያልሆነውስ? የቱ ነው ነውር? የቱ ነው ነውር ያልሆነውስ? የቱ ነው በጎ ነገር? የቱ ነው በጎ ያልሆነው? የሚለውን ለመመለስ ዐላማ ያደረገ ነው:: ዓለም አቀፍ (universal) የሞራል እሴቶች በመባል የሚጠቀሱትም በአብዛኛው ዓለም በጎ ምግባር ተብለው የሚታመንባቸው ናቸው:: ለምሳሌ እኩልነት፣ ሰብአዊ መብት፣ ሰብአዊ ክብር፣ ሰላም፣ ነጻነት፣ ፍትሕ የመሳሰሉት በተባበሩት መንግሥታት ዩኒቨርሳል ሞራላዊ እሴቶች በመባል የተጠቀሱበት ጊዜ አለ[59]::

---

[57] Over 500 business-ethics courses are currently taught on American campuses; fully 90% of the nation's business schools now provide some kind of training in the area. There are more than 25 textbooks in the field and 3 academic journals dedicated to the topic. https://hbr.org/1993/05/whats-the-matter-with-business-ethics

[58] **Generally, the terms** *ethics* **and** *morality* **are used interchangeably.** Both morality and ethics loosely have to do with distinguishing the difference between "good and bad" or "right and wrong." https://www.britannica.com/story/whats-the-difference-between-morality-and-ethics

[59] UNIVERSAL VALUES - PEACE, FREEDOM, SOCIAL PROGRESS, EQUAL RIGHTS, HUMAN DIGNITY https://www.un.org/press/en/2003/sgsm9076.doc.htm

የሞራል ሕግን በተመለከተ ሃይማኖትም ትልቅ ቦታ እንዳለው የሚታወቅ ነው:: የብዙ ሃይማኖቶች የሥነ ምግባር መመሪያም ከልዩነቱ ይልቅ መመሳሰሉ እንደሚበዛም ይታወቃል:: እንደየእምነቱ አስተምህሮ ይዘቱና ግቡ ልዩነት ያለው ቢሆንም የዚያኑ ያህል የሚቀራረብም ነው:: ሁሉም እንደየእምነቱ ለፈጣሪም ለሰውም የሚመች ዜጋን ለማነጽ ዐላማ ያደረገ ነው ማለት ይቻላል:: መቼም ሰዎች ለጥቅማቸው እንደሚመቻቸው ተርጉመው ካልተጠቀሙበት በስተቀር ጥላቻን፣ ስርቆትን፣ ሰው መግደልን፣ ማመንዘርን፣ ኢፍትሐዊነት፣ አለመከባበርን፣ ሕገ ወጥነትን እና የመሳሰሉትን የሚሰብክ ሃይማኖት የለም:: ሰዎች ለጥቅማቸው እንደሚመቻቸው ተርጉመው ካልተጠቀሙበት በስተቀር ሁሉም እንደየእምነቱ በመተሳሰብና በመፈቃቀር ከመኖር ሌላ በጦርነትና በመገፋፋት የሚያምንም መቼም አለ ብሎ ማሰብም ትርጉም አይሰጥም::

9.1 በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሥነ ምግባር

በእርግጥ በፍልስፍና ላይ የተመሠረተና በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሥነ ምግባር መሠረታዊ ልዩነት አላቸው:: አንደኛው ልዩነት "እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ" (ዘፍ 3፥22) ተብሎ እንደተጻፈ ሕግ በጽሑፍ ከመሰጠቱም በፊት ይሁን ሕግም ከተሰጠ በኋላ ለሰው መልካሙን ከክፉ ለመለየት የሚያስችል አእምሮ የሰጠ ፈጣሪ ነው የሚለው ነው:: እንዲህ የማያምኑ አሉና ነው ልዩነቱ:: አልተማርኩም፣ ሕጉን አላውቅም ማለት የማይቻለውም መልካሙን ከክፉ ለመለዬት የሚያስችል ሕሊና ለሰው ሁሉ ከፈጣሪ የተሰጠ በመሆኑም ነው:: "እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፣ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ::" የሚለው ቃል ይሄንን ነው የሚያሳየውም:: (ሮሜ 2፥15)

በጎ ማድረግ እንደሚያሸልም ሁሉ ክፉ ማድረግም በፈጣሪ ዘንድ የሚያስጠይቅ ነው የሚለው ከዚህ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል:: "እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል::" መባሉም ለዚህ ነው:: (ሮሜ 2፥6) ይህ ሁለተኛው ልዩነት ሊሆን ይችላል:: በምድራዊ ሕግ ብቻም

ሳይሆን በፈጣሪም ዘንድ ተጠያቂነት አለ ብለው የማይምኑ ይኖራሉና:: በተመሳሳይ የሥነ ምግባር ሕግ አንጻራዊ (relative)[60] ነው የሚሉ እንዳሉ የሚታወቅ ቢሆንም በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሥነ ምግባር ግን ፍጹም እንጂ አንጻራዊ አይደለም የሚለው ነው:: ምክንያቱም እንደሁኔታው ትክክል የሚሆን እንደሁኔታው የሚቀያየር እውነት የለምና:: ይህ በሦስተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችል ልዩነት ነው:: እንዲሁም በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሥነ ምግባር ውጤቱ ብቻ ትክክል መሆኑ ሳይሆን ውጤቱ ላይ የሚያደርሰው መንገድም ትክክል መሆን አለበት:: የተሠራው ሥራ ብቻ ሳይሆን የተፈጸመበት መንገድም ትክክል መሆን አለበት:: ፍጻሜው ላይ ለመድረስ ያልተገባ ነገር ቢደረግ ፍጻሜው እስካማረ ድረስ ምንም ችግር የለውም (the end justifies the means)[61] የሚለውም ብዙውን ጊዜ ተቀባይነት አይኖረውም:: በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሥነ ምግባር ፍጻሜው ብቻ ሳይሆን ሂደቱም፣ መዳረሻው ብቻ ሳይሆን መሄጃ መንገዱም ቀና ሊሆን ይገባል:: ይህም ሌላው ልዩነት ነው::

በሌላ በኩል ሰው ሰውን ቢፈራ ተደብቆ ጸያፍ ነገርን ሊፈጽም ይችላል:: ሰው ሕግን ቢፈራም ማስረጃ እንዳይገኝ አርጎ ይፈጽመዋል:: ከእግዚአብሔር ግን ተደብቆ ክፉን ሥራ መሥራት አይቻልም:: ሥነ ምግባር በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሲሆን ሰው ቢያይም ባያይም፣ የተሠራው በጨለማ ቢሆን በብርሃን፣ የሕግ የበላይነት ቢኖርም ባይኖርም፣ ሁል ጊዜም ሙሉ ሰው ሆኖ ለመኖር ያስችላል:: ምክንያቱም ሰው ባያይ እግዚአብሔር ያያል የሚለው እምነት ስላለው:: ሰው ፈጣሪውን የሚፈራ ከሆነ በብርሃን ቢሆንም በጨለማ፣ በስውር ይሁን በግልጽ የሚሠራው፣ ከፈጣሪ ሊሰወር አይችልም የሚል እምነት ከሌለው ሃይማኖት አለው ሊባልስ እንዴት ይቻላል?

[60] Values are relative to the point of view of the person holding the value, whether he or she believes it comes from God, from what is best for the society, or what is best for one's self. file:///C:/Users/wb242998/OneDrive%20-%20WBG/References/Ethics.pdf Understanding our Human Values, Book 4, page 141

[61] The end justifies the means. https://edukacjaetyczna.pl/wp-content/uploads/2017/17_2_Mahrik.pdf

ለዚህ በቅዱስ መጽሐፍ የዩሴፍን ታሪክ መጥቀሱ ነገሩን ለማብራራት ይጠቅማል:: እንደ ዮሴፍ እንዴት ይህን ክፉ ነገር አደርጋለሁ? ማለት የሚቻለው ፈሪሃ እግዚአብሔር ሲኖር ነው:: ዮሴፍ ያሳዳሪው የጲጥፋራ ሚስት አብረን እንተኛ ስትለው በእርግጥ ኀጢአቱን ለመፈጸም ራሱን ሊያሳምን የሚችልበት ምክንያት ማዘጋጀት ይቻለው ነበር:: አንድም ነጻነት የሌለው በባርነት የሚኖር ነበርና አሳዳሪውን እምቢ ለማለት የሚያስችል ዓቅም የለውም:: በሌላ በኩል ደግሞ የጲጥፋራ ሚስት እንዳለችው በዚያ ወቅት ከእርሷና ከዮሴፍ ሌላ የሚያይ የሚሰማም ሰው ስለሌለ ኀጢአቱን ለመክደን የሚያሳስብ አልነበረም:: እግዚአብሔርን መፍራት ሲኖር፤ ሰው አየ አላየ፣ ሰው ሰማ አልሰማ፣ በሚመች ጊዜ ይሁን በአስቸጋሪ ሁኔታ፣ እንደ ዮሴፍ ለሕሊና መታመን ይቻላል:: ራስን ለእስር፣ ለእንግልት በሚያጋልጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እንኳ ክፉ ነገርን መቃወም፣ የታመኑበትን አደራ ጠብቆ መኖር የሚቻለው ፈሪሃ እግዚአብሔር ሲኖር ነው ማለት ይቻላል:: ለሕሊና መታመን ሲቻል እንደ ዮሴፍ "ለዚህ ቤት ከእኔ የሚበልጥ ሰው የለም፤ ሚስቱ ስለ ሆንሽ ከአንቺም በቀር ያልሰጠኝ ነገር የለም፤ እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?" ማለት ይቻላል:: (ዘፍ 39፥7-13) በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሥነ ምግባር እንዲህ ለሕሊና መታመንን ገንዘብ ያደርጋል::

9.2 የሥነ ምግባር ዐላማዎች

በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሥነ ምግባር ዐላማዎቹን በአራት መክፈል ይቻላል::

❁ እግዚአብሔርን መምሰል

የመጀመሪያው የሥነ ምግባር ዐላማ ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረ በመሆኑ ሰው ፈጣሪውን ይመስላል ከሚለው የሚመነጭ ነው:: "እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው::" እንዲል:: (1ጢሞ 6፥6) ሰው ለዘላለማዊ ሕይወት እንደመፈጠሩም የሰው ሕይወት ዐላማ አለው፣

ትርጉ አለው:: ሰውም ለዚህ ዐላማ በተስፋ፣ በእምነት ይኖራል የሚል ነው:: እግዚአብሔርን መምሰል ማለት እግዚአብሔር በባሕርዩ እውነተኛ እንደሆነ ሁሉ ሰውም እውነተኛ እንዲሆን ይጠብቅበታል:: እግዚአብሔር ፍትሕ የባህርዩ ገንዘቡ እንደሆነ ሰውም ፍትሕን ይወዳል:: እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ ሁሉ ሰውም ፍቅርን ይፈልጋል:: እግዚአብሔር ቅድስና የባሕርይ ገንዘቡ እንደሆነ ሰውም የቅድስና ሕይወትን የንጽሕና ሕይወትን መኖር ይችላል የሚሉትን ሁሉ ያጠቃልላል:: "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ" ተብሎ እንደተጻፈ:: (ዘሌ 19፥2)

በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ የሥነ ምግባር መርህ መሠረቱም ፍጻሜውም ፍቅር ነው:: ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ነውና:: "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ እንዲሁም ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚሉት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል" ተብሎ እንደተጻፈ አምላክን በፍጹም ልብ መውደድ ሲቻል ሰውንም ያለ ልዩነት መውደድ ይቻላል:: (ማቴ 22፥37-39) እግዚአብሔርን እና ሰውን መውደድ ሲኖር የሌላውን መመኘት፣ የሌላውን መፈለግ፣ የሌላውን ክብር ማዋረድ፣ በጉልበት መመካት አይኖርም:: ይልቁንም ለሌላው ማሰብ፣ ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌላው መኖር ይጀመራል:: መቻቻልም ቀላል ይሆናል:: ፍቅር ካለ ሁሉም አለና:: ፍቅር ካለ ሁሉም ይቻላል::

እግዚአብሔርን መመስል የሚቻለውም ያለማቋረጥ በማደግ ነው:: የሰው እድገቱ ሁል ጊዜም የማይቋረጥ ነውና:: በሥጋ ማደግ እንዳለ ሁሉ ሰው በእግዚአብሔርም በሰውም ፊት በጥበብ ያደጋል፤ ሰው በሞገስ ያድጋል:: በመንፈሳዊ ሕይወትም ዘወትር ማደግ ይችላል:: "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ::" እንዲል መጨረሻው ክርስቶስን መምሰል ነው:: (1ኛ ቆሮ. 11፥1)

በሰው ሕይወት እድገት በመጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው የተካተተ ሲሆን አንድ ምሳሌ ማዬት ይቻላል:: "ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፤ በበጎነትም ዕውቀትን፤ በዕውቀትም ራስን መግዛት፤ ራስንም በመግዛት መጽናትን፤ በመጽናትም እግዚአብሔርን

መምሰል፤ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፣ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።" የሚለው መልእክት የሚያስገነዝበውም የማይቋረጥ የሰውን ልጅ እድገት ነው:: (2ኛ ጴጥ. 1፥5-7) ከአንዱ ደረጃ ወደሌላው የሚታደገው እንዲህ ባለው መንገድ ነው:: በጎነት በየጊዜው ይጨምራል፥ ራስን መግዛትን በየጊዜው ማሳደግ ይቻላል፥ መጽናናትም እንዲሁ የእድገት ውጤት ነው፥ ወድማማችነትና ደግነት ፍቅርን ይህን ሁሉ ማሳደግ ይቻላል::

ይህ በሃይማኖታዊ ዐይን ስለሚታይ ብቻም አይደለም፥ በሌላውም የሚነገረው ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል:: ራስን መግዛት(self control) መጽናናት (perserverance)፥ የወንማማች መዋደድ (brotherly kindness) እንዲሁም ፍቅርን የማይሰብክ የለም ማለት ይቻላል:: ሰው በአመለካከትም ያድጋል:: አስተዋይነትና አርቆ አሳቢነት እያደር ይጭመራል:: ሰው ይጨምታል፤ ይረጋጋል፤ በበጎ ሥራ በየጊዜው ያድጋል:: እድገት ካለፈው ስሕተት እየተማሩ፣ ያለፈውን ስሕተት ሳይደግሙ፣ ወደፊት የተሻለ ፍሬ የሚያፈራ የተሻለ ሰው መሆን መቻልም ነው::

❁ በጎ ማድረግ

ሁለተኛው የሥነ ምግባር ዐላማ ለሰው ሁሉ በጎ ማድረግ ነው:: ሰው ማኅበራዊ ፍጡር እንደመሆኑ በመተሳሰብና በመረዳዳት ላይ ነው ሕልውናው የተመሠረተ:: ሰዎች በጋራ ሲኖሩ ማኅበራዊ ደኅንነት፣ ሰላም፣ መረዳዳት፣ ፍትሕ፣ፍቅር፣ ይቅርታ ያስፈልጋቸዋል:: እግዚአብሔርም ይህን ስለሚያውቅ ለአብሮነት የሚያስፈልጉ "አባትህንና እናትህን አክብር" በማለት ለቤተሰብ መታዘዝን፣ ቤተሰብን ማገልገል፣ ቤተሰብን ማክበር ከትእዛዛት አንዱ አድርጎ ሰጥቶናል::(ዘጸ 20፥12) በተመሳሳይ የተራበን ማብላት፣ የታረዘን ማልበስ፣ የተጠማን ማጠጣት፣ የታሰረን መጠየቅ፣ እንግዳን መቀበል እና የታመመን መጠየቅ የመሳሰሉትን ትእዛዛት ለሰው ልጆች ሰጥቷል::

ወርቃማ ሕግ በመባል የሚታወቀው “እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፣ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና።“ የሚለው ሲሆን፤ ይህ ትእዛዝ በመተሳሰብ ላይ ነው የተመሠረተው:: (ማቴ 7፥12) መከበርን የማይፈልግ የለም፤ አንድ ሰው መከበር የሚፈልግ ከሆነ ሰውን ያለልዩነት ሊያከብር ይገበዋል ማለት ነው ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው የሚባለው:: መወደድንም የማይፈልግ የለም ሌላውም ጥላቻን አይፈልግምና መፈቀር እንደምንፈልግ ሌላውን በፍቅር ማየት ይገባል ማለት ነው:: ያላግባብ ሰዎች በውሸት እንዳያጭበረብሩን፣ በግፍ ሀብታችንን እንዳይቀሙን፣ እንዳይሰርቁን፣ እንዳያታልሉን እንደምንፈልግ ሁሉ ከእንዲህ ዐይነቱ አድራጎት መቆጠብ ማለትንም ይጨምራል፤ ሌላውም ይህንን ይፈልገዋልና:: ልጆቻንን በሰላም ማሳደግና ለወግ ለማዕረግ ማብቃት እንደምንፈልግ ሁሉ ይህን የማይፈልግ እንደሌለ ተረድቶ ከዓመፅ ከማፈናቀል መቆጠብ ያስፈልጋል የሚለውም ሁሉ በዚህ ሊካተት ይችላል::

ይህ ወርቃማ ሕግ ምንጩ ቅዱስ መጽሐፍ ቢሆንም በሚያምኑም በማያምኑትም እንደሚዘወተርም የሚታወቅ ነው:: “ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው” ማለት ማድረግ ለሚችሉ፣ ውለታ ለሚመልሱ ሰዎች ብቻ በጎ ማድረግ ማለትም አይደለም:: በእርግጥ በአብዛኛው የተለመደው እንዲህ ዐይነቱ ሊሆን ይችላል:: ያለው ያለውን ይጋብዛል፤ ያለው ላለው ብድራትን እያሰበ ያደርጋል እንጂ ድሀን ማሰብ ከስንት አንድ ነው:: የዚህ ዓለም ስርዓቱ በአብዛኛው “እከክልኝ ልከክልህ“ የሚሉት ዐይነት ነው:: የዚህ መርህ ዐላማ ግን እድል ለተጣመመባቸው፣ ዓቅም ላነሳቸው፣ ቀን ለጨለመባቸው አቅመ ደካሞች ሁሉ የሚቻለውን ማድረግ እንደሚገባ ነው:: የተደረገላቸውን ወሮታ ለመክፈል ለማይችሉ፣ ዓቅም ለሌላቸው ለተራቡ ማብላት፣ ለተጠሙ ማጠጣት፣ ለታረዙ ማልበስ፣ የታመሙትን የታሰሩትን መጎብኘት በዓለም ፍጻሜ በፍርድ ቀን የሚያሸልሙ ትእዛዛት የመሆናቸው ምስጢርም ይሄው ነው::

☸ ክፉ አለማድረግ

ሦስተኛው የሥነ ምግባር ዐላማ በሰው ሁሉ ላይ ክፉ አለማድረግ ነው:: አትግደል፤ አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፤ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ" የሚሉት ትእዛዛት በዚህ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው:: (ዘጸ 20፥13-17) ከዚህ በተጨማሪ የሥጋ ሥራ ተብለው የተዘረዘሩ ሥራዎች ግፍ፣ መመኘት፣ ክፋት፣ ቅናት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ተንኰል፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ ትዕቢት፣ ትምክህት፣ ጭካኔ፣ ዓመፃ ሁሉ እና የመሳሰለው በቅዱስ መጽሐፍ አታድርግ በሚል ለሰው የታዘዙት እገዳዎች የተከለከሉበት ምክንያት ለሚያደርገውም ሰው ሆነ ለማኅበረሰብ ጎጂ ስለሆኑ ነው:: (ገላ 5፥20-21) ክፉ ጠባይ በእግዚአብሔርም የተጠላ ነው:: ማድረግ ስለተቻለ ብቻ፣ ነጻነት ስለተሰጠ ብቻ፣ በልቅነት እንኖራለን ቢባል ለሰው ለራሱም ደግ አይደለም:: ትርፉ ለምንም የማይጠቅም ይልቁንም ሸክም የሚሆን ዜጋን ማፍራት ነው የሚሆነው:: ትርፉ ማኅበራዊ ቀውስ ነው:: ክፋት፣ ቅናት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ተንኰል፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ ትዕቢት፣ ስካር፣ ዝሙት፣ በዕፅ መደንዘዝ የሚጎዳው ራሱን ግለሰቡን ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰብንም ነውና:: አእምሮው እንደ ሰው ማሰብ ሲያቆም ለሰው ልጆች ሰላማዊ ኑሮ አስጊ ይሆናል:: አገሮችም እነዚህ ነገሮች በሕጎቻቸው መከልከላቸውና በሚተላለፉትም ላይ ቅጣት መጣላቸው ከዚህ የተነሣ ነው::

በገዛ ሰውነቱ የፈለግሁትን ማድረግ ለምን አልችልም? የሚል ቢኖርም ከላይ እንደተጠቀሰው ጉዳቱ የግለሰብ ብቻ ሳይሆን ለማኅበረሰብ የሚተርፍ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ አይከብድም:: በሥነ ምግባር የታነጸ ዜጋን መገንባት ካልተቻለስ ትውልድ እንዴት ሊቀጥል ይችላል? አምራች ዜጋን እንዴት ማግኘት ይቻላልስ? የሚሉትን መጠየቅ ተገቢ ነው የሚሆነው:: "ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ::" ተብሎ መታዘዙንም ማስተዋል ተገቢ ነው::

(1 ቆሮ 16፥19-20) ሰው የፈጣሪ የእጁ ሥራ እንደመሆኑም በሰው ላይ የሚደረግ ማንኛውም ግፍ በፈጣሪ ላይ እንደሚደረግ ግፍ ሆኖ መቆጠሩም ከዚህ የተነሣ ነው:: ሰውን መግደል የእግዚአብሔርን የእጁን ሥራ ማፍረስ ነው:: ሰውን መስድብም እንዲሁ ፈጣሪን እንደመሰድብም ነው:: አንዱ የሌላውን ክብር ማኮሰስ እግዚአብሔርን ማሳዘን መሆኑንም እናያለን::

“እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና::“ የሚለው ወርቃማ ሕግ “ሌሎች ሊያደርጉባችሁ የማትወዱትን እናንተም በሌላው ላይ አታደርጉ” ማለትንም ይጨምራል:: ክፉ ነገር በሌላው ላይ ሲደረግ በሌላው ሰው ላይ የሚያደርሰውን ቁስል፣ ሕመሙን የሚያውቀው የደርሰበት ሰው ብቻ ነው:: ያልተነካ ሕመሙ ሊሰማው አይችልም:: ሰው ላይ ግፍ ማድረግ፣ ለግፍ ተቀባዩ እንጂ ሕመሙ ለግፍ አድራጊው ቀላል ነው የሚሆነው:: ሰው ማሰቃየት ለሚሰቃየው ሰው ነው እንጂ ሕመሙ ለስቃይ አድራጊው ደስታን ሊሰጥ ይችል ይሆናልም:: በግፍ ሀብት ንብረቱን የተነጠቀ ሰው ስብራቱ ንብረቱን ላጣው እንጂ ለነጣቂው ሊሆን አይችልም:: ይህ ሁሉ ነገር ጊዜው ተገላብጦ በግፍ አድራጊው ላይ ሲደርስ ነው የሕመሙ መጠን የሚሰማው:: ሰውን በእስር ባሰቃዩበት እስር ቤት ተራው ደርሷቸው ሲገቡበት ያኔ ነው የእስር ቤት ስቃይ ምን እንደሚመስል መረዳት የሚቻለው:: በአንድ ወቅት በእኛ ላይ የተደረገብንን ክፉ ድርጊት በሌሎች ላይ ብናደርስባቸው ያ እኛን ይሰማን የነበረው ቁስልና ሕመም እንደሚሰማቸው በማሰብ ከክፉ ግብር መቆጠብን ነው የሚያስተምረው “ሌሎች ሊያደርጉባችሁ የማትወዱትን እናንተም በሌላው ላይ አታደርጉ” የሚለው መልእክት::

❁ ራስን መግዛት

አራተኛው ራስን መግዛትን የተመለከተ ነው:: ሰውን ከእንስሳት የሚለየው ትልቁ ቁምነገር በጎውን ከክፉ ለይቶ የሚያውቅበት አእምሮ የተሰጠው ክቡር ፍጥረት መሆኑ ነው:: ክፉውን ከደግ መለየት የሚችል

አእምሮ የተሰጠው ይህ ክቡር ፍጥረት ሰው ግን ክፉውንም ደጉንም ለመሥራት ነጻ ፈቃድ ተሰጥቶታል:: የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን ነገር ለይቶ ማወቅና መሥራት ለሰው የተሰጠ ሓላፊነት ነው:: የሰው ልጅ ሁሉንም ለማድረግ ነጻነት የተሰጠው ቢሆንም ሁሉ ግን የሚጠቅመው አይደለም:: "ሁሉ ተፈቅዶልኛል፤ ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም፤ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፤ ነገር ግን ሁሉ የሚያንጽ አይደለም::" እንደተባለ (1ኛ ቆሮ. 10፥23)

አንድን ነገር ለበጎም ለክፉም ማዋል ይቻላል:: ሁሉም ነገር እንደ አጠቃቀሙ ነው:: ዕውቀት ለክፋት ሲውል ሕዝብን ለማጫረስ፣ አገርን ለማውደም መሳሪያ ይሆናል:: ብዙ ሰዎችን ማዳን፣ የተሻለ ኑሮን እንዲኖሩ ማድረግ የሚቻለውም በዚሁ ዕውቀት ነው:: አንደበት ከሌለ ብዙ ነገር ይጎድላል:: አንደበትን ግን ለመልካም ሳይሆን ለክፉ ከዋለ ለጥቅም የተሰጠ አንደበት የጥፋት መሳሪያ ሊሆን ይችላል:: አንደበት ብርሃንን ሊሰጥ፣ የሰውን የጨለመ አእምሮ፣ የተጣመመ አመለካከትን ሊያስተካክል እንደሚችል ሁሉ በአግባቡ ካልተጠቀሙበትም አንደበት እሳት ሆኖ አገር ሊያቃጥል፣ አገር ሊያፈርስ ይችላል:: ቅዱስ ያዕቆብ "እንዲሁም አንደበት ደግሞ ትንሽ ብልት ሆኖ በታላላቅ ነገር ይመካል:: እነሆ፥ ትንሽ እሳት እንዴት ያለ ትልቅ ጫካ ያቃጥላል::አንደበትም እሳት ነው::" ሲል ጥቂት እሳት ጫካ እንደሚያቃጥል፣ አንደበት ትንሽ ሆኖ ሳለ ጥፋቱ ግን ብዙ እንደሚሆን መናገሩም ለዚህ ነው:: (ያዕ 3፥5) አገር ሊያፈርስ ይችላል የተባለለት አንደበት ልጓም ካልተበጀለት ጉዳቱ ሁሉም ጋር ነው የሚሆነው፤ በትዳርም፥ በቤተሰብም:: በማኅበረሰብም፥ በሥራ ቦታም:: በተለይ በመሪነት ደግሞ የሚኖረውን ተጽእኖ ማሰብ ይቻላል:: አፍ ጠባቂ ካልተበጀለት፣ አንደበት ካልተገታ፣ በንግግር ላይ ጨው ከሌለበት እንዲሁም ቅመም ሲጎድለው ብዙ ነው መዘዙ:: በተመሳሳይ ገንዘብን ለመልካም ተግባር ወይም ለጥፋት ሊውል ይችላል፤ እንዳጠቃቀሙ ነው:: የተራቡ ሰዎችን መመገብ የሚቻለው ገንዘብ ሲኖር ነው፤ ገንዘብ ግጭትንና ብጥብጥን ለማስፋፋት ሊውልም ይችላል:: ክህሎትን ለጥፋት ወይም ለልማት መጠቀምም እንዲሁ:: ውበትንም ለበጎም ለክፉም መጠቀም የባለቤቱ ምርጫ ነው::

በጥቅሉ “አእምሮ የሌለው ክቡር ሰው እንደሚጠፋ እንስሶች መሰለ።” እንደተባለ ሰው አእምሮውን ተጠቅሞ መልካሙን ከክፉ መለዬት ሲሳነውና እንደ እንስሳት በልቅነት መኖርን ምርጫው ካደረገ ግብሩ እንስሳትን ሊመስል ይችላል። (መዝ 49፥20) ከዚህ የተነሣ ሰው ከተፈጥሮ ባሕርይው ወጥቶ እንስሳት እንኳ የማይፈጽሙትን ተግባር ወደ መፈጸም ይወርዳል። ዛሬ በዓለም ተስፋፍቶ የሚታየው የሰው ልጅ ውድቀት ይህን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል። የገዛ ወገናቸውን መግደልና ማፈናቀል፣ በሱስ መደንዘዝ፣ ዝሙት፣ ስካር፣ ተንኮል፣ ሴራ፣ መካካድ፣ ግብረ ሰዶማዊነት የመሳሰለው ሁሉ በእንስሳት እንኳ የለባቸውምና።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ሰው ከእግዚአብሔር ሲርቅ ልቦናው ይጨልማል፤ መልካምና ክፉውን መለየት ይሳነዋል፣ ከበጎ ይልቅ ወደ ጥፋት ያዘነብላል፤ ወደ ሚጎዳ ርኩሰት ራሱን በፈቃዱ ለባርነት አሳልፎ ይሰጣል። እንዲህ የሰው ልቦና ሲጨልም፣ የሰው አእምሮ ሲደነዝዝ፣ አእምሮ ማሰብ ማመዛዘን ሲሳነውና ከንቱ ሲሆን፣ ሰው ከዕውቀት ይልቅ በስሜት ሲነዳ እንደምናዬው የሞራል ዝቅጠት ይመጣል። ለአእምሮ የሚከብዱ ነገሮች ሲሰሩ የሚታዬውም እንዲህ የሰው ሕይወት ሲጨልም ሊሆን ይችላል። ሰው አእምሮውን መጠቀም አልፈልግም ያሻኝን አደርጋለሁ ሲል “እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ። ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፣ .. ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኵስነት አሳልፎ ሰጣቸው... እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፣” እንደተባለ ያኔ ነው ከሰውነት ክብር የሚወርደው። (ሮሜ 1፥20-28)

ሰው በነጻነት ሊኖር፣ በነጻ ሕሊና በነጻነት እንዲያስብ የተፈጠረ ቢሆንም “ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው።” እንደተባለ ሰው ለተሸነፈበት ለማንኛውም ነገር አገልጋይ፣ ተገዥ መሆኑም አይቀርም። (ዮሐ 8፥34) ለምሳሌ ሰው በፈቃዱ ለሱስ ተገዥ ሲሆን ማየት የተለመደ

ነው:: በፈቃዳቸው ከተገዙለት ሱስ በፈቃድ ለመውጣት ግን እንደ ጅማሬው ቀላል አይደለም:: ብዙ ሰዎች ከሱስ መላቀቅ፣ ነጻ መውጣት እየፈለጉ ዓቅም አጥተው የመቸገራቸውም ነገር ከዚህ የተነሣ ሊሆን ይችላል::

ሰው ከሥነ ምግባር ሲርቅ የሚጎዳው ራሱንም ጭምር መሆኑም ብዙም የሚያከራክር አይሆንም:: ብዙውን ጊዜ ግን ከዕውቀት ስሜት ሲያይል፣ ማስተዋል ሲጠፋ ከሥነ ምግባር መራቅ የሚያደርሰውን ጉዳት መገንዘብ የሚቻለው ቀኑ ካለፈ ከዘገየ በኋላ ሊሆን ይችላል:: የጠፋው ልጅ በመባል በሚታወቀው ታሪክ ከፍቅር ይልቅ ገንዘብን፣ ከአንድነት ይልቅ መለያየትን፣ በሕግ ከመኖር ይልቅ መረን ኑሮን የመረጠ ሰው ነበረ:: አባቱም ይህን ሁሉ እንደማይጠቅመው እያወቀም ቢሆን ነጻነቱን ለመከልከል አልፈለገምና ፈቀደለት:: የጠፋው ልጅ ከአባቱ ተለየ:: የሚደርሰውን የልጅነት ውርስ ያዘና ወደ ሩቅ አገር ተሰደደ:: በዚያም ገንዘቡ አለቀና የሰው ምግብ ሳይሆን የእርያ ምግብን እንኳ ማግኘት አልችል አለ:: ገንዘብም አለቀ ሰውም ጠፋ:: (ሉቃ 15፥17-21)

ሁሉን ነገር ለማድረግ ከልካይ ላይኖረን ይችላል:: ነጻነት ያለበት ነገር ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም፣ ኪሳራው ብዙ ሊሆን ይቻላል:: ይህ ሰው መማር የቻለው ከብዙ ክስረት በኋላ፣ በመከራ ውስጥ ነበር:: አስቅድሞ ማየት መረዳት ሲያቅት ሌላው አማራጭ "ምክረው ምክረው እንቢ ካለ ግን መከራ ይምከረው" እንደተባለ መማር የሚቻለው በመከራ መካከል ሊሆን ይችላል:: ልብ ሲገኝ መጸጸት ቢኖርም መማር የሚቻለው እሳቱ ካቀጠለ በኋላ ነው የሚሆነው:: ፈሪሃ እግዚአብሔር እንደ ኋላቀርነት፣ እንደ አላዋቂነት የሚቆጠርበት ጊዜም ብዙ ነው:: ሁሉም በስሜት መንጎድ እንጂ የሚሠራው ሥራ ይጠቅማል ወይ? ጉዳቱ ምንድን ነው? ይህ ነገር ማለፉ አይቀርም ግን ሲያልፍ ትቶት የሚያልፈው ጠባሳ ምን ይሆናል? የሚለውን ማስተዋል በማይኖርበት ጊዜ የሚያጋጥመው እንዲህ ዐይነቱ ነገር ሊሆን ይችላል:: ይህ ደግሞ በእምነት ዐይን ስለሚታይ ብቻም አይደለም:: ከዚያም ውጭ ባለው እይታም በተጨባጭ የሚታዬው ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል:: ስሜት አይሎ ማስተዋል

የሚሳንበት ምን ያህል ጊዜ ነው? መጸጸት የሚመጣውስ ከምን የተነሣ ነው? ምን ያህል ጊዜ ነው መጸጸት የሚያጋጥመን?

9.3 ትክክል የሆነው የሚለየው በምን መንገድ ነው?

የግብረ ገብነት ውሳኔዎች በምን መንገድ ነው የሚወሰኑት? ትክክል የሆነውን ትክክል ካልሆነው፣ ጥሩውን ከመጥፎው የሚለየው በምን መንገድ ነው? የሚለውን ስናይ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር በአመዛኙ ሦስት መንገዶችን ማንሣት ይቻላል[62]::

1ኛ. በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈ አድርግ፣ አታድርግ የሚሉት ትእዛዛትን በመከተል (Command — What do the rules say is the right way to act) ሲሆን ይህም አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፣ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፣ የባልንጀራህን ሚስት ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ፣ ከሚሉት በተጨማሪ ግፍ፣ መመኘት፣ ክፋት፣ ቅናት፣ ክርክር፣ ጥል፣ ቁጣ ተንኰል፣ ክፉ ጠባይ፣ ስድብ፣ ሴራ፣ አድመኛነት፣ ሐሜት፣ ትዕቢት፣ መለያየት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ መጎምጀት እና ከዓመፃ ሁሉ መራቅ አታደርግ በሚለው የሚታቀፉ ናቸው:: (ሮሜ 1፥29-30; 1ኛ ቆሮ 6፥9-10) ሊደረግልን የምንፈልገውን ማድረግ፣ ወይም በአጠቃላይ የእርስ በርስ መረዳዳት፣ የተራበን ማብላት፣ የታረዘን ማልበስ፣ የተጠማን ማጠጣት፣ የታሰረን መጠየቅ፣ እንግዳን መቀበል፣ የታመመን መጠየቅ፣ ጠላትን መውደድ እና የመሳሰሉት ትእዛዛትም በዚሁ የሚጠቃለሉ ናቸው::

ዐላማውም ይሁን ይዘቱ ይለያይ እንጂ እነዚህን አታደርግ በሚል የተዘረዘሩትን አብዛኞቹ ትእዛዛት በመንግሥታት ሕጎች የተካተቱና የሚሠራባቸው እንደሆኑም የታወቀ ነው:: ከሃይማኖት ውጭ ነን የሚሉ ወገኖችም ብዙዎቹን ሞራላዊ እሴቶች በሚል የሚቀበሏቸውም ናቸው: በየተቋሙ የሚገኙ የተጻፉም ይሁኑ ያልተጻፉ የሥነ ምግባር

[62]Three general approaches to ethics have achieved widespread use both in Christian moral thinking and in the world at large. The approaches are: command, consequences and characheter.https://www.theologyofwork.org/key-topics/ethics

መመሪያዎችም የተከለከሉ ድርጊቶችን ከነቅጣታቸው የሚዘረዝሩ መሆናቸውም የሚታወቅ ነው:: ሕጉ ምን ይላል? መመሪያው ወይም አሠራሩ ይፈቅዳል ወይ? በሚል መጠዬቅም እንግዳ ነገር አይደለም::

2ኛ. ለሰው የሚጠቅመው ምንድን ነው? ለሰው የሚጎዳውስ ምንድን ነው? ለማኅበረሰብ የሚጎዳው ምንድን ነው? ለማኅበረሰብ የሚጠቅመውስ ምንድን ነው? (Consequences — what actions are most likely to bring about the best outcome?) በሚል ትክክለኛውን ነገርና ትክክለኛ ያልሆነውን ነገር አሳቡ ወይም ተግባሩ በሚያስገኘው ውጤት ወይም በሚያስከትለው ጉዳት በመመዘን ለመለየት የሚቻልበት መንገድ ነው:: ከላይ የተዘረዘሩትን ዝሙት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ የመሳሰሉት ለግለሰብም ይሁን ለማኅበረሰብ ጉዳት እንጂ ጥቅም እንደማያስገኙ የሚያከራክር አይሆንም:: በዚህ መንገድ ነው ግለሰብን ይሁን ማኅበረሰብን ከሚጎዱ ክፉ ነገሮች መራቅ ይገባል የሚባለውም:: ሰው እንዲህ ያሉ ነገሮችን ፈቅዶ ወይም ተታሎ ወይም በተለያዬ ምክንያት ተገፋፍቶና ተገዶ ቢገባባትም ለጤናም ለውስጣዊ ሰላምም ጉዳትን እንጂ ጥቅም እንደማይስገኙለት ነው በተግባር የሚታዬውም:: ሱስና የመሳሰለው ተግባር በግለሰብ ላይ ብቻ ሳይሆን በአገር ላይ ያለውን ጉዳት ግምት ውስጥ በማስገባት መንግሥታት ጉዳቱን ለመቀነስ የሚቻላቸውን ሁሉ እንደሚያደርጉም የሚታወቅ ነው::

3ኛ. ሰብእናን መሠረት ያደረገ ነው:: ምን ዐይነት ጠባይ እንዲኖረኝ ነው የምፈለገው? ምን ዐይነት ሰው መሆን ነው የምፈልገው? (Character - What kind of moral person do I want to be or become?) የሚለውን ጥያቄ በመጠየቅ መልካሙን ጠባይ ከክፉ ጠባይ መለየት መቻልና በዚሁ አግባብ ሰብእናን መገንባት መቻል ነው:: ትርጓሜው ቢለያይም ጥሩ ሰው መሆን እፈልጋለሁ፤ እንዲሁም አርያነት ያለው ሰው መሆን እፈልጋለሁ የምንለው ይህንን የሚያመለክት ነው::

አንቀጸ ብፁዓን የሚባለው የወንጌል ክፍል የሚዘረዝራቸው የዋህነት፣ ልበ ንጹሕነት፣ ምሕረት ማድረግ፣ አስታራቂነት፣ ደግነት መዕናናትና ጽድቅ በዚህ መንገድ የሚጠቃለሉ ናቸው:: (ማቴ 5፥3-11) በተጨማሪም

የመንፈስ ፍሬ በመባል የተዘረዘሩ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሀት፣ ራስን መግዛት በዚህ ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው (ገላ 5፥22)::

9.4 ሕግና ሥነ ምግባር

በአጠቃላይ ሰው አእምሮውን ለደግነት ሳይሆን ለክፋት ሲያውለው ማኅበረሰብ ይቸገራል:: የሰው ግንኙነት ከሕግ ይልቅ እርስ በርስ በመተማመን ላይ የተመሠረተ መሆኑም የታወቀ ነው:: ሥነ ምግባር ሲጠፋ በሰው ልጆች መካከል መተማመን ይጎድላል:: ሕገ ወጥነትም ይሠለጥናል:: በሌብነት መክበር ነውር መሆኑ ይረሳል:: ሐሰት ይነግሣል:: ታማኝነት እንደ ሞኝነት፣ ክህደት እንደ አዋቂነት ሲቆጠር ክፋት ይበዛል::

አሁን እየታየ ያለው ፖለቲካዊ ምስቅልቅል ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊም፣ ማኅበራዊም ነው የሚያሰኙ ብዙ ምልክቶች አሉ:: ግብረ ገብነት በጎደለበት ምንም ያህል ጠንካራ መሪዎች ቢኖሩ ዘላቂ ሰላም የሰፈነበት የበለጸገ አገርን እንዴት መገንባት ይቻላል? ሰው ከሰው ጋር በሰላምና በመቻቻል የሚኖር ትውልድ፣ እርስ በርሱ የሚተማመን እና የሚታመን አመራርን፣ ከሱስ ነጻ የሆነ ለአገር የሚያስብና አገሩን የሚያገለግል ዜጋን መፍጠር የሚቻለውም ግብረ ገብነት ሲኖር ነው::

የግብረ ገብነት አስፈላጊነት በሕግ ሊተካ የሚችልም አይደለም:: አገር በሕግ ወይም በሰራዊት ብቻ እንዴት ሊጠበቅ ይችላል? ከሕግ ማስከበር ጋር ሥነ ምግባርም አስፈላጊ ነውና:: "ጻድቃን በበዙ ጊዜ ሕዝብ ደስ ይለዋል፣ ኀጥኣን በሠለጠኑ ጊዜ ግን ሕዝብ ያለቅሳል" (ምሳ 29፥2) እንደተባለ ሥነ ምግባር ከአገር ሲጠፋ ስርዓት አልበኝነት ይስፋፋና ከሕግ ዓቅም በላይ ሊሆን ይችላል:: በዚህ ምክንያት ነው ኀጥኣን በሠለጠኑ ጊዜ ሕዝብ ያለቅሳል የተባለው:: ሥነ ምግባር እያሽቆለቆለ ነው፤ ሙስና ባህል ሆኗል፤ ዘረኝነት ተስፋፍቷል፤ ፍርድ በገንዘብ ሆኗል፤ ፍትሕ ጠፍቷል ማለት ብቻ አይበቃም:: የሞራል ውድቀት ባለበት ጠንካራ መንግሥት

ቢኖር እንኳ አገር ሰላም ውሎ ሰላም ማደር እንዴት ይችላል? አገር የሚጠበቀው በሠራዊት ብቻ ሳይሆን በሕዝብም ነውና:: ይህንኑ ነው የብዙ አገሮች ታሪክ የሚያስተምረንም:: ሩዋንዳ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ መቶ ቀን ባልሞላ ጊዜ ሲያልቅ[63] በዩጎዝላቪያና ኮሶቮ ሕዝብ በጅምላ ሲረግፍ እንደጥላ እንደዋዛ ነበር ያለፈው:: ሰራዊትም ሊታደገው አልተቻለም ነበር::

መሪ ጠፍቶ ሕገ ወጥነት ተስፋፍቶ ወንጀል በርክቶ ግብረ ገብነት ጠፍቶ በነበረበት በመሳፍንት ዘመን በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን:: "በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፣ ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር" የሚል ነው:: (መሳ. 17፥16፥ 21፥25) ታሪኩ ሰፊ ነው:: የሥነ ምግባር ዝቅጠቱ ደግሞ ለመናገር የሚከብድ ነበር:: ለሦስት መቶ ስድሳ ዓመታት ጠንካራ የአገር መሪ ጠፍቶ እርስ በርስ ሽኩቻ የነበረበት፤ በየጊዜው የጎበዝ አለቃ በሚባል ዐይነት መሳፍንት የሚባሉ መሪዎች በነጻ አውጭነት እየተነሡ ጠላትን ተዋግተው እያሸነፉ ሕዝቡን በፈለጋቸው መንገድ ሲገዙ የነበሩበት ዘመን ነው:: በታሪኩ ፍጻሜ መሪ ባለመኖሩ ምክንያት የመንጋ ፍርድ በርክቶ ሁሉም በመሰለው የመሰለውን ያለ ከልካይ ያደርግ በነበረበት ዘመን በደቦ የተፈጸመ የአስገድዶ መድፈር ታሪክን ያነሣና በዚያም ምክንያት በሕዝቦች መካከል ጦርነት መቀስቀሱን ያሳያል::

በዚህ በተጠቀሰው ዘመነ መሳፍንት እንደነበረው ግብረ ገብነት ሲጠፋ መሪ አልባነት ይመጣል:: መሪ ያጣ ሕዝብ ደግሞ እንደመሰለው በየፊናው መሄዱ አይቀርም:: መሪ ሲጠፋ ሁሉም በመሰለው ስሜቱን ተከትሎ ይነጉዳል:: የሚሄድበትንም መድርሻውንም ሳያውቅ እንዲሁ እንደመሰለው ይጓዛል:: ፍርድ በመንጋ ይሆናል፡፡ ግብረ ገብነት ሲጎድል ሕገ ወጥነት ይሰፍናል::

[63] In just 100 days in 1994, about 800,000 people were slaughtered in Rwanda by ethnic Hutu extremists. Neighbours killed neighbours and some husbands even killed their Tutsi wives, saying they would be killed if they refused. At the time, often with machetes which most Rwandans kept around the house.https://www.bbc.com/news/world-africa-26875506

የሰላም መጥፋትና ስርዓት አልበኝነት ልዩነት አላቸው:: ስርዓት አልበኝነት (anarchy or a state of lawlessness or political disorder due to the absence of governmental authority) የሚለው ሲሆን የመዝገበ ቃላት ትርጉሙ[64]: እሳቤው ግን ብዙ ጉዳዮችን ያካተተና ሰፊ ነው:: ፖለቲካውንም፥ ሃይማኖቱንም፥ ማኅበራዊውንም የሚመለከት እንደሆነ ነው የሚተነትነው::: ስርዓት አልበኝነት ከሕገ አራዊት የከፋ ነው:: ማንም ማንንም አያድንም:: ማንም ማንን አይታደግም:: አሸናፊም ተሸናፊም አይኖርም:: ብቻ መጠፋፋት ነው የሚሆነው::

“ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር” ሲል ምን ማለት እንደሆነ ማጤን የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው:: እንዲህ ባለ ጊዜ ነውር የሚባል ነገር አይኖርም:: እንዲህ ባለ ጊዜ የሚገስጽ፣ እረ ይሄ ጸያፍ ነገር ነው የሚል ሽማግሌም ይጠፋል:: እንዲህ ባለ ጊዜ ኃጢአት እንደ ጽድቅ ሲፈጸም ማየት እንግዳ ነገር ላይሆን ይችላል:: ምክንያቱም ሁሉም እንደመሰለው ስለሚፈጽመው:: በጎ ልማድና ባህሉን፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር፣ የመንግሥት ሕግ ተዘንግቶ ሁሉም በስሜቱ በመሰለው መንገድ ቁጣና ንዴት በተሞላበት አካሄድ የሚሄድበት መንገድ ነው እንዲህ ዐይነቱ መንገድ:: ትክክል የሆነው ሳይሆን ሰው ሁሉ ለራሱ እንደተመቸው እንደመሰለው የመሰለውን ያለ ከልካይ ሲያደርግ የሚከሠተውንም ማሰብ ይቻላል::

በመንጋ ማሰብ ሲያይልም ወደ ልብ መመለስ የሚቻለው ከብዙ ጥፋት በኋላ ሊሆን ይችላል:: እንደ እንስሳት ያለ ሕግና ሥርዓት በደቦ የሚደረግ ነገር ለጊዜው ማሸነፍ ቢመስልም ጸጸቱ ግን ለዘላለም አይጠፋም:: ዛሬ በዓለም ላይ ግብረ ገብነት የጎደላቸው መሪዎች በፈጸሙት እልቂት ስንት ሕዝቦች ናቸው አንገታቸውን ቀና አድርገው ለመሄድ የሚቸገሩ?

[64] Varaities of Anarchisim: Political Anarchsim, Religious Anarchism, Theoretical Anarchisim, Applied Anarchsims ..https://plato.stanford.edu/entries/anarchism/

9.5 የሥነ ምግባር (የሞራል) ዝቅጠት

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው የሞራል ዝቅጠት የሚባለው ጉዳይ ነው:: የሞራል ዝቅጠት ገጥሞናል የሚባለውን ያህል አይ አይደለም የተጋነነ አገላለጽ ነው የሚል አሳብ እየተነሣ ባለበት ዘመን፣ ምን ያህል ነው የወረድነው? እንዲህ ለምን ሆነ? የሚለውን በበቂ ለመመለስ ጉዳዩ ሰፊና የባለሙያ ጥናትና ምርምር የሚፈልግ ነው:: ቢሆንም የሥነ ምግባር ማሽቆልቆል መታየቱና ይህም ለተከሠቱት አገራዊ ችግሮችና የአመራር ውድቀት የራሱ አስተዋጽዖ እንዳለው ታሳቢ ማድረግ ይቻላል:: የችግሩ መጠንና ጥልቀት ምን ያህል ነው? የሚለውን ለመረዳት ግን የሚከተሉትን እና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በሰፊው መመርመር ያስፈልጋል:: መካካድ የበዛበት፣ ሰው በቃሉ የማይገኝበት፣ አደራ የሚበላበት፣ ቃል ኪዳን የረከሰበት፣ ራስ ወዳድነት፣ እኔን ብቻ ይድላኝ ማለት በዝቶ የሚታይበት በአሳብ ተነጋግሮ መግባባት የማይቻልበት፣ ችግርን ለመፍታት መግባባት ሳይሆን ጉልበት ቅድሚያ የሚሰጥበት፣ አንዱ የሚናገረውን ሌላው የማያዳምጥበት፣ አንዱ ሌላውን የሚነቅፍበት ዘመን ላይ ስላለን የሥነ ምግባር ማሽቆልቆል ለማጋጠሙ ማሳያ ሊሆን ይችላል::

ለሥልጣን በሚደረግ ሽኩቻ የእርስ በርስ መተላለቅ ማቆም ካለመቻሉ የተነሣ፣ በመገዳደል ታሪክ በዓለም ላይ ከመታወቅ የከፋስ ምን ነገር አለ? በዚህ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን አሰቃቂ የእስር ሰቆቃ የደረሰባቸው፣ በግፍ ሀብት ንብረታቸውን የተነጠቁ፣ ፍርድ የተዛባባቸው ሰዎችስ ቁጥራቸው ስንት ነው? በእምነት ስም ቤተ ክርስቲያንና መስጊን ከማቃጠል የከፋ በደል ምን ይኖር ይሆን? ሱስና አደንዛዥ ዕፅ ቤቱን ያልጎበኘውስ ስንት ቤተሰብ ይገኝ ይሆን? ክፉ ቃል ነውር መሆኑ የተረሳበት ዘመን፣ ስድብ ፋሽን የሆነበት፣ ሚዲያው ለጥቅም ሳይሆን ክፉ ቃላትን ለመውራወሪያ፣ ለመበሻሸቂያ አንዱ ሌላውን ለማዋረድ፣ ለማንቋሸሽ የሚጠቀምበት ሰው ምን ያህል ነው? እነዚህና የመሳሰሉ ጥያቄዎች ሲጠየቁ የሚገኘው መልስ የችግሩን መጠን ሊያሳይ ይቻላል:: ይህ ሁሉ ለምን ሆነ? የሚለው ግን ጥልቅ ጥናትንና ውይይትን የሚፈልግ ነው::

በአጠቃላይ የሞራል ዝቅጠትም ተብሎ ተጠራ፤ የሞራል ማሽቆልቆል ወይም የሥነ ምግባር መጉደል፤ አደጋው ምን ያህል ነው? የሚለውን ግን እነዚህን እና የመሳሰሉ ሁኔታዎችን ከግምት እያስገቡ መፈተሽ አስፈላጊ የሚሆንበት ዘመን ላይ ነን ማለት ይቻላል::

9.6 ሃይማኖተኛ ሕዝብ

የሥነ ምግባር ችግር ጎልቶ በሚታይበት ጊዜ በቀዳሚነት ሊነሳ የሚችለው እንዴት ሃይማኖተኛ ሕዝብና በሃይምኖት አገር ይህ ሊሆን ይችላል? የሚል ነው:: የእምነት ሰው መሆንና ግብረ ገብነት እጅግ የተቆራኙ መሆናቸው የሚጠበቅ ቢሆንም ይህ ሳይሆን የሚገኝበት አጋጣሚ ግን ቀላል የሚባል አይደለም::

በዓለም ላይ ሃይማኖተኛ ሕዝብ በመባል መኩራት የሚያስፈልግ ቢሆን ሊያኮራ የሚገባ ታሪክ እንደ ኢትዮጵያ ያለ አገር ብዙም አይገኝም ማለት ይቻላል። ክክርስትናው በኋላ ቢቆጠር እንኳ አብዛኛው አገር ሃይማኖቱ በቅኝ ገዥዎች ተጽእኖ ሲደረግበት፣ የኢትዮጵያን ግን መንካት አልተቻለም:: የዓለም የሃይማኖት ታሪክ በፖለቲካ ሲታመስ የኢትዮጵያ ግን ልዩ ነው:: ደም ሳይፈስ ታላላቆቹን ሃይማኖቶች በሰላም ያስተናገደ አገር ከኢትዮጵያ ሌላስ ማንን መጥቀስ ይቻላል? ጥንታዊነትም በራሱም ኩራት ብቻ ሳይሆን ብዙዎች የሚቀኑበት ትልቅ ሀብት ነው:: በዓለም ታሪክ ክርስቲያን ሙስሊሙ በመቻቻል ብቻ ሳይሆን በመፈቃቀር ለዘመናት የሚኖርበት አገር እንደ ኢትዮጵያስ የት ማግኘት ይቻል ይሆን?

ታዲያ እንዲህ በሚያኮራው ታሪክ ላይ አሁን የግብረ ገብነት ጉድለት ጎልቶ ከታየ ይህን ወርቃማ ታሪክ ጥላሸት መቀባቱ የሚጠበቅ ነው:: አንድ አገር ብዙ አማኞች ስላሉበት ብቻ፣ ብዙ ቤተ እምነቶች ስለሚገኙበት ብቻ ሃይማኖተኛ ሕዝብ አያሰኝም:: ሃይማኖተኛ ሕዝብ በፍሬው ይታወቃል:: ሃይማኖተኛ ሕዝብ በተግባር የተፈተነ ነው:: ሃይማኖተኛ ሕዝብ ፈሪሃ እግዚአብሔር ከሌላቸው፣ ፈጣሪን ከማያውቁ ወይም ፈጣሪን ከማያምኑ ሰዎች በበጎ አስተሳሰብም ይሁን በበጎ ግብር የተለየ ነው:: ሃይማኖተኛ

ሕዝብ እርስ በርስ ባለው ሰላም፣ እርስ በርስ ባለው ፍቅር፣ እርስ በርስ ባለው መከባበር፣ እርስ በርስ ባለው መረዳዳትና መተሳሰብ፣ እርስ በርስ ባለው መተማመን እና የአሳብ አንድነት ሁሉ ይታወቃል:: "የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር::" ተብሎ እንደተጻፈ የአብርሃምን ግብር መያዝ ካልተቻለም የአብርሃም ልጅነት "ልጆች ነን " በማለት ብቻ አይገኝም:: (ዮሐ 8፥39)

❁ ሃይማኖተኛ ሕዝብ በምን ይታወቃል?

1ኛ. አንደኛው መለያ በሚያፈራው ፍሬ ነው:: ሃይማኖተኛ ሕዝብ መሆናችን መገዳደልን፣ ሐሰት መናገርን፣ በሐሰት መመስከርን፣ የሌላውን መመኘት፣ ቅናትና በቀልን አድመኛነትን እና ዘረኝነትን ካላስቀረልን፣ አብሮ ካላስኖረን፣ ችግራችንን በሰላም መፍታት ካላስቻለን፣ ይቅርታ ማድረግን ካላስተማረን ጥቅሙ ምኑ ላይ ነው? መገፋፋትን ሳይሆን መከባበርን፣ ጥልን ሳይሆን ፍቅርን ካልሰጠን መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬን ሊያፈራ አይችልምና ሃይማኖተኛ ሕዝብ መባላችንም ጥያቄ ውስጥ መግባቱ አይቀርም:: በእኛ ምክንያት ሃይማኖታችን መነቀፍን፣ በእኛ ምክንያት የእግዚአብሔር ስም መሰደብን ሊያመጣም ይቻላል:: ምግባረ ብልሹነት ከነገሠ ጥልና ክርክር፣ መጠላላትና መገፋፋት፣ መለያየትና መካካድ ከበዛ ሃይማኖት ባለበት አገር ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ማሰኘቱም አይቀርም:: የእምነት መለያዬት ቢኖርም ሰው እንደእየእምነቱ መጠን በጎ ፍሬ እንዲያፈራ የማይሰብክ፥ ጥረት የማያደርግ እምነትስ ወዴት አለ?

"ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ:: ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፤ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል:: መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፣ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም" የሚለው የወንጌል ቃል የማያወላዳ መልስ ነው:: (ማቴ 7፥16-18) ፍሬው ፍቅር፣ ሰላም፣ መከባበር፣ ትዕግሥት፣ መቻቻል ከሆነ የሃይማኖት ሰዎች ናቸው እንደሚያሰኘው ሁሉ ፍሬው በተቃራኒው ከሆነም እንዴት የሃይማኖት ሰዎች ሊባሉ ይችላሉ? ማሰኘቱም ግድ ነው::

ዛሬ የስድብ መዓት በየአደባባዩ፣ በየሚዲያው እምነት አለኝ በሚለውም በማይለውም ተማርኩ በሚለውም ተርታ ሰው በሚባለውም በሁሉም በዝቶ ሲነገር መስማት እንግዳ ነገር አይደለም:: ያም ሆኖ የሃይማኖት ሰው ነኝ ማለቱን አይረሳውም:: "አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው::" እንደተባለ ከንቱ አምልኮ ነው የሚሆነው:: (ያዕ. 1፥26) ማስተዋል ከተቻለ ከንቱ አምልኮ የሚባል ነገር አለ:: የእምነት ሰው መምሰልና በእግር መመላለስ አይደለም ቁም ነገሩ::

ሃይማኖተኛ ሕዝብና ሃይማኖተኛ በመባል በሚታወቅ አገር ሃይማኖት የሌለው ሰው ሊፈጽመው እንኳ የሚከብዱ ጸያፍና አሳፋሪ ነገሮች መሠራታቸው የአደባባይ ምስጢር ነው:: በሃይማኖት አገር በቀይና በነጭ ሽብር ወንድማማቾች እንዴት ሊጨራረሱ ቻሉ? ወንድም ወንድሙን ገድሎ እንደጀገና የሚፎክርባት አገር እንዴት ልትሆን ቻለች? ወላጆች በግፍ የተገድሉ ልጆቻቸውን አስከሬን በክብር አልቅሰው ለመቅበር የሚከለክል ትውልድ ከየት መጣ? መካካድ እንዴት እንዲህ ሊበዛ ቻለ? መቻቻል እንዴት ጠፋ? ትውልዱስ በተስፋ የተሻለ አገርን ለመገንባት ጥረት ከማድረግ ይልቅ እንዴት በጫት፣ በመጠጥ እና በዕፅ የሚደነዝዘው ቁጥር በየጊዜው ሊጨመር ቻለ? የሃይማኖት መሪዎች ሳይቀሩ በጥቅም ወይም በፍርሃት እንዴት አደርባይ ሊሆኑ ቻሉ? የሚል ጥያቄ መነሣቱ የሚጠበቅ ነው::

ሌላው ቢቀር ካለፈ ስሕተት ተምሮ የመሻሻል ተስፋም የሚታይ አይመስልም:: ወንድም ወንድሙን በአሳብ ልዩነት ወይም ለሥልጣን ሲል መግደል የሚያቆምበት ጊዜ መቼ ነው? ልዩነትን በጉልበት ሳይሆን በአሳብ ልዕልና፣ በይቅርታ፣ በምሕረት መፍታት የሚጀምረውስ ምን ቢሆን ነው? የአሳብ ልዩነትን በፍቅር፣ በትዕግሥትና፣ በመቻቻል ማስተናገድ የሚቻለውስ ምን ቢሆን ነው?

2ኛ. ሁለተኛው እምነት አለን የሚሉ ሰዎች እምነት ከሌላቸው ሰዎች በሥነ ምግባር የማይሻሉ ከሆነ፤ የሃይማኖት ትርጉም ጥያቄ ውስጥ ይገባል የሚለው ነው::: እምነት ካለ በሥራ ይገለጣል:: እምነትን በሥራ

መግለጽ ካልተቻለ፣ እምነት አለኝ የሚል ሰው እምነት ከሌለው ሰው የተሻለ ሥራን መሥራት ካልቻለ የእምነት ትርጉሙስ ምን ሊሆን ነው? “ወንድሞቼ ሆይ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?” እንዲል። (ያዕ. 2፥26) እምነት ካለ በሥራ ሊገለጽ ግድ ነውና። በሥነ ምግባር የማይገለጽ እምነት አለኝ የሚባል ከሆነ እምነቱ በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሳይሆን እንዲሁ በልማድ፣ ለታይታ፣ ለማኅበራዊ ሕይወት ሲባል ብቻ የሚደረግ መመላስ ነው ሊያሰኝም ይችላል። እምነት በሥራ ሊገለጽ የሚችል ካልሆነ፣ አምናለሁ እያሉ ከእምነት ሰዎች የሚጠበቅ በጎ ምግባር ሲጠፋ እንደተጻፈ “እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ ነው”።

የሚጾመውን ያህል፣ የሚጸለየውን ያህል፣ የሚዘመረውን ያህል፣ ቤተ አምልኮ የመመላለሱን ያህል በጎ ምግባር ከሌለ “ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው” እንደተባለው መመላለሱ የልማድ ብቻ ነው የሚሆነውም። (ማቴ. 15፥8) አፍ ምስጋናን እያቀረበ ልብ በተቃራኒው ያለውን ክፋት ሲሠራ የሚገኝበት ጊዜ ብዙ ነውና።

የደጉ ሳምራዊ ታሪክ የተነገረውም እንዲህ እምነታቸው በልማድ በመመላለስ ወይም በማስመሰል ብቻ የሚኖሩ ሰዎች ስላሉ ነው። የተግባር ሰው በመሆኑ ነው ደጉን ሳምራዊ ደግ ያሰኘው። እምነት አለን የሚሉቱ አዘኔታቸውን ከንፈር በመምጠጥ ብቻ ሲገልጹ የተግባር ሰው የሆነው ደጉ ሳምራዊ ግን በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ረዳት ለሌለው ያ ሰው በሆነው ጉዳት ሁሉ አዘነለት። የእምነት ሰው እንደነበረው እንደ ሌዋዊው ገለል ብሎ አላለፈውም። ቀርቦ ዘይትና የወይን ጠጅ በቁስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው፤ በራሱ አህያም ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማደሪያ ወሰደው፤ ጠበቀው እንጂ። በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና “ጠብቀው ከዚህም በላይ የምትከስረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ” አለ እንጂ ከንፈሩን መጦ ገለል ብሎም አላለፈውም። (ሉቃ 10፥30-37)

ከእምነት ጋር የተግባር ሰው መሆን ሲቻል እንዲህ ነው:: ለእምነት ቀረብን ከሚሉ ሰዎች ይልቅ ብዙም በማይመጻደቁ ሰዎች ዘንድ ሥነ ምግባር በዝቶ የሚታየው ከላይ እንዲህ እንደሌላዊውና ሳምራዊው ስለሚሆን ሊሆን ይችላልም፡፡ ደጉ ሳምራዊ በደል የደረሰበትን መንገደኛ ባያውቀውም፣ ወገኑ ባይሆንም፣ ወገኔ ካልሆነ ምን ችገረኝም አላለም:: የእምነት ሰው እንደ ደጉ ሳምራዊ ያቅሙን ያደርጋል እንጂ ማንም ይሁን ማንም በደል የደረሰበትን ሰው ገለል ብሎም አያልፍም::

3ኛ. ሦስተኛው መመዘኛ ሊሆን የሚችለው ፍቅር ነው:: የእምነት ሰው ነኝ ብሎ ጥላቻን የሚሰብክ ሰው በየትኛው መለኪያ የእምነት ሰው ሊባል ይችላል? ምን ዐይነት እምነት? ሃይማኖት አለኝ በአንድ ፈጣሪ አምናለሁ የሚል ሰው ክቡር የሆነውን ንጹሕ ሰው በግፍና በጭካኔ የሚገድል ከሆነ እንዲህ ዐይነቱ ሰው የሚከተለው ፍትሐዊውንና የፍቅር አምላክን ሊሆን እንዴት ይችላል? ፍቅርን ከመስበክ መለያየትንና ጠብን የሚዘራ ሰውም እንዲሁ:: "እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፣ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ፡፡" (ዮሐ.13፥35) የሚለው የመጽሐፍ ቃል የሚያሳዬንም ይህንን እውነታ ነው:: ሰው እምነቱ ቢለያይም ፈጣሪን መፍራት ካለ በፍቅር ይገለጻል:: ንጹሓንን በመግደል ለፍትሕ መቆም፣ ንጹሓንን በማሳደድ ለወገን ተቆርቋሪ መሆን አይቻልም:: በተግባር ተግዳሮቱ ብዙ ቢሆንም ፍቅርን የማይሰብክ እምነትስ ከወዴት ይገኛል? ይህ ሃይማኖት ስላለ ብቻም አይደለም:: እምነት የሌለው ሰው ቢሆንም ትርጉም የሚሰጠው እንዲህ ሲሆን ነው:: እምነት ለሌለው ሰውም ቢሆን እንደ ሰው ማሰብ ከተቻለ ንጹሓንን በግፍ መግደል ምን ሊባል ይችላል?

4ኛ. ሥነ ምግባር ትርጉም የሚኖረው ሙሉ (integral)[65] ሲሆን ነው የሚለው አራተኛው መመዘኛ ሊሆን ይችላል:: አንድ የሚነገር ተረት አለ:: ሰውዬው ባላጋራዬ የሚለውን ሰው ሊገድል እየፎከረ መሳሪያውን

[65] Integrity is defined, in the Oxford Dictionary, as the quality of being honest and having strong moral principles, the state of being whole and not divided. The word "integrity" derives from the Latin integritas or integer, which means intact or whole. http://globalvisioninstitute.org/integrity-wholeness-essential/1241

ይዞ ከቤቱ በጠዋቱ ሲወጣ ሚስቱ ባይሆን ቁርስ በልተህ ውጣ እንጂ አለችው:: ቀኑ ጾም ነበርና " አይ ጾም ነው አልበላም" አለ ይባላል:: ሰው ለመግደል እየወጣ ጦሙን ግን ልማድ ሆኖበታልና አልረሳውም:: ተመሳሳይ ታሪክ ብዙ ጊዜ ሲደገም ይታያል:: መቼም እየጸሙ እየጸለዩ ከእግዚአብሔር ቤት መስረቅ የሞራል ዝቅጠት ነው:: በአንድ በኩል እየጸሙ እየጸለዩ በሌላ በኩል ሰው ማፈናቀል፣ ሰው መግደል የባሰ በደል ነው:: "ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ?" እንደተባለም በአንድ ራስ ሁለት ምላስ ነው የሚሆነው::

"ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፣ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፣ አታመንዝር ያለው ደግሞ:: አትግደል ብሎአልና:: ባታመነዝርም፣ ነገር ግን ብትገድል፣ ሕግን ተላላፊ ሆነሃል::" እንዲል ቃሉ የማያሻማ ነው:: (ያዕ. 2፥10-11) ጎደሎ እምነት ዋጋ ቢስ ነው የሚሆነው:: አንካሳ እምነትም አይጠቅምም:: ግማሽ ማመን ግማሽ አለማመንም አይቻልም:: ግማሽ ብርሃን፣ ግማሽ ጨለማ አብሮ የሚሄድ ነገር አይደለምም:: ብርሃን ካለ ጨለማ ቦታ ይለቃል፣ ብርሃኑ ሲጠፋ ጨለማ መንገሡ ግድ ነውና::

"በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ:: በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር:: እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው::" የሚል ቃል በመጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል:: (ራእ 3፥15) ለብታ መሀል ሰፋሪ ነው፤ ሙቅም አይደለም፥ ቀዝቃዛም አይደለም:: እንዲህ ዐይነት የለብታ ሕይወትም የተለመደ ነው:: የእምነት ሰው እየተባለ ምግባሩ ካማያምኑ አንሶ የሚገኝበት፤ የሚናገረውን፣ የሚሰብከውን በተግባር የማይኖርበት ሕይወትን ነው የለብታ ሕይወት የሚያመለክተው:: ጥቅም ሲገኝ የሃይማኖት ሰው፣ ፈተና ሲመጣ ደግሞ በተቃራኒው መሰለፍ ሲኖር፣ ከአንዱም ሳይኖርበት ሁሉም ቦታ አለሁበት የሚል፣ ሁሉ አማራሽ የሆነው ሲበዛ ነው የለብታ ሕይወት የሚያሰኘው:: ለሰው ጻድቅ መስሎ መታየት፣ በሰው ፊት መልአክ መስሎ በተግባር ግን አንሶ ሲገኝ፣ ግብዝነት ሲጠናወት ነው የለብታ ሕይወት የሚያሰኘው:: እንዲህ ዐይነት የሁለት አገር ሰው ቁጥሩ

ስንት ይሆን? ለሚለው ማስመሰል ስለሚበዛበት ራሱ ግለሰቡና ፈጣሪ ብቻ ነው የሚያውቀው::

9.7 ሥነ ምግባርን የመገንባት ድርሻ

ሥነ ምግባርን የመገንባት ሓላፊነት ለተወሰኑ አካላት ብቻ የሚሰጥ አይደለም:: ሰው የቤተሰብ ውጤት ነው፤ የጎረቤት ውጤት ነው፤ የማኅበረሰብ ውጤት ነው:: ጎረቤት ሁሉ የወላጅ ያህል ላልወለደው ልጅ ተቆርቋሪ ሲሆንና ሳይሆን የሚኖረውን ግብረ ገብነት ማሰብ ይቻላል:: ሰው የትምህርት ቤት ውጤት ነው:: ሰው አካባቢውን ይመስላል፤ ሰው ጓደኞቹን ይመስላል:: ሰው እምነቱን ይመስላል:: ሥነ ምግባር የመንግሥት ፖሊሲም ውጤት ነው:: ግብረ ገብነት የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ነው የሚባለው:: በተለይ ልጆች በጓደኞቻቸው የሚያገኛውን ተጽእኖ እና የመሳሰለው በብዙ ጥናቶች ነው በየጊዜው የሚጠናው[66]:: በማይመች አካሄድ አትጠመዱ በሚልና በሌላም አገላለጽ በቅዱስ መጽሐፍ ሰፊ ሽፋን ከተሰጣቸው መካከልም ከክፉዎች ተጽእኖ ራስን መጠበቅን የተመከተ ነው:: “ ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ምን ተምራ መጣች” ነው ብሂሉም::

ለሥነ ምግባር መላሸቅ የማኅበረሰብ ድርሻ ምንድን ነው? የመሪዎችስ? የሚለውን በባለሙያዎችና ታሪክ አጥኝዎች ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ሕዝብ መሪዎችን ይወልዳልና በመሪዎች የሚታይ የሥነ ምግባር ጉደለት መሪዎቹ ከወጡበት ማኅበረሰብ ጉድለት ቢኖር ነው ያሰኛል:: ሕዝብም መሪዎችን ይከተላልና ችግሩ የሕዝቡም ጭምር ቢሆንም መሪዎች ግን የራሳቸውን ድርሻ መውሰዳቸው ግን አይቀርም:: በጎም ይሁን ክፉ ከመሪዎቹ ያየውን ምግባር ትውልድ ተቀብሎ ይሠራዋል:: የሃይማኖት መሪዎች፣ የማኅበረሰብ መሪዎች፣ የወጣት መሪዎች፣ ልሂቃን፣ የተቋማት መሪዎች፣ ታዋቂ ሰዎች፣

66 Peer Influences on Adolescent Decision Making
https://www.ncbi.nlm.nih.gov/pmc/articles/PMC4276317/

የጥበብ ሰዎች እነዚህ ሁሉ መሪዎች ናቸውና:: መሪ ማለት ተከታይ ያለው ነውና መደበኛ ሥልጣን ቢኖረውም ባይኖረውም ተከታይ ያለው ሁሉ መሪ ነውና:: የሥነ ምግባር መሪ ሲገኝ ሕዝቡም መሪውን ይከተላልና ሥነ ምግባር ያለው ዜጋን ለመፍጠር እድል ይሰጣል:: ሥነ ምግባር ያለው መሪ ሲጠፋም የሥነ ምግባር ዝቅጠቱ የዚያኑ ያህል የከፋ ነው የሚሆነው:: ከዚህም ሌላ መሪዎች በሚያውጧቸውና በሚያስፈጽሟቸው ሕጎችና ፖሊሲዎች ሥነ ምግባርን መገንባት፣ ሥነ ምግባርን ማፍረስ እንደሚችሉም በየጊዜው የሚታይ እውነት ነው:: ትውልድ በጫት እንዳይደነዝዝ፣ በመጠጥና በአደንዛዥ ዕፅ እንዳይጠፋ መሪዎች ትልቅ ሓላፊነትም ግዴታም አለባቸው:: አውቀውም ይሁን በግዴለሽነት ይህን ግዴታቸውን በጊዜውና በአግባቡ መወጣት ሳይችሉ ሲቀር ግን የሚያደርሰው ጥፋት ጉዳቱ ለሁሉም የሚተርፍ መሆኑም አጠያያቂ አይሆንም::

ሥነ ምግባር ሲጎድል የሚጎዳውም ሁሉም ነው:: መንግሥት ይጎዳል፤ ነጋዴው ይጎዳል፤ ሕዝብ ይጎዳል፣ አገር ይጎዳል:: በሰላም ወጥቶ መመለስ የሚቻለው ሕግ የሚያስከብር አካል ስላለ ብቻ ሳይሆን ለሕግ የሚገዛ ማኅበረሰብም ሲኖር ነውና:: ሥነ ምግባር በሌለበት ልማትም ትርጉም የለውም:: ስንት ዓመት የተደከመበት ልማት፣ ስንት ዓመት የተደከመበት ሀብት በአንድ ሌሊት ሲወድም ማየት የተለመደ ሆኗልና:: ሌላው ቀርቶ ግብረ ገብነት ሲጠፋ በሃይማኖት ተቻችሎ በሰላም አምልኮን መፈጸም የሚቻልበት እድል እንኳ ይጠፋል:: ግብረ ገብነት በሌለበት አምራች ዜጋን ማግኘትም ይቸግራል:: ሥነ ምግባርን የመገንባት ሓላፊነት የሁሉም ድርሻ የሚሆንበት አንዱ ምክንያትም ይህ ነው::

ሥነ ምግባር በቤተ እምነት ብቻ የሚገነባም አይሆንም:: መልካም ዜጋን መፍጠር የሚቻለው ሁሉም ሲሠራ ነው:: በሁሉም ዘርፍ ያሉ መሪዎች አስተዋጽዖ ሲኖር ነው በሥነ ምግባር የታነጸ ዜጋን ለመገንባት የሚቻለው:: በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት፣ በጎረቤት፣ በማኅበረሰብ፣ በእምነት ተቋማት ያልተገነባ ሥነ ምግባር ወዴትም ሊገኝ አይችልም:: “መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ

ያደርጋል።" እንደተባለ መልካም ቤተሰብ፣ መልካም ጎረቤት፣ መልካም ባልንጀራ፣ መልካም ማኅበረሰብ ከሌለ መልካም ዜጋንና መልካም መሪን ማፍራት ይከብዳል:: (ማቴ 7፥17) በለስ ወይራን ወይም ወይን በለስን ልታፈራ አትችልምና:: ከጨው ውኃም ጣፋጭ ውኃ አይወጣምም::

አንድ ትውልድ እየጠፋ ነው በሚባልበት ሁኔታ በመንግሥት፣ በበጎ አድራጎት ተቋማት፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በባለ ሀብቶች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በማኅበረሰብ፣ በጎረቤት፣ በእድሩና በሌላውም ማኅበራዊ ተቋም እየተሠራ የነበረው፣ አሁን ችግሩ አፍጥጦ ከመጣ ወዲህ እንኳ እየተሠራ ያለው ሥራ ምን ይመስላል? የሚለው ነው አንገብጋቢው ጉዳይ:: ጥያቄው ሥነ ምግባርን በመገንባት፣ መልካም ዜጋን ለመቅረጽ እየተሠራ ያለው ሥራ ምነው እንዲህ አናሳ ሆነ? የሚለው ነው:: ሳይሠራ መልካም ዜጋን፣ መልካም መሪን አጣን ቢባል ያልዘራነውን ለማጨድ የመመኘት ያህል ነው የሚሆነው::

ሥነ ምግባር በየተቋማቱ እንዲጎለብት ማድረግም በሙስና በመልካም አስተዳደር እጦት የሚደርስ በደልን እና የሀብት መባከንን ለመከላከል ያለውን ጠቀሜታና የሚኖረው ከፍ ያለ ሚናም የሚያከራክር አይደለም:: ችግሩ ያለው ሥነ ምግባርን ለማጎልበት አስተዋጾ የሚኖራቸውን ተቋማት በየደረጃው መገንባት እንዴት ይቻላል? ሥራዎችን እንዴት ማቀናጀት ይገባል? የሚለው የአረዳድ ወይም የአፈጻጸም ዓቅም ላይ ነው:: በየተቋማቱ በዚህ ረገድ ዘላቂና ወጥነት ያለው ሥራን በጀት መድቦ ቢሠራበት የሚያዋጣ እንጂ የሚያከስር ሊሆን አይችልም:: በሽታውን ከማከም በሽታን መከላከል አዋጭ መንገድ ነውና:: በተመሳሳይ የሃይማኖት ተቋማትም ቢሆኑ በጋራ ወይም በተናጥል የሥነ ምግባርን ትምህርት በመገናኛ ብዙኃን የሚያቀርቡበትን መንገድ ማመቻቸትና ማበረታታት ቢቻልም የሚጠቅም ነው:: ሥነ ምግባርን ማስተማር እምነትን ማስተማር የግድ መሆን የለበትምና:: በጥንቃቄ ከተሠራበት ለሁሉም በሚመች መልኩ መጥኖ የሚቀርብበትን መንገድ በጥናት ላይ ተመሥርቶ ማዘጋጀት የማይቻልበት ምክንያት አይኖርም::

መደበኛውን ትምህርት ከሃይማኖት ጋር መቀላቀል ችግሮች አሉት ቢባልም ለሁሉም የጋራ የሆኑ የሥነ ምግባር መርሆችን ግን በሥነ ምግባር ትምህርቶች ማካተት የሚያስከትለው ችግር ምን ሊሆን ይችላል? በብዙ አገሮች ያለው ተሞክሮ ይህንን የመሰለ ነው:: መልካም ዜጋን ለማፍራት አትዋሽ፣ አትስረቅ፣ የባልንጀራህን የሆነውን ሁሉ አትመኝ፣ አትግደል፣ እናትና አባትህን አክብር፣ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ፣አትስከር፣ አትዝረፍ፤ ጠብንና መለያዬትን አትዝራ፤ የሰላም ሰው ሁን፣ የይቅርታ ሰው ሁን፣ ሩኅሩኅና አዛኝ ሁን፤ ቁጣ፣ ንዴት፣ መራርነት እና የመሳሰሉትን አርቅ የሚሉት መርሆዎች ምንጫቸው የትም ይሁን የት በሥነ ምግባር ትምህርቶች በሰፊው መሰጠት ቢቻል መልካም ዜጋን ለመፍጠር የሚኖረውን አስተዋጽዖ ጠቃሚ መሆኑም ብዙም የሚያከራክር አይሆንም::

የግብረ ገብ ትምህርት በኢትዮጵያ የነበረውን በጎ አስተዋጾ እንደገና መፈተሽና ለዘመኑ በሚስማማ መልኩ ተስተካክሎ በትምህርት ቤቶች እንዲሰጥ ቢደረግ ግብረ ገብነትን ለማስፋፋት የሚኖረው ሚና ጉልህ በሆነ ነበር:: በብዙ አገሮች በሃይማኖት ተቋማት ባለቤትነት የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች አሁንም ድረስ እምነት ሳይለዩ መሠረታዊ የሚባሉ ግብረ ገብነትን ያስተምራሉ:: በተመሳሳይ በተወሰኑ አገሮች በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የግብረ ገብነት ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን እንዲህ ባሉ አገሮች ልጆች መሠረታዊ የሚባሉ የሞራል እሴቶችን ከልጅነታቸው እንዲለማመዱና እንዲዋሀዳቸውም ይደረጋል:: በለጋ ዕድሜያቸው ውሸት መናገር፣ ዘረኝነት፣ ጥላቻ፣ ስድብ ወዘተ ጸያፍ ነገር መሆኑን ይማሩታል:: አንዱ የሌላውን ባህል እንዲያደንቅ እድል ይፈጠራል፣ በየዕለቱ ይሰበካል:: መስረቅ፣ ማታለል እንግዳ ነገር ነው:: ይህ ሁሉ እንደ ባህል ሆኖ ያድግና በአገር ደረጃ እሴትነቱ ደርጅቶ የዓለም ሕዝብ ተሰባስቦ በሰላም ለመኖር ካስቻላቸው ነገር አንዱም ይህ ሊሆን ይችላል:: የሃይማኖት ተቋማት ተጽዕኗቸው እየተዳከመ ነው በሚባልበት ጊዜ እንኳ በትምህርት ቤት፣ በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብ ደረጃ መሠረታዊ የሞራል እሴቶችን አጠንክረው በተለያየ መንገድ ስለሚዘራና ስለሚንከባከቡት ፍሬ

አፍርቶ በአመዛኙ ግብረ ገብ ማኅበረሰብን መፍጠር አስችሏቸዋል[67]:: ከዚህ ሁሉ ጋር ሕጉም ያግዛቸዋል:: መጠጥ የዕድሜ ገድብ አለው:: የጾታ ግንኙነትም እንዲሁ:: ሁሉም ነገር ጥብቅ ነው:: በአደንዛዥ ዕፅ ከተያዙ ቅጣቱ ባልገባሁበት የሚያሰኝ ነው::

በአጠቃላይ

- ሥነ ምግባር የሚገነባው በየዘርፉ ያሉ መሪዎች ለነገው ተረካቢ ትውልድ በቃልና በኑሮ ምሳሌ መሆን ሲችሉ ነው::

- ታዋቂ ሰዎች ተከታያቸው ብዙ ነው:: አለባበሳቸው፣ ጸጉር አሠራራቸው፣ አነጋጋገራቸው እና የመሳሰለው ሁሉ ይኮረጃል:: በበጎ ምግባር ምሳሌ ሲሆኑ የሚከተላቸው የሚበዛውን ያህል በተቃራኒው ሲሄዱም የሚሳሳተው የዛኑ ያህል ነው:: ስለሆነም የበጎ ምግባር አምባሳደሮችን እንዴት ማብዛት ይቻላል? በሚል ታስቦ ቢሠራበት ለውጥ የሚመጣው እንዲህ ባለው መንገድ ሊሆን ይችላል::

- ሚዲያዎች ክፉ ክፉውን ከማጉላት በጎ በጎ ላይ ማተኮር ቢችሉ፣ መልካም ቤተሰብ የሚመሩትን፣ የተሳካ የትዳር ሕይወት ያላቸውን፣ የተሳካላቸውን መሪዎችን፣ ሰናይ ምግባር ያላቸው ወጣቶችን፣ የበጎ ፈቃድ አገልጋዮችን በአርአያነት ወደ አደባባይ እንዲወጡ ማድረግ ቢችሉ፤ የሕይወት ተሞክሯቸው የሚያስተምረው ከቃል በላይ እጅግ ብልጫ አለው::[68] እንዲህ

[67] …it is now central for both educators in schools and higher education to openly debate the issues of education for morals, ethics and citizenship in the community and their place in the curriculum , EDUcation for Values, :///C:/Users/wb242998/OneDrive%20-%20WBG/References/[Roy_Gardner]_Education_for_Values_Morals__Ethics(BookFi.org).pdf

[68] The vast scholarly work on the role of media in children's lives suggests that media (such as books, newspapers, magazines, television, radio, cinema, computers, Internet, mobile phones) serve today as one of the most central socializing agents, informing behaviours, attitudes and world views. https://www.unicef.org/cwc/files/CwC_Final_Nov-2011(1).pdf

ዐይነቱ ሥራ አሁንስ አይሠራም ወይ? የሚል አይደለም ጥያቄው:: ምን ያህል ታስቦበት፣ ተቀናጅቶና በአግባቡ ድጋፍ ተሰጥቶት በዘላቂነት ይሠራል የሚለው ነው ዋናው ቁምነገር::

- በፍቅር ለረጅም ዘመናት አብሮ የኖረ ሕዝብ፤ እንዲህ የሃይማኖት አገር ተብላ በምትታወቅ አገር፤ እስከ መገዳደል የሚያደርስ፣ እስከ ማፈናቀል የሚያደርስ ግጭት የተፈጠረው ከምን የተነሣ ነው? እርስ በርስ መጠላለፍን፣ ቅናትን፣ ምቀኝነትን፣ ቂምንና በቀል፣ ሱሱና ዝሙቱ እየበረከተ ትንሽ ትልቁን ማክበር እየጠፋ በሚሄድበት ሁኔታ ሥነ ምግባር እያደገ ሳይሆን እያሽቆለቆለ ለመሄዱ ጠቋሚ ነው:: ይህ ችግር እየተባባሰ የመጣው እንደየእምነቱ ከሃይማኖት መሪዎች ምን ቢጎድል ነው? ከሃይማኖት አስተምህሮው ምን ቢጎድል ነው? ከአማኙስ ምን ቢጎድል ነው? የሚሉትን በመፈተሽ ከቀደመው ወርቃማ ዘመን መማርና የጎደለውን ለማስተካከል ሰፊ ዘመቻ፣ ሰፊ ሥራ መሥራት ከተቻለም ለውጥ ሊመጣ ይችላል::

ሳይረፍድ ነው...

ሥነ ምግባር ያለውን ዜጋ መገንባት ግን እንዲህ እንደማፍረሱ ቀላል አይሆንም:: ማፍረስ ነው ቀላሉ:: "አንድ ሞኝ የተከለውን ሃምሳ ሊቃውንት አይነቅሉትም" እንደሚባለው ዛሬ ባለፉት ዘመናት የተዘራ የክፋት ዘር መንቀል እንዴት ከባድ እንደሆነ እየታየ ነው:: ተንኮለኛ መሪዎች መሠሪ ዐላማቸውን ለማስፈጸም የሚችል ሰው ሲያገኙ የማይነቀል ክፉ ተንኮልን ተክለው ያልፋሉ:: ቀደም ሲል የውጭ ቅኝ ገዥዎች በየሀገሩ ሕዝቡን በመከፋፈል ሲገዙ ሊኖሩ አስበው ሕዝቡን በዘር በሃይማኖት ለመከፋፈል በየደረሱበት የተለያዩ ተንኮል እንደሚዘሩ የታወቀ ነው:: ቅኝ ግዛት ከተነቀለ ከብዙ አሥርት ዓመታት በኋላም በሽታውን ከብዙ አገሮች ማጽዳት አቅቶ እስካሁን ወንድማማቾችን ሲያጫርስ እንደሚኖርም የአደባባይ ሚስጥር ነው::ሥነ ምግባርን መልሶ

መገንባት የሚቻለው ረጅም ጊዜ ነው[69]:: ትውልድን ማነጽ አድካሚ ሥራ ነው:: አንድ ትውልድ ከተበላሸ የተበላሸ ዘርን ነቅሎ አዲስ ዘር መዝራትን ይጠይቃልና ማጽዳቱም አዲሱን በአሮጌው ቦታ አብቅሎ ማሳደጉም እጅግ አድካሚ ሊሆን ይችላል:: በተለይ በዚህ ቴክኖሎጂ በረቀቀበት፣ ቁሳዊነትና የግል ነጻነት ፍልስፍናና ክህደት በሚበዛበት፣ የሱስ ተገዥነትና ጥገኝነት በተጠናወተበት ዓለም በሥነ ምግባር የታነጸ ዜጋን ማፍራት ቀላል የማይባል የተቀናጀና የማያቋርጥ ሥራን መፈለጉ ግድ ነው::

በተለይ" ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፣ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።" እንዲል ሳይረፍድ ነው መሥራት የሚያስፈልገው:: (ምሳ. 22፥6) በለጋ አእምሮ የተተከለ በጎ አስተሳሰብና አመለካከት አብሮ ያረጃል:: በለጋነት ማስተማርና ከረፈደ ለማስተማር መሞከር ውጤታማነቱ ከፍተኛ ልዩነት እንዳለው ሳይንሱም የሚናገረው ነው[70]:: ውጤታማ መሆን የሚቻለው ወቅቱ ሳያልፍ ሲዘራ ነው:: ወቅቱ ካለፈ የሚዘራ ዘር ፍሬ ሳያፈራ በአባባ ይቀራል ወይም አረሙ ብዙ ነው የሚሆነው:: አረም ከመንቀልም አረም እንዳይበቅል መከላከል ወይም መሬቱን በደንብ አለስልሶ መዝራት ይቀላል።። አረም ሲነቀል ስንዴውም አብሮ መነቀሉ አይቀርምና:: "አይ ከንቱ ድካም ነው፤ አሁን ይህንን ነገር መለውጥ ይቻላል ብላችሁ ነው? ተላልፎናል እኮ፥ አብሮ ያደገ ክፋትን ማጽዳት እንዴት ይቻላል?" የሚል ነገር መስማት የተለመደው ይህንን የሚያንጸባርቅ ሊሆን ይችላል:: እውነት ነው ቡቃዬው በለጋነቱ ሲኮተኮት ነው ለፍሬ የሚበቃው::

[69] Behavior change is hard. Successful change comes only in stages. How long it takes is an individual matter. Change is a process, not an event. https://www.health.harvard.edu/mind-and-mood/why-behavior-change-is-hard-and-why-you-should-keep-trying

[70] Main Developmental Characteristics Early Years (Birth through 6 years): Cognitive, Behavioural/Physical, Social/Emotional, Communication Needs, pp 18, https://www.unicef.org/cwc/files/CwC_Final_Nov-2011(1).pdf

ሥነ ምግባር ያለው ዜጋን መገንባት ከምንም ይቀድማል:: ክፉ ዘርም የማይፈወስ በሽታ እስከመሆን የሚደርሰው በለጋነት ዕድሜ ሲዘራ ነው:: ይህ ትውልድ ምን እያየ አደገ? ይህ ትውልድ ምን እየሰማ አደገ? ይህ ትውልድ ምን እያነበበ አደገ? ይህ ትውልድ ምን እየተማረ አደገ? መልሱ ከባድ አይሆንም:: ያፈራውን ፍሬ ማየት ነው:: ሰው ለልጆቹ እንዴት ጥላቻን ያስተምራል? እንዴት እንዲህ ካለ ብሔረሰብ ጋር እንዳትጋባ፤ እንዲህ ያሉት ሰዎችን በጠላትን ተመልከታቸው፤ እንዲህ ዐይነት ሰዎችን ጊዜ ስታገኝ ተበቀላቸው ብሎ ያስተምራል? የሚለው ጥያቄ ግን ቀላል መልስ የማይገኝለት ነው:: "ሰው የዘራውን ያንኑ ያጭዳል" ይሄን ማምለጥ አይቻልም:: የሚታጨደው እንክርዳድ ሲበዛ ግን ሁሉም ነው የሚጎዳው:: ከባድ ጥያቄ የሚሆነው በሽታውን አሁን መፈወስ ይቻላል ወይስ የማይፈወስ በሽታ ሆኖብናል? የሚለው ነው::

በአጠቃላይ በእንቁላሌ በቀጣሽኝ ነው ነገሩ:: ግብረ ገብነት ሲጠፋ እንደዋዛ፣ አይቶ እንዳላዩ ቢያልፉት ጦሱ ብዙ ነው:: ይቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም የሚለው ብሂል ለዚህም ይሠራል::

ምዕራፍ አሥር

ግብረ ገብ መሪ

10 መሪነትና ሥነ ምግባር

ግብረ ገብ መሪ (Ethical Leader) **ማለት የሚመራበት መርህ ያለውና ለመርሁ የታመነ፣ ትክክል ያልሆነውን እየተወ ትክክል የሆነውን ለመሥራት የሚተጋ፣ እውነተኛና ፍትሐዊ የሆነውን ነገር በመሥራት ለተከታዮቹ አርአያ የሚሆን ማለት ነው**[71]::

መሪ ችሎታ ብቻ ሳይሆን ሥነ ምግባር ሊኖረው ይገባል:: ከምንም በላይ ራሱን በአግባቡ መምራት የማይችል ሌሎችን ሊመራ አይችልምና መሪ ምንም ችሎታ ቢኖረው ግብረ ገብነት ከጎደለው ሥራውም ጎደሎ ነው የሚሆነው:: መቼም ብቃት ቢኖረው እንኳ የሚሰክር፣ የማይታመን፣ የሚያጭበረብር፣ የሚዋሽ፣ የሚሰርቅ መሪን የሚፈልግ የለም:: መሪ

[71] Leading ethically is believed to be a process of inquiry – asking questions about what is right and what is wrong – and a mode of conduct – setting the example for followers and others about the rightness or wrongness of particular actions (Guy, 1990). http://www.ef.uni-lj.si/docs/osebnestrani/MIhelic_Lipicnik_Tekavcic_2010_clute.pdf

በሥነ ምግባር የታነጸ ሲሆን፤ ለራሱ የተስተካከለ መሪ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለሚመራቸውም አርአያ ስለሚሆን ሠርቶ ማሠራት፣ ሁሉንም በፍቅር ማስተባበር ይቻለዋል[72]:: በአጠቃላይ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የመሪ የግል ሕይወቱና የመሪነት ሕይወቱ የሚነጣጠል አይደለም::

ለመምራት የሞራል ብቃትም ያስፈልጋል:: ሰውን እያሰቃዩ ስለ ፍትሕ መስበክ የሞራል ብቃት ከወዴት መጥቶ ነው ያሰኛል እንጂ ሰሚ አያተርፍም:: አገልጋይነትም የሚቻለው የሞራል ብቃት ሲኖር ነው:: ራስን መግዛት ሳይቻል እየሰከሩ፣ እየተንዘላዘሉ፣ በሱስ በአደንዛዥ ዕፅ ባርነት እየማቀቁ፣ ሌላውን እመራለሁ ቢባል ባዶ ቅዠት ነው የሚሆነው:: ይህን ለማለት የሞራል ብቃት የለህም ያሰኛልና:: ስለ ሕዝብ እቆረቆራለሁ ለማለትም የሚቻለው የሞራል ብቃት ሲኖር ነው:: ሕዝብ እየዘረፉ ስለ ሕዝብ እቆረቆራለሁ ለማለት ቢሞክር የሞራል ብቃት አይኖርም:: ቀን ከሌሊት እየዋሹ ስለ እውነት ለመስበክ መሞከር ከሌላው ጋር ብቻ ሳይሆን ከራስም ጋር መጣላትን ያስከትላልም::

በብዙ አገሮች እንደሚታየው በመሪዎች ምርጫ ግብረ ገብነት ግምት ውስጥ ይገባል:: አንድ መሪ የሞራል ካምፓስ (Moral compass- a natural feeling that makes people know what is right and wrong and how they should behave[73]) እንዲሁም መርህ ወይም የሥነ ምግባር መመሪያ (code of conduct[74]) አለው ወይስ በተቃራኒው የሚለው በተለያየ አጋጣሚ የመሪን ብቃት ለመመዘን የሚቀርብ ነው:: ለምሳሌ

[72] A leader with high ethical standards conveys a commitment to fairness, instilling confidence that both they and their employees will honor the rules of the game. https://hbr.org/2016/03/the-most-important-leadership-competencies-according-to-leaders-around-the-world

[73] One person's moral compass may not point in the same direction as another's, as far as right and wrong conduct and belief are concerned. https://www.vision.org/what-guides-our-moral-compass-410

[74] code of conduct clarifies an organization's mission, values and principles, linking them with standards of professional conduct. https://www.ethics.org/resources/free-toolkit/code-of-conduct/

በአሜሪካ ፕሬዜዳንታዊ ምርጫ መሪዎች ሞራል ካምፓስ ወይም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው መሆኑ አንዱ የሚመዘኑበት መስፈርት ነው:: የመሪ ችሎታው ብቻ ሳይሆን ቅንነቱ ይመዘናል:: ቃልና ተግባሩ የሚስማማ፣ የተናገረውን የሚፈጽም፣ በትሕትና ከተቃናቃኞቹ ጋር እንኳ ተግባብቶ የሚሠራ፣ የተረጋጋና ስሜቱን የሚገዛ እና የመሳሰሉት ሁሉ በምርጫ ወቅት ሚዛን ውስጥ ይገባሉ:: የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ተስፋ ሲደረግበት ተከታይ ያገኛል::

በተመሳሳይ በአደገው ዓለም አንድ ሰው ለሥልጣን መፎካከር ሲጀምር በግል፣ በድብቅ የተሠራ ነውር ነገር እየተቆፈረ ወደ አደባባይ መውጣቱም የሚጠበቅ ነውና የቀደመ ሕይወታቸው መሰናከል ሆኖ የሚያስቀራቸው ብዙዎች ናቸው:: የተደበቀ ገመና ሁሉ ይገለጣል:: ብዙ ጣጣ ያለበት ከመሀል መንጠባጠቡም አይቀሬ ነው::

መሪ ግብረ ገብነት እንዲኖረው የሚያስፈልግበት ምክንያት ዘርፉ ብዙ ነው:: መሪ በዘፈቀደ ሲኖርና ግብረ ገብ ሲሆን በመሪነት ሕይወቱ ልዩነት አለው:: ከሃዲ መሪን፣ ዋሾ መሪን፣ አጭበርባሪ መሪን ምን ቢናገር በየትኛው መልኩ ቢናገር ማን ሊያምነው ይችላል? እውነት ቢናገር እንኳ እገሌን አትመኑት የሚታመን ሰው አይደለም ሊባል ይችላል:: ምግባረ ብልሹ መሪ ሓላፊነቱን እንዴት በአግባቡ ሊወጣ ይችላልስ? ምግባረ ብልሹ መሪ ከአድሏዊነት እንዴት የጸዳ ሊሆን ይችላል? የሚንዘላዘል ሰውስ እንዴት አደራ ይጣልበታል? በአጠቃላይ ራሱን በአግባቡ መምራት የማይችል ሰው ሌሎችን ይመራል ተብሎ እንዴት ተስፋ ሊደረግበት ይችላል? የሚለው መሪ በመሪነት ሕይወቱም ቢሆን ሥነ ምግባር ያስፈልገዋል የሚለውን የሚያሳይ ነው::

መሪ እምነቱና አመለካከቱ በስብዕናው ላይ እንዲሁም በአመራር ዘይቤው ላይ በአንድም በሌላም ተጽዕኖ እንደሚያደርጉበትም የታወቀ ነው:: መሪ እንደማንኛውም ሰው አስተሳሰቡ፣ አመለካከቱ፣ ዓለምን የሚረዳበትና የሚያይበት መነጽሩ በመሪነት ሕይወቱ፣ በሚወስናቸው ውሳኔዎች፣ በአመራር ዘይቤው ላይ ተጽእኖ ያስድርበታል:: ሰው እምነቱ ይለያይ

እንጂ፤ ማን ነኝ? ከየት መጣሁ? ሰው የመሆኔ ዐላማ ምንድን ነው? የሕይወት ትርጉም ምንድን ነው? እንዴት መኖር አለብኝ? ፍጻሜዬ ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልስበት አመለካከት ወይም እምነት አለው:: የአንድ መሪ የአመራር ፍልስፍናው ዓለምን ከሚረዳበትና ከሚያይበት መነጽር፣ ከአመለካከቱና ከእምነቱ ጋር የሚያያዝ ነው::

አንድ መሪ ስለ ሰው የሚኖረው አረዳድም ከእምነቱ፣ ከአመለካከቱ፣ ከአስተሳሰቡ ጋር ይያዛልም:: አንድ መሪ፤ ሰው በዘፈቀደ ወይም በተፈጥሮ ሂደት ተገኘ፣ ፍጻሜውም በዚህ ዓለም የሚወሰን ዘለዓለማዊነት የሌለው ነው ብሎ ሲያምና፤ ሰው በፈጣሪው ዘንድ ክብር ያለው፣ የዘላለም ተስፋ ያለው፣ ክቡር ፍጥረት ነው ብሎ ሲያምን በመሪነት ፍልስፍናው ላይ ልዩነት አለው:: ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው መሪና የሌለው መሪ ስለ ሰው ክብር ያላቸው አረዳድ የተለያየ እንደሚሆን የሚጠበቅ ነው:: ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለው መሪ ፍትሕን፣ ነጻነትን፣ እኩልነትን የመሳሰሉ ጉዳዮችን የሚያይበት መነጽር ፈሪሃ እግዚአብሔር ካለው መሪ የተለየ ሊሆን እንደሚችልም የሚጠበቅ ነው:: ስለ ሥነ ምግባር፣ ስለ አገልግሎት፣ ስለ በጎ እሴት እና በመሳሰሉ ጉዳዮች በእነዚህ በሁለቱ ሰዎች መካከል ያለው አመለካከት የተራራቀ ሊሆን ይችላል::

በተመሳሳይ መሪ ፈሪሃ እግዚአብሔር ወይም ግብረ ገብነት ከሌለው እውነቱን ከሐሰቱ፣ ትክክሉን ትክክል ካልሆነው፣ ነውሩን እና ጽድቁን ነገርስ የሚለይበት፣ የሚመራበት መርህ ሊያገኝ የሚችለው ከየት ነው? እንደ እኛ ባለ አገር ደግሞ የሕግ የበላይነት ባልጎለበተበት ሁኔታ መሪ ፈሪሃ እግዚአብሔር ከሌለው ሥልጣኑን ሊገድበው የሚችል ምን ነገር ይኖራል? መሪ ፈሪሃ እግዚአብሔር ወይም ግብረ ገብነት ወይም የሚመራበት መርህ (moral compass) ከሌለው ከሳሽ ወቃሽ ሕሊናስ እንዴት ሊኖረው ይችላል?

በቅዱስ መጽሐፍ ለመሪነት ከቀረቡት መስፈርቶች መካከል አብዛኞቹ መልካም ሰብእናንና ግብረ ገብነትን የሚመለከቱ ናቸው:: ከተጠቀሱት አሥራ ስድስት ጠባያት መካከል የማይኮራ፣ የማይቆጣ፣ በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ፣ ጠንቃቃ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ፣ ገር የሆነ፣

የማይከራከር፣ ገንዘብን የማይወድ፣ የማይነቀፍ፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ ነውረኛ ረብ የማይወድ፣ በንጹሕ ሕሊና ምሥጢር የሚይዝ፣ በነገር ሁሉ የታመነ፣ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር የሚሉት ለሁሉም መሪዎች የሚያስፈልጉ ናቸው:: የገዛ ቤቱን በአግባቡ መምራት የማይችል ሌላውን ሊመራ አይችልምና የመሪ የሥራ ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን የቤተሰብ ሕይወቱም መስፈርት ውስጥ ይገባል:: (ቲቶ 1፥7-8; 1ጢሞ 3፥1-13)

በመልእክቱ ላይ ቅዱስ ጳውሎስ ትኩረቱ የሃይማኖት መሪ ቢሆንም እነዚህ መስፈርቶች በአሁኑ ጊዜ በየትኛው የመሪ ምርጫ መስፈርት ሆነው ሲቀርቡ ማየት ግን የተለመደ ነው:: ጥናቶች የሚያሳዩትም ግብረ ገብነት ለመሪነት ተመራጭ መሆኑን ነው:: ለምሳሌ በአንድ ጥናት ከቀረቡ ስምነት መለኪያዎች ሰባ አምስት በመቶው ግበረገብነትን ተመራጭ ሲያደርጉ ስድሳ ስምንት በመቶው ደግሞ ፍትሐዊነትን ተመራጭ አድርገዋል[75]:: ከመቼውም ጊዜ በላይ በአሁኑ ጊዜ የመሪዎች ምርጫ በእነዚህና እነዚህን በመሰሉ መስፈርቶች መመዘን በአብዛኛው ሲተገበር የሚታይ ነው::

10.1 በምሳሌነት የሚመራ

መሪነት "እየጠጣ መጠጥ ይጎዳል" ብሎ እንደሚመክር ሐኪም አይደለም:: የሰው ልጅ በአብዛኛው የሚማረው ከሚሰማው ይልቅ በሚያየው ነው ይባላል:: ከጆሮው ዐይኑን የበለጠ ያምናል:: እንደ ቶማስ በዐይኑ የሚያዬውን በእጁ ካልዳሰሰ ለማመን መቸገርም ይኖራል:: ተመሪ መሪውን ሲከተልም በሚደሰኮር ፕሮፖጋንዳ ሳይሆን ቃልና ተግባር መዛመዱን እያረጋገጠ ነው:: ቃልና ተግባር ሲጣጣም፣ መሪን የተናገርውን በተግባር ሲኖር፣ የገባውን ቃል ሲፈጽም በምሳሌነት መምራት (Leading by Example

[75] What Is The Most Important Leadership Attribute?, In a survey by consulting firm Robert Half, 75 percent of employees ranked "integrity" as the most important attribute ofaleaderhttp://rh-us.mediaroom.com/2016-09-22-What-Is-The-Most-Important-Leadership-Attribute

where leader's actions set standards for others[76]) ይቻላል::

በአብዛኛው የአመራር ችግር የሚከሰተው ወይም ከአመራር ችግር በቀላሉ መውጣት የማይቻለው ምሳሌ የሚሆኑ መሪዎችን በበቂ ማግኘት አስቸጋሪ ስለሚሆን ነው:: አርአያነት ያለውን ሥራ የሚሠራ፣ በቃሉ የሚገኝ፣ ቃልና ተግባሩ የተስማሙ፣ የምነገራችሁን አድርጉ ብቻ ሳይሆን የማሳያችሁን አድርጉ የሚል፣ እኔ እንዳደረኩላችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ እንዲሁ አድርጉ የሚል መሪ ሲገኝ ነው በምሳሌ የሚመራ መሪ ሊባል የሚችለው::

ከላይ ያለው መሪ ሌባ ሲሆን የታችኛው መሪም አለቃዬ እየሰረቀ እኔ ሐቀኛ እንዴት ልሆን እችላለሁ? በሚል መስረቅ ይጀምራል:: ለአለቃው ጉቦ ከፍሎ የተቀጠረ ወይም እድገት ያገኘ ሰው ያለቃውን ሌብነት እንደ ማሳመኛ ምክንያት ያቀርብና ራሱን በአለቃው ሙሰኝነት እያጽናና እርሱም በተራው እድሉን ሲያገኝ የባሰ ሌባ ሊሆን ይችላል:: በአንጻሩ የሚሰርቅ መሪ አትሰረቁ ለማለት፣ የሚዋሽ መሪ አትዋሹ ለማለት ድፍረት ሊኖረው አይችልም:: ድፍረት ቢኖረውም ሕጉን ካልፈራ በስተቀር እንዲህ ዐይነቱን መሪ የሚሰማው፣ በፈቃድ የሚከተለው፣ የሚያከብረው እንዴት ሊኖር ይችላል?

"መኰንን ሐሰተኛ ነገርን ቢያደምጥ ከእርሱ በታች ያሉት ሁሉ ዓመፅኞች ይሆናሉ" እንዲል መሪዎች በሥነ ምግባር ምሳሌ ካልሆኑ አመራሩም በአመዛኙ እንደሚበከል የሚጠበቅ ነው:: (ምሳ. 19፥12) ከላይ ያሉት መሪዎች የማይታመኑ ሲሆኑ ታችኛው ሹምም እንዲሁ ይሆናል:: ሌላው ቀርቶ መሪዎች ሐሰተኞች ከሆኑ እውነተኛ ሕዝብን ማፍራት እንዴት ይቻላል? መሪዎቹ ደጋግመው ቃላቸውን የማያከበሩ ከሆኑ ታማኝ ማኅበረሰብን መፍጠርስ እንዴት ይቻላል? መሪዎች ዘረኞች ከሆኑ

[76] Serious leaders understand that, both by design and default, they're always leading by example. Some want to "lead from the front" while others prefer "leading from behind." But everyone senses their success — and failure — at leading by example is integral to their "leadership brand." https://hbr.org/2016/10/like-it-or-not-you-are-always-leading-by-example

አንድ የሚሆን በመረዳዳት የሚያምን ማኅበረሰብን መገንባት እንዴት ይቻላልስ? መሪዎች ያወጡትን ሕግ የማያከበሩ ከሆነ በሕግ የበላይነት የሚያምን ማኅበረሰብን መፍጠርስ እንዴት ይቻላል? በአጠቃላይ ክፉ መሪዎች ሲበረክቱ መንጋውም ይበከላል፤ መልካም እረኛ ሲገኝ ደግሞ ወድቆ የነበረ ሞራል ሊገነባ ይችላል::

በምሳሌነት መምራት ማለት በትሕትና እና በበጎ ሥራ ሁሉ ሠርቶ ማሳየት ነው:: ለዚህ ክቅዱስ መጽሐፍ ምሳሌ መጥቀስ ይጠቅማል:: "እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና::" በማለት የትሕትና አምላክ የፍጥረቱን እግር ዝቅ ብሎ እስከ ማጠብ የደረሰው ለአብነት ነው:: (ዮሐ 13፥1-17) በምሳሌነት መምራት ምን ማለት እንደሆነ የሚያሳይ ነው:: "ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ" የሚል ቃልም በመጽሐፍ ቅዱስ ይገኛል:: (1ኛ ጴጥ. 5፥2-4) በምሳሌ መምራት በግድ ሳይሆን በውድ ተከታይ ማፍራትን ያስችላልና ነው እንዲህ መባሉ:: እውነተኛ መሪ ታማኝ ተከታይን ማፍራት የሚቻለው በዚሁ መንገድ ነው:: ትሑት መሪ ከላይ ሲኖር ከሥሩ ያሉ መሪዎችም ትሑታን የመሆን እድላቸው ከፍ ያለ ነው የሚሆነው:: መሪ ታታሪ ሲሆንም እንዲሁ ተከታዮቹ እርሱን ይከተላሉ:: መሪ የማይሰርቅ ንጹሕ ሲሆን የሚሰርቁት ያንሳሉ::

መሪ በመድረክ ሕይወት ብቻ ሳይሆን በግል ሕይወትም ነቀፌታ የሌለበት ሲሆን በምሳሌነቱ የሚከተሉት ይበዛሉ:: መሪ ንግግሩ ቁጥብ ሲሆን ንግግሩ የሚያምረው ክፉ ቃል ከመናገር የሚቆጠበው ይበዛል:: መሪ በአኗኗሩ ብቻ ሳይሆን በንግግሩም ሊጠነቀቅ ይገባልና:: ሥልጣን አለኝ ብሎ በቸልታ ቢናገሩት መዘዙ ብዙ ነው:: ሕዝብ የመሪውን አፍ ይጠብቃልና:: የመሪ ቃል ሕዝብን አንድ ያደርጋል፤ የመሪ ቃል ሕዝብን ይለያያል:: የመሪ ቃል ዘረኝነትን ይዘራል፤ የመሪ ቃል የተለያየውን አንድ ያደርጋል:: ይህ ደግሞ ባለፉት ዓመታት በደንብ ታይቷል:: ሌላው ቀርቶ የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ መሪ ሲገኝ በዙሪያው ያሉት ሁሉ ረስተውት የነበሩትን የእግዚአብሔርን ስም መጥራትን ይጀመራሉ:: መሪ ከፊት ሲመራ፣ ሠርቶ እንሥራ ሲል ሰሚ ያገኛል፤ መሪ አብነት

ሲሆን ሌሎች መሪዎችን ማፍራትም ያስችላል:: መሪ እርሱ ሊያደርገው የማይፈልገውን ወይንም የማይደፍረውን ነገር አድርጉት ቢል ሰሚ ከወዴት ይገኛል? ቃላቸውና ተግባራቸው ለየቅል የሆኑ መሪዎች በሚበዙበት ጊዜ ትውልድ የሚያየው፣ አብነትም የሚያደርገው ያጣና ዝቅጠት ይመጣል:: በእርግጥም የአመራር ችግራችን ምን ያህል አርያ የሚሆኑ መሪዎችን ከማጣት ጋር የሚያያዝ ነው? የሚለው ጠለቅ ያለ ዳሰሳ የሚፈልግ ይሆናል::

ችግሩ ሁሉን በኃይል ሁሉንም በግድ ማስፈጸም ልማዳቸው የሆኑ መሪዎች ኃይል እንጂ ምሳሌነት በእነርሱ ዘንድ ዋጋ የሌለው መሆኑ ነው:: "ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም::" እንደተባለው በቃል የሚናገሩትን በተግባር የሚሠሩ መሪዎችን ማግኘት ጭንቅ የሚሆነብት ጊዜ አለ:: (ማቴ 23፥4) ሥልጣን እስካለ ድረስ የሚፈልጉትን ማድረግ እየተቻለ በምሳሌ መምራት፣ አርአያ መሆን ምን ያስፈልጋል? የሚል እምነት ያለ ይመስላል:: ለዚህ ደግሞ ሥራቸው ምስክር ነው:: አዝምተው የሚያስገድሉ እንጂ ዘምተው የሚሞቱ መሪዎችን ማየት በዛሬው ጊዜ ከስንት አንድ ነው:: መደስኮር እንጂ የገቡትን ቃል በተግባር መኖርም እንዲሁ::

ከምንም በላይ የተናገሩትን በሕይወት መኖር፣ የሚመኙትን ሆኖ መገኘት እንደማውራቱ ቀላል አይደለም:: በምሳሌ መምራት ዋጋን ያስከፍላል:: ዋጋን ለመክፈል መዘጋጀትንም ይጠይቃል:: ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው እውነትን መናገር፣ ለእውነት መኖር ዋጋን ሊያስከፍል ይችላል:: ሌብነት በበዛበት ሁኔታ እንኳን ሌቦችን መታገል ይቅርና እኔ አልሰርቅም ቢባል እንኳ መነጠልን ሊያስከትል እንደሚችልም የሚታይ እውነት ነው:: በትሕትናና በየዋህነት አርአያ ለመሆን ሲሞከርም እንደ ደካምነት ሊታይና በሌላ ሊተረጎም ከቻለም ብዙ ነው ጣጣው:: እውነተኛ ለውጥን ለማምጣት በምሳሌነት መምራት ያለውን ጠቀሜታ ሲታሰብ ነው ዋጋ ቢያስከፍልም፣ በተግባር ተግዳሮቱ የበዛ ቢሆንም በምሳሌነት መምራትን ተመራጭ የሚያደርገው::

መስበኩ እንጂ ቀላሉ የሚናገሩትን በሕይወት መኖር ከባድ መሆኑን የሚያሳይ አንድ ተረክ አለ:: የኔታ ሁለት ያለው አንዱን ለሌለው ይስጥ፤ የሚለውን የወንጌል ቃል ሲሰብኩ ባለቤታቸው ከልባቸው ሲያዳምጡ ቆዩ:: የኔታ እንዲህ ካሉማ ከእኛ ቤት መጀመር ይገባል ብለው የኔታ ፈጻጽመው ቤት እስኪመለሱ ሴትዮዋ ቀደም ብለው ቤት ደርሰው የየኔታንም የእርሳቸውንም አንድ አንድ ነገር አስቀርተው ሌላውን ልብስ ለኔ ቢጤ መጽውተው ጠበቋቸው:: የኔታም ባለቤታቸውን በመገረምና በመቆጣት "ምን ነው እኅቴ!" ብለው ቢጠይቋቸው "ባለቤታቸውም "ምነው የተናገሩትን ምን ጊዜ ረሱት?" አሏቸው:: የኔታም "ይህን ስብከት የሰበኩት ለሌላው ሰው እንጂ መቼ ለእኛ ቤት ተናገርኩና" አሉ ይባላል::

በምሳሌነት መምራት ሲቻል ብዙ መልካም መሪዎችን ማፍራት ይቻላል:: ለዚህ በቅዱስ መጽሐፍ የነቢዩ የሳሙኤል ታሪክ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል:: ሳሙኤል እስራኤልን ነቢይ፣ መሪና ካህን ሆኖ ሲመራቸው ቆይቶ ሕዝቡ ንጉሥ አንግሥልን ብለው በጠየቁት መሠረት ሳኦልን አነገሠላቸው:: በዚህ ጊዜ ሳሙኤል ሕዝቡን ሰብስቦ "አሁንም እነሆ ንጉሡ በፊታችሁ ይሄዳል፤ እኔም አርጅቻለሁ ሸምግያለሁም፤ እነሆም ልጆቼ ከእናንተ ጋር ናቸው:: እኔም ከሕፃንነቴ ጀምሬ እስከ ዛሬ ድረስ በፊታችሁ ሄድሁ:: በእግዚአብሔርና እርሱ በቀባው ፊት መስክሩብኝ:: የማንን በሬ ወሰድሁ? የማንንስ አህያ ወሰድሁ? ማንንስ ሸነገልሁ? በማንስ ላይ ግፍ አደረግሁ? ዐይኖቼንስ ለማሳወር ከማን እጅ ጉቦ ተቀበልሁ?" ሲል ጠየቃቸው:: እንደ ሳሙኤል በልበ ሙሉነት ኑና እንዋቀስ የሚል፣ በድያችሁ ከሆነ ፍረዱብኝ የሚል፣ በንጽሕናው የሚተማመን ስንት መሪ ማግኘት ይቻል ይሆን? እየሰረቁ ሌብነት በየሚዲያው ሲኮንኑ መዋል ሌላ ነገር ነው:: እንዲህ ዐይነት መሪዎችን ማዬት በሽ ነውና:: በሌብነት ተዘፍቀው ሌብነትን በአፍ ሲጸየፉት ላዬ ሁለት የተለያዩ ሰዎች በአንድ ሰው ላይ ተዳብለው የሚኖሩ እንጂ አንድ ሰው አይመስልምም:: ሳሙኤል ንጹሕ ነበርና ሕዝቡም "አልሸነገልኸንም ግፍም አላደረግህብንም ከሰውም እጅ ምንም አልወሰድህም አሉ"። (1ኛ ሳሙ. 12፥2-4) እንደ ሳሙኤል እጁ ንጹሕ የሆነ በልቡ ቅንነት በምሳሌነት ሕዝብን የመራ መሪ ሲገኝ

በሌቦች ወጥመድ አይወድቅም:: በልበ ሙሉነት ሌቦችን ቢቃወም ኃይል ይኖረዋልም::

እንደ ሳሙኤል እጹ ንጹሕ የሆነ መሪን ማግኘት ግን ከስንት አንድ ነው:: በተለይ የሃይማኖት መሪዎች ለሌሎች መሪዎች የሞራል ልዕልና መሪ መሆን በተገባቸው ነበር:: ችግሩ ግን በአንዳንዶቹ ዘንድ የሚብስ ይመስላል:: በአንዳንዶቹ የሃይማኖት ተቋማት ከእግዚአብሔር በቀር ብዙም ጠያቂ ያለም አይመስልም:: ግልጽነት የለም፤ ተጠያቂነትም እምብዛም ነው:: በእምነት ስም ማጭበርበሩም እየተሻለ ሳይሆን እየከፋ ሄዷል:: የእምነት ሰዎች የሚጠበቀውን ሆነው ሳይገኙ ሲቀር ግን፤ እግዚአብሔርን እንፈራለን የሚሉት ሰዎች እንዲህ ከሆኑ እኔ ምን እዳ አለብኝ ያሰኛል:: ሰው ባያይ እግዚአብሔር ያያል ብሎ የሚያምን፣ ሰውን ባይፈራ እንኳ እግዚአብሔርን ይፈራል ተብሎ ይገመት ነበርና:: ዓለም በቃኝ ፈጣሪዬን አገለግላለሁ ብሎ ሳይገደድ የሕይወቱን አቅጣጫ የመረጠ የሃይማኖት መሪ በሌብነት ሲታይ፣ ሹመት በዘመድ አዝማድ በሃይማኖት ቤት ሲታይ የሞራል መሪዎች እንዲህ ካደረጉማ ስለሚያስብል የሞራል ውድቀትን ሊያመጣ ይችላል:: ሰው ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ከሰረቀ ከባድ ችግር ነው:: ሃይማኖት ዘር የለውምና ዘረኝነትን በሃይማኖት ተቋማት ማየት መቼም የሚከብድ ነገር ነው:: በእርግጥ የችግሩ ምንጭ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ቢሆንም የተጣሉትን በማስታረቅ ምሳሌ መሆን የሚገባቸው የሃይማኖት መሪዎች እነርሱ እርስ በእርሳቸው መስማማትም መታረቅም አቅቷቸው ሌላ ሰው ካስታረቃቸው የመሪነት ዝቅጠት በዚያች አገር ምን ያህል የከፋ ደረጃ መድረሱን የሚያሳይ ሊሆንም ይችላል::

ሳሙኤል በራሱ ብቻም ሳይሆን በልጆቹም ንጽሕና ይተማመናል:: በጊዜው በዙሪያው የነበሩ ባለሥልጣናት ልጆቹ ነበሩና ልጆቹም እንደ ሳሙኤል ማንንም አልበደሉም፤ ከማንም መማለጃን አልተቀበሉም:: በአንጻሩም ከሳሙኤል በፊት የነበረ ዔሊ የሚባል መሪ እርሱ ንጹሕ ቢሆንም ልጆቹን ግን መቆጣጠር አልቻለም ነበር:: ሕዝቡ የሚያመጣውን መሥዋዕት እየበሉ ሕዝቡን እያንገላቱ ሴቶቻቸውን እየደፈሩ እጅግ

ኃጢአትን ሲያደርጉ ዔሊ ልጆቹን ባለመገሰጹና ባለማስቆሙ መቅሰፍት በእርሱ በልጆቹ እንዲሁም ውርደትና መማረክም በሀገሩ ላይ እንደደረሰ ተጽፏል:: (1ኛ ሳሙ 4፥11)

“እሳቸው እኮ ንጹሕ ናቸው ሚስታቸው ናት ሌባ፣ መሪዎቹ ንጹሕ ናቸው የበታች ሹሞች ናቸው የሚሰርቁት“ የሚል ነገር እየተለመደ ነው:: “ምን ያድርጉ ሌቦችን ማስቆም ከባድ ነው “ ሲባልም ይሰማል:: ሓላፊነትን ተቀብሎ ከደመ ነጻ መሆን እንደ ጲላጦስ ለመሆን መሞከር ነው የሚሆነው:: መሪ በየደረጃው ሓላፊነቱ አለመስረቅ ብቻ ሳይሆን አለማሰረቅም ነው:: የዔሊ ታሪክ ራስ ንጹሕ ሆኖ በዙሪያው ያሉ ሰዎችን እንዲታረሙ አለማድረግ ከተጠያቂነት እንደማያድን ነው የሚያመላክተው::

10.2 ፈሪሃ እግዚአብሔር ከመሪዎች ሲጎድል

ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ሌላው ቀርቶ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ ሲባል የሚሳቅበት ዘመን ተደርሶ ነበር:: በመሪዎች ዘንድ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት እንደ ነውር የሚቆጠር የሚመስልበት ዘመን ነበር ይታይ የነበረው:: ከጥቂቶቹ በቀር በአመዛኙ በመሪዎች ዘንድ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር አለው መባል፣ በአምልኮ ቦታ መገኘት፣ መሪ ሆኖ በእምነት አካባቢ መታየት፣ እምነትን መግለጽ ነውር የሚመስልበት ጊዜ ነበር:: አንዳንድ ጊዜም መሪዎች ማንነታቸው የሚለየው በቀብራቸው ወቅት እስከመሆንም ተደርሶ ነበር የሚባል ነገር አለ:: ችግሩ ሰነባብቷል::

መሪ ሆኖ እምንትን መግለጽ የሚያስቀጣበት ዘመን፣ በግላጭ ፈጣሪን መካድ ተራማጅ አድርጎ የሚያቆጥርበት ዘመን ወዴት አደረሰን? ውጤቱ ምንድን ነው? የሚለውን ለመመርመርም ትክክለኛው ጊዜ ነው ማለት ይቻላል:: ጉዳዩ ግን እጅግ ሰፊ ነው፣ በባለሙያ ሰፊ ጥናት የሚያስፈልገው:: በዚህ ሂደት ያለፉ መሪዎች ተሞክሯቸውን፣ በዚህ ረገድ የተማሩትን፣

በመሪነት ሕይወታቸው ላይ የነበረውን ተጽእኖ በሰፊው የሚያካፍሉበትና በገለልተኝነት ተጠንቶ ለመጭው ትውልድ የሚተላለፍበት እድል ቢኖር ብዙ ጠቀሜታ ሊኖረው፤ ብርሃንን ሊፈነጥቅ ይችላል::

አብዛኞቹ የፖለቲካ መሪዎች ሠርቶ አገር እንደማሳደግ የፈጣሪን ኃይል በገሀድ በመካድ ምኑም ሳይጨበጥ በራሳችን ኃይል ተፈጥሮን በቁጥጥር ሥር እናውላለን በሚል ቅዠት ከእግዚአብሔር ጋር ግብግብ መፍጠሩን ለምን እንደመረጡት ከልብ የተረዱት ግን አይመስልም:: በዚያ ታሪክ ያለፉ አሁን አንዳንዶች መሪዎች ልብ ገዘተው "ሁሉንም ሳናላምጥ እንውጥ ነበር" እንደሚሉት ከሌሎች ያዩትን በስሜት ከመኮረጅ በቀር ከሚመሩት ሕዝብ አንጻር ነገሩን ከልብ የተረዱት ነበር ለማለትም ያዳግታል:: እንዲህ ባለው ሁኔታ ሀገሪቱ ወዴት እየሄደች እንደነበር ግን አመላካች ነበር:: እንዲህ ዐይነቱ ነገር መርገምን እንጂ በረከትን ሊያመጣ አይችልምና:: መርገሙም በታሪክ እንደታየው ሁሉ ለአገርም የሚተርፍ ነው የሚሆነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ጎልተው ከሚታዩ ታሪኮች መካከል አንዱ መሪዎች ከእግዚአብሔር በራቁ ጊዜ መከራው ለሕዝቡና ለአገሪቱ ይተርፍ እንደነበረ ነው::

በዓለም ሥልጣኔ ማማ የተቀመጡ ሀገራትን የሚመሩ መሪዎች ሳይቀሩ በእግዚአብሔር የሚታመኑ ሆነው እያየን ባለንበት ዘመን የእኛ መሪዎች ምኑም ሳይጨበጥ እንዲህ መሆን መቼም ምን ነክቷቸው ነው? ሊያሰኝ ይችል ይሆናል:: መሪዎች እምነታቸው ቢለያይም በአብዛኛው የሚታየው በፈጣሪ የሚያምኑ መሆኑን ነው:: ዛሬም ድረስ ብዙ ያደጉ አገራት መሪዎች ቃለ መሐላቸውን ሲፈጽሙ "የገባሁትን ቃል እንድፈጽም ፈጣሪ ይርዳኝ" ከሚለው ጀምሮ በንግግራቸው ማጠቃለያ ሁሉ "ፈጣሪ አገሪቷንና ሕዝቦቿን ይባርክ" ማለታቸውም የተለመደ ነው:: ቃለ መሐላ ሲፈጸምም እንደየእምነታቸው በእምነታቸው ቅዱስ መጽሐፍ እንጂ በእኛ እንደሚታየው በባዶው አይደለም:: ምክንያትም አላቸው:: እንዲህ ማድረጋቸው ለፈጣሪ ተጠያቂነት አለብኝ፣ ፈጣሪ ምስክር ይሁንብኝ ለማለት ነው:: ይህን ማድረጋቸው ሥልጣኔ ቢኖርም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለውን ጠቀሜታ ስለተረዱት ነው የሚሆነው:: ለሳይንሱ

ከሆነም እነሱው ይቀርባሉ:: በፈጣሪ በመታመናቸውም ተጠቀሙበት እንጂ አልተጎዱበትምም::

ቀደም ሲል ለማንሣት እንደተሞከረው ፈጣሪያቸውን በሚፈሩና እምነት አልባ ነን በሚሉ መሪዎች መካከል በመሪዎች የአመራር ፍልስፍና ላይ ልዩነት አለው:: ምክንያቱም አንደኛ ፈጣሪውን የሚፈራ መሪ በምድሪቱ ሕግ ብቻ ሳይሆን ለሚሠራው ሥራ ሁሉ በፈጣሪ ዘንድ በዚህ ዓለምም ይሁን በመሚጣው ዓለም፣ ተጠያቂነት እንዳለ ማመን እና አለማመን ልዩነት አለው:: ሁለተኛ የሰውን አመጣጥና የሰውን የወደፊት ተስፋ እንዲሁም የሰውን ክብር በመረዳት ረገድ ያለው ልዩነት በመሪው አመለካከትና የመሪነት ሕይወት የራሱ አስተዋጽዖ አለው:: ይህን ከተሞክሮም ማየት ይቻላል:: እምነት አልባ ነን ያሉን መሪዎች ያደርጉት የነበረው ምንድን ነው? ፍጻሜያቸውስ ምንድን ነበረ?

ፈሪሃ እግዚአብሔር አለን ይሉ የነበሩ መሪዎችስ ምን የተለየ ነገር ነበራቸው? የሚል ነገር ይነሣ ይሆናል:: ትክክለኛ ጥያቄ ነው:: የመጀመሪያው ሁሉም ነገር አንጻራዊ ነው:: የትኞቹ የተሻሉ ነበሩ ከሚለው አንጻር መመዘን ከተቻለ ለማለት ነው:: ሁለተኛው ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው መሪዎች ማለት በእምነት ስም የሚያታልሉ ማለት ሳይሆን በሕይወት የተመሰከረላቸው፣ ፈጣሪን በመፍራትና ሰውን በማክበር የሚታወቁትን ለማለት ነው::

ያም ሆነ ይህ የመምራት በቂ ዝግጅት ያልነበራቸው ሰዎች ታላላቅ ሓላፊነትን ሲይዙ ቢያንስ እንኳ እግዚአብሔርን መፍራት ቢኖር በጊዜ ሂደት ማስተዋል ይገኝ ነበር ብሎ ማሰብ ይቻላል:: ለዚህ ሁሉ ግን ራስን ለማወቅ፣ የዓቅም ውሱንነትን ለመረዳት የሚያስችል ትሑት ልብ ያስፈልጋል:: መሪ የሚወስነው ውሳኔ በሚመራው ሕዝብ ወይም ተቋም ላይ በአጭር ጊዜም ይሁን በረጅም ጊዜ የሚኖረውን ተጽዕኖ ወይም ጉዳት የሚረዳበት ልብ ከሌለው በማን አለብኝነት ወይም በግዴለሽነት ብዙ ነገር ሊያበላሽ ይችላል:: የትሕትና ልብና አስተዋይነት ሲኖር መሪ ቆም ብሎ ማሰብ፣ ማሰላሰል፣ የቀናውን መንገድ ለመምረጥ ይረዳዋል::

በእግዚአብሔርም መታመን የሚቻለውም በራስ ዕውቀትና ጉልበት አለመመካት ሲቻል ነው::

መሪነት ከባድ ሸክም ነው:: መሪነት የተለያዩ አካላትን ለጋራ ዐላማ አስተባብሮ መምራትን ይጠይቃልና:: ያመኑት ሊከዳ ይችላል፤ ወዳጅ የነበረው ባላንጣ ሆኖ ይነሣል፤ ተስፋ ያደረጉት መክኖ ይቀራል:: የታሰበው ሳይሆን ድንገተኛው ይበዛል:: ጥጋብ ነው ሲባል ራብ፣ እድገት ነው ሲባል ኪሳራ፣ ሰላም ነው ሲባል ጦርነት፣ ፍቅር ነው ሲባል ግጭት፣ የአገር ውስጥ ሲባል የውጭው ጉዳይ የሚያጋጥመው ችግር በያይነቱ ነው:: በተለይ ድህነት በበዛበት፣ ሥራ አጥነት ትልቅ ችግር በሆነበት፣ መግባባት እና መደማመጥ በሌለበት ሁኔታ እንኳን አገርን ቤተሰብን ማስተዳደር ከባድ ነው:: መሪነት በእግዚአብሔር ለተመረጠ የእግዚአብሔር አጋዥነት ላልተለየው ለሙሴ እንኳ ከባድ ነበረ:: ነቢዩ ሙሴ አስቸጋሪ ሕዝብን በበረሀ አርባ ዓመት መሉ ሲመራ ውጣ ውረዱ ቢበዛበት "ለምን በባሪያህ ላይ ክፉ አደረግህ? ለምንስ በፊትህ ሞገስ አላገኘሁም? ለምንስ የዚህን ሕዝብ ሁሉ ሸክም በእኔ ላይ አደረግህ?" በማለት ነበር ምሬቱን ለእግዚአብሔር የገለጸው:: (ዘኁ. 11፥11-15)

መሪም የመሪነት ክብሩና ጥቅሙን ሳይሆን ከባድ ሸክምነቱን አውቆ ቢገባበት፣ ዝናብ ሲዘንብ ነፋስ ሲነፍስ ማዕበል ሲነሣ ጸንቶ መቆም ይቻለዋል:: መሪነት እንዲያው የታሪክ አጋጣሚ ሓላፊነቱን ስለጣለብኝ ነው እንጂ ብቃቱ አልነበረኝም ነበር፤ ለቦታው አልመጥንም ብዬ ነበር፤ ሰው ስለጠፋ ግዴለም ቦታውን ለጊዜው ያዘው ተብዬ ነው ተብሎ በቸልተኝነት የሚገባበት አይደለም:: ሥልጣን በታሪክ አጋጣሚ ስለተገኘ ብቻ በድፍረት እና በስሜት ሲገባበት የሚያስከትለው ጉዳት እንደታየው ነው:: ሥልጣን በጉልበትም ሊገኝ ይችላል:: በጉልበት ግን ለተወሰነ ጊዜ መግዛት ቢቻል እንጂ መምራትና በጎ አሻራን ትቶ ማለፍ አያስችልም:: ለጊዜው የሚቻል ቢመስልም ፍጻሜው ግን ጥፋትና ኪሳራ መሆኑ በታሪክ ተደጋግሞ የታየ ነው::

በሌላ በኩል መቼም መሪነት በትምህርት ብቻ እንደማይገኝም የታወቀ ነው። ይልቁንም የሚባዘው የመሪነት ዕውቀት ሌሎች መሪዎችን በማየት፣ ታሪካቸውን በማወቅ እና ጠንካራ መሪዎችን አብነት በማድረግ እነርሱን በሆንሁ በሚል ምኞት የሚቀሰመው ልምድና የሚፈጥረው መነሣሣት በምንም ሊተካ የሚችል አይደለም። ትውልድ አርአያ የሚያደርጋቸው መሪዎችን በዘመኑ ወይም በታሪኩ ሲያጣ የሚፈጠረው ክፍተት ቀላል የሚባል አይደለም። ከሁሉም የሚበዛው ኪሳራ ክህደት እንደ አዋቂነት እምነት እንደ ሞኝነት በታየበት ዘመን ሁሉ እንዲህ ካሉ መሪዎች ትውልድ ምን እየተማረ አደገ? የሚለው ነው። ሃይማኖትን መዳፈር ይህ ትውልድ የተማረው ከማን ነው? መልሱ ቀላል ነው። አሁን ያለንበትን፣ እየተሠራ ያለውን ማየት በቂ ሊሆን ይችላል። መሪዎች እርስ በርሳቸው እየተካካዱ ሲጠፋፉ፣ አገርን የሚመለከት ትልልቅ ውሳኔ እንደ ቀላል ነገር በስሜትና በእብሪት ሲወሰን፣ ጥፋት ቢኖርም ለአገር የአቅማቸውን የደከሙ ሰዎችን በስሜትና በማን አለብኝነት በእጅ ብልጫና በጩኸት እገሌ ይሙት እገሌ ይዳን በሚል የደቦ ፍርድ ፍትሕ ሲንጋደድ፣ እያየ ያደገ ትውልድ መዳረሻው ምን ሊሆን ይችላል? መካድ ልማድ ሲሆን፣ ሁሉም ነገር ከዜሮ ሲጀመር፣ የተገነባው ሲፈርስ፣ ታሪክ ሲከለስ፣ ተንኮልና መጠላለፍ ሲበዛ ይህን እያዬ ያደገ ትውልድ ምን እንዲሆን ነው የሚጠበቀው? በዚህም አለ በዚያ አሁን እየታጨደ ያለው ፈሪሃ እግዚአብሔር በሌላቸው ወይም ቅንነት በጎደላቸው መሪዎች በየዘመኑ ከተዘራው ነው የሚለው ነገር ትርጉም ሊሰጥ ይችላል። ይህን ማንሣት ያለፈን መውቀስ አሁን ምን ያደርጋል? የሚል ጥያቄም ይነሣ ይሆናል። ቁም ነገሩም እርሱ ነው። ካለፈው ስሕተት መቼ ነው የምንማረው? የሚለው።

ፈሪሃ እግዚአብሔር ለመሪዎች አስፈላጊ የሚሆንበት ሌላም ምክንያት አለው። እንኳን ድሀ ሕዝብን ይዞ ሀብት ቢኖር እንኳ መሪ ያለ እግዚአብሔር እርድታ አገርን መምራት እንዴት ይችላል? ከሰው ዓቅም በላይ የሆነ ስንት ነገር አለ። "እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ

በከንቱ ይተጋል።" የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይህን የሚያሳይ ነው:: (መዝ 127፥1) አገር የሚጠበቀው በሠራዊት ብዛት ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቸርነትም ነው:: እግዚአብሔር ካልጠበቀ ለዘመናት የተገነባው ሁሉ በሰዓታት ሊፈርስ እንደሚችል በየሀገሩ የሚገጥመውን ሰው ሠራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ማየት በቂ ሊሆን ይችላል:: የተፈጥሮው ይቅርና ሰው ሠራሽ አደጋ እንኳ ከደረሰ በኋላ ለመከላከልም ሆነ በቁጥጥር ሥር ለማዋልም እንዴት እንደሚያስቸገር የየዕለት ገጠመኝ የሆነበት ዓለም ነው:: ይህ ድሀ ለሆኑ ብቻም አይደለም:: ሰለጠኑ አደጉ የተባሉ አገሮችም ዕጣ ፈንታም ተመሳሳይ ነው:: እውነት ነው የእግዚአብሔር ጥበቃ እንጂ የሰው ዓቅምስ ውሱን ነው::

በእግዚአብሔር የታመኑ መሪዎች እግዚአብሔርን ተስፋ አድርገው በየዘመናቸው ከባድ ችግርን አልፈዋል:: በሰው ዓቅም ብቻ የማይቻሉ በእግዚአብሔር ኃይል ትልልቅ ሥራዎችን አከናውነዋል:: መረቡን በቅንነትና በእምነት በቀኝ መጣል እስኪቻል በድካም ዘመን የመቁጠሩን ያህል ጠብ የሚል ውጤት ላይገኝ ይችላል። በደከመ ብቻም አይደለም:: ደክሞ ብላሽ ሆኖ የቀረ፣ ውጤት አልባ ሆኖ የቀረ ስንት ነገር አለ? ዓሣው እንዲበዛ መረቡን በቀኝ በኩል መጣል ያስፈልጋል:: የእግዚአብሔር ረድኤቱ ሲጨመርበት ነው መረቡ የሚሞላው:: ያለዚያ መባዘን ብቻ ነው የሚሆነው:: ለሚያምን ሁሉ ይቻላል ነው ነገሩ:: በእምነትና በቀናነት ያሰቡት ይሳካል። ቀናውን መንገድ ማየት ይቻላል፣ የተጣመመው ይቃናል፤ ቢያደክምም ያሰቡበት ይደረሳል:: ቅዱስ መጽሐፍ ከደቀመዛሙርቱ ታሪክ የሚያስተመረን ይህን ነው:: (ዮሐ 21፥6) መሪዎች ፈሪሃ እግዚአብሔር ቢኖራቸው ጠቃሚ ነው የሚያሰኘው ሌላው መከራከሪያ ይኸው ነው::

የመሪነትን ከባድ ሸክምነት እና የሰው ዓቅም ውሱንነትን በአግባቡ የተረዳ መሪ ሲኖር በእግዚአብሔር ይታመናል:: የቀደሙ መሪዎች የውጭ ወራሪ በመጣባቸው ጊዜ የነበረውን የዓቅም ልዩነት አልተገነዘቡትም ማለት መቼም አይቻልም:: ጥያቄው ታዲያ ያንን ያህል ቆራጥነት፣ ያንን ያህል ልበ ሙሉነት ከየት አገኙት? የሚለው ነው:: በአንድም

በሌላም እንደታየው ተስፋቸው ከምንም በላይ በፈጣሪያቸው ላይ በመሆኑ የማይቻል የሚመስለውን እንደቻሉና ሊሻገሩት አስቸጋሪ የሆነውን እንደተሻገሩ ነው መማር የሚቻለው::

በተመሳሳይ ተስፋ አስቆራጭ በሚሆንበት ጊዜ መሪ ተስፋ የሚያገኘው ከየት ነው? ለአንድ መሪ ተስፋ የሚሰጡት ነገሮች ምንድን ናቸው? ሰው የሚያምንበት ተስፋ ከሌለው ችግርን እንዴት ሊሻገር ይቻለዋል? ለሚለው ጥያቄ ፈሪሃ እግዚአብሔር ላለው ሰውና ለሌለው ሰው የሚገኘው ምላሽ ልዩነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ ነው:: በፈጣሪ ተስፋ አልቆርጥም ማለት በሚችል መሪና እንዲህ ዐይነቱን ተስፋ በሚያቃልል መሪ መካከል፤ ከጨለማ ማዶ ብርሃንን በማየት፣ ወድቆ በመነሣት በእነዚህ በሁለቱ መሪዎች መካከል ልዩነት እንዳለ የብዙ መሪዎች ሕይወት ያስተምረናል:: በዓለም ላይ ስንቶቹ መሪዎች ናቸው በአብሪት ዓለም ጠበበኝ ሲሉ ኖረው ችግር ሲገጥም በቀቢጸ ተስፋ ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በማጥፋት ታሪካቸው የተጠናቀቀው? በፈጣሪ ተስፋ አልቆርጥም ፈጣሪ ኢትዮጵያንም ይተዋታል ብዬ አላምንም የሚል ተስፋ ለመሪ ትልቅ ጉልበት ነው:: "እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፤ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፤ አይደክሙም::" ተብሎ እንደተጻፈ ከፍርሃት ጀርባ ልበ ሙሉነት፣ ከመታወክ ወደ መጽናናት መሸጋገር የሚቻለው ሁሉን በሚችል ፈጣሪ ተስፋ ማድረግ ሲቻል ነው:: (ኢሳ 40፥31)

ለአንዳንዶች እንደሚመስላቸው በእግዚአብሔር መታመን ማለት የደካምነት መገለጫ ግን አይደለም:: በእግዚአብሔር መታመን ማለት እጅና እግርን አጣጥፎ ተአምር ብቻ መጠበቅ ማለትም አይደለም:: በእግዚአብሔር መታመን ማለት በእኛ ስንፍና፣ በእኛ ጥፋት፣ በመሪዎች ጠማማነት የመጣውን መከራ ሁሉ የፈጣሪ ቁጣ እንደሆነ አድርጎ ፈጣሪን በሁሉም ነገር ማማረር ማለትም አይደለም:: በፈጣሪ መታመን ማለት በሰው ዓቅም ሊከናወን ለሚችለው ነገር ሁሉ በእኛ ስንፍና

እንግዲህ ምን ይደረግ ፈጣሪ ያውቃል ማለትም አይደለም:: ይልቁንም እንደ ነህምያ “እኛም እንሠራለን የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል” ማለት መቻል ነው እንጂ:: (ነህ 2፥20) ነህምያ ሕዝቡን አስተባብሮ የፈረሰውን የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሲሠራ ጠላት ቢነሣበት፣ ሕዝቡን በአንድ እጃቸው መከላከያ መሳሪያቸውን ይዘው፣ በሌላ እጃቸው ቅጥሩን ሠርተው እንዲያጠናቅቁ ያደረገ ብርቱ መሪ ነው:: “እኛም እንሠራለን የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል” የሚለውን ቃል የተናገረው በዚህ ጊዜ ነው::

እኛም እንሠራለን የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል ማለት ሰው የሰውን ድርሻ ሲሠራ እግዚአብሔር ደግሞ የአምላክነቱን ሥራ ይሠራልናል ማለት ነው:: ቀይ ባሕርን ማሻገር የእግዚአብሔር ሲሆን በእምነት መሻገር ደግሞ የሰው ነው:: ኢያሪኮን ማውረስ የእግዚአብሔር፣ ኢያሪኮን ቅጥር ሰባት ጊዜ እየዞሩ መጮህ ደግሞ የሕዝቡ ነው፡፡ ኢትዮጵያን እጅ ለእጅ ተያይዞ ማልማት የሰው፣ ኢትዮጵያን መባረክ ደግሞ የፈጣሪ ድርሻ:: ጥሩ መሪዎችን ኮትኩቶ ማሳደግም የሕዝቡ ድርሻ ነው:: መቼም እግዚአብሔር ከመካከል ካፈራነው እንጂ ከሰማይ መሪ የሚያመጣልን አይደለም:: “እርዱኝ እረዳችኋለሁ” እንደሚለው አባባል ነው:: እንዲያው ሳይሠሩ እግዚአብሔርን ማማረር፣ መሪ ባጠፋ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደሆነ ማሰብ፣ ሳይሠሩ እንግዲህ ምን ይደረግ እያሉ እግዚአብሔርን መውቀስ አላዋቂነትና የስንፍና ምልክት ነው የሚሆነው::

10.3 የመርህ ሰው

የሥነ ምግባር አንዱ መገለጫ የመርህ ሰው መሆን ነው:: የመሪ ውሳኔዎች በፈታኝ ምርጫዎች የተሞላ ነውና:: ለውሳኔ የሚያስቸገሩ ምርጫዎች በአንዴ የሚጋጥመበት ጊዜም ቀላል የሚባል አይደለም:: ከአገርና ከጎሳ፣ ከድርጅትና ከቤተሰብ፣ ከፓርቲና ከአገር፣ ከሰውና ከእግዚአብሔር፣ ለእውነት ከመቆምና መስሎ መኖር፣ እውነትን ተናገሮ ከመሸበት ማደርና በክፉ ሥራ ተባባሪ ሆኖ መሾም መሸለም፣ እውነትን ወይም ጥቅምን ማስቀደም፤ እነዚህን የመሰሉ ምርጫዎች በአንድ ወይም በሌላ

ጊዜ ሊያጋጥሙ ይችላሉ:: መሪ ውሳኔ ሲወስን የሚመራበት፣ አንዱን ከሌላው የሚያስበልጥበት፣ ትክክሉን ትክክል ካልሆነው የሚለይበት መስመር እንዳይስት የሚጠበቅበት መርህ (Principles) ያስፈልገዋል[77]::

መርህ መሪ ከሚያምንበት እምነት የሚመነጭ ነው:: በሚያምንበት እምነት እየተመራም ትክክሉን ትክክል ካልሆነው ይለያል፤ መልካሙን ከመጥፎው ይመርጣል:: መሪ እንዲህ ውስጣዊ እምነት ሲኖረው ባለ መርህ መሪ ይባላል::

መርህ ያለው መሪ እሴት ያለው ነው:: መርሁ የሚመነጨውም ከእሴቱ ነው:: አንድ መሪ ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ወይም በአንጻሩ ዋጋ የማይሰጠው ወይም ያነሰ ዋጋ የሚሰጠው በምን ዐይነት ነገሮች ነው? የሚለው የሚገለጸው በእሴቱ ነው:: ከፋፋይ ለመሆን ወይም አንድ ለማድረግ፣ ይቅር ባይ ለመሆን ወይም ጨካኝ ለመሆን፤ ወሳኙ የሚያምንበት እምነት ወይም የሚቆምለት መርህ ነው የሚሆነው:: አንድ መሪ ከሁሉም ድርጊቱ ጀርባ እምነት አለው:: ይህ እምነቱ ደግሞ በመርህ ይገለጻል::

ሰው የሚኖርለት ብቻ ሳይሆን የሚሞትለት እምነት ከሌለው ውጤታማ መሪ ሊሆን እንደማይችል የዓለም ታሪክ ያስተምረናል:: ማንዴላ በ1964 ሪቮኒያ ክስ የሦስት ሰዓት ንግግራቸው "በሕይወት እያለሁ እውን ሆኖ ማየት የምፈልገው፣ ልኖርለት የምሻ፣ ተስፋ የማደርገው መርህ አለኝ፡፡ ካስፈለገም ግን ለዚህ መርህ ለመሞትም ዝግጁ ነኝ"[78] በሚለው ዐረፍተ ነገር ያንጸባረቁትም የመርህን አስፈላጊነት ነው:: ባለ መርህ መሪ እንዲህ ተሳክቶ ማየት የሚፈልገው ሕልም እንዲሳካ በሚያደርገው ሩጫ እስከ ሞት ድረስ ዋጋ የሚያስከፍለው ቢሆን እንኳ ጽዋውን ለመቀበል የተዘጋጀ ነው::

---

[77] Principles, on the other hand, are deep fundamental and timeless truths that have application to any and all organizations, allowing them to make wise decisions.Leading from within, Page 8, file:///C:/Users/wb242998/OneDrive%20-%20WBG/References/Leading_from_Within.pdf

[78] It is an ideal for which I hope to live for and to see realised. But, My Lord, if it needs be, it is an ideal for which I am prepared to die" Nelson Mandela, https://www.nelsonmandela.org/news/entry/i-am-prepared-to-die

እንደእነ ማንዴላ በነጻት ልንኖርባት የምንናፍቃት ኢትዮጵያ አለች፤ ለነጻነቷም ሕይወታችንን ለመስጠት ዝግጁ ነን ብለው ለነጻነት መሥዋዕትነትን የከፈሉ ብዙ ጀግኖች በነበሩባትና ባሉባት አገር ለመርህ መቆም ማለት እንግዳ ነገር አይደለም:: ለወገኖቻቸው ነጻነት ሲሉ የሞት ጽዋን በቆራጥነትና በሙሉ መንፈሳዊ እምነት የተቀበሉ አባቶች፣ በሚያምኑበት እምነት ጸንተው ኢትዮጵያን በባርነት ቀንበር ሥር እንዳትወድቅ ሕይወታቸውን መሥዋዕት ያደረጉ ነገሥታትና ጀግኖች የነበሩባት አገር ስለሆነች ኢትዮጵያ የመርህ ምንነት በተግባር የተተረጎመባት አገር ናት ማለት ይቻላል:: አሁን ለመርህ መቆም ምነው እንዲህ መነመነ? ምን ነካው? የሚለው የሚያሳስበውም የቀደመ ታሪክን ሲያስታውሱ ነው::

የመርህ ሰው በተመቸው ጊዜ መርሁን የሚከተል፣ አጣብቂኝ ሲገባ የሚተወው ማለት አይደለም:: ደጋፊ ቢኖርም ባይኖርም፣ ቢነቀፍም ጭብጨባው ቢደምቅም፣ ቢወገዝም ቢወደሰም፣ ዋጋ ቢያስከፍልም ቢያሸልምም የመርህ ሰው በጊዜውም ያለጊዜውም በአመነበት የሚጸና ነው:: የአቡነ ጴጥሮስንና የእርሳቸውን ፈለግ የተከተሉትን የብዙዎችን ባለ መርህ መሪዎች ቆራጥነት ሩቅ ሆኖ ባናስታውሰውም፤ በቅርብ እንኳ ስንቶቹ ናቸው ላመኑበት መርህ ከባድ ዋጋን እስከመክፈል የደረሱት:: ዋጋ ቢያስከፍለኝም ለቃሌ ታማኝ ነኝ፤ ቃሌን በፍርሃት አልለውጥም ብለው መከራን የተቀበሉ ባለ መርህ መሪዎችን በዚህ ባለንበት ዘመንም እየታዩ ነው::

መርህ ያለው መሪ በምንም ሁኔታ ሊያቋርጠው የማይሻው ቀይ መስመርን ለራሱ ያሰምራል:: ሕግን ወይንም ሰውን ባይፈራም ቅዱስ ጳውሎስ "በነገር ሁሉ በመልካም እንድንኖር ወደን መልካም ሕሊና እንዳለን ተረድተናልና" ሲል እንደተናገረ በሕሊናው ያሰመረውን መስመር ሲጠብቀው ይኖራል:: (ዕብ 13፥18) እግዚአብሔርን የሚፈራ መሪ ለሕሊናው የታመነ ነው:: ሰው ለሕሊናው ታማኝ ከሆነ ለእግዚአብሔርም ለሰውም ታማኝ የመሆን እድሉ ሰፊ ይሆናል:: ሰው ለሕሊናው ካልታመነ ግን እንዴት ለሌላው ሊታመን ይችላል?

ሥልጣንን መከታ አድርጎ ከሕግ ማምለጥም ይቻል ይሆናል:: ከራስ ግን መደበቅ አይቻልም:: ሕሊና ክፉ ሥራን እየተከታተለ መክሰሱ፥ መውቀሱ፥ ከእንቅልፍም መቀስቀሱ አይቀርምና:: "ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ ብትል ጆሮችህ በኋላህ መንገዱ ይህች ናት በእርስዋም ሂድ የሚለውን ቃል ይሰማሉ::" እንደተባለ ሕሊና በሄድንበት ጥላ ሆኖ ይከተለናል:: (ኢሳ 30፥21) ስንተኛም ሕሊና አያንቀላፋም:: እንዲህ ማድረግ አልነበረብኝ በሚል ከራስ ጋር ሙግት የምንገጥምበት ጊዜ ይኖራል:: እንዲህ ማድረግ ነበረብኝ ብለን ራሳችንን የምንረግምበት ጊዜም አለ:: ሕሊና ነው ሞጋቹ:: ሕሊና ሲወቅስ ሰው ከራሱ ጋር ሊጣላ ይችላል የሚባለው ከዚህ አንጻር ነው:: ለሰው መዋሸት አንድ ነገር ነው:: ራስን መዋሸት ግን የከፋ ነው የሚሆነው:: ሰው ራሱን ከዋሸ ከራሱ ጋር እንዴት ሊታረቅ ይችላልስ? ስሕተትንስ እንዴት ማስተካከል ወይም ወደፊት መቀየር ይቻላል?

ሰው መርህ የለሽ ሲሆን፣ ለእውነትም ለጊዜያዊ ጥቅምም ለሁለቱም ማደር ለሁለቱም መገዛት ሲመኝ፣ በሚዋልልበት ጊዜ፥ አንዱ ከሌላው በውስጥ እየተጋጨ እረፍት ይነሳዋል:: "እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ::" እንዲልም በጎ ነገር ማድረግ እንዳለብን እያወቅን ክፉ ሥራ ስንሠራ ከራስ ጋር ጥል ይጀመራል:: (ሮሜ 2፥15) ክፉ መሪዎች በሚበዙበት ጊዜ፤ ሰዎች ከሚያምኑበትና ከሚኖሩለት እምነት በተቃራኒው የአምባገነኖችን ትእዛዝ እንዲፈጽሙ ሲገደዱ ለመኖር ሲሉ በሠሩት ሥራ የሕሊና ጸጸት የሚኖረውም ለዚህ ነው:: ከራስ ጋር መጣላት ግን ከጥል ሁሉ የሚብሰው እርሱ ሳይሆን አይቀርም:: ምክንያቱም ሰው ከሰው ቢጣላ አስታራቂ ሽማግሌ ሊገኝ ይችላል:: ሰው ከራሱ ከተጣላ አስታራቂ ከወዴት ሊገኝለት ይችላል? ሰው ጠብ አጫሪ፣ ጭር ሲል አልወድም የሚል ዐይነት የሚሆነውም ከራሱ ጋር ሲጣላ ሊሆን ይችላል:: በውስጥ ያለው ግጭት ወደ ውጭ እየወጣ::

ለሕሊናው የማይታመን፥ ለሕሊናው የማይገዛ መሪ መርህ ሊኖረው አይችልም::

መርህ አልባ መሪዎች ብዙውን ጊዜ ከሕዝብና ከአገር ይልቅ የፓርቲያቸውን፣ የራሳቸውን፣ ወይም የቡድናቸውን ጥቅም ሲያሰቅድሙ ይታያሉ:: ከመርህ ወይም ከሕግ ይልቅ ለግለሰቦች ታማኝ በመሆን ብዙ ጥፋትም ያደርሳሉ:: ሕግ ሲጣስ "ጎመን በጤና" እያሉ አይቶ እንዳላዩ መሆን ወይም ተባባሪ መሆንም እንግዳ ነገር አይደለም:: ከሕሊና ይልቅ ለጊዜያዊ ጥቅም ያደሉ ሰዎች በሚበዙበት ጊዜ ለሕሊናው የሚያድር የመርህ ሰው እምብዛም ማግኘት ይከብዳል:: እስኪ ዛሬ ስንት መሪዎች ናቸው ከሚገኘው ጊዜያዊ ትርፍ ባሸገር የሚያምኑበት መርህ ያላቸው? በሚናገሩት ልክ የሚኖሩ፣ ልባቸውና አፋቸው የሚስማማ ስንት መሪዎች ይኖራሉ? ጭብጨባ በሌለበት ነቀፌታ በሚበዛበት ሁኔታ ጸንተው መቆም የሚቻለቸውስ ስንት ይሆኑ? ችግሩ የሚታወቀው እንዲህ ዐይነት ጥያቄ ሲጠየቅ ነው::

10.3.1 ግትርነት እና ለመርህ መቆም

የ1966ቱ በመባል የሚጠራው ትውልድ "አቋሜ ነው" ከሚለው ፍንክች የማይል፣ በአቋሙ የጸና፣ ለሚያምንበት ራሱን ለሞት ያዘጋጀው የሚበዛበት፣ ክችች ካለ የማይመለስ ትውልድ ነው የሚል ወቀሳ መስማት የተለመደ ነው:: አሁንም ድረስ የሚያስችግረው እንዲህ ዐይነት የድርቅና ባህል ነው የሚባል ነገር ይሰማል:: ያሁኑን ትውልድ ደግሞ የዚህ ተቃራኒ አድርገው የሚያቀርቡት አሉ:: አሁን ያዋጣኛል ወይስ አያዋጣኝምን እንጂ ለመርህ ዋጋ የሚሰጠው ብዙም አይደለም ይባላል::

ያም ሆነ ይህ ለመርህ መቆምን እና ግትርነትን መለየት ግን አስፈላጊ ነው:: መርህ አልባነት ምን አደጋ አለው? የሚለውንም እንዲሁ:: መርህ አልባ መሪ ዛሬ ያመነበትን አሳብ ነገ ሲሸረው፣ ይህ ሰው ዐላማው እንዲህ ነው ሲባል እንዲያ ሆኖ የሚገኝ ወላዋይ፣ ጥቅም እንጂ የሚያምንበትና

በአመነበት እምነት የማይጸና የሆነ እንደሆነ ነው:: "ከአሳቤ ፍንክች አልልም"፣ "የእኔ መንገድ ወይም ገድል"፣ "ከአሳቤ ከምዛነፍ ብሞት ይሻለኛል" የሚለው ደግሞ በሌላኛው ጫፍ የሚታይ ነው:: ለመርህ መቆም ማለት ከሁለቱም አይደለም:: ሁለቱም ዋልታ ረገጥ የሚሉት ዐይነት ነው::

ሰው ለአንድ ዐላማ ሲሰለፍ የሚያምንበት፣ ዋጋን መክፈል ቢያስፈልግ ዋጋ ሊከፍል የሚችልለት እምነት ያስፈልገዋል:: ከዚህ መለስ እንዲህማ አይደረግም፤ እንዲህማ አላደርግም የሚልለት የራሱን መስመር ማስመር ካልቻለ፣ ነፋስ በመጣ ቁጥር በነፈሰበት የሚወዛወዝ ከሆነ ዐላማውን ማሳካት እንዴት ይቻለዋል? በሥራ አመራር ግን በእኔ መቃብር ካልሆነ እንዲህ ዐይነት ነገር አይደረግም፤ ከአቋሜ ፍንክች ከምል ብሞት ይሻለኛል፣ የእኔ መንገድ ወይም አውራ መንገድ (my way or highway) የሚል አቋም መያዝ ከባድ ችግር ነው::

በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ የሠሩ የተወሰኑ ዲፕሎማቶች በነበራቸው ውይይት የኢትዮጵያን መሪዎች የገለጹበት መንገድ "መሪዎቹ በአብዛኛው ግትርነት ያጠቃቸዋል፤ ሰጥቶ መቀበል የሚል መርህ ብዙም የተለመደ አይደለም" የሚል ነበር:: ይህ ነገር ምን ያህል ሥር የሰደደ ነው? ምን ያህል መሪዎችንስ ሊገልጽ ይቻላል? የሚለው ጥያቄ ሰፊ ዳሰሳ የሚጠይቅ ነው:: ቢሆንም "እናሸንፋለን" እና "እናችንፋለን" በሚል የወንድማማቾች መገዳደል፤ የእኔ መንገድ ካልሆነ፣ የእኔ አሳብ ካልሆነ በሚል መሆኑን ስናስብ፣ ግትርነት ምን ያህል ከባድ ችግር እንደሆነና ያለውንም አሉታዊ ተጽዕኖ መረዳት እንችላል:: በመቃብራችን ላይ ካልሆነ እንዲህ ዐይነት ፖለሲ አይለወጥም ወይም ካልሞትን እንዲህ አይደረግም፤ ከእነ እገሌ ጋር አንወያይም እና የመሳሰሉ አጋጣሚዎችም የሚያስታውሱን የግትርነት ጠባይን ነው:: መቼ ነው ተቃዋሚ ወይም ተፎካካሪ የሚባሉ የፖለቲካ መሪዎች በአሳብ ተስማምተው፣ በአሳብ ተቀራርበው፣ አንዱ ለሌላው ተሸንፎ በጋራ የሠሩበት ዘመን? በአንዳንድች የአፍሪካ አገሮች እንደታዬው እንኳ የተለያየ አሳብ ያላቸው መሪዎች በጋራ ሊሠሩ፤ የጥምር መንግሥት የሚባለው ሊመሠረቱ ይችላሉ? ተብሎ ቢጠየቅ

የመሳካቱ እድል አጠራጣሪ እንደሚሆን ካለፈው ታሪካችን መገመት የሚከብድ አይሆንም::

በአሳብ ለመስማማትና አብሮ ለመሥራት በሁሉም ወገን ግማሽ መንገድ መምጣትን ይጠይቃልና:: ይህ ግን ግትርነት ባህል ባልሆነበት ሁኔታ ነው:: ከአቋም ፈቀቅ ማለት ወላዋይ፣ አቋም የለሽ፣ ሽርታታ የሚል ስምን በሚያሰጥበት፤ ግትርነት፣ ድርቅና እንደ ጀግንነት በሚቆጠርበት ባህል ለመርህ መቆም ማለት የተሳሳተ ትርጉም የተሰጠው ይመስላል::

መርህን መያዝ እንደ ወቅቱ፣ እንደ አስፈላጊነቱ፣ እንደ ሁኔታው፣ ነገሮችን እንደ አመጣጣቸው ማስተናገድን (Pragmatisim) አይከለክልም [79]:: ድርድር የማይደረግበት ሃይማኖት ብቻ ነው:: ሃይማኖት አንድ እውነት ነውና:: በዘመን ሊቀያየር የሚችልም አይደለምና:: ትናንትም ዛሬም በየትኛው ጊዜ ሊለውጥ የሚችል ነገር አይደለም:: የሌላን ሳያጥላላ ሁሉም የራሱን እምነት ቢይዝ የሚገባ ነው:: መሪነት ግን እንዲህ አይደለም:: በመሪነት ሁሉም ነገር ለድርድር ክፍት ነው::

10.3.2 መርህ ሲሸረሸር

አሁን አሁን እየተሸረሸሩ ካሉ እሴቶች መካከል መርህ በዋናነት የሚጠቀስ ነው:: ለሚያምኑበት እምነት ሳይፈሩ በጽናት ለመቆም ቁርጠኝነቱ ያላቸው፣ ለሕሊናቸው የሚታመኑ፣ ለሚያምኑበት ነገር በችግር መካከል የሚጸኑ ስንት መሪዎችን ማግኘት ይቻል ይሆን? ተብሎ ቢጠየቅ ምናልባት ብዙ ሰው ማግኘት ከባድ ሊሆን ይችላል:: በእርግጥ ጥቂት ይሆናሉ እንጂ ለመርህ የሚቆም ሰው ማግኘት አስቸጋሪ ሆኗል በሚባልበት በአሁኑ ዘመን እንኳ ሳይፈሩ፣ ከወገናችን እንነጠላለን፣ ወዳጅ ዘመድ ያወግዘናል ሳይሉ ለሚያምኑበት እውነት የሚቆሙ ዛሬም ይኖራሉ:: በአመኑበት እውነት የሚጸኑ፣ የሚበልጠውን ዐላማ የሚያስቀድሙ፣

[79] Pragmatic leaders focus on the practical, “how do we get this done,” side of any task, initiative or goal. **Pragmatic leaders** are practical thinkers. They focus on the processes behind any task, initiative, or goal. https://www.linkedin.com/pulse/3-principles-pragmatic-leaders-paul-larkin

ከብሔረሰብ፣ ከወዳጅ ዘመድ ወይም ከፖለቲካ ዐላማ አገርን እና ሕዝብን የሚያስቀድሙ ሰዎች አሁንም በቃልም በኑሮም ይታያሉ:: ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን በፈተና መካከል ነው:: ባልገባቸው ወይም ጠባብ ዐላማ ባላቸው ወገኖቻቸው እንደ ባንዳ ሊያስቆጥራቸው እንደ ከሀዲ ተቆጥረው ብቻቸውን ሊያቆማቸው፣ ከባድ ዋጋንም ሊያስከፍላቸው ይችላልና::

ለመርህ መቆምን ከባድ የሚያደርገው፡-

- ላመኑበት ነገር መቆም ደጋፊን ሊያሳጣ ይችላል:: ዲሞክራሲ ጎልብቶባቸዋል በሚባሉ አገሮች ሳይቀር የፖለቲካ መሪዎች በሚያምኑበት ነገር ጸንቶ ከመቆም ይልቅ፥ በሚያምኑበት ነገር ሕዝባቸውን ከመምራት ይልቅ፥ በደጋፊ ብዛት መነዳት ለመርህ አልባነት እንደ ምክንያት ይቀርባል:: በሚያምኑበት ነገር ጸንተው ከመቆምና ለሕዝቡ ይጠቅማል ብለው የሚያምኑትን ነገር ከማስፈጸም ይልቅ ስለ ቀጣይ ምርጫቸው በማሰብና የተመረጡበትን ሕዝብ ደስ ለማሰኘት ብቻ የተሳሳቱ ቢሆንም ከመንጋው ጋር መንጎድ፣ ጩኸት ወደበዛበት ማዘንበል መሪዎች ከሚወቀሱባቸው ድርጊቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ላመኑበት ነገር መቆም ብቻን ሊያስቀር ይችላል:: ደጋፊ በበዛበት ለመርህ መቆም የሚከብድ ነገር የለውም:: ፈተናው ደጋፊ ሲሸሽ ብቻን ሆኖ ለመርህ መቆም መቻል ነው::

- መርህ አልባ የሆኑ ሰዎች በሚበዙበትና ኃይልና ጉልበቱም ያለው በእነዚህ ሰዎች በሚሆንበት ጊዜ መርህ ያለው ሰው ብዙም አይወደድም:: ሰዎች ሥራቸው ጨለማ ከሆነ ብርሃንን ሊወዱት አይችሉምና፡፡ ብርሃን ካለ ጨላማውን ሊገልጥ ይችላልና:: ሰው የሚፈተነው በጨለማ መካከል ማብራት ሲጀምር ነው:: ነገር ያልገባው፣ አንዳዱም ያበደ ሰው ያስብላልም:: የተሳሳተው ብዙኃኑ ቢሆኑም ብቻን ሆኖ ብዙኃኑን መጋፋት የመርህ ሰው መሆንን ይጠይቃል::

- መሪነትን አስቸጋሪ ነው ከሚያሰኙት ነገሮች አንዱ ለመርህ መቆም መስመሩ ግልጽ አለመሆኑም ነው:: ትክክለኛውን

ነገር ማስፈጸም ይገባል የሚባለውን ያህል ትክክሉ የቱ ነው? የሚለውም ሆነ ምርጫዎች ጥቁርና ነጭ የማይሆኑበት፤ የሚቀርቡት አማራጮች አንዱን መርጦ ሌላውን ለመጣል ቀላል የማይሆኑባቸው ክሥተቶችም ብዙ ናቸው:: ለምሳሌ ቀይ መስመር ተጥሷል ፍትሕ መቅደም አለበት የሚባልበት ክሥተት ሲፈጠር በሌላ ሚዛን ደግሞ የሚያስከትለው ጣጣ የአገር ደህንነትና ሰላም ከባድ ስጋት ሆኖ ሊቀርብ ይችላል:: ሁለቱም አስፈላጊ ናቸው:: ፍትሕም ሰላምም:: አንዱን ለማግኘት ሌላው አደጋ የሚሆን ሲሆን ምንድን ነው ማድረግ የሚቻለው? ለችግሩ መፍትሔ ከመሆን ይልቅ ችግሩን የሚያባብስ ከሆነስ ምን ማድረግ ይሻላል? ከባዱ የውሳኔ ፈተና እንዲህ ዐይነቱ ነገር ሊከሠት ነው:: እንዲህ ዐይነት ክሥተቶች በዛ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ::

- ለመርህ መቆምን ሌላም ከባድ የሚያደርገው ነገር አለ:: የሰው ዝንባሌ "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ጅግራ ነሽ ይሏታል" የሚባለው አነጋገር ዐይነት ነው:: ሰው ማድረግ ለፈለገው ነገር ትክክል እንዳልሆነ ልቡ እያወቀ የሚጣጣረው ነገሩን አሳማኝ ምክንያት በማቅረብ ትክክል እንደሆነ ራስን ለማሳመንና ለማጽናናት መሞከር ነው:: እንዲህ ባለው ጊዜ ነው የሕሊና ሙግትም የሚከሠተው:: ይህ ደግሞ በቅዱስ መጽሐፍ የመጀምሪያ የሰው ልጅ ታሪክ ጀምሮ በግልጽ የታየ ነው:: አዳምም ሔዋንም የተላለፉትን ሕግ ለምን እንደተላለፉ ልባቸው እያወቀ እግዚአብሔር ሲጠይቃቸው አላደረግንም ሳይሆን ያሉት ያደረግነው እባብ ስላሳሳተን ነው የሚል ነበር:: እንግዲህ ምን ማድረግ እችላለሁ? ሌላ ምርጫ የለኝም? አንዳንዶም ፈጣሪ የማያውቀው የለም እንግዲህ እርሱ ይቅር ይበለኝ እያልን የምንተላለፈው መስመር ብዙ ነው:: እንዲህ እያለ መስመሩ በየጊዜው ሲረገጥ መስመርነቱ መጥፋቱ አይቀሬ ነው:: መርህ አልባነት የሚስፋፋበት እንዲህ ባለው ምክንያት ሊሆን ይችላል::

- በመጨረሻ እውነት ማሸነፏ የማይቀር ቢሆንም ለመርህ መቆም ለጊዜው በአንድም በሌላም ዋጋ የሚያስከፍል ሊሆን ይችላል። በተመቸ ጊዜ የመርህ ሰው መሆን ይቻላል። መሥዋዕትነትን መክፈል ግድ በሚልበት ጊዜ ጸንቶ መቆም መቻል ግን ለጥቂቶች ብቻ የሚቻል ነው።

በመጨረሻም በፈተና መካከል ለመርህ መቆምን የሚያሳይ ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንሳቱ ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ይጠቅማል። ወደ ከነዓን በተደረገው ጉዞ በመርህ መጽናትን የተመለከተ ታሪክ ተመዝግቦ እናገኛለን። ሙሴ ከንዓንን ምድር ይሰልሉ ዘንድ ከእያንዳዱ ነገድ አንድ አንድ ሰው አሥራ ሁለት ሰዎችን መረጠና ላካቸው። አሥራ ሁሉቱም ሰዎች ከነዓንን ከሰለሉ በኋላ ያቀረቡት መልስ የተለያየ ነበረ። ሊሰልሉ ከተላኩት አሥሩ ሰዎች "በምድሪቱ ያሉ ሰዎች በኃይል ከእኛ ይበረታሉና በዚህ ሕዝብ ላይ መውጣት አንችልም አሉ"። ይህንን አሥሩ በተናገሩ ጊዜ ሕዝቡ እጅግ ስለፈሩ "በጦርነት ከምናልቅ ወደ ግብፅ ባርነት መልሱን" ሲሉ ጮሁ። ኢያሱና ካሌብ ብቻቸውን በአንድ በኩል ቆመዋል። ካሌብም ሕዝቡን በሙሴ ፊት ዝም አሰኘና። "እግዚአብሔርስ ከወደደን ወተትና ማር ወደምታፈስሰው ወደዚች ምድር ያገባናል እርስዋንም ይሰጠናል፤ ማሸነፍ እንችላለንና እንውጣ እንውረሰው አለ።"

በዚህ መካከል በድምፅ ብልጫ ሳይሆን በመርህ የሚያምን፣ በጩኸት ብዛት ደጋፊ አጣለሁ ደጋፊ ካጣሁ ምን ይውጠኛል ብሎ የማይሸበር መሪ ያስፈልግ ነበር። ያ ቆራጥና ባለ መርህ መሪ ሙሴ በአቋሙ ጸንቶ፣ ሕዝቡን አበርትቶ የተስፋይቱን ምድር እንዲወርሱ እንዳደረጋቸው የተጻፈበት ታሪክ ነው። በዚህ ወቅት ተቃዋሚዎች ቢበዙም፣ ሊሰልሉ ከተላኩት ከአሥራ ሁሉቱ መልእክተኞች ሁለቱ ብቻ በሙሴ ጎን ቆመው ሌሎቹ ተሸብረው ሕዝቡን ቢያሸብሩት መርሁን የሚያውቀው ታላቁ ሰው ሙሴ ከኢያሱና ካሌብ ጎን ቆሞ ብዙዎችን አሸነፋቸው። በአቋሙ በመጽናት ሕዝቡን የተስፋይቱን ምድር እንዲወርሱ አስቻላቸው። (ዘኁ. 13 እና 14)

ስንብት

ለሚያምን ሁሉ ይቻላል!

ቅንነት ካለ ብዙ ለውጥ ማምጣት ይቻላል!

የኢትዮጵያ ትንሣኤዋም ሩቅ አይሆንም!

የሰውን መብት የሚያከበሩ፣ ሰውን በሰውነቱ የሚያዩ፣ ፍትሕና እኩልነትን የሚያሰፍኑ፣ እውነትን የሚናገሩ፣ እውነትን የሚኖሩ፣ በትሕትና ሕዝባቸውን የሚያገለግሉ ቅን መሪዎች የሚወልዱበት የሚበረክቱበት ጊዜም ሩቅ አይሆንም:: ያን ጊዜ በሥልጣን ምክንያት እርስ በርስ መጠፋፋት ይቀራል:: ሕዝብ መሪዎቹን በነጻነት ይመርጣል:: ሰው በሠራው ልክ ይመሰገናል:: ሰው በሠራው ሁሉ ተጠያቂ የሚሆንበት ስርዓት ይኖራል:: ሕግ ከፍ ከፍ ይላል:: አገሪቱም የሕግ አገር ትሆናለች:: መልካም አስተዳደርም ብርቅ አይሆንም::

መሬቶቿ የሚለሙባት፣ የተፈጥሮ ሀብቶቿ ጥቅም ላይ የሚውልበት፣ ራብ ታሪክ የሚሆንበት፣ ለልጆቿ ሥራ የምታቀርብበት ጊዜም ሩቅ አይሆንም:: ሦስት ጊዜ መብላትም ብርቅ አይሆንም:: የልመና አኮፋዳዋም የሚሰቀልበት፣ ተመጽዋችነት ታሪክ የሚሆንበት ጊዜም ይመጣል::

ከዚህ በኋላ ልጇቿ በየበርሀው መባዘን፣ የውቅያኖስ ሲሳይ፣ የባዕዳን አገሮች እስር ቤት እዳ ታሪክ የሚሆኑበት ጊዜም ሩቅ አይሆንም::

በየምክንያቱ የተበተኑ ልጆቿ የሚሰበሰቡበትና አገራቸውን ማልማት የሚችሉበት እድልም ይፈጠራል:: የወደቀው የትምህርት ጥራት ተቃንቶ፣ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ከአገራቸው አልፈው ለዓለም የሚተርፉበት ጊዜም ይመጣል::

ሁሉም ወደ ልቡ ተመልሶ፣ ክፋት የሚጠላበት፣ ሌብነት እና መካካድ የሚያሳፍርበት፣ እውነት ወደ ቀደመ መንበሩ የሚመለስበት፣ ፍትሕ የሚሰፍንበት ቀንም ሩቅ ላይሆን ይችላል::

ፈሪሃ እግዚአብሔር በተግባር የሚገለጽበት፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ታጋሽ፣ ይቅር ባይ፣ ሰላም ወዳድ፣ ሰላማዊ ሕዝብ፣ ሃይማኖተኛ ሕዝብ የሚለው ስም የሚታደስበት ጊዜም ሩቅ አይሆንም::

ይህን ሁሉ ይቻላል ብለው የሚያምኑ ቅን፥ አገልጋይና ግብረ ገብ መሪዎች ከበረከቱ፣ ሕልሙ ሩቅ ቢመስልም ሁሉም ይቻላል::

እንዴት ይቻላል?

ችግራችን ከሌሎች አገሮች የተለዬ አይደለም:: ባለፈው ግማሽ ክፍለ ዘመን ወደ ብልጽግና ከተሸጋገሩ አገሮች የተሻለ ቢሆን እንጂ ያነሰ ሀብት የታደለች አገር አይደለችምም:: እንዲህ ካሉ አገሮች የተሻለ ማኅበራዊ፣ መንፈሳዊ እሴት፣ የሚያኮራ የቀደመ የሥልጣኔና የነጻነት ታሪክ ይዞ እንዲህ ከተለወጡ አገሮች ተርታ መሰለፍ ታዲያ ምን የሚያግድ ነገር ይኖራል?

ችግራችንን የተለየ የሚያደርገው ቅን መሪዎችን ማጣታችን ነው:: በቀና አስተሳሰብ፣ በቀና አመለካከት ትልቅ ሕልም ያለው ብቻ ሳይሆን ትልቁን ሕልሙን በቅንነት ለመፈጸም የሚተጋ፣ በሚሠራው ሁሉ በታማኝነት የሚመሰከርለት፣ ለእውነት የቆመ፣ አድሎዎን የሚጸየፍ፣ ለፍትሕ የሚያደላ፣ እንዲህ ያሉ መሪዎች ከበረከቱ የተሻለ ነገን ማየት ሩቅ

አይሆንም:: ችግር የሆነው በመሪዎች ዘንድ ቅንነት እየጠፋ ነው:: ችግር የሆነው ለበጎ ራእይ ሳይሆን ለክፉ ዐላማ እርስ በርስ መቧደን እና እርስ በርስ መወነጃጀል አለማቆሙ ነው:: እርስ በርስ ተደማምጦ፣ በአንድ አሳብና በአንድ ልብ ተግባብቶ መምራት አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን እርስ በርስ በሚደረግ ሽኩቻ ለዘመናት አንዱ ሲሠራ ሌላው እያፈረሰ የሚጸና ነገር መጥፋቱ ነው:: ችግር የሆነው በመሪዎች ዘንድ መደማመጥና መተባበር እየጠፋ አለመግባባቱን በአፈ ሙዝ ለመፍታት አንዱ ሌላውን አሸንፎ ሥልጣን ለመያዝ አገሪቱ ከግጭት አዙሪት መውጣት አለመቻሏ ነው:: ችግር የሆነው ፖለቲካው ተንኮልና መጠላለፍ የበዛበት እየሆነ ዓቅም ያላቸው የአገሪቱ ልጆች የመሥራት እድል ማጣታቸውና በየምክንያቱ እንዲሰደዱ መደረጋቸው ነው:: ይህ ሁሉ በቅንነት ይፈታል:: ይህ ሲሆን ነገን የተሻለ ለማድረግ የሚሳን አይሆንም::

ችግራችንን የተለየ የሚያደርገው አገልጋይነት በበቂ ሁኔታ አለመለመዱ ነው:: ከእኛ አገራችን ትቅደም፤ እኛ ተጎድተን አገር ትበልጽግ፤ እኛ አልፈን አገር በነጻነት በሰላም ትኑር የሚሉ ልጆች የበዙባቸው አገሮች ከወደቁበት ሲነሱ፣ የጎበጠው ወገባቸው ሲቃና ለማየት የተቻለበት ዘመን ላይ ነው ያለነው:: አገልጋይ መሪዎች ማግኘት የቻሉ አገሮች ሲያድጉ ሲመነደጉ አይተናል:: አገልጋይ መሪዎችን የታደሉ አገሮች ከችጋር አረንቋ ሕዝባቸውን አውጥተው ለዓለም ተስፋ የሆኑበት ክፍለ ዘመን ነው:: ይህ ሁሉ የሚገኘው ለሥልጣን ያለው እይታ ሲስተካከል ነው:: በጎቹን የሚነዳ ሳይሆን የሚመራ፣ ምንደኛ ሳይሆን መልካም እረኛ ቢገኝ አገር ትበለጽጋለች:: ሥልጣን ማገልገያ መሆኑን ከልብ የሚያምኑ መሪዎች በሌሉበት አገልግሎት ስም ብቻ ሆኖ ነው የሚቀረው:: አገልግሎት በተግባር እውን የሚሆነው ከራስ ጥቅም የወገንን ጥቅም የሚያስቀድም ልብ ሲኖር ነው:: የአገርና የሕዝብ ፍቅር ልባዊ ሲሆን ነው አገልግሎት በተግባር እውን የሚሆነው:: በሁሉም ዘርፍ ነገን የተሻለ ለማድረግ የቆረጠው ሲበዛ አገልግሎት በተግባር እውን ይሆናል:: በአገልግሎት ስም መነገዱ፣ በአገልግሎት ስም ዘርፎ መክበሩ፣ ራስንና ዘመድ አዝማድን መጥቀሚያ የሚያደርገው ባህል እስኪቀዩር ግን የበለጸገችን አገር ማየት ባዶ ተስፋ ሆኖ ነው የሚቀረው::

ባለኝ በተሰጠኝ ድርሻዬን ልወጣ የሚለው ከእኔ ምኞት የፈረሰች አገሬ ትሠራ፤ ከእኔ ጥቅም የወገኔ ጥቅም ይቅደም፤ አንገቱን የደፋ ሕዝብ ይቃና ማለት በሌለበት ይህ ሁሉ ግን ከምኞት አያልፍም። ሰውን የሚያስቀድሙ፣ የሰውን ክብር የተረዱ፣ የሥልጣናቸውን ድንበር የሚያውቁ፣ በቃል የሚሰብኩትን በሕይወት የሚኖሩ፣ አድርጉ የሚሉትን ቀድመው ሠርተው ምሳሌ የሚሆኑ፣ ቃላቸውና ተግባራቸው የተስማማ፣ ሌሎችን ለማትጋት የተጉ፣ በዐላማቸው የጸኑ አገልጋይ መሪዎችን ማግኘት ሲቻል ነው መንገዱ ሁሉ የተቃና የሚሆነውም። አገሬን ልገልገልባት፣ በአገኘሁት አጋጣሚ ልመዝብራት፤ ልዝረፋት የሚለው አንሶ፣ አገሬን ላገልግላት የሚለው ሲባዛ ሩቅ የሚመስለው ሕልም በቅርብ የሚደረስበት ይሆናል።

ችግራችንን የተለየ የሚያደርገው የነበረንን ፈሪሃ እግዚአብሔር እና ግብረ ገብነት ስናቃልለውና ሲሸረሸር ነው። የሃይማኖት አገር፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሕዝብ መሆን ትልቅ ጸጋ ነው። በዚህም ሥነ ምግባር ያለው ትውልድ ይገኛል። በዚህም ፍቅር ያለው ትውልድ ይገኛል። በዚህም የሚተማመን ትውልድን ማግኘት ይቻላል። በዚህም የሚተዛዘን ትውልድን ማፍራት ይቻላል። በዚህ ተስፋ ያለው፣ በችግር የማይፈታ፣ አሻግሮ የሚያይ ማስተዋልና ጥበብ ያለው ትውልድ ይገኛል። ሥነ ምግባር ባለበት ሌብነት ነውር ይሆናል። ግብረ ገብነት ሲያብብ ለአገር የሚያፈራው ፍሬ ጣፋጭ ነው። ሕግ ማክበር፣ ለሕግ ተገዥ መሆን፣ መከባበር፣ ከስድብና መገዳደል መራቅ ይህ ሁሉ የሥነ ምግባር ፍሬ ነው። ሥነ ምግባር ባለበት እናት አባትን ማክበር፣ እናት አባትን መርዳት ይኖራል። ሥነ ምግባር ባለበት ትሕትና፣ ርኅራኄ፣ የዋህነት፣ በጎነት፣ ይሰፍናል። ሥነ ምግባር ባለበት መለያየት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘረኝነት ይመክናል። ሞራል ከወደቀም ፍሬው መራራ እንደሚሆን የሚጠበቅ ነው።

የሞራል ውድቀት ባለበት የተሻለ አገርን ቢመኙት የማይጨበጥ ተስፋ ነው የሚሆነው:: ይህን ደግሞ የብዙ አገሮችን ታሪክ በመመልከት መማር ይቻላል:: ቅንነትና አገልጋይነት ሲስፋፋ፣ ግብረ ገብነት ከወደቀበት ሲነሣ፣ የተሻለ ነገን ማየት ሩቅ አይሆንም::

ዋቤ መጻሕፍት

1. **መጽሐፍ ቅዱስ** https፣//bible.org/foreign/amharic/
2. **የአመርኛ መዝገበ ቃላት**, https፣//dictionary.abyssinica.com/
3. The Importance of Trust in Leadership, David L. mineo
4. The Servant as Leader by Robert K. Greenleaf, Robert K. Greenleaf
5. Servant Leadership in Action፣ How You Can Achieve Great Relationships and Results, by Ken Blanchard, Renee Broadwell, et al.
6. The Heart of Leadership, Mark Miller
7. The Extraordinary Leader, Turning Good Leaders in Great Leaders, Jhn H. Zenger & Joseph R. Folman
8. BECOMING A BETTER LEADER APPLYING KEY STRATEGIES, A ROUTLEDGE FREEBOOK
9. Christian Ethics in Secular Cultures

10. The 360-Degree Leader፡ Developing Your Influence from Anywhere in the Organization, John Maxwell

11. The Leadership Challenge by James Kouzes and Barry Posner, 5th Edition

12. Integrity፡ The Courage to Meet the Demands of Reality Dr. Henry Cloud

13. Theology of work, https፡//www.theologyofwork.org/

14. Servant Leadership Roadmap፡ Master the 12 Core Competencies of Management Success with Leadership Qualities and Interpersonal Skills (Clinical Mind Leadership Development) (Volume 2) by Cara H Bramlett

15. Servant Leadership in Action፡ How You Can Achieve Great Relationships and Results

16. Character and Servant Leadership፡ Ten Characteristics of Effective, Caring Leaders, Larry C. Spears, The Spears Center by Ken Blanchard, Renee Broadwell, et al.

17. Servanthood: Leadership for the Third Millennium by Benett j Sims

18. Meeting the Ethical Challenges of Leadership: Casting Light or Shadow, by Craig E Johnson

19. Ethical Leadership by Rober J. Startt

20. The 7 Habits of Highly Effective People፡ Powerful Lessons in Personal Change, by Stephen R. Covey

21. HBR Guide to Dealing with Conflict, Amy Gallo

22. An Understanding of Humility-Based Leadership Impacting Organizational, Climate, Robert B. Huizinga Regent University

23. The Path to Humility፣ Six Practical Sections for Becoming a Humbler Person, Caroline R. Lavelock, B.A. Everett L. Worthington, Jr., PhD Virginia Commonwealth University

24. Humility by Andrew Murray

25. LEADING FROM WITHIN፣ Building Organizational Leadership Capacity, by David R. Kolzow, PhD

26. The honest truth about dishonesty, Dan Ariely

27. Overcoming conflict, Bob Philips

28. The Five Dysfunctions of a Team: Team Assessment

29. HBR's 10 Must Reads on Teams - Squarespace

30. A History of Ethiopia Harold G. Marcus UNIVERSITY OF CALIFORNIA PRESS Berkeley · Los Angeles · Oxford © 1994 The Regents of the University of California, by Patrick M. Lencioni

31. A History of Modern Ethiopia, 1855–1991፣ Second Edition (Eastern African Studies) by Bahru Zewde

32. **የኢትዮጵያ ታሪክ (ከአፄ ይኩኖ አምላክ እስከ አፄ ልብነድንግል**, Tekle Tsadik Mekuria

33. **አጤ ቴዎድሮስ በጳውሎስ ኞኞ** 1985

34. **እርካብና መንበር ዲራአዝ**

35. **ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት, ተክለጻድቅ መኩሪያ**

36. **አብዮቱና ትዝታዬ, ፍሥሐ ደስታ**